መጽሐፍ ቅዱስን ሊገነዘቡት ይችላሉ!

# የጳውሎስ መልዕክት፡ ወደ ሮሜ ሰዎች

ቦብ አትሊ
የትርጓሜ ሊቅ (ፕሮፌሰር)
(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)

የጥናት መመሪያ ሐተታዊ ጽሑፍ
አዲስ ኪዳን፣ ቅጽ 5

ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ማርሻል፣ ቴክሳስ
1998
በ2010 የተከለሰ

# ማውጫ

በዚህ ሐተታ ጥቅም ላይ የዋሉ አጽሕሮተ ጽሑፎች........................................i
የጸሐፊው አስተያየት፡ ይህ ሐተታ እንዴት ሊረዳዎት ይችላል?........................................iii
ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ........................................v
ሐተታ፡
የሮሜ መግቢያ........................................1
ሮሜ 1........................................5
ሮሜ 2........................................33
ሮሜ 3........................................46
ሮሜ 4........................................60
ሮሜ 5........................................70
ሮሜ 6........................................84
ሮሜ 7........................................94
ሮሜ 8........................................105
ሮሜ 9........................................128
ሮሜ 10........................................141
ሮሜ 11........................................148
ሮሜ 12........................................156
ሮሜ 13........................................166
ሮሜ 14........................................177
ሮሜ 15........................................185
ሮሜ 16........................................196
ተጨማሪ አንድ፡ የግሪክ ሰዋስዋዊ መዋቅር አጭር መግለጫ........................................208
ተጨማሪ መግለጫ ሁለት ጽሑፋዊ ትንተና........................................216
ተጨማሪ መግለጫ ሦስት፡ መዝገበ ቃላት (የቃላት ፍቺ)........................................219
ተጨማሪ አራት፡ የእምነት መግለጫ........................................227

## ለሮሜ ልዩ ርዕሶች የይዘት ማውጫ


የተላከ (ሐዋርያ)፣ 1፡1 ..........7
የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስብከት፣ 1፡2 ..........8
የእግዚአብሔር ልጅ፣ 1፡3 ..........9
ሥጋ፣ 1፡3 ..........10
የመለኮት ስሞች፣ 1፡4 ..........12
የቦብ ወንጌላዊ ቅድመ ሐሳብ፣ 1፡5 ..........15
መጠራት፣ 1፡6 ..........16
ቅዱሳን፣ 1፡6..........17
አብ፣ 1፡7..........18
ጽድቅ፣ 1፡17 ..........21
"እውነት" በጳውሎስ ጽሑፎች፣ 1፡18 ..........24
ማበላሸት፣ ማጥፋት፣ መበስበስ፣ 1፡23..........27
ልብ፣ 1፡24 ..........27
ለዘላለም (የግሪክ ዘይቤ)፣ 1፡25 ..........28
አሜን፣ 1፡25 ..........28
ግብረ ሰዶማዊነት፣ 1፡26፣27 ..........30
በአዲስ ኪዳን መጥፎ ምግባርና መልካም ምግባር፣ 1፡28-31 ..........30
የጳውሎስ የሁፐር ድብልቆች አጠቃቀም፣ 1፡30 ..........31
ንስሐ፣ 2፡4 ..........35
ዘረኝነት፣ 2፡11 ..........38
ትምክህት፣ 2፡17 ..........42
የግሪክ ቃላት ለ "ፍተና" እና ልዩ ትርጉማቸው፣ 2፡18 ..........42
ባዶ እና ዋጋቢስ 3፡3..........48
ክብር፣ 3፡23..........54
የሐ.ኪ. ማስረጃ ስለ አንዱ መዳን፣ 3፡24 ..........54
ዋጆ/መቤዠት፣ 3፡24 ..........55
ሃይማኖት/እምነት፣ 4፡5 ..........63
ማኅተም፣ 4፡11 ..........65
ዋስትና፣ 4፡16 ..........67
ሰላም፣ 5፡1..........72
አቋም ፣ 5፡2..........73

መከራ፣ 5:3 ....................75
በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ፣ 5:17፣18 ....................81
ጥምቀት፣ 6:3-4 ....................86
መቀደስ፣ 6:4 ....................87
ቅርጽ (Tupos)፣ 6:17 ....................91
የጳውሎስ ውዳሴ፣ ጸሎት፣ እና ምስጋና ለእግዚአብሔር፣ 7:25 ....................103
ኢየሱስና መንፈስ፣ 8:9 ....................110
ሥላሴ፣ 8:11 ....................111
የአማኞች ውርስ፣ 8:17 ....................115
የተፈጥሮ ሀብት፣ 8:19 ....................116
ተስፋ፣ 8:25 ....................119
የመቀጠል አስፈላጊነት፣ 8:25 ....................120
የመንፈስ አካላዊነት፣ 8:26 ....................121
በኵር፣ 8:29 ....................123
መመረጥ/ቀድሞ መታደል እና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት፣ 8:33 ....................124
አርኬ፣ 8:38 ....................126
የምልጃ ጸሎት፣ 9:3 ....................131
ርግማን 9:3....................133
ቃል ኪዳን፣ 9:4 ....................134
ቅሬታ (ቅሪት)፣ ሦስት አግባቦች፣ 9:27-28 ....................138
የማዕዘን ድንጋይ፣ 9:33 ....................140
መገዛት፣ 10:3 ....................142
የግሪክ የግስ ጊዜያት ለደኅንነት የዋሉ፣ 10:4 ....................143
መናዘዝ (ኃጢአትን) 10:9 ....................144
የጌታችን ስም፣ 10:9 ....................144
የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ 10:13 ....................145
ምሥጢር፣ 11:25 ....................153
ቅዱስ፣ 12:1 ....................157
ይህ ዘመን እና መጪው ዘመን፣ 12:2 ....................158
መታደስ ፣ 12:2....................158
የእግዚአብሔር ፍቃድ፣12:2....................159
የሐዲስ ኪዳን ትንቢት፣ 12:6 ....................160
ልግስና፣ ልባዊ፣ 12:8....................161
ህብረት፣ 12:13....................163
የሰዎች መንግሥት፣ 13:1 ....................167

የጳውሎስ እይታ በሙሴ ሕግ፣ 13:9 ....................................................................................170
ማስታወሻ በዘጸአት፣ 20፣13:15፣17 ....................................................................................170
ድካም፣14:1....................................................................................................................178
ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው መፈራረድ ይገባቸዋልን?፣ 14:13 ......................................................181
የእግዚአብሔር መንግሥት፣ 14:17 ....................................................................................182
ማነጽ፣ 15:2 ...........................................................................................................186
መትረፍረፍ፣ 15:13.........................................................................................................189
ክርስቲያን እና የተራብ፣ 15:26 ....................................................................................192
ሴቶች በመፅሐፋ ቅዱስ ውስጥ ያላቸው ድርሻ፣ 16:1 ......................................................198
ቤተ ክርስቲያን፣ 16:1......................................................................................................200
ግላዊ ክፋት፣ 16:20.........................................................................................................204
የዘላለም ፣ 16:26...........................................................................................................207

# ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| መመቅ | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ዊሊያም ፎክስ ዌል ኦልብራይት እና ዳቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጁት |
| መመቅመዝ.ቃ | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (6ቅጾች)፣ ዴቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጀው |
| ትቁብኪ | ትንተናዊ ቁልፍ የብሉይ ኪዳን በጆን ጆሴፍ ኦውንስ |
| ጥቅምጽ | ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ጽሑፎች፣ ጀምስ ቢ. ፕሪቻርድ |
| ብድብ | ዕብራይስጥ እና እንግሊዝኛ ሥርወ-ቃል በብሉይ ኪዳን በኤፍ. ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር እና ሲ. ኤ. ብሪግስ |
| ቢሄስ | ቢብላ ሄብሪካ ስቱትጋርቴንሲያ፣ ጂቢስ፣ 1997 |
| ተመዝመቅ | የተርጓሚ መዝገበ ቃላት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ (4 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ጆርጅ ኤ. በትሪክ |
| ዓአመመቅኢ | ዓለም አቀፍ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንሳይክሎፔድያ (5 ቅጾች) አዘጋጅ ጀምስ ኦር |
| ኢመቅ | ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| አሕማየአ | ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ማሶረቲክ ጽሑፍ፡ አዲስ ትርጉም (የአይሁድ የሕትመት ማኅበረሰብ የአሜሪካ) |
| ኮባ | የዕብራይስና የአራማዊ ሥርወ-ቃል የብሉይ ኪዳን በሉድዊግ ኮህለር እና ዋልተር ባዉምጋርትነር |
| ላ'ም | መጽሐፍ ቅዱስ ከጥንታዊ የምስራቅ የብራና ጽሑፎች (ፓሺታ) በጆርጅ ኤም ላምሳ |
| ሰባ | ሴፕቱዋጊንት (የግሪክ እንግሊዝኛ) በ ዞንደርቫን፣ 1970 |
| ሞ'ፍ | አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በጀምስ ሞፋት |
| ማጽ | ማሶረቲክ ዕብራይስጥ ጽሑፍ |
| አአመቅ | አዲሱ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ |
| አአመመቅ | አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አእመቅ | አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አእት | አእትመጽሐፍ ቅዱስ፡ አዲሱ የእንግሊዝኛ ትርርጉም፣ ሁለተኛ ቤታ ትርጉም |

| | |
|---|---|
| አዓአመቃብኪሥት | አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የብሉይ ኪዳን ሥነመለኮት እና ትርጓሜ (5 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ዊሊም ኤ. ቫንጀሚረን |
| አየመመቅ | አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አኢቅ | አዲሱ ዓለም አቀፍ ቅጂ |
| አኢመቅ | አዲሱ ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| ብኪምመ | የብሉይ ኪዳን የምስጋና መመሪያ በቶድ ኤስ. ቤል፣ ዊሊየም ኤ. ባንክስ እና ኮሊን ስሚዝ |
| ተእመቅ | የተከለሰ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| ተመቅ | የተከለሰ መደበኛ ቅጂ |
| ሴፕት | ሴፕትዋጊንት (ግሪክ-እንግሊዝኛ) በዞንደርቫን፣ 1970 |
| አእቅ | የአሁን እንግሊዝኛ ቅጂ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተሰብ |
| ወጽት | የወጣቶች ጽሑፋዊ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ በሮበርት ያንግ |
| ዞስመቅኢ | ዞንደርቫን ስዕላዊ መጽሐፍ ቅዱስ ኢንሳይክሎፔድያ (5ቅጽ)፣ አዘጋጅ ሜሪል ሲ. ቴኒ |
| (አኪ) | (አዲስ ኪዳን) |
| (ብኪ) | (ብሉይ ኪዳን) |

# የጸሐፊው መልእክት፡
# ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው።

መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል። (1) ለእሱ፣ (2) እሱን ለማወቅ እና (3) እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል። ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል። በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው።

የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው። እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ላንወሰድ ይገባል። ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን። ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም። ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።

### የመጀመሪያው መርሕ

የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል። ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው። ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም። የእሱ ፍላጎት– የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍለ ሃይማኖታዊ ፍላጎት አይደለም– ቁልፉ ነው። ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል። እሱም ደግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው። ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው። ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል። እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማዕከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው።

### ሁለተኛው መርሕ

ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው። ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ከሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም። ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል። ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም– ምዕራፎች፣ አንቀጾች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ትርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው። የአንቀጽን ሆነ የምዕራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል።

ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፉ ነገር ነው። አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርዕስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው። እያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ውስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል። ይወስኑታል፣ ያስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል። ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው። ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ የተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው። እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው፡

1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም (የተመጽማ[4])። ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል።
2. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ትርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፕትስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርዕሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
3. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ስልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማዕከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርዕሰ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።
4. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርዕሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢት እንደተደረገው። ለተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ[4]) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት አሀድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።
5. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።
6. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

**ሦስተኛው መርሕ**

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጻረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንገዝ ይረዱናል።

ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሿቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጫችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ እንደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አትሊ
ኢስት ተክሳስ ባፕቲስት ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 27፣1996

# ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላስሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9-11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል አድርጌ ነው። በኢየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተሻ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማዕከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ።

እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው። ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን በማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማዕከል– ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ?

ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት ዕብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ። የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልኦዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ሲያመላክተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር!

ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም  ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው!

እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ያገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

I. ቅድመ ግምቶች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን መለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ አግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም– እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ መተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ አይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

መ. እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ መሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

1. የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
2. ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ ዐውድ
3. የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
4. ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም የእያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
5. መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
6. መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት
7. ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት ዓላማ ሆኗል። ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና የግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

## II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ ዐውድ ችላ በማለት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ መግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል።


ለ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ

ሐ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ


መ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ ዐውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ-መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ

ሠ. ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል።

በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡



ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ተመስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ አካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትኝ፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት እንዴት አድርገን መፈተሽ እንችላለን? ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

### III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው።

የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ዑደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ።

ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል። አምስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡

1. የዋናው ጸሐፊ
    ሀ. ታሪካዊ መቼት
    ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ ዐውድ
2. የዋናው ጸሐፊ ምርጫ
    ሀ. ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
    ለ. የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
    ሐ. የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)
3. የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ
    ሀ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ዑደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ሀ. የመጀመሪያው የንባብ ዑደት

1. መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሶመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ ቀጥተኛ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. የሙሉ ንባቡን ማዕከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።
3. የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምዕራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማዕከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።
4. ዋነኛውን ገጽ የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
      (1) ይዕብራይስጥ ትረካ
      (2) የዕብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
      (3) የዕብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
      (4) ሕግጋት
   ለ. አዲስ ኪዳን
      (1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
      (2) ምሳሌዎች (ወንጌላት)
      (3) ደብዳቤዎች/መልዕክቶች
      (4) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

ለ. ሁለተኛው የንባብ ዑደት

1. ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
2. ዋናዎቹን ርዕሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
3. የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

ሐ. ሦስተኛው የንባብ ዑደት

1. ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ ዐውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ.
2. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ
   ሀ. ጸሐፊው
   ለ. ዘመኑ
   ሐ. ተቀባዮች
   መ. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
   ሠ. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
   ረ. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ
3. የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምዕራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።
4. የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

መ. አራተኛው የንባብ ዑደት

1. የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሶመቅ፣ አየተመት)
   ለ. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ ኢመቅ)
   ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
2. ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ

ሀ. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1:6፣12፣13
ለ. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8:31
ሐ. ተጻጻሪ ጽንሰ-ሐሳቦች
3. የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ
ሀ. ወሳኝ ቃላት
ለ. ያልተለመዱ ቃላት
ሐ. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
መ. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች
4. ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ
ሀ. ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
(1) "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
(2) የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
(3) የቃላት ዝርዝር
ለ. በርዕሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ:: አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች የሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ማለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው:: መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልዕክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል::
ሐ. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው— መንፈስ ቅዱስ::
5. ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ ዐውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ::
ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣ አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ማለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው::)

## IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን:: ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ ሊተገብሩት ይገባል:: የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣ "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው::

ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት እንደፈለገ እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ሊለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!

የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ዑደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል:: ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም:: ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊል- ጽሑፍ ደረጃ ነው:: ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው:: በመንፈስ ቅዱስ አብራሪነት (ማብራሪያ) የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል:: ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም:: "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት:: ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ::

የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል:: ይህም ተገቢ የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው:: በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ::

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳለው ነው:: ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው:: በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ:: አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው::

## V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ:: አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ:: የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

ሀ. ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1፡26-2፡16)::

ለ. ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)::

ሐ. ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)::

መ. አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ::

ሠ. ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ::

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው:: የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

ሀ. ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ *ቃሉን መጠምዘዝ (ማጣመም)* ገጽ 17-18

> "ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን:: በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም:: እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ የእውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም:: ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው:: ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው::"

ለ. በኬርክጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡

> እንደ ኬርክጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው:: "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቀ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት:: መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳበ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም:: አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው::"

ሐ. ኤች. ኤች. ሮውሊ *በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ*፣ ገጽ 19፡

> "የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም:: ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው:: እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል:: መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ::"

## VI. የሐተታው ዘዴ

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡

ሀ. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ:: "የንባብ ዑደት ቁጥር 3" ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት::

ለ. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

ሐ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)
2. አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)
3. አዲሱ ኪንግ ጀምስ ዕትም (አኪጀዕ)
4. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)
5. አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)
6. ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማዕከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር አይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርዕሰ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ይኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

1. ሥነ ጽሑፋዊ ተንዳኝ ጽሑፍ
2. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
3. ሰዋሰዋዊ መረጃ
4. የቃላት ጥናቶች
5. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመት ጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፡

1. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት "ቴክስተስ ሪሴፕተስ" የሚከተል ነው።
2. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
3. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
4. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፡

1. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
2. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
3. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
4. አሻሚ ጽሑፎች

የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ ዒላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሰ. በእያንዳንዱ ምዕራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምዕራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ዒላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

# መግቢያ ወደ ሮሜ ሰዎች

**የመክፈቻ አንቀጽ**

ሀ. ሮሜ በእጅጉን ስልታዊ፣ አመክኖአዊ መሠረተ እምነት የሆነ የሐዋርያው ጳውሎስ መጽሐፍ ነው። ሮም የነበረው ሁኔታ ተጽዕኖ ስላለበት "ሁኔታዊ" ዶሴ ነው። ጳውሎስ መልእክቱን ይጽፍ ዘንድ አንድ ምክንያት ተፈጥሯል። ቢሆንም ከጳውሎስ ጽሑፎች መካከል እጅግ ገለልተኛው ይሄ ነው። ማለትም፣ ጳውሎስ በችግሮች ላይ ከሚያተኩረው (በተለይ በአማኝ አይሁድና በአሕዛብ አመራር መካከል ባለው መቀናናት፣ 14፡1-15፡13) ግልጽ የሆነ የወንጌል አስተዋጽዖ እና የእሱም የየዕለት ሕይወት ተጽዕኖ ያሳያል።

ለ. የጳውሎስ ወንጌል በሮሜ የቀረበው በሁሉም ዘመን ያለውን የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ይመለከታል።

1. አውግስጢኖስ በ386 ዓ.ም የተለወጠው ሮሜ 13፡13-14 አንብቦ ነው።
2. የማርቲን ሉተር የደኅንነት መረዳት በ1513 ዓ.ም ፍጹማዊ ለውጥ ያሳየው መዝ. 31፡1 ከሮሜ 1፡17 (ዕንባ. 2፡4) ጋር እንዳወዳደረ ነው።
3. ጆን ዌስሊ በ1738 ለሚኖናይት ስብሰባ ለንደን ላይ ሲጓዝ የተለወጠው የሉተርን ስብከት፣ በሮሜ መግቢያ ላይ ያለው ሲነበብ ነው፤ በወቅቱ የተመደበው ሰባኪ በመዘግየቱ ሳቢያ!

ሐ. ሮሜን ማወቅ ክርስትናን ማወቅ ነው! መልእክቱ ሕይወትን ያንጻል፣ እንደዚሁም የኢየሱስን ትምህርቶች፣ የሁልጊዜም የሆነችው ቤተክርስቲያን የመሠረት ድንጋይ እውነት ነው። ማርቲን ሉተር ስለዚህ ሲናገር፣ "የሐ.ኪ. ዋነኛው መጽሐፍና ንጹሑ ወንጌል!" ብሎታል።

**ጸሐፊው**

ጳውሎስ በትክክል ጸሐፊው ነው። የተለመደው ሰላምታው በ1፡1 ይገኛል። በአጠቃላይ እንደ ተስማሙበት የጳውሎስ "የሥጋዬ መውጊያ" የዐይኑን ችግር ሲሆን፣ ራሱ ጽሑፉን እንዳልጻፈና ተርቲዩስ በተባለ ጸሐፊ እንዳስጻፈ ይታመናል (16፡22)።

**ጊዜው**

ሀ. የሮሜ መልእክት የተጻፈበት ጊዜ ከ56-58 ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል። ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ጊዜአቸው በትክክልና በርግጠኝነት ከታወቁት አንዱ ነው። ይህም የሆነው ሐዋ. 20፡2 ከሮሜ 15፡17 ጋር በማነጻጸር ነው። ሮሜ ምናልባት ከቆሮንቶስ ሳይጻፍ እንዳልቀረና በጳውሎስ ሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ማገባደጃ ላይ ልክ ከኢየሩሳሌም ከመልቀቁ በፊት እንደሆነ ይገመታል።

ለ. የጳውሎስ ጽሑፎች በጊዜ ቅደም ተከተል፣ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ እና ሙሪ ሃሪስ በመጠነኛ ማስተካከያ ቀጥሎ ቀርቧል።

| | መጽሐፍ | ዘመን | የተጻፈበት ስፍራ | ከሐዋ ሥራ ጋር ግንኙነቱ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ገላትያ | 48 | ሶሪያ አንቲሆች | 14፡28፤ 15፡2 |
| 2. | 1ኛ ተሰሎንቄ | 50 | ቆሮንቶስ | 18፡5 |
| 3. | 2ኛ ተሰሎንቄ | 50 | ቆሮንቶስ | |
| 4. | 1ኛ ቆሮንቶስ | 55 | ኤፌሶን | 19፡20 |
| 5. | 2ኛ ቆሮንቶስ | 56 | መቄዶንያ | 20፡2 |
| 6. | ሮሜ | 57 | ቆሮንቶስ | 20፡3 |
| 7.-10. | የእስር ቤት መልእክቶች | | | |
| | ቆላይስስ | በ60ዎቹ መግቢያ | | |
| | ኤፌሶን | በ60ዎቹ መግቢያ | በሮሜ | |
| | ፊሊሞን | በ60ዎቹ መግቢያ | | |
| | ፊሊጵስዩስ | ከ62-63 ማገባደጃ | | 28፡30-31 |
| 11.-13. | አራተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ | | | |
| | 1ኛ ጢሞቲዎስ | 63 (ወይም ወዲህ፣ | መቄዶንያ | |
| | ቲቶ | 63 ግን በፊት | ኤፌሶን (?) | |
| | 2ኛ ጢሞቲዎስ | 64 ዓ. ም 68) ሮም | | |

**ተቀባዮች**

የደብዳቤው መቀበያ አድራሻ ሮም እንደሆነ ያመለክታል። በሮም ቤተ ክርስቲያንን ማን እንደመሠረተ አናውቀውም።

ሀ. ምናልባት በበዓለ ሃምሳ ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘት ከሄዱት ሰዎች አንዳንዱ የተለወጡት ወደ አገራቸው ሲመለሱ ቤተክርስቲያኑን ጀምረውት ይሆናል (ሐዋ. 2፡10)
ለ. ከእስጢፋኖስ መገደል በኋላ በኢየሩሳሌም በተፈጠረው ስደት የሸሹት ሐዋርያት ሊሆኑ ይችላሉ (ሐዋ 8፡4)
ሐ. ከጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች በኋላ የተለወጡት ወደ ሮም ተጉዘው ሊሆን ይችላል፡፡ ጳውሎስ ይሄንን ቤተ ክርስቲያንን ጎብኝቶት አያውቅም፣ ምንም እንኳ ጉጉት ቢኖረውም (ሐዋ. 19፡21)፡፡ እዛ ብዙ ጓደኞች አሉት (ሮሜ 16)

አጠቃላይ ሐሳቡ፣ ወደ ስጳንያ በሚያደርገው ጉዞው ሮምን ለመጎብኘት ነበር፣ (ሮሜ 15፡28) ኢየሩሳሌምን ከጎበኘና "የፍቅር ስጦታ" ከተቀበለ በኋላ፡፡ ጳውሎስ ከሜዲትራንያን በስተምስራቅ ያለው አገልግሎቱ እንደተገባደደ ተረድቷል፡፡ ሌሎች አዳዲስ ቦታዎችን ቃኘ (15፡20-23፣28)፡፡ ደብዳቤውን ከጳውሎስ፣ ከግሪክ ወደ ሮም ይዛ የሄደችው በዛ አቅጣጫ በጉዞ ላይ የነበረችው ዲያቆኒቷ ፎቤ ሳትሆን አትቀርም (ሮሜ 16፡1)፡፡ ይሄ በቆሮንቶስ መንደሮች በአንደኛው ክፍለ ዘመን በአንድ ድንኳን ሠሪ ይሁዲ የተጻፈ ደብዳቤ ለምን ይሄን ያህል ዋጋ ያለው ሆነ? ማርቲን ሉተር "የሐዲስ ኪዳን ዋነኛው መጽሐፍና ንጹሑ ወንጌል" ብሎታል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዋጋ የሚገኘው በጥልቀት ከተብራራው እውነት በተለወጠው ራቢ (የአይሁድ መምህር)፣ የተርሴሱ ሳኦል፣ ለአሕዛብ ሐዋርያ ሊሆን ከተጠራው ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የጳውሎስ መልእክቶች አገሬያዊ ሁኔታዎችን የሚያንጸባርቁ ሲሆኑ፣ ሮሜ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ የሐዋርያውን እምነት የሚያሳይ ስልታዊ አቀራረብ ነው፡፡

ወንድም ክርስቲያን አስተውለዋልን፣ በዚህ ዘመን የምንጠቀምባቸውን አብዛኞቹን ሞያዊ ቃላት፣ "እምነት" ("መጽደቅ፣" "ኃላፊነት" "ልጅነት" እና "መቀደስ") ከሮሜ እንደተገኙ አውቀዋልን? ይህ (ሮሜ) የገላትያ መልእክት ሥነ መለኮታዊ እድገት እውነታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን አስደናቂ መልእክት እንዲገልጽልዎ ይጸልዩ፣ ሁላችንም የሱን ፍቃድ እንደምንፈልገው፣ ለአሁኑ ሕይወታችን እንዲሆነን!

**ተግባር**

ሀ. ወደ ስጳንያ ለሚያደርገው ሐዋርያዊ ጉዞው ርዳታ ለማግኘት የጠየቀበት ነው፡፡ ጳውሎስ በምስራቃዊ ኢየሩሳሌም የነበረው ሐዋርያዊ ተግባር መገባደዱን ተመልክቷል (15፡20-23፣28)፡፡
ለ. በሮሜ ቤተ ክርስቲያን በአማኝ አይሁድና በአማኝ አሕዛብ መካከል የነበረውን ችግር ለመቅረፍ ነው፡፡ ይህ ምናልባት ሁሉም አይሁድ ከሮሜ እንዲወጡ የተደረገበትና ኋላ ላይ መመለሳቸው የፈጠረው ይሆናል፡፡ በወቅቱ የአይሁድ ክርስቲያን መሪዎች በአሕዛብ ክርስቲያን መሪዎች ተተክተው ነበር፡፡
ሐ. ራሱን ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን ለማስተዋወቅ፡፡ በጳውሎስ ላይ ጠንከር ያለ ተቃውሞ በኢየሩሳሌም ካሉት በእውነት ከተለወጡት አይሁድ የሰነዘር ነበር፡፡ (የኢየሩሳሌም መማክርት ሐዋ. 15)፣ ከእውነት ካልሆኑት አይሁድም (የገላትያ ይሁዲዎች እና 2ኛ ቆሮንቶስ 3፣ 10-13)፣ እንዲሁም ከአሕዛብ (ቆላስይስ፣ ኤፌሶን) ወንጌልን በራሳቸው አግባቢ ንድፈ-ሐሳብ ወይም ፍልስፍና (ግኖስቲስዝም) ለመደባለቅ ከሚሞክሩት፡፡
መ. ጳውሎስ አደገኛ አነሣሽ ተብሎ ተከሶ ነበር፣ ከኢየሱስ ትምህርት ጋር ያለ አግባብ በማከል፡፡ የሮሜ መጽሐፍ በተለመደው ስልታዊ በሆነ መልኩ የሱ ወንጌል ትክክለኛ መሆኑን ለማሳየትና ለማስረገጥ ሲሆን ከብሉይ ኪዳንና ከኢየሱስ ትምህርቶች (ከወንጌል) ተጠቅሟል፡፡

**አጭር መግለጫ**

ሀ. መግቢያ (1፡1-17)
   1. ሰላምታ (1፡1-7)
      ሀ. ጸሐፊ (1-5)
      ለ. መዳረሻ (6-7$_{ሀ}$)
      ሐ. ሰላምታ (7$_{ለ}$)
   2. ጊዜው (1፡8-15)
   3. ጭብጥ (1፡16-17)
ለ. የመለኮታዊ ጽድቅ አስፈላጊነት (1፡18-3፡20)
   1. የአሕዛብ ዓለም ማክተም (1፡18-32)
   2. የአይሁድ ግብዝነት ወይም የአምልኮተ ጣዖት ግብረገብነት (2፡1-16)
   3. የአይሁድ ፍርድ (2፡17-3፡8)
   4. አጠቃላይ ኩነኔ (3፡9-20)
ሐ. መለኮታዊ ጽድቅ ምንድነው (3፡21-8፡39)
   1. ጽድቅ በእምነት ብቻ (3፡21-31)
   2. የጽድቅ መሠረቶች፡ የእግዚአብሔር ተስፋ (4፡1-25)
      ሀ. የአብርሃም ትክክለኛ አቋም (4፡1-5)
      ለ. ዳዊት (4፡6-8)
      ሐ. የአብርሃም ከግዝረት ጋር ያለ ግንኙነት (4፡9-12)
      መ. የእግዚአብሔር ተስፋ ለአብርሃም (4፡13-25)

3. የጽድቅ መድረስ (5፡1-21)
   ሀ. ተያያዥ ገጽታዎች፡ የማይገባ ፍቅር፣ የማይመጣጠን ደስታ (5፡1-5)
   ለ. ተጨባጭ መሠረት፡ የእግዚአብሔር አስደናቂ ፍቅር (5፡6-11)
   ሐ. አዳም/ክርስቶስ ምድብ፡ የአዳም መተላለፍ፣ እግዚአብሔር ያዘጋጀው (5፡12-21)
4. መለኮታዊ ጽድቅ በራስ ጽድቅ መታየት አለበት (6፡1-7፡25)
   ሀ. ከኃጢአት ነጻ መሆን (6፡1-14)
      1) የሚታሰበው ግብ (6፡1-2)
      2) የጥምቀት ምሥጢር (6፡3-14)
   ለ. የሰይጣን ባሪያ ወይም የእግዚአብሔር ባርያ፡ የርስዎ ምርጫ (6፡15-23)
   ሐ. የሰው ጋብቻ ከሕግ ጋር (7፡1-6)
   መ. ሕጉ መልካም ነው፣ ኃጢአት ግን መልካሙን ይከለክላል (7፡7-14)
   ሠ. በአማኝ ውስጥ የሚካሄድ የመልካምና የክፉ መጨረሻ የሌለው ትግል (7፡15-25)
5. የመለኮታዊ ጽድቅ ሊታዩ የሚችሉ ውጤቶች (8፡1-39)
   ሀ. የመንፈስ ሕይወት (8፡1-17)
   ለ. የፍጥረት መዋጀት (8፡18-25)
   ሐ. የመንፈስ ቋሚ ርዳታ (8፡26-30)
   መ. በመንፈስ የሆነ ጽድቅ የፍርድ ድል (8፡31-39)

መ. የሁሉም የሰው ልጅ መለኮታዊ ተግባር (9፡1-11፡32)
1. የእስራኤል መመረጥ (9፡1-33)
   ሀ. የእምነት ርግጠኛ ወራሾች (9፡1-13)
   ለ. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት (9፡14-26)
   ሐ. የእግዚአብሔር አጠቃላይ እቅድ አረማውያንንም ያካትታል (9፡27-33)
2. የእስራኤል መዳን (10፡1-21)
   ሀ. የእግዚአብሔር ጽድቅ ወይም የሰው ልጅ ጽድቅ (10፡1-13)
   ለ. የእግዚአብሔር ምሕረት ያስገኛቸው መልእክተኞች፣ ለዓለም ተልእኮ የሆነ ጥሪ (10፡14-18)።
   ሐ. የእስራኤል ቀጣይነት ያለው በክርስቶስ አለማመን (10፡19-21)
3. የእስራኤል ውድቀት (11፡1-36)
   ሀ. የአይሁድ ቅሬታ (ቀሪዎች) (11፡1-10)
   ለ. አይሁዳዊ ቅናት (11፡11-24)
   ሐ. የእስራኤል ጊዜያዊ ዕውርነት (11፡25-32)
   መ. የጳውሎስ በደስታ መሞላት (11፡33-36)

ሠ. የመለኮታዊ ጽድቅ ጸጋ ውጤት (12፡1-15፡13)
1. ለመቀደስ መጠራት (12፡1-2)
2. የጸጋ ስጦታዎችን መጠቀም (12፡3-8)
3. አማኞች ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸው ግንኙነት (12፡9-21)
4. ከመንግሥት ጋር የሚኖር ግንኙነት (13፡1-7)
5. ከጎረቤቶች ጋር የሚኖር ግንኙነት (13፡8-10)
6. ከጌታችን ጋር የሚኖር ግንኙነት (13፡11-14)
7. ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ጋር የሚኖር ግንኙነት (14፡1-12)
8. በሌሎች ላይ ያለን ተጽዕኖ (12፡13-23)
9. ክርስቶስን ከመምሰል ጋር ያለን ግንኙነት (15፡1-13)

ረ. መደምደሚያ (15፡14-33)
1. የጳውሎስ የግል እቅዶች (15፡14-29)
2. የጸሎት አደራ (15፡30-33)

ሰ. ቅጥያ ጽሑፎች (16፡1-27)
1. የስንብቻ ሰላምታ (16፡1-27)
2. ቃለ ቡራኬ (16፡25-27)

**የንባብ ዑደት አንድ (ገጽ Viii ተመልከቱ)**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሐተታ ነው፣ ያም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግል ከመተርጎም አኳያ ራሱ ተርጓሚው ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። እርስዎ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜው ቅድሚያ ናችሁ። ይህን በሐተታ አቅራቢው ልዩ ትርጉም መያዝ አይኖርብዎትም።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል በአንድ ጊዜ ያንብቡት። የመጽሐፉን ሙሉውን ክፍል ማዕከላዊ ጭብጥ በራስዎ ቃል ይጻፉት።

1. የሙሉ መጽሐፉ ጭብጥ

2. የሥነ- ጽሑፉ ዓይነት (ዘውግ)

**የንባብ ዑደት አንድ (ገጽ Viii ተመልከቱ)**

ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ ነው፣ ያም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግል ከመተርጎም አኳያ ራሱ ተርጓሚው ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። እርስዎ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜው ቅድሚያ ናችሁ። ይህን በሐተታ አቅራቢው ልዩ ትርጉም መያዝ አይኖርብዎትም።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍል በድጋሚ በአንድ ጊዜ ያንብቡት። ዋናዎቹን ርዕሰ-ጉዳዮች ዘርዝሩና አንዱን ርዕሰ-ጉዳይ በአንድ ዓረፍተ ነገር ያቅርቡ።

1. የመጀመሪያው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ

2. የሁለተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ

3. ሦስተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ

4. አራተኛው ጽሑፋዊ ምድብ ርዕሰ-ጉዳይ

5. ወዘተርፈ

# ሮሜ 1

## በዘመናችን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| ዩ.ቢ.ኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰላምታ | ሰላምታ | ሰላምታ | ሰላምታ | አድራሻ |
| 1:1-7 | 1:1-7 | 1:1-6 | 1:1 | 1:1-2 |
| | | | 1:2-6 | |
| | | | | 1:3-7 |
| | | 1:7ሀ | 1:7ሀ | |
| | | 1:7ለ | 1:7ለ | |
| ጳውሎስ ሮሜን ለመጎብኘት የነበረው ፍላጎት | ሮምን ለመጎብኘት መፈለግ | ምስጋና | የምስጋና እና ጸሎት | ጸሎት እና ምስጋና |
| 1:8-15 | 1:8-15 | 1:8-15 | 1:8-12 | 1:8-15 |
| | | | 1:13-15 | |
| የወንጌል ኃይል | በእምነት ብቻ ኑር | የመልዕክቱ ጭብጥ | የወንጌል ኃይል | ጭብጡ ሲገለጥ |
| 1:6-17 | 1:6-17 | 1:6-17 | 1:6-17 | 1:6-17 |
| የሰው ልጆችበደለኝነት | በኀጢአን ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ | በኀጢአት ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ | የሰው ልጆች በደል | በአሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ |
| 1:18-23 | 1:18-3 2 | 1:18-23 | 1:18-23 | 1:18-25 |
| 1:24-32 | | 1:24-25 | 1:24-25 | |
| | | | | 1:26-27 |
| | | 1:26-27 | 1:26-27 | |
| | | 1:28-32 | 1:28-32 | 1:28-32 |

***ንባብ ዑደት ሦስት***
***በአንቀጽ ደረጃ የደራሲውን ሀሳብ መከተል***

*ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻ የማጥኛ መመሪያ ነው’፣ ይህ ማለት ለራሳችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ ተጠያቂዎች እኛው ራሳችንን ነን:: እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን ልመላለስ ይገባል:: በትርጉም ሂደት ውስጥ አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ዋነኞች በመሆናችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች እነዚህን መለወጥ አይገባም::*

---

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው:: እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል:: እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕሰ-ጉዳይ፣ እውነት፣ ወይም እሳቦት አለው:: እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል:: ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ::

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)፣ አኪያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን:: መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አምክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው:: ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም:: የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው::

አንድን ምዕራፍ በአንድ ጊዜ ንባብ አንብበህ ጨርስ። ዋና መልዕክቱን ለይ። የአንተን መልዕክት ክፍፍል ከአምስት መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር አነጻጽር። ትርጓሜ እንብርት የሆነው የአንቀጽ ክፍፍልን መከተል ምንም እንኳ የደራስውን ዓላማ ለማግኘት ቁልፍ ቢሆንም ነገር ግን የአንቀጽ ክፍፍል ከስህተት የጸዳ ግን አይደለም። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ መልክት ብቻ ይኖረዋል።

1. አንቀጽ አንድ

2. አንቀጽ ሁለት

3. አንቀጽ ሶስት

4. ወዘተ

**አውዳዊ መረዳት**

ሀ. ከመልዕክቱ መግቢያ ከቁጥር 1-7. ይህ ከሁሉም የጳውሎስ መልዕክቶች ረጅሙን መግቢያ ነው። ጳውሎስን በግል ለማያውቁት እንዲያውም ይህ ምንአልባት ስለ እርሱ መጥፎ ነገር ሰምተው ለሚያውቁ ሰዎች እራሱን እና ስነ-መለኮቱን ለማስተዋወቅ ያደረገው ሙከራ ነው።

ለ. ቁጥር 8-12 የምስጋናን ጸሎት የቀረበበት መክፈቻ። ይህ በአጠቃላይ የግሪክ በተለይም በጳውሎስ ደብዳቤዎች መለያ ባሕርይ ነው።

ሐ. ቁጥር 16-17 የመጽሓፉን ጭብጥ ይገልጣል።

መ. ከቁጥር 18 እስከ 3÷20 የዘፍጥረት 3 ነጸብራቅ ነው። (የአይሁድ መምህራን በምያስገርም ሁኔታ ለዚህ ክፍል ትኩረት ሳይሰጡ ነገር ግን ዘፍጥረት 6 የኀጢአት መነሻው አድርገው ይመለከታሉ) የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ያደርግ ዘንድ፣ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ (አነጻጽር ዘፍ 1:26-27)። ነገር ግን የሰው ልጆች አብርሆተ አእምሮን እና የኃይል ተስፋ እና የልቅት መንገድን መረጡ። ውጤቱም ሰዎች በእግዚአብሔር ፊንታ ራሳቸውን ለወጡ ፤(ሰዋዊ ኢ-አማን ሆኑ)።

ሠ. ይህንን ክስተት እግዚአብሔር ፈቅዶታል፣ ምናልባትም አዘጋጅቶታል። በእግዚአብሔር መልክ መሆን ማለት ኃላፊንትን መቀበል፣ ግብረ ገባዊ ተጠያቂ መሆንን፣ የተለያዩ ውጤቶችን ማስከተል የሚችሉ ውሳኔዎችን መስጠት የሚያስችል ነጻ ፍቃድ እንድኖረው ያደርጋል። እግዚአብሔር ከሰዎች በፍቃዳቸው እና (በቃል ኪዳን ግንኙነት) መሠረት ተለየ! ሰዎች እራሳቸውን ከሚያስከትለው ውጤት ጭምር ይመርጡ ዘንድ ፈቀደ። በዚህም እግዚአብሔር አዝኗል (ንጽጽር ዘፍ 6:5-7) ነገር ግን ሰው ልጅ ሙሉ መብት እና ኃላፊነት ነጻ ፈቃድ ያለው ግብረገባዊ ፍጡር ነው። በድግግሞሽ የተገለጹት ሀረጎች "አሳልፎ ሰጣቸው" (አነጻጽር 1:24፣ 26፣ 28) ማለት የዚህን ነጻ ፍቃድ ውጤትን እውቅና መስጠት ማለት እንጂ ሆን ተብሎ በእግዚአብሔር ዘንድ ማጣት ማለት አይደለም። ይህ የእግዚአብሔር ምርጫ አይደለም። ይህ እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው ዓለም ይህ አይደለም (አነጻጽር ዘፍ 3:22፣ 6:5-7፣ 11-13)!

ረ. የ1:18-3:20 ስነ-መለኮታዊ ማጠቃለያ በ3:21-31 ውስጥ ይገኛል። ይህ የመጀመሪያው ወንጌል "መልካም ዜና" ነው፤ ሁሉም የሰው ልጆች ኀጢአተኞች እና የእግዚአብሔር ይቅርታ ያስፈልጋቸዋል። እግዚአብሔር በጸጋው ወደዚያ ጥብቅ ግንኙነት መመለሻ መንገድን አዘጋጅቷል። ( ይህ ማለት በኤደን ገነት ያለው ልምምድ ነው)

ሰ. በዚህ በመጀመሪያው የጳውሎስ ወንጌል አቀራረብ ስነ ጽሑፋዊ ውቅር ውስጥ የሰው ልጆች ለውድቀታቸው በሴጣን ወይም በዳብሎስ ላይ ሳያላክክ የሰው ልጆችን ለውድቀታቸው ተጠያቂ ማድረጉን መመልከት ይቻላል። (ማነጻጸር ሮሜ 1:18-3:20) ይህ ክፍል በዘፍ 3 ላይ ያለውን ስነ መለኮት ነጸብራቅ ነው፤ ነገር ግን ካለ ፈታኝ ነው። (ማነጻጸር ዘፍ 3:12) የሰው ልጆች በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩ ናቸው። (ማነጻጸር ዘፍ 1:26፣ 5:1፣3፣ 9:6) የሰው ልጆች ለመምረጥ መብቱ፣ ኃይሉ እና ኃላፊነት አላቸው። የሰው ልጆች በምርጫቸው በአዳም ውስጥ የወል እንዲሁም በግል ለሆነ ኀጢአት ተጠያቂዎች ናቸው (ማነጻጸር 3:23)።

1፡1-6)
***ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤ በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ።***

1፡1 **"ጳውሎስ"** በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አብዛኛው አይሁዶች ሁለት ስም ነበራቸው፤ አንድ የአይሁድ እና ሌላ የሮምማዊያን ስም ናቸው (*ማነጻጸር ሐዋ* 13፡9)። የጳውሎስ አይሁዳዊ ስሙ ሳኦል ነው። የእርሱ እንደ ጥንቱ የእስራኤላዊያን ንጉሥ ከቢንያም ወገን ነበር። (*ማነጻጸር ሮሜ* 11፡1፤ *ፊል* 3፡5) የሮማዊያን ስሙ ደግሞ የግሪክ ቋንቋ ይዘት ሲኖረው ጳውሎስ ይባላል፤ ትርጓሜውም "ትንሽ" ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው አንድም በቅኖና መጽሐፍት ውስጥ ባልተካተቱት በሁለተኛው ምዕተ ዓመት "የጳውሎስ ሥራ" በመባል በሚታወቀው መጽሐፍት ውስጥ ስለ ተሰሎንቄ በሚገልጸው ምዕራፍ ውስጥ "ጳውሎስ እና ቴክላ" ተብሎ የተጠራው የእርሱ ምስል ነው።

1. በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያንን ያሳድድ ስለ ነበር ስለ እርሱ ማንነት በቅዱሳን ዘንድ በጥቅቱም ሳይታወቅ አይቀርም (አነጻጽር 1ቆሮ 15፡9፣ ኤፌ 3፡8፤ 1ጢሞ 1፡15)
2. ይህ ስም በቀላሉ ከውልደቱ አንስቶ በወላጆቹ የተጠው ሊሆን ይችላል።
3. ሶስተኛው አማራጭ ከሁሉም የተሻለ ነው።

▣ **"እስረኛ ባሪያ"** አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉምኒው፣ ሪቫይስድ ስታንዳርድ ቨርዥን፣ አእቅ ስሉ እና ኢመቅ "ባሪያ" ብሎ ይተረጉመዋል። ይህ ሃሳብ (1) የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት እና የጳውሎስን ባሪያነት ለማሳየት የታሰበ ተቃራን ሀሳብ ልሆን ይችላል፤ ወይም (2) እንደ ብሉይ ኪዳን የክብር ስም ሊሆን ይችላል (አነጻጽር ሙሴ በዘኍ 12፡7 እና በኢያሱ 1፡ 1፤ ኢያሱ በኢያሱ 24፡29፤ እና ዳዊት በመዝ (ስም) እና ኢሳያስ 42፡1፣ 19፣ 52፡13)

▣ **"ሐዋሪያ ሊሆን የተጠራሁ"** ይህ የእግዚአብሔር ምርጫ እንጂ የእርሱ ምርጫ አልነበረም (*አነጻጽር የሐዋ* 9፡15፤ *ገላ* 1፡15፤ *ኤፌ* 3፡7)። ጳውሎስ በአካል አግኝቷት ለማያቃት ቤተ ክርስቲያን ያለውን መንፈሳዊ ብቃት እና ስልጣን በ1ቆሮ 1፡ 1፣ 2ቆሮ 1፡1፣ ገላ 1፡1፣ ኤፌ 1፡1፣ ቆላ 1፡1፣ 1ጢሞ 1፡1፣ ቲቶ 1፡1፡ላይ እንዳደረገው ሁሉ ለዝህይች ቤተ ክርስቲያን እያረጋገጠ ይነግራታል። ልዩ ርዕስ 1፡6 የሚለውን ተመልከት።

"ሐዋሪያ" የሚለው ቃል በመጀመሪያው ምዕተ በፍልስጤም አከባቢ ለሚኖሩ ሰዎች የነበረው ትርጉም፦ "ሕጋዊ ወክል ሆነ የተላከ ሰውን ነው" (ከ2ዜና 17፡7-9 *ጋር ያነጻጽሩ*)። በአዲስ ክዳን ውስጥ ይህ ቃል በሁለት መልኩ በአገልግሎት ላይ ውሏል (1) ለአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት እና ለጳውሎስ፤ (2) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቀጣይነት ለሚቀጥለው መንፈሳዊ ስጦታ (ከ1ቆሮ 12፡28-29፣ ኤፌ 4፡11 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

**ልዩ ርዕስ፦ የተላከ (አፖስቶሎ)**

ይህ "መላክ"ን የሚያመለክት የተለመደ የግሪክ ቃል ነው (አፖስቶሎ)። ይህ ቃል የተለያዩ ስነ መለኮታዊ አጠቃቀሞች ይኖሩታል።

ሀ. በአማሪኛ "እንደራሴ" ብለን እንደምንጠራው ሁሉ የአይሁድ መምህራን ይህንን ቃል በሕጋዊ መንገድ አንድ ሰውን የሚወክል ሰውን ለማመልከት ይጠቀሙበታል (ከ2ቆሮ 5፡20 *ጋር* አነጻጽር)።

ለ. በወንጌላት መጽሓፍት ውስጥ ይህ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ መላኩን ለማመልከት ውሏል። በዮሐንስ ወንጌል ይህ ቃል የኢየሱስን መስሕነት ለማመልከት ውሏል (ከ*ማቴ* 10፡40፤ 15፡24፤ *ማር* 9፡37፤ *ሉቃ* 9፡48 እንዲሁም በተለይም በዮሐ 4፡34፤ 5፡24፣30፣36፣37፣38፤ 6፡29፣38፣39፣40፣57፤ 7፡29፣ 8፡42፣ 10፡36፣ 11፡ 42፣ 17፡3፣8፣18፣23፣25፣ 20፡21 *ጋር* አነጻጽር)። እንዲሁም ኢየሱስ አማኞችን መላኩን ለማመለከት ውሏል (ከዮሐ 17፡18፤ 20፡21 *ጋር* አነጻጽር)።

ሐ. በአዲስ ክዳን ውስጥ ይህ ቃል ለደቀ መዛሙርቱ ውሏል።

1.የመጀመሪያዎቹ ዐስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለማመልከት ውሏል (ከሉ 6፡13፣ የሐዋ 1፡21-22 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

2.የሐዋርያት ልዩ ረዳት እና አጋዥ የሆኑ ሰዎችን ለማመልከት ውሏል

ሀ. ባርናባስ (ከሐዋ 14፡4፣ 14 *ጋር ያነጻጽሩ*)

ለ. አንዲራኒቆንና ዩልያስ (ክንግ ጀምስ ቨርዥን ዩልያን ይለዋል፣ ይህንን ከሮሜ 16፡7 *ጋር ያነጻጽሩ*)

ሐ. አጶሎስ (ቆሮ 4፡6-9

መ. የጌታ ወንድም የሆነው ያዕቆብ (ገላ 1:19)
ሠ. ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስ (1ተሰ 2:6)
ረ. ቲቶም ምንአልባት በዝይህ ተጠርቶ ልሆን ይችላል (2ቆሮ 2:25)
ሰ. አፍሮዲጡም በዝይህ ተጠርቶ ልሆን ይችላል (ፍል 2:25)
3. በቤቴክርስቲያን ውስጥ ያለ ቀጣይ ስጦታ
መ. ጳውሎስ ይህንን መጠሪያ በአብዛኞቹ የእርሱ ደብዳቤዎች ውስጥ የክርስቶስ ወክል እንዲሆን እግዚአብሔር ስልጣንን እንደሰጠው ለማረጋገጥ ተጠቅሞበታል (ከሮሜ 1:1፣ 1ቆሮ 1:1፣ 2ቆሮ 1:1፤ ገላ 1:1፤ ኤፌ 1:1፤ ቆላ 1:1፤ ጢሞ 1:1፤ 2ጢሞ 1:1 እና ቲቶ 1:1 ጋር ያነጻጽሩ)።

▣ ይህ የሚያመለክተው እርሱ በእግዚአብሔር ለዝይህ አገልግሎት የተለየው በአላፈ ጌዜ እንደሆነ ነው (ከኤር 1:5 እና ገላ 1:15 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሁም በነበረበትም ጊዜ ይህ መለየቱ የሚያመለክት ነው። ይህ ምንአልባትም "ፈርሳዊ" በሚለው የአራማይክ ቃል ላይ የተደረገ የቃላት ጫወታ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ፈርሳዊያን ለአይሁዳዊያን ሕግ አጥባቂነት የተለዩ መሆናቸው (እንዲሁም ጳውሎስ (ፊል 3:5) በደማስቆ መንገድ ላይ ከኢየሱስ ጋር ከመገናኘቱ በፊት እንደነበረው) በማሳየት አሁን ግን ለወንጌል የተለየ መሆንን ለማመልከት ነው።

ይህ ቃል "ቅዱስ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ተዛማጅነት ስኖረው ትርጓሜውም "ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ" ማለት ነው (ከዘጸ 19:6፣ 1ጴጥ 2:5 ጋር አነጻጽር)። "ቅዱሳን"፣ "መቀደስ" እና "መለየት" የሚሉ ቃላት "ቅዱስ" (ኀግዮስ) የሚባል ተመሳሳይ የግሪክ ስረወ ግንድ ቃል ነው ያላቸው።

▣ **"ለእግዚአብሔር ወንጌል"** በዚህ አውድ እና (በቁጥር 5) ላይ የሚገኘው "ኢስ" የሚለው የግሪክ የሚያመለክተው የጳውሎስን (ቁ. 1ለ) እና "መለየት (1. ሐ) ላይ ያለውን "የመጠራት" ግብን ነው።

ወንጌል የሚለው ቃል የመጣው ከሁለት የግሪክ ቃላት ጥምረት ስሆን፤ እነርሱም "መልካም" የሚል ትርጓሜ ካለው "ኢዩ" ከሚል የግሪክ ቃል እና "መልዕክት" የሚል ትርጓሜ ካለው "አንግሎስ" ከሚል የግሪክ ቃል ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔር የተገለጠውን አስተምህሮ ለማመልከት ችሏል (ከኤር 31:31-34፣ ሕዝ 36:22-32)ይሄውም እግዚአብሔር እንደሚመጣ ቃል የገባው መስሕ ነው (ቁ 3-4)።

ይህ የጳውሎስ ሳይሆን የእግዚአብሔር ወንጌል ነው (ከ15:16፤ ማር 1:14፤ 1ቆሮ 11:7፤ 1ተሰ 2:2፣8፣9፣ 1ጴጥ 4:17 ጋር አነጻጽሩ)። ጳውሎስ ፈጣርም ወይም ባሕልን የሚለውጥ ሰው ሳይሆን የተቀበለውን እውነት የሚሰብክ ሰው ነበር (ከ1ቆሮ 1:18-25 ጋር አነጻጽር)።

1:2 **"በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው"** ይህ ወንጌል እግዚአብሔር ኋላ ላይ ያሰበው ነገር ሳይሆን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅዱ ነበር (ከዘፍ 3:15፤ ኢሳ 53፤ መዝ 118፣ ማር 10:45፤ ሉቃ 2:22፤ ሐዋ 2:23፤ 3:18፤ 4:28፤ ቲቶ 1:2)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙት ቀደምት ስብከቶች (የእምነት መግለቻዎች) ኢየሱስን የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃላት እና ትንብቶች ፍጻሜ አድርገው ያቀርቡታል።

**ልዩ ርዕስ፡ ኢ መ ቅ**

1. በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔር የተሰጠው የተስፋ ቃል መስሕ የሆነው ኢየሱስ በመምጣቱ አሁን ፍጻሜን አግኝቷል (ሐዋ 2:30፣ 3:19፣24፤ 26:6-7፣22፤ ሮሜ 1:2-4፤ 1ጢሞ 3:16፤ ዕብ 1:1-2፤ 1ጴጥ 1:10-12፤ 2ጴጥ 1:18-19)
2. ኢየሱስ ስጠመቅ በእግዚአብሔር መስሕ ሆኖ ተቀብቷል (ሐዋ 10:38)
3. ኢየሱስ በገሊላ አገገልግሎቱን የጀመረው ቀጥምቀት በኋላ ነበር (ሐዋ 10:37)
4. የአገልግሎቱ መገለጫ የነበረው በእግዚአብሔር ኀይል መልካም እና ድንቅ ነገሮችን ማድረግ ነበር (ማር 10:45፤ የሐዋ 2:22፤ 10:38)።
5. መስሕው የተሰቀለው እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ነበር (ማር 10:45፤ ዮሐ 3:16፤ የሐ 2:23፣ 3:13-15፣ 18፣ 4:11፣ 10:39፣ 26:23፣ ሮሜ 8:34፣ 1ቆሮ 1:17-18፤ 15:3፤ ገላ 1:4፤ ዕብ 1:3፤ 1ጴጥ 1:2፣ 19፣ 3:18፤ 1ዮሐ 4:10)
6. ከሞ ተነስቷል እንዲሁም ለደቀመዛሙርቱ ታይቷል (ሐዋ 2:24፣ 31-32፣ 3:15፣ 26፣ 10:40-41፣ 17:31፤ 26:23፤ ሮሜ 8:34፤ 10:9፤ 1ቆሮ 15:4-7፣ 12፤ 1ተሰ 1:10፣1ጢሞ 3:16፣ 1ጴጥ 1:2፤ 18፣21)
7. ኢየሱስ በእግዚአብሔር አብ ከብሯል እንደሁም "ጌታ" የሚል ስምም ተሰጥቶታል (ሐዋ 2:25-29፣33-36፣ 3:13፣ 10:36፤ ሮሜ 8:34፤ 10:9፤ 1ጢሞ 3:16፤ ዕብ 1:3፤ 1ጴጥ 3:22)
8. አዲስ የእግዚአብሔር ማህበረሰብን ለመመስረት መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷል (ሐዋ 1:8፣ 2:14-18፣ 38-39፣ 10:44-47፣ 1ጴጥ 1:12)

9. ለፍርድ እና ሁሉንም ነገር ለማደስ ዳግም ይመጣል (ሐዋ 3፡20-21፣ 10፡42፤ 17፡31፤ 1ቆሮ 15፡20-28፣ 1ተሰ 1፡10)
10. መልዕክቱን የሰሙ ሁሉ ንሰሃ ሊገቡ እና ልጠመቁ ይገባል (ሐዋ 2፡21፣ 38፣ 3፡19፣ 10፡43፣47-48፣ 17፡30፤ 26፡20፣ ሮሜ 1፡17፤ 10፡9፣ 1ጴጥ 3፡21)

ይህ ዋና መልዕክት ምንም እንኳ የአዲስ ኪዳን ተለያዩ ጸሓፍት በስብከታቸው ለአንዱ ነጥብ አጽኖት ሰጥተውት ለሌላው ብነፍጉትም ይህ ሁሉ ግን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንኳር የስብከቷ አክል ነበር። የማርቆስ ወንጌል ከጴጥሮስ የስብከት መልዕክት ጋር በጣም ተቀራራብ ነው። ማርቆስ በተውፊት ጴጥሮስ በሮሜ የሰበከውን ስብከት በማቀናጀት በመጻፍ የማርቆስን ወንጌል እንደጻፈ ይታመናል። ማቴዎስ እና ሉቃስም የማርቆስን መሠረታዊ የአጻጻፍ መዋቅርን ተከትለዋል፡፡

1፡3 **"ስለ ልጁ ነው"** የወንጌል ማዕከላዊ መልዕክት ከድንግል ማሪያም ተወለደው ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። በብሉይ ኪዳን ሀገር፣ ነጉሥ እንዲሁም መስሑ "ልጅ" ተብለው ተጠርተዋል (2ሳሙ 7፡14፤ ሆሴ 11፡1፤ መዝ 2፡7፤ ማቴ 2፡15)።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በባሪያዎቹ እና በነቢያቱ በኩል ተናግሯል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አገልጋይ አይደለም። እርሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ነው። (ከዕብ 1፡1-2፣ 3፡6፣ 5፡8፣ 7፡28 አነጻጽር)። በሚያስገርም ሁኔት ይህ ስፍራ ጳውሎስ በዝይህ ጽሑፍ በዝይህ ስፍራ ላይ ብቻ ነው ስለ ሥነ ክርስቶስ ያተኮረው። ሮሜ ሙሉ ሥነ መለኮትን የያዘ አይደለም።

**ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ**

ይህ በአዲስ ክዳን ውስጥ ለኢየሱስ ከተሰጡት ስሞች መካከል አንዱ ነው። በእርግጥ ይህ መለኮታዊ ነገር ታሳብ ያደረገ ነው። ይህ ኢየሱስን "ብቸኛው ልጅ" ወይም "ልጄ"፤ እግዚአብሔርን እንደ "አባት" አስቀመጠበት ነው። ነአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል ከ124 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። ኢየሱስ "የሰው ልጅ" ተብሎ የተጠራበትም ቢሆን በዳን 7፡13-14 ባለ ው መሠረት መለኮታዊ የራስ መጠሪያ ነው።

በብሉይ ኪዳን "ልጅ" የሚለው መጠሪያ አራት የተለያዩ ቡድኖችን ለማመልከት ውሏል

1. መላዕክት (ብዙ በብዙ ቁጥር ይገለጣል ከዘፍ 6፡2፣ እዮ 1፡6፣ 2፡1 አነጻጽር)
2. እስራኤልን ንጉሥ (ከ2ነገ 7፡14፤መዝ 2፡7፤ 89፡26-27 አነጻጽር)
3. የእስራኤል ሀገር በአጠቃላይ (ከዘጸ 4፡22-23፤ ዘዳ 14፡1፤ ሆሴ 11፡1፤ ሚል 2፡10 ጋር አነጻጽር)
4. የእስራኤል መሳፍንት (ከመዝ 82፡6 ጋር አነጻጽር

ከዚይህ በላይ ከተጠቀሱት ሁለተኛው አጠቃቀም ነው ከኢየሱስ ጋር ግንኙነት ያለው። በዚይህ መንገድ "የዳዊት ልጅ" እና "የእግዚአብሔር ልጅ" ሁለቱም ከ2ሳሜ 7፤ ከመዝ 2 እና 89 ጋር ይገናኛሉ። በብለይ ኪዳን ውስጥ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ቃል መስሑን ለማመልከት ብቻ ውሎ አያውቅም፤ ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን እንደሚመጣው እንደ አንዱ "የተቀባው" የእስራኤል ንጉሥ እንጂ። ነገር ግን ዴድ ሲይ መጽሐፍ ተብለው በሚጠሩት መጽሐፍት ውስጥ ግን ይህ መጣርያ መስሒያዊ ስያሜን ታሳብ አድረጎ ተገኝቷል (የዚህን ተጨማሪ መረጃ Dictionary of Jesus and the Gospels, ገጽ 770 ላይ ይመልከቱ)። በተጨማሪም "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠሪያ በሁሉት በጨለማው ዘመን በተጻፉ የአይሁዳዊያን መጽሐፍት ውስጥ ተገኝተዋል። (ከ2ኢድርስ 7፡28፣ 13፤ 32፣37፣52፣ 14፡9 እና 1ሔኖክ 105፡2 ጋር አነጻጽር)።

1. ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለኢየሱስ የዋለበትን መንገድ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት በዙ ክፍሎችን እንመለከታለን፡-ከፍጥረት በፊት መኖሩን (ዮሐ 1፡1-18)
2. ከደንግል በልዩ ሁኔታ መወለዱን (ማቴ 1፡23፤ ሉቃ 1፡31-35)
3. ጥምቀቱን (ማቴ 3፡17፤ ማር 1፡11፣ ሉቃ 3፡222። ከሰማይ የተሰማው እግዚአብሔር ድምጽ በመዝ 2 ላይ ያለውን መከራን ለመከቀበል የመጣው በኢሳ 53 ላይ ከተገለጸው ጋር እንድዋሃድ አድርጎታል።)
4. የእርሱ በሴታን መፈተን (ማቴ 4፡ 1-11፣ ማር 1፡12፣ 13፣ ሉቃ 4፡1-3። የተፈተነው ልጅነቱን እንድጠራጠር ነው ወይስ በትንሹ ተልዕኮውን በመስቀል በኩል ሳይሆን በሌላ መንገድ ይፈጽም ዘንድ ነው።)
5. ተቀባይነት ባሌላቸው ተናዛዮች ስለ እርሱ የተናገሩት ምስክርነት
   ሀ. ዳብሎስ (ማር 1፡23-25፣ ሉቃ 4፡31-37፣ ማር 3፡11-12)
   ለ. ያላመኑ ሰዎች (ማቴ 27፡43፣ ማር 14፡61፣ ዮሐ 19፡7)
6. በእራሱ ደቀ መዛሙርት ስለ እርሱ የተነገረ ምስክርነት
   ሀ. ማቴ 14፡33፣ 16፡16
   ለ. ዮሐ 1፡34፣ 49፣ 6፡69፣ 11፡27
7. እርሱ ስለ እራሱ የመሰከረው ምስክርነት
   ሀ. ማቴ 11፡25-27

ሀ. ዮሐ 10፡36

8. እግዚአብሔርን እንደ አባት የሚጠቀምበት የተለመዱ ምሳሌዎቹ
   ሀ. ለእግዚአብሔር "አባ" የሚለው ቃል መጠቀሙ
      1. ማር 14፡36
      2. ሮሜ 8፡15
      3. ገላ 4፡6
   ለ. ከመለኮት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ አባት (ፓተር) የተጠቀመበት መንገድ ለማጠቃለል ያህል "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ቃል ብሉይ ኪዳንን ለሚያውቁ እንዲሁም የብሉይ ኪዳንን የተስፋ ቃል እና የቃሉን አጠቃቀም ለሚያውቁ ሰዎች ትልቅ ሥነ መለኮታዊ ትርጓሜ ያለው ነው፡፡ የአዲስ ክዳን ጸሓፍ ግን ስለ ቃሉ አጠቃቀም ፍራቻ አላቸው፤ ምክንያቱም በአሕዛብ መካከል ካሉት "የአማልክቶች" አመለካከት የተመሳ ነው፡፤ እነዚህ አማልክት ከሴቶች ጋር በመገናኘት በጣም "ትንንሽ" ወይም "ትልልቅ" ልጆችን ይወልዳሉ ይላሉና፡፡

▣ "ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ" ይህ ከሁለተኛ ሳሙኤል 7 ጋር ተዛማጅ ነው፡፡ መስሑ ከዳዊት ከነገሥታት ዘር (ከኢሳ 9፡ 7፣ 11፡1፣ 10፣ ኤር 23፡5፣ 30፡9፣ 33፡15 ጋር አነጻጽር) ከይሁዳ ነገድ የሆነ (ከዘፍ 49፡4-12፤ ኢሳ 65፡9)፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ኢየሱስ በዚህ መጠርያ ብዙ ጊዜ ተጠርቷል (ከ9፡27፤ 12፡23፤ 15፡22፤ 20፡30) ይህ የሚያመለክተው አይሁዳዊያን ስለ መጭው አዳኝ የነበራቸውን ተስፋ ያንጸባርቃል፡፡

ጳውሎስ የኢየሱስን ይህንን ገጽታ ላይ ትኩረት አለመስጠቱ የሚያስገርም፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሀሳብ ያነሳው በዚህ ስፍራ እና በ2ጢሞ 2፡8 ላይ ብቻ ነው፡፡ ሁለቱም ክፍሎች ምንአልባትም የተወሰዱት ከጥንት ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ ላይ ነው፡፡

**አየመመቅ፣**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እንደ ሥጋ"** |
| **አእቅ** | **"እንደ ሰውነቱ"** |
| **ኢመቅ** | **"እንደ ሰው ተፈጥሮ"** |

ይህ የትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ በመሆን በመጀመሪያ ምዕተ ዓመት ኃይማኖታዊ አለም ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት የሚያረጋግጥ ነው (1ዮሐን 1፡1-4፤ 4፡1-3)፡፡ ይህ ቁጥር እንደሚያሳየው ጳውሎስ "ሥጋ" (ሳርካ) የሚለው ቃል ሁል ጊዜ መጥፎ ነገር ለማመልከት እንደማይጠቀምበት ያመለክትል (ከ2፡28፤ 9፡3 ጋር አነጻጽር)፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ብዙ "ሥጋን" ከ"መንፈስ" ጋር በማነጻጸር ያስቀምጠዋል (ከ6፡19፤ 7፡5፣ 18፣ 25፣ 8፡3-9፣12፣ 13፣ 1ቆሮ 5፡5፣ 2ቆሮ 1፡17፤ 11፡18፣ ገላ 3፡3፤ 5፡13፣ 16፣17-19፣ 24፣ 6፡8፤ ኤፌ 2፡3፤ ቆላ 2፡11፤13፣ 18፣ 23)

በቁጥር 4 ላይ ኢየሱስ ሰውም (እንደ ሥጋ ቁ. 3) መለኮትም (እንደ መንፈስ ቁ. 4)፡፡ ይህ የትስብእት አስተምህሮ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው (1ዮሐንስ 4፡1-3)፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ እራሱ የተመረጠ "የሰው ልጅ" እንደሆነ አመላካች ነው (መዝ 8፡4፤ ሕዝ 2፡1 [ሰው] ዳን 7፡13 [መለኮት]፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሥጋ (ሳርካ)**

ይህ የሚያመለክተው ሰዋዊ ጥበብን ወይም ምድራዊ መስፈርትን ነው (1ቆሮ 1፡20፣ 2፡6፣8፣ 3፡18)፡፡ ጳውሎስ በጽሑፎቹ ውስጥ ሥጋ (ሳርካ) የሚለውን ቃል በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሚል፦

1. የሰው ልጅ አካል (ሮሜ 2፡28፣ 1ቆሮ 5፡5፤ 7፡28)
2. የሰው ልጅ የዘር ትውልድ ( የአባት-ልጅ፣ ሮሜ 1፡3፤ 4፡1፤ 1ቆሮ 10፡18)
3. የሰው ልጆችን በጠቅላላ (1ቆሮ 1፡26፣ 29) በዘፍ 3 ላይ በተከሰተው
4. የሰው ልጆች ውድቀት ምክንያት የሚከሰት የሰው ልጆች ድካምን (ሮሜ 6፡19፣ 7፡18)

1፡4 "ስለ ተገለጠ" እግዚአብሔር ኢየሱስን "የእግዚአብሔር ልጅ" አድርጎታል፡፡ ይህ እንድሁ የኢየሱስ መጀመሪያ ቤተልሔም ነው ማለት አይደለም ወይም ኢየሱስ ከአባቱ ያንሳል ማለት አይደለም፡፡ ስለ ሥላሴ በቀረበው ልዩ ርዕስ ስር በቁጥር 8፡11 ያለውን ተመልከት፡፡

▣ "የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ" የአዲስ ኪዳን ጸሓፍት ብዙ ጊዜ ለኢየሱስን "እግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠሪያው አይጠቀሙም ነበር፡፡ (ማቴ 4፡3) ይህ ትክክል ያለሆነ የግሪክ አማልክት አፈታርክ ተጽእኖ ምክንያት (ለድንግልም መውለድም ተመሳሳይ ነው) ሊሆን ይችላል፡፡ የኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት "ብቸኛ፣ አንዲያ" (ሞኖጅነስ) በሚሉ ገላጭ ቃላት ተለይቶ ይገለጻል (ዮሐ 1፡18፤ 3፡16፤18፤ 1ዮሐ 4፡9)፡፡ የዚህ ትርጓሜ "ኢየሱስ ፣ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ" ማለት ነው፡፡

አዲስ ኪዳን ሁለት ከእግዚአብሔር አብ እና ልጅ በመሆነው ከኢየሱስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥነ መለኮታዊ አእማዶቸ አሉ (1) እኩል ናቸው (ዮሐ 1፡1፤ 5፡18፤ 10፡30፣ 14፡9፤ 20፡28፤ 2ቆሮ 4፡4፣ ፊል 2፡6፣ ቆላ 1፡15፣ ዕብ 1፡3) እና (2) የተለያዩ አካላት ናቸው (ማር 10፡18፣ 14፡36፣ 15፡34)።

▣ *"ከሙታን መነሣት"* እግዚአብሔር አባት ለኢየሱስን ሕይወት እና መልዕክትን እርሱን ከሞት በማስነሳት ማረጋገጫ ሰጥቷል (4፡24፣ 6፡4፣ 9፡ 8፡11)። የኢየሱስ አማላክነት (ዮሐ 1፡1-4፣ ቆላ 1፡15-19፣ ፊል 2፡6-11) እና ትንሳዔ (4፡15፣ 1ቆሮ 15) የክርስትና ሁለቱ አእማዶች ናቸው።

▣ ይህ ቁጥር ብዙውን ጊዜ "ተቃባት" ተብሎ የሚጠራውን፤ ኢየሱስ ለታዛዥ ለሆነው አኗኗሩ እግዚአብሔር ኢየሱስን ሽልማት እና ክብርን ሰጠው ለሚል የስህተት ትምህርት ለማስተማር ይጠቀሙበታ። ይህ የስህተት ትምህርት ኢየሱስ በማንነቱ፣ ሁል ጊዜ መለኮት ሳይሆን እግዚአብሔር ከሙታን ባስነሳው ጊዜ መለኮት እንደሆነ ያስተምራል። ምንም እንኳ ይህ ስህተት ቢሆንም፣ እንደ ዮሐንስ 1 እና 17 ካሉ ብዙ የመጻሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሀሳብ እጅግ የራቀ ቢሆንም ኢየሱስ ከሞት በተነሳበት አስደናቅ ነገር ግን ተከናውኗል። በእርግጥ መለኮት ሽልማትን እንዴት መቀበል እንደሚችል ማስረዳት አስቸጋር ቢሆንም ነገር ግን የሆነው ነገር ያ ነው። ምንም እንኳ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ዘላለማዊ ክብርን በእኩልነት ቢጋራም፣ የተሰጠውን ደንነት ሥራን በተሳካ መልኩ ስለፈጸመ የነበረው ክብር በሆነ መልኩ ጨምሯል። ትንሳኤ እግዚአብሔር አብ የናዝሬቱ ኢየሱስን ሕይወት፣ ምሳሌ፣ ትምህርት እና የመስዋዕትነት ሞት ማረጋገጫ ነው፤ ዘላለማዊ መለኮት፣ ሙሉ ሰው፣ ፍጹም አዳኝ ፍጹም ልዩ ልጅ በመሆን ተመለሰ እንዲሁም ሽልማትን አገኘ። ተቃባት የሚለውን ተመልከት።

▣

**አአመመቅ** *"እንደ ቅድስና መንፈስ"*
**አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** *"እንደ ቅድስና መንፈስ"*
**አእቅ** *"እንደ መለኮታዊ ቅድስና መንፈስ"*
**ጀሩሳሌም ባይብል** *"እንደ መንፈስ፣ የቅድስና መንፈስ አሠራር"*

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በዚህ ክፍል ውስጥ መንፈስ የሚለውን ቃል ዬትኛው መንፈስ እንደሆነ ለመለየት ይጥራሉ። አንዳንዶች ይህ የሚያመለክተው  የኢየሱስን መንፈስ እንደሆነ ይናገራሉ። ምክንያቱም የእግዘብሔር አብ መንፈስ እንዳለ ሁሉ  የኢየሱስም መንፈስ ይኖራልና። የጥንቱ የዕብራይስጥ እና የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ስምን የመለያ ስርዓት፣ ስርዓተ ነጥብ፣ የቁጥር እና የምዕራፍ ክፍፍል አልነበረውም። ስለዚህም እነዚህ ሁሉ ነጥቦች ትውፊት ወይም የተርጓሚዎቹ መረዳት ነው።

ቁጥር 3 እና 4ን የምንረዳበት ሦስት መነንገዶች አሉ፦

1. የኢየሱስን ሁለቱን፣ መለኮታዊ እና ሰዋዊ ባሕርይውን እንደሚያመለከት፡
2. በምድር ላይ ሲኖር የነበረውን ሁለት ደረጃዎች፣
3. ሰዋዊ እና የትንሳኤው ጌታ የሚያመለክት ነው

▣ **"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ"** ከሚለው ጋር ትይዩ እንደሆነ የሚያሳይ

▣ **"ኢየሱስ"** የአራማያን ቋንቋ የሆነውኢየሱስ የሚለው ስም ከዕብራይስጡ ኢያሱ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ቃል የ"ያሕዌ" እና "ደንነት" የሚሉ ሁለት ቃላት ጥምረት የተገኘ ነው። ስለዚህም "ያሕዌ ያድናል"ወይም "ያሕዌ ይታደጋል" ወይም "ያሕዌ ደንነት ነው" የሚል ትርጓሜ ሊኖረው ይችላል። ትክክለኛው የቃሉ ትርጓሜ ከማቴ 1፡21፣ 25 ላይ ይገኛል።

▣ **"ክርስቶስ"** ይህ መስሕ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የግሪክ ትርጓሜው ሲሆን ትርጉሙም "የተቀባው" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የተለያዩ መሪዎች (ነቢያት፣ ካህናት እና ነገሥታት) በእግዚአብሔር መመረጣቸው እና በእርሱ መታጠቃቸውን ምልክት ይሆን ዘንድ ተቀብተው ነበር። ኢየሱስ እነዚህ ሦስቱን ቢሮዎች በሕይወቱ ፈጽሞአቸዋል (ዕብ 1፡ 2-3)

▣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አግዚአብሔር ልዩ የሆነ የጽድቅ ዘመንን የሚያገለግል "የተቀባውን" እንደሚልክ ተንቢዬ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልዩ "አገልጋይ"፣ "ልጅ" እና "መስሕ" ነበር።

▣ "ጌታ" በአይሁዳዊያን ዘንድ ይህ ያሕዌ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስሙ ነው፤ ይህ ቃል ቅዱስ ከመሆኑ የተነሳ የአይሁድ መምህራን መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ሰዓት ይህንን ቃል "ጌታ" (አዶናይ) በሚል ሌላ ቃል ይተኩታል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ስም በከንቱ በመጥራት በዚያ ከአስርቱ ትዕዛዛት መካከል አንዱ የሆነውን እንዳይተላለፉ ስለሚፈሩ ነው (ዘጸ 20፡7፣ ዘዳ 5፡11)። የአዲስ ኪዳን ጸሓፍት ኢየሱስን "ጌታ" (ኩርዮስ) ብለው የሚጠሩት በሥነ መለኮታዊ አውዱ ውስጥ ሆነው ስለሆነ፤ የሚያረጋግጡልን የእርሱን መለኮታዊነት ነው (ሐዋ 2፡36፣ ሮሜ 10፡9-13፣ ፊል 2፡6-11)።

**ልዩ ርዕስ፦ የመለኮት ስም**

ሀ. ኤል

1. ይህ ለመለኮት በጠቅላላ በጥንት ጊዜ ይውል የነበው ስም በግልጽ አይታወቅም፤ ነገር ግን እንኳ ብዙ ምሁራን ይህ ቃል የአካዲያን ቋንቋ ሥረወ ግንድ እንዳለው ያምናሉ፤ ትርጓሜውም "መጠንከር" ወይም "ኃያል መሆን"ማለት ነው። (ዘፍ 17፡1፤ ዘኍ 23፡19፤ ዘዳ 7፡21፤ መዝ 50፡1)
2. በከነዓናዊያን ፓንቶን ትልቁ አምላካቸው ኤል ነው (ራስ ሻማራ ጽሑፍ እንደሚለው)
3. በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኤል ከሌሎች ቃላት ብዙ ጊዜ በጥምረት አይመጣም። ይህ ጥምረት የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
   ሀ. ኤል-ኤሎን (ልዑል እግዚአብሔር) ዘፍ 14፡ 18-22፤ ዘዳ 32፡8፤ ኢሳ 14፡14
   ለ. ኤል-ሮኢ ("እግዚአብሔር ያያል" ወይም "እግዚአብሔር እራሱን የሚገልጥ ነው") ዘፍ 16፡13
   ሐ. ኤል-ሻዳይ ("እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ርሁሩ ነው" ወይም "የተራሮች አምላክ") ዘፍ 17፡1፣ 35፡11፣ 43፡14፤ 49፡25፤ ዘጸ 6፡3
   መ. ኤል-ኦላም (ዘላለማዊ አምላክ) ዘፍ 21፡33። ይህ ቃል እግዚአብሔር ለዳዊት ከገባው ቃል ጋር ሥነ-መለኮታዊ ቁርኝት አለው። 2ሳሙ 7፡13፣16
   ሠ. ኤል-ብሪ ("የቃል ኪዳኑ አምላክ") መሣ 9፡46
4. ኤል ብዙ ጊዜ ከእነዚህ ቃላት ጋር ይጠቀሳል፦
   ሀ. ያሕዌ በመዝ 85፡8፤ ኢሳ 42፡5
   ለ. ኤሎሄም በዘፍ 46፡3፤ ኢዮ 5፡8፣ "የአባቶችህ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ"
   ሐ. ሻዳይ በዘፍ 49፡25
   መ. "ቀናተኛ" በዘጸ 34፡14፤ ዘዳ 4፡24፤ 5፡9፤ 6፡15
   ሠ. "መሐሪ" በዘዳ 4፡31፤ ነህ 9፡31፤ "ታማኝ" በዘዳ 7፡9፣ 32፡4
   ረ. "ታላቅ እና የሚያስፈራ" በዘዳ 7፡21፤ 10፡17፤ ነህ 1፡5፤ 9፡32፤ ዘዳ 9፡4
   ሰ. "አዋቂ" በ1ሳሙ 2፡3
   ሸ. "አምባ" 2ሳሙ 22፡33
   ረ. "በቀሌን የሚመልስልኝ" በ2ሳሙ 22፡48
   ቀ. "ቅዱሱ" በኢሳ 5፡16
   በ. "ኃያል" በኢሳ 20፡21
   ተ. "መድኃኒቴ" በኢሳ 12፡2
   ቸ. "ታላቅ እና ኃያል" በኤር 51፡56
   ኘ. "ፍዳ" በኤር 51፡56
5. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና የሚባሉ የእግዚአብሔር ስሞች ጥምረት በኢያሱ 22፡22 ላይ ይገኛል። (ኤል፣ ኤሎሄም፣ ያሕዌ)

ለ. ኤለዮን

1. የዚይህ ቃል መሠረታዊ ትርጉሙ "ትልቅ"፣ "የከበረ" ወይም "ከፍ ከፍ ያለ" ማለት ነው (ዘፍ 40፡17፣ 1ነገ 9፡8፤ 2ነገ 18፡17፣ ነህ 3፡25፣ ኤር 20፡2፣ 36፡10፤ መዝ 18፡13)
2. ይህ ቃል ከሌሎች የእግዚአብሔር ስሞች እና መጠሪያዎች ጋር በተለያየ መንገድ ትይዩ በሆነ መልኩ ተገልጿል።
   ሀ. ኤሎሄም- መዝ 47፡1-2፣ 73፡11፤ 107፡11
   ለ. ያሕዌ- ዘፍ 14፡22፣ 1ሳሙ 22፡14
   ሐ. ኤልሻዳይ- መዝ 91፡1፣9
   መ. ኤል- ዘኍ 24፡16
   ሠ. ኤላህ- ይህ ቃል በብዛት በዳንኤል 2-6 እና በዕዝራ 4-7 ላይ የሚገኝ ስሆን ኢላር ከሚል ቃል ጋር ተዛማጅነት ያለው ነው (ይህ ቃል በአራማይክ "ለታላቁ አምላክ" የሚሰጥ ስያሜ ነው) በዳን 3፡26፣ 4፡2፣ 5፡18፣21።
3. ይህ ቃል እስራኤላዊያን ባልሆኑ ሰዎች ብዙ ግዜ ጥቅም ላይ ይውል ነበር።
   ሀ. መልከ ጼዴቅ ዘፍ 14፡18-22
   ለ. በለዓም ዘኍ 24፡16

ሐ. ሙሴ፣ በዘዳ 32:8 ላይ ስለ አሕዛብ ስናገር

መ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለአሕዛብ የተጻው የሉቃስ ወንጌል የዚይህ ቃል የግሪክ አቻው የሆነውን ሁፕስቶስ የሚለውን ቃል ተጠቅሟል:: (1:32፣35፣76፣ 6:35፣ 8:28፣ የሐዋ 7:48፤ 166:17)

ሐ. ኤሎሂም (ብዙ ቁጥር)፣ ኤሎሃ (ነጠላ ቁጥር) ሲሆን በዋናነት በግጥም ውስጥ ይጠቀሙታል

1. ይህ ቃል ከብሉይ ኪዳን ውጭ አልተገኘም
2. ይህ ቃል የእስራኤል አምላክን ያመለክታል ወይም የአሕዛብ አማልክትንም ሊያመለክት ይችላል (ዘጸ 12: 12፣ 20:3):: የአብረሃም ቤተ ሰቦች ብዙ አማልክትን የሚያመልኩ ነበሩ:: (ኢሳ 24:2)
3. ይህ ቃል የእስራኤላዊያን መሣፍንትም ሊያመለክት ይችላል:: (ዘጸ 21:6፣ መዝ 82:6)
4. በዘዳግም 32:8 ላይ ሰባ ሊቃውንት በመባል በሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ኤሎሂም የሚለው ቃል ለሌሎች መንፈሳዊያን አካላትንም ለማልከት ውሏል(መላእክትን፣ ዳብሎስን)፤ መዝ 8:5፣ ኢዮ 1:6፣ 38: 7:: እንዲሁም ይህ ቃል መሣፍምትንም ሊወክል ይችላል:: (ዘጸ 21:6፤82:6)
5. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ቃል በመጀመሪያ የመለኮት ስያሜ/መጠሪያ ነው:: (ዘፍ 1:1) ከያሕዌ ጋር በጥምረት በዘፍ 2:4 እስከ ቀረበበት ድረስ ቃሉ ሌሎችን የማያካትት ነው:: መሠረታዊ በሆነ የሥነ-መለኮት እሳቤ ይህ ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በዚይች ምድር ውስጥ የሚኖሩ ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ፈጣር፣ እንድቀጥል የሚያደረግ እና ሰጭ ነው:: (መዝ 104)ኤል ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጓሜ ያለው ነው:: (ዘዳ 32:15-19) እንዲሁም በመዝ 14 ላይ የተገለጠው (ኤሎሄም) በመዝ 53 ከተገለጠው (ያሕዌ) ከመለኮታዊ ስም በስተቀር በፍጹም ተመሳሳይ ነው::
6. ምንም እንኳ ይህ ቃል የብዙ ቁጥርን አመልካንች ቢሆንም፣ እንዲሁም ለሌሎች አማለክትም ስምነት የዋለ ቢሆንም ነገር ግን ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው የእስራኤልን አማላክ ነው:: ነገር ግን አንድ አምላክነትን ለማመልከት ብዙ ጊዜ ነጠላ ግስን ይጠቀማል::
7. ይህ ቃል እስራኤላዊያን ባልሆኑ ሰዎች አምላካቸውን መጠርያ ስምነት ውሏል::
   ሀ. መልከ ጼዴቅ ዘፍ 14:18-22
   ለ. በለዓም ዘኍ 24:16
   ሐ. ሙሴ፣ በዘዳ 32:8 ላይ ስለ አሕዛብ ስናገር
8. የአንድ አምላክ አምላኪ የሆኑት እስራኤላዊይን አምላክ መጠሪያ ስሙ የብዙ ቁጥር አመልካች መሆኑ የሚያስገርም ነው! ምንም እንኳ ይህ ለምን እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም እነዚህ ጥቅት መላ ምቶች ናቸው፦
   ሀ. ዕብራዊያን ብዙ ጊዜ ብዙ ቁጥርን የሚጠቀሙት አጽኖት ለመስጠት ነው:: ከዚይህ ሀሳብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ለብዙ ዘመናት በኃላ የተጀመረው የግሪክ ስዋሰው አካል "አክብሮትን የሚያመለክት ብዙ ቁጥር" ሲሆን ይህ ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል አገልግሎቱ ሀሳቡ ጎልቶ እንድወጣ ማድረግ ነው::
   ለ. ይህ ቃል ምን አልባትም እግዚአብሔር ከመላእክት ጋር በሰማያዊ ስፍራ የሚያደሪገው ስብሰባ እና ውሳኔን የሚያስተላልፍበት የመላእክት ጉባኤን ሊያመለክት ይችላል (1ነገ 22:19-23፣ ኢዮ 1:6፣ መዝ 82:1፣ 89:5፣7)::
   ሐ. ይህ ቃል ምንአልባትም በአዲስ ኪዳን ተገለጠውን አንደ አምላክ በሦስት አካልነት የመገለጡን እውነት ሊያሳይ ይችላል:: በዘፍ 1:1 እግዚአብሔር አብ ፈጠረ፤ በዘፍጥረት 1:2 መንፈስ ይሰፍፍ ነበር እንዲሁም ከአዲስ ኪዳን እንደሚንረዳው ኢየሱስ በፍጥረት የእግዚአብሔር አብ ሠራተኛ ነበር (ዮሐ 1፤3፣ 10፣ ፤ ሮሜ 11:36፣ 1ቆሮ 8:6፤ ቆላ 1:15፣ ዕብ 1:2፣ 2:10)::

መ. ያሕዌ

1. ይህ ስም ይህ አምላክ ቃል ኪዳንን ማድረግ የሚችል አምላክ መሆኑን የሚያመለክት ነው፤ እግዚአብሔር አዳኝ እና ታዳጊ አምላክ መሆኑን ያሳያል:: ሰዎች ቃል ኪዳናቸውን ሊያፈርሱ ይችላሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለቃሉ፣ ለተስፋ ቃሉ እና ለቃል ኪዳኑ የታመነ ነው (መዝ 103)::

   ይህ ቃል ለመጀመሪያ ከያሕዌ ጋር በጥምረት የቀረበው በዘፍ 2:4 ላይ ነው:: በዘፍጥረት 1-2. ውስጥ ሁለት የስነ ፍጥረት ታርኮች የሉም፤ ሁለት የተለያዩ አጽኖት የተሰጣቸው ነገሮች አሉ:: (1) እግዚአብሔር የአጽናፍ አለሙ (የቁሳዊ አካል) ፈጣር መሆኑ እና (2) እግዚአብሔር ልዩ ፍጥረት ሆነው የሰው ልጅ ፈጣሪ መሆኑ:: ዘፍጥረት 2:4 የሚጀምረው ለሰው ልጆች የተሰጣቸው ልዩ ስፍራ እና ዓላማ ምን እንደሆነ በሚገልጠው ልዩ መገለጥ ነው:: በተጨማሪም ኀጢአት ያስከተለው ችግር እና ለሰው ልጆች ከተሰጣቸው ልዩ ስፍራ የተነሳ የተከሰተው አመጽን ያመለክታል::
2. ዘፍጥረት 4:26 እንዲህ ይላል "በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ::" (ያሕዌ) ነገር ግን ዘጸ 6:3 እንደሚናገረው ቀደምት የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች (አባቶች እና ቤተ ሰቦቻቸው) እግዚአብሔርን የሚያውቁት ኤል ሻዳይ በሚለው ስሙ ብቻ ነበር:: ያሕዌ ለሚለው የእግዚአብሔር ስም ማብራሪያ የተሰጠው በዘጸ 3:13-16 ላይ እንድ ጊዜ ብቻ በተለይም በቁጥረ 14 ላይ ነው:: ነገር ግን የሙሴ አጻጻፍ ብዙ ጊዜ ቃላቶችን በታወቁ ቃላት ፍች በመለወጥ መጠቀም እንጂ ሥረወ ግንዲ ጥናት ላይ ያተኮረ አይደለም (ዘፍ 17:5፣ 27:36፣ 29:13-35):: ስለዚህ ስም ምንነት ብዙ አይነት አመላካከቶች አሉ (ከአይ.

ዲ. ብ ቁ 2 ገጽ 409-411 የተወሰደ)
ሀ. ቃሉ የአረብ ሥረወ ግንድ ሲኖረው "ፍጹም ፍቅርን ያሳያል"
ለ. ቃሉ የአረብ ሥረወ ግንድ ሲኖረው "ማፈንዳት" (ያሕዌ የማዕበል አምላክ)
ሐ. ቃሉ የከነዓናዊያን ሥረወ ግንድ ሲኖረው "መናገር"
መ. የፊኖሲያዊያንን ጥንታዊ ጽሑፍ ተከትሎ፣ ምክንያታዊ የሚል ትርጉም አለው ሲሆን "እንዲቀጥል የሚያደረግ" ወይም " የሚያቋቁም" ማለት ነው።
ሠ. ቃሉ በዕብራይስጥ ቋዋል አወቃቀር የመጣ ከሆነ "ያለ እና የነበር" ወይም " ያለ" (ለወደፊቱም "የሚኖር") የሚል ትርጓሜ አለው።
ረ. ከዕብራይስጥ ሄፊል አወቃቀር መጣ ከሆነ "እንዲኖር የሚያደረግ" የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል።
ሰ. "የሚኖር" ከሚል የዕብራይስጥ ቃል ሥረወ ግንድ የመጣ ሲሆን (ምሳሌ 3፡20) ትርጓሜውም "ሲኖር ነበር ወይም ብቸኛው ኗሪ" የሚል ይሆናለ።
ሸ. ከዘጸአት 3፡13-16 አውድ በመነሳት "ያለ እና የሚኖር" ወይም "እንደነበርኩ እኖራለሁ" የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል ።
   (1) ያህ (ምሳሌ ሃሌሉ-ያህ)
   (2) ያሁ (ምሳሌ ስም፡ ኢሳያስ)
   (3) ዬ (ምሳሌ ስም፡ ኢዬኤል)

3. በኃላ ዘመን በተነሱት አይሁደዊያን ዘንድ ይህ ስም ቅዱስ (ቴትራግራሜንቴሽን) ከመሆኑ የተነሳ በዘጸ 200፡7፣ ዘዳ 5፡11፣ 6፡13 ላይ አለውን እግዚአብሔርን ትዕዛዛት ላለመተላለፍ ሲሉ እስራኤላዊያን ይህንን ስም አይጠሩትም ነበር። ስለዚህም ይህንን ስም በሌላ "ባለቤት"፣ "ጌታ"፣ "ባለ ንብረት" ተብሎ በተተረጎመ አዶን - አዶናይ (ጌታዬ) በሚል የዕብራይስጥ ቃል ተክተውታል። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍን በሚያነቡበት ወቅት ይህ ቃል ሲገጥማቸው "ጌታ" በሚለው ይተኩታል። ስለዚህም ነው በአማሪኛው መጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሕዌ የሚለው ቃል ጌታ ተብሎ የተተረጎመው።
4. እንደ ኤል ሁሉ ያሕዌ የሚለው ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በመዋኂድ የእስራኤል አምላክ የገባውን ቃል ኪዳን የተወሰነ መገለጫ አጽኖት በመስጠት ይገልጻል። ምንም እንኳ ብዙ ከዚህ ስም ጋር ሲጣመሩ የሚችሉ ቃለት ቢኖሩም እነዚህ ግን ጥቂቶቹ ናቸው፦
ሀ. ያህዌ ይርኤ (ያህዌ ያዘጋጃል) ዘፍ 22፡14
ለ. ያህቂ ሮፍኸካ (ያህዌ ፈዋሽ) ዘጸ 15፡26
ሐ. ይህዌህ ንሲ (ያህዌ አርማዬ) ዘጸ 17፡15
መ. ያህዌ ሜቃዲሽኬም (ያህዌ ቀዳሽ) ዘጸ 31፡13
ሠ. ያህዌ ሻሎም (ያህዌ ሰላም) መሳ 6፡24
ረ. ያህዌ ሰንበት (ያህዌ የሠራዊ) 1ሳሙ 1፡3፣ 4፡4፣5፤2፣ ብዙ በነቢያት መጽሓፍት ውስጥ ይገኛል)
ሰ. ያህዌ ሮኢ (ያህዌ እረኛዬ ነው) መዝ 23፡1
ሸ. ያህዌ ሲደቂኑ (ያህዌ ጽድቃችን) ኤር 23፡6
በ. ያህዌ ሻማኽ (ያህዌ እዚህ ነው) ሕዝ 48፡35)

1፡5 ምንም እንኳ ጳውሎስ በሌሎች ደብዳቤዎች መግቢያ ላይ የሌሎች ሰዎችን ስም መጥቀሱ ተለመደ ቢሆንም በዚህ መግቢያ ላይ ግን የማንንም ስም አልጠቀሰም። በዚህ ክፍል የመጀመሪያው ሀረግ የሚገልጸው የጳውሎስን የደማስቆ መንገድ ላይ ልምምድ እና የተሰጠውን ኃላፍነት (የሐዋ 9) ነው። ስለዚህም በሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የተጠቀሰው ቃል የሚያመለክተው የአርታይ አጠቃቀምን ነው።

▣ "ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤" ጳውሎስ በክርስቶስ የተቀበለው ድነትን ብቻ እንዳልሆነ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን መጠራቱንም ያረጋግጣል። ይህ ሁሉ የሆነው በቅጽበት በደማስዎ መንገድ ላይ (የሐዋ 9) ነው። ይህ እንድሁ በዘፈቀደ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዓላማ ነበር።

▣ "እንዲገኝ" ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ግብን የሚታሳየው የግርክ ቃል "ኢስ" ጸሓፍው የተጠቀመበት ነው (ከቁ.1 ጋር አነጻጽር)። ወንጌል በኢየሱስ በማመን በሰው ልጅ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን መልክ ያድሳል። ይህ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር እቅድ የነበረውን ሰዎች የእርሱን ባሕርይ ያንጸባርቁ ዘንድ እንድሆን እድልን ይፈጥራል። (ቁ.7)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አእቅ** | **"የእምነት የሆነ መታዘዝ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ከእምነት ለሚሆን መታዘዝ"** |

| | |
|---|---|
| **አየመመቅ፣** | **"ከእምነት የሆነ መታዘዝን ለማምጣት"** |
| **አእቅ** | **"ለማመን እና ለመታዘዝ"** |

ይህ በሮሜ መልዕክት ውስጥ የሚገኘው "እምነት" የሚለውን ቃል አጠቃቀም ወሳኝ ነው:: በዚህ መጽሐፍም ይሁን ምዕራፍ ይህ ቃል በሦስት ፈጽሞ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል::

1. ቁጥር 5 ይህ በእውነት አካል ወይም ከኢየሱስ እና ክርስቲያን ሕይወት ጋር በተያየዘ መንገድ ቀርቧል:: (ሐዋ 6፡ 7፣ 13፡8፣ 14፡22፣ 16፡5፣ ሮሜ 14፡1፣ 16፡26፣ ገላ 1፡23፣ 6፡10፣ ይሁ 3፣20)::
2. ቁጥር 8 ይህ ቃል በኢየሱስ በግል ማመን ተብሎ ተወስዷል:: "ማመን"፣ "መታመን" የሚለው ቃል አንድ የግሪክ ቃል ትርጉም ነው (ፕስቴስ/ ፕስቶስ):: ወንጌል አስተምህሮ እና ግላዊ ነው (ቁ. 16፤ ዮሐ 1፤12፣ 3፡16)::
3. ቁጥር 17. በዚህ ስፍራ ይህ ቃል የብሉይ ኪዳን ውስጥ በተገለጠው መልኩ የሚታመን እና ታማኝ በምል መልኩ ቀርቧል:: የዕብ 2፡4 ትርጉም ይህ ነው:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ እምነት የጠነከረ የእምነት አስተምህሮ አይገኝም ነገር ግን በእምነት የሆነ አኗኗር ምሳሌያዊ ሕይወት ግን ይገኛል:: (አብረሃም በዘፍ 15፡6) ነገር ግን ይህም ፍጹም የሆነ እምነት ሳይሆን የእምነት ትግል ነው (ዕብ 11):: የሰው ልጅ ተስፋ በራሳቸው ጥረት ይህንን ማድረግ መቻላቸው ወይም በትክክል ማመን ሳይሆን ነገር

ግን በእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ መገኛታቸቸው ነው:: እግዚአብሔር ብቻ ታማኝ::

*ሀ. ንስሃ* (2፡4፣ *ማር* 1፡15፣ *ሉቃ* 13፡3፣5፣ *ሐዋ* 3፡16፣ 19፣ 20፡21)
*ለ. ማመን/እመነት* (1፡16፣ *ዮሐ* 1፡12፣ 3፡16፣ *ሐዋ* 16፡31፣ *ጥምቀት የተጠማቂው እምነት የአደባባይ እወጃ ነው*)
*ሐ. መታዘዝ* (2፡13፣ 2ቆሮ 9፡13፣ 10፡5፣ 1ጴጥ 1፡2፣ 22)
*መ. መጽናት* (2፡7፣ *ሉቃ* 18፡1፣ 2ቆሮ 4፡1፣16፣ *ገላ* 6፡9፣ 2ተሰ 3፡13

እነዚህ የአዲስ ኪዳን ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው:: እግዚአብሔር ለሰዎች በክርስቶስ በኩል የሰጠውን ስጦታ አንዴ መቀበል እና ሁሌም መቀበላቸውን መቀጠል አለባቸው:: (ቁ. 16፣ ዮሐ 1፡12)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ስለ ስሙ ሲል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ስለ ስሙ"** |
| **አየመመቅ፣** | **"ስለ ስሙ ሲል"** |
| **አእቅ** | **"ለክርስቶስ ሲል"** |
| **ኢመቅ** | **"ስለ ስሙ ክብር ሲል"** |

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየመመቅ፣** | **"በአሕዛብ ሁሉ መካከል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በአሕዛብ ሁሉ መካከል"** |
| **አእቅ** | **"ሕዝቦች ሁሉ"** |
| **ኢመቅ** | **"አሕዛብ ሕዝቦች ሁሉ"** |

ይህ አለማቀፋዊ ወንጌል ነው:: በዘፍጥረት 3፡15 የተገለጠው የእግዚአብሔር የድነት የተሰፋ ቃል ሁሉን የሰው ልጆችን ያቀፈ ነው:: የኢየሱስ የምትክነት ሞት የአዳም ልጆችን ሁሉ የሚያካትት ነው (ዮሐ 3፡16፣ 4፡42፣ ኤፌ 2፡11-3፡13፣ 1ጢሞ 2፡4፤ 4፡10፤ ቲቶ 2፡11፤ 2ጴጥ 3፡9):: ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን እንድሰብክ የተሰጠውን ተልዕኮ ልዩ መሆኑን ተመልክቷል (ሐዋ 9፡15፤ 22፡21፣ 26፡17፣ ሮሜ 11፡13፤ 15፡16፣ ገላ 1፡16፣ 2፡29፣ ኤፌ 3፡2፣8፣1ጢሞ 2፡7፣ 2ጢሞ 4፡17)::

**ልዩ ርዕስ: የቦብ ወንጌላዊ ቅድመ እሳቤ**

ለአንባቢዎች በዚይህ ስፍራ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ስነ አፈታቱ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችለውን ቅድመ እሳቤ እንዳለኝ ልነግራችሁ እወዳለሁ:: የሚቀበለው ስነ መለኮት የካልቬንስቶች ወይም የዲስፔንሽናልስቶች አይነት አይደለም፤ ነገር ግን የታላቁ ተልዕኮ ወንጌላዊነት ነው:: እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ የማዳን ዘላለማዊ እቅድ እንዳለው አምናለሁ (ዘፍ 3፡15፣ 12፡3፤ ዘጸ 19፡5-6፤ ኤር 31፡31-34፣ ሕዝ 18፣ 36፡22-39፣ የሐዋ 2፡23፣ 3፡18፣ 4፡28፣ 13፡29፣ ሮሜ 3፡9-18፣ 19-29፣ 21-32)፤ እነዚህ ሁሉ በእርሱ መልክ እና ምሳሌ ተፈጥረዋልና (ዘፍ 1፡26-27):: ቃል ኪዳኖቹ በኢየሱስ ውስጥ ተዋህዷል (ገላ 3፡28-29፣ ቆላ 3፡11):: ኢየሱስ የእግዚአብሔር የተደበቀ፣ ምስጥር ነው፤ ነገር ግን በዚይህ ዘመን ተገልጧል (ኤፍ 2፡11-3፡13)::

ይህ የእኔ ቅድመ እሳቤ በእኔን የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ላይ ተጽእኖ ያደርግበታል (ይህ ማለት ዮናስ):: ሁሉንም የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የማነበው በዚይህ መነጽር ነው! ይህ ደግሞ እያንዳንዱ የመጸሐፍ ቅዱስ አንባቢ ልኖረው የሚገባ እና ያለው ቅድመ እሳቤ ነው:: ይህ ማለት ግን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን ቅድመ እውቀት ግን አይደለም::

1:6 "እናንተ ደግሞ" ጳውሎስ (የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ የነበረው) የእግዚአብሔር ጸጋ ጥሩ ምሳሌ ነው ነገር ግን የእርሱ ጽሑፍ አንባቢያንም በሆኑ የእግዚአብሔር ጸጋ የማይገባቸው ሰዎች ምሳሌ ናቸው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ"** |
| **አየመመቅ፣** | **"እናንተ የተጠራችሁት የክርስቶስ ትሆኑ ዘንድ ነው"** |
| **አእቅ** | **"እናንተን እግዚአብሔር የክርስቶስ ትሆኑ ዘንድ ጠርቷችኋል"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብል** | **"በእርሱ ጥር የክርስቶስ ሆናችኋል"** |

ይህ ምንአልባትም፦

1. "ቤተ ክርስቲያን" ትርጓሜውም "የተጠሩ" ወይም "የተሰበሰቡ" የሚለው ቃል ላይ የተደረገ የቃላት ጫወታ ልሆን ይችላል።
2. *መለኮታዊ ምርጫ* (ሮሜ 8፡29-30፣ 9፡1፣ ኤፌ 1፡4፣ 11፣ 3፡21፣ 4፡1፣4)
3. ሪቫይስድ ኢንግልሽ ባይብል ትርጉም ይህንን ሀረግ እንዲህ ይፈታዋል "እናንተ ይህንን ጥር የሰማችሁ እና በክርስቶስ የሆናችሁ"

በዚህ ሀረግ ላይ እንዲህ አይነቱ መረዳት አየመመቅ፣ አእቅ እና ኢመቅትርጉሞች ላይ ተንጸባርቋል። ከዚይህ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**ልዩ ርዕስ፡ መጠራት**

ሰዎችን በመጥራት፣ በመምረጥ እና ለራሱ በማድረግ እግዚአብሔር ዘወትር ቅድሚያውን ይወስዳል (ዮሐ 6፡44፣ 15፡16፣ 1ቆሮ 1፡12፣ ኤፌ 1፡4-5፣11)። *"መጠራት"* የሚለው ቃል በተለያዩ ስነ መለኮታዊ ትርጓሜዎች ተወስዷል፦

- *ሀ.* ኀጢአተኞች በመስቀል ላይ በተጠናቀቀ የክርስቶስ *ሥራ* እና በመንፈስ ቅዱስ የማሳመን *ሥራ* ለድነት በእግዚአብሔር ጸጋ ተጠርተዋል። (ይህ በግሪክ ክልቶስ ይባላል፤ ሮሜ 1፡6-7፣ 9፡24 ይህ ከ1ቆሮ 1፡1-2 እና ጢሞ 1፡9፣ 2ጴጥ 1፡10 ጋር በስነ መለኮታዊ ይዘቱ ተመሳሳይ ነው።)
- *ለ.* ኀጢአተኞች ያድናቸው ዘንድ የጌታን ስም ይጠራሉ (ይህ በግሪክ ኢፒከኪልቶስ ይባላል፤ ሐዋ 2፡21፣ 22፡16፣ ሮሜ 10፡9-13።) ይህ ዓረፍተ ነገር የአይሁዶች የአምለኮ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።
- *ሐ.* አማኞች የተጠሩት ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት እንዲኖራቸው ነው። (ይህ በግሪክ ክልሲስ ይባላል፤ 1ቆሮ 1፡2፣ 7፡20፣ ኤፌ 4፡1፣ ፊል 3፡14፣ 1ተስሎ 1፡11፣ 2ጢሞ 1፡9)
- *መ.* አማኞች ለአገልግሎት ይጠራሉ (ሐዋ 13፡2፣ 12፡4-7፣ ኤፌ 4፡1)

1:7 "በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ" ይህ ሀረግ ኢየሱስ አዘውትሮ የሚጠቀመው ሀረግ ነበር (ማቴ 3፡17፣ 17፡5)። በዚህ ስፍራ ላይ ለሮሜ ሰዎች ውሏል። ይህ የሚያሳየው በልጁ ለሚታወኑ ሰዎች እግዚአብሔር ያለውን ጥልቅ ፍቅር ነው። ይህ ዓይነቱ የፍቅር ትስስር በኤፌ 1፡20 ላይ (ስለ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ያደረገውን) እንዲሁም 2፡5-6 (ኢየሱስ ለአማኞች ሲል ያደረገውን) እንመለከታለን።

▣ "በሮሜ" ጳውሎስ በሮም ያለችን ቤተክርስቲያን አልተከለም። ምን እንደመሠረታት ማንም ሰው አያውቅም። የሮሜ መጽሐፍ በሮም ተመሥርታ ላለች ቤተ ክርስቲያን እራሱን ለማስተዋወቅ የጻፈው ደብዳቤ ነው። የሮሜ መጽሐፍ ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል በጥሩ ሁኔታ የተገለጸበት መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳ በጽሑፉ ውስጥ ጳውሎስ ደጋግሞ በአይሁዳዊያን እና በአሕዛብ አማኞች መካከል ስላለው ግንኙነት አስተያየት ቢሰጥም ጽሑፉን ግን ይህ ሁኔታ ተጽእኖ በጣም አላደረገበትም።

**አአመመቅ1:7**
**በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።**

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እንደ ቅዱሳን የተጠራችሁ"** |
| **አየመመቅ፣** | **"ቅዱሳን ትሆኑ ዘንድ የተጠራችሁ"** |
| **ኢመቅ** | |
| **አእቅ** | **"የእርሱ ሕዝቦቸ ትሆኑ ዘንድ የተጠራችሁ"** |

"ቅዱሳን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አማኞች በክርስቶስ ያላቸውን ስፍራ እንጂ የእነርሱን ኀጢአት አልበኝነት አይደለም። እንዲሁም እያደገ የሚሄደውን ክርስቶስን መምሰል የሚለውን ሀሳብ የሚገልጽ ነው። ይህ ቃል ከፊል 4:21 ነገርን ያመለክታል። ክርስቲያን መሆን ማለት የማሕበረሰቡ፣ የቤተሰቡ እና የአካሉ አንድ አካል መሆን ማለት ነው።

ቁጥር 1 ጳውሎስ ሐዋርያ ይሆን ዘንድ እንደተጠራ ያመለክታል። በቁጥር 6 ላይ አማኞች "በክርስቶስ እንደተጠሩ" ያመለክታል። እንዲሁም በቁጥር 7 ላይ አማኞች "ቅዱሳን" ተብለው ተጠርተዋል። ይህ ጥሪ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የነገር ሁሉ አነሳሽ የመሆኑን እውነት የሚያረጋግጥ ነው። በኀጢአት የወደቀ ሰው እራሱን መጥራት አይችልም (3:9-13፣ ኢሳ 53:6፣ 1ጴጥ 2:25)። ዘወትር እግዚአብሔር መጀመሪያውን እርምጃ ይወስዳል (ዮሐ 6:44፣ 65፣ 15:16)። ቃል ኪዳኑን እርሱ ወደ እኛ ዘወትር ያቀርባል። ይህ ለድነታችን (በተካፈልነው ጽድቅ ወይም በእግዚአብሔር የሕግ መለኪያ) ነገር ግን ለውጤታማ አገልግሎት ያለን ስጦታ (1ቆሮ 12:7፣11) እና በክርስትና ሕይወታችን እውነት ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ ቅዱሳን**

ይህ የግሪክ ቃል የዕብራይስጥ አቻ ትርጉሙ ካዶሽ ሲሆን፤ የዚይህ ቃል መሠረታዊ ትርጉሙ አንድን ሰው፣ አንድን ነገር ወይም አንድን ቦታ ለያህዌ ብቻ መለየትን ያመለክታል። ይህ ቃል አንድ ዓለማ የተለየ የሚለውን የአማርኛ ሀሳብን ያመለክታል። ያህዌ በባሕርይው ከሰው ልጆች ሀሉ የተለየ ነው (ዘላለማዊ ያልተፈጠረ መንፈስ ነው) እንዲሁም ባሕርይው (ግብረገባዊ ፍጹሚነት የተላበሰ ነው)። እርሱ ነገሮች ሁሉ የሚመዘኑበት እና ብያኔ የሚያገኙበት መለኪያ መስፈርት ነው። እርሱ የነገሮች ሁሉ መለኪያመስፈርት፣ ቅዱስ እና ከሌሎች ተቀደሰ ነው።

እግዚአብሔር ሰዎች ከእርሱ ጋር ሕብረት ያደርጉ ዘንድ ቢፈጥራቸውም ሰዎች ግን በኀጢአት ወደቁ (ዘፍ 3)፤ ይህም ቅዱስ በሆነ እግዚአብሔር እና በኀጢአተኞቹ ሰዎች ግንኙነት መካከል ግንኙነታዊ እና ግብረገባዊ እንቅፋትን ፈጠረ፤ እግዚአብሔር ይህንን ተበላሸ ግንኙነት ለማደስ ፈለገ፤ ስለዚህም ሕዝቡን "ቅዱስ" ብሎ ጠራቸው (ዘኍ 11፡ 44፣ 19:2፣ 20:7፣6፣ 21:8)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከያህዌ ጋር ባላቸው እምነት ግንኙነት ፤ ከእርሱ ጋር ባላቸው የቃል ኪዳን ቦታ ቅዱሳን ይሆናሉ። ነገር ግን ቅዱስ የሆነ ኑሮንም ይኖሩ ዘንድ ተጠርተዋል (ማቴ 5:48)።

ይህ ቅዱስ አኗኗር የተቻለበት ምክንያት አማኞች በእግዚአብሔር ዘንድ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ስላገኙ እና በኢየሱስ ሕይወት የኀጢአት ይቅርታን ስላገኙ፤ በአእምሮአቸው እና በልባቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እና መገኘት ስላለ ነው። ይህ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ሁኔታን ይፈጥራል፦

ቅዱሳን የሆኑት የክርስቶስ ቅድስና ለእነርሱ ስለተቆጠረላቸው ነው ቅዱሳን እንድሆኑ የተጠሩት

1. መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ ስለሚገኝ ነው።
2. በሕይወታችን የቅዱሱ (የእግዚአብሔር) ፍቃድ

በቅዱስ ልጅ (በኢየሱስ) በኩል በተሠራ ሥራ፣ እና በቅዱስ መንፈስ መገኘት ምክንያት አማኞች ቅዱሳን (ሃጊዮ) ናቸው።

አዲስ ኪዳን ዘወትር ቅዱሳን ብሎ የሚጠራው በብዙ ቁጥር (በፊል 4:12 ላይ ከሚገኘው አንድ ክፍል በስተቀር፤ በዚህይም ሰፍራ ላይም ብሆን አውዱ ግልጽ የሚያደርገው ብዙ ቁጥር መሆኑን ነው)። ድነት ማለት የቤተሰቡ አካል መሆንን፣ አካልነትን፣ ሕንጻ መሆንን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚጀምረው በግል ከመቀበል ነው፣ ነገር ግን ግቡ ሊሆን የሚገባው በአንድነት ወደ ሚደረግ ሕብረት ነው። እያንዳንዳችን ለቤተ ክርስቲያን (የክርስቶስ አካል) (1ቆሮ 12:7) ጤናማናት፣ እድገት እና መልካምነት ስጦታ ተሰጥቶናል (1ቆሮ 12:11)። እግዚአብሔርን እናገለግል ዘንድ ድነትን ተቀብለናል። ቅድስና የዚይህ ቤተሰብ መለያ ባሕርይ ነው።

▣ **"ከእግዚአብሔር ጸጋ እና ሰላም ለእናንተ ይሁን"** ይህ የጳውሎስ የደብዳቤዎቹ ሁሉ መለያ የሆነው የደብዳቤዎቹ መጀመሪያ የበረከት መልዕክት መክፈቻ ነው። ይህ የግሪክ የቃላት ጫወታ ሲሆን "ሰለምታ" (ቻርን) እና የክርስቲያኖች ልዩ የሆነው ቃል የግሪክ ቃል ትርጓሜ የሆነው "የጸጋ" (ቻርስ) መካከል የተካሄደ ነው። ጳውሎስ በመክፈቻው ላይ የዕብራይስጥ "ሰላም" ወይም ሻሎም የሚለውን ቃል ከግሪክ ቃልን በማዋሃድ ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ መላምት ብቻ ነው። ስነ መለኮታዊ ጸጋ ሁል ጊዜ ሰላምንን እንደሚያስቀድም አስተውሉ።

▣ **"ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ"** ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ለሁለቱም ስሞች የሚጠቀመው ተመሳሳይ ሰዋሰውን ነው። (1ቆሮ 1:3፤ ገላ 1:3፣ ኤፌ 1:2፣ ፊል 1:2፣ 1ተሰሎ 1:2፣ 1ጢሞ 1:2፣ ቲቶ 1:4)። ይህ ጳውሎስ የሥላሴ ሁለቱን አካላት በሰዋሰዋዊ ቀመር የሚያገናኝበት መንገድ ነው። ይህ የኢየሱስን መለኮት እና እኩልነት የሚገልጽ ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ አባት**

ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን አባትነት የሚገልጸውን ዘይብያዊ አነጋገር ያስተዋውቃል

1. እስራኤላዊያን ብዙ ጊዜ የያህዌ "ልጆች" ተብለው ተጠርተዋል (ሆሴ 11፡1፣ ሚል 3፡17)
2. በዘዳግም መጀመሪያዎቹ ምዕራፍ የእግዚአብሔር አምላክነት ምሳሌነት ተገልጾ እናገኛለን (ዘዳ 1፡310
3. በዘዳ 32 ላይ እስራኤል "የእግዚአብሔር ልጅ" እና እግዚአብሔር ደግሞ "አባታችሁ" ተብሎ ተገልጿል።
4. ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በመዝ 103፡13 እንዲሁም ግልጽ በሆነ መልኩ በመዝ 68፡5 (የወላጅ አልባ ልጆች አባት) ተገልጿል።
5. በነቢያት መጽሐፈት ውስጥ ይህ ሃሳብ በብዛት ይገኛል (ኢሳ 1፡2፣ 63፡8፣ እስራኤል እንደ ልጅ፣ እግዚአብሔር እንደ አባት፣ 63፡16፤ 64፡8፤ ኤር 3፡4፣ 19፣ 31፡9)።

ኢየሱስ ይናገር የነበረው አረማይክ የሚባል ቋንቋ በመሆኑ "አባት" የሚል ቃል በምናገኝበት ሥፍራ ሁሉ፣ የግሪክ ፓተር የሚል ቃልን እናገኛለን፤ ይህ ደግሞ አባ የሚል የአራማይክ ቃል ነው (14፡36)። አባ የሚለውም ቃል ኢየሱስ መጠቀሙ የሚገልጽልን ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ያለን ቅርበት ነው። ይህንንም ለተከታዮቹ የገለጸበትም ምክንያት ከአባት ጋር ያለንን ግንኙነት ያጠናከረው ዘንድ ነው። ይህ በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በዋነኝነት የሚገልጥልን ነው።

**ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል፡ ክፍል 1፡8-15**

**እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ። በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፤ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ። ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና፤ ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው። ወንድሞች ሆይ፥ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤ ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።**

1.8 **"አስቀድሜ"** በዚህ አውድ ውስጥ "አስቀድሜ" የሚለው ቃል ትርጉም "ከመጀመሪያ" ወይም "ስለምጀምር" (ጄ.ብ. ፊልፕስ)

▣ **"አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል አመሰግናለሁ"** ጳውሎስ ጸሎቱን ዘወትር በክርስቶስ በኩል የማድረግ ልምድ አለው። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ብቸኛው መንገድ ነው። ልዩ መልዕክቱን ተመልከቱ፦ የጳውሎስ የምስጋና ጸሎት እና ምስጋን በ7፡25 ላይ ተመልከቱ።

▣ **"ስለ ሁላችሁም"** ይህ "ሁላችሁም" የሚለው ቃል በቁጥር 7 ላይ እንደተገለጸው በኒሮ አዋጅ ምክንያት የተሰደዱትን አማኝ አይሁዳዊያን መሪዎች እና እነርሱን ለጥቂት አመታት በተኩት አማኝ የአሕዛብ መሪዎች መካከል የነበረውን ቅንአት እና ግጭትን ሊያሳይ ይችላል። ሮሜ 9-11 ያለው ክፍል ይህንን ሀሳብ በደንብ ያብራራዋል። ምንአልባትም ይህ በሮም "ደካሞች" እና "ብርቱዎች" ተብለው ተጠሩትን ለማመልከት ተጻፈም ልሆን ይችላል (14፡1-15፡3)። እግዚአብሔር በሮም የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ባጠቃላይ ይወዳታል እንዲሁም የሚወዳቸው እኩል በሆነ ደረጃ ነው።

▣ **"እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች"** ሮሜ 16፡9ን ስለዚይህ እውነት ይናገራል። ይህ በእርግጥ በሮም ሁሉ የመሠማቱ ዜና ግነት ነው (ከ1ተሰለ 1፡8 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፡9 **"እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና"** ጳውሎስ በእግዚአብሔር ስም መሃላን ይገባ ነበር (9፡1፤ 2ቆሮ 1፡23፤ 11፡10-11፣ 31፣ 12፡19፣ ገላ 1፡20፣ 1ተሰ 2፡5)። ይህ የእርሱ እውነተኝነቱን የሚያስረግጥበት የአይሁዳዊነት መንገድ ነው።

▣ **"በመንፈሴ"** ይህ ኑማ የሚለውን የግሪክ ቃል ለሰው መንፈስ ለማመልከት ጥሩ ምሳሌ ነው (ከ8፡5፣10፣ 16፣ 12፡11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም ቃል የተገለጸው የሰው ልጅን ሕይወት ለማመልከት ነው። (ይህ ማለት እስትንፋስ፣ በዕብራይስጥ ደግሞ ሩሃ ይባላል ከዘፍ 2፡7 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፡10 **"እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ"** ጳውሎስ ይህችን ቤተ ክርስቲያን አልመሰረታትም ነገር ግን ሁል ጊዜ ለሌሎች ቤተ ክርስቲያናት እንደሚጸልየው ሁሉ ለእነርሱም ሳያቋርጥ ስለ እነርሱ ግን ይጸልይ ነበር (ከ2ቆሮ 11፡28 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለ

መልእ ጸሎት በ9:3 ላይ የተጻፈውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ። ነገር ግን ምዕራፍ 16 በግልጽ እንደሚያሳየው ጳውሎስ በሮም ብዙ ጓደኞች እና የሥራ አጋራሮች ነበሩት።

▣ "እንዲቀናልኝ" ይህ የመጀመሪያው የቢሆንልኝ ዐረፍተ ነገር ስሆን ታሳቢ የሚያደርገውም ከክጸሓፊው ዓላማ ወይም ስነጽሒፋዊ ዓላማ በመነሳት እውነት መሆኑን ነው። ጳውሎስ ወደ እስፔን በሚያደረገው ጉዞው በእግረ መንገዱን ሮምን ለመጎብኘት ፈልጓል (15:22-24)። ምንአልባትም በዚያ ብዙ ጊዜ ለመቆየት አለሰበም ይሆናል። ጳውሎስ ሁል ጊዜ ሰዎች ከዚይህ በፊት ሠርተውበት የማያውቁትን ሥፍራ ነው (15:20፣ 2ቆሮ 10:15፣16)።ወደ ሮም ደብዳቤ የጻፈበት ምክንያት ምንአልባትም ለእስፔን ጉዞው ለሚያስፈልገው ወጭ ብር ለማሰባሰብ ሊሆን ይችላል (15:24)።

▣ "አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ" ይህ በቁጥር 13 እና 15:32 ላይ በትይዩ ቀርቧል። ጳውሎስ ሕይወቱ እና ያቀደው ጉዞ የእርሱ እንደሆነ አላሰበም ነገር ግን የእግዚአብሔር ነው (ከየሐ 18:21፣ 1ቆረ 4:19፣ 16:7)። ልዩ ርዕስ 12:2ትን ተመልከቱ።

1:11 "ላያችሁ እናፍቃለሁና" ይህ ከ15:23 ጋር ትይዩ ነው። ጳውሎስ በሮም ካሉ አማኞች ጋር ለመገናኘት ብዙ ጊዜ ፈልጓል (ከየሐዋ 19:21 ጋር ያነጻጽሩ)

▣ "መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ" "መንፈሳዊ ስጦታ" የሚለው ሀረግ በዚህ ስፍራ ላይ የተገለጸው መንፈሳዊ መረዳትን ወይም ባርኮትን ለማመልከት ነው (ከ11:29፣ 15:27 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ እራሱን ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን ልዩ በሆነ ሁኔታ የተጠራ አድርጎ ይመለከት ነበር። (ከቁጥር 15 ጋር ያነጻጽሩ)

▣ "ትጸኑ ዘንድ" በ5:2 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ።

1:12 ይህ የክርስቲያኖች ሕብረት ዓላማ ነው። ስጦታ የመሰጣቸው ዋና ዓላማ አማኞችን በሕብረት እንዲሆኑ በማድረግ የእምነት ማህበረሰቡን ማገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው። ለአማኞች ስጦታ የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው (ከ1ቆሮ 12:7 ጋር ያነጻጽሩ)። ሁሉም ስጦታዎች ጠቃሚዎች ናቸው። ሁሉም ስጦታዎች አማኙ ድነትን ሲያገኝ ተሰጥቶታል (ከ1ቆሮ 12:11 ጋር ያነጻጽሩ)። እያንዳንዱ አማኝ ተጠርቷል፣ ስጦታ ተሰጥቶታል እንዲሁም የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነው (ከኤፌ 4: 11-12 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ ያለውን የሐዋርያነት ስልጣን በግልጽ አስቀምጧል ነገር ግን ይህም ብሆን ለማህበረሰቡ ጥቅም ነው። አማኞች እርሱ በእርሳቸው ይፈላለጋሉ።

1:13 "ወንድሞቼ፤ ይህንን ሳታውቁ እንደትቀሩ አልፈልግም" ይህ ጳውሎስ በጣም አስፈላጊ የሆነን ዓረፍተ ነገርን ለመጀመር የሚቀምበት ዘይባዊ አነጋገር ነው (ከ11:25፣ 1ቆሮ 10:1፣ 12:1፣ 2ቆሮ 1:8፣ 1ተሰሎ 4:13 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ኢየሱስ "እውነት እውነት" እላችኋለው ብሎ ከተናገረው ቃል ጋር ተመሣሣይ ስነ ጽሑፋዊ ዓላማ አለው።

▣ "እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ" ይህ ተሻጋር ግስ ነው። ተመሳሳይ ሀረግ በ1ተሰ 2:18 ሴጣን የድርግቱ ፈጻም ሆኖ ላይ ይገኛል። ጳውሎስ የእርሱ ሕይወት የሚመራው በእግዚአብሔር እንደሆነ ነገር ግን በሴጣን ግን ልስተጉል እንደሚችል ያምናል። በሆነ መልኩ ሁለቱም ሀሳቦች ትክክል ናቸው (ከኢዮ 102፣ ዳን 10 ጋር ያነጻጽሩ)። በ15:22 ላይ ያለው የዚህ ቃል አጠቃቀም እንደሚያመለክተው በምስራቅ ሜድትራንያን አከባቢ የነበረው የጳውሎስ የምስኦናዊነት ሥራ እንደተስተጓጐለ፣ በመሆነም እንደልተጠናቀቀ ነው።
▣ "በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ" በዚህ አውድ መሰረት "ፍሬ" የሚያመለክተው ድነት የሚቀበሉ ሰዎችን ሲሆን በዮሐ 15: 1-8 እና 5:22 ላይ ግን የሚያመለክተው ክርስቲያናዊ ብስለት ነው። ማቴዎስ 7 እንዲህ ይላል "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።" ነገር ግን ይህ የቃሉን ፍች አይሰጥም። የዚህ ቃል ተመሣሣይ ፍች የሚገኘው ምንአልባት በፊል 1:22 ላይ ጳውሎስ የግብርናን ዘይቤያዊ አነጋገር በምጠቀምበት ስፍራ ላይ ነው።

1:14 "ዕዳ አለብኝ፤" ጳውሎስ ይህንን ቃል በሮሜ መልዕክት ውስጥ በብዙ ስፍራ ተጠቅሞታል
ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን ይሰበክ ዘንድ ታዟል (በዚህ ስፍራ ላይ)
ጳውሎስ "ለስጋው" ተገዷል (8:12)
የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን በእየሩሳሌም ለምትገኘው እናት ቤተ ክርስቲያን እርዳታን ይልኩ ዘንድ ግዴታ አለባቸው (15:17)

▣ "ለግሪኮች" ይህ ቃል የሚያመለክተው በሜድትራንያን አከባቢ ለነበሩ ለሰለጠኑ፣ ባሕል ላላቸው ሕዝቦችን ነው። ታላቁ አሌክሳንደር እና ተከታዬቹ በዚያን ጊዜ የሚታወቀውን ኣለም ሄሌናይዝድ አድርገውት ነበር። ሮማዊያን ደግሞ ይህንን የግሪክን ባሕል በመውደስ እና ከራሳቸው ጋር አማዋሃደውት ነበር።

▣ "ላልተማሩም" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል ኦኖማቶፖኢዓ ስሆን ይህም ቃል የሚያመለክተው ወደ በዚያ ዘመን በሚታወቅ ዓለም ወደ ሰሜን የሞኖሩ የባርባሪያን ሰዎችን ያመለክታል። ይህ ቃል የግሪክ ቋንቋ የማይናገሪ ሕዝቦችን ያመለክታል።

▣ *"ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም"* ይህ ቃል *"ያልተማሩ"* የተባሉትን ባርባራያንን በብዙ ቁጥር ሊያመለክት ይችላል። ነገር ግን ይህ ማለት ይህንን ብቻ ያመለክታል ማለት አይደለም። ይህ ምናአልባተም የተለያዩ መህበረሰቦችን እና ግለሰቦችን የማመልከቻ ሌላ መንገድም ሊሆን ይችላል።

> **ኒው አሜሪካም ስታንዳርድ ባይብል ክፍል፡ 1:16-17**
> **"በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።"**

1:16-17 ቁጥር 16-17 የመጽሐፉ በጠቅላል ጭብጥን የያዘ ነው። ይህ ጭብጥ በ3:21-31 ላይ በደንብ ተብራርቶ እና ተጠቃሎ ቀርቧል።

1:16

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ* | *"በወንጌል አላፍርምና፤"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"በክርስቶስ ወንጌል አላፍርማና"* |
| *አእቅ* | *"በወንጌል ሙሉ እምነት አለኝ"* |
| *አመቅ* | *"በወንጌል አላፍርም"* |

ጳውሎስ ምንአልባትም በማር 8:38 እና ሉቃ 9:26 ላይ የተጠቀሰውን የኢየሱስ ንግግርን ተመርኩዞ ይህንን ጽፎት ልሆን ይችላል። እርሱ በወንጌል ይዘት ወይም ይህ ወንጌል በሚያስከትልበት ስደት አለፈረም (ከ2ጢሞ 1:12፣ 16፣ 18 *ጋር ያነጻጽሩ*)።

በ1ቆሮ 1:23 ላይ አይሁዳዊያን በወንጌል እንደሚያፍሩ ተገልጿል፤ ምክንያቱም ለአይሁዳዊያን ወንጌል የመስሕውን መከራ መቀበልን ስለሚገለጽ የሚያፍሩበት ነው እንዲሁም ለግሪኮች ወንጌል የትንሳኤ አካልን ስለምገልጽ የሚያሳፍር ነገር ሆኖባቸዋል።

▣ *"ድነት"* በብሉይ ኪዳን (ያሻ) የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን በዋነኝነት የሚያመለክተውም አካላዊ ነጻ መውጣት ነው (ከያዕ 5:15 *ጋር ያነጻጽሩ*) ነገር ግን የአዲስ ኪዳን የግሪክ ቃል (ሶዞ) ሲሆን ይህም በዋነኝነት የሚመለክተው መንፈሳዊ ነጻ መውጣት ነው (ከ1ቆሮ 1:18፣ 21 *ጋር ያነጻጽሩ*)። በሮብረት ቢ. ጊረድሰቶን፣ ስናንምስ ኦፈ ዝ ኦልድ ቴስታመንት የተጻውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

▣

| | |
|---|---|
| *ኒው አሜርካን ስታንዳር ባይበብል* | *"ለሚያምኑ ሁሉ"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"ለሚያምን ሁሉ"* |
| *ኒው ሪቫይዝድ ሳታንዳርድ ቨርዥን* | *"እምነት ለሚኖረው ሁሉ"* |
| *አእቅ* | *"ላመነ ሁሉ"* |
| *ጀሩሳሌም ባይብብል* | *"እምነት ላለው ሁሉ"* |

ወንጌል ለሰው ልጆች ሁሉ ነው (ኦ *"ለሁሉም ሰው"፣ "ለሚያምኑ ሁሉ" "ለሁሉም"* የሚሉ ቃላትን እንዴት እወዳቸዋለሁ) ነገር ግን ማመን ይህንን ለመቀበል ማመን አንዱ መስፈርት ነው (የሐዋ 16:30-31)። ሌላኛው ንሰን ነው (ማር 1:15፣ ሐዋ 3:16፣ 19፣ 20:21)። እግዚአብሔር ከሰው ልጆች *ጋር* የሚሰራው በቃል ኪዳን ነው። እርሱ ዘወትር መነሳሳቱን እና እቅዱን ያዘጋጃል (ከዮሐ 6:44፣ 65 *ጋር ያነጻጽሩ*)። ነገር ግን ብዙ ሌሎች የተገላቢጦሽ ሁኔታዎች አሉ፤ ለዚይህ የ1:5 ማስታወሻ ይመልከቱ።

በዚህ ስፍራ ላይ በአማርኛ *"ማመን"* ተብሎ የተተረጎመው ቃል *"እምነት"* ተብሎ ልተረጎም ይችላል። ይህም ማለት በሁለት እግሩ መረት ረግጦ እንዳይንቀሳቀስ ሆኖ የቆመ ሰውን ይመስላል። የዚህ ቃል የብሉይ ኪዳን ተቃራን ሆነው ዘይቤአዊ አነጋገር "እግሮቼን ከረግረግም ጭቃ አወጣኝ" (መዝ 40:2)፤ " "እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ፥ አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ።" (መዝ 73:2)። የዕብራይስጥ እሙን፣ እሙናህ፣ አማን የሚባሉ ቃላት የሚታመን፤ ታማኝን ሰውን የሚያመለክቱ ናቸው። የሚያድን እምነት በኀጢአት የወደቀ ሰውን ችሎታ ሳይሆን የእግዚአብሔን ችሎታ ያሳያል። ድነት የእርሱ ታማኝነት፣ መታመን እና የተስፋ ቃል ውጤት ነው።

▣ *"ለአይሁዶች"* የዚህ ነገር ምክንያት ሰፋ ባለ ሁኔታ በ2:9-10 እና 3 እንዲሁም በምዕራፍ 9-11 ላይ ተብራርቷል። ይህ ክፍል በማቴ 10:6፣ 15<24 እና ማር 7:27 ላይ የሚገኘውን የኢየሱስን ንግግር መሠረት ያደረገ ነው።

ይህ ምንአልባትም በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአይሁድ እና አሕዛብ መካከል የተከሰተውን ቅንአት *ጋር* ተቆራኝ ሊሆን ይችላል።

1:7 *"የእግዚአብሔር ጽድቅ"* በዚህ አውድ ውስጥ ይህ ቃል (1) የእግዚአብሔርን ባሕርይ እና (2) ይህንን ባሕርይውን እንዴት ለኀጢአተኞቹ የሰው ልጆቾች እንደሰጠ ሊያመለክት ይችላል። የጀሩሳሌኢ ባይብል ትርጉም እንዲህ ያስቀምጠዋል

"ይህ ነው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ፍርድ ገለጠው" ብሎ ተርጉሞታል። ምንም እንኳ ይህ ሀረግ የአማኞችን የግብረገባዊ ሕይወትን የሚያመለክት ብሆንም በዋናነት ግን የሚያመለክተው ጻድቅ በሆነው ፈራጅ ፊት ያላቸውን የሕግ ከለላ ነው። ይህ እግዚአብሔር ለወደቁት ለሰው ልጆች ሰጣቸው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው። ከተሃድሶ ዘመን አንስቶ መለያው "በእምነት መጽደቅ" የሚል ሆኗል (ከ2ቆሮ 5፡21፣ ፊል 3፡9 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህች ቁጥር ናት የማርት ሉተርን ስነ መለኮት እና ሕይወት የለወጠችው። ነገር ግን የመጽደቅ ግብ ግን መቀደስ፣ ክርስቶስን መመስል ወይም የእግዚአብሔር ጻድቅ ባሕርይ መላበስ ነው (ከሮሜ 8፡28-29፣ ኤፌ 1፡4፣ 2፡10፣ ገላ 4፡19 ጋር ያነጻጽሩ)። መጽደቅ ሕጋዊ ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን ቅዱስ አኗኗር ለመኖር መጠራትንም ያካትታል፤ ይህም ማለት በሰው ልጆች ውስጥ ያለው እግዚአብሔር መልክ በተግባር ይታደሳል (ከ2ቆሮ 5፡21 ጋር ያነጻጽሩ)።

**ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ**

"ጽድቅ" የሚለው ቃል በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት ማንኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ በግሉ ሰፊ ጥናት ሊያደርግበት የሚገባ ሃሳብ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር በባሕርይው "ጻድቅ" እና "ቅን ፈራጅ" እንደሆነ ተገልጿል። ይህ የቃል ሥረወ ግንድ የሆነው የሜሶፖታሚያዊ ቃል የሚያመለክተው በግንባታ ሂደት ውስጥ የግድግዳውን ወይም አጥሩን ቀጥተኝነት ለመለካት የሚያገለግል ውሃ ልክን ከሚያመለክት ቃል ነው። እግዚአብሔር ይህንን ቃል የእርሱን ባሕርይ ለማመልከት በዘይቤአዊ መልኩ ተጠቅሞታል። እርሱ ነገሮች ሁሉ የሚለኩበት የውሃ ልክ ነው። ይህ ሃሰብ የእግዚአብሔር ጻድቅ መሆን እና ለመፈረድም መብት እንዳለው ያረጋግጥልናል።

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መልክ ተፍጥሯል (ከዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፣3፣ 96 ጋር ያነጻጽሩ)። የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ያደርጉ ዘንድ ተፈጥረዋል። ፍጥረታት ሁሉ በሰዎች እና በእግዚአብሔር መካከል በሚኖረው ግንኙነት ውስጥ መድረክ ለመሆን የተፈጠሩ ናቸው። ከእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ የላቀ ስፍራ ያለቸው የሰው ልጆች እርሱን ያውቁት፣ ይወዱት፣ ያገለግሉት እና እርሱን ኢመስሉት ዘንድ እግዚአብሔር ፈልጓል። በዘፍ 3 ላይ የሰው ልጅ ታማኝነት የተፈተነበት እናም የመጀመሪያዎቹ ጥንዶ የወደቁበት ነው። ውጤቱም በእግዚአብሔር እና በሰው ልጆች መካከል መበላሸትን አስከተለ (ከዘፍ 3፣ ሮሜ 5፡12-21 ጋር ያነጻጽሩ)።

እግዚአብሔርም ይህንን የተበላሸ ግንኙነት አንደገና ለማደስ እና ለመጠገን ቃል ገባ (ዘፍ 3፡15)። ይህንን ያደረገው በገዛ ራሱ ፍቃድ እና በልጁ በኩል ነው። የሰው ልጆች የተሰበረውን ግንኙነት ለመጠገን ብቃቱ የላቸውም (1፡18-3፡20)።

ከሰውልጆች ውድቀት በኋላ ለዚይህ ተሃድሶ እግዚአብሔር የመጀመሪያው እርምጃ በእርሱ ጠርነት እና በሰው ልጆች ንሰን፣ ታማኝነት እና መታዘዝ ላይ የተመሠረተ የቃል ኪዳን ሃሳብ ነው። በውድቀት ምክንያት የሰው ልጆች ለዚይህ መልካም ሥራ ምላሽ መስጠት አይችሉም (ሮሜ 3፡21-31፣ ገላ 3)። ስለዚህም እግዚአብሔር እራሱ ቃል ኪዳንን አፍራሽ የሆኑትን የሰው ልጆችን ለመታደግ የተነሳሳሽነቱን ስፍራ ወሰደ። ይህንን ያደረገው፦

1. ኃጢአተኞች ሆኑት የሰው ልጆችን በክርስቶስ ሥራ ቅዱሳን ብሎ በማወጅ ነው
2. በክርስቶስ ሥራ ለሰው ልጆች ጽድቅን በነጻ በመስጠት
3. በሰው ልጆች ውስጥ ጽድቅን ያፈራ (ስነ ምግባራዊ ጽድቅን) ዘንድ በውስጣቸው እንዲያድር መንፈስ ቅዱስን በመስጠት
4. በአማኞች ውስጥ (ግንኙነታዊ ጽድቅን) በክርስቶስ የእግዚአብሔርን መልክ በሰውች ውስጥ የማደስ ሥራ አማካኝነት በኤደን ገነት የነበረውን ግንኙነት ማደስ (ዘፍ 1፡26-27)።

ነገር ግን ለዚይህ ሁሉ እግዚአብሔር ቃል ኪዳናዊ ምላሽን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ይወስናል (በነጻ ይሰጣል) እንዲሁም ይሰጣል ነገር ግን የሰው ልጆች ምላሽን መስጠት አለባቸው እንዲሁም በምላሻቸው መቀጠል አለባቸው።

1. በንሰኀ
2. በእምነት
3. በአኗኗር መታዘዝ
4. በጽናት

ስለዚህ ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር እና በእርሱ ልዩ ፍጥረታት መካከል ያለ ቃል ኪዳባዊ (የሁለትዮሽ) ግንኙነት ማለት ነው። ይህም መሠረት የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ባሕርይ፣ የክርስቶስን ሥራ እና የመንፈስ ቅዱስን ማስቻል ሲሆን ለዚህይም እያንዳንዱ ሰው በግል ቀጣይነት ባለው መልኩ በትክክል መልሻ መስጠት ይጠበቅበታል። ይህም ሀሳብ "መጽደቅ ይባላል።" ይህ ሀሳብ ምንም እንኳ በዚይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በይገለጽም ሀሳቡ ገን ተገልጿል። ይህ ቃል በመጀመሪያ ደረጃ በጳውሎስ የተብራራ ሲሆን፣ ጳውሎስ በጽሑፎቹ ውስጥ "ጽድቅ" የሚለውን ቃል ከ100 በላይ በሆኑ ቦታዎች በተለያየ መልክ ተጠቅሞባቸዋል።

ጳውሎስ የአይሁድ ስልጡን መምህር እንደመሆኑ መጠን 'ዳካኦሱን' የሚለውን ቃል የተጠቀመው ቅዱስ በሚለው የዕብራይስጥ ፍችውን በተጸባረቀበት በሰባ ሊቃውንት በተገለጸው መልኩ ነው። በግሪክ ስነ ጽሑፍ ውስጥ የቃሉ ፍች የተቀራኘው አማልክት እና ማህበረሰቡብ የሚጠብቁበትን ነገር ያሟላ ሰውን በማመልከት ላይ ነው። በዕብራይጥ የዚይህ ቃል ፍች ሁል ጊዜ የቃል ኪዳን ቃል ነው። ያህዌ ጻድቅ ፈራጅ፣ ሥነ ምግባራዊ እና ግብረገባዊ አምላክ ነው። ኢንት

የእርሱ ሕዝቦቹም የእርሱን ባሕርይ ያንጸባርቁ ዘንድ ይሻል። የተዋጀው የሰው ልጅ አድስ ፍጥረት ይሆናል። ይህ አዲስ ፍጥረት መሆን አዲስ የአኗኗር ዜይቤን በመፍጠረ እግዚአብሔራዊ ሕይወትን ያስከትላል (የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጽድቅ ላይ ትኩረት ትሰጣለች)። እስራኤል በእግዚአብሔራዊ አገዛዝ የምትመራ ሀገር ከመሆኗ የተነሳ አለማዊ እና መንፈሳዊ ሕግ የሚባል ነገር የላትም። ይህ የግሪክ እና የዕብራይስጥ የቃሉ አጠቃቀም በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም "ፍትሕ" (ከህብረተሰብ ጋር በተያያዘ) እና "ጽድቅ" (ከኃይማኖት ጋር በተያያዘ) በሚሉ ሁለት ቃለት ተንጸባርቋል።

የኢየሱስ ወንጌል በኀጢአት የወደቀው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያደርግ ዘንድ ታድሷል የሚል ነው። የጳውሎስ እርስ በእርስ የሚጋጭ የሚመስለው ሀሳብ እግዚአብሔር በደል ቀጥተዐል የሚል ነው። ይህ የተፈጸመው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ርህራሄ እና ጸጋ ሲሆን በልጁ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሳኤ እና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ ወንጌል መቅረብ እና ለወንጌል መሸነፍ ችለናል። መጽደቅ እግዚአብሔር ነጻ ሥራ ስሆን ፈጻሜውም እግዚአብሔራዊ ሕይወት ነው (አግስትን በዚይህ ነገር ላይ የነበረው መረዳት በአንድ በኩል የተሃድሶአዊያንን ለወንጌል አጽኖት መስጠትን ሲያንጸባርቅ በሌላ መልኩ ደግሞ የካቶሊካዊያንን በፍቅር የተለወጠ ሕይወት እና ታማኝነት የሚለውን ያንጸባርቃል። የታሃድሶአዊያኑ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" የሚለው ቃል ነባራዊ ባሌበት ነው (ይህ ማለት ኀጢአተኛ የሆነውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንድኖረው ማስቻል ማለት ሲሆን ይህ ለካቶሊካዊያን ግላዊ ባሌቤትነት ወይም እግዚአብሔር ወደ መምሰል የሚንሄድበት መንገድ ነው (ልምምዳዊ የእድገት ቅድስና)። በገሀዱ አለም እነዚይ ሁለቱ አንድ ናቸው።

እኔ ስለ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ባለኝ አመለካከት ከዘፍ 4 እስከ ራዕ 20 ድረስ ያለው የእግዚአብሔር በኤደን ገነት የነበረውን ግንኙነት ለማደስ ያደረገውን ነገር የተዘገበበት ነው። በእግዚአብሔር እና በሰዎች መካከል በለ ምድራዊ ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ የተጀመረው (ዘፊ 1-2) እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜው የሚሆነውም በዚይህ አውድ ውስጥ ይሆናል (ራዕ 21-22። የእግዚአብሔር መልክ እና ዓላማ እንደገና ይታደሳል።

ከዚይህ በላይ ያለውን ገለጻ በመረጃ ለማስደገፍ የተለያዩ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶችን በመውሰድ በግሪክ ቃላት ይበልጥ ማብራረት ይቻላል፦

1. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ይህ ብዙ ጊዜ እንደ ዳኛ ይታያል)
   - ሀ. ሮሜ 3፡26
   - ለ. 2ተሰ 1፡5-6
   - ሐ. 2ጢሞ 4፡8
   - መ. ሮሜ 16፡5
2. ኢየሱስ ቅዱስ ነው።
   - ሀ. ሐዋ 3፡14፣ 7፡52፣ 22፡14 (የመስሑ ስም)
   - ለ. ማቴ 27፡19
   - ሐ. 1ዮሐ 2፡1፣ 29፣ 3፡7
3. እግዚአብሔር ፍጥረታቱ ሁሉ ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ ፍቃዱ ነው።
   - ሀ. ዘለ 19፡2
   - ለ. ማቴ 5፡48 (ከ5፡17-20 ጋር አነጻጽር)
4. ሰዎችን እግዚአብሔር ቅዱሳን እንዲሆኑ የሚያደርግበት መንገድ ነው።
   - ሀ. ሮሜ 3፡21-31
   - ለ. ሮሜ 4
   - ሐ. ሮሜ 5፡6-11
   - መ. ገላ 3፡6-14
   - ሠ. በእግዚአብሔር የተሠጠ ነው፦
     1) ሮሜ 3፡24፣ 6፡23
     2) 1ቆሮ 1፡30
     3) ኤፌ 2፡8-9
   - ረ. በእምነት የምንቀበለው ነው
     1) ሮሜ 1፡17፣ 3፡22፣ 26፣ 4፡3፣5፣14፣ 9፡30፣ 10፡4፣6፣10
     2) 1ቆሮ 5፡21
   - ሰ. በወልድ በኩል በሚሠራ ሥራ
     1) ሮሜ 5፡21-31
     2) ቆሮ 5፡21
     3) ፊል 2፡6-11
5. የእግዚአብሔር ፍቃድ የእርሱ ተከታዬች ሁሉ ቅዱሳን ይሆን ፈቃዱ ነው።
   1) ማቴ 5፡3-48፣ 7፡244-27
   2) ሮሜ 2፡13፣ 5፡1-5፣ 6፡1-23

3) 2ቆሮ 6፡14
4) 1ጢሞ 6፡11
5) 2ጢሞ 2፡22፣ 3፡16
6) 1ዮሐ 3፡7
7) 1ጴጥ 2፡24

6. እግዚአብሔር ዓለማችን ላይ የሚፈርደው በጽድቅ ነው፡፡
ሀ. የሐ 17፡31
ለ. 2ጢሞ 4፡8

ጽድቅ ለኀጢአተኛው የሰው ልጅ በክርስቶስ በኩል የተሰጠ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፡፡

1. የእግዚአብሔር ውሳኔ ነው
2. የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
3. የክርስቶስ ተግባር ነው

ነገር ግን ይህ በአጽኖት እና በትጋት ልክተሉት የሚገባ ጻድቅ የመሆኛ መንገድ ነው፤ ይህ በኢየሱስ ዳግም ምጻት ወቅት ሙሉ ፍጻሜን ያገኛል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት በድነት ወቅት የታደሰ ሲሆን ሙሉ በሙሉ እርሱን ፍት ለፊት መመልከት በሞት ወይም በዳግም መጻት ወቅት የሚፈጸም ህደት ነው፡፡

ከድክሽነር ኦፍ ፖል ኤንድ ህዝ ሌተር ከተባለ በአይ ቪ ፐ መጽሐፍ የተወሰደ ጥቅስ

"ከሉተር በላይ ካልቭን ግንኙነታዊ የእግዚአብሔር ጽድቅ ይዘት ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የሉተር ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ያለው አመለካከት በውስጡ የሚሰጥ ጽድቅ ይዘት አለው፡፡ ካልቭን ድንቅ የሆነውን የእግዚአብሔር ጽድቅ ለእኛ አካፍሏል፡፡" (ገጽ 834)

ለእኔ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነትን በሦስት መንገድ እረዳዋለሁ፦

1. ወንጌል አካል ነው (የምስራቅ ቤተ ክርስቲያን እና የካልቭን ትኩረት)
2. ወንጌል እውነት ነው (ኦግስትን እና የሉተር ትኩረት)
3. ወንጌል የተለወጠ ሕይወት ነው (የካቶሊኮች ትኩረት)

እነዚይህ ሁሉ በአንድነት እውነት በመሆናቸው በአንድነት ለጤናማ፣ ለትክክለና፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ልንቀበል ይገባል፡፡ ከእነዚይህ መካከል አንዱ ላይ ትኩረት መስጠት ወይም አንዱን ትኩረት መንፈግ ችግርን ያስከትላል፡፡

ኢየሱስን መቀበል ያስፈልጋል!
በወንጌል ልናምን ይገባል!
ክርስቶስን መምሰልን ከልባችን ልንሻ ያስፈፈልጋል!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከእምንት ወደ እምነት"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | |
| **ኒው ሪቫይዝድ ሳታንዳርድ ቨርዥን** | **"በእምነት ለእምነት"** |
| **አእቅ** | **"በእምነት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብብል** | **"እምነት ወደ እምነት እንደሚመራ ማሳየት"** |

ይህ ሀረግ ኤክ እና ኤስ የሚባሉ ሁለት ሽግግርን አመልከች የሆኑ መስተዋድዶችን የያዘ ነው፡፡ ይህንን የመሰለ ቀመር በ2ቆሮ 2፡16 ላይ ስጠቀም እንመለከታለን፡፡ እንዲሁም በ2ቆሮ 3፡18 ላይ ተጠቀመው መስተዋድድ ኣፖ እና ኤስን ነው፡፡ ክርስትና የባሕርይ እና የአኗኗር ለውጥን የሚጠብቅ ስጠታ ነው፡፡

ይህንን ሀረግ ለመተርጎም ብዙ አይነት አማራጮች አሉ፡፡ ዌልያምስ ኤን ቲ የተባለ ሰው "ወደ ትልቅ እምነት የሚመራ የእምነት መንገድ" በማለት ትርጉሞቷል፡፡ ዋና ዋና የሚባሉ ሥነ መለኮታዊ ነጥቦች፦ (1) እምነት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው ("የሚገለጥ ነው")፤ (2) የሰው ልጆች ምላሽ መስጠት እና መላሽ እየሰጡ መቀጠል አለባቸው፤ እንዲሁም (3) እምነት እግዚአብሔራዊ ሕይወትን ማስገኘት አለበት፡፡

አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን እንችላለን እርሱ "በክርስቶስ ያለ እምነተ" በጣም አስፈላጊ ነው (ከ5፡1፣ ፊል 3፡9) ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ የእግዚአብሔር የድነት አቅራቦት በእምነት ምላሽ ላይ የተሞረከዘ ነው (ማር 1፡15፣ ዮሐ 1፡12፣ 3፡16፣ የሐ 3፡16፣ 19፣ 20፡21)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **ኒው አሜርካን ስታንዳር ባይበብል** | **"ነገር ግን ጻድቅ ሰው በእምነት ይኖራል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ጻድቅ በእምነት ይኖራል"** |
| **ኒው ሪቫይዝድ ሳታንዳርድ ቨርዥን** | **"ጻድቅ የሆነ ሰው በእምነት ይኖራል"** |
| **አእቅ** | **"ከእግዚአብሔር ጋር በጽድቅ የሞኖር በእምነት ይኖራል"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብብል** | **"ጻድቅ ሰው በእምነት ሕይወትን ያገኛል"** |

ይህ ከእንባቆም 2፡4 ሲሆን ነገር ግን ከሜዞሬቲክ ወይም ከሰባ ልቃውንት መጽሐፍ የተወሰደ ግን አይደለም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ "እምነት" ተለጠጠ ዘይቤአዊ ትርጓሜ ያለው ስሆን ፍቸውም "መታመን"፣ "ታማኝ መሆን" ወይም "ሀቀኛ" የሚል ነው። የሚያድን እምነት መሠረቱ የእግዚአብሔር ታማኝነት ነው (ከ3፡5፣ 21፣ 25፣ 26 ጋር አነጻጽሩ።) ይሁን እንጂ የሰው ልጆች ታማኝነት ማለት በእግዚአብሔር አቅራቦት ላይ ያለቸው እምነትን ያሳያል።

በዘመናችን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች በቁጥሩ ነጨረሻ ላይ ስለሚገኘው ስለዚይህ ሀረግ ያላቸውን መረዳት መዘርዘሩ ጠቃም ነው።

1. ሽኡጋሃ፡ "በእምነት መጀመር እና በእምነት መጨረስ"
2. ሆጅ፡ "በእምነት ብቻ"
3. ባርት "በምንም ነገር መሠረት ላይ ሳይሆን በእምነት ብቻ"
4. ኖክስ "እምነት የመጀመሪያም የመጨረሻም"
5. ስታግ "ጻድቅ ከእምነት

**ኒው አሜሪካም ስታንዳርድ ባይብል ክፍል 1፡18-23**
**እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ።**

1፡18 "በ" በቁጥር 16-17 ባሉ ዓረፍተነገሮች ውስጥ "በ" ተብሎ ተተረጎመው ጋሪ የሚለው የግሪክ ቃል ብዚ ጊዜ መጠቀሱን ተመልከቱ፤ ሦስት ጊዜ እንዲሁም በዚህም ስፍራ ጭምር ይህ የወንጌሉ ነጥብ መግቢያ ሆኖ አገልግሏል (1፡18-3፡31)ይህ ለድነት ከሚሆነው የእግዚአብሔር ኃይል ጋር በ1፡16-17 ተነጻጽሮ ቀርቧል።

▣ **"የእግዚአብሔር ቍጣ"** ቁጥር 18-23 በጳውሎስ ዘመን የነበረውን የአሕዛብን አከባቢ ይዳስሳል። የጳውሎስ የአሕዛብ መንደ መገለጫ በአይሁዳዊያን ስነ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል (ከሰለሞን ጥበብ 13 እና የአርቴሳኢ ደብዳቤዎች 134-38 ጋር ያነጻጽሩ)። በተጨማሪም በግሪክ እና በሮማን ስነ ምግባራዊ ጉዳዮችን በሚዳስሱ ጽሑፎቻቸው ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ በሚገልጽልን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የእግዚአብሔር ቍጣንም ይገልጽ ፍቅር ሰዋዊ ቃላት ናቸው። እነኝህ ቃላት አማኞች እግዚአብሔር በምፈልገው መንገድ ምላሽ ልሰጡበት እና ልኖሩበት የሚገቡ እውነቶችን ያዘለ ነው። የአንድ ሰው በፍቃደኝነቱ እግዚአብሔር ፍቃድን (የክርስቶስን ወንጌል) አለመቀበል በዚህ ቁጥር ላይ እንደሚንመለከተው ጊዜያዊ እና በመጨረሻው ዘመን የሚሆን ውጤት ያስከትላል (ከ2፡5 ጋር ያነጻጽራሉ)። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚታደግ ብቻ እንደሆነ መታየት የለበትም። ቅጣት ብዙ ጊዜ ያልተለመደ "የእግዚአብሔር ሥራ" ነው (ከኢሳ 28፡21 ጋር ያነጻጽሩ)።፡ፍቅር የእግዚአብሔር መለያ ባሕርይ ነው (ዘዳ 5፡9 እና 5፡10፤ 7፡9 ጋር ያነጻጽሩ)። በእርሱ ባሕርይ ውስጥ ፍትሕ እና ርህራሄ ጐልተው የሚታዩ ባሕርያት ናቸው። ነገር ግን ሁሉም ባሕርያት ግን የእግዚአብሔር መገለጫዎች ናቸው (ከማህ 12፡13-14፣ ገላ 6፡7) እንዲሁም እነዚህ ባሕርያት የክርስቲያኖች መገለጫ መሆን አለባቸው (ከ14፡10-12፤2ቆሮ 5፡10)።

▣ **"ተገልጧል"** ወንጌል የተገለጠ እውነት እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር ቍጣም እንዲሁ ነው (ቁጥር 17)! ሁለቱም የሰው ልጅ ግኝት ወይም ጥበብ ውጤት አይደለም።

▣ **"እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ"** ይህ የሚያመለክተው በለማወቅ የሚሆንን ሳይሆን በፍቃደኝነት ላለመቀበል መፈለግን ነው (21፣32፣ ዮሐ 3፡17-21)። ይህ ሀረግ (1) እውነትን እያወቁ የማይቀበሉ፣ (2) አኗኗራቸው እውነትን እንዳልተቀበሉ የሚያሳዩትን ወይም (3) ሕይወታቸው እና ከአፋቸው የሚወጣው ቃል ሌሎች እውነትን እንዳያውቁ እና እንዲያቀበሉ የሚያደረግ የሚያሳዩትን ሊያመለክት ይችላል።

**ልዩ ርዕስ፡ በጳውሎስ መልዕክት ውስጥ "እውነት" ማለት ነው።**
የዚይህ ቃል የጳውሎስ አጠቃቀም ከብሉይ ኪዳን አቻው "ኤሜት" ከሚለው፣ የሚታመን ወይም ታማኝ የሚል ትርጓሜ ካለው ቃል የመጣ ነው። በአዋልድ መጽሐፍት ውስጥ ይህ እውነት የሚለው ቃል ከሐሰት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። ምንአልባተም በሙት ባሕር ውስጥ የተገኙት ጽሑፎች የተሻሸለ በትይዩ ንጽጽር የበቀረበ ጽሑፍ ውስጥ በተገለጠ አስተምህሮ እንዲህ ይላል "የምስጋ መዝሙሮች"። የእሴንስ የተባሉ ማህበረሰቦች "እውነት ምስክሮች" ተብለው ተጠርተዋል።

ጳውሎስ ይህ ቃል ኢየሱስን ወንጌል ለማመልከት ተጠቅሞታል።

1. ሮሜ 1:18፣ 25፣ 2:8፣ 20፣ 3:7፣ 15:8
2. 1ቆሮ 13:6
3. 2ቆሮ 4:2፣ 6:7፣ 11:10፣ 13:8
4. ገላ 2:5፣ 14፣ 5:7
5. ኤፌ 1:13፣ 6:14
6. ቆላ 1:5፣6
7. 2ተስ 2:10፣12፣13
8. 1ጢሞ 2:4፣ 3:15፣ 4:3፣ 6:5
9. 2ጢሞ 2:15፣18፣ 25፣ 3:7፣8፣ 4:4
10. ቲቶ 1:1፣ 14

ጳውሎስ ይህንን ቃል የተናገረው እርግጠኛ ነገር መሆኑን ለማመልከት ተጠቅሟል

1. የሐዋ 26:25
2. ሮሜ 9:1
3. 2ቆሮ 7:14፣ 12:6
4. ኤፌ 4:25
5. ፊል 1:18
6. 1ጢሞ 2:7

በ1ቆሮ 5:8 ላይ ጳውሎስ መነሻ ሀሳቡን እና አኗኗሩን ለመገለጽም ተጠቅሟል። እንዲሁመ ለሁሉም ክርስቲያኖች በኤፌ 4ለ24፣ 5:9፤ ፊል 4:8 ተገልጿል። አንዳንድ ጊዜም ለሰዎችም ውሏል፦

1. ለእግዚአብሔር በሮሜ 3:4 (ከዮሐ 3:33፣ 17:17)
2. 2. ለኢየሱስ በኤፌ 4:21 (ከዮሐ 14:6 ጋር ተመሣሣይ ነው)
3. 3. በሐዋርያት ምስክርነት ውስጥ ቲቶ 1:13
4. 4. ጳውሎስ 2ቆሮ 6:8

ጳውሎስ ብቻ ነው ይህንን ቃል በግስ መልክ በኤፌ 4:16 እና ኤፌ 4:15 ለወንጌል የተጠቀመው።

1:19 **"እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና።"** የሰው ልጆች በሙሉ ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ ነገር ያውቃሉ (ከቁጥር 20፣ እዮ 12:7-10 እና መዝ 19:1-6 (በተፈጥሮ)፣ 12-15 (በመጽሐፍ ቅዱስ) እንዲሁም ጥበብ)። በሥነ መለኮት ይህ ተፈጥሮአዊ መገለጥ ይባላል። ምንም እንኳ ይህ ሙሉ ባይሆንም ነገር ግን "ልዩ መገለጠ" በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ፍጹም የሆነ መገለጠን ደግሞ በኢየሱስ በኩሉ ላላገኙ ሰዎች እግዚአብሔር ተጠያቂ የሚያደርግበት መሠረት ሆኖ ያገለግላል (ከቆላ 1:15፣ 2:9 ጋር ያነጻጽሩ)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ማወቅ" የሚለው ቃል በሁለት መንገድ አገልግሎት ላይ ውሎ ይገኛል። (1) እንደ ብሉይ ኪዳን የቃሉ ትርጉሙ የሚያመለክተው ጥብቅ የሆነ ግላዊ ግንኙነትን ነው (ዘፍ 4:1፣ ኤር 1:5) እንዲሁም (2) በግሪክ የቃሉ ትርጉም መሠረት ስለ አንድ ነገር ተጨባጭ ሁኔታን ማወቅ ማለት ነው። (ከ ቁጥር 21 ጋር ያነጻጽሩ) ወንጌል ወደ ውስጥ ልጋበዝ የሚገባ ግለሰብ እንዲሁም ስለሚንቀበለው ግለሰብ የተነገረ መልዕክት እን ልታመን የሚገባ እውነት ነው። በዚህ ቁጥር ላይ የቃሉ ትርጓሜ በሁለተኛው የተገለጸው ነው።

1:20 በዚህ ቁጥር ሦስት እግዚአብሔር መገለጫ ባሕርያት ተገልጠዋል፦

1. የማይታዩ ባሕርያት (ከቆላ 1:15፣ 1ጢሞ 1:17፣ ዕብ 11:27)
2. ዘላለማዊ ኃይሉ (በተፍጥረትየታየው)
3. መለኮታዊ ባሕርይው (በሥራው እና በመፍጠሩ ምክንያት የታየው)

▣ **"ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ"** አፖ "ከ" የሚለው መስተዋደዳዊ ቃበፊል በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ጊዜን በሚያመለክት መልኩ ነው። ተመሳሳይ ሀረግ በማር 10:6፣ 13:19፣ 2ጴጥ 3:4 ላይ ይገኛል። ይህ የማይታየው አምላክ አሁን (1) በቁሳዊ ፍጥረታቱ (በዚህ ቁጥር)፤ (2) በቅዱሳት መጻሕፍት (መዝ 19፣ 119) እና (3) በመጨረሻም በኢየሱስ በኩል (ከዮሐ 14:9 ጋር ያነጻጽሩ) ታይቷል።

▣ **"መለኮታዊ ባሕርይው"** ከግሪክ ስነ ጽሑፍ ውስጥ "ቲዮቴስ" የሚለው ቃል "መለኮታዊ ክብር ተብሎ ልተረጐም ይችላል። ይህም በኢየሱስ በኩል በላቀ ሁኔታ ታይቷል። እርሱ ልዩ በሆነ ሁኔታ የአምላክን መልክ የያዘ ነበር (ከ2ቆሮ 4፡ 4፣ ዕብ 1:3 ጋር ያነጻጽሩ)። እርሱ በሰው መልክ ተገለጠ ፍጹም አምላክ ነው። (ቆላ 1:19፣ 2:9) እጅግ በጣም ጥሩ የሆነው የወንጌል እውነት በኀጢአት የወደቁት የሰው ልጆች በክርስቶኢ በማመን ክርስቶስን የመመስል ይችላሉ የሚል ነው (ዕብ 12፤10፣ 1ዮሐ 3:2)። በሰው ልጆች ውስጥ ያለው እግዚአብሔር መልክ (ዘፍ 1:26-27) ታድሷል (2ጴጥ 1:3-4)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከተሠሩት ግልጥ ሆኖ ይታያል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ከተሠሩት ነገሮች በግልጥ ይታያል"** |
| **ኒው ሪቫይዝድ ሳታንዳርድ ቨርዥን** | **"ከተሠሩት በገሮች በግልጥ ይገነዘቡታል እንዲሁም ይታያል"** |
| **አእቅ** | **"በግልጥ ይታያል፤ እግዚአብሔር ከሠራቸው ነገሮች በግልጽ መገንዘብ ይቻላል"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብብል** | **"የተፈጠሩት ነገሮች በአእምሮ በመረዳት በግልጥ ይታያል"** |

ኒዮ የሚለው የግሪክ ቃል እና ካቶራኦ የሚለው ቃል ውህደት የሚያመለክተው ትክክለኛ መረዳት ነው:: እግዚአብሔር እራሱን የገለጠባቸው ነገሮች አሉ:: እነርሱም (1) ተፈጥሮ እና (2( ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው:: ሁሉም ሰዎች ሊረዷቸው የሚችሉ እና ከሰዎችም ምላሽን የሚጠብቁ ናቸው:: (ጥበብ 13፡1-9)::

▣ **"ስለዚህምየሚያመካኙት አጡ"** ይህ በግልጽ የሚያሳየው "ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት እንደሌላቸው ነው":: ጸሐፍው በዝይህ ስፍራ ላይ የተጠቀመው የግርክ ቃል በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ስፍራ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ይሄውም በዝይህ ስፍራ 2፡1 ላይ ነው:: ምዕራፋ 1፡18-3፡20 ያለው ክፍል ሥነ መለኮታዊ ዓላመው የሰው ልጆች ሁሉ መንፈሳዊ ውድቀት ለማሳየት መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው:: የሰው ልጆች ስላላቸው እውቀት ኃላፍነት አለባቸው:: እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የሚጠይቀው ባላቸው እውቀት ወይም ልኖራቸው በሚችለው እውቀት ነው::

1፡21 **"ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ"** የሰው ልጆች በሂደት ኃይማኖተኞች አልሆኑም:: ነገር ግን በሂደት ክፍዎች እየሆኑ ግን ሄደዋል:: ከዘፍጥረት 3 በኃላ ሰው ልጆች ሁሉ ወደታች አሽቆልቁለዋል:: ጨለማው ለጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል!

▣ **"እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩት ወይም ስላላመሰገኑት"** በቁጥር 23፣ 24 ላይ የሚገኘው የኢ-አማኞች የጣኦት አምልኮ ትረጂድ ነው (ከኤር 2፡9-13 ጋር አነጻጽር)::

▣ **"ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ።"** የሰው ልጆች ኃያማኖታዊ ቀመር የእነርሱን አመጸኝነት እና እብርት የሚያሳይ ነው:: በዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀሱት ግሦች የአለፊ ጊዜን የሚያመለክቱ እና ኢተሻጋር ግሦች ናቸው:: ኢ-ተሻጋር ግሦች የሚያመለክቱት የሰው ልጆች እግዚአብሔርን ያለዋቃቸው እና ተገቢውን ምላሽ ያለመስጠታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ልባቸውን እንዳያስተውሉ ጋርዶት ወይስ የተገለጠላቸውን ብርሃን ባለመቀበላቸው ምክንያት ልባቸውን ደንንድኖ ይሆንን? (፤10፡12-16፣ 2ነገ 17፡15፣ ኤር 2፡5፣ ኤፌ 4፡17-19)?

▣ **"ልብ"** ይህ ቃል በዝይህ ስፍራ ላይ የሚያገለግለው በብሉይ ኪደን ውስጥ በገለገለበት መልኩ ሲሆን የሚያመለክተውም ሙሉ ሰውን ነው:: ነገር ግን ይህ ቃል ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው የማሰብን እና የስሜትን ሂደት ነው:: 1፡24 ላይ ተገለጸውን ልዩ ርዕስ ተመልከት::

1፡22

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳር ቨርዥን** | **"ጥበበኞች ነን ብለው ስናገሩ ደንቆሮወች ሆኑ"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"ጥበብባን መሆናቸውን ብናገሩም ደንቆሮች ናቸው"** |
| **ኢመቅ** | **"ፈላስፋ መሆናቸውን በተናገሩ ቁጥር በድንቁርናቸው ይበልጥ እያደጉ ይሄዳሉ"** |

በግሪኩ "ደንቆሮ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በአማርኛ "ደደብ" እንደማለት ነው"" ችግሩ የሰው ልጆች ባላቸው እውቀት መመካት እና በራስ መተማመን ነው (1ቆሮ 1፡18-31)፣ ቆላ 2፡8-23):: ይህ ደግሞ በዘፍ 3 ላይ ወደ ተከሰተው ነገር ወደኃላ ይመልሰናል:: እውቀት መለየት እና ፍድን አምጥቷል:: ይህ ማለት ግን ሰው ልጆች እውቀት ሁል ጊዜ ስሕተት ነው ማለት ሳይሆን ነገር ግን ይህ እውቀት ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ አይደለም ማለት ነው::

1፡23 በፍቃደኝነታቸው ቸልተኞች የሆኑት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈተሩት የሰወ ልጆች (ከዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፣3፣ 9፡6 ጋር ያነጻጽሩ) እግዚአብሔር ከምድራዊ ፍጥረታት ጋር አመሳሰሉት:: እነዚህም፡

1. እንስሳት (ግብጻዊያን)
2. የተፈጥረሮ ኃይላት (ፐርሽያ)
3. የሰው ልጆች ቅርጽ (ግሪካዊያን እና ሮማዊያን)- ጣኦታት! የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሆኑትም ብሆን ይህንን አድረገዋል (ዘዳ 4፡15-24)::

ይህ ነገር በዘመናችን በአዲስ መንገድ መገለጥ ጀምሯል

1. የተፈጥሮ መብት ተቆራቋሪዎች (እናት መሬት)
2. የምስራቁ ዓለም የአዲሱ ጊዜ አመለካከት (ገዳማዊነት፣ አመንፋሽነት እና ጥንቆላ)

3. ሰዋዊ ኢኣማንነት (ማርክዝም፣ ዩቶጵያንዝም፣ ፕሮግሬስቭ አይዲያልዝም እና በፖለቲካ ላይ ፍጹም እምነትም መጣል ወይም በትምህርት ላይ ፍጹም እምነት መጣል።)
4. ሁለተናዊ ሕክምና (ጤንነት እና ረጅም እድሜ መኖርያ መንገድ)
5. ትምህርት

▣ **"ክብር"** 3፡23 ስር ያለውን ልዩ ርዕስ ተመ

**ልዩ ርዕስ፡ "የተበላሸ ሰው"**

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱልዩ **ርዕስ፡ ማበላሸት፣ ማጥፋት (ፓዜሮ)**
ፓዜሮ የሚለው የዚይህ ቃል መሠረታዊ ትረርጉም ማጥፋት፣ ማበላሸት ማለት ነው። ይህም ቃል ከዚይህ በታች በተዘረረዘሩት መልኩ በጥቅም ላይ ወሏል

1. ማዕለ ነዋዊ ብክነት (2ቆሮ 7፡2)
2. አካላዊ ጥፋት 91ቆሮ 3፡17ሀ)
3. ግብረ ገባዊ ብልሽት 9ሮሜ 1፡23፤ 8፡21፤ 1ቆሮ 15፡33፤ 42.50፣ ገላ 6፡8፣ ራዕ 19፡2)
4. ግብረስጋዊ ማነሳሳት 92ቆሮ 11፡3)
5. ዘላለማዊ ጥፋት (2ጴጥ 2፡12፣ 19)
6. የሰው ልጆች ትውፍት መጥፋት (ቆላ 2ለ22፣ 1ቆሮ 3፡17ለ)

ብዙ ጊዜ ይህ ቃል በተመሳሳይ አውድ ውስጥ የትክክለኛው ነገር ተቃራን ሆኖ ይቀርባል 9ሮሜ 1፡23፣ 1ቆሮ 9፡25፣ 15<50፣53)። ምድራዊው ቁሳዊ አካል እና ሰማያዊው ዘላለማዊ አካል ተነጻጸረበትን ስፍራ ያስተውሉ።

1. የሚበላሸው እና የማይበላሸው 1ቆሮ 15፡42፣ 50
2. የማያከብር እና ክብር 1ቆሮ 15፡43
3. ድክመት እና ጥንካሬ 1ቆሮ 15፡43
4. ተፈጥሮአዊው ሰውነት እና መንፈሳዊው ሰውነት 1ቆሮ 15፡44
5. የመጀመሪያ አዳም እና ሁለተኛው አዳም 1ቆሮ 15፡45
6. መድራዊው መልክ እና ሰማያዊው መልክ 1ቆሮ 15፡49

**ኒው አሜሪካም ስታንዳርድ ባይብል ክፍል 1፡24-25**
**ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።**

1፡24፣ 26፣ 28 **"እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው"** ይህ ሊከሰት ከሚችሉት እጅግ ክፉ የሆነ የፍርድ አይነት ነው። እግዚአብሔር "የወደቁት የሰው ልጆች የራሳቸውን መንገድ ይከተሉ' አለ። (መዝ 81፡12፣ ሆሴ 4፡17፣ የሐ 7፡42)። በቁጥር 23-24 ላይ የሚንመለከተው እግዚአብሔር የአሕዛቡን ኣለም ለራሱ ፍላጎት እና ኃይማኖታዊነት መተውን (ለጊዜውም ብሆን) ነው። የአሕዛባዊነት ዋነኛ መገለጫው ልቅ ፍተወት እና ብዝበዛ ነው።

1፡24 **"ልብ"** የሚከትለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ

**ልዩ ርዕስ፡ ልብ**

የዕብራይስጡን "ልብ" የሚለው ቃል የሰባ ሊቃውነትም ሆነ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ለማመልከት ተጠቀሙበት የግሪክ ቃል ካርዲያ ይባላል። ይህም ቃል በተለያየ መልኩ አገልግሎት ላይ ውሏል (ባዎር፣ አርደተ፣ ጊነገሪች እና ዳንክር፣ ግሪክ እንግልሽ ሌክስከን፣ ገጽ 403-404)

1. ለሰው ልጆች የሚውል ዘይባዊ አነጋገር ሲሆን የሚያመለክተውም የሰው ልጆችን አከላዊ ሕይወት ማዕከል ሆነውን ነው (የሐ 14፡17፣ 2ቆሮ 3፡2-3፣ ያዕ 5፡5)
   ሀ. የመንፈሳዊ (የግብረገባዊ) ሕይወት ማዕከልን
   ለ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃ 16፡15፣ ሮሜ 8፡27፣ 1ቆሮ 14፡25፤ 1ተሰሎ 2፡4፤ ረራዕ 2፡23)
2. ለሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት (ማቴ 15፡18-19፣ ሮሜ 6፡17፣ 1ጢሞ 1፡5፣ 2ጢሞ 2፡22፣ 1ጴጥ 1፡22)
3. የማሰብ ማዕከል ሆነውን (ይህም ማለት አእምሮን ማቴ 13፡15፣ 24፡28፣ የሐዋ 7፡23፣ 16፡14፣ 28፡27፣

ሮሜ 1፡21፣ 10፡6፣ 16፡18፣ 2ቆሮ 4፡6፤ ኤፌ 1፡18፣ 4፡18፣ *ያዕ* 1፡26፣ 2ጴጥ 1፡19፣ *ራዕ* 18፡7፤ ልብ ብዙ ጊዜ ከአእምሮ ጋር ተመሳሳይ ፍች አለው 2ቆሮ 3፡14-15 እና ፊል)።

4. የፍቃድ ምንጭ (የሐዋ 5፡4፣ 1፡23፣ 1ቆሮ 4፡5፣ 7፡37፣ 2ቆሮ 9፡7)
5. የስሜት ማዕከል (ማቴ 5፡28፣ የሐዋ 2፡26፣ 37፣ 7፡45፣ 21፤13፣ ሮሜ 1፡24፣ 2ቆሮ 2፡4፣ 7፡3. ኤፌ 6፡ 22፤ ፊል 1፡7)
6. መንፈስ የሚሰራበት ልዩ ስፍራ (ሮሜ 5፡5፣ 2ቆሮ 1፡22፣ ገላ 4፡6 (ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ነው ኤፌ 3፡ 17)
7. ልብ በዘይባዊ አነጋገር የሰው ልጅን ሁለንተናንን ይወክላል (ማቴ 22፡37 ከዘዳ 6፡5 የተወሰደው)። የአመለካከት፣ የመነሻ ምክንያት እና የድርግት ተግባራት በጠቅላላ ልብ እንዳደረጋቸው የሚነገሩት ልብ የሰውየውን ማንነት ስለሚገልጽ ነው። የብሉይ ኪዳን ጸሐፍት ልብን በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጠቅመውበት እናገኛለን፦

**1፡25 "የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ"** ይህንን ሀረግ በተለያዩ መንገዶች ልንረዳው እንችላለን (1) የሰው ልጆች እራሳቸውን ያበለሻሹበት (2ተሰ 2፡4፤ 11) (2) የሰው ልጆች የሁሉ ፈጣር የሆነውን ያህዌን ሳይሆን የእጆቻቸውን ሥራ ማምለካቸውን (ጣኦታትን) (ኢሳ 44፡20፣ ኤር 13፡25፣ 16፡19) (18 -23) ወይም (3) የሰው ልጆችን በወንጌል የተገለጠው እውነት ፈጽመው ለመቀበል አለመፈለጋቸውን (ዮሐ 14፡17፣ 1ዮሐ 2፡21፣ 27)። በዚህ አውድ ውስጥ ሁለተኛው አማራጭ ከሌሎቹ በተሻለ ይስማማል።

▣ **"ስላመለኩና ስላገለገሉ"** የሰው ልጆች ዘወትር የሚያመልኩት ነገር አላቸው። የሰው ልጆች ሁሉ የሆነ ነገር፣ የሆነ እውነት ወይም ከእነርሱ በላይ የሆነ ነገር እንዳለ ይሰማቸዋል።

▣ **"እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።"** ጳውሎስ እርሱ ጽሑፎች ዋነኛ መገለጫ ወደሆነው ወደ አይሁዳዊያን ባርኮት ይገባል። (ሮሜ 9፡5፣ 2ቆሮ 11፡31)። ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ስጽፍ ይጸልያል (9፡5፣ 11፡36፣ 15፡33፣ 16፡27)።

▣ **"ለዘላለም"** ከዚይህ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ ለዘላለም (ግሪክ ኢዲኦማስ)**

በግሪክ ቋንቋ አንዱ በተለምዶ የሚነገር ዘይቤአዊ አነጋገር "ለዘመናት" የሚለው ሲሆን (በሉቃ 1፡33፣ ሮሜ 1፡25፣ 11፡36፣ 16፡27፣ ገላ 1፡5፤ 1ጢሞ 1፡17 ላይ ይገኛል) ይህ ምናልባትም የዕብራይስጡን "ኦላም" የሚለውን ቃል ሳያመለክት አይቀርም። ሌላኛው "ለዘመናት" ከሚለው ቃል ጋር ዛማጅ የሆነው ቃል (በማር 21፡19 በሉቃ 1፡55፤ ዮሐ 6፡58፣ 8፡35፣ 12፡34፣ 13፡8፣ 14፡16፣ 2ቆሮ 9፡9) እንዲሁም "ከዘመን ዘመናት" የሚለው ሀረግ (ከኤፌ 3፡21 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ቃል "ዘላለማዊ" ከሚለው ቃል በትርጓሜ ልዩነት ያለው አይመስልም። "ለዘመናት" የሚለው ቃል በምሳሌያዊ አነጋገር ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ በእብራዊያን ስዋሰዋዊ ቀመር ይህ "አክብሮታዊ ብዙ ቁጥር" በመባል ይታወቃሉ ወይም ይህ ቃል "ያልታወቁ ዘመናትን" የሚያመለክተውን የእብራዊያንን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚይህ ዘመናት "የአመጽ ዘመን"፣ "የሚመጣው ዘመን"፣ ወይም "የጽድቅ ዘመን" ተብለው ይጠራሉ።

▣ **"አሜን" ከዚይህ በታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመለከቱ።**

**ልዩ ርእስ፡ አሜን**

1. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የመጣው ከእብራይስጡ እውነት የሚል ትርጓሜ ካለው ኢሜት ወይም እውነተኛ (እሙን ፣ እሙናህ) እና እምነት ወይም ታማኝ ማለት ነው።
   ለ. የቃሉ ሥረወ ግንድ የሰውዬው አካላዊ ቋም መግለጫ እንደ ማለት ነው። የዚይህ ተቃራንው የአንድ ሰው ማወላመል፣ ማደለጥን ያመለክታል (ዘዳ 28፡64-67፣ 38፡16፣መዝ 40፡2፣ 73፡18፤ ኤር 23፡12) ወይም እንቅፋትን ያሳያል (መዝ 73፡2)። ከዚይህ እነ ጽሑፋዊ የቃሉ አጠቃቀም ዘይቤአዊው የቃሉ ተቀጽሌአዊው ትርጓሜ የመነጨ ስሆን ትርጓሜውም ታማኝ፣ የሚታመን ትርጉም ማለት ይሆናል (ዘፍ 15፡16፤ ዕብ 2፡4)።
   ሐ. የቃሉ ልዩ አጠቃቀም።
      1. ማማ 2ነገ 18፡16 (1ጢሞ 3፡15)
      2. ማረጋገጫ ዘጽ 17፡12
      3. መጽናት ዘጽ 17፡12

4. አለመወላወል ኢሳ 33፡6፣ 34፡5-7
5. እውነት 1ነገ 10፡6፣ 17፡24፣ 22፡16፣ ምሳ 12፡22
6. ጽናት 2ዜና 20፡20፣ ኢሳ 7፡9
7. የሚደገፉት (ብሔረ ኦርት) መዝ 119፡43፣ 142፣ 151፣ 168

መ. ስለ እምነት ሥራ ለመግለጽ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት በእብራይስጥ ቃል በጥቅም ላይ ውለዋል
1. ባታኽ፤ መታመን
2. ያራ፤ ፍራቻ፣ አክብሮት፣ አምልኮ (ዘፍ 22፡12)

ሠ. ከመታመን ወይም ታማኝነት ከሚለው የቃሉ ትርጓሜ በመነሳት ይህ ቃል የአንድን በጽሑፍ የቀረበ የእምነት መግለጫ ታማኝነት ለማረጋገጥ የሚያገለግል ዓረፍተ ነገር ውሏል (ዘዳ 27፡15- 26፣ ነህ 8፡6፣ መዝ 41፡13፣ 72፡19፣ 89፡52፣ 106፡48)።

ረ. የዚይህ ቃል ሥነ መለኮታዊ ቁልፍ ሀሳብ ከሰው ልጆች ታማኝነት ጋር ተቆራኝ ሳይሆን የያህዌ ታማኝነት ነው (ዘፍ 34፡6፣ ዘዳ 32፡4፣ መዝ 108፡4፣ 115፡1፣ 117፡2፣ 138፡2)። ኀጢአተኞ የሆኑት የሰው ልጆች ብቸኛ ተስፋ ርሁሩህ እና የያህዌ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆን እና የተስፋ ቃሉ ናቸው፡፤

ያህዌን የሚያውቁ ሰዎች እርሱን ልመስሉ ይገባል (ዕብ 2፡4)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የራሱን መልክ እንደገና ለማደስ ያደረገው ነገር ታርክ እና ይህንን የዘገበ መጽሐፍ (ዘፍ 1፡26-27) ነው። ድነት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ የሚችልበት አቅም የሚያድስ ነው። ለዝይህም ነው እኛ የተፈጠርነው።

2. አዲስ ኪዳን

ሀ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለመደው ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ የእምነት መግለጫዎች ተዓማንነት ለማረጋገጥ ነው (19፡5፣ 11፡36፣ 1ቆረ 14፡16፣ 2ቆሮ 1፡20፣ ራዕ 1፡7፣ 5፡14፣ 7፤12)።

ለ. ይህ ቃል የጸሎት መዝጊያ ሆኑ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቦታዎች ውስጥ ውሏል። (ሮሜ 1፡25፣ 9፡5፣ 11፡36፣ 16፡27፣ ገላ 1፡5፣ 6፡18፣ ኤፌ 3፡21፣ ፊል 4፡20፣ 2ተሰ 3፡18፣ 1ጢሞ 1፡17፣ 6፡16፣ 2ጢሞ 4፡18)።

ሐ. ይህንን ቃል በጣም ጠቃም የሆኖ ዓረፍተነገረን ለመጀመር የተጠቀመበት ኢየሱስ ብቻ ነው (በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጥቅሞታል) (ሉቃ 4፡24፣ 12፡37፣ 18፡17፣29፣ 21፡32፣ 23፡24)።

መ. በራዕ 3፡14 ላይ ይህ ቃል የኢየሱስ መጠሪያው ሆኖ አገልግሏል (ምናአልባትም በኢሳ 65፡16 ላይ የያህዌ መጠሪያም ሆነ አገልግሎ ሊሆን ይችላል።)

ሠ. ታማኝነት ወይም እምነት፣ የሚታመን ወይም እሙን የሚሉ ቃላት መልዕክትን የሚያስተላልፉት የግሪክ ቃል "ፔስቶስ ወይም ፒስቲስ ወደ አማርኛ መታመን፣ እምነት እና ማመን ብምሉ ቀላት ተተርጉመዋል።

**ሮሜ 1፡26-27**

**ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።**

1፡26-27 ግበረሰዶማዊያን የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የፍጥረት ፍቃድ ውጭ ለመሆናቸው አንዱ ምሳሌ ነው። (እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ብሏልና) ይህ ኀጢአት እና ዋነኛ ባህላዊ ችግር ነው (1) በብሉይ ኪዳን ውስጥ (ዘለ 18፡22፣ 20፣ 20፡13፣ ዘዳ 23፡18) (2) በግሪካዊያን- ሮማዊያን ዓለም ውስጥ (1ቆሮ 6፡9፣ 1ጢሞ 1፡10) እና (3) በእኛም ዘመን ውስጥ።

ሙሉ አውዱ ዘፍ 1-3 ያለውን ክፍል ታሳብ ያደረገ በመሆኑ ግብረሰዶማዊነት የወደቀው ሰው ሕይወት ምን እንደሚመስል ለማሳየት እንደ አንድ ምሳሌ የቀረበ ነው። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል (ዘፍ 1፡26-27፣ 5፡13፤ 9፡6)። የሰው ልጅ ወንድ እና ሴት ሆኖ ተፈጥሮአል (ዘፍ 1፡27)። እግዚአብሔር የሰው ልጆች እንዲባዙ እና ምድርን እንድሞሏት አዟል (ዘፍ 1፡28፣ 9፡1፣ 7)። የሰው ልጆች በዘፍጥረት 3 ላይ በመውደቃቸው ምክንያት የእግዚአብሔርን እቅድ እና ፍቃድ አበላሽተዋል። ግብረሰዶማዊያን ግልጽ የሆነ አመጽ ነው። ነገር ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የተገለጸው ኀጢአት ይህ ብቻ እንዳልሆነ ግን ግልጽ ልሆን ይገባል። (29-33) በእነዚህ ክፍል ውስጥ የተገለጡት ኀጢአቶች ሁሉ የሚያሳዩት የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር መለየታቸው እና ሁሉ ቅጣት እንደሚገባቸው ነው። ሁሉም ኀጢአቶች በተለይም የሕይወት ዘይቤ የሆነ ኀጢአት በእግዚአብሔር ዘንድ ጸያፊ ነው።

**ለዩ ርዕስ ፡ ግብረሰዶማዊነት**

በዚይህ በዘመናዊው ባህል ውስጥ ግብረሰዶማዊነትን እንደ አማራጭ የሕይወት ዘይቤ እንድንቀበለው የሚገፋፉን ብዙ ዘመናዊ ባህሎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ከእግዚአብሔር የሥነ ፍጥረት ፍቃድ ውጭ የሆነ አፍራሽ የሕይወት ዘይቤ በመሆኑ ይኮንነዋል።

1. በዘፍ 1 ላይ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት የሚለው እግዚአብሔርን ትዕዛዝ ይጣረሳል።
2. ይህ የአሕዛብን ባሕል እና አምለኮን የሚያንጸባርቅ ነው (ዘሌ 18፡22፣ 20፡13፣ ሮሜ 1፡26-27 እና ይሁ 7)።
3. ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ ራስን ማዕከል ማድረግን ያ፣ለክታል (1ቆሮ 6፡9-10)

ነገር ግን ይህንን ርዕስ በዚይህ ላይ ከመቋጨቴ በፊት አንድ ነገር ልጨምር፤ ይሄውም ለአመጸኞቹ የሰው ልጆች ያለውን የእግዚአብሔር ፍቅር እና ይቅርታ ነው። ክርስቲያኖች በተለይም በዚይህ ዓይነት ኀጢአት ላይ ልዩ ጥላቻ ማሳየት የለባቸው፤ ምክንያቱም ሁሉ ኀጢአት አለበትና። ጸሎት፣ እንክብካቤ፣ ምስክርነት እና ርህራሄ ከመፍረድ የበለጠ ነገር ይሰራሉና።

እኛ ከፈቀድንላቸው የእግዚአብሔር ቃል እና መንፈስ የመውቀሱን ነገር እነርሱ ይሰሩታል። ሁሉም ወስባዊ ኀጢአቶች፣ ይህ ብቻ ሳይሆን በእግአብሔር ዘን ጸያፎች እና ቅጣትን የሚያስከትዩ ላቸው። የግብረስጋ ግንኙነት ለሰው ልጆች መልካምነት፣ ደስታ እና የተረጋጋ ማህበረሰብን ለመፍጠር የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ነገር ግን ይህ በእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ብዙ ጊዜ በአመጻ፣ በራስ ወዳድነት፣ ደስታ ፍለጋ "በማንኛውም ዋጋ ለኔ ብዙ በሚል እሳቤ ይለወጣል (ሮሜ 8፡1-8፣ ገላ 6፡7-8)።

1፡28-32

**እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።**

**1፡28-31** ይህ በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አረፈተ ነገር ነው። የሚያመለክተውም አመጻኛውን፣ የወደቀውን እና እምድበተኛውነ ሰው ልጅን ነው (ሮሜ 13፡13፣ 1ቆሮ 5፡11፣ 6፡9፣ ገላ 5፡19-21 ኤፌ 5፡5፣ 1ጢሞ 1፡10፣ ራዕ 21፡8)።

የሰው ልጆች ኀጢአት ሆነባቸው ነገር ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ ሕያውንትን ስለፈለጉ ነው። ስኦል ደግሞ በቋምነት የተዘጋጀ ይህ ስፍራ ነው። ነጻነት ውሸት ነው! የሰው ልጅ እግዚአብሔር አስፈልገዋል፣ የሰው ልጅ ጠፍቷል፣ ከእግዚአብሔር ውጭም የሰው ልጅ ባዶ እና ብቁ የማይሆን ነው። በስኦል ውስጥ ከሁሉ የከፋው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር አለመገናኘት ነው!

**ልዩ ርዕስ፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መገዛት እና መልካም ባህርይ**

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመገዛት እና መልካም ባህርይን የሚያመለክቱ ክፍሎች ዝርዝር ብዙ ነው። ብዙ ጊዜ የረብዎችን (የአይሁድ መምህራንን) እና የባህላዊ (የሄሊኒስቲክ ባህልን) የሚያንጸባርቁ ናቸው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ እነዚይህ ነገሮችረ ዝርዝር፦

| | <u>መገዛት</u> | <u>መልካም ባህርይ</u> |
|---|---|---|
| 1. ጳውሎስ | ሮሜ 1፡28-32 | . . . |
| | ሮሜ 13፡13 | ሮሜ 2፡9-21 |
| | 1ቆሮ 5፡9-11 | . . . |
| | 6፡10 | 1ቆሮ 6፡6-9 |
| | 2ቆሮ 12፡20 | 2ቆሮ 6፡4-10 |
| | ገላ 5፡19-21 | ገላ 5፡22-23 |
| | ኤፌ 4፡25-32 | . . . |
| | 5፡3-5 | . . . |
| | . . . | ፊል 4፡8-9 |
| | ቆላ 3፡5፣8 | ቆላ 3፡12-14 |
| | 1ጢሞ 1፡9-10 | . . . |

| | | |
|---|---|---|
| | 6:4-5 | . . . |
| | 2ጢሞ 2:22*ሀ*፣ 23 | ቲቶ 1:8-9፣ 3:1-2 |
| 2. *ያዕቆብ* | *ያዕ* 3:15-16 | *ያዕ* 3:17-18 |
| 3. ጴጥሮስ | 1ጴጥ 4:3 | 1ጴጥ 4:7-11 |
| | 2ጴጥ 1:9 | 2ጴጥ 1:5-8 |
| 4. ዮሐንስ | *ራዕ* 21:8 | . . . |
| | 22:15 | |

1:29 **"*የማይረባ አእምሮ*"** *የወደቀው ሰው እንደ ነጻነት ተመለከተው ነገር እራስን ማምለክ ነው፡ "ሁሉን እና ማንኛውንም ነገር ለኔ" ማለት ነው።* በ1:24፣ 26፣ 25 *ላይ የተገለጸው አዲረግ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው ነገር ግን በዚህ አውድ ውስጥ እና ከዘፍ 1-3 ጋር ባለው ግንኙነት የሰው ልጆች የማውቅ እና የእራስ ምርጫ የችግሩ መነሻ መሆኑን እንገነዘባለን። እግዚአብሔር ፈጥረታቱ የምርጫቸውን ውጤት ኢቀበሉ ዘንድ ፈቅዷል።*

▣ **"*ተሙሉ*"** *የሰው ለጆች ትኩረት በምሰጡት ነገር ይሞላሉ በዚያም ይመስላሉ። የአይሁድ መምህራን በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ጥቁር ውሻ* (*ክፉ 'ይተዝር*) *እንዲሁም ነጨኢ ውሻ* (*መልካም 'ይተዝር*) *አለ ይላሉ። ብዙ ግዜ የመቀለበው እርሱ ትልቅ ይሆናል።*

**ልዩ ርዕስ፡ ጳውሎስ "ሁፐር" ተባለውን የግሪክ ቃል ጥምር ቃለትን ለመፍጠር እንዴት እንደተጠቀመበት**
*ጳውሎስ የግሪክ ቃል ሆነው "ሁፐር" የሚለውን መስተዋደዳዊ ቃል በመጠቀም ብዙ ጥምር ቃላትን ፈጥሯል። የዚይህ ግሪክ ቃል መሠረታዊ ትርጉም "በላይ" "የላይኛ" ማላት ነው። ከአገናዛቢ ጋር ይህ ቃል ስገናኝ ትርጓሜው "በእርሱ ፍንታ" ይሆናል። በተጨማሪም ይህ ቃል "ስለ" የሚል ትርጓሜ አለው። እንዲሁም የግሪክ ቃል "ፔሪ" ይህ ቃል ከተሳቢ ጋር ስመጣ ትርጓሜውም "በላይ" ወይም "ከላይ" "በተጨማሪ" የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል። ከዚይህ በታች ያለቱ ጳውሎስ ይህንን መስተዋድዳዊ ቃል በጥምር ቃል መልኩ የተጠቀመበትን ዝርዝር ነው።*

*ሀ*. *ሀፓክሳ ሌጎምኖን* (በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል አንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ ውሏል)

1. *ሁፐርካምስ*፣ የቀድሞ ሕይወት 1ቆሮ 7:36
2. *ሁፐርኤዝአና*፣ ይበልጥ መጨመር 2ተሰሎ 1:3
3. *ሁፐርባና*፣ መተላለፍ ተሰሎ 4:6
4. *ሁፐርኬና*፣ ባሻገር 2ቆሮ 10:16
5. *ሁፐርኬና*፣ በጣም የተለጠጠ 2ቆ፣ መገሮ 10:14
6. *ሁፐርቱገቻና*፣ መማለድ ሮሜ 8:26
7. *ሁፐርኒካኦ፣* ባለድል ወይም አሸናፍ መሆን ሮሜ 8:37
8. *ሁፐርፐሊኦናዞ*፣ መትረፈረፍ 1ጦሞ 1:14
9. *ሁፐርዩፐሶ*፣ በጣም ከፍ ከፍ መላት ፊል 2:9
10. *ሁፐርፊሮኒኦ*፣ ከፍ ያለ አመለካከት መኖር ሮሜ 12:3

ለ. በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ ብቻ የሚገኙ ቃላት

1. ሁፐርኤሮማይ፣ እራሳን ከፍ ከፍ ማድረግ 2ቆሮ 12:7፣ 2ተሰ 2:4
2. ሁፐርባሎነቶስ፣ ከመስፈርት በላይ፣ 2ቆሮ 11:23)
3. ሀፐርቦሌ፣ የተመነጠቀ፣ ከመቅጽፈት የሚወነጨፍ ሮሜ 7:13፣ 1ቆሮ 12:3፣ 2ቆሮ 1:8፣ 4:7፤ 17፣ 22:7፣ ገላ 1:13
4. ሁፐርከፐሪሶዩ፣ ከመስፈርት ሁሉ በላይ ኤፌ 3:20፣ 1ተሰ 3:10፣ 5:13
5. ሁፐርሊአን፣ በከፍተኛ ሁኔታ፣ በዋነኝነት 2ቆሮ 11:5፣ 12:11
6. ሁፐርኦቸኢ፣ የታወቀ፣ ውጤታማ 1ቆሮ 2:1፣ 1ጢሞሜ 5: 2:2
7. ሁፐርፐሪሶ፣ መትረፈረፍ፣ ከመቂ በላይ መሆን ሮሜ 5:20

ሐ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ አልፈው አልፈው የሚገኙ ነገር ግን ጳውሎስ የተጠቀመባቸው ቃላት

1. ሁፐርአኖ፣ በጣም ከላይ ኤፌ 1:21፣ 4:10 እና ዕብ 9:5
2. ሁፐርኢኮ፣ የተሳካ፣ የታወቀ ሮሜ 14:1፣ ፊል 2:3፣ 3:8፣ 4:7፣ 1ጴጥ 2:13
3. ሁፐርኤፋኖስ፣ *መገመት* ሮሜ 1:30፣ 2ጢሞ 1:30፣ 2ጢሞ 3:2 እና ሉቃ 1:51፣ *ያዕ* 4:6፣ 1ጴጥ 5:5

*ጳውሎስ ትልቅ ጥንካሬ የነበረው ሰው ነበር፤ ነገሮች ወይም ሰዎች መልካም ሲሆን* <u>በጣም</u> *መልካም ይሆናሉ እንዲሁም መጥፎ ስሆኑም እንዲሁም በጣም መጥፎ ይሆናሉ። ይህ ወስተዋደዳዊ ቃል ይህንን ስለ ኀጢአት፣ ስለ ራሱ፣ ስለ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌል አለውን ተለዋዋጭ ስሜቱን መግለጽ እንድችል አድርጎታል።*

**1:29-30** እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ውጭ ሆነ ሕይወት መገለጫዎች እና ውጤቶች ናቸው። እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገለተውን እግዚአብሔርን አልቀበል ያሉ ግለሰቦች እና ማህበረሰብ መገለጫ ባሕርያት ናቸው። እነዚህ ጳውሎስ የዘረዘራቸው ብዙ የኀጢአት ዝርዝሮችረ ናቸው (1ቆሮ 5:11፣ 6:9፣ 2ቆረ 12:20፣ ገላ 5:19-21፣ ኤፌ 4:31፣ 5:3-4፣ ቆላ 3:5-9)።

**1:30** "አመጻ" ከዚይህ ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**1:32 "እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል"** ይህ ዓረፍተ ነገር የሙሴን ሕግጋት ነጸብራቅ ይታይበታል። ይህም በሮሜ 6:16፣ 21፣ 23፣ 8:6፣ 13 ተጠቃሎ ቀርቧል። ሞት የእግዚአብሔር ፍቃድ እና እግዚአብሔራዊ ሕይወት ተቃራን ነው (ሕዝ 18:32፣ 1ጢሞ 2:4፣ 2ጴጥ 3:9)።

▣ **"እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም"** የሚያሳዝን የፍቅር አጋሮች ናቸው። የወደቀው የሰው ልጅ የሌሎችን ኀጢአት "ሁሉም ሰው የሚያደርገው ነው" በማለት ለማስተባበያነት ይጠቀምበታል። የተለያዩ ባሕሎች የሚፈጽሙት የተለየ ኀጢአት መገለጫቸው ነው።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> የመጽሐፍ ቅዱስ መፊቻ ነው። ይህ ማለት እናንተ መጽሐፍ ቅዱሰን ስለምትፈቱበት መንገድ እራሱ ተጠያቂዎች ናችሁ። እያንዳንዳችን እንዳለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል። እናንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜያችሁ ውስጥ ቀዳሚዎች ናችሁ። ይህንን በምንም ዓይነት መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ መፊቻዎች ልትተካቸው አይገባም።*

*እነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡት በዚህ የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ሀሳቦችን እራሳችሁን በደንብ እንድታስቡበት ለማገዝ ነው። ዋነኛ አላማቸው እንድታስቡ ለማድረግ እንጅ ትርጓሜን ለእናንተ ለመስጠት አይደለም።*

1. ጳውሎስ ለምን ለሮሜ ሰዎች ይህንን መልዕክ ጻፈላቸው?
2. ለምን የሮሜ መጽሐፍ ለክርስቲያኖች ዋነኛ ሥነ መለኮታዊ እውነት ሆነ?
3. ሮሜ 1:8-3:20 ያለውን ክፍል በራሳችሁ ቃላት በንዑስ ሀሳቦች ከፋፍሏቸው
4. ወንጌልን ለመስማት እድሉን ያላገኙ ሰዎች በክርስቶስ ባለማመናቸው ይፈረድባቸዋል ወይ?
5. በ"ልዩ መገለጥ" እና "በተፈጥሮአዊ መገለጥ" መካካል ያለውን ልዩነት አስረዳ
6. የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ውጭ ያለውን ሕይወት ግለጽ
7. ቁጥር 24-27 ያለው ስለ ግብረሰዶማዊነት የሚናገር ክፍል ነውን?

# በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቤስ | ኒው ኪንግ ጀምስ ቨርዥን | ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን | ቶዴይ ኢንግልዥ ቨርዥን | ጀሩሳሌም ባይበል |
|---|---|---|---|---|
| ጻድቅ የሆነው የእግዚአብሔር<br>አይሁዳዊያንን የእግዚአብሔር<br>ፍርድ | የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ | መሆን | የአይሁዳዊያን በፍርድ ስር | የእግዚአብሔር ፍርድ<br>ቁጣ አያገኛቸውም |
| 2፡1-16 | 2፡1-16 | 2፡1-11 | 2፡1-16 | 2፡1-11 |
| አይሁዳዊያን እና ሕግ<br>ሕጉ አያድናቸውም<br>በደል | እንደ አሕዛብም የአይሁዳዊያን | | የፍርድ መሠረት | አይሁዳዊያን እና ሕግ |
| | | 2፡12-16 | | 2፡12-16 |
| 2፡17-3፡8 | 2፡17-24 | 2፡17-24 | 2፡17-24 | 2፡17-24 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
**የጸሐፍውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ**

ይህ የጥና መመርያ የመጽሐፍ ቅዱስኢ መክፈቻ ነው፤ ማለትም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምትረተጉሙበት መንገድ እራሳችሁ ኃላፊነቱነረ ትወስዳላችሁ። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል። አንተ፣ መጽሐፈ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ትክክለኛ ፍች ለማግኝት በምደረገው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊዎቸ ናችሁ። ይህንን እድል ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች ልንለውጠው አይገባም።

አንድን ምዕራፍ በአንድ ጊዜ አንብብ። የምዕራፉን ዋና ጭብጥ ለይ። ያገኘኸውን ጨብጥ ከሌሎች አምስት የመጽሐፍ ቅዱስት ትርጉሞች ጋር አነጻጽር። የአንቀጽ ክፍፍልሎች ምንም እንኳ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሠሩ ባይሆንም የስነ ትርጓሜ ማዕከል የሆነው የጸሐፍውን ዓለማ ለማወቅ ቁልፎች ናቸው። እያንዳንዱ አንቀጽ ሁል ጊዜም አንድ ጭብጥ ብቻ ይኖረዋል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተ

**ሮሜ 2፡1-3፡20 አውዳዊ መረዳት**

ሀ. ምዕራፍ 2 እና 3 በቁጥር 1፡18 ላይ የሚገኘውን ሀሳን ሙሉ የሚያደርጉ ናቸው። ይህ ክፍል የሚያወሳው፡-
1. የሰው ልጆች ሁሉ የተፉ መሆናቸውን
2. በኀጢአት ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ
3. የሰው ልጆ በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚያስፈልገው ይኸውም ማመን እና ንሰሓ በመግባት እንደሆነ

ለ. በምዕራፍ 2 ላይ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ሰባት መሪያዎች

1. ቁጥር 1 እንደ እውነት
2. ቁጥር 5 የተከማቸ በደል
3. ቁጥር 6 እና 7 እንደ *ሥራ*
4. ቁጥር 11 ሰዎችን ሁሉ እንደሚያካት
5. ቁጥር 13 የአኗኗር ዘይቤ
6. ቁጥር 16 የሰው ልጆች ልብ ምስጥር
7. ቁጥር 17-29 የተለዩ ሕዝቦች እንደሌሉ

ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች ውስጥ ምዕራፍ 2፡1-17 ለማን እንደ ተጻፈ ብዙ አይነት አመለካከቶች አሉ፡፡ ቁጥር 2፡12-29 ያለው አይሁዳዊያን አንደሚያመለክት ምንም አይነት ጥርጥር የለም፡፡ ቁጥር 1-17 ሁለት አላማዎች ያሉት ስሆን እነርሱም ግብረገባዊ አሕዛብን እና የሙሴ ሕግ ያላቸውን አይሁዳዊያንን ያመለክታል፡፡

መ. በ1፡18-21 ላይ ጳውሎስ የሰው ልጆች በተፈጥሮ አማካኝነት እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚችሉ ይናገራል፡፡ በ2፡ 14-15 ላይ ለሰው ልጆች ሁሉ ደግሞ በእግዚአብሔር የተሰጠ የሕልና ግብረገብ እንዳለ ይናገራል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ፍጥረት እና ሕልና ምንም እንኳ ብሉይ ኪዳን ወይም ወንጌልን ለመስማት እድሉን ባያገኙም እግዚአብሔር ሰዎች ላይ ከመፍረድ እንድችል መሠረት በመሆን ያገለግሉታል፡፡ የሰው ልጆች በተቀበሉይ ብርሃን መጠን መኖር ስላልቻሉ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

*ቃላት እና የሀረጎች ጥናት*

2፡1-11

**ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና፡፡ እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን፡፡ አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፥ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን? ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ፡፡እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ *ሥራው* ያስረክበዋል፤ በበጎ *ሥራ* በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል፡፡ ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ *ሥራ* ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና፡፡**

2፡1

| | |
|---|---|
| **ኒው አሜርካን ስታንዳር ባይብል** | **"የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"አንተ የምትፈረድ ሰው የሚፈረድብህ ነህ"** |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | **"በሌሎች ላይ ስትፈርድ፣ አንተ ማንም ብትሆን አንተም ከዝይህ ፍርድ አታመልጥም"** |
| **ቱደይስ እንግልዝ ቨርዥን** | **"አንተ ምንም ብትሆን ከፍርድ ልታመልጥ አትችልም፡፡ ምክንያቱም በሌሎች ላይፍረደሃልና"** |
| **ኢመቅ** | **"ምንም ሁንበሎሎች ላይ ከፈረድኽ ከፍርዱ ማምለጥ አትችልም"** |

የዚህ ቀጥተኛ ትርጓሜ "ሕጋዊ መሠረት የለው" ማለት ነው (ከ1፡20 ያነጻጽሩ)፡፡ ይህ ቃል በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ሀረግ በመጀመሪያ መምጣቱ ይህ ሀረግ በጣም አስፈልጊ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ቁጥር 1-16 እራሳቸውን ሕግን በመበቅ ለመጽደቅ በምሞክሩ ከአይሁዳዊያን እና ግብረገባዊያን ለመሆን ከሚሞክሩ ግሪካዊያን ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ሌሎችን በመኮነናቸውን በእራሳቸው ላይ ፍርድን አመጡ፡፡

2፡2 **"እናውቃለን"** ይህ ተውላጠ ስም ምናአልባትም አይሁዳዊያን ወይም ክርስቲያኖችን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ከቁጥር 2-4 ውስጥ በውሎስ እርሱ መንገድ በሆነው በጥያቄ እና መልስ መልክ እውነትን ገለጸላቸው፡፡ ይህ መንግድ በጳውሎስ ብቻ ሳይሆን በዕንባቆም፣ በሚልክያስ እና በመምህራን እንዲሁም በግሪክ ፈላስፎች (ሶቅራተስ እና ስቶክ) ጨምር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ "እናውቃለን" የሚለው ሀረግ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶ እናገኛለን (2፡2፣ 3፡19፣ 7፡14፣ 8፡ 22፣ 22)፡፡ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ላይ ታሳቢ የሚያደደረግው አድማጮቹ በምዕራፍ 1 ላይ እንደተገለጠው እንደ አሕዛብ ሳይሆን የተወሰነ እውቀት እንዳለቸው ነው፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ፍርድ"** *መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚኢህ እውነት ግልጽ ነው፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ ለዚይህ የሕይወት ስጦታ ለእግዚአብሔር እውቅናን ይሰጣሉ* (ቁጥር 5-9፣ *ማቴ* 25፤31-46፣ *ራዕ* 20፡11-15 )፡፡ *ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ስለዚህ ምክንያት በክርስቶስ ፊት የቆማሉ* (14፡10-12፣ 2ቆሮ 5፡10)፡፡

2፡3 *ኢ-አዎንታዊ ምላሽን የሚጠብቀው የጳውሎስ ጥያአዎቂ የዓረፍተ ነገር ቀመር*፡፡

▣ **"ይመስልሃልን"** *ተብሎ ወደ አማርኛ የተተረጎመው የግሪክ ግሥ ሎጊዞማይ ነው፡፡ ይህንንም ቃላ ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ተጠቅሞታል* (ሮሜ 2፡3፣ 26፣ 3፡28፣ 4፡3፣ 4፣ 5፣ ፣ 6፣ 8፣ 10፣ 11፣ 22፣ 23፣ 24፣ 6፡11፣ 8፡18፣ 36፣ 9፡8፣ 14፡14፣ *ገላ* 3፡6 *እና በ*1 *እና* 2 *ቆሮ ውስጥ አስር ጊዜ እንዲሁም በፊል ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሟል፡፡ ስለዚይህ በ*4፡3 *እና* 8፡18 *ላይ የተሰጠውን ማብራርያ ይመልከቱ*፡፡

▣ *"አንተ ሰው" ይህ በቁጥር* 1 *ላይ ከተገለጸው ምሳሌያዊ አነጋገር ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ በ*9፡20 *ላይ ይህ የሚያመለክተው አይሁዳዊያንን ነው*፡፡

2፡4 *ይህም በግሪክ ጥያቄ ያለበት ቁጥር ነው*፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት"** *ብዙ ጊዜ የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ምሕረት እና ትእግስት በትክክለኛው መንገድ አይረዱትም እንዲሁም ንሰሓ እንደ መግባት ፈንታ ይህንን እድል ኀጢአተ የሚያደርጉበት አጋጣሚ አድረገው ይወስዱታል*፡፡ (2ጴጥ 3፡9)

*ጳውሎስ ብሱ ጊዜ የእግዚአብሔርን ባሕርይ "ቸርነት" (የተትረፈረፈ) በማለት ይገልጠዋል* (9፡23፣ 11፡33፣ *ቆላ* 1፡27፣ *ኤፌ* 1፡7፣ 18፣ 2፡4፣ 3፡8፣16፣ *ፊል* 4፡19)፡፡

▣ **"ወደ ንስሐ እንዲመራህ"** *ንሰሓ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖር በእምነት ለሚሆን ቃል ኪዳን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው*፡፡ (*ማቴ* 3፡2፣ 4፡17፣ *ማር* 1፡15፣ 6፡12፣ *ሉቃ* 13፡3፣ 5፣ *የሐዋ* 2፡38፣ 3፡16፣ 19፣ 20፡21) *በእብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጉም የድርግት ለውጥን ሲያመለክት በግሪክ ግን የአመለካከት ለውጥን ያመለክታል፣ ንሰሓ እራስን ካማከል ሕይወት በእግዚአብሔር ወደሚመራ እና ከእግዚአብሔር ትዕዛዝን ወደሚቀበል ሕይወት ለመለወጥ መፈለግን ያመለክታል፡፡ ይህ ለራስ ቅድሚያ ከሚሰጥ እና የእራስ እስረኛ ከሆነ ሕይወት ለመራቅ የቀረበ ጥር ነው፡፡ ይህ አዲስ አመለካከት፣ አዲስ ንጽረተ ዓለም፣ አዲስ አለቃን በራስ ላይ የመሾም መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ንሰሓ በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈተሬ በኀጢአት ለወደቁ የአዳም ልጆች ሁሉ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው* (*ሕዝ* 18፡21፣ 23፣ 32 *እና* 2ጴጥ 3፡9)፡፡

2ቆሮ 7፡8-11 *ያለው ክፍል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዛት ከተጠቀሰው ንሰሓን ከሚያመለክተው የግሪክ ቃል ለዩ የሆነ አጠቃቀምን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡* (1) *ሉፔኦ ትርጓሜውም "ማዘን" ወይም "ሐዘን" ማለት ሲሆን በቁ* 8 (*ሁለት ጊዜ*)፣ *ቁ*.9 (*ሦስት ጊዜ*)፣ *ቁ*. 10 (*ሁለት ጊዜ*)፣ *ቁ*. 11፡(*አንድ ጊዜ*) *ይገኛል፡፡* (2) *ሜታሜለማይ ትርጓሜው "ጸጸት" ማለት ስሆን ይህም በቁ*. 8 (*ሁለት ጊዜ*) *እና ቁጥር* 9 *ላይ ይገኛል፡፡* (3) *ሜታኖያ ማለት "ንሰነ" ወይም "ሃሳብን መቀየር" ማለት ሲሆን ይህም በቁ*. 9 *እና* 10 *ላይ ይገኛል፡፡ እውነተኛ ንሰሓ ከእውነተኛ ካልሆነ ንሰሓ ጋር ተነጻጽሮ በማቴ* 27፡3 *እና ዕብ* 12፡16-17 *ላይ ቀርቧል*፡፡

*እውነተኛ ንሰሓ* (1) *ለአዲስ ኪዳን ቅድነ ሁኔታ ሆኖ በኢየሱስ ተሰብኳል* (*ማቴ* 4፡17፣ *ማር* 1፡15፣ *ሉቃ* 13፣ 3፣ 5፤ ፡(2) *በሐዋርያት ስብከት ውስጥ የእምነት መግለጫ ሆኖ ቀርቧል* (*የሐዋ* 3፡16፣ 19፣ 20፡21)፤ (3) *የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ስጦታ ሆኖም ቀርቧል* (*የሐዋ* 5፡31፣ 11፡18 *እና ጢሞ* 2፡25) *እንዲሁም* (4) *ከመጥፋት ጋር ተያይዞ ቀርቧል* (2ጴጥ 3፡ 9)፡፡ *ስለዚይህ ንሰሓ አማራጭ ያለው ጉዳይ አይደለም*፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ንሰሓ**

*ንሰሓ ከእምነተ ጋር የሁለቱም የብሉይ ኪዳንም* (*ናካም* 1*ነገ* 8፡47፣ *ሱዋ* 1*ነገ* 8፡48፣ *ሕዝ* 14፡6፣ 18፡30፣ *ኢዮ* 2፡12-13፣ ዘካ 1፡3-4) *እና የአዲስ ኪዳን መስፈርት ሆኖ ቀርቧል*፡፡

1. *መጥመቁ ዮሐንስ* (*ማቴ* 3፡2፣ *ማር* 1፡4፣ *ሉቃ* 3፡3፣ 8)
2. *ኢየሱስ* (*ማቴ* 3፡2፣ *ማር* 1፡15፣ 2፡17፣ *ሉቃ* 5፡32፣ 13፡3፣5፣ 15፡7፣ 17፡3)
3. *ጴጥሮስ* (*የሐዋ* 2፡38፣ 3፡19፣ 8፡22፣ 11፡18፣ 2ጴጥ 3፡9)
4. *ጳውሎስ* (*የሐዋ* 13፡24፣ 17፡30፣ 20፡21፣ 26፡20፣ *ሮሜ* 2፡4፣ 2ቆሮ 2፡9-10)

*ነገርግን ንሰሓ ማለት ምን ማለት ነው? ኀዘን ማለት ነውን? ወይስ ኀጢአት መስራት ማቆም? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህንን ሃሰብ በደንብ ለመረዳት የሚያገለግለን ክፍል በ*2ቆሮ 7፡8-11 *ያለው ሲሆን ይህም ሶስት እርስ በእርሳቸው የተገናኙ ነገር ግን የተለያዩ የግርክ ቃላትን በዚይህ ስፍራ በገልግሎት ላይ ውለዋል*፡፡

1. *"ኀዘን"* (*ሉፔ ቁ*. 8 (*ሁለት ጊዜ*)፣ 9 (*ሶስት ጊዜ*)፣ 10 (*ሁለት ጊዜ*)፣ *እና* 11፡፡ *ትርጓሜውም ማዘን ሲሆን ሥነ መለኮታዊ መሃል ሰፋርነት መንፈስ አለበት*፡፡

2. "ንስሓ" (ሜታኖያ ቁ. 9፣ 10):: "በኃላ" እና "አእምሮ" የሚል ትርጓሜ ባላቸው የግርክ ቃላት ጥምረት የተፈጠረ ቃል ነው:: የሚያመለክተውም አዲስ አእምሮን፣ አዲስ አስተሳሰብን እና ስለ ሕይወት እና ስለ እግዚአብሔር አዲስ አመለካከት ማደበርን ነው:: ይህ እውነተኛ ንስሓ ነው::

"መጸጸት" (ሜታሜሎሚ ቁጥር 8 (ሁለት ጊዜ እና 10):: ይህ ቃል "በኃላ" እና "ጥንቃቄ" የሚል ትርጓሜ ባላቸው የግሪክ ቃላት ጥምረት የመጣ ነው:: ይህ ቃል በማቴ 27:3 ለይሁዳ እንዲሁም በዕብ 12:16-17 ለሳኦል በጥቅም ላይ ውሏል:: የሚያመለክተውም ድርግቱ በሚያስከትለው ነገር ማዘንን እንጂ በድርግቱ ማዘንን አይደለም::

ንስሓ እና እምነት የቃል ኪዳን አስፈላጊ ድርግቶች ናቸው (ማር 1:15፣ የሐዋ 2:38፣ 41፣ 3:16፣ 19፣ 20፡ 21):: ንስሓ በእግዚአብሔር እንደሚሰጥ የሚያመለክቱ አንዳንድ የመጽሐፍ ክፍሎች አሉ (የሐዋ 5:31፣ 11:18፣ 2ጢሞ 2:25):: ነገር ግን አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ንስሓን እግዚአብሔር ለሰጠው ነጻ ድነት የሰው ልጆች ሚላሽ ቃል ኪዳናዊ ምላሽ የሚሰጡበት አስፈፊላግ ነገር እንደሆነ ያስረግጣሉ::

የዕብራይጡ እና የግሪኩ ቃል ሙሊ ፍች የቃሉን ሙሉ ትርጉም ለመረዳት አጋዥ ነው:: የዕብራይጡ የቃሉ ትርጓሜ "የድርግት አቅጣጫን መቀየርን" ሲያመለክት የግሪኩ የቃሉ ትርጓሜ "የአመለካከት ለውጥን" ያመለክታል:: ድነትን ያገኘው ሰው አዲስ አእምሮን እና ልብን ያገኛል:: አዲስ በሆነ መንገድ ማስብ እና መኖር ይጀምራል:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእርሱ ዋነኛ ጥያቄው "ይህ ለእኔ ምን ያደረገልኛል?" ሳይሆን "የእግዚአብሔር ፍቃድ ምንድ ነው?" ይሆል:: ንስሓ ከጥቂ ጊዜ በኃላ የሚጠፋ ስሜት ወይም ፈጽሞ ከኀጢአት በጻ መሆን ማለት ሳይሆን ከቅዱሱ ጋር የተጀመረ አዲስ ግንኙነት ነው:: ይህም ግንኙነት አማኞቹን በሂደት ወደ አንዱ ቅዱስ እየለወጣቸው ይሄዳል::

2:5-9 እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት (1) የወደቁት የሰው ልጆች  ክፋት እና (2) የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ፍርድ ይሆናል::

2:5 **"ክፋት"** እስራኤላዊያን በዘጸ 32:9፣ 33:3፣ 5፣ 34:9፣ ዘዳ 9:6፣ 13፣ 27 ላይ በዚህ መልክ ተገልጸዋል::

▣ **"ልብ"** በ1:24 ላይ የቀረበውን ልዩ ርዕስ ተመልከት::

▣ **"በቁጣ ቀን"** ይህ በብሉይ ኪዳን "የጌታ ቀን" ተብሎ ይጠራም (ኢዮኤል እና አሞጽን ተመልከቱ):: ይህ የፍርድ ቀን ወይም ለአማኖች የትንሣኤ ቀን ሃሰብ መሠረት ነው:: የሰው ልጆች እግዚአብሔር ለሰጣቸው ሕይወት ተጠያቂዎች ናቸው (ማቴ 25:31-46፣ ራዕ 20:11-15)::

ኀጢአተኞች እራሳቸው ("አንተ" እና "አንተ እራስህ") ጥፋታቸውን እንደሚያከማቹ ማስተዋል ተገቢ ነው:: በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ይህ የተጠራቀመ ቁጣን እውን እንደሆን እና ጥፋትን እንድፈጽም ይፈቅዳል::

ቁጣን እንደ ሌሎች ሰዋዊ ቃላት ሁሉ ለእግዚአብሔር ስውል የመለኮትን ድርግት ወይም ንግግር በሰውኛ አገላለጽ መቅረቡን አመለክታል:: እግዚአብሔር ዘላለማዊ፣ ቅዱስ እና መንፈስ ነው:: የሰው ልጅ ጊዜአዊ፣ ኀጢአተኛ እና ቁሳዊ ነው:: እግዚአብሔር ስሜታው ቁጣ የለውም:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ኀጢአጠኖችን እንደሚወድ እና ንስሓ እንዲገቡ እንደሚፈለግ ይገልጻል፤ ነገር ግን ይህ ማለት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን አመጽ ይደግፋል ማለት ግን አይደለም:: እግዚአብሔር አካለዊ ነው፤ ኀጠአትን በግለሰቦች ደረጃ ይወስደል እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ስለ ራሱ ኀጢአት ተጠያቂ ነው::

ስለ እግዚአብሔር ቁጣ አንድ ተጨማሪ ነገር አለ::  በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ በጊዜ ውስጥ (ጊዜን ማዕከል ያደረገ ነው 1:24፣26፣ 28) እና በጊዜ መጨረሻ (በመጨረሻው ዘመን 2:5-8):: የጌታ ቀን (የፍርድ ቀን) ወደ እስራኤል የተላኩት የብሉይ ኪዳን ነቢያት እስራኤላዊያን ለወደፊት ፍርድ ሳይሆን ባርኮት እንዲያገኛቸው ንስሓ ይገበ ዘንድ የሚያስጠነቅቁበትን ጊዜ ያመለክታል (ዘዳ 27-28):: የብሉ ኪዳን ነቢያት በዘመናቸው የሚገኙት ቀውሶች በማሳየት በመጨረሻው ዘመንም ይህ እንደሚሆን ይተነብዩ ነበር::

2:6 ይህ ከመዝ 62:12 የተወሰደ ክፍል ነው:: ይህ አለማቀፍ ተቀባይነት ያለው መርሆ ሆነ ሰዎች ሁሉ ለድርግታቸው ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያሳይ እና በእግዚአብሔር ፍትም የሚጠየቁበት መሆኑን የሚያመለክት ነው:: (እዮ 34:11፣ ምሳ 24:12፣ መክ 12:14፣ ኤር 17:10፣ 32:19፣ ማቴ 16:27፣ 25: 31-46፣ ሮሜ 2:6፣ 14:12፣1ቆሮ 3:8፣ ገላ 6:7-10፣ 1ጢሞ 4:14፣ 1ጴጥ 1:17፣ ራዕ 2:23፣ 20:12፣ 22:12):: አማኞችም ብሆኑ ስለኖሮአኗኗራቸው እና ክርስቶስን ስለማገልገላቸው ተጠያቂዎች ናቸው (2ቆር 5:10):: አማኞች ድነትን የሚያገኙት በሥራ አይደለም ነገር ግን ድነትን ያገኙት መልካም ሥራን እድሠሩ ግን ነው:: (ኤፌ 2:8-10 (በተለይም 2:14-26) ያዕቆብ እና 1ዮሐንስ)::

2:7 **"ለ . . ."** በቁጥረ 7 እና 8 ላይ በተገለጹት ሰዎች መካከል ንጽጽር አለ ("ነገር ግን ለ . . .

▣

አአመመቅ

"በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም
ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤"

| | |
|---|---|
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በጽናት በጎ ሥራ በመስራት ለምቀጥሉ ምስጋናን፣ ክብርን እና የማይጠፉ ሕይወተን ለሚፈልጉ የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል።** |
| **አየመመቅ** | **"በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናን፣ ከብርን እና የማይጠፋ ሕይወትን ለሚፈልጉ እርሱ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸዋል።** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"በመልካም ሥራ በመጽናት ምስጋናና ክብርን የማይጠፋ ሕይወትንም ለሚፈልጉ እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል።"** |
| **ኢመቅ** | **"ዘወትር መልካምን በማድረግ እውቅናን፣ ክብርን እና የማይጠፋ ሕይወትን ለሚፈልጉ ዘላለማዊ ሕይወት አለላቸው።"** |

ይህ የሚያመለክተው እንደ ቆርናሌዎስ ያሉትን ሰዎች ነው (የሐዋ 10፡34-35)። ይህ ምንባብ ምንአልባት በሥራ መጽደቅን የሚያስተምር ልመስል ይችላል ነገር ግን እንዲህ ያለ አመለካከት ከሮሜ መጽሐፍ ዋነኛ ጭብጥ ጋር የሚቃረን ነው። ከቁጥር 1-16 ወይም 1-11 ያለው አንድ አንቀጽ እንደሆነ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። የዚህ ምንባብ ስነ-መለኮታዊ ዋና ሀሳቡ እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጆች ተጠያቂ አይደለም (ቁ. 11) እና ሁሉም ኀጢአተን ሠርተዋል (ቁ.12)። የሰው ልጆች በተቀበሉት ብርሃን መጠን ከተመላለሱ (አጠቃላይ መገለጥ ለአሕዛብ እና ልዩ መገለጥ ለአይሁዳዊያን) ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ይኖራቸዋል። ነገር ግን ቁጥር 3፡9-1፣ 33 የሚያሳየው ማንም ይህን አለማድረጉን ወይህ ማድረግ አለመቻላቸውን ነው!

የአማኙ ወደ እግዚአብሔራዊ አኗኗር መለወጥ የእርሱን የእምነት ምላሽ የሚያረጋገጥ እና የሚአስረግጥ ነው። የተለወጠ ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ መሆንን ማረጋጋጭ ነው ( ቁትር 10፣ 13፣ ማቴ 7፣ ኤፊፌ 2፡8-10፣ ያዕ 2፡ 14-26 እና 1ዮሐ)። በ8፡25 ላይ ያለውን የመጽናት አስፈላጊነት የሚለውን ልዩ ርዕስን ተመልከት።

▣ **"ዘላለማዊ ሕይወት"** ይህ የዮሐንስ ጽሑፎች መለያ ባሕርይ ሲሆን በተመሳሳይ ወንጌላት ውስጥ በስፋት ተሰራጭቶ ይገኛል። ጳውሎስ ይህንን ሀረግ ከዳን 12፡2 ላይ ስለ መጭው ዘመን ሕይወት፣ እግዚአብሔርን የማምለክ ሕይወት እና የትንሣኤ ሕይወትን ከሚያመለክተው ክፍል የተወሰደው ይመስላል (ቲቶ 1፡2፣ 3፡7)። በመጀመርያ ይህንኑ ሀረግ በገላ 6፡8 ላይ ተጠቅሞታል። ይህ ሀረግ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ በአስተምህሮው ክፍል ውስጥ በብዛት የተገለጠ ነው (2፡7፣ 5፡21፣ 6፡22፣ 23)። እንዲሁም የመጋቢያን መልዕክቶ ተብለው በሚታወቁት የጳውሎስ መልዕክቶች ውስት በብዛት ይገኛል (1ጢሞ 1፡16፣ ቲቶ 1፡2፣ 3፡7)።

2፡8

| | |
|---|---|
| **ኒው አሜርካን ስታንዳር ባይብል** | **"በአድመኞች"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳረርድ ቨርዥን** | **"የራሳቸውን ጥቅም በሚፈልጉ"** |
| | **"ሌሎች ራስ ወዳዶች የሆኑ"** |
| **ኒው ኢመቅ ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"ከቅናት የተነሳ"** |

ይህ ቃል በመጀመሪያ " በቅጥር መሥራትን" ያመለክታል (ጦቢያ 2፡11) Louw and Nida, Greek-English Lexicon, vol. 2, p. 104, ሁለት የቃሉን ትርጓሜዎች ዘርዝሯል

1. "ራስወዳድ መሻት" በሮሜ 2፡8ን መሠረት "ከለሎች የተሻሉ ሆነው ለመታየት መፈለግን" ለዚይህ አውድ ተስማሚ ይሆናል።
2. "ጥል" በፊል 1፡17 መሠረት "ተቀናቃኝ" የሚለው አቻ ትርጉሙ ነው (2ቆሮ 12፡20፣ ገላ 5፡20፣ ፊል 2፡3፣ ያዕ 3፡14፣ 16)።

▣ **"ለእውነት ለማይታዘዙና"** "እውነት" (አሌቲያ) የሚለው ቃል በጥቅም ላይ የዋለው በዕብራይስጡ (እሜት) እውነተኛ እና የሚታመን በሚለው ትርጓሜው ነው። በዚህም አውድ የቃሉ ትርጓሜ አእምሮአዊ ሳይሆን ሞራላዊ አንድምመታ አለው። በ1፡18 ላይ እውነት በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

2፡9 **"ሰው ነፍስ ሁሉ"** ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ላይ "ፓሳ" የሚለው የግሪክ ቃል ተጠቅሟል፤ ትርጓሜውም "ሁሉም" ሲሆን ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ መዕራፎች ውስጥ ይህንን ቃል "መጥፎ ዜናን" (የሰው ልጆች መጥፋትንን እና የእግዚአብሔርን የማያዳላ ፍርድ) እንዲሁም "መልካም ዜና" (የእግዚአብሔርን ነጻ ስጦታ እና በንስኀ ለሚመለሱ እና ለሚያምኑ ሁሉ የሚሆነውን ፍጹም የኀጢአት ይቅርታ) ለማመልከት ተጠቅሟል።

2፡9-10 **"በመጀመሪያ ለአይሁዳዊያን"** ይህ በድጋሚ የቀረበው ለአጽኖት ነው። አይሁዳዊይን ይህንን እድል በመጀመሪያ ያገኙት የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ስለተሰጣቸው ነው (1፡16፣ ማቴ 10፡6፣ 15፡2፣ ዮሐ 4፡22፣ የሐዋ 3፡26፣ 13፡46) ነገር ግን እነርሱ በፍርድም የመጀመሪያዎቹ ናቸው (9-11) ምክንያቱም መገለጡን ተብለዋልና (9፡4-5)።

2፡11

**ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል**

| | |
|---|---|
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "በእግዚአብሔር ዘንድ አድሎ የለምና።" |
| ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን | "እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።" |
| ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን | "እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ላይ በአንድ መስፈረት ይፈርዳል" |
| ኒው ኢመቅ | "በእግዚአብሔር ዘንድ ማዳላት የለም" |

የዚህ ቃል ቀጥተኛ ትርጓሜውም "ፊትን ቀና ማድረግ" ማለት ነው። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ባለ የፍርድ አካሄድ ውስጥ የሚጠቀሙበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው (ዘሌ 19፡15፣ ዘዳ 10፡17፣ 2ዜና 19፡7፣ የሐዋ 10፡34፣ ገላ 2፡6፣ ኤፌ 6፡ 9፣ ቆላ 3፡25፣ 1ጴጥ 1፡17)። ዳኛው ፍርድን በምሰጥበት ሰዓት ፍርድን የሚቀበለውን ሰውዬ ፍት ከተመለከተ ዳኛው ለሰውዬ አዳልቷል ማለት ይቻላል። ስለዚህም ዳኘው ከፊቱ የተቀመጠው ሰው ፊት ቀና ማድረግ የለበትም።

**ልዩ ርዕስ፡ ዘረኝነት**

I. *መግቢያ*

*ሀ.* ይህ የወደቀው የሰው ልጅ በማህበረሱ ውስጥ ያለው አለማቀፍ መገለጫ ነው። ይህ የሰው ልጆች በሌሎች ሰዎች ጫንቃ ላይ እራስን የመደገፍ የእኔነት ስሜት ነው። ዘረኝነት በተለያዩ መንገዶች የዝይህ ዘምን መገለጫ ስሆን ሀገራዊነት (ብሔርተኛንት) ግን ይጥንታዊነት መገለጫ ነው።

ለ. አገራዊነት የተጀመረው በባቤል (በዘፍ 11) ሲሆን፤ ይህም በመጀመሪያ ከኖህ ሦስት ልጆች ጋር የተቀራኘ ነው (ዘፍ 10)። ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ የሆነው ነገር የሰው ልጆች ሁሉ ከአንድ ዘር መሆናቸው ነው (ዘፍ 1-3፣ የሐዋ 17፡24-26)።

ሐ. ዘረኝነት አንዱ ኢ-ፍትሐዊነት ነው። ሌሎቹ (1) የትምህርት ልቅነት (2) የማህበረሰባዊ ኢኮኖም ልቅነት (3) እራስን የማጽደቅ ኃይማኖታዊ ወግ አጥባቂነት እና (4) ጽንፈኛ ፖለቲካ ደጋፍነት ናቸው።

II. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች*

*ሀ.* ብሉይ ኪዳን

1. ዘፍ 1፡27- የሰው ልጆችን ልዩ የሚያደርጋቸው የሰው ልጆች ሁሉ፣ ወንድም ሴትም በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ መፈጠራቸው ነው። እንዲሁም ይህ የእያንዳንዱን አስፈላጊነት እና ክብር ያሳያል (ዮሐ 3፡16)
2. ዘፍ 1፡11-25- ይህ ክፍል ". . . በራሳቸው አምአል" የሚል ሀረግን በውስጡ አስር ጊዜ ይዟል። ይህ የዘር ክፍፍልን እንደሚያመለክት ለእማኘነት ለዘመናት ሰዎች ስጠቀሙበት ቆይተዋል። ነገር ግን ከአውዱ እንደምንረዳው ይህ የሚያመለክተው እንስሳትን እና እጽዋትን እንጅ የሰው ልጆችን አይደለም።
3. ዘፍ 9፡18-27 ይህ ለዘመናት የአንድን ዘር ከሌሎች መብለጥን ለማመለክት ስጠቀሙበት ነበር። አንድ ማስተዋል ያለብን ነገር እግዚአብሔር ከነአን አልረገመውም። ኖህ፣ አያቱ ከስካሩ በነቃ ጊዜ ነው የረገመው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እርግማን ስያረጋግጥ በዬትኛው ስፍራ እንመለከትም። ይህ እውነት እንኳ ብሆን ይህ ጥቁሮችን ሊያካትት አይችልም። ከነአን ፍለስጤምን እና ግብጽን ውስጥ የሞኖሩ ሕዝቦች አባት ነው። እነዚይህ ሰዎች ደግሞ ትቁሮች እንዳልሆኑ በግድግዳዎች ላይ ተገኙ የጥንት ስነ ጥበባዊ ቅርጾች ያመለክታሉ።
4. ኢያ 9፡23 ይህ አንድ ዘር ሌላውን እንደሚያገለግል ያመለክታል ተብሎ ይተታሰብ ነበር። ነገር ግን ገቦናዊያን እንደ አዬኢሁዳዊያን ሁሉ አንድ ዝርያ ናቸው
5. ዕዝ 9-10 እና ነህ 13- ይህ ብዙ ጊዜ ከዘረኝት ጋር ተያይዞ በአገልገሎት ላይ ውሏል። ነገር ግን ጋብቻ የተኮነነው በዘር ምክንያት ሳይሆን በኃይማኖት ምክንያት ነበር።

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ወንጌላት

   *ሀ.* ኢየሱስ የአይሁዳዊያን እና የሰማሪያዊያንን ጥላቻ ብዙ ጊዜ በምሳሌነት ተጠቅሞታል፤ ይህም የዘር ጥላቻ ትክክል እንዳልሆነ ያሳየል።

   (1) የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ (ሉቃ 10፡25-37)
   (2) በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያለችው ሴትዮ (ዮሐ 4)
   (3) አመስጋኙ ለምጻም (ሉቃ 17፡7-19)

   ለ. ለሰዎች ሁሉ የሆነ ወንጌል

   (1) ዮሐ 3፡16
   (2) ሉቃ 24፡46-47
   (3) ዕብ 2፡9
   (4) ራዕ 14፡6

   ሐ. የእግዚአብሔር መንግስት ሁሉን ታቅፋለች

   (1) ሉቃ 13፡29

(2) ራዕ 5

2. የሐዋርያት ሥራ
   ሀ. የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 የእግአብሔርን ዓለማቀፋዊ ፍቅር እና የወንጌልን ዓለማቀፋው ምልዕክትነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው።
   ለ. ጴጥሮስ በሐዋርያት 11 ላይ ስላደረገው ነገር ጥቃት ስደርስበት እንመለከታለን፤ ይህ ችግርም በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ ተገለለጠው የሐዋርያት ጉባኤ እስከ ተካሄደበት ጊዜ ድረስ አልተፈታም ነበር። በመጀመሪያው ምዕተ አመት በነበሩ አይሁዳዊያን እና አሕዛቦች መካከል የነበረው ጠብ የከረረ ነበር።
3. ጳውሎስ
   (ሀ) በክርስቶስ ምንም አይነት ግድግዳ የለም
      (1) ገላ 3፡26-29
      (2) ኤፌ 2፡11-22
      (3) ቆላ 3፡11
   (ለ) እግዚአብሔር አያደላም
      (1) ሮሜ 2፡11
      (2) ኤፌ 6፡9
4. ጴጥሮስ እና ያዕቆብ
   ሀ. እግዚአብሔር ለማንም አያደለም 1ጴጥ 1፡17
   ለ. እግዚአብሔር ለማንም ስለማያደለ ፄትኛውም ሕዝብ ቢሆን የእርሱ ሕዝብ ለመሆን ተገባው አይደለም ያዕ 2፡1
5. ዮሐንስ
   ሀ. በ1ዮሐ 4፡20 ላይ የአማኞች ጠንካራ ኃላፍነት ተገለጠበት አንዱ ስፍራ ነው።

III. ማጠቃለያ

ሀ. ዘረኝነት ወይም ማንኛውም አይነት ኢ-ፍትሐዊነት በእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ ፈጽሞ የተገባ አይደለም።

ለ. ይህ ችግር ለክርስቲያኖች የክርስቶስን ፍቅር የሚመስል ፍቅር ለማሳየት፣ ይቅርታ እና የጠፋውን ዓለም ለመረዳት እድል ኢሰጣቸዋል። በእንድህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ ለመስራት ክርስቲያን አሻፈረኝ ስል፣ ይህ የሚያሳየው አለመብሰለን እና ክፉው የአማኙን እምነት፣ እድገት እና ጽናት በተገቢው መጠን እንደያድግ እንዲያደረግ እድል መስጠት ነው። እንዲሁም ወደ ክርስቶስ ለሚመጡ የጠፉ ሰዎች እንቅፋት ይሆናል።

ሐ. ምን ላድርግ? (ይህ ክፍል የተወሰደው የክርስቲያኖች የሕይወት ተልዕኮ ከተበለ በራር ወረቀት ነው። ርዕሱም "የዘር ግንኙነት" የሚል ነው።

"በግለሰብ ደረጃ"

★ በዘርግ ጉዳይ ለሚነሱ ችግሮች መፍትሔ ለመሰጠት የራስህን ኃላፊነት ተቀበል።

★ ከሌሎች ብሔሮች ጋር አብረህ በመጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት እንዲሁም ሕብረት በማድረግ የዘር መድሎን ከውስጥህ ለማጥፋት ጥረት አድርግ።

★ የብሔር አክራርዎች ባሉበት ሥፍራ ስለ ዘረኝነት እና ብሔርኝነት ያለህን አቋም ግለጽ።

"በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ"

★ ስለ ሌሎች ብሔሮች ቤተሰቡ በሚኖረው አመለካከት ላይ የቤተሰብ ድርሻ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

★ ወላጆች እና ልጆች ከቤት ውጭ ስለ ብሔር የሚሰሙትን ነገር ለማስቀረት እና ክርስቲያናዊ አመለካከትን ለማዳበር ጣር።

★ ወላጆች ከሌሎች ብሔረሶች ጋር ባላቸው ግንኙት ክርስቲያናዊ ምሳሌ ለመሆን በጥንቃቄ መኖር ይጠበቅባቸዋል።

"በቤተክርስቲያን"

★ ስለ ብሔር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን በመስበክ እና በማስተማር አማኙን ማሕበረሰብ በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ምሳሌያዊ ሕይወት እንድኖር ማነሳሳት ይቻላል።

★ በአዲስ ኪዳን ውስት ይገኙ የነበሩ ቤተ ክርስቲያኖች የብሔር ልዩነት እንዳላገዳቸው ሁሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ማናቸውም የአምላኮ፣ የሕብረት እና አገልግሎቶች ለሁሉም ሰዎች ክፍት መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል። (ኤፌ 2፡11-22፣ ገላ 3፡26-29)

"በዕለት ተዕለት ሕይወት"

★ በሥራ ስፍራ ማናቸውንም የብሔር መድሎዎችን ለማሸነፍ በሚደረግ ጥረት ውስጥ አጋዥ ሁን

- ★ በማሕበረሱ ውስጥ የሰዎችን እኩልነት እና እኩል እድል እንዲያገኙ በሚሠወሩ ድርጅቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድረግ፣ ነገር ግን ሰዎችን ሳይሆን የብሔር መድሎ ግን ችግሩ በመሆኑ ዘወትር ትኩረትህ ይህ ብቻ ይሁን። ዓላማውም ቅምን እና ጥላቻን ለመፍጠር ሳይሆን ግንዛቤን ለመፍጠር ነው።
- ★ አስፈላጊ መስሎ ከታየህ ልዩ ኮሚቴን በማቋቋም ማሕበረሰቡን ለማስተማር የሚያስችል የግንኙነት መንገድን ዘረጋ
- ★ የብሔር ፍትሓዊነትን የሚደግፉ ሕግጋት ድንጋጌን ደግፍ በተቃራንው ሰዎች ለራሳቸው ፖለቲካዊ ጥቅም የብሔር መድሎን የሚጠቀሙ ሰዎችን ተቃወም።
- ★ የሀገርቱን ሕግጋት ያለምንም ማዳለት የሚያስፈጽሙ ሰዎችን ፈልግ
- ★ ከአመጽ ራቅ እና ለሕግ ተገዥ ሁን፤ እንደ ክርስቲያን ዜጋ ሕጋዊ የሆነው መዋቅር ለብሔርተኞች መጠቀሚያ እንዳይሆን የሚቻልህን ያህል አድርግ፡፤
- ★ በእየንዳንዱ ግለሰባዊ ግንኙነት ውስጥ የክርስቶስን መንፈስ እና አእምሮ ምሳሌ አድርግ

2:12-16

***ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና። ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። ይህም ግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል።***

2:12 **“*ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ*”** እግዚአብሔር ምንም እንኳ ሰዎች ብሉይ ኪዳንን ወይም ወንጌልን ለመስማት የታደሉ ባይሆንም ተጠያቂ ግን ያደርጋቸዋል። ሰዎች ሁሉ ከተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁት ነገር አላቸው። (1፡19-20 ፣ መዝ 19፡1-6) እንዲሁም በውስጣው ግብረገባው ስለ እግዚአብሔር ሕልውና የሚገነዘቡት ነገር አላቸው። (2፡14-15) የሚያስገርመው ነገር ሰዎች ሁሉ በፍቃዳቸው የተቀበሉትን ብርሃን ተላልፈው ተገኝተዋል (1፡21-23፣ 3፡9፣ 19፣ 23፣ 11፡32፣ ገላ 3፡22)።

▣ **“ሕግ”** በሮሜ ውስጥ ጳውሎስ “ሕግ” የሚለው ቃል በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞታል (1) የሮም ሕግ (2) የሙሴ ሕግ ወይም (3) የሰው ልጆች የማህበረሰብ ሕግ ሀሳብ። ጳውሎስ በዝይህ ስፍራ ላይ ዬትኛውን ሕግ ለማለት አንደፈለገ አውዱ ግልጽ ያደረጋል። ይህ አውድ ግልጽ እንደሚያደረገው የሰው ልጆች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ የሚያውቁት ነገር አላቸው፤ ይህም በልባቸው ውስጥ ባለ ተፈጥሮአዊ መገለጥ አማካኝነት ነው (ቁጥር 15)።

2:13 **“በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።”** “የሚሰሙት” የሚለው ቃል በሙሴ ሕግ ተማርዎች ዘንድ ልዩ ትርጉም ያለው ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሓፍት ምንም እንኳ በኮኔ ግሪክ መጽሐፍቶቻቸውን የጻፉ ብሆንም በአስተሳሰባቸው ግን ዕብራዊያን እንደነበሩ ማስታወሱ ተገቢ ነው። ስለዚይህ የዚህ ቃል ጥናት ልጀምር ሚገባው ከሰባ ሊቃውንት እንጂ ከግሪክ ቃል መፍቻ መሆን የለበትም።

▣ **“ጽድቅ” ወይም “መጽደቅ”** የሚለው ቃል በጳውሎስ ሥነ-መለኮት ውስጥ ወሳኝ ቃል ነው (3፡4፣ 20፣ 24፣ 26፣ 30፣ 4፡2፣ 5፣ 5፡1፣ 9፣ 6፡7፣ 8፡30፣ 33)። “ጻድቅ”፣ “ጽድቅ” የተባሉ ቃላት ሥረወ ግንዳቸው ዲያኪዮስ የተሰኘ የግሪክ ቃል ነው። በ1፡17 ላይ ያለውን “ጽድቅ” የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ። በዕብራይስጥ ጻድቅ የሚለው ቃል ነገሮችን ለመለካት የሚያገለግለውን ከ15-20 ጫማ ርዝማኔ ያለውን ልምጭ የሚያመለክት ነው። ከጊዜ በኃላም በምሳሌነት የእግዚአብሔር የፍርድ መለኪያ ሆኖ ማገልገል ጀመረ። የሚሰጠን ጽድቅ ጻድቅ ሆነን እንድንኖር ልያደርገን ይገባል። እግዚአብሔር ኀጢአትን ይቅር ይላል እንዲሁም ኀጢአተኞችን ይለውጣል። የጳውሎስ የቃሉ አጠቃቀም ሕጋዊ እና ሥነ-ምግባራዊም ነው። አዲስ ኪዳን ለሰው ልጆች ሕጋዊ መሠረት ይሰጣቸዋል ነገር ግን እግዚአብሔራዊ ሕይወትን ግን ከእነርሱ ይጠብቃል። ነጻ ነው ግን በጣም ውድ ነው።

▣ **“ነገር ግን ሕግን የሚያደረጉ”** እግዚአብሔርን ማወቅ አዲስ መታዘዝ ሕይወት እንዲኖረን ይጠብቃል (ዘለ 18፡5፣ ማቴ 7፡24-27፣ ሉ 8፡21፣ 11፡28፣ ዮሐ 13፡17፣ ያዕ 1፡22-25፣ 2፡14-18)። በተለያየ መንገድ ይህ ሀሳብ ሽማ የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ላይ ተንጸባርቆ ይገኛል፤ ትርጓሜውም መስማት ማለት ማድረግ ማለት ነው (ዘዳ 5፡1፣ 6፡4፣ 9፡1፣20፡3፣ 27፡9-10)።

2:14

| | |
|---|---|
| ኒው አሜርካን ስታንዳርብ ባይብል | **"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ በደመነፍስ የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤"** |
| ኒው ከንግ ጀምስ ቨርዥን | **"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው በሕግ ያለውን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ ምንም እንኳ ሕግ ባይኖራቸው ለራሳቸው ግንሕግ ናቸው፤"** |
| ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ባይብል | **"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ በደመነፍስ በሕግን ያለውን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤"** |
| ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን | **"አሕዛብ ሕግ የላቸው ነገር ግን በገዛ ፍቃዳቸው ግን ሕጉ የሚያዘውን ነገር ኢፈጽማሉ፣ በእርግጥ ሕግ የላቸው ነገር ግን ለራሳቸኢ ሕግ ናቸው ማለት ይቻላል።** |

በዓለማችን ያሉ ባሕሎች ሁሉ በውስጣቸው ግብረገባዊ ሕግ አላቸው። ላለቸው ብርሃን ተጠያቂዎችን ናቸው (1ቆሮ 9፡ 21) ይህ ቁጥር በባሕላቸው *መሠረት* ከኖሩ ከእግዚአብሔር *ጋር* ትክክለኛ ግንኙነት ይኖራቸው ማለት ግን አይደለም፣ ነገር ግን ይህ የሚያሳየው በውስጠቸው ላለው ስለ እግዚአብሔር ስላላቸው እውቀት ተጠያቂዎች መሆናቸውን ነው።

2:15 **"እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ *ሥራ ያሳያሉ*።"** በውስጣቸው የሚጮህ ድምጽ አለ፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ልታመን የሚገባው። ውድቀት በእኛ ሕሊና ላይ ተጽእና አምጥቷል። ነገር ግን ተፈጥሮ (1፡18-20) እና ይህ የውስጥ፣ ግብረገባዊ ሕግ (2፡14-15) የሰው ልጆች ስለ እግዚአብሔር ያለቸው እውቀት ነው። ሕሊና ተብሎ ለተተረጎመው የግሪክ ቃል በዕብራይስጥ አቻ ትርጓሜ የለው። የውስጥ ግብረገባዊ ትክክለኛ እና ስሕተትን መለያ ሆነው የግሪክ ሀሳብ በስቶክ ፈላስፋዎች ዘንድ የሚነገር ነገር ነው። ጳውሎስ የእነዚህ ፈላስፋዎች እውቀት ያውቅ ነበር (እንዲያውም በሐዋ 17፡28 ላይ የከሌንተስን፣ በ1ቆሮ 15፡33 ላይ ሜናንድረን እንዲሁም በቲቶ 1፡12 ላይ የኤፈሜኒድስን ጠቅሷል) በቱርሳስ ካገኘው ትምህርት በመውሰድ ተገልግሎበታል። የጳውሎስ የትውልድ ሀገር በፍልስፍና ትምህርት በጣም የታወቁ ነበር።

2:16 **"በፍርድ ቀን"** በ2፡5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

▣ **"በእኔ ወንጌል"** በዝይህ አውድ *መሠረት* ጳውሎስ ስሰብክ የነበረው በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን መገለጥ ነው። "ለእኔ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ ስለ ተሰጠውን የወንጌል አደራ ጳውሎስ የነበረውን መረዳት ነው 916፡25፣ 1ቆሮ 15፡1፣ ገላ 1፡11፣ 1ጢሞ 1፡11፣ 2ጢሞ 2፡8)። ይህ ወንጌል ለእርሱ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን እርሱ የአሕዛብ ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን በግርኮ ሮማን ግዛት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የማሰራጩት ግዴታ እንዳለበት ለማሳየት ነው።

▣ **"በሰዎች የተደበቀውን ነገር እግዚአብሔር ይፈርዳል"** እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ልብ ያውቃል (1ሳሙ 2፡7፣ 16፡7፣ 1ነገ 8፡39፣ 1ዜና 28፡9፣ 2ዜና 6፡30፣ *መዝ* 7፡9፣ 44፡21፣ 139፡1-6፣ *መዝ* 15፡11፣ 21፡ 2፣ ኤር 11፡20፣ 17< 10፣ 20፡12፣ *ሉቃ* 15፡16፣ *ሐዋ* 1፡24፤ 15፡8፣ *ሮሜ* 8፡27፣ *ራዕ* 2፡23)። እግዚአብሔር አብ በልጁ አማካኝነት የሰው ልጆችን መነሻ ምክንያት እና ድርግት ይመዝናል (*ማቴ* 25፡31-46፣ *ራዕ* 20፡11-15)።

▣ **"በክርስቶስ ኢየሱስ"** ኢየሱስ ወደዚይህች ምድር የመጣው ፈራጅ ለመሆን አይደለም (ዮሐ 3፡17-21)። እርሱ የመጣው እግዚአብሔር አብን ለመግለጥ፣ የሚተክ ሞት ለመሞት እና ለአማኞች ምሳሌያዊ ሕይወትን ለማሳየት ነው። ሰዎች ኢየሱስ ሊቀበሉት ባልወደዱ መጠን በራሳቸው ላይ ይፈርዳሉ።
ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ በፍድር ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር አብን እንደሚወክል የስተምራል (ዮሐ 5፡22፣ የሐዋ 10፡42፣ 17፡31፣ 1ጢሞ 4፡1)። ኢየሱስ ፈራጅነት እና አዳኝነት መካከል ያለው የሀሳብ ውጥረት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በግልጽ ይታያል (3፡17-21 9፡39)።

አአመመቅ2:17-24
**አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ፥ ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ፤ በሕግም የእውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ፥ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር እንደ ሆንህ በራስህ ብትታመን፤ እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።**

▣ **"በእግዚአብሔርም ብትመካ፥"** አብዛኛዎችዩ አይሁዳዊያን የሚመኩት (1) በዘር ሀረጋቸው እና (2) በእግዚአብሔር ፍት ተቀባይነት ለማግኘት የሙሴን ሕግ በመጠበቅ ብቃታቸው ነው። ነገር ግን ይህ እራስን የማጽደቅ ሕግ አጥባቂነታቸው እነርሱን ከእግዚአብሔር ለያቸው (ማቴ 5፡20፣ ገላ 3)። ምን የሚያስገርም ነገር ነው!

ጳውሎስ መመካት የሚለውን ሀሳብ በ1ቆሮንቶስ ውስጥ አሳድጎታል። ጳውሎስ ልቅ የሆኑ እስራኤላዊያን እና ግሪካዊያን ጠብባን ገጥመውታል። ዋናው ሀሳብ በእግዚአብሔር ፊት ማንኛው ሥጋ ለባሽ ሁሉ በእግዚአብሔር ፍት ክብር በራሱ አያገኝም (ኤፌ 2:8-9)።

**ልዩ መልዕክት፡ መመካት**
ይህ ቃል በጳውሎስ ሰላሰ አምስት ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በሌሎች አዲስ ኪዳን መጽሐፍት ግን ሁለት ጊዜ አገልግሎት ላይ ውሎ ይገኛል። ይህ ቃል በብዛት አገልግሎት ላይ የዋለው በ1 እና 2ኛ ቆሮንቶስ መልዕክቶች ውስጥ ነው።
ከመመካት ጋር የተቆራኙ ሁለት እውነቶችን እናገኛለን፦
- ★ ሰጋለባሽ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አይመካ (1ቆሮ 1:29፣ ኤፌ 2:9)
- ★ አማኞች በጌታቸው ልመኩ ይገባል (1ቆሮ 1:31፣ 2ቆሮ 10:17 ይህ ቃል ከኤር 9:23-24 የተጠቀሰው)

ስለዚይህ ትክክለኛ እና ትክክለኛ ያልሆነ መመካት አለ
1. ትክክለኛው መመካት
   ሀ. በክብር ተስፋ (ሮሜ 4:2)
   ለ. በክርስቶስ ኢየሱስ በእግዚአብሔር (ሮሜ 5:11)
   ሐ. በኢየሱስ መስቀል ይህ ማለት የጳውሎስ ዋና ሀሳብ ነው 1ቆሮ 1:17-18፣ ገላ 6:14)
   መ. ጳውሎስ በክርስቶስ መስቀልይመካ ነበር
      1) ከለምንም ድጎማ መገልገሉ (1ቆሮ 9:15፣ 16፣ 2ቆሮ 10:12)
      2) ከክርስቶስ ባገኘው ስልጣን (2ቆሮ 10:8፣ 12)
      3) በሌሎች ሰዎች ሥራ አለመመካት ( 2ቆሮ 10:15)
      4) በዘር ሀረጉ (2ቆሮ 11:17፣ 12:1፣ 5፣ 6)
      5) በቤተ ክርስቲያኑ
         ሀ. ቆሮንቶስ (2ቆሮ 7:4፣ 14፣ 8:24፣ 9:2፣ 11:10
         ለ. ተሰሎንቄ (2ተሰለ 1:4)
      6) በእግዚአብሔር ላይ መታመን እና መውጣት (2ቆሮ 1:12)
2. አለመመካት
   ሀ. ከአይሁድ ዘር ጋር ባለው ግንኙነት (ሮሜ 2:17፣ 23፣ 3:27፣ ገላ 6:13)
   ለ. አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይመኩ ነበር
      1) በሰው (1ቆሮ 3:21)
      2) በጥበብ (1ቆሮ 4:7)
      3) በነጻነት (1ቆሮ 5:6)
   ሐ. በቆሮንቶስ ባለችው ቤተ ክርስቲያን የነበሩት የስህተት አስተማርዎች ይመኩ ነበር (2ቆሮ 11:2)።

2:18 "መረጋገጥ" በሚያስከትለው ስለ ፈተና የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ተመለክቱ።

**ልዩ ርዕስ፡ "ፈተና" የግሪኩ ቃል እና ተያያዥ ሀሳቦቹ**

አንድን ሰው ለተወሰነ ዓለማ መፈተን የሚለውን ትርጉም ያዘሉ ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ\
1. ዶከማዞ
   ይህ ቃል የአንድ ነገር ትክክለኝነት በእሳት መፈተንን የሚያመለክት ነው። እሳት እውነተኛ ብረትን ከዝገቱ ያጠራዋል። ይህ ቁሳዊ ሂደት በእግዚአብሔር እና ሌሎች ሰዎች በመፈተን ውስጥ ያለውን ነገር ለማሳየት እንደ ምሳሌያዊ አነጋገር ሆኖ ያገለግላል። ይህ ቃል በአገልግሎት ላይ የዋለው በአዎንታዊ መልኩ ስሆን አላማው ተቀባይነትን ማግኘት ነው።
   ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፈተና ተብሎ ተተርጉሟል
   ሀ. በሬ ሉቃ 14:19
   ለ. ለሰዎች 1ቆሮ 11:28
   ሐ. እምነታችን ያዕ 1:3
   መ. ለእግዚአብሔር ዕብ 3:9
   የዚህ ፈተና ውጤት አውንታዊ እንደሚሆን ታሳብ ያደርጋል (ሮሜ 1:28፣ 14:22፣ 16:10፣ 2ቆሮ 10:18፣ 13:3፣ ፊል 2:27፣ 1ጴጥ 1:7)። ስለዚህም ይህ ቃል የሚያስተላልፈው መልዕክት አንድ ሰው ተመዝኖ ታየ መሆኑን ነው
   ሀ. የተገባው

ለ. መልካም
ሐ. ታማኝ
መ. ጠቃም
ሠ. የሚከበር
2. ፔኢራዞ
ይህ ቃል ስህተትን ወይም አንድ ነገር ብቁ እንዳልሆነ ማሳያት አላማን  መሠረት የሚደረግ መመዘኛን የሚያመለክት ነው። በዙ ጊዜ ይህ ቃል ከኢየሱስ ክርስቶስ የበረሃ ፈተና ጋር ይቆራኛል።
ሀ. ኢየሱስን ለማጥመድ የተደረገውን ሙከራ ያሳያል (ማቴ 4፡1፣ 16፡1፣ 19፡3፣ 22፡18፣35፣ ማር 1፡13፣ ሉቃ 4፡2፣ 10፡25፣ ዕብ 2፡18)
ለ. ይህ ቃል ለሴጣን መጠርያ ስሙ ሆኖ አገለግሏል ማቴ 4፡3፣ 1ተሰለ 3፡5
ሐ. ከሌሎች ቃላት ጋር ተዋህዶ ስመጣ ቃሉን ኢየሱስ እግዚአብሔርን መፈተን እንደማይገባ ለማሳየት ውሏል (ማቴ 4፡7፣ ሉቃ 4፡12፣ እንዲሁም 1ቆሮ 10፡9 ተመክከቱ)።
መ. ይህ ቃል ከአማኞች ፈተና እና መከራ ጋር ተያይዞ ቀርቧል (1ቆሮ 7፡5፣ 10፡9፣ 13፣ ገላ 6፡1፣ 1ተሰ 3፡5፣ዕብ 2፡18፣ ያዕ 1፡2፣ 13፣ 14፣ 1ጴጥ 4፡12፣ 2ጴጥ 2፡9)

▣ **"ሕግ"** ቁጥር 17 በኃላ የአሉ ክፍሎች የሚዳስሱት ስለ አይሁዳዊያን ስለሆነ "ሕግ" የሚለው ቃል በዝይህ አውድ ውስጥ የሚያመለክተው  የሙሴ ሕግን ነው። ይህ በቁጥር 25 ላይ ስለ ግርዛት በሚገልጸው ክፍል ልረጋገጥ ይችላል።

2፡18-20 አይሁዳዊያን መርዎች መንገዳቸው ትክክል እንደሆነ፣ ወደ እግዚአብሔር የሚያመራ ብቸቸኛው መንገድ እንደሆ ያምኑ ነበር። ስለ ኃይማኖታዊ ነገር እውነተኛ አስተማርዎች እንደሆኑ እርግጠኞች ነበሩ። ዕድል ተጠያቂነት አለው (ሉቃ 12፡48)።

የእነርሱ እርግጠኝነት የሚያመለክቱ ንጽጽሮችን አስተውሉ
1. ለእውሮች ምርትን ቁጥር 19
2. በጨለማ ላሉ ብርሃንን ቁጥር 19
3. ለሞኞች ትክክለኛውን ነገር ቁጥር 20
4. ላልበሰሉት ትምህርት ቁጥር 20
5. በሕግ ውስጥ የእውቀት እና እውነት መገኘት ቁጥር 20

2፡21-24 አንድ ሰው በግላዊ መታዘዙ ከታመነ ይህ መታዘዙ ፍጹም መሆን አለበት 9ማቴ 5፡20፣ 48፣ ገላ 3፡10 ይህ ከዘዳ 27፡26 የተወሰደ ክፍል ስሆን እንዲሁም ያዕ 2፡10)። ይህ ደግሞ ለወደቀው ሰው ልጅ የማይቻል ነገር ነው። ጳውሎስ ለአይሁዳዊያን ተደራሲያኖቹ ወይም አድማጮቹ ይህንን መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርብላቸዋል ቁጥር 21-23።

2፡22 በቁጥር 22-23 ባለው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ማንን በምመለከት እንደጻፈ ማወቅ አስቸጋር ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ የገለጸበት መንገድ በጳውሎስ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ኤኢሁዳዊያንን ስለማይመስል ነው። ስለዚህም ይህ ምንአልባት ጳውሎስ ኢየሱስ በማቴ 5፡20–48 ላይ ሕግን መንፈሳዊ በሆነ መልኩ እንደተረጎመው በዚህ ስፍራ ላይም ጳውሎስ ኀጢአትን መንፈሳዊ መንገድ ገልጾት ሊሆን ይችላል። ጌርጎር ላድ ተባለ ሰው በአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት መጽሐፉ እንዲህ ብሏል "ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መቀማትን፣ መንፈሳዊ ጣኦት አምልኮን እና  እራሰን እንደ ፈራጅ እና ጌታ በፍጥረታት ሁሉ ላይ ከፍ ክፍ በማድረግ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ፈጽሞ መሰጠትን ያመለክታል።" ገጽ 505

2፡22  **"ጣዖትን የምትጸየፍ"** ይህ ቃል ከአንድ ነገር ፈጽሞ ዞር ማለትን አሳያል ምክንያቱም የዚህ ቃል ምንጩ መናጠቅን የሚያመለክት ነውና።

▣ **"ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን"** በእርግጥ ይህ ሀረግ ምንን እንደሚያመለክት በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ነገር ግን ከጣኦት አምልኮ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ግን ማወቅ ይቻላል።
2፡24 ይህ ከሰባ ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ከኢሳያስ 52፡5 የተወሰደ ነው። እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ቃል ኪዳኑን ብጠብቁ ሊባርካቸው ቃል ገብቷል፤ አላማውም ለዓለም ሁሉ ምስክሮቹ ይሆኑ ዘንድ ነው (ዘዳ 27-28)።አለምን ሁሉ ወደ ያህዌ ታመጣ ዘንድ ነው (ዘፍ 12፡3፣ ኤፌ 2፡11-3፡13)።

2፡25-29
**ሕግን ብታደርግ መገረዝስ ይጠቅማል፤ ሕግን ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ አለ መገረዝ ሆኖአል። እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርዓት ቢጠብቅ አለመገረዙ እንደ መገረዝ ሆኖ አይቈጠርለትምን? ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ሕግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሃል። በግልጥ**

**አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።**

2:25 "**ግርዛት**" ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ለይ እየተቃወመ ነው የጻፈው:: አንዳንዶች በትንሹም ብሆን እኛ የተገረዝን ሰዎችን ነው (ዘፍ 17:10-11) ልሉ ይችላሉ፡፤ እንዲሁም እኛ የአብረሃም ልጆች ነን። ጳውሎስ ግን በግልጽ እና በቆራጥ ቃላት ትምክክታቸውን በማኮላሸት የአይሁዳዊያንን ተስፋ ባዶ አደረገው (ማቴ 3:7-10፣ ዮሐ 8:31-53)።

በእስራኤላዊያን አከባቢ ይኖሩ ከነበሩ ሕዝቦች ከፍልስጤማዊያን ውጭ ሁሉም ተገረዙ ነበሩ። ድርግቱ ብቻ አልነበረም አስፈላጊው ነገር፣ ነገር ግን በተቀባዬቹ በኩል ቀጣይነት ያለው እውነት አስፈላጊ ነበር (ቁጥር 26-27)። ይህ ለማንኛው ኃይማኖታዊ ሥርዓት አስፈላጊ ነገር ነው። ኃይማኖታዊ ሰዎች ሁል ጊዜም ብሆን የአምላካቸውን ባርኮት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን መሻታቸው ያለ እነርሱ ድርሻ ነው።

2:26-27 እነዚህ ቁጥሮች አሕዛብ ለተገለጠላቸው ብርሃን ስለሰጡት ምላሽ ያላቸውን ተስፋ የሚያሳይ ነው። ለዚይህ ነገር ብቸኛው ምሳሌ የሚሆነው በሐዋ 10 ላይ ተገለጸው ቆርኖሌዎስ ነው። ነገር ግን በእርግጥ እርሱንም ስንመለከተው በዚህ ጎራ ውስጥ አይመደብም ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔርን የሚፈራ እና በአጥቢያ ምኩራብ ውስጥ የሚያመልክ ስለነበር ነው።

እነዚህ ቁጥሮች አይሁዳዊያንም ድነት እንደሚአስፈልጋቸው ሞገተባቸው ክፍሎች ናቸው። ሮሜ 3:23 ሁሉም የሰው ልጆች ከክርስቶስ ች ከሆኑ የጠፉ መሆናቸውን ጠቅላል ባለ መልኩ የቀረበበት ነው። ከአሕዛብ መካከል እግዚአብሔር በተፈጥሮ እና በሕሊናው በገለጠለት ብርሃን የኖረ ሰው ካለ እግዚአብሔር በሆነ መንገድ፣ በሆነ ጊዜ ድነትን ያዘጋጅለታል።

2:28-29 "**አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ . . . አይሁዳዊ ነው**" ይህ በእርግት በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው ምክንያቱም በዘመናችን ድስፔንሴሽናልስት በመባል በሚታወቀው ሥነ መለኮታዊ አቋም መሠረት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በብሉይ ኪዳን ሕዝቦች እና የአዲስ ክዳን ሕዝቦች ብለው ስለሚከፍሉት ነው። እውነተኛው ግን አንድ ኪዳን እና አንድ ሕዝብ ነው (ሮሜ 9:6፣ ገላ 3:7-9፣ 29፣ 6:16፣ 1ጴጥ 3:6)። አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን እድገት እና ሙላት ነው። እግዚአብሔር ሕዝብ መሆን በዘር ሀረግ ሳይሆን ሁል ጊዜም በእምነት ነው። እነርሱ "የልብ ህዝቦች" እንጅ የኃይማኖታዊ ሥርዓትን ሚፈጽሙ ወይም በዘር ሀረጋቸው የተመረጡ ህዝቦች አይደሉም። እምነት እንጅ ወላጆች ቁልፍ አይደሉም። ቃል ኪዳናዊ አስተሳሰብ እንጂ የቃል ኪዳን ምልክት አስፈላጊ አይለደም።

▣ "*ሥጋ*" በ1:3 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

2:29 በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው የቃል ኪዳን ምልክት የነበረው ግርዘት የአንድ ሰውን ለእግዚአብሔር ክፍት መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ይህንን ምሳሌ የሚታየው በተለያየ መልኩ ስሆን (1) በልብ ግርዘት (ዘዳ 10:16፣ ኤር 4:4) (2) በጆሮ ግርዘት (ኤር 6:10) እና (3) በከንፈር ግርዘት (ዘጸ 6:12፣30)። ሕጉ ፈጽሞ ውጫው ስርኣት እንዲሆን አልታቀደም ነበር፤ ነገር ግን ሕይወትን የሚለውጥ እንደሆን የታለመ ነው። በ13:9 ላይ ተገለጸውን የጳውሎስን የሕግ አመለካከት ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በመንፈስ የሚደረግ የልብ እንጂ በመጽሐፍ አይደለም"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በመንፈስ የሚደረግ የልብ እንጂ በመጽሐፍ አይደለም"** |
| **አየመመቅ** | **"የልብ ጉዳይ . . . መንፈሳዊ እንጅ ሥጋዊ"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"የጽሑፍ ሕግ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ የሆነው"** |
| **ኢመቅ** | **"በልብ ውስጥ . . . ከፍዳል ሳይሆን ከመንፈስ የሆነ"** |

ይህ ቃል በግሪኩ አወዛጋቢ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን ቃል በመንፈሳዊ እና ሥጋዊ በለውታል። ሌሎቹ በመንፈስ ቅዱስ እና በፍድል መካከል እንደላ ንጽጽር አስቀምጠውታል።

ጳውሎስ በዝይህ ስፍራ ላይ አንዳንድ አይሁዶች ከሕግ ውች ለእግዚአብሔር የሚያስድስት መሰዋዕት የመሆናቸውን እውነት የገለጽበት ነው። ይህ እውነት ከሆነ የእግዚአብሔር ልጆች በሥጋ የተገረዙት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም (አሕዛብንም) ያካትታል። የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ከአይሁዳዊነት ዝርያ ይሰፋል (ዘፍ 3:15፣ 12:3፣ ዘጸ 19:5)፣ እዮብ፣ መልከጼዴቅ፣ ዮቶርን፣ ካሌብ፣ ራአብ እና ሩት በዝርያ አይሁዳዊያን አልነበሩም። ከዚይህ በተጨማር የኤፍሬም እና የሚናሴ ነገዶችም ብሆን ግማሽ ግብጻዊን ነበሩ (ዘፍ 41:50-52)።

*የመወያያ ጥያቄዎች*

*ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻ ነው። ይህ ማለት አንባቢው ስለሚደርስበት ትርጓሜ እራሱ ተጠያቂ ነው ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተቀበልነው ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል። አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜ ላይ ዋነኛውን ስፍራ ትይዛላችሁ። ይህንን እድል በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች መለወጥ ተገቢ አይደለም።*

*እነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች የተሰጡት በመጽሐፉ ውስጥ ዋና ዋና በምባሉ ሀሳቦች ላይ አጽኖት ስጥታችሁ እንድታስቡ ለማድረግ ነው። ዋነኛ አላማቸው እንድታስቡ ማድረግ እንጅ ትርጓሜን ለመስጠት አይደለም።*

1. *እንዴት የአይሁዳዊያን ታማኝ አለመሆን በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተጽእኖ አሳደረተ*? 3:3-4
2. *አይሁዳዊ መሆን በእግዚአብሔር ፍት የሚያስገኘው ጠቀሜታ አለን*? 3:1-8
3. *መስቀለኛ ጥያቄ ማለት ምን ማለት ነው*?
4. *በመስቀለኛ ጥያቄ ጳውሎስ ማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት ምንድን ነው ቁጥ* 5-8
5. *መጽደቅ በጸጋ ከሰው ሥራ ውጭ በእምነት ከሆነ አንድ ሰው አኗኗር ምን ፋይዳ ይኖረዋል*? 3:8
6. *ፈጽሞ መጥፋት የሚለው ሀሳብ ምን ሥነ-መለኮታዊ ሀሳብ በውስጡ አዝሏል*? 3:10-18
7. *የሙሴ ሕግ አላመ ምንድነው*? *ወይም አጠቃላይ የሕግ አላማ ምንድነው*> 3:20 *ገላ* 3*ለ*24-25
8. *በምዕራፍ* 1-3 *ባለው ክፍል ውስጥ ስለ ሰዎች መጥፋት በሚያወራው ክፍል ውስጥ የሴጣን ስም ለምን አልተጠቀሰም*?
9. *የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃል በሁኔታዎች ተገደበ ወይስ አልተገደበ ነው*?
10. (1) *በአይሁዳዊያን እና* (2) *በአሕዛብ የሙሴ ሕግ ዓላም ምንድን ነው*?
11. 1:18-3:20 *ያለውን ክፍል በራስህ ቃላት የጳውሎስን ሙግት ውቅር ጻፍ።*

# ሮሜ 3

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ [4] | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | ኒው ርቫይዝድ ስታንዳር ቨርዥን | ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን | ጀሩሳሌም ባይብል |
|---|---|---|---|---|
| አይሁዳዊያን እና ሕግ የተስፋ (2፡17-3፡8) | ለእግዚአብሔር ፍርድ ሙግት | አይሁዳዊያን ጥቅም | አይሁዳዊያን እና ሕግ (2፡17-3፡8) | የእግዚአብሐር ቃል አያድናቸውም |
| 3፡1-8 | 3፡1-8 | 3፡1-8 | 3፡1-4 | 3፡1-8 |
| | | | 3፡5-6 | |
| | | | 3፡7-8 | |
| ማንም ጻድቅ የለም | ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋል | ሁሉ በደለኞች ናቸው | ጻድቅ የሆነ ሰው ለም | ሁሉ በድለዋል |
| 3፡9-20 | 3፡9-20 | 3፡9-18 | 3፡9-18 | 3፡9-18 |
| | | 3፡19-20 | 3፡19-20 | 3፡19-20 |
| በእምነት የሚሆን ጽድቅ | በእምንት የሚሆን ጽድቅ | እውነተኛ ጽድቅ | እግዚአብሐር እንዴት ሰዎችን እንደሚያስተካክል | እግዚአብሔር ቅንት ስገለጥ |
| 3፡21-26 | 3፡21-26 | 3፡21-26 | 3፡21-26 | 3፡21-26 |
| | | ትምክት አያስፈልግም | ትምክት አያስፈልግም | እምንት ምን እንደሚሠራ |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥና መመሪያ የመጽሐፍ ቅዱሰኢ መክፈቻ ነው፤ ማለትም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምትረተጉሙበት መንገድ እራሳችሁ ኃላፊነቱነረ ትወስዳላችሁ። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል። አንተ፣ መጽሐፈ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱሰን ክፍል ትክክለኛ ፍች ለማግኘት በምደረገው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊዎቸ ናችሁ። ይህንን እድል ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች ልንለውጠው አይገባም።

አንድን ምዕራፍ በአንድ ጊዜ ንባብ አንብበህ ጨርስ። ዋና መልዕክቱን ለይ። የአንተን መልዕክት ክፍፍል ከአምስት መጽሓፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር አነጻጽር። ትርጓሜ እንብርት የሆነው የአንቀጽ ክፍፍልን መከትል ምንም እንኳ  የደራስውን ዓላማ ለማግኘት ቁልፍ ቢሆንም ነገር ግን የአንቀጽ ክፍፍል ከስህተት የጸዳ ግን አይደለም። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ መልክት ብቻ ይኖረዋል።

1. አንቀጽ አንድ

2. አንቀጽ ሁለት

3. አንቀጽ ሶስት

4. ወዘተ

**አውዳዊ መረዳት**

ሀ. ከ1-8 ያሉቱ ቁጥሮች ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች የሚያወሱ ብሆንም እንኳ የጳውሎስን አመክኖአዊ የክርክር ነጥቦችን መከተል በጣም አዳጋች ነው፤ ምክንያቱም መስቀለኛ ጥያቄዎችን ያካተተ ስነ ጽሑፋዊ ዘዴን ስለሚከተል ነው።

ለ. በ2:17-29 ላይ ጳውሎስ እንዴት አይሁዳዊያን ለጥያቄው ምላሽ እንደሚሰጡ የሚጠብቅ ይመስላል። ስለዚህም ለእነርሱ የተቃዎሞ ምላሽ የእራሱን ምላሽ ይሰጣል።

1. ጥያቄ አንድ፦ አይሁዳዊ መሆን ምንም ጥያቄ የለውምን? (1-2)
2. ጥያቄ ሁለት፦ አንዳንድ አይሁዳዊያን ታማኝ ካለመሆናቸው የተነሳ የእግዚአብሔር ቃል አይፈጸምም ማለት ነውን? (3-4)
3. ጥያቄ ሦስት፦ እግዚአብሔር አይሁዳዊያንን የራሱዩን ባሕርይ ልገለጽ ከተጠቀመባቸው ታዲያ አይሁዳዊያን በእርሱ ፍት ተጠያቂዎች ናቸውን? (5-8)

ሐ. ማጠቃላያው ወደ 2:11 ይመለሳል። በእግዚአብሔር ዘንድ ማዳለት የለም። ሰዎች ሁሉ ከተቀበሉት ብርሃን ውጭ (አጠቃላይ መገለጥም ይሁን ለልዩ መገለጥ) ለኖሩበት ነገር ተጠያቂዎች ናቸው።

መ. ቁጥር 9-18 የአይሁዳዊያንንን ኀጢአቶች ያሉት ከብሉይ ኪዳን የተወሰዱ ጥቅሶች ናቸው።

ሠ. ቁጥር 19–20 የእስራኤላዊያን መንፈሳዊ ሁኔታ እና የብሉይ ኪዳን መጽሐፍን አላማ የሚያጠቃልል ነው። (ገላ 3)

ረ. ቁጥር 21-31 ያለው  የ1:18-3:20 ጥቅል ሀሳብ ነው።  በመጀመሪያ ይህ የመንጌል ሥነ መለኮታዊ ዋና ሀሳቡ ነው።

**የቃላት እና የሀረጎች ጥናት**

> 3:1-8
> **እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው። አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። ታዲያ ምንድር ነው? የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? እንዲህ አይሁን፤ በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን። ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል? በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል? ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።**

3:1 **"እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው?"** ጳውሎስ መልዕክቱን ለማስተላለፍ የመስቀለኛ ጥያቄ የሥነ ጽሑፍ ጥበቡብ ብዝይህ ስፍራ ላይም ቀጥሏል። ምክንያቱም በዚህ ስፍራ ላይ የአይሁዳዊያንን ጥቅም ይዘረዝራልና። 3:2 እና 9: 4-5 የሚለውን ተመለክት።

3:2 **"ከሁሉ አስቀድሞ"**  ጳውሎስ በ1:8 ላይ ቅድሚያ የሚለውን ቃል ሲጠቀም ግን በሁለተኛው ስፍራ ይኽንን ስይዘረዝር ነበር። በዚህ ስፍራ ተመሳሳይ ነገርን ነው ያደረገው። የጳውሎስ ጽሁፎች አንድ ላይ የታጨቁ ናቸው። እንዲሁነም ቃል በቃል የተነገረ አይነት ስለነበር።

3:3 **"ከሁሉ አስቀድሞ"**  ቢሆንስ ይህ የመጀመሪያ የይሆን አረፍተ ነገር ነው። ይህም ከፀሐፊው አመለካከትና አስተሳሰብ አንጻር ነው ተብሎ ይገመታል። ቁጥር 5 እና 7 በተጨማሪ ይኽንኑ አመልካች ናቸው።

▣ **"የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው።"**  የእግዚአብሔር መገለጥ መቀበል የሚያስደንቅ ኃላፍነት እና ትልቅ ጥቅም ነው (9:4-5)። እነርሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ባለ አደራዎች ናቸው።

"ቃላት" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በሰባ ልቃናት ከእግዚአብሔር የሆነ ቃል ተብሏል (ዘኍ 24:4፣ 16፤ ዘዳ 33:9፣ መዝ 119:67፣ ኢሳ 5:24፣ 28:13)። በሐዲስ ኪዳናት መጽሐፍት ውስጥ ይህ ቃል በዚህ መልኩ አገልግሎት ላይ ውሏል (የሐ 7:38፣ ዕብ 5:12፣ 1ጴጥ 4:11)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"አንዳንዶች አላመኑም"** |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን፣ ኢመቅ** | **"አንዳንዶች ታማኝ አልነበሩም"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"አንዳንዶች ታማኝ ካልነበሩ"** |

ይህ ምንአልባትም የእስራኤላዊያን ግለሰቦችን (1) ታማኝ አለመሆን ወይም (2) ያህዌን በግል ያለማመንን ልያመልክት ይችላል። የእግዚአብሔርን በሁኔታዎች ያልተገደበ የተስፋ ቃል ከሰው በሁኔታዎች የተገደበ ምላሽ ጋር ማያያዝ እስቸጋር ነው። ነገር ግን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት እስቸጋር የሆነ ነገር ነው(3:4-5)። የእርሱ ሕዝቦች ታማኝ ባልሆኑበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ታማኝ ነው (ሆሴ 1፣3)።

▣ *"ማስቀረት"* ከዚይህ በታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልክት

**ልዩ ርዕስ፡ ባዶ እና ምንም የሌለበት (ካታረግኦ)**

ካታረግኦ ጳውሎስ አዘውትሮ ከሚጠቀማቸው ቃላት መካከል አንዱ ነው። ጳውሎስ ይህንን ቃል ከ25 ጊዜ በላይ በጽሑፎቹ ውስጥ የተጠቀመ ስሆን ቃሉም በጣም ሰፍ ትርጓመ አለው።

ሀ. የቃሉ ሥረወ ግንድ "አረጎስ" ሲሆን ትርጓሜውም
1. የማይንቀሳቀስ
2. ምንም የማይሠራ
3. ጥቅም ላይ ያልዋለ
4. የማይጠቅም
5. የማይሠራ

ለ. ይህ ቃል ከ"ካታ" ጋር በጥምረት ስመጣ የሚያመለክተው
1. የማይሠራ
2. የማይጠቅም
3. የተሰረዘ
4. ተስፋ የተቆረጠበት
5. ከጥቅም ውጭ እንደሆነ የተደረገ

ሐ. ይህ ቃል በሉቃስ ወንጌል ውስጥ አንድ ጊዜ ፍሬ ያላፈራ ዛፍን ለማለክተር አገልግሎት ላይ ውሏል (ሉቃ 13:7)።

መ. ጳውሎስ ይህንን ቃል በምሳሌነት በዋናነት በሁለት መንገድ ተጠቅሞታል
1. ለሰው ልጆች ጠላት የሆነውን ነገር እግዚአብሔር አስወግዶታል
   ሀ. የሰው ልጆችን ኀጢአታዊ ተፈጥሮ ሮሜ 6:6
   ለ. የእግዚአብሔር ተስፋ የሆነው "ዘር" ከሙሴ ሕግ ጋር ያለው ግንኙነት ሮሜ 4:14፣ ገላ 3:17፣ 5:4፣ 11፣ ኤፌ 2:15
   ሐ. መንፈሳዊ ኃይላት 1ቆሮ 15:24
   መ. "የጥፋት ልጅ" 2ተሰ 2:8
   ሠ. አካላዊ ሞት 1ቆሮ 15:26፣ 2ጢሞ 1:16 (ዕብ 2:14)
2. እግዚአብሔር አሮጌውን ቃል ኪዳን በአዲሱ ለውጦታል
   ሀ. ከሙሴ ሕግ ጋር ግንኙነት አላቸውን ነገሮች ሮሜ 3:3፣ 31፣ 4:14፣ 2ቆሮ 3:7፣11፣13፣14
   ለ. ስለ ሕግ ለማስረዳት የተጠቀማቸውን የጋብቻ ምሳሌዎች ሮሜ 7:2፣6
   ሐ. ስለዚይህ ዘመን ነገሮች 1ቆረ 13:8፣ 10፣11
   መ. ይህ አካል 1ቆረ 6:13
   ሠ. የዚይህ አለም ገዥ 1ቆረ 1:28፣ 2:6

ይህ ቃል ምንም እንኳ በተለያየ መንገድ ልተረጎም ብችልም ነገር ግን ትርጓሜው በዋናነት የአንድን ነገር ጠቃም አለመሆን፣ ባዶ፣ የማይሠራ፣ ኃይል የሌለው መሆንን የሚያሳይ እንጂ ህሉዕ ያልሆነ፣ ፈጽሞ የተወገደ ወይም ፈጽሞ የጠፋ የሚለውን አያመለክትም።

3:4

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እንዲህ አይሁን"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም፣ ቱደይስ እንግልሽ ቨርዥን** | **"በፍጹም አይሆንም"** |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | **"በምን መንገድ አይሆንም"** |
| **ኢመቅ** | **"ይህ የማይመስል ነገር ነው"** |

ይህ "እንድህ አይሁን" ተብሎ ልተረጎም የሚገባው ፍላጎትን የሚያመልክት የግርክ ሥዋሰዋዊ ቀመርን የተከተለ ነው። ይህ ሀረግ ያለማመናቸው ጳውሎስ በአጋራሞት ለመግለጥ አዘውትሮ የሚገልጽበት መንግድ ነው (3:4፣ 6፣ 31፣ 6:2፣ 15፣ 7:7፣ 13፣ 9:14፣ 11:1፣ 1ቆሮ 6:15፣ ገላ 2:17፣ 3:21፣ 6:14)። ከጽሑፉ በፍት ተገለጠውን ዐረፍተ ነገር ጳውሎስ በአጽኖት ለመቃወም የሚጠቀምበት መንገድ ነው።

ጳውሎስ የተቃውሞ ጥያቄዎችን እና ዐረፈተ ነገሮችን የሚቃወምበትን ምንገድ ማስተዋል ተገቢ ነው

1. "እንዲህ አይሁን" 4፣6
2. "ሰው ሁሉ ውሽተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።" ቁ.4

3. "(እንደ ሰው ልማድ እላለሁ።)" ቁ 5
4. "(እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና።)" ቁ.8

▣ **"ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።"** ይህ ውቅር የሀሳቡን ቀጣየነት ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነው፤ እግዚአብሔር ታማኝ እና እውነተኛ ነው፤ ነገር ግን ሰዎች የማይታመኑ እና ዋሾች ናቸው። ይህ ክፍል ከመዝ 116፡11 የተወሰደ ስሆን እዮብ በ32፡2፣ 40፡8 ላይ ከተማረው ጋር ተመሳሳይ ነው።
በዝይህ ምዕራፍ ውስጥ የኀጢአትን አለም አቀፋዊነት በጳውሎስ "ፓሳ" የሚለውን ቃል አጠቃቀም በመመልከት መገነዘብ ይቻላል ቁጥር 4፣9፣12፣19፣20፣23፣24 ።

▣ **"እንደተጻፈ"** ቀጥተኛ ትርጓሜው "ተጽፏል እንዲሁም እየተጻፈ ነው" የሚል ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስን በእግዚአብሔር እስትንፋስ መጻፍን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው (ማቴ 5፡17-19)። ይህ ሀረግ ተወሰደው ከመዝ 51፡4 ከሳባ ሊቃነት መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

**3፡5-6** በእነዝይህ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ እግዚአብሔር እስራኤላዊያን ልዩ በሆነ መንገድ መምረጡን ለማመልከት መከራከርያ ነጥቦቹን ያስቀምጣል (ዘፍ 12፡3፣ ዘጸ 19፡5-6)። በብሉይ ኪዳን **"ምርጫ"** የሚያመልከተው አገልግሎትን እንጂ ልዩ የሆነ ጥቅምን አይደለም። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል። እርሱ ታማኝ ነበር፤ እነርሱ ግን ታማኞች አልነበሩም (ነህ 9)። እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትን እስራኤላዊያንን የመቅጣቱ ገሃድ እውነታ የሚያመለክተው የእርሱ ጻድቅነት ነው።
እስራኤላዊያን ተልዕኮ የነበረው አሕዛብን ለመድረስ መንገድ ሆነው እንድያገለግሉ ነበር። እነርሱ ግን ይህንን ልያደርጉ አልቻሉም (3፡24)! የእስራኤላዊያን ውድቀት እግዚአብሔርን አለምን (ዘፍ 3፡15) ሁሉ የማዳን አላማ አያደናቅፈውም ። እንዲያውም በሮሜ 9-11 ላይ የእግዚብሔር ለመጀመሪያው ቃል ኪዳን ያለውን ታማኝነት የሚያስረግጥበት ስፍራ ነው። የማያምኑ እስራኤላዊያን ስጣሉ የሚያምኑት ግን የእግዚአብሔርን የመዋጀት እቅድ ከፍጻሜ ያደርሳሉ።
3፡5

▣ **"ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ"** "ዓመፃችን" የሚለው ቃል ተውላጠ ስማዊ ተቀጽላ ስላለው ይህ ተቀጽላ የሚያመለክተው ሁሉንም አይሁዳዊያንን ነው። በ1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

▣ **"ምን እንላለን?"** ጳውሎስ እዚይህ ስፍራ ላይ መስቀለኛ ጥያቄን አቅርቧል (3፡5፣ 7፡7፣ 8፡31፣ 9፡14፣39)። ጳውሎስ ያቀረበውን ሀሳብ ተቃውሞ በምመስሉ ጥያቄዎችን በማንሳት እና ምላሽ በመስጠት አብራርቷል (ሚል 1፡2፣6፣7፣12፣13፣ 2፡14፣ 17 (ሁለት ጊዜ)፣ 3፡7፣ 13፣ 14)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በሰው ቋንቋ እናገራለሁ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"እንደ ሰው እናገራለሁ"** |
| **ኒው ርቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | **"በሰው መንገድ እናገራለሁ"** |
| **ቱደይስ እንግልሽ ቨርዥን** | **"ሰዎች እንደሚናገሩት እናገራለሁ"** |
| **ኢመቅ** | **"የሰዎችን ምሳሌ ለመጠቀም"** |

ጳውሎሰ ብዙ ጊዜ የራሱን ሥነ መለኮታዊ የመመከራከርያ ነጥብ ለማስቀመጥ የሰዎችን አመክንዮ ይጠቀማል (6፡19፣ 1ቆሮ 9፡8፣ ገላ 3፡15)። በዚህ ስፍራ ላይ ጳውሎስ ተቃውሞ ተብሎ ሊቀርብ የሚችለውን ሀሳብ ጳውሎስ የተቃወመብት ነው።

**3፡7-8** በቁጥር 5 እና 7 መካከል ግልጽ የሆነ ነጽጽር አለ። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ለይ (1) መስቀለኛ ጥያቄአዊ የስነ ጽሑፍ ዘይቤውን ተጠቅሟል (3፡5፣ 7፣ 7፡7፣ 8፡31፣ 9፡14፣ 30) ወይም (2) መጽደቅ በእምነት ብቻ ነው የሚለውን አስተምህሮን በመቃወም የጻፈውን ነው (ቁ.8)።
ጳውሎስ ክሱን በደንብ አላብራራም ወይም ለክሱ ምላሽ አልሰጠም ነገር ግን ክስን በአጽሞት ግን ተቃውሞታል። የማይገባ፣ በነጻ የተሰጠ ጽድቅ ወደ ስርዓት አልባለነት ወይም ወደ አለመታዘዝ ልያመራ ይችላል ብሎ መቃወም አግባብነት አለው። ጳውሎስ በአዲስ መንፈስ አመካኝነት ክርስቶሰን ወደ መምሰል እና ወደ ምስጋና ሕይወት ይመራል ብሎ ያምናል። አይሁዳዊያንም ሆኑ፣ ግሪኮች እንዲሁም ጳወሎስ ወደ እነርሱ አመከካከት ተለወጡ ሰዎች ሥነ-ምግባራዊ ለውጥን በሕይወታቸው አንድለማመዱ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ይህ የሚሆነው ውጫዊ ሥርዓት ሕጎችን በመጠበቅ ሳይሆን አዲስን ልብን በማግኘት ነው (ኤር 31፡31-34፣ ሕዝ 36፡22-36)

▣ **"ላቀ"** በ15፡13 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

▣ **"ለክብሩ"** በ3፡23 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**አአመመቅ 3:9-18**
**እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋልና፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ። ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም። ጕሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በመላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።**

3:9 "ከእነርሱ እንደልጣለንን?" በዚህ ስፍራ ላይ ያለው ስዋሰው አሻሚ ነው። እርግጥ ነው የዚህ ስፍራ ዋና ሀሳቡ የሰው ልጆች ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚፈልጋቸው መግለጽ ነው (3:9፣ 19፣ 23፣ 11:31 ፣ ገላ 3:22)። ነገር ግን ይህ ቁጥር በእርግጥ አይሁዳዊያንን (ጳውሎስን እና ዘመዶቹን ቱዳይ እንግለሽ ቨርዥን፣ ርቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን እንደሚሉት) ወይም ክርስቲያኖች (ጳውሎስ እና ሌሎች ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ አማኞች በመሆን ክርስቲያን ወንድሞች የሆኑነትን) እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም። አይሁዳዊያን የተወሰነ ጠቀሜታዎች ነበሯቸው (ቁጥር 1-2፣ 9:4) ነገር ግን ይህ ያገኙት ጠቀሜታ የበልጥ ኃላፊነት እንድሰማቸው አድርጓል። የሰው ልጆች ሁሉ መንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ ስለሚገኙ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልጋቸዋል።

የሮሜ መልእክት ከጳውሎስ መልክቶች በተለየ ሁኔታ ለአንድ አከባቢ እንዳልተጻፈ ብዙ ሰዎች ይናገራሉ። በዝይህ አውድ ውስጥ እና በምዕራፍ 9 አውድ ውስጥ በአይሁዳዊያን መሪዎች እና በአሕዛብ መሪዎች መካከል የነበረው በቅናት የተነሳ ግጭት  የክፍሉ ታርካዊ ዳራ ልሆን ይችላል።

▣ "ከኀጢአት በታች" ጳውሎስ ኀጢአትን ሰውኛ በማድግ በወደቁት ሰዎች ላይ የነገሠ ክፉ ንጉሥ አድርጎ ያቀርበዋል። (6:16-23)

3:10-18 "እንደ ተጻፈ" ይህንን ሀረገ በቁጥር 4 ላይም ተጠቅሞታል። ከዚይህ ቀጥሎ የቀረቡት ተከታታይ ከብሉይ ኪዳን የተወሰዱ ትቅሶች ስሆኑ የሰው ልጆችን በኀጢአት የወደቁ መሆናቸውን ለማሳየት ጳውሎስ ዘይቤአዊ አነጋገሮችን ተጠቅሟል። (1) 10-12፣ መክ 7:20 ወይም መዝ 14:1-3፣ (2) ቁ. 13፣ መዝ 5:9 ወይም መዝ 140:3፣ (3) ቁ.14 መዝ 10:7፣ (4) ቁ. 15-17፣ ኢሳ 59:7 -8  እና ምሳ 1:16 እና (5) ቁ.18 መዝ 36:1።  ጳውሎስ ኢሳ 53:6 አለመጠቀሙ በጣም የሚያስገርም ነው።

**3:19-20 አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።**

3:19 "እናውቃለን" በ2:2 ላይ የተገራራውን ተመልከቱ

▣ "ሕግ" በዚህ አውድ መሠረት ይህ ሙሉ ብሉ ኪዳንን ልያመለክት ይችላል። ምክንያቱም 10- 18 ባሉ ቁጥሮች ውስጥ ሆኖ ጳውሎስ "ኀጢአትን" በሰውኛ ቋንቋ እንደገለጸው ሁሉ በቁጥር 9 "ሕግን"ም ገልጿል (6:16-23)።

▣  "ከሕግ በታች ላሉት" ይህ በግልጽ ለአይሁዳዊያን እና ወደ አይሁዳዊነት የተለወጡትን ያመለክታል። እንዲሁም አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አሕዛብን እንደሚያመለክቱ መናገር ይቻላል።

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ እንዲሁም አለምም ሁሉ ለእግዚአብሔር ተጠያቂ ይሆን ዘንድ ነው" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "አፍ ሁሉ ዝም ይል ዘንድ እና ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ይሆን ዘንድ ነው" |
| ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ | "እንደበት ሁሉ ዝም ይል ዘንድ እና ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፍት ተጠያቂ ይሆን ዘንድ ነው። |
| ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን | "የሰው ልጆች ማመከኛ ለማስቆም እና ዓለምን ሁሉ በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ለማስቀመጥ ነው።" |
| ጀሩሳሌም ባይብል | "ነገር ግን አለማው ሁሉንም ዝም ለማሰኘት እና ሁሉንም ለእግዚአብሔር ፍርድ ክፍት ለማድረግ ነው።" |

በቁጥር 3:23 ላይ የ1:18-3:20 ጠቅላላ ምዕራፍ ጥቅል ሀሳብ የሚገኝበት ነው።

▣ *"አፍም ሁሉ"* በቁጥር 19-20 *ሁሉንም የሰው ልጆች የሚያመለክቱ በጣም ብዙ ሀረጎች አሉ።*

1. *"አፍም ሁሉ"* ቁጥር 19
2. *"ዓለም ሁሉ"* ቁጥር 19
3. *"ሥጋ ለባሽ ሁሉ"* ቁጥር 20

**3:20 "ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤"** *ይህ ክፍል የተወሰደው ከመዝ 143:2 ነው ነገር ግን ትንሽ ሀረጎች ተጨምረውበታል። ይህ የጳውሎስ ወንጌል አንዱ መገለጫው ነው* (ገላ 2:16፣ 3:11)። *እንደተሰጠ ፍርሳዊ የኃየማኖት ቀናተኝነት እና ስርዓትን መፈጸም ውስጣዊ ሰላምን እንደማይሰጡ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።*

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | **"በሕግ በኩል ኀጢአት ምን እንደሆነ ማወቅ ይመጣል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በሕግ ኀጢአት ምን እንደሆ ይታወቃልና"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"ሕግ የሚያደረገው የሰው ልጅ ኀጢአትን እንዳደረገ ማሳወቅ ነው"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብል** | **"ብቸኛ ሕግ ልያደረግ የሚችለው ኀጢአት ምን እንደሆነ መናገር ነው"** |

*ይህ የብሉይ ኪዳን አንዱ አላማ ነው። በ*13:9 *ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት። የሕግ አለማ ለሰው ልጆች ድነትን ለማስገኘት ፈጽሞ አልነበረም። አላማው የሰው ልጆችን ኀጢአተኝነት መግለጥ እና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔረኢ ምሕረት መምራት ነው* (4:15፣ 5:13፣ 20፣ 20፣ 7:7፣ *ገላ* 3:19-22፣ 23-29)

***የመወያያ ጥያቄዎች***

*ይህ የጥና* <u>*መመሪያ*</u> *የመጽሐፍ ቅዱስኢ መክፈቻ ነው፤ ማለትም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምትረተተሙበት መንገድ እራሳችሁ ኃላፊነቱነሪ ትወስዳላችሁ። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል። አንተ፣ መጽሐፈ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ትክክለኛ ፍች ለማግኘት በምደረገው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊዎቸ ናችሁ። ይህንን እድል ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች ልንለውጠው አይገባም።*

*እነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች  የተሰጡት በመጽሐፉ ውስጥ ዋና ዋና በምባሉ ሀሳቦች ላይ አጽኖት ሰጥታችሁ እንድታስቡ ለማድረግ ነው። ዋነኛ አላማቸው እንድታስቡ ማድረግ እንጅ ትርጓሜን ለመስጠት አይደለም።*

1. *የአይሁዳዊያን ታማኝ አለመሆን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እንዴት ሊያደናቅፍ ይችላል?* (3:3-4)
2. *በእግዚአብሔር ፍት አይሁዳዊ መሆን ጠቀሜታ አለውን?* (3:1-8)
3. *በቁጥር* 5-8 *ውስጥ ያው ተቃውሞ የሚመስል (መስቀኛ ጥያቄ) ጠቀሜታው ምንድነው?*
4. *መጽደቅ ከሥራ ውጭ በጸጋ በእምነት የሚሆን ከሆነ የአንድ ሰው የአኗኗር ሁኔታ ጠቀሜታ አለውን?*
5. *ሥነ መለኮታዊ ሀሳብ የሆነውን ፈጽሞ መጥፋት የሚለውን የካልቭን ሀሳብ ግለጽ* (3:10-18)
6. *የሙሴ ሕግ ወይም ሕጎች በጣቃላይ አላማቸው ምንድ ነው?* (3:20፣ *ገላ* 3:24-25)
7. *በምዕራፍ* 1-3 *ባሉት ክፍሎች ውስጥ ሰለው ሰዎች መጥፋት በሚያወሳው ክፍል ውስጥ የሴጣን ስም ፈጽሞ ያልመጠቀሱ ምክንያት ምንድነው?*

**በሮሜ 3:21-31 ባለው ክፍል ውስጥ አውዳዊ መረዳት**

*ሀ. ሮሜ* 3:21-31
1. 1:18-3:20 *ላይ ዋና ማጠቃለያው ይገኛል*
2. *በ*1:16-17 *መገለጨው ነው*
3. *የምዕራፍ* 4-8 *መግቢያ (በተለይም* 3:28)

*ለ. ይህ መጽደቅ በእምነት ብቻ የሚለው አስተምህሮ ዋነኛ ማጠቃለያ በተሀድሶ አረማጆች መለያ ነበር*
1. *ማሪት ሉተር ይህንን እንደ "ዋነኛ ነጥብ እና የመልዕክቶች እና የሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል" አድርጎ ይመለከተው ነበር።*
2. *ጆን ክለቪን ይህንን ሀሳብ "በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በክርስቶስ ያለውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ በግልጽ የሚያስቀምጥ እንደዚይህ ጥቅስ የለም" ብሏል።*

*ሐ. ይህ የወንጌላዊያን ሥነ መለኮታዊ እሴት ነው። ይህንን መረዳት ክርስትናን መረዳት ነው። ዮሐ* 3:16 *ወንጌል እንደሆነ ሁሉ ይህ በሁለት አንቀጽ ወንጌል በጥቅል የቀረበበት ነው። ይህ የጳውሎስ የወንጌል አቀራረብ ልብ እና ነፍስ ነው።*

*ሦስት መሠረታዊ የአተረጓጎም ጥያቄዎች አሉ*
1. *"ሕግ" የሚለው ቃል ትርጓሜው ምንድነው?*
2. *"እግዚአብሔር ጽድቅ" የሚለው ሀረገት ትርጓሜው ምንድነው?*
3. *"እምነት" እና "ማመን" የሚሉ ቃላት ትርጓሜያቸው ምንድነው?*

መ. በቍጥር 22 (29) ላይ "ሁሉም" እና 24 (5፡15፣ 17፣ 6፡23) ላይ "ስጦታ" ለሚሉ ቃላት እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡

**የቃላት እና የሀረጎች ጥናት**

> 3፡21-26
> **አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፡፡ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፡፡**

**3፡21 "አሁን ግን"** ጳውሎስ በዝይህ ስፍራ ላይ አሮጌውን ኪዳን ከአዲሱ ኪዳን ጋር ያነጻጽረዋል፤ አሮጌውን የአመጽ ዘመን ከአዲሱ የጽድቅ ዘመን ጋር ያነጻጽራል፡፡ ስለዚይህ ይህ ከ"አሁኑ ዘመን" ጋር ትይዩ ነው (ቁጥር 26 "አሁን ግን" እና 6፡22. 7፡6)፡፡

▣ **"ያለ ሕግ"** በዚህ የመክፈቻ ምዕራፍ ላይ ጳውሎስ በዚህ ቃል የሙሴን ሕግ (ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል) ወይም ሕግን (ኒው ሪቭይዝድ ስታንዳርድ ቨረዥን፣ ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን፣ ኒው ጀሩሳሌም ባይብል፣ ኒው እንተረናሽናል ቨርዥን) እንደሚያመለከት በእርግጠኝነት መናገረኢ አይቻልም፡፡ በዚህ አውድ መሠረት ይህ ቃል የአይሁዳዊያንን ሕን ያመለክታል የሚለው ሀሳብ ከጳውሎስ የመከራከርያ ነጥብ ጋር ይስማማል፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ ማንኛውንም የግብረገናዊ ሕግጋትን፣ የማህበረሰቡን ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ መመሪያ ተላልፈዋል፡፡ በኀጢአትን እንደወደቀ ሰው ትልቁ ችግራችን ከራሳችን በስተቀር፣ ራስ ወደድ ከሆነ መሻታችን በስተቀር ምንም አይነት መመሪያ አለመፈለጋችን ነው፡፡ (ዘፍ 3)

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የእግዚአብሔር ጽድቅ"** |
| **ኒው ክንግ ጀምስ ቨርዥን፣ ኒው ርቫይዝድ ቨርዥን** | **"እግዚአብሔር ጽድቅ"** |
| **ቱደይስ እንግልሽ ቨርዥን** | **"እግዚአብሔር ሰዎችን ከራሱ ጋር በትክክለኛው መንገድ ለማስታረቅ ተጠቀመበት መንገድ"** |
| **ኒው ጀሩሳሌም ባይብል** | **"የእግዚአብሔር የሚያድን ፍትሕ"** |

"ዲያኮሶኒ" የሚለው ቃል እና ሪቢው (የ2፡13 ማብራሪያ ይመልከቱ) በዚህ አውድ ውስጥ ጠቀሜታን ብዙ ጊዜ ያመለክታሉ (1፡17፣3፡5፣ 21፣22፣ 25፣ 26፣ 4፡3፣ 5፣ 6፣9 11፣ 13፣ 22፣ 5፡17፣ 21፣ 6፡13፣ 16፣ 18< 19፣ 20፣ 8፡10፣ 9፡28፣ 30፣ 31፣ 10፡3፣4፣5፣6፣10፣ 17)፡፡ ይህ ቃል የመጣው ከብሉይ ኪዳን (ጻዴቅ) ከሚለው የግንባታ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ትርጓሜውም "መለኪያ" ወይም "መለኪያ በትር" ማለት ነው፡፡ መለኪያው እግዚአብሔር እራሱ ነው፡፡ ይህ ቃል ለሰው ለወደቁት የሰው ልጆች በነጻ በክርስቶስ የተሰጠውን እግዚአብሔርን ባሕርይ ነው (2ቆሮ 5፡21)፡፡ ራስ ወደድ እና ትምክተኛ ለሆነው ሰው ልጅ የሚያስፈልገውን በመገንዘብ እና እግዚአብሔርን ስጦታ አጥባቂ እና ኃይማኖተኛ ለሆነ ሰው፡፡ በ1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

▣ **"ተገልጦአል"** ይህ ቃል ከ1፡17 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን የግስ ልዩነት ግን አለው፡፡ እግዚአብሔር ወንጌልን በብሉይ ኪዳን (ምዕራፍ 4) እና በኢየሱስ በግልጽ ገልጦአል፡፡

▣ **"በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት"** ይህ የሚያመለክተው ከዕብራዊያን ሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍፍል (ሕግ፣ ነቢያት አና ጽሑፎች) ውስጥ ሁለቱን ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሁሉንም ያካትታሉ (በ3፡19 ላይ የተሰጠውን ማብራርያ ይመልከቱ)፡፡ ይህ በግልጽ እንደሚያሳየው ወንጌል በመጀመሪያ ደረጃ በብሉይ ኪዳን ውስጥ መካተቱን ነው (ሉቃ 24፡27፣ 44፣ የሐዋ 10፡43)፡፡ ይህ ከግዜ በኋላ የታሰበበት ሁለተኛ ዕቅድ ወይም የመጨረሻ ሰዓት በአጣብቅኝ ውስጥ ስኮን የታቀደ አይደለም (1፡2)፡፡

**3፡22 "በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን"** ይህ ሀረግ በገላ 2፡16 እና በፊል 3፡9 ላይ ተድግሟል እንዲሁም ከሮሜ 3ለ26፣ ገላ 2፡ 16፣ 20፣ 3፡22 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ (1) እምነት ዌኢም የኢየሱስ ታማኝነት ወይም (2) የምናምናው ነገር ኢየሱስን እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል፡፡ በገላ 2፡16 ላይ ያለው ተመሣሣይ ሰዋሰዋዊ ቀመር በተራ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰውን ይበልጥ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ጽድቅ ዋነኛ መለያውን ነው። ለአንድ ሰው በሕይወቱ አንድሰራ በክርስቶስ በኩል በምስጥ ነጻ ስጦታ የሚሠራ የክርስቶስ ጽድቅ ነው (4:5፣ 6:23)፤ ይህንን ጽድቅ ልንቀበል የሚንችለው በእምነት/በማመን ነው (ኤፌ 2:8-9) እንዲሁም በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ልንኖረው ይገባል (ኤፌ 2:10)።

▣ **"ለሁሉም"** ወንጌል ለሰው ልጆች ሁሉ ነው (ቁ፣ 24፣ ኢሳ 53:6 ሕዝ 18:23፣ ዮሐ 3:16-17፣ 4:42፣ 1ጢሞ 2:4፣ 4:10፣ ቲቶ 2:11፣ 2ጴጥ 3:9፣ 1ዮሐ 4:14)። ይህ ምንኛ ታላቅ እውነት ነው! ይህ ስለ ምርጫ ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ማመዛዘን አለበት። የእግዚአብሔር ምርጫ እንደ ሙስልሞች ውሳኔ መሆን የለበትም ወይም አጥባቂ ካልቬንስቶች እንደሚሉት ጥቀቶች ተመርጠዋል ሎሎች ግን አልተመረጡም እንደሚሉት መሆን የለበትም። የብሉይ ኪዳን ምርጫ ለአገልግሎት ነው ስለዝይህ እድል አይደለም! እግዚአብሔር በኀጢአት የወደቀውን የሰው ልጅን ለማዳን ቃል ገብቷል (ዘፍ 3:15)። እግዚአብሔር በእስራኤል አማካኝነት የሰው ልጆችን ሁሉ ጠርቷል እንድሁም መርጧል (ዘፍ 12:3፣ ዘጸ 19:5-6)። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመርጠው በክርስቶስ በማመናቸው ነው። እግዚአብሔር ዘወትር የድነት የመጀመሪያ መነሳሳቱን ይወስዳል (ዮሐ 6:44፣ 65)። ኤፌሶን 1 እና ሮሜ 9 በኦግስትን እና በካልቭን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው በቅድመ ውሳኔ አስተምህሮ ውስጥ ጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ናቸው።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለድነት ብቻ አይመርጣቸውም (መጽደቅ) ነገር ግን ለቅድስና (ኤፌ 1:4.ቆላ 1:12) ጭምር ነው። ይህ (1) በክርስቶስ ያለን ስፍራ (2ቆሮ 5:21 ወይም (2) እግዚአብሔር በልጆቹ ውስጥ የራሱን በህርይ ማባዛት መፈለጉን ሊያሳይ ይችላል (ሮሜ 8:28-29፣ ገላ 4:19፣ ኤፌ 2:10)። እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው እቅድ በምድር ላይ እርሱን እንድመስሉ እና በሰማይ ለወደፊት ከእርሱ ጋር እንድኖሩ ነው።

የቅድመ ውሳኔ ግብ ቅድስና እንጅ ጠቀሜታ አይደለም! የእግዚአብሔር ጥር ጥቅት የአዳም ልጆችን ለመምረጥ አይደለም ነገር ግን ሁሉንም ነው። ጥርውም ወደ እርሱ በሕርይ ነው (1ተሰ 5:23፣ 2ተሰ 2:13) የሰው ልጆች ስነመለኮታዊ አመላካከት አስገራሚው ነገር ይህንን የቅድመ ሁኔታን አስተምህሮ ከቅዱስ አኗኗርነት ወደ ስነመለኮታዊ ምህዋሮች መቀየሩ ነው። ብዙ ጊዜ ሥነ መለኮታዊ አመለካከታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎችን እንድናጣምም ያደርገናል።
ምርጫ/ቅድመ ውሳኔ እና ሥነ መለኮታዊ ማመዛዘን አስፈላጊነት የሚለውን ልዮ ርዕስ ተመልከት

**"ለሚያምኑ"** ኢየሱስ ሞተው ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፡፤ በመርህ ደረጃ ሁሉም ሰዎች ለመዳን ይችላሉ። የሰው ልጆች የግል ለመቀበል መፈለግ ነው የኢየሱስ ጽድቅን በሕይወታቸው የሚተገበር የሚያደረገው (1:16፣ ዮሐ 1:12፣ 3:16፣ 20:31 ሮሜ 10:9-13፣ 1ዮሐ 5:13)። መጽሐፍ ቅዱስኢ ስለሚንካፈለው ጽድቅ ሁለት ዓይነት መስፈት ያስቀምጣል። ይሄውም እምነት እአ ንሰሓ ነው (ማር 1:15፣ የሐዋ 3:16፣ 19፣ 2:31 እና 1:5 ማብራርያ ተመልከቱ)። ይህ ጥቅስ የድነትን ኣለማቀፋዊ ገጽታ ያስረዳል ነገር ግን ሁሉም ሰዎች አይድኑም።

▣ **"ልዩነት የለምና፤"** ሰዎች (አይሁዳዊያንም ሆኑ አሕዛቦች) የሚድኑበት አንድ ብቻ መንገድ እና ሰው አለ (ዮሐ 10:1-2፣ 7፣ 11:25፣ 14:6)። ማንም ሰው እና ሁሉም ሰው በኢየሱስ በማመን መዳን ይችላል (1፤16፣ 4:11፣ 16፣ 10:4፣ 12፣ ገላ 3:28፣ ቆላ 3:11)።

3:23-26 ይህ በግሪክ አንድ አረፍተ ነገር ነው

3:23
**አአመመቅ**
**አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም**
**ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** "ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋል እንዲሁም ጎድለዋል"
**ቱደይስ ኢንግለሽ ቨርዥን** "ሰዎች ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋል እንዲሁም ርቀዋል"
**ኢመቅ**"ኀጢአት ሠርተዋል እንዲሁም ርቀዋል"

ይህ 1:18-3:20 ማጠቃለያ ነው። ሁሉም ሰው በክርስቶስ መዳን አለበት (3:9፣ 19፣ ገላ 3:22፣ ኢሳ 53:6)። ይህ ሀረግ ምንአልባትም የሰው ልጆች በአጠቃላኢ በአዳም ውስጥ ወድቀው ልሆን ይችላል (5:122-21) እንዲሁም በቀጣይነት እያንዳንዱ በሕይወቱ የሚያደርገው ደግሞ አመጽ ልሆን ይችላል። በዘመናችን የሚገኙ የትኞቹም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ልዩነት አጉልተው አያሳዩም። ይነት እያንዳንዱ በሕይወቱ የሚያደርገው ደግሞ አመጽ ልሆን ይችላል። በዘመናችን የሚገኙ የትኞቹም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ልዩነት አጉልተው አያሳዩም።
ይህ ቁጥር ሥነ መለኮታዊ ቁርኝቱ ከቁጥር 21 ጋር እንጂ ከቁጥር 24 ጋር አይደለም።

▣ **"የእግዚአብሔር ክብር"** በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለው ቃል "ካቦድ" በመጀመሪያ የንግድ ቋንቋ ነበር (የሚያመለተውም ጥንዲያ መልክያዎችን ነበር) ትርጓሜውም ከባድ ማለተ ነው። ይህ ከባድ ሆነው ነገር ጠቃም ወይም አስፈላጊ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ግርማ ለማመልከት ብዙ ጊዜ ብርሃን ቃሉ

ጋር ተጨምሮበት ይገኛል (ዘጽ 19፡16-18፣ 24፡17፣ ኢሳ 60፡1-2)። የሰው ልጆች ልያውቁት ከሚችሉት በላይ ጠብብ ነው (ዘጸ 33፡17-23፣ ኢሳ 6፡5) እግዚአብሔር በእውነት ልታወቅ የሚችለው በክርቶስ በኩል ብቻ ነው (ኤር 1፡14፣ ማቴ 17፡ 2፣ ዕብ 1፡3፣ ያዕ 2፡1)።

"ክበር" የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ አሻሚ ቃለ ነው። (1) "ከእግዚአበብሔር ጽድቅ" ጋር ትይዩ ትርጉም ልኖረው ይችላል (ቁ. 21)፤ (2) እግዚአብሔር ማረጋገጥ ሊያመለክት ይችላል (ዮሐ 12፡43) (3) የሰው ልጆች የበመጀመሪያ ተፈጠሩበትን ነገር ግን በኂለ በአመጻቸው ምክንያት ያበላሹት(ዘፍ 3፡1-22) እግዚአብሔርን መልክ ሊያመለክት ይችላል (ዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፣ 9፡6)። ነገር ግን ይህ የተበላሸው በክርስቶስ በኩል ታድሷል (2ቆሮ 3፡18) ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ አገልግሎት ላይ የዋለው የያህዌን ከሕዝቡ ጋር መገኘት ለማመልከት ነው (ዘጸ 16፡7፣ ዘለ 9፡23፣ ዘዳ 14፡10)። አሁንም ግቡ ይህ ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ ክብር**

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብር ትርጓሜን ለመስጠት ያስቸግራል። የአማኞቸደ ክብር ወንጌልን ይረዱት ዘንድ እና እራሳቸውን ሳኢሆን በእግዚአብሔር ክብር እንድሰማቸው ነው (1፡29-31፣ ኤር 9፡23-24)።

"የእግዚአብሔር ክብር" በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለው ቃል "ካቦድ" በመጀመሪያ የንግድ ቋንቋ ነበር (የሚያመለተውም ጥንዲያ መልክያዎችን ነበር) ትርጓሜውም ከባድ ማለተ ነው። ይህ ከባድ ሆነው ነገር ጠቃም ወይም አስፈላጊ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ግርማ ለማመልከት ብዙ ጊዜ ብርሃን ቃሉ ጋር ተጨምሮበት ይገኛል (ዘጽ 19፡16-18፣ 24፡17፣ ኢሳ 60፡1-2)። የሰው ልጆች ልያውቁት ከሚችሉት በላይ ጠብብ ነው (ዘጸ 33፡17-23፣ ኢሳ 6፡5) ያህዌ በእውነት ልታወቅ የሚችለው በክርቶስ በኩል ብቻ ነው (ኤር 1፡14፣ ማቴ 17፡2፣ ዕብ 1፡3፣ ያዕ 2፡1)።

"ክበር" የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ አሻሚ ቃለ ነው። (1) "ከእግዚአበብሔር ጽድቅ" ጋር ትይዩ ትርጉም ልኖረው ይችላል (ቁ. 21)፤ (2) እግዚአብሔር ማረጋገጥ ሊያመለክት ይችላል (ዮሐ 12፡43) (3) የሰው ልጆች የበመጀመሪያ ተፈጠሩበትን ነገር ግን በኂለ በአመጻቸው ምክንያት ያበላሹት(ዘፍ 3፡1-22) እግዚአብሔርን መልክ ሊያመለክት ይችላል (ዘፍ 1፡26-27፣ 5፡1፣ 9፡6)። ነገር ግን ይህ የተበላሸው በክርስቶስ በኩል ታድሷል (2ቆሮ 3፡18) ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ አገልግሎት ላይ የዋለው የያህዌን ከሕዝቡ ጋር መገኘት ለማመልከት ነው (ዘጸ 16፡7፣ ዘለ 9፡23፣ ዘዳ 14፡10)።

3፡24 **"በጸጋው ይጸድቃሉ።"** እዚይህ ጋ ነው አንግዲህ ወንጌል ፤ ጽድቅን የሚሰጠው የእግዚአብሔር ጸጋ የሚጀምረው (5፡15-17፣ 6፡23)። "መጽደቅ" የሚለው የግሪካል "ጽድቅ" ከሚለው ቃል ጋር አንድ አይነት ሥረወ ግንድ አላቸው። እግዚአብሔር ዘወትር መነሻ ምክንያቱን ይወስዳል (ዮሐ 6፡44፣ 65)።

በቁጥር 24-25 ውስጥ ድነተን ለማብራራት ሦስት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጥቅም ላይ ውለዋል፦ (1) **"ይጸድቃሉ"** ይህ ቃል የሕግ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም "አይቀጣም" ወይም ጥፋተኛ አይደለህም ብሎ መናገር ማለት ነው (2) **"ቤዛነት"** ይህ ቃል ተገኘው ከባሪያ ንግድ ገቢያ ሲሆን ትርጓሜውም "ማስመለስ" ወይም 'ነጻ ማውጣት" ማለት ነው እና (3) "ማስተሰረያ" ይህ ቃል ተገኘው ከመስዋዕት ስርኣት ውስጥ ስሆን ትርጓሜውም መሸፈኛ ቦታ ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ መስዋዕት በምቀርብበት እለት የመስዋዕት ደን የሚቀመትበት ስፍራ ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ ስለ አንድ ሰው መዳን የአዲስ ኪዳን ማረጋገጫ ድነት**

1. የአብ ባሕርይ (ዮሐ 3፡16)፣ የወልድ ሥራ (2ቆሮ 5፡21) እና የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው (ሮሜ 8፡14-16) እንጂ የሰው ልጅ ሥራ፣ የመታዘዝ ዋጋ፣ አዋጅ አይደለም።
2. ስጦታ ነው (ሮሜ 3፡24፣ 6፡23፣ ኤፌ 2፡5፣ 8-9)
3. ይህ አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ንጽረተ አለም ነው (ያዕቆብ እና 1ዮሐንስ)
4. ይህ እውቀት (የወንጌል)፣ ሕብረት (በእምነት እና ከኢየሱስ ጋር) እና አዲስ አኗኗር (በመንፈስ የመመራት ክርስቶስን የመመስል) ነው። እነዚይህን ሦስቱን ያካተተ እንጂ ከእነዚይህ አንዱን ብቻ አይደለም።

▣ "ስጦታ" ጳውሎስ ይህንንነ ሀሳብ በተለያዩ ቃላት ብዙ ጊዜ ገልጾታል

1. ዶርአን (ገላጭ) "በነጻ"
2. ዶራ (ስም) "ነጻ ስጦታ"
3. ዶሮን (ስም) "ስጦታ" (ኤፌሶን 2፡8)
4. ካርዝማ (ስም) "ነጻ ስጦታ" ወይም "ነጻ እድል" (1፡11፣ 5፡15፣16፣ 6፡23፣ 11፡29፣ 12፡6)
5. ካርዞማይ (ግሥ) "ነጻ እድልን ማረጋገጥ" (8፡23)
6. ካሪስ (ስም) "ነጻ አድል" ወይም "ነጻ ስጦታ" (4፡4፣ 16፣ 11፡5፣6፣ ኤፌ 5፡8)

▣ **"በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት"** ድነትን ያገኘንበት መንገድ ኢየሱስ ስ እኛ ድነት በእኛ ፈንታ ሞቶ በመነሳቱ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዝይህ ነገር አጽኖት ሰጥቶ የሚነግረን ምን ያህል ተከፈለልን ወይም ለማን ተከፈለ ሳይሆን የሰው ልጆች ከበደለኝነት ነጻ የመውጣታቸውን እውነታ እና ነጻ የውጡበትም መንገድ ንጹህ የሆነ ምትክ በእነርሱ ፈንታ ቅጣታቸውን ስለተቀበለ ነው (ዮሐ 1፡29፣ 36፣ 2ቆሮ 5፡21፣ 1ጴጥ 1፡19)

በተጨማሪም ይህ ቁጥር ዘፍ 3፡15 ምን ያህል ውድ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ኢየሱስ የሰዎችን ኀጢአት ተሸክሟል (ገላ 3፡ 13) እና የሰው ልጆችን ተክቶ ሞቷል (2ቆሮ 5፡21)፡፡ ድነት ነጻ ልሆን ይችላል ነገር ግን በእርግጠኝነት የተገዛው ግን ርካሽ በሆነ ነገር አይደለም፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ቤዛ/መዋጃ**

1. ብሉይ ኪዳን
   - ሀ. ይህንን ሀሳብ የሚገልጹ ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት አሉ
     1) "ጎል" መሠረታዊ ትርጓሜው በተከፈለ ዋጋ "ነጻ መውጣት" ማለት ነው፡፡ ጎል የሚለው ቃል ይዘት በሃሰቡ ላይ አንድ ነገርን ይጨምራል ፤ ይሄውም የግል አማላጅ፣ መካከለኛ የሚሆኦን ሰውን፤ ይህ ብዙ ጊዜ የቤተሰብ አበል ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ባሕላዊ ገጽታ አንድን እቃ፣ እንስሳ፣ መሬት መልሶ ለመግዘት ያለን መብት (ዘለ 25፡27) ወይም ዘመድ (ሩት 4፡15፣ ኢሳ 29፡22)፤ እንዲሁም ይህ ቃል ያህዌ እስራኤላዊያን ከግብጽ ምድር ሳወጣበትም ጥቅም ላይ ውሏል (ዘጸ 6፡6፣ 15፡13፣ መዝ 74፡2፣ 77፣ 15፣ ኤር 31፡11)፡፡ እርሱ ተቤዣቸው (ያዕ 19፡25፣ መዝ 19፡14፣ 78>35፣ ምሳ 23፡1፣ ኢሳ 41፡14፣ 43፡14፣ 44፡6፣24፣ 47፡4፣ 48፡17፣ 49፡7፣ 26፣ 54፤ 5፣8፣ 59<20፣ 60፡16፣ ኤር 50፡34)
     2) "ባዳህ" ይህ "ማስወጣ" ወይም "መታደግ" የሚል መሠረታዊ ትርጉም አለው፡፡
        - ሀ. የበኩር ልጅ መዋጀት ዘጸ 13፡13፣ 14 እና ዘኍ 18፡15-17
        - ለ. መንፈሳዊ መዋጀት ከሥጋዊ መዋጀት ጋር ስነጻጸር መዝ 49፡7፣8፣15
        - ሐ. ያህዌ እስራኤላዊያንን ከኀጢአትን እና ከአመጻ ዋጅቷቸዋል መዝ 130፡7-8
   - ለ. በእነዚይህ ሶስት ቃለት ዙርያ የሚሽከረከር ሥነ መለኮታዊ ሀሳብ
     1) እስር መኖር አለበት
        - ሀ. አካላዊ
        - ለ. ማህበረሰባዊ
        - ሐ. መንፈሳዊ (መዝ 130፡8)
     2) ለመለቀቀ፣ ለመዋጀት እና ለመታደስ ዋጋ መከፈል አለበት
        - ሀ. ለእስራኤላዊያን (ዘዳ 7፡8)
        - ለ. ለግለሰቦች (ያዕ 19፡25-27፣ 33፡28)
     3) አንድ ሰዉ መካከለኛ መሆን አለበት፡፡ ይህ ሰው የቅርብ ሰው ወይም ቤዘመድ መሆን አለበት፡፡
     4) ያህዌ ብዙ ጊዜ እራሱን እንደ ቤተዘመድ ያቀርባል፡፡
        - ሀ. አባት
        - ለ. ባል
        - ሐ. የቅርብ ወዳጅ

ቤዛነት የሚረጋገጠው በያህዌ በምልከው አስፈጻም ነው፣ ዋጋው ተከፍሏል እናም መዋጀቱም ፍጻሜን አግኝቷል፡፡

2. አዲስ ኪዳን
   - ሀ. ይህንን ሥነ መለኮታዊ ቃል ለመግለጽ ብዙ ቃላት በአገልግሎት ላይ ውለዋል
     1) አጎራዞ (1ቆሮ 6፡20፣ 7፡23፣ 2ጴጥ 2፡1፣ ራዕ 5፡9፣14፡34)፡፡ ይህ ለአንድ ነገር የተከፈለ ዋጋን የሚያመለክት የንግድ ቋንቋ ነው፡፡ እኛ በደም የተገዛን ሕዝቦች ነን ስለዚይህም ሕይወታችንን አንቆጣጠርም ፡፡ እኛ የክርስቶስን ነን፡፡
     2) ኤክአርጎማዞ (ገላ 3፡13፣ 4፡5፣ ኤፌ 5፡16፣ ቆላ 4፡5)፡፡ ይህም ንግድ ቋንቋ ነው፡፡ የኢየሱስን በእኛ ፈንታ መሞትን ያንጸባርቃል፡፡ ድርግት የሚጠይቀውን የህግን እርግማን ኢየሱስ ስለ እኛ ተሸክሟል (የሙሴ ሕግን) ይህንን በኀጢአት ወደቁ ሰው ልጆች ሊያደረጉት አይችሉም፡፡ ለሁላችን መርገምን ተሸክሟል (ዘዳ 21፡13) በኢየሱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር እና ፍትሕ በመዋሃድ ይቅርታን፣ መቀበልን እና እድልን አገኘን፡፡
     3) ሉኦ "መልቀቅ"
        - ሀ. ሉተሮን "የተከፈለ ዋጋ" (ማቴ 20፡28፣ ማር 10፡45)፡፡ ከኢየሱስ አንደበት ወደዚህች ምድር ስለ መጣበት ዓላማ አንድ በጣም ኀይለኛ ቃል ወጥቷል፣ እርሱ የሌለበትን ነገር ግን የዓለምን ኀጢአት የኀጢአትን ዋጋ በመክፈል ሊያስወግድ መጥቷል፡፡ (ዮሐ 1፡29)
        - ለ. ሉተሮ "መልቀቅ"
          1) እስራኤልን መዋጀት ሉቃ 24፡21
          2) ሕዝቡን ለመዋጀት እና ለማንጻት እራሱን መስጠት ቲቶ 2፤14
          3) ኀጢአት የሌለበት ምትክ መሆን 1ጴጥ 1፡18-19

ሐ. ሉተሮሲስ "መዋጀት፣ ነጻ መውጣት፣ ነጻነት"

1) ዘካርያስ ስለ ኢየሱስ ትንብዮያል ሉቃ 1፡68
2) ሐና ስለ ኢየሱስ እግዚአብሔርን አመስግናለች ሉቃ 2፡38
3) ኢየሱስ አንድ ጊዜ የተሻለ መስዋዕትን አቅርቧል ዕብ 9፡12
4) አፖሌተሮሲስ
   ሀ. በዳግም ምጻት ጊዜ መዋጀትን (የሐዋ 3፡19-21)
      (1) ሉቃ 21፡28
      (2) ሮሜ ፡23
      (3) ኤፌ 1፡14፣ 4፡30
      (4) ዕብ 9፡15
   ለ. በክርስቶስ ሞት መዋጀት
      (1) ሮሜ 3፡24
      (2) 1ቆሮ 1፡30
      (3) ኤፌ 1፡7
      (4) ቆላ 1፡14
5) አንቲለይሮን (1ጢሞ 2፡6)። ይህ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው (ቲቶ 2፡14) ይህ ከኢየሱስ የምትክነት ሞት ጋር ተያያዥነት ያለው ክፍል ነው። ለሰዎች ሁሉ የመተው እርሱ ብቸኛ እና ተቀባይነት ያለው መስዋእት ነው
   (ዮሐ 1፡29፣ 3፡16-17፣ 4፡42፣ 1ጢሞ 2፡4፣4፡10፣ቲቶ 2፡11፣ 2ጸጥ 3፡9፣ 1ዮሐ 2፡2፣4፡14)።
   ለ. በዝይህ ቃል የተገለጸው ሥነ መለኮታዊ ሀሳብ
      1) የሰው ልኦጆች ለኀጢአት ባሮች ናቸው (ዮሐ 8፡34፣ ሮሜ 3፡10-18፣ 6፡23)
      2) የሰው ልጅ በኀጢአት ባርነት ሥር የመሆናቸው እውነተ በሙሴ ሕግ ወደ ገሀድ ወጥቷል። (ገላ 3) እንዲሁም ይህ በኢየሱስ የተራረው ስበከት ላይ ተገልጿል (ማቴ 5-7)። የሰው ልጆች ሥራ የሚመራቸው ወደ ሞት ነው (ቆላ 2፡14)።
      3) ኀጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ በእኛ ፈንታ ሞቷል። (ዮሐ 1፡29፣ 2ቆሮ 5፡21)። እግዚአብሔርን ለማገልገል ከኀጢአት ተዋጅተናል (ሮሜ 6)።
      4) ይህ በተዘዋዋር የሚነግረን ሁለቱም ያህዌ እና ኢየሱስ ለእኛበእኛ ፈንታ የሚሠሩ የቅርብ ዘመዶች ናቸው። ይህ ቀጣይነት ያለው የቤተሰብ ምስሌ ነው። (ይህ ማለት አባት፣ ባል፣ ልጅ፣ ወንድም፣ የቅርብ ዘመድ)።
      5) የቤዛነት ክፍያ የተከፈለው ለሴጣን አይደለም (ሜድቫል ሥነ መለኮት) ነገር ግን ቤዛነት የእግዚአብሔርን ቃል እና ፍትሕን ከእግዚአብሔር ፍቅር እና ከክርስቶስ የድነት ስጦታ ጋር ማስታረቅ ነው። በመስቀል ሠላም ወርዷል፣ የሰው ልጆች አመጽ ይቅር ተብሏል፣ በመጀመሪያው ህብረት የእግዚአብሔር መልክ በሙላት መሥራት ይጀምራል፡፤

እንዲሁም የመዋጀት የወደፊት ሁኔታ አለ (ሮሜ 8፡23፣ ኤፌ 1፡14፣ 4፡30) ይህ የእኛን የትንሳኤን አካል መልበስን የሚያካትት እና ከአሃዱ ስለሱስ አማለክ ጋር የጠበቀ ግንኙነትን የሚያካትቱ ናቸው።

3፡25

**ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል** "እርሱንም እግዚአብሔር በአደባባይ አቆመው"
**አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** "እርሱንም እግዚአብሔር አቆመው"
**ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** "እግዚአብሔር ያቀረበው"
**ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** "እግዚአብሔር አዘጋጀው"
**ጀሩሳሉም ባይብል** "በእግዚአብሔር የተወሰነው"

ይህ ማለት እግዚአብሔር እራሱ ልቡን እና አለማውን በኢየሱስ ሞት በኩል ገልጧል (ኤፌ 1፡9) የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ኢየሱስን የመስዋእት ሞት ያካተተ ነበር (ኢሳ 53፡10፣ ራዕ 13፡8)። በ9፡11 ላይ የለውን ማብራርያ ይመልከቱ

ኢንድካኖማይ የሚለው የግሪክ ቃል በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ በብዙ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል (2፡15፣ 9፡17፣ 23፣ በሰባ ልቃናት መጽሐፍ ቅዱስ በዘጸ 9፡16)። የዚህ ቃል መሠረታዊ ትርጉሙ መግለጥ ወይም ግልጥ ማድረግ ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰው ልጆች የእርሱን የማዳን ዓላማ፣ እቅድ እና ጽድቅ በግልጽ እንዲያውቁ ይፈልጋል። ይህ አውድ የመጽሐፍ ቅዱስን ንጽረተ ዓለም ያሳያል

1) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ

2) ስለ ክርስቶስ ሥራ
3) ስለ ሰው ልጆች የሚያስፈልጋቸው ነገር
4) ስለ ድነት ዓላማ

እግዚአብሔር እኛ እንድንረዳ ይፈልጋል! ይህ አውድ ክርስትናን በትክክል እንድንረዳ በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ቃላት እና ሀረጎች ግራ የሚያጋቡ ወይም በተለያዩ መንገዶች ልንረዳቸው እንችላለን ነገር ግን ሁሉንም ማመን ግልጽ ነው። ይህ አውድ የአዲስ ኪዳን የሥነ መለኮት የሰሜን ኮከብ ነው።

▣

| | |
|---|---|
| **ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል** | **"በደሙ እንደሚሆን ማስተሰሪያ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በደሙ የሚሆን ማስተሰሪያ"** |
| **ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | **"በደሙ እንደ የስርዔት መስዋእት"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"በደሙ የሰዎች ኀጢአት ይቅር የሚባልበት እንድሆን፡"** |
| **ጀሩሳሌም ባይብል** | **"ሕይወቱን መስዋዕት ያደረግ ዘንድ በዚህም የማስታረቅን ሥራ ይሠራ ዘንድ ነው"** |

በግሪኮ-ሮማን ዓለም ይህ ቃል ከእንግዳ አማልክት ጋር ያለን ግንኙነት ዋጋን በመክፍል እንደገና የማደስ ሀሳብን በውስጡ ያዘለ ነው ነገር ግን በሰባ ልቃነት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ይህ ሀሳብ አይገኝም፡፤ በሰባ ልቃናት እና በዕብራዊያን መጽሐፍ ውስጥ ይህ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው "የምህርት ወንበር" ማለትም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ያለው የቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ለሀገር መስዋዕት በምቀርብበት ዕለት መስዋእቱ የሚቀመጥበት ሥፍራ ነው (ዘለ 16)።
ይህ ቃል እግዚአብሔር ኀጢአተን ምን ያህል እንደሚጠላ በሚያሳይ መልኩ በጥንቃቄ ልጠና ይገባል ነገር ግን ኀጢአተኛውን ለማዳን እንደሚፈልግም ከግምት ውስጥ ልገባ ይገባዋል። ስለዝይህ ነገር ጥሩ የሆነ ዳሰሳ ጀምስ ስትዋርት በተባለ ሰው "በክርስቶስ ያለ ሰው" በተባለ መጽሐፋቸው ተቀምጧል ገጽ 214-224።

▣ **"በደሙ"** የሚለው ቃል የዕብራዊያን አስተሳሰብ አንድምታ ያለው እና ንጹህ ሆነው እግዚአብሔር በግ የሚትክነት መስዋዕት መሆኑን የሚያመለክት ነው (ዮሐ 1፡29) ይህንን ሀሳብ በትክክል ለመረዳት ዘለ 1-7 አስፈላጊ ነው፤ በተጨማሪም በምዕራፍ 16 ላይ ያለው የመስወዕት ቀንን ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል። ደም በደለኛ ለሆነ ሰው ተከፈለ ኀጢአት የለለውን ሕይወትን ያመለክታል 9ኢሳ 52፡13-53፡12)።

▣ **"በእምነት"** ይህ እንደገና በክርስቶስ የምትክ ሞት ምክንያት ተገኘውን አመች ሁኔታ ለማግኘት ተዘጋጀ መንገድ ነው። (1፡17፣ 3፡22፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 30)።

▣ **"ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው"** እግዚአብሔር ለባሕርይው እና ለቃሉ እውነተኛ መሆን አለበት (ሚል 3፡6)። በብሉይ ኪዳን ኀጢአትን የሚትሠራ ነፍስ እንደሚትጠፋ ይናገራል (ሕዝ 18፡4፣20)። እግዚአብሔር ለበደለኛው እንደማይራራይ ይናገራል (ዘጸ 23፡7)። እግዚአብሔር በኀጢአት ለወደቀው የሰው ልጅ ያለው ፍቅር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ እርሱ ራሱ ሰው ለመሆን ፍቃደኛ ሆነ፣ ሕግንም ፈጸመ እንዲሁም በሰው ልጆች ፈንታ ሞተ። ፍቅር እና ፍትሕ በኢየሱሰስ ውስጥ ተገናኙ (ቁ.26)።

▣

**ኒው ስታንዳር ባይብል**

| | |
|---|---|
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በፊት የተደረገውን ኀጢአቶች ተዋቸው"** |
| **ቱደይስ ኢንግልሽ ቨርዥን** | **"ባለፉት ዘመን እርሱ ትእግስተኛ በመሆን የሰዎችን ኀጢአት ቸል ብሏል"** |
| **ኒው ጀሩሳሌም ባይብል** | **"ባለፉት ዘመናት ኀጢአት ሳይቀጣ ኖሯል"** |

"የተተወ" የሚለው ቃል ትርጓሜ ያለው የግሪክ ቃል "ፓሪሲስ" ሲሆን ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በአዲስ ክዳን ውስጥ ብቻ እንጂ በሰባ ልቃናት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይደለም። ግሪካዊያን አባቶች እና ጀሮም የዚህን ቃል ቀጥተኛ ትርጉም "የዕዳ ይቅርታ" ወስደዋል። ነገር ግን ቃሉ በግሥ መልክ የምኖረው ትርጓሜ "እንዲያል ማድረግ" ወይም "መፍታት" ማለት ነው (ሉቃ 11፡42)።

ስለዚይህ ጥያቄው እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ኢየሱስን ወደ ፊት እየተመለከተ ኀጢአትን ይቅር ብሏል ወይስ የኀጢአትን ችግር የኢየሱስ ሞት እንደሚፈታው በማወቅ እንዲሁ ቸል ብሎታል? ውጠቱ ተመሳሰይ ነው። የሰው ልጆች የአሁንም፣ ያለፈውም፣ የወደፊቱም የኀጢአት ችግር መፍትሔን የሚያገኘው በክርስቶስ መስዋዕትነት ነው።

ይህ የክርስቶስን ሥራ አስቀድሞ የተመለከተ የእግዚአብሔር የጸጋ ድርግት ነው (የሐዋ 17፡30፣ ሮሜ 4፡15፣ 15፡13) እንዲሁም የአሁኑን እና የወደፊቱን (26)። እግዚአብሔር ኀጢአተን ቀላል አድርጎ ተመልክቶት አያውቅም ለወደፊትም አይመለከትም ነገር ግን የሰው ልጆችን አመጽ እና ከእርሱ ጋር ለዘላለም ህብረት እንዳያደርጉ እንቅፋት እየሆነ ያስቸገረውን ነገር ለማስወገድ የኢየሱስን መስዋዕትነት ሙሉ እና የመጨረሻው መፊትሄ አድርጎ ተቀብሎታል።

3፡27-30
**ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፥ የተገረዘን ስለ እምነት ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለ ሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው።**

3፡26 በቁ. 25 ላይ "ጽድቅ" የሚለው ቃል በሥረወ ግንዱ ከ"ጻድቅ" እና "የሚያጸድቅ" ከሚለው ቃል ጋር ግንኙነት አለው። እግዚአብሔር የእርሱ ባሕርይ በአማኞች ሕይወት ውስጥ በክርስቶስ በማመን እንድጸባረቅ ይፈልጋል። ኢየሱስ ለእኛ ጽድቃችን ሆኗል (2ቆሮ 5፡21) ነገር ግን አማኞች ወደ እርሱ ጽድቅ እና መልክ ግን መለወጥ አለባቸው (ሮሜ 2፡8-9)። በ1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

3፡27 "ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው?" ይህ የሚያለክተው አይሁዳውያን ትምክት ነው (2፡17፣ 23)። ወንጌል እራሳችንን ዝቅ ዝቅ እንድናደረግ ያደርገናል። በኀጢአት የወደቁት የሰው ልጆች (አይሁዳዊያንም ይሁኑ አሕዛቦች) እራሳቸውን መርዳት አልቻሉም (ኤፌ 2፡8-9)። በትምክት ላይ በ2፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ

▣ "እርሱ ቀርቷል" ይህ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው በዚህ ስፍራ እና በገላ 4፡17 ላይ ብቻ ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙም "መተው" ማለት ነው"

▣ "በእምነት ሕግ" በሕዝ 31፡31-34 ላኢ ተገለጸው የእግዚአብሔር አዲስ ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገው በእኛ ተግባር ላይአይደለም ነገር ግን በእኛ  በእርሱ ጸጋ እና የተስፋ ቃል ላይ ባለን እምነት፣ መታመን፣ ማመን (ፒስቲስ)።  አሮጌው እና አዲሱ ኪዳን ሁለቱም አላማቸው የወደቀውን የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ባሕርይ (ጽድቅ) የመቀየር አላማ ነበራቸው። አሮጌው በውጫው ሕግ፤ አዲሱ ደግሞ በአዲስ ልብ (ሕዝ 36፡26-27)። ግቡ ግን አንድ ነው!

3፡28 "ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና።" ይህ 3፡21-26 ማጠቃለያ ነው እንዲሁም ከምዕራፍ 4-8 ላለው ክፍል መንደርደርያ ነው (2ጢሞ 1፡9፣ ቲቶ 3፡5)። ድነት ባለቀው የኢየሱስ ሥራ በማመን የሚገኝ ነጻ ስጦታ ነው(3፡24፣ 5፤15፣ 17፣ 6፡23፣ ኤፌ 2፡8-9)። ነገር ግን መብሰል ግን "ብዙ ዋጋ የስከፍላል" የሕይወት መታዘዝን፣ አገልግሎትን እና አምልኮን (ገላ 5፡6፣ ኤፌ 2፡10፣ ፊል 2፡12 እና በ1፡5 ላይ ያለውን ማብራርያ ተመልከት)፡፤

3፡29 የእግዚአብሔር የዘወትር አላማው በእርሱ መልክ የተፈጠሩትን የሰው ልጆች መታደግ ነው (ዘፍ 1፡26፣ 5፡1፣ 9፡6)። በ3፡15 ላይ ቃል ተገባው የመዋጀት የተስፋ ቃል ለሰው ልጆች ሁሉ ነው። አለምን ለመምረጥ አብረሃምንም መረጠው (ዘፍ 12፡31፣ ዘጸ 19፡4-6፣ ዮሐ 3፡16)።

ይህ እንደ 3፡9 ሁሉ በኤሮ አዋጅ ምክንያት ሮምን ለቀው በሄዱ አይሁዳዊያን መሪዎች እና በኔሮ አዋጅ ምክንያት የቤተክርስቲያን መሪነት በተቀበሉት አሕዛብ መሪዎች መካከል የነበረን ግጭት ሊያመለክት ይችላል። ምዕራፍ 9-11 ይህንን ውጥረት ይዳስሳል፡"

3፡30

| | |
|---|---|
| **ኒው አሜርካን ስታንዳር ባይብል** | "በእርግጥ እግዚአብሔር አንድ ሰለ ሆነ" |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | "በእርግጥ አንድ አምካል ስላለ" |
| **ኒው ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን** | "በእርግጥ እግዚአብሔር አንድ ነው" |
| **ቱደይስ ኢንግለሽ ቨርዥን** | "እግዚአብሔር አንድ ነው" |
| **ጀሩሳሌም ባይብል** | "በእርግጥ አንድ ብቸኛ አምላክ ስለለ" |

አንድ አምላክነት እውነት ከሆነ እርሱ እግዚአብሔር ነው (ዘጸ 8፡10፣ 9፡14፣ ዘዳ 4፡35፣ 39፣ 6፡4፣ 1ሳሙ 2ለ2፣ 2ሳሙ 7፡22፣ 22፡32፣ 1ነገ 8፡23፣ መዝ 86፡8፣ 10፣ ኢሳ 43፡11፣ 44፡6፣8፣ 45፡6-7፣ 14፣ 18፣ 21-22፣ 46፡5፣9፣ ኤር 2፡11፣ 5፡7፣ 10፡6፣ 16፡20) ሲለዝይህም እርሱ የሁሉ አምላክ ነው፡፤

▣ "የተገረዙትን በእምነት ያጸድቃል' "መጽደቅ" የሚለው ቃል ሥረወ ግንድ "ጽድቅ" ከሚለው ቃል ሥረወ ግንድ ጋረ ተመሣሣይ ነው። 1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት። ከእግዚአብሔር ጋር በትክክለኛው መንገድ ለመገናኘት አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለው (ሮሜ 9፡30-32) ለድነት ሁለቱ መስፈርቶች እምነት እና ንሰሓ ናቸው (ማር 1፡15፣ የሐዋ 3፡ 26፣ 10፣ 20፡21)። ይሁ ለሁለቱም ለአይሁዳዊያንም ሆነ ለአሕዛብ እውነት ነው፡፤

▣ "በእምነት . . በእምነት" በእነዚህ ሁለቱ ሀረጎች መካከል ግልጽ የሆነ ንጽጽር አለ። ሁለቱም "በ" የሚል መስተዋደድን ተጠቅመዋል። በእርግጥም ምንም ልዩነት የላቸውም።

3፡31 እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።

3:31

| | |
|---|---|
| ኒው አሜርካን ስታንዳርድ ባይብል | "እንግዲህ በእምነት ሕግን ባዶ እናደርጋለንን?" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "እንግዲህ በእምነት ሕግን እንሽራለንን?" |
| ኒው ሪቫይዝ ስታንዳርድ ቨርዥን | "እንግዲህ በዚህ እምነት ሕግን እናስቀራለንን?" |
| ቱደይስ ኢንግለሽ ቨርዥን | "ይህ ማለት በዚህ እምነት ከሕግ ጋር ያለነግ ግንኙነት ያበቃል ማለት ነውን?" |
| ጀሩሳሌም ባይብል | "እምነት ሕግን ጥቅም አልባ ያደርገዋል ማለት ነውን?" |

አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን በሁለት መንገድ ይገልጸዋል፡

1) የእግዚአብሔር እስትነስፋስ ያለበት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰጠው መገለጥ የሚወገድ አይደለም (ማቴ 5:17-19፣ ሮሜ 7:12፣ 14፣ 16)
2) ይህ አብቅቷል እነዲሁም አልፏል (ዕብ 8:13)

ጳውሎስ "ማስወገድ" የሚለው ቃል በያንስ 25 ጊዜ ተጠቅሞታል፡፡ ይህም ቃል "ባዶ ማድረግ"፣ "ኃይል ማሳጣት" እና "ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ በ3:3 ላይ የቀረበውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡ ለጳውሎስ ሕግ ሞግዝት ነው (ገላ 3:23) እና የሚያስለጥን ነው (ገላ 3:24) ነገር ግን ዘላለማወዊ ሕይወትን ግን የሚሰጥ አይደለም (ገላ 2:16፣ 19፣ 3:19)፡፡ ሕግ የሰው ልጅ ኩነኔ መሠረት ነው (ገላ 3:13፣ ቆላ 2:140፡፡ የሙሴ ሕግጋት ግባራቸው  እንደ መገለጥ እና እንደ "መልካሙን እና ክፉውን እንደሚታስታውቀው ዘፍ" የግብረገብ መለኪያ ነው፡፡

ጳውሎስ ሕግ ስል ምን መማለቱ እንደሆነ በእርግጠኝነር መናገር አይቻልም

1. በአይሁዳዊያን ዘንድ ያለ የጽድቅ ሥርዓት
2. በክርስቶስ ለመዳን አሕዛብ ሊያልፉት የሚገባ ደረጃ (በገላቲያ ያሉ አይሁዳዊያን)
3. ሰው ልጅ መድረስ ያልቻለው መለኪያ (ሮሜ 1:18-20፣ 7:7-25፣ ገላ 3:1-29)

▣ "ሕግን እናጸናለን" ከዚይህ በፍት ባለው ሀረግ መሠረት ይህ ሀረግ ምን ማለት ነው? ይህ ይህንን ሊያመለክት ይችላል?

1. ሕግ የድነት መንገድ ሳይሆን የግብረገብ መመሪያ ሆኖ ሊቀጥል ይችላል
2. "ጽድቅ በእምነት ነው" የሚለውን አስተምህሮ ያረጋግጣል
3. የሕግ  አለመቻል (በሰው ልጆች አመጽ ምክንያት ሮሜ 7፣ ገላ 3) በኢየሱስ ሞት እርካታን አግንቷል
4. የመገለጥ አላማ በሰዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን መልክ ማደስ ነው

በ13:9 ላይ ያለው የጳውሎስ የሕግ አመለካከት የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ

የሚያስደነግጠው እና ግራ የሚያጋበው ነገር ሕግ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለመመስረት አልቻለም ነገር ግን በእምን በሚሆን የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሱ መወገድ ክርስቲአኖች ጻድቅ፣ እግዚአብሔራዊ ሕይወት መኖር ቻሉ፡፡ የሕግ ግብ ከፍጻሜ ደርሷል ነግር ግን በሰው ልጅ ጥረት አይደለም ነገር ግን በክርስቶስ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው! "መመሥረት" ለሚለው በ5:2 ላይ የተሰጠውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ

## *መወያያ ጥያቄዎች*

ይህ የጥና <u>መመሪያ</u> የመጽሐፍ ቅዱስኢ መክፈቻ ነው፤ ማለትም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለምትረተጉሙበት መንገድ እራሳችሁ ኃላፊነቱነረ ትወስዳላችሁ፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጠን ልንመላለስ ይገባል፡፡ አንተ፣ መጽሐፈ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱሰን ክፍል ትክክለኛ ፍች ለማግኘት በምደረገው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊዎቸ ናችሁ፡፡ ይህንን እድል ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መፍቻዎች ልንለውጠው አይገባም፡፡

እነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች  የተሰጡት በመጽሐፉ ውስጥ ዋና ዋና በምባሉ ሀሳቦች ላይ አጽኖት ሰጥታችሁ እንድታስቡ ለማድረግ ነው፡፡ ዋነኛ አላማቸው እንድታስቡ ማድረግ እንጅ ትርጓሜን ለመስጠት አይደለም፡፡

1) ሮሜ 3:21-31 ያለውን የሀሳብ ውቅር በራስህ ቋንቋ ጻፍ
2) ባለፉት ዘመናት እግዚብሔር የሰዎችን ኀጢአት አልቆጠረም (ቁ.25)?
3) የብሉይ ኪዳን አማኞች ከኀጢአት እንዴት ይድኑ ነበር (3:25)?
4) በኢየሱስ ማመን እንዴት ሕግን ማረጋገጥ ልሆን ቻለ (3:31)?

# ሮሜ 4

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| የተየመቅሶ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእመቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የአብርሃም ምሳሌነት | አብርሃም በእምነት ጸደቀ | አብርሃም በእምነት ጸደቀ | የአብርሃም ምሳሌነት | አብርሃም በእምነት ጸደቀ |
| 4:1-12 | 4:1-4 | 4:1-8 | 4:1-8 | 4:1-8 |
| | ዳዊትም ተመሳሳይ እውነት አከበረ | | | ከግዝረት በፊት ጸደቀ |
| | 4:5-8 | 4:9-12 | 4:9-12 | 4:9-12 |
| | አብርሃም ከግዝረት በፊት ጸደቀ | | | |
| | 4:9-12 | | | |
| ተስፋው በእምነት በኩል እውን ሆነ | ተስፋው በእምነት በኩል ተረጋገጠ | የአብርሃም እውነተኞቹ ዘሮች | የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀበለ | ሕግን በመፈጸም አልጸደቀም |
| 4:13-25 | 4:13-25 | 4:13-15 | 4:13-15 | 4:13-17 |
| | | 4:16-25 | 4:16-25 | |
| | | | | የአብርሃም እምነት ለክርስቲያን እምነት ምሳሌ ነው |
| | | | | 4:18-25 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (viii **ተመልከት**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛው አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. የጳውሎስ ኃይለኛ ሥነ መለኮት በ3፡21-31 ላይ እንደሚያስረዳው የወደቀው ሰው ሊጸድቅ የሚችለው ከሙሴ ሕግ ጨርሶ በተለየ መልኩ በእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ጳውሎስ ለማስረገጥ እየሞከረ ያለው ይህ አዲስ ፈጠራ አለመሆኑን ሲሆን (3፡21ለ) ከብኪ ሁለቱንም ዳዊትና አብርሃምን ምሳሌ ይጠቅሳል (ቁ. 6-8)

ለ. ሮሜ 4 ከሙሴ ሕግ፣ ከዘፍ. - ዘዳ. ድረስ በእምነት ስለ መጽደቅ መሠረተ እምነት ማስረጃዎችን ያመላክታል፡፡ ይህም በ3፡21-31ተጠቃሏል፡፡ ለአይሁድ ከሙሴ መጻሕፍት መጥቀስ ታላቅ ሥነመለኮታዊ ክብደት አለው፤ በተለይ ከአብርሃም ጋር የሚገናኘው፣ እሱ የአይሁድ ሕዝቦች አባት ተደርጎ ስለሚወሰድ፡፡ ዳዊትም እንደሚመጣው መሲሕ ተደርጎ ይታይ ነበር (2ኛ ሳሙ. 7)፡፡ በሮም፣ በአማኝ አይሁድ እና በአማኝ አሕዛብ መካከል የነበረው የሐሳብ ግጭት ምናልባት በዚህ ነጥብ ላይ በነበረው ውይይት ይሆናል፡፡ የአይሁድ ክርስቲያን መሪዎች በኔሮ ተገደው (የሁሉንም የአይሁድ የአምልኮ ሥርዓት የሻረው) ሮምን ለቀው ሄደው ሊሆን ይችላል፡፡ በአንጻሩም በአሕዛብ ክርስቲያን መሪዎች ተተክተዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ምድብ ተመላሾች የአመራር ቦታውን የሚይዘው ማን እንደሆነ ክርክር አስነሥተዋል፡፡

ሐ. ሮሜ 4 የሚያሳየው የወደቀው የሰው ልጅ ሁልጊዜ የሚድነው በእምነትና በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብና በመንፈሳዊ ብርሃን ባለው ግንኙነት ነው (ዘፍ. 15፡6፤ ሮሜ. 4፡3)፡፡ አዲሱ ኪዳን (ወንጌል) በብዙ መልኩ ከብሉይ ኪዳን ጽንፋዊ ልዩነት የለውም )ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ.36፡22-38)፡፡

ሠ. የዚህ ዓይነቱ የእምነት ጽድቅ ለሁሉም ግልጽ ነው እንጂ ለአባቶች፣ ወይም ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ አይደለም፡፡ ጳውሎስ እዚህ ጋ አብርሃምን በመጠቀም ገላትያ 3 ላይ የጀመረውን ሥነመለኮታዊ ክርክሩን በማጠናከር ያስፋፋል፡፡

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

> **4፡1-8 [1]እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን? [2]አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም፡፡ [3]መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፡፡ [4]ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ [5]ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል፡፡ [6]እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል፦ [7] "ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤" [8] "ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው፡፡"**

4፡1 **"እንግዲህ አባታችን አብርሃም ምን ሆነ እንላለን?"** የአብርሃም ስም "የብዙዎች አባት" ማለት ነው (ቁ.16-18)፡፡ ዋነኛ ስሙ፣ አብራም፣ "ባለ ማዕርግ አባት" ማለት ነው፡፡
እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው የአጻጻፍ ዘዴ ሂስ (ወቀሳ) ዓይነት ነው 4፡1፤ 6፡1፤ 7፡7፤ 8፡31፤ 9፡14፣30)፡፡ አብርሃም የሚለው ስም ጥቅም ላይ የዋለበት ምክንያት (ዘፍ. 11፡27- 25፡11) ለምሳሌ ያህል አንድም (1) አይሁዶች እንዲህ ዓይነቱን ማዕርግ ለዘርያቸው መነሻ ይጠቀሙበት ስለነበር (ማቴ. 3፡9፤ ዮሐንስ 8፡33፣ 37፣ 39)፤ (2) በሌላ ምክንያትም የሱ ግላዊ እምነት የኪዳኑን መንገድ ምሳሌ ለማድረግ (ዘፍ. 15፡6)፤ (3) የሱ እምነት የሙሴ ሕግ መሰጠትን በመቅደሙ (ዘዳ. 19፡20)፤ ወይም (4) እሱ በሐሰተኛ መምህራን ጥቅም ላይ ውሎ ሊሆን ይችላል (ያም ማለት፣ በይሁዲዎች፣ በገላትያውያን)፡፡

▣ **"ሥጋ"** በ1፡3 ያለውን ልዩ ርእስ ተመልከት፡፡

4፡2 **"በ… ከ… (ቢሆን)"** ይህ አንደኛ ምድብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር (ኤ.ቲ. ሮበርትሰን፣ *ሥዕላዊ ቃላቶች*፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 350)፣ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ለጽሑፋዊ ጥቅሙ ነው፡፡ ይህ ለአንደኛ ደረጃ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ጥሩ ምሳሌ ሲሆን ከተጨባጭነት አኳያ ስህተት ሆኖ፣ ነገር ግን የሥነ መለኮት ነጥብ ለማስቀመጥ ይጠቅማል፡፡ (ቁ. 14)፡፡

ዮሴፍ ኤ. ፊትሜየር፣ *መልሕቅ መጽሐፍ ቅዱስ*፣ ቅጽ፣ 33፣ ገጽ 372፣ እንደሚለው፣ ይህ ምናልባት ድብልቅ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር፣ የመጀመሪያው ክፍል ሁለተኛ ምድብ (ከሀቅ ጋር በሚቃረን)፣ እንዲሁም ሁለተኛው አንደኛ ምድብ ነው፡፡

▣ **"በሥራ መጽደቅ"** ይህ በኢየሱስ በማመን መጽደቅ የሚለውን የሚጻረር ነው፡፡ ይህን መሰሉ በሰው ጥረት የሚሆን የመዳን መንገድ (4፡4)፣ የሚቻል ቢሆን ኖሮ የክርስቶስን ያገልግሎት አላስፈላጊ ባደረገው ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ፣ ብኪ በግልጽ

የሚያሳየው የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን የኪዳን ሥራ መፈጸም አለመቻሉን ነው። ስለዚህ፣ ብኪ ርግማን፣ የሞት ፍርድ ሆኗል (ገላ. 3፡13፤ ቆላ. 2፡14)።
የአይሁድ ሊቃውንት አብርሃም ከሙሴ ሕግ በፊት መኖሩን ያውቃሉ፤ ነገር ግን እሱ ሕጉ ይሆናል ብሎ ተስፋ የደርግ እንደነበረና እንደጠበቀውም ያልናሉ፣ (ሲራክ 44፡20 እና ኩፋሌ? 6፡19፤ 15፡1-2)።

▣ "የሚመካበት አንድ ነገር አለውና፣" ይህ ጭብጥ በጳውሎስ ጽሑፎች ዘወትር የተለመደ ነው። የፈሪሳውያንነት የኋላ ታሪኩ ለዚህ ዓይነቱ ችግር አብቅቶታል (3፡27፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡29፤ ኤፌ. 2፡8-9)። ልዩ ርእስ፡ ትምክህትን 2፡17 ላይ ተመልከት።

4፡3
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**
**አየተመት፣ አእመቅ** "አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ"
**ኢመቅ** "አብርሃም እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ጣለ"

ይህ ከዘፍ. 15፡6 የተጠቀሰ ነው። ጳውሎስ ይህንን በዚህ ምዕራፍ ላይ ሦስት ጊዜ ተጠቅሟል (4፡3፣ 9፣22)፣ ይህም የሚያሳየው በጳውሎስ የደኅንነት መረዳት ያለውን ጠቀሜታ ነው። "እምነት" የሚለው ቃል በብኪ ታማኝነት፣ ትክክለኝነት፣ የታመነ መሆን እና እግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጫ እንጂ የእኛን አይደለም። እሱም የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል (ኢሙን፣ ኢሙናህ) ሲሆን "ርግጠኛና የተረጋጋ መሆን" ማለት ነው። የመዳን እምነት የአእምሮ ስምምነት (የእውነት መገኘት)፣ ፍቃዳዊ መሰጠት (ውሳኔ)፣ ግብረ ገባዊ ሕይወት (የአኗኗር ዘዴ)፣ እንዲሁም በቅድሚያ ግንኙነታዊ (ሰውን መቀበል) ነው።

አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባው፣ የአብርሃም እምነት በወደፊቱ መሲሕ ላይ ሳይሆን ነገር ግን በእግዚአብሔር ተስፋ ማለትም እሱ ልጅ እና ዝርያ እንደሚኖረው ነው (ዘፍ. 12፡2፤ 15፡2-5፤ 17፡4-8፤ 18፡14)። አብርሃም በእግዚአብሔር በማመን ለዚህ ተስፋ ምላሽ ሰጥቷል። በዚህ ተስፋ ላይ ጥርጣሬና ችግሮች ነበሩበት፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ለመፈጸም (ተስፋው) አስራ ሦስት ዓመት ወስዶበታል። ይህ ፍጹም ያልነበረው እምነቱ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አግኝቷል። እግዚአብሔር እንከን ከሚገኝባቸው የሰው ልጆች ጋር ለመሥራት ፍቃደኛ ነው፣ ለሰጠው ተስፋ የእምነት ምላሽ እስከ ሰጡ ድረስ፤ የሰናፍጭ ዘር ቅንጣት ቢያክል እንኳ (ማቴ. 17፡20)።

4፡3፣4፣5፣6፣8፣9፣10፣22፣23፣24
**አአመመቅ፣ አየተመት** "እሱም በእውቅና ተያዘለት"
**አኪጀቅ፣** "እሱም ተቆጠረለት"
**አእመቅ** "እግዚአብሔር ተቀብሎታልና"
**ኢመቅ** "ይህ እምነቱም እግምት ውስጥ ገባለት"

"እሱ" የሚለው የአብርሃምን እምነት፣ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ያለውን ነው።

"ተቆጠረለት" (ሎጊዞሚና) ቀመራዊ ቃል ሲሆን "ውጤትን ወይም ክምችትን በአንዱ መዝገብ (ሒሳብ)" ያለውን ማለት ነው። (LXX ዘፍ. 15፡6፤ ሌዋ. 7፡18፤ 17፡4)። ይህ ተመሳሳይ እውነት በጥሩ ሁኔታ ተገልጿል በ2ኛ ቆሮ. 5፡21 እና ገላ. 3፡6 ላይ። ይህም ማለት፣ ጳውሎስ ዘፍ. 15፡6 እና መዝ. 32፡2 አዋሕዷቸዋል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱም "ተቆጠረ" የሚለውን ቀመራዊ ቃል በመጠቀማቸው ነው። ይህ የጽሑፎች ውሕደት በአይሁድ መምህራን (ራቢ) ጥቅም ላይ የሚውል የጽሑፎች ትርጓሜ መተንተኛ መርሕ በመሆኑ ነው።

ብኪ ይህን ቃል በሴፕተዋጂንት ሲጠቀም እምብዛም ከባንክ ጋር የተጎዳኘ የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ቃል አድርጎ ሳይሆን፣ ይልቁን ከዳን. "መጻሕፍት" 7፡10፤ 12፡1 ጋር በተያያዘ ነው። እነዚህ ሁለት ዘይቤአዊ መጻሕፍት (የእግዚአብሔር ማስታወሻዎች)፣

1. የድርጊቶች ወይም የመታሰቢያ መጻሕፍት (መዝ. 56፡8፤ 139፡16፤ ኢሳ. 65፡6፤ ሚል.3፡16፤ ራዕ. 20፡12-13)
2. የሕይወት መጽሐፍ (ዘጻ.32፡32፤ መዝ. 69፡28፤ ኢሳ.4፡3፤ ዳን.12፡1፤ ሉቃስ 10፡20፤ ፊሊ.4፡3፤ ዕብ. 12፡23፤ ራዕ. 3፡5፤ 13፡8፤ 17፡8፤ 20፡15፤ 21፡27)።

የአብርሃም እምነት በእግዚአብሔር ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት መጽሐፍ "የሕይወት መጽሐፍ" ይባላል።

4፡3፣5፣6፣9፣10፣11፣13፣22፣25 **"ጽድቅ ሆኖ"** ይህ የሚያንጸባርቀው የብኪን ቃል "የመለኪያ ሸንበቆ (ዘንግ)" (ጻዳቅ) ነው። የማከናወኛ ዘይቤ ሆኖ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ቀና ሲሆን ሁሉም የሰው ልጆች ግን ጠማሞች ናቸው። በአኪ ጥቅም ላይ የዋለው የሥልጣን ቦታን፣ ሕጋዊ (ምርመራ ነክ) ስሜትን ይዞ ሲሆን ይህም እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የአኗኗር ዘይቤ ባሕርይ ማደግን ያመለክታል። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ያለው ግብ የራሱን ባሕርይ፣ ወይም በሌላ መልኩ ለማስቀመጥ፣ ክርስቶስን መምሰል ነው (ዝኪ. 8፡28-29፤ ገላ. 4፡19)። 1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

4፡5 የእምነት ዋነኛው ጉዳይ ራሱን ለገለጠው ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት ሲሆን ይህም በራስ በሚደረግ ጥረት ወይም ዋጋ፣ ጨርሶ ባለመታመን ነው። ይህ ማለት ግን፣ አንድ ጊዜ ከዳንን እና መንፈሱ ካደረብን የሕይወት ዘይቤአችን ጠቃሚ አይደለም ማለትን አያመለክትም። የክርስትና ግቡ ስንሞት የሚሆን መንግሥተ ሰማያት አይደለም፣ ነገር ግን አሁንም

ክርስቶስን መምሰል ነው። እኛ በሥራችን አልዳንም፣ አልጸደቅንም ወይም ትክክለኛ አቋም በመያዛችን አይደለም፤ ነገር ግን ለመልካም ሥራ ነው የተዋጀነው (ኤፌ. 2፡8-9 እና 10፤ ያዕቆብና 1ኛ ዮሐንስ)። የአንድ ሰው መዳን ማስረጃው የተለወጠና እየተለወጠ ያለ ሕይወት ነው። ጽድቅ ቅድስናን ማምጣት ይኖርበታል!

▣ "አማኞች" ከበታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ እምነት (ፒስቲስ [ስም]፣ ፒስቲኦ ፣ [ግሥ]፣ ፒስቶስ [ቅፅል])**

ሀ. ይህ ጠቃሚ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው (ዕብ. 11፡ 1፣6)። እሱም የኢየሱስ ፊተኛ ስብከት አካል ነው (ማርቆስ 1፡15)። ቢያንስ ሁለት አዲስ ኪዳኖች ያስፈልጋሉ፡ ንስሐ እና እምነት (1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21)።

ለ. ሥርወ ቃል (የቃላት ሥርና ትርጉም)

1. "እምነት" የሚለው ቃል በብኪ. ታማኝነት፣ ትክክለኝነት፣ የታመነ መሆን እና እግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጫ እንጂ የእኛን አይደለም።
2. እሱም የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል (ኢሙን፣ ኢሙናህ) ሲሆን "ርግጠኛና የተረጋጋ መሆን" ማለት ነው። የመዳን እምነት የአእምሮ ስምምነት (የእውነት መገኘት)፣ ግብረ ገባዊ ሕይወት (የአኗኗር ዘዴ)፣ እንዲሁም በቅድሚያ ግንኙነታዊ (ሰውን መቀበል)፣ ፍቃዳዊ መሰጠት (ውሳኔ) ነው።

ሐ. የአኪ አጠቃቀሙ

አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባው፣ የአብርሃም እምነት በወደፊቱ መሲሕ ላይ ሳይሆን ነገር ግን በእግዚአብሔር ተስፋ ማለትም እሱ ልጅ እና ዝርያ እንደሚኖረው ነው (ዘፍ. 12፡2፤ 15፡2-5፤ 17፡4-8፤ 18፡14)። አብርሃም በእግዚአብሔር በማመን ለዚህ ተስፋ ምላሽ ሰጥቷል። በዚህ ተስፋ ላይ ጥርጣሬና ችግሮች ነበሩበት፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ለመፈጸም (ተስፋው) አስራ ሦስት ዓመት ወስዶበታል። ይህ ፍጹም ያልነበረው እምነቱ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አግኝቷል። እግዚአብሔር እንከን ከሚገኝባቸው የሰው ልጆች ጋር ለመሥራት ፍቃደኛ ነው፣ ለሰጠው ተስፋ የእምነት ምላሽ እስከ ሰጡ ድረስ፤ የሰናፍጭ ዘር ቅንጣት ቢያክል እንኳ (ማቴ. 17፡20)።

መ. የአኪ አጠቃቀሙ

"አመነ" የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል (ፒስቲኦየመጣ ሲሆን በተጨማሪም "ማመን" "እምነት" ወይም "መታመን" ማለት ነው። ለምሳሌ፣ ስሙ በዮሐንስ ወንጌል አይገኝም፣ ግን ግሡ በብዛት ጥቅም ላይ ውላል። በዮሐንስ 2፡23-25 የሕዝቡ ቅን የሆነ ቁርጠኝነት ጉድለት፣ የናዝሬቱ ኢየሱስን መሲሕ አድርጎ ላለመቀበል የጥርጥር ሁኔታ ታይቷል። የዚህ ቃል "እምነት" ተራ (ግልብ) አጠቃቀም ሌሎች ምሳሌዎች፣ በዮሐንስ 8፡ 31-59 እና ሐዋ. 8፡13፣ 18፡24 ይገኛሉ። እውነተኛው ቅዱስ መጽሐፋዊ እምነት በመነሻው ላይ ከተደረገው መቀበል ይበልጣል። የደቀ መዝሙራዊነት ሂደት ሊከተለው ይገባል (ማቴ. 13፡20-22፣ 31-32)።

ሠ. ከመስተጻምር ጋር ያለው አጠቃቀም

1. ኢስ eis "በውስጥ" ማለት ነው። ይህ የተለየ አገባብ አጽንኦት የሚሰጠው አማኞች እምነታቸውን መጣል ያለባቸው በኢየሱስ ሆኖ
   ሀ. በስሙ ላይ (ዮሐንስ 1፡ 12፤ 2፡23፤ 3፡18፤ 1ኛ ዮሐንስ5፡13)
   ለ. በእሱ ላይ (ዮሐንስ 2፡11፤ 3፡15፣18፤ 4፡39፤ 6፡40፤ 7፡5፣31፣39፣48፤ 8፡30፤ 9፡36፤ 10፡42፤ 11፡45፣ 48፤ 17፡37፣ 42፤ ማቴ. 18፡6፤ ሐዋ. 10፡43፤ ፊሊ. 1፡29፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡8)
   ሐ. በእኔ ላይ (ዮሐንስ 6፡35፤ 7፡38፤ 11፡25፣26፤ 12፡44፣46፤ 14፡1፣12፤ 16፡9፤ 17፡20)
   መ. በልጁ ላይ (ዮሐንስ 3፡36፤ 9፡35፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡10)
   ሠ. በኢየሱስ ላይ (ዮሐንስ 12፡11፤ ሐዋ. 19፡4፤ ገላ. 2፡16)
   ረ. በብርሃኑ ላይ (ዮሐንስ 12፡36)
   ሰ. በእግዚአብሔር ላይ (ዮሐንስ 14፡1)
2. ኢን (en) "ውስጥ" ማለት ነው፣ እንደ ዮሐንስ 3፡15፤ ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 5፡14
3. ኢፒ "ውስጥ" ወይም በላይ ማለት ነው፣ እንደ ማቴ. 27፡42፤ ሐዋ. 9፡42፤ 11፡17፤ 16፡31፤ 22፡19፤ ሮሜ. 4፡5፣24፤ 9፡33፤ 10፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡6
4. ቀጥተኛ ያልሆነ የግሥ ተሳቢ ያለ ምንም መስተጻምር፣ እንደ ገላ. 3፡6፤ ሐዋ. 18፡8፤ 27፡25፤ 1ኛ የሐንስ 3፡23፤ 5፡10
5. ሆቲ "ያመነውን፣" ማለት ሲሆን ምን እንደሚታመን ይዘቱን ያሳያል፣
   ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ነው (ዮሐንስ 6፡69)
   ለ. ኢየሱስ ያለና የሚኖር (እኔ ነኝ) ነው (ዮሐንስ 8፡24)
   ሐ. ኢየሱስ በአብ አለ፣ አብም በርሱ አለ (ዮሐንስ 10፡38)
   መ. ኢየሱስ መሲሕ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)
   ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐንስ 11፡27፤ 20፡31)
   ረ. ኢየሱስ የተላከው በአብ ነው (ዮሐንስ 11፡42፤ 17፡8፣21)

ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር አንድ ነው (ዮሐንስ 14፡10-11)
ሸ. ኢየሱስ የመጣው ከአብ ነው (ዮሐንስ 16፡27፣30)
ቀ. ኢየሱስ ራሱን የገለጠው በአብ የኪዳን ስም፣ "ያለና የሚኖር" (እኔ ነኝ) ብሎ ነው፣ (ዮሐንስ 8፡24፤ 13፡19)
በ. ከእርሱ ጋር እንኖራለን (ሮሜ. 6፡8)

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ "እምነቱ"**
**አየተመት "ይህ እምነት"**
**አእመቅ፣ ኢመቅ "ይህ እምነት ነው"**
የአብርሃም እምነት ለእሱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ይህም የሆነው በአብርሃም ድርጊት ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን በአዝማሚያው ነው።
"ተቆጠረለት" የሚለው ቃል ደግሞ ጥቅም ላይ የዋለው በፊንሐስ LXX በመዝ. **106፡31** ሲሆን ዘኁል. 25፡11-13 ን ያጣቅሳል። በዚህም ምክንያት እውቅና የተሰጠው በፊንሐስ ድርጊት ላይ ተመሥርቶ ነው እንጂ በዘፍ.15፡6 እንዳለው አብርሃም አይደለም!

▣ ***"ነገር ግን ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ የሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጥሮለታል"*** ይህ ግልጽ የሆነ ትይዩ ለአብርሃም ነው በቁ. 3 (ዘፍ. 15፡6)። ጽድቅ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ የሰው ሥራ ውጤት አይደለም። ልዩ ርዕስ 1፡17 እይ።

▣ ***"ዳዊት"*** እንደ አብርሃም ፍጹም ሰው ባይሆንም፣ ሆኖም በእምነት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖአል፣ በእጅጉን ኃጢአተኛ የሆነው ዳዊት (መዝ. 32 እና 51)። እግዚአብሔር ከወደቀው ሰው ጋር መሥራትን ይወዳል፣ (ዘፍ. 3) በእርሱ የመታመን አዝማሚያ ያሳየውን (ብኪ) እና በልጁ (አኪ)።

4፡6 ***"ከሥራ ባሻገር"*** ጳውሎስ ይህንን ሐረግ አጽንዖት የሚሰጠው ከብኪ ከጠቀሰው (መዝ. 32፡1-2) ቀደም ብሎ በማስገባት ነው። ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቀው በጸጋው በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት፣ በራሱ በግለሰቡ እምነት በኩል እንጂ በእነሱ ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች አይደለም።

4፡7-8 ይህ የተጠቀሰው ከመዝ. 32፡ 1-2 ነው። ሁለቱም ግሦች በቁ. 7፣ "ይቅርታ ተደርጎላቸዋል" እና "ተከድኖላቸዋል" የሃላፊ ጊዜ ተደራጊ ነው። አድራጊው እግዚአብሔር ነው። ቁጥር 8 ጠንካራ ድርብ አሉታ ይዟል፣ "በምንም ምክንያት ቢሆን" አይገኝም፣ እውቅና አይገኝለትም፣ አይቆጠርም፣ የዚህን ጥቅስ ሦስቱንም ግሦች ተመልከት፤ ሁሉም ከኃጢአት ነጻ መሆንን ያሳያሉ።

4፡7 ***"ኃጢአታቸው የተከደነላቸው"*** ይህ የተጠቀሰው ከመዝ. 32፡1 ነው። "መከደን" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ በእስራኤል የመሥዋዕትነት ገጽታ ማዕከላዊ የሆነ የአምልኮ ሥርዓት ነው። በእግዚአብሔር ኃጢአት ይከደናል፣ እሱም ከውስጡ ያወጣዋል (ብራውን፣ ድራይቨር፣ ብሪግስ፣ ገጽ 491)። ይሄው ተመሳሳይ ፅንሰ ሐሳብ የተለየ የዕብራይስጥ ቃል ሆኖ "የተከደነለት" (ካፋር)፣ በሚል በአምልኮ የሥርየት ቀን (መከደን)፣ ደም "በምሕረት መንበሩ" ላይ በሚደረግበት ጊዜ የእስራኤልን ኃጢአት ያስተሰርያል። ተመሳሳይ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ የሚሆነው የአንዱን ኃጢአት ማጥፋት ወይም መደምሰስ ነው።

4፡8 ***"ብፁዕ ነው፣ ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው"*** ይህ የተጠቀሰው ከመዝ. 32፡2 ነው። ይህም ቃል "እውቅና መስጠት፣" "ድርሻ (የጥፋተኝነት)" ወይም "በሌላ ሒሳብ ማኖር፣" በአሉታዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ ውሏል። እግዚአብሔር የኃጢአት አስተዋጽዖ የለውም (ድርብ አሉታ) በአማኝ መንፈሳዊ የባንክ ሒሳብ ውስጥ፤ ጽድቅን ነው የሚያስቀምጠው። ይህም የተመሠረተው በእግዚአብሔር የጸጋ ባሕርይ፣ ስጦታ፣ ሥልጣናዊ አዋጅ ላይ ነው እንጂ በሰው የሚገባው መሆን፣ መቀዳጀትና መልካምነት አይደለም!

4፡9-12
**[9]እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረ? ወይስ ደግሞ ስለ አለመገረዝ? እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንላለንና። [10]እንዴት ተቆጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም፥ ሳይገረዝ ነበር እንጂ። [11]ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው፥ [12]ለተገረዙትም አባት እንዲሆን ነው፤ ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው።**

4:9-12 ጳውሎስ ይህን የግዝረት ማብራሪያ ሊያቀርብ የቻለበት ምክንያት፣ ይሁዲዎች ለመዳን የግዝረትን አስፈላጊነት በማጋነናቸው ነው (የገላትያ መጽሐፍ እና የኢየሩሳሌም ምክር ቤት፣ የሐዋርያት ሥራ 15)።
ጳውሎስ፣ የሠለጠነው በራቢአዊ የትርጓሜ አግባብ ሲሆን፣ በዘፍ. 15፡6 እና መዝ. 32፡2 ተመሳሳይ ግሥ (በሁለቱም በዕብራይስጥ እና ግሪክ) መገኘቱን ያውቃል። ይህም እነዚህን አንቀጾች ለሥነ-መለኮታዊ ተግባር ያዋሕዳቸዋል።

4፡9 በቁጥር 9 ያለው ጥያቄ "ምንም" መልስ አይጠብቅም። እግዚአብሔር በእምነት ሁሉንም ሕዝቦች ይቀበላል፣ አሕዛብንም። ዘፍጥረት 15፡6 በድጋሚ ተጠቅሷል። አብርሃም፣ የአይሁድ ሕዝቦች አባት፣ ጻድቅ ሆኖ ተቆጥሯል፣ ከመገረዙ በፊት።

4፡10-11 **"የግርዛቱ ምልክት፣ የእምነት የጽድቅ ማኅተም"** አብርሃም ከተጠራ እና ጽድቅ ሆኖ ከተቆጠረለት በኋላ፣ እግዚአብሔር እንደ ኪዳን ምልክት መገረዝን ሰጠው (ዘፍ. 17፡9-14)። ሁሉም ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ሕዝቦች ተገርዘዋል፣ መነሻቸው ግሪክ አጂያን ደሴቶች ከነበረው ከፍልስጥኤማውያን በተቀር። ግርዛት ለእነሱ ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት መሸጋገሪያ ባህላዊ ሥርዓት ነበር። በአይሁድ ሕይወት፣ የኪዳን አባልነት ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ሆኖ ከተወለደ ስምንት ቀን በሞላው ወንድ ልጅ ላይ የሚፈጸም ነበር።
በዚህ ቁጥር "ምልክት" እና "ማኅተም" በትይዩ ተቀምጠው ሁለቱም የአብርሃምን እምነት የሚያመለክቱ ናቸው። መገረዝ የሚታይ ምልክት ሆኖ አንዱ በእግዚአብሔር ማመኑን ያሳያል። አገናዛቢው ሐረግ "ከእምነት የሆነ ጽድቅ" ቁ. 13 ላይ ተደግሟል። በቅዱሱ በእግዚአብሔር ጻድቅ ለመባል ቁልፉ ነገር መገረዝ ሳይሆን እምነት ነው።

4፡11 "**ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው**" የሮሜ መልእክት የተጻፈው ከገላትያ መልእክት በኋላ ነው። ጳውሎስ ለአይሁድ የማመን አዝማሚያ ስሱ የነበረው (1) በእነሱ የዘር አካሄድ (ማቴ. 3፡9፤ ዮሐንስ 8፡33፣37፣39) እና (2) የጊዜው የአይሁድ ትርጓሜ አተገባበር፣ ማለትም የሙሴአዊ ኪዳን (ሥነ-ቃል፣ ወይም የሽማግሌዎች ባህል፣ እሱም ኋላ ላይ ተጽፎ ታልሙድ ተብሎ የተጠራው ነው።) ስለሆነም አብርሃምን በእምነት ለሚታመኑት ምሳሌ አድርጎ ወስዶታል፣ (ሳይገረዙ ለሚያምነት አባት የሆነውን፣ ገላ. 3፡29)።

▣ **"ማኅተም"** ከበታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**ልዩ ርዕስ፡ ማኅተም**
የእግዚአብሔር ማኅተም በራዕይ 9፡4 እና 14፡1 እና ምናልባትም 22፡4 ላይ ተጠቅሷል። የሰይጣን ማኅተም 13፡16፤ 14፡9፤ እና 20፡4 ላይ ተጠቅሷል። ማኅተም ምናልባት ጥንታዊ የማሳያ መንገድነቱ
1. እውነትን (የሐንስ 3፡33)
2. ባለቤትነትን (ዮሐንስ 6፡27፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡19፤ ራዕ. 7፡2-3)
3. ደኅንነትን ወይም ጥበቃን (ዘፍ. 4፡15፤ ማቴ. 27፡66፤ ሮሜ. 15፡28፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ.1፡13፤ 4፡30)
4. ምናልባትም ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሔር የጸጋ ተስፋ እውነተኝነት የሚያሳይ ምልክት ነው (ሮሜ. 4፡11 እና 1ኛ ቆሮ. 9፡2)።

የዚህ ማኅተም ዓላማ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመለየት፣ ብሎም የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳያገኛቸው ነው። የሰይጣን ማኅተም የሱን ሕዝቦች የሚለይ ሲሆን፣ እኒህም የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያገኛቸው ናቸው። በራዕይ ላይ፣ "ታላቁ መከራ" (ያ ማለት፣ ትሊፕሲስ) ዘወትር፣ የማያምኑ አማኞችን እንደሚያሳድዱ ሲሆን፣ ቁጣ/መዓት (ማለትም፣ ኦርጊ orgê ወይም ቱሞስ)፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በማያምኑ ላይ ሆኖ፣ ምናልባትም ንስሐ ገብተው ወደ ኢየሱስ እምነት እንዲመጡ ነው። ይህ አዎንታዊ የፍርድ ዓላማ በዘዳ. 27-28 በርግማንና በበረከት ኪዳን ላይ ይታያል። "ሕያው እግዚአብሔር" የሚለው ሐረግ ያሕዌ በሚለው ስያሜ ውስጥ አለ (ዘፀ. 3፡14፤ መዝ. 42፡2፤ 84፡2፤ ማቴ. 16፡16)። ይህ ተመሳሳይ የቃላት አገባብ በቅዱሳት መጻሕፍት መሐላዎች፣ "ሕያው እግዚአብሔርን" በሚለው ውስጥ ይገኛል።

4፡12 **"መንገዱን ለሚከተሉ"** ይህ ወታደራዊ ቃል ሲሆን (ስቶይኪኦ stoicheô) ወታደሮች በነጠላ ፈለግ መጓዛቸውን ያመለክታል (ሐዋ. 21፡24፤ ገላ. 5፡25፤ 6፡16፤ ፊሊጵ.3፡16)። ጳውሎስ በዚህ ቁጥር ላይ ለአይሁድ የሚለው ("የመገረዝ አባት") ስለሆነው አማኝ ነው። አብርሃም በእግዚአብሔር ያለውን እምነት እና ተስፋዎች ለሚለማመዱ አባት ነው።
በድርብ መስተአምር (ቶይስ tois) ሳቢያ ይህ ሁለተኛው ገጽታ ("መንገዱን ለሚከተሉ") የሚለው የእምነት የአኗኗር ስልትን (የአሁን መካከለኛ ጥገኛ ቦዝ አንቀጽ) የሚያሳይ ሲሆን የአንድ ጊዜ እምነትን አይደለም። ደኅንነት ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ነው እንጂ ውሳኔ ወይም የአፍታ ፍላጎት መግለጫ አይደለም።

4፡13-15
[13]**የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም።** [14]**ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተስፋውም ቃል ተሽሮአል፤** [15]**ሕጉ መቅሠፍትን ያደርጋልና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም።**

4:13 **"ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል"** እግዚአብሔር ለአብርሃም "የርስት እና የዘር" ተስፋ ገብቶለታል (ዘፍ. 12:1-3፤ 15:1-6፤ 17:1-8፤ 22:17-18):: **ብኪ** በርስቱ (ፍልስጥኤም)፣ ላይ ነው የሚያኩረው፣ **አኪ** ደግሞ የሚያተኩረው "ዘሩ" ላይ ነው (ኢየሱስ መሲሑ፣ ገላ. 3:16፣19)፣ ግን እዚህ ላይ "ዘሩ" የሚያመለክተው የአምነት ሕዝቦችን ነው (ገላ. 3: 29):: የእግዚአብሔር ተስፋዎች የሁሉም አማኞች መታመኛ መሠረት ነው (ገላ. 3:14፣ 17፣ 18፣ 19፣ 21፣ 22፣ 29፤ 4:28፤ ዕብ. 5:13-18)

▣ **"የዓለምም ወራሽ እንዲሆን"** ይህ አጠቃላይ ቃል በጣም ወሳኝ ነው፣ ከዘፍ. 12:3፤ 18:18፤ 22:18 እና ከዘጸ. 19:5-6 አኳያ:: እግዚአብሔር አብርሃምን ጠራው የሰው ልጆችን ሁሉ ለመጥራት (ዘፍ. 1:26-27፤ 3:15)! አብርሃምና ዘሮቹ ማለት ለመላው ዓለም መገለጥ እንደ ማለት ሆነዋል:: ይህም ሌለኛው ዓይነት በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ማሳያ ነው (ማቴ. 6:10)::

▣ **"በሕግ በኩል አይደለም"** የሙሴ ሕግ እስካሁን ድረስ አልተገለጠም:: ይህ ሐረግ በግሪክ ዓረፍተ ነገር መጀመሪያ የተደረገው ጠቀሜታውን ለማሳየት ነው:: ይህም በሰዎች ጥረትና በመለኮታዊ ጸጋ መካከል ያለውን ልዩነት በአጽንዖት ለማሳየት እጅግ ጠቃሚ ነጥብ ነው (3:21-31):: ጸጋው ለመዳን መንገድ ሕጉን ሥራ ላይ እንዳይውል አደረገው (ዕብ. 8: 7፣ 13):: ልዩ ርዕስ: የጳውሎስ አተያይ በሙሴ ሕግ ላይ 13:9 ተመልከት::

4:14 "እንደ ሆነ..." ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ከጸሐፊው ሐሳብ ወይም ከጽሑፋዊ ዓላማው ተገቢ መስሎ የሚታይ ነው:: ጳውሎስ ይህንን አስገራሚ ቃል የተጠቀመው አመክኖአዊ ክርክሩን ለማቅረብ ነው:: ይህ አንደኛ ደረጃ ሁኔታዊ ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖታዊ ማግባቢያ ለማድረግ ነው:: እሱም የዚህን ቃል ልክነት አያምንም፤ ነገር ግን ያቀረበው ግልጽ የሆነ ተፋለሱን ለማመላከት ነው (ቁ.2)::
በዘራቸው አይሁድ የሆኑና የሚታይ የመገረዝ ምልክት ያላቸው ዓለምን እንዲወርሱ ነው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍቃድ እና ቃል የሚያምኑ እነርሱ ወራሾች ናቸው:: አካላዊ ግዝረት ትክክለኛው እውነተኛው ምልክት አይደለም፣ እምነት እንጂ (2:28-29)::

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"እምነት ዋጋ አጣ"** |
| **አየተመት** | **"እምነት ባዶ ሆነ"** |
| **አእመቅ** | **"የሰው እምነት ማለት ምንም ነው"** |
| **ኢመቅ** | **"እምነት ውጤት አልባ ሆነ"** |

ይህ የኬኖ ኃላፊ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ አጽንዖት የሚሰጠውም የጸና ሁኔታን፣ ጠንካራ የግሪክ ግሥ ፍቺውም "ባዶ ማድረግ፣" "ያለ መሠረት መሆንን ለማሳየት፣" ብሎም "ስህተትን ለማሳየት" ነው (1ኛ ቆሮ. 1:17):: ይሄው ቃል በተጨማሪም በጳውሎስ ጥቅም ላይ የዋለው በ1ኛ ቆሮ. 1:17፤ 9:15፤ 2ኛ ቆሮ. 9:3 እና ፊሊጵ. 2:7) ላይ ነው::

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ተስፋው ባዶ ሆነ"** |
| **አኪጀቅ** | **"ተስፋው ትርጉም አልባ ሆነ"** |
| **አየተመት** | **"ተስፋ ዋጋ አጣ"** |
| **አእመቅ** | **"የእግዚአብሔር ተስፋ ያለ ዋጋ ሆነ"** |
| **ኢመቅ** | **"ተስፋው ያለ ጥቅም ሆነ"** |

ይህም ደግሞ የኃላፊ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ አጽንዖት የሚሰጠውም የጸና ሁኔታን፣ ጠንካራ የግሪክ ግሥ ፍቺውም "ባዶ ማድረግ፣" "መሻር፣" "ወደ ፍጻሜ ማምጣት፣" እንዲያውም "መደምሰስ ወይም ድምጥማጡን ማጥፋት" ማለት ነው:: ይህ ቃል ደግሞ በጳውሎስ ጥቅም ላይ ውሏል በሮሜ. 3:3፣31፤ 6:6፤ 7:2፣6፤ 1ኛ ቆሮ. 2:6፤ 13:8፤ 15:24፣ 26፤ 2ኛ ቆሮ. 3:7፤ ገላ. 5:4፤ 2ኛ ተሰ. 2:8:: በዚህ ቁጥር ላይ ግልጽ የሆነ ትይዩነት አለ:: ለመዳን ሁለት መንገዶች አይኖሩም:: አዲሱ የጸጋ ኪዳን አሮጌውን የሥራ ኪዳን ባዶ እና ዋጋ ቢስ አደረገው! ልዩ ርዕስ: ባዶ እና ዋጋ ቢስን በ3:3 ተመልከት::

4:15 "ሕጉ... ሕግ" የመጀመሪያው የዚህ ቃል አጠቃቀም የግሪክ መስተአምር ይኖረዋል ሁለተኛው ግን አይኖረውም:: ምንም እንኳ ወደ ግሪክ መስተአምር ትኩረት በጣም ሰጥቶ ማካተትም ሆነ ማስቀረት አደገኛ ቢሆንም፣ በዚህ አግባብ ግን ጳውሎስ ለማሳየት እንዲረዳው የተጠቀመው በሁለት ታሳቢዎች ነው፡ (1) የሙሴ ሕግ፣ ከሥነ ቃላዊ ባህሉ ጋር፣ ይህም አንዳንድ አይሁድ ለመዳናቸው ያምኑት የነበረውን፣ እና (2) የሕግን ጽንሰ- ሐሳቦች በአጠቃላይ:: ይህም በዋንኛ መልኩ የሚያካትተው የአሕዛብ የግል ጽድቅ ማለትም በዚህም ሆነ በዚያ ባሕላዊ የሥነ-ምግባር ደንብ ወይም ሃይማኖታዊ የአምልኮ ሥርዓት ጋር የሚገጥሙት እና በሚያደርጉት ክዋኔ ከመለኮት ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ለሚመስላቸው ነው::

▣ **"ሕጉ ቁጣ ያመጣልና"** ይህ የሚያናውጥ ቃል ነው (ዝኒ ከማሁ. 3:20፤ ገላ. 3:10-13፤ ቆላ. 2:14):: የሙሴ ሕግ ፈጽሞ የመዳን መንገድ ማለት አይደለም (ዝኒ ከማሁ. ገላ. 3:23-29):: ይህም ለአይሁድ (ለሕግ አዋቂ) ለመረዳት ወይም ለመቀበል፣ በጣም ጠንካራ እውነት ሲሆን፣ ዳሩግን ለጳውሎስ የክርክሩ መሠረት ሆነል:: ልዩ ርዕስ፡ 13:9 ተመልከት::

▣ **"ነገር ግን ሕግ በሌለበት፣ መተላለፍ አይኖርም"** እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ራሳቸውጋ ባለ በሚጠየቁበት ብርሃን ይይዛቸዋል:: አሕዛብ ፈጽሞ ባልሰሙት በሙሴ ሕግ አይፈረድባቸውም:: ተፈጥሯዊ በሆነ መገለጥ ተጠያቂ ይሆናሉ (ዝኒ ከማሁ. 1:19-20፤ 2:14-15)::

ይህ እውነት እዚህጋ በጳውሎስ ክርክር አንድ ደረጃ ወደፊት ተወስዷል:: የሙሴ ሕግ በግልጽ ከመገለጡ በፊት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን መተላለፍ አልመዘገበም (ዝኒ ከማሁ. 3:20፣ 25፤ 4:15፤ 5:13፣ 20፤ 7:5፣ 7-8፤ ሐዋ. 17:30፤ 1ኛ ቆሮ. 15:56)::

> 4:16-25
> **[16-17]ስለዚህ ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተስፋው ቃል እንዲጸና እንደ ጸጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው፤ እርሱም፦ ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው::[18]ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፥ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ:: [19]የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ [20-21]ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም:: [22]ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት:: [23]ነገር ግን ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ፤ [24-25]ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታንችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቆጠርልን ዘንድ አለው::**

4:16 ይህ ግሩም የሆነ የጳውሎስ የክርክር መልክ ማጠቃለያ ሲሆን ቁ. 14፡ (1) ሰዎች በእምነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው፤ (2) ለእግዚአብሔር የጸጋ ተስፋ፤ (3) ተስፋው ለሁሉም ዝርያዎቹ ርግጥ ነበር (አይሁድ እና አሕዛብ) የአብርሃምን እምነት የሚለማመዱት ፤ እንዲሁም (4) አብርሃም በእምነት የሆኑት ሁሉ ምሳሌ ነው::

▣ **"ዋስትና ማግኘት"** የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት::

> **ልዩ ርዕስ፡ ዋስትና**
> ይህ የግሪክ ቃል በቢባዮስ ሦስት ልዩ ትርጉሞች አሉት::
> 1. ርግጠኛ የሆነ፣ አስተማማኝ፣ ወይም እምነት የሚጣልበት (ሮሜ. 4:16፤ 2ኛ ቆሮ. 1:7፤ ዕብ. 2:20፤ 3:6፣ 14፤ 6:19፤ 2ኛ ጴጥ. 1:10፣19)::
> 2. የአንድ ነገር የታማኝነት ሂደት የሚታይበት ወይም የሚጸናበት (ሮሜ. 15:8፤ ዕብ.2:2፣ ሉው እና ኒዳ፣ *የግሪክ እንግሊዝኛ የአዲስ ኪዳን ሥርወ ቃል፣* ቅጽ 1፣ ገጽ340፣ 377፣ 670)::
> 3. በወረቀት ላይ የተጻፈው ዶሴ እሱ ሞያዊ ቃል ሆኖ ለሕጋዊ ዋስትና የሚሆን ነው (ሙልተን እና ሚሊጋን፣ የግሪክ አዲስ ኪዳን መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 107-8)::
>
> ይህም ለቁ. 14 የተቃርኖ ሐሳብ ይሆናል:: የእግዚአብሔር ተስፋዎች ርግጠኞች ናቸው!

▣**"ሁሉም... ሁሉም"** ይህ የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞች (አይሁድና አሕዛብን) ነው::

4:17:23 ጳውሎስ አብርሃምን በድጋሚ ይጠቅሳል፣ ቅድሚያ የሚሰጠውን ለማመላከት (1) የእግዚአብሔር የማነሣሻ ጸጋ ተስፋዎች (ኪዳን)፤ እና (2) ከሰው ልጆች የሚጠበቅ መነሻ እምነትና ቀጣይነት ያለው የእምነት ምላሽ (ኪዳን):: (በ1:5 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት::) ኪዳናት ዘወትር የሁለት አካላትን ድርጊት ያካትታሉ::

4:17 **"እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፣ 'የብዙ ሕዝቦች አባት'"** ይህ የተጠቀሰው ከዘፍ. 17:5 ነው:: ሴፕቱዋጂንት (LXX) "አሕዛብ" አሉት:: እግዚአብሔር ዘወትር የሚፈልገው የሁሉም የአዳም ልጆችን መቤዠት ነው እንጂ (ዘፍ 3:15)፣ የአብርሃምን ልጆች ብቻ አይደለም:: የአብራም አዲሱ ስም፣ አብርሃም፣ "የብዙዎች አባት" ማለት ነው:: አሁን ሥጋዊ ዝርያዎችን ብቻ ሳይሆን፣ የእምነት ዝርያዎችን ጭምር እንደሚያካትት ተረድተናል::

▣ **"ለሙታን ሕይወት የሚሰጥ"** በጽሑፉ ይሄ የሚያመለክተው የአብርሃምንና የሳራን የወሲባዊ አካል ኃይል መታደሱን ነው (ቁ. 19)::

▣ *"የማይኖረውን ወደ ሕይወት አምጥቷልና"* ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው የሳራ ይስሐቅን መፅነስ ሲሆን፣ ነገር ግብ በተጨማሪም የእምነትን ወሳኝ ገጽታ ያሳያል (ዕብ. 11፡1)።

4፡18

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ተስፋ የማይደረገውን በተስፋ አምኗል"** |
| **አኪጀቅ** | **"እሱም፣ ተስፋ ያልሆነውን በተስፋ አምኗልና"** |
| **አየተመት** | **"ተስፋ የማይደረገውን አምኗል"** |
| **አእመቅ** | **"አብርሃምም አመነ ተስፋም አደረገ፣ ምንም እንኳ ተስፋ የሚያደርግበት ምክንያት ባይኖርም"** |
| **አኢመቅ** | **"ምንም ተስፋ ያለ ባይመስልም፣ እሱ ተስፋ አደረገ አመነም"** |

ልዩ ርዕስ "ተስፋ" በ12፡12 ላይ ይገኛል። ቃሉ ሰፋ ያለ የፍቺ መስክ አለው። ሀሮልድ ኬ. ሙልቶን፣ *የተከለሰው የግሪክ ሥርወቃል ትንታኔ*፣ ገጽ 133፣ በርካታ ጠቀሜታዎችን ይዘረዝራል።

1. *መሠረታዊ ፍቺ*፣ ተስፋ (ሮሜ. 5፡4፤ ሐዋ. 24፡15)
2. ተስፋ የሚለው ቃል (ሮሜ. 8፡24፤ ገላ. 5፡5)
3. ጸሐፊው ወይም ምንጩ (ቆላ. 1፡27፤ 1ጢሞ. 1፡1)
4. *ማመን*፣ *መተማመን* (1ኛ ጴጥ. 1፡21)
5. የዋስትናው አስተማማኝነት (ሐዋ. 2፡26፤ ሮሜ. 8፡20)

በዚህ ጽሑፍ ተስፋ ጥቅም ላይ የዋለው በሁለት የተለያዩ አገባቦች ነው። በሰው ችሎታና ኃይል ተስፋ ማድረግ (ቁ. 19፡21) አልያም በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተስፋ ማድረግ (ቁ. 17)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"ዘሮችህም እንዲህ ይሆናሉ"** |
| **አየተመት** | **"ዘሮችህም እንደዚህ የበዙ ይሆናሉ"** |
| **አእመቅ** | **"ዘሮችህም ብዙ ይሆናሉ"** |
| **ኢመቅ** | **"ዘሮችህም እንደ ሰማይ ከዋክብት ብዙ ይሆናሉ"** |

ይህ የተጠቀሰው ከዘፍ. 15፡5 ሲሆን እሱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ወንድ ልጅ የሰጠውን ተስፋ፣ ርግጠኝነት አጽንዖት ይሰጣል (ቁ. 19፡22)። አስታውስ፣ ይስሐቅ የተወለደው

1. ከተስፋው ከአስራ ሦስት ዓመት በኂላ መሆኑን
2. አብርሃም ሳራን ሊለያት ከሞከረ በኂላ መሆኑን (ሁለት ጊዜ በዘፍ. 12፡10-19፤ 20፡1-7)
3. አብርሃም ከግብፃዊቷ የሳራ አገልጋይ ከአጋር ወንድ ልጅ ከወለደ በኂላ መሆኑን (ዘፍ. 16፡1-16)
4. (4) ሁለቱም፣ ማለትም ሳራ (ዘፍ. 18፡12) እና አብርሃም (ዘፍ. 17፡17) በተስፋው ላይ ከሳቁ (ካሾፉ) በኂላ ነው።

ፍጹም የሆነ እምነት አልነበራቸውም! ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፣ ደኅንነት ፍጹም እምነትን አይሻም፣ ነገር ግን ተገቢውን አካል እንጂ (እግዚአብሔር በብኪ እና ልጁ በአኪ)።

4፡20 ከመነሻው አብርሃም ከሳራ ልጅ እንደሚያገኝ የተሰጠውን ተስፋ ሙሉ ለሙሉ አልተረዳም። የአብርሃምም እምነት ፍጹም አይደለም። እግዚአብሔር ፍጹም ያልሆነን እምነት ይቀበላል፣ ይሠራበታልም፣ ምክንያቱም ፍጹም ያልሆኑ ሰዎችን ስለሚወድ!

▣ **"ባለማመን ምክንያት አልተናወጠም"** ይህ ተመሳሳይ *ግሥ*፣ *ዲያክሪኖ* (diakrinô)፣ በኢየሱስ ጥቅም ላይ የዋለው በማቴ. 21፡21፤ ማርቆስ 11፡23 ላይ ነው። በሁሉም አካላዊ ምክንያቶች (ቁ. 19) የእግዚአብሔርን ቃል ለማጠየቅ፣ በምትኩ አብርሃም ጠንክሮ እንዲያድግ።
ሁለቱ ቁጥሮች በቁ. 20 ላይ ያሉት የድርጊት ተገብሮ አመላካች ናቸው። ተገብሮ ግሡ የሚያመለክተው አድራጊው እግዚአብሔር መሆኑን ሲሆን አብርሃም ግን የእግዚአብሔር ኃይል በእሱ ላይ ይሠራ ዘንድ መፍቀድ ነበረበት!

▣ **"ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ"** ልዩ ርዕስ 3፡23 ተመልከት።

4፡21

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ሙሉ ዋስትና አግኝቷል"** |
| **አኪጀቅ፣ አየተመት** | **"በሙሉ የሚያምን ሆኗል"** |
| **አእመቅ** | **"በፍጹም ርግጠኛ ነበር"** |
| **ኢመቅ** | **"በሙሉ አምኗል"** |

ይህ የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ፣ የአንድን ነገር ሙሉ ዋስትና የሚያመለክት ነው፣ (ሉቃስ 1፡1፤ ቆላ. 4፡12) ወይም የአንድን ሰው (4፡21፤ 14፡5)። ስሙ ጥቅም ላይ የዋለው ለሙሉ ዋስትና ነው፣ በቆላ. 2፡2 እና 1ኛ ተሰ. 1፡5። ይህ በእግዚአብሔር ፍቃድ፣ ቃል፣ እና ኃይል ያለ መተማመን ሰዎችን በእምነት እንዲንቀሳቀሱ ያስችላቸዋል!

▣ **"እግዚአብሔር ቃል የገባውን፣ ራሱ ደግሞ ሊፈጽመው ይችላል"** ይህ የተጠናቀቀ የመካከለኛ አመላካች ሲሆን፣ ፍችውም ባለፈው የተከናወነው ድርጊት ወደ ፍጻሜ መምጣቱንና ሐሳቡም ወደ ሕላዌ መቀየሩን ያሳያል። የእምነት ቁም ነገር አንዱ በእግዚአብሔር ባሕርይና ተስፋ ሲያምን ነው፣ (ቁ. 16:25፤ ኤፌ. 3:20፤ ይሁዳ 24) እና በሰዎች ሥራ ያልሆነ (ኢሳ. 55:11)። እምነት በተስፋ አምላክ መታመን ነው (ኢሳ. 55:11)፣ እሱም እንደሚፈጽመው (ዘፍ. 12:1-3 እና 15:6፣ 12-21፤ ሕዝ. 36:22-36)።

4:22 ይህ የዘፍ. 15:6 (ቁ.3)፣ ማጣቀሻ ሲሆን፣ ይህም በጳውሎስ ሥነ-መለኮታዊ ነጥብ ቁልፉ የክርክር ማቅረቢያ ማለትም እግዚአብሔር የራሱን ጽድቅ ለኃጢአተኛ ሰዎች እንደሚሰጥ ነው።

4:23-25 እነዚህ ቁጥሮች በግሪክ አንድ ዓረፍተ ነገር ናቸው። አካሄዱን አስተውል።

1. ለአብርሃም ብሎ፣ ቁ. 23
2. ለሁሉም አማኞች ብሎ፣ ቁ. 24
3. በእግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ቁ. 24
4. ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ተሰጥቷል (ዮሐንስ 3:16)፣ ኢየሱስ የተነሣው ኃጢአታችን ይቅር እንዲባል (ስለ ጽድቃችን) ነው፣ ቁ. 25።

4:24 የአብርሃም እምነት ለሁሉም በእውነት ለሚከተሉት ዘሮቹ መንገድ ሆነ። አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፣ ተስፋ ስለተገባለት ልጁ እና ዝርያዎቹ፣ (ልዩ ርዕስ 4:5 ተመልከት)። የአዲሱ ኪዳን አማኞች ኢየሱስ መሲሑ ለሁሉም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ለወደቀው የሰው ልጅ ለተሰጡት ፍጻሜ እንደሆነ ያምናሉ። "ዘሩ" የሚለው ቃል የነጠላም ሆነ የብዙ ነው። (ልጁ፣ ሕዝቡ)

▣ ለ "ተነሥቷል" 8:11 ማስታወሻ ተመልከት።

4:25 **"ስለ መተላለፋችንም አሳልፎ የሰጠው"** ይህ ሕግ ነክ ቃል ሲሆን፣ "አንዱን ለፍርድ አሳልፎ መስጠት" ማለት ነው። ቁጥር 25 አስደናቂ ክርስቶሳዊ ቃል ሲሆን ከሴፕቱዋጂንት (LXX) ከኢሳ. 53:11-12 ነው።

▣ **"ስለ ጽድቃችን ተነሥቷልና"** ሁለቱ ሐረጋት ቁ. 25 ትይዩዎቹ (አንድ ዓይነት መስተጻምር እና ሁለቱም የድርጊት ተገብሯዊ አመላካች ናቸው። የፍራንክ ስታግስ ትርጉም (የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ገጽ 97) "አሳልፎ የሰጠው ምክንያት ስለመተላለፋችን ሲሆን ያስነሣውም እኛ ጻድቅ ሆነን እንድንገኝ ነው" የሚለው መልካም አድርጎ ይገልጸዋል። ይህ ትርጓሜ የጳውሎስን "መጽደቅ" የሚለውን የቃል አጠቃቀም ሁለቱን ገጽታዎች ይዟል፣ (1) ሕግ ነክ (ሕጋዊ) አቋም እና (2) መልካምነት፣ ክርስቶስን የመሰለ ሕይወት! ልዩ ርዕስ 1:17 ተመልከት።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን የመጽሐፉን ክፍል ዋና ዋና ቁም ነገሮችን እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት ለበለጠ ነገር እንዲያነሣሡህ ታስቦ ነው እንጂ በዚህ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ የሮሜ ክፍል ለምን በእጅጉን ጠቃሚ ሆነ?
2. ጳውሎስ አብርሃምንና ዳዊትን ለምን እንደ ምሳሌ ተጠቀመባቸው?
3. የሚከተሉትን ቁልፍ ቃላት፣ (በራስህ መግለጫ ሳይሆን) በጳውሎስ አጠቃቀም ግለጽ
   ሀ. "ጽድቅ"
   ለ. "ተቆጠረለት"
   ሐ. "እምነት"
   መ. "ተስፋ"
4. ግዝረት ለአይሁድ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው (ቁ. 9-12)?
5. በዚህ ቁጥር 13 እና 16 "ዘሩ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለማን ነው?

# ሮሜ 5

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጽድቅ ውጤቶች | እምነት ችግሩን አስወገደ | ከጽድቅ በኋላ የሚከተሉት | ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኝነት | እምነት ደኅንነትን አረጋገጠ |
| 5:1-11 | 5:1-5 | 5:1-5 | 5:1-5 | 5:1-11 |
| | ክርስቶስ በእኛ ስፍራ | 5:6-11 | 5:6-11 | |
| | 5:6-11 | | | |
| አዳምና ክርስቶስ | በአዳም ሞት፣ በክርስቶስ ሕይወት | አዳምና ክርስቶስ፤ ተመሳስሎ እና ተቃርኖ | አዳምና ክርስቶስ | አዳምና ኢየሱስ ክርስቶስ |
| | 5:12-21 | 5:12-14 | 5:12-14ለ | 5:12-14 |
| 5:12-14 | | | 5:14ሐ-17 | |
| 5:15-21 | | 5:15-17 | | 5:15-21 |
| | | 5:18-21 | 5:18-19 | |
| | | | 5:20-21 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (viii **ተመልከት**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።*

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*

2. *ሁለተኛው አንቀጽ*

3. *ሦስተኛ አንቀጽ*

4. *ወዘተርፈ*

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ቁጥር 1-11 በግሪክ አንድ ዓረፍተ ነገር ነው። እነሱም የጳውሎስን "በእምነት መጽደቅ" የሚለውን ዋነኛ ጽንሰ-ሐሳብ ያጠናክራሉ (ዝኒ ከማሁ 3:21-4:25)።

ለ. የዋና ሐሳቦች ዝርዝር ቁ. 1-11፡

| ቁጥር 1-5 | ቁጥር 6-8 | ቁጥር 9-11 |
|---|---|---|
| የደኅንነት ጠቀሜታዎች | የደኅንነት መሠረቶች | መጻኢው የደኅንነት ርግጠኝነት |
| የጽድቅ ተያያዥ ልምዶች | የጽድቅ ተጨባጭ ሀቆች | መጻኢው የደኅንነት ርግጠኝነት |
| ጽድቅ | የተሻሻለ መቀደስ | ክብር |
| የሰው ዘር ጥናት (አንትሮፖሎጂ) | ሥነ መለኮት | የሥነ መለኮት ክፍል (እስካቶሎጂ) |

ሐ. ቁጥር 12-21 የሚያብራራው ኢየሱስ እንደ ዳግም አዳም ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡21-22፣ 45-49፤ ፊሊጵ. 2፡6-8)። እሱም አጽንዖት የሚሰጠው በሥነ-መለኮት ጽንሰ-ሐሳብ ለሁለቱም ማለትም ለግል ኃጢአትና በውርስ በደል ላይ ነው። ጳውሎስ የሰው ልጆችን (እና የተፈጥሮን) በአዳም የተነሣ መውደቅ ከአይሁድ መምህራን (ራቢ) ፈጽሞ በተለየ መልኩ ነው የሚያቀርበው፤ ዳሩግን የእሱ የሥጋዊነት አስተሳሰብ በእጅጉን ከአይሁድ መምህራን (ራቢ) መስመር ጋር ተያይዞ እያለ። ይህም የሚያሳየው የጳውሎስን ችሎታ ሲሆን፣ ኢየሩሳሌም በገማልያል ሥር በሚማርበት ወቅት (ሐዋ. 22፡3) የተገነዘበውን እውነት ለተመስጧዊ ጠቀሜታ እና ለሐሳብ ማጠናከሪያነት ተጠቅሞበታል።

ተሐድሷዊው የወንጌላዊ መሠረተ እምነት፣ የመነሻው ኃጢአት ከዘፍ. 3 እየተብራራ የመጣው በአውግስጢኖስ እና በካልቪን ነው። እሱም በመሠረቱ የሚያስረዳው የሰው ልጆች በኃጢአት መወለዳቸውን (ጨርሶ መበላሸት) ነው። መዝሙር 51፡5፤ 58፡3፤ እና ኢዮብ 15፡14፤ 25፡4 እንደ ብኪ ማስረጃ ጽሑፎች ያገለግላሉ። አማራጩ የሥነ መለኮት አቋም፣ ማለትም ሰዎች በአካሄድ የግብረ-ገባዊም ሆነ የመንፈሳዊ ኃላፊነት በራሳቸው ምርጫም ሆነ ከመዳረሻ ግባቸው እንዳላቸው የተብራራው በፐሌጊስ እና በአርሚኒስ ነው። ለእነሱም አመለካከት የተወሰኑ ማስረጃዎች አሉ፣ ዘዳ. 1፡39፤ ኢሳ. 7፡15፤ እና ዮና. 4፡11፤ ዮሐንስ 9፡41፤ 15፡22፣24፤ ሐዋ. 17፡30፤ ሮሜ. 4፡15። የዚህ ሥነ-መለኮታዊ አቋም መተማመኛ ሊሆን የሚችለው፣ ልጆች ክፉ ደጉን እስከሚያውቁበት ዕድሜ ድረስ ንጹሕ መሆናቸውን፣ (ይህ ለአይሁድ መምህራን (ራቢ) ለወንዶች 13 ዓመት ለሴቶች ደግሞ 12 ዓመት) የሚያሳየው ነው።

በዚህ ላይ ደግሞ በስተመካከል የሆነ አቋም አለ፣ የሁለቱንም ማለትም የውርስ የክፋት ዝንባሌ እና ክፉ ደጉን የመለየት ዕድሜ ትክክል የሚሆኑበት! ክፋት የውርስ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን እያደገ የሚመጣ ክፋት ማለትም ግለሰባዊ በሆነ ኃጢአት (ሕይወት ከእግዚአብሔር እየራቀ ይሄዳል)። የሰው ኃጢአተኝነት አይደለም ጉዳዩ (ዘፍ. 6፡5፣ 11-12፣13፤ ሮሜ. 3፡9-18፣ 23)፣ ግን መቼ፣ በውልደት ወይም ኋላ በሕይወት ጉዞ?

መ. ስለ ቁ. 12 ተጽእኖ በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ይኖራሉ

1. ሁሉም ሰዎች ይሞታሉ ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች ኃጢአትን ለማድረግ ስለመረጡ (ፔሌጊስ)
2. የአዳም ኃጢአት ሞላውን ፍጥረት ነካው፣ እናም ሁሉም ሞቱ (ቁ. 18-19፣ አውግስጢኖስ)
3. በእውኑ ግን፣ ሊሆን የሚችለው የመነሻ ኃጢአትና የፍቃድ ኃጢአት ነው

ሠ. የጳውሎስ ንጽጽር ቁ. 12 ላይ የሚጀምረው "ልክ እንደ" ቁ.18 እስኪደርስ ድረስ አያበቃም። ቁጥር 13-17 ቅንፍ ተበጅቶለታል፣ እንደ ጳውሎስ ጽሑፎች ጠባይ።

ረ. የጳውሎስ የወንጌል አቀራረብ፣ 1፡18-8፡39 አንድ ወጥ መከራከሪያ መሆኑን አስተውል። ሁሉም መታየት የሚኖርበት ክፍሎቹን ባግባቡ ለመተርጎምና ለማብራራት እንደሆነ መወሰድ ይኖርበታል።

ሰ. ማርቲን ሉተር ስለ ምዕራፍ 5 እንዲህ ብሏል፣ "ከሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ አሸናፊ ጽሑፍ ጋር አቻ የሆነ ሌላ ምዕራፍ ማግኘት አዳጋች ነው።"

**የቃል እና የሐረግ ጥናት**

5፡1-5

**[1]እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ [2]በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። [3]-[4]ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤ [5]በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።**

**5፡1 "ስለዚህ"** ይህ ቃል ዘወትር የሚያመለክተው (1) እስከ እዚህ ነጥብ ያለውን የሥነ- መለኮት ክርክር ጭምቅ-ሐሳብ፤ (2) በሥነ-መለኮታዊ ገለጻው ላይ የተመሠረተ ማጠቃለያ፤ እና (3) የአዲስ እውነት አቅርቦት (ዝኒ ከማሁ 5፡1፤ 8፡1፤ 12፡1)።

▣ **"ከጸደቅን"** ይህ የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው፤ እግዚአብሔር አማኞችን አጽድቋል። ይህ በግሪኩ ዓረፍተ ነገር በመጀመሪያ የተቀመጠው (ቁ. 1-2) ለአጽንዖት ነው። እዚህጋ የጊዜ ቅደም ተከተል ያለ ይመስላል፣ ቁ.1-11፡ (1) ቁ. 1-5፣ የእኛ የጊዜው የጸጋ ልምምድ፤ (2) ቁ. 6-8፣ ክርስቶስ በእኛ በኩል ሆኖ ሥራውን ፈጽሟል፤ እና (3) ቁ. 9፡11፣ መጻኢው የመዳን ዋስትናችንና ተስፋችን። በጽሑፋዊ ይዘት ለ ላይ ያለውን የዋና ሐሳብ ዝርዝር ተመልከት።

በብሉይ ኪዳን "ጽድቋል" (ዲካዮ dikaioô) የሚለው ቃል ዳራ "ቀጥ ያለ ጫፍ" ወይም "የመለኪያ ዘንግ" ማለት ነው። ይህም በዘይቤአዊ አግባብ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ 1፡17 ላይ ተመልከት። የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ቅድስና፣ ብቸኛው የፍርድ መለኪያ ነው (LXX የሌዋ. 24፡22፤ እና ሥነ-መለኮታዊ በማቴ. 5፡ 48)። በኢየሱስ መሥዋዕታዊ፣ የተለዋጭነት ሞት፣ አማኞች ሕጋዊ (ሕግ-ነክ) ስፍራዊ አቋም በእግዚአብሔር ዘንድ አላቸው። (5፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።) ይህም የሚያመለክተው የአማኞችን ያለ ኃጢአት መሆን አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁን ምሕረት መደረጉን እንጂ። ሌላው ቅጣቱን ተቀብሏል፣ (2ኛ ቆሮ. 5፡21)። አማኞች ምሕረት እንደተደረገላቸው ታውጇል (ቁ. 9፣ 10)።

▣ **"በእምነት"** እምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልበት እጅ ነው (ቁ.2፤ ሮሜ. 4፡1)። እምነት በአማኙ ቁርጠኝነት ወይም ውሳኔ ደረጃ ወይም ብርታት ላይ አያተኩርም (ማቴ. 17፡20)፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ባሕርይና ተስፋ ላይ እንጂ (ኤፌ. 2፡8-9)። የብኪ. ቃል "እምነት" በዋነኝነት የሚያመለክተው የጸና አቋምን ነው። ይህም በዘይቤአዊ አገላለጽ፣ ታማኝ ለሆነ፣ አብሮ የሚቆምና ታማኝነት ላለው ሰው ነው። እምነት በእኛ ታማኝነት ወይም የታመንን መሆን ላይ አያተኩርም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር እንጂ። ልዩ ርዕስ፡ እምነት 4፡5 ላይ ተመልከት።

▣ **"ሰላም አለን"** እዚህጋ የግሪክ የእጅ-ጽሑፍ ልዩነት አለ። ይህ ግሥ አንድም፣ የአሁን የድርጊት አኳኋን (ኢኮሜን echômen) ወይም የአሁን የድርጊት አመላካች (ኢኮሜን echomen) ነው። ይህን መሰል ሰዋሰዋዊ አሻሚነት ቁ. 1፣ 2 እና 3 ላይ ይገኛል። ጥንታዊዎቹ የግሪክ ጽሑፎች የድርጊት አኳኋኑን የሚደግፉት ይመስላል MSS ፣ ሀ፣ ለ*፣ ሐ፣ መ)። የአኳኋን ከሆነ ሊተረጎም የሚችለው "በሰላማችን እየተደሰትን እንቀጥል" ወይም "በሰላም እየተደሰታችሁ ቀጥሉ" የሚል ይሆናል። አመላካች ከሆነ ደግሞ "ሰላም አለን" በሚል ይተረጎማል። የቁ. 1-11 ጽሑፍ ይዘት ማሳመኛ ዓይነት አይደለም፣ አማኞች ቀደም ሲል በክርስቶስ በኩል የሆኑትን ወይም ያላቸውን ማጽኛ (ማወጃ) እንጂ። ስለሆነም፣ ግሡ ሊሆን የሚችለው የአሁን የድርጊት አመላካች ነው፣ "ሰላም አለን።" ዩቢኤስ[4] ይህን አማራጭ ለ"ሀ" (ተገቢነት) ይሰጣል።

አብዛኞቹ ጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎች የሚዘጋጁት አንድ ሰው ጽሑፉን እያነበበ እና ሌሎች በርካቶች ደግሞ እየጻፉ ነው። አንድ ዓይነት ንባብ ያላቸው ቃላት ዘወትር ያሳስታሉ። እዚህ ላይ ጽሑፉ እና አንዳንዴም የአጻጻፍ ዘዴው እንዲሁም የተለመደው የጸሐፊው ቃላት የትርጓሜ ውሳኔውን አመቺ ለማድረግ ይረዳል።

▣ **"ሰላም"** ከበታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ ሰላም**

የግሪኩ ቃል በመጀመሪያ የሚለው "የተሰበረውን አንድ ላይ መጠገን ነው" (ዮሐንስ 14፡27፤ 16፡33፤ ፊሊጵ. 4፡7)። በአኪ. ሦስት ዓይነት የሰላም መግለጫ መንገዶች አሉ፡

1. እንደ ተሳቢ ገጽታ (ተጨባጭ) በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም (ቆላ. 1፡20)
2. እንደ ባለቤት ገጽታ (ተያያዥ) ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ መሆናችን (ዮሐንስ 14፡27፤ 16፡33፤ ፊሊጵ. 4፡7)
3. እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል አማኝ አይሁድን እና አሕዛብን ወደ አንድ አዲስ አካል ማምጣቱ (ኤፌ. 2፡ 14-17፤ ቆላ. 3፡15)። አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ካለን፣ ከሌሎችም ጋር ሰላም ሊኖረን ይገባል! የወደላዩ የወደጎንም መሆን አለበት።

ኒውማን እና ኒ፣ *በጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ላይ የተርጓሚዎች መመሪያ*፣ ገጽ 92፣ ስለ "ሰላም" መልካም የሆነ አስተያየት አለው።

"በሁለቱም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን <u>ሰላም</u> የሚለው ቃል ሰፋ ያለ ትርጉም አለው። በመሠረቱ የሚያስረዳው የሰዎችን ሕይወት አጠቃላይ ደኅንነት ሲሆን፤ ይህም በአይሁድ እንኳ የሰላምታ መግለጫ ተደርጓል። ቃሉ ጠለቅ ያለ ትርጉምም አለው፣ ይህም በአይሁድ ጥቅም ላይ ሲውል መሲሓዊ ደኅንነትን ይገልጻል። ከዚህም ሀቅ የተነሣ፣ 'ከእግዚአብሔር ጋር በተገቢ ግንኙነት መሆን' በሚል ተመሳሳይ ትርጉም የሚይዝበት ጊዜ አለ። እዚህጋ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተመሠረተውን ኅብራዊ ግንኙነት ለማመልከት ሲሆን፣ በመሠረቱም እግዚአብሔር ሰውን ከራሱ ጋር በትክክል ማስቀመጡን ያሳያል" (ገጽ 92)

▣ **"በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር"** ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ሰላም አድራጊው ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ሰላም ብቸኛው መንገድ ነው (ዮሐንስ 10፡7-8፤ 14፡6፤ ሐዋ. 4፡12፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡ 5)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚለው ቃል 1፡4 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

5፡2 **"መግባትን አግኝተናልና"** ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት አመላካች ነው፤ ስላለፈ ድርጊትና ስለተጠናቀቀ፣ ውጤቱ ግን አሁን የሚታይ ነው። "መግባት" የሚለው ቃል በጥሬ ቃሉ "አድራሽ መንገድ" ወይም "ፍቃድ" ማለት ነው (ፕሮሳጎጊ prosagôge፣ ዝኒ ከማሁ ኤፌ. 2፡18፤ 3፡12)። በዘይቤአዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ለ (1) ወደ ንጉሣዊ መግባት ወይም (2) ወደ ወደብ በደኅና መድረስ በሚል ነው።

▣ ይህ ሐረግ የግሪክን የተለያየ ጽሑፎች ይዟል። ጥቂት የጥንት ጽሑፎች "በእምነት" የሚል ተጨማሪ ያደርጋሉ (ዝኒ ከማሁ. ?*.[2]፣ ሐ እንዲሁም የጥንት ላቲን ፣ ቫልጋቴ፣ ሲሪያዊ፣ እና ኮፕቲክ ቅጂዎች)። ሌሎች ጽሑፎችም "በ እምነት" ላይ መስተጻምር ይጨምራሉ (ዝኒ ከማሁ. ?[1]፣ ሀ፣ እና ጥቂት የቫልጋቴ ቅጂዎች)። ሆኖም፣ የተለዩት የእጅ ጽሑፎች ለ፣ መ፣ ረ፣ እና ሰ ሁሉንም ይገድፏቸዋል። ይህም ሊሆን የሚችለው ጸሐፊዎቹ፣ 5፡1 እና 4፡16 (ሁለቴ)፣ 19፣ እና 20 ያሉትን ትይዩዎች በመሙላታቸው ይሆናል። "በእምነት" የጳውሎስ የወቅቱ ጭብጥ ነው።

▣ **"ወደዚህ ክብር"** ይህ ቃል (ቻሪስ charis) የሚለው የእግዚአብሔርን የማይገባንን፣ መተሳሰሪያ ገመድ የሌለንን፣ ከጥረታችን ያልሆነውን ፍቅር የሚያሳይ ነው (ኤፌ. 2፡4-9)። ይህም በኃጢአተኛው የሰው ልጅ ምክንያት የክርስቶስን ሞት በግልጽ ያመላክታል (ዝኒ ከማሁ. ቁ.8)።

▣ **"የቆምንበትን"** ይህም ሌላው የተጠናቀቀ ድርጊት አመላካች ነው፤ በጥሬ ትርጉሙ "ቆመናል እናም በመቆማችን እንቀጥላለን" ማለት ነው። ይህም የሚያንጸባርቀው የአማኞችን ሥነ-መለኮታዊ አቋም፣ በክርስቶስ ያላቸውንና በእምነት ቁርጠኝነት መቀጠል እንዳለባቸው ሲሆን ይህም የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (1ኛ ቆሮ. 15፡1) እና የሰዎችን ነጻ ፍቃድ (ኤፌ. 6፡11፣ 13፣14) ላይ ያለውን አያዎ (ፓራዶክስ) የሚያዋሕድ ይሆናል።

**ልዩ ርዕስ፡ መቆም (ሂስተሚ HIST ĒMI)**
ይህ የተለመደ ቃል በበርካታ ሥነ-መለኮታዊ አግባቦች በአዲስ ኪዳን ላይ ጥቅም ላይ ውሏል

1. ለማጽናት
   ሀ. የብኪ ሕግ፣ ሮሜ.3፡31
   ለ. የአንዱ የራሱ ጽድቅ፣ ሮሜ. 10፡3
   ሐ. አዲሱ ኪዳን፣ ዕብ. 10፡9
   መ. ለማጽናት፣ 2ኛ ቆሮ. 13፡1
   ሠ. የእግዚአብሔር እውነት፣ 2ኛ ጢሞ. 2፡19
2. በመንፈሳዊነት ለመቃወም
   ሀ. ሰይጣን፣ ኤፌ. 6፡11
   ለ. የፍርድ ቀን፣ ራዕ. 6፡17
3. ስፍራው ላይ ቆሞ ለመቃወም
   ሀ. ወታደራዊ ዘይቤ፣ ኤፌ. 6፡14
   ለ. ሲቪል ዘይቤ፣ ሮሜ. 14፡4
4. በእውነት ላይ ያለ አቋም፣ ዮሐንስ 8፡44
5. በጸጋ ላይ ያለ አቋም
   ሀ. ሮሜ. 5፡2
   ለ. 1ኛ ቆሮ. 15፡1
   ሐ. 1ኛ ጴጥ. 5፡12
6. በእምነት ላይ ያለ አቋም
   ሀ. ሮሜ 11፡20
   ለ. 1ኛ ቆሮ. 7፡37
   ሐ. 1ኛ ቆሮ. 15፡1
   መ. 2ኛ ቆሮ. 1፡24
7. የእብሪተኛ አቋም፣ 1ኛ ቆሮ. 10፡12

ይህ ቃል የሚገልጸው ሁለቱንም ኪዳናዊ ጸጋንና የሉዓላዊውን የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲሁም አማኞች መያዝ ያለባቸውን እውነት እና ከእሱም ጋር በእምነት መጣበቅ እንዳለባቸው ነው! ሁለቱን ቅዱስ መጽሐፋዊ ሐቆች ናቸው። እነሱም አንድ ላይ መያዝ አለባቸው!

▣ "እንደሰታለን" ሰዋሰዋዊ አገባቡ ሊሆን የሚችለው (1) የአሁን መካከለኛ አመላካች፣ "እንደሰታለን" ወይም (2) የአሁን መካከለኛ ባለቤት፣ "እንደሰት" ማለት ነው:: ሊቃውንት በእነዚህ አማራጮች ተከፋፍለዋል:: አንዱ "እኛ አለን (እኛ ...ላለን" ቁ. 1.ን እንደ አመላካች ቢወስድ፣ ትርጓሜው እስከ ቁ. 3 ድረስ አይለዋወጥም::

"መደሰት" የሚለው ቃል ሥሩ "መመካት" ነው፣ (አየተመቅ፣ ኢመቅ):: በ2፡17 ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት:: አማኞች በራሳቸው አይደሰቱም (ዝኒ ከማሁ. 3፡27)፣ ጌታ ለእነርሱ ባደረገላቸው እንጂ (ኤር. 9፡23-24):: ይህ ተመሳሳይ የግሪክ ሥር ቁ. 3 እና 11 ላይ ተደግሟል::

▣"ተስፋ የምናደርገው" ጳውሎስ ይሄንን ቃል አዘውትሮ በተለያዩ ግን ዝምድና ባላቸው አገባቦች ይጠቀማል:: 4፡18 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት:: ዘወትር የሚያያዘው የአማኙ እምነት ከሚቀዳጀው ጋር ነው:: ይህም ሊገለጽ የሚችለው እንደ ክብር፣ የዘላለም ሕይወት፣ የመጨረሻው ድኅነት፣ ዳግም ምጽዓቱ፣ ወዘተ ጋር ነው:: መቀዳጀቱ ርግጠኛ ነው፣ ግን የጊዜው ጉዳይ መጻኢ እና የማይታወቅ ነው:: ዘወትር ከ"እምነት" እና ከ"ፍቅር" ጋር ይያያዛል (1ኛ ቆሮ. 13፡13፤ ገላ. 5፡5-6፤ ኤፌ. 4፡2-5፤ 1ኛ ተሰ. 1፡3፤ 5፡8):: የጳውሎስ አጠቃቀም ከፊሉ ዝርዝር ቀጥሎ ተመልክቷል::

1. ዳግም ምጽዓት፣ ገላ. 5፡5፤ ኤፌ.1፡18፤ ቲቶ 2፡13
2. ኢየሱስ ተስፋችን ነው፣ 1ኛ ጢሞ. 1፡1
3. አማኞች ለእግዚአብሔር ይሰጣሉ፣ ቆላ. 1፡22-23፤ 1ኛ ተሰ. 2፡19
4. ተስፋ በሰማይ ተቀምጧል፣ ቆላ. 1፡5
5. የመጨረሻው መዳን፣ 1ኛ ተሰ. 4፡13
6. የእግዚአብሔር ክብር፣ ሮሜ. 5፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡12፤ ቆላ. 1፡27
7. የመዳን ዋስትና፣ 1ኛ ተሰ. 5፡8-9
8. የዘላለም ሕይወት፣ ቲቶ 1፡2፤ 3፡7
9. በክርስትና የመብሰል ውጤቶች፣ ሮሜ. 5፡2-5
10. የፍጥረት ሁሉ መቤዠት፣ ሮሜ. 8፡20-22
11. የእግዚአብሔር ማዕርግ፣ ሮሜ. 15፡13
12. ልጆች የሚቀዳጁት፣ ሮሜ. 8፡23-25
13. ብኪ እንደ መመሪያ ለአኪ አማኞች፣ ሮሜ. 15፡4

▣ "የእግዚአብሔር ክብር" ይህ ሐረግ የብኪ ፈሊጥ ሲሆን የእግዚአብሔርን አካላዊ ሕላዌ ያሳያል:: ይህም የሚያመለክተው አማኞች በትንሣኤ ቀን በእግዚአብሔር ፊት መቆማቸውን ይህም ከኢየሱስ ባገኙት የእምነት ጽድቅ ይሆናል (2ኛ ቆሮ. 5፡21):: እሱም ዘወትር በሥነ-መለኮታዊ ቃሉ "መክበር" በሚል ይጠራል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 9-10፤ 8፡30):: አማኞች ኢየሱስን የመምሰል ድርሻ ይኖራቸዋል (1ኛ ዮሐንስ 3፡2፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡4):: ልዩ ርዕስ፡ ክብር 3፡23 ላይ ተመልከት::

5፡3

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን" |
| አኪጀቅ | "ያም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን" |
| አየተመት | "ያም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን" |
| አእት | -ተገድፏል- |
| ኢመቅ | "ያም ብቻ አይደለም" |

ጳውሎስ የቃላት ቅንብሮችን ብዙ ጊዜ ተጠቅሟል (ዝኒ ከማሁ. 5፡3፣ 11፤ 8፡23፤ 9፡10፣ እና 2ኛ ቆሮ. 8፡19)::

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "በመከራችንም ደግሞ እንመካለን" |
| አኪጀቅ | "በመከራችንም ደግሞ እናከብራለን" |
| አየተመት | "በመከራችን ደግሞ እንመካለን" |
| አእት | "በችግሮቻችን ደግሞ እንመካለን" |
| ኢመቅ | "እንደሰት፣ በጣም፣ በመከራችን" |

ዓለም ኢየሱስን ከጠላው፣ የሱን ተከታዮችም ይጠላል (ማቴ.10፡22፤ 24፡9፤ ዮሐንስ 15፡18-21):: ኢየሱስ ሙሉ ነበር፣ እንደ ሰው አገላለጽ፣ በተቀበለው መከራ ሁሉ (ዕብ. 5፡8):: መከራ ጽድቅን ያመጣል፣ ይህም ለእያንዳንዱ አማኝ የሆነ የእግዚአብሔር እቅድ ነው (ዝኒ ከማሁ. 8፡17፡19፤ ሐዋ. 14፡22፤ ያዕቆብ 1፡2-4፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡12-19)::

▣ "እናውቃለን" የተጠናቀቀ ቦዝ አንቀጽ ነው፣ "ኦይዳ oida":: በቅርጽ የተጠናቀቀ ይመስላል፣ ነገር ግን አገባቡ እንደ የአሁን ጊዜ ነው:: የአማኞች አረዳድ በዚህ የወንጌል ሐቅ ላይ፣ ከመከራ ጋር ሲያያይዙት ሕይወትን በደስታና በጽናት እንዲጋፈጡ፣ ይህም በሁኔታዎች በማይወሰን መልኩ፣ ሊገደሉ ባለ ጊዜ እንኳ የሚደረግ ነው (ፊሊጵ. 4፡4፤ 1ኛ ተሰ. 5፡16፣ 18)::

5:3 “መከራ” የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

**ልዩ ርዕስ፡ መከራ**
በጳውሎስ እና በዮሐንስ መካከል የዚህ (ትሊፕሲስ thlipsis) የሚለው ቃል አጠቃቀም ሥነመለኮታዊ ልዩነት ይኖረዋል፡

I. የጳውሎስ አጠቃቀም (የኢየሱስን አጠቃቀም የሚያንጸባርቀው)
  ሀ. ችግሮች፣ መከራዎች፣ በወደቀው ዓለም ላይ የተገኘ ክፉ
    1. ማቴ. 13፡21
    2. ሮሜ. 5፡3
    3. 1ኛ ቆሮ. 7፡28
    4. 2ኛ ቆሮ. 7፡4
    5. ኤፌ. 3፡13
  ለ. ችግሮች፣ መከራዎች፣ በማያምኑት የተፈጠረ ክፉ
    1. ሮሜ. 5፡3፤ 8፡35፤ 12፡12
    2. 2ኛ ቆሮ. 1፡4፣ 8፤ 6፡4፤ 7፡4፤ 8፡2፣ 13
    3. ኤፌ. 3፡13
    4. ፊሊጵ. 4፡14
    5. 1ኛ ተሰ. 1፡6
    6. 2ኛ ተሰ.1፡4
  ሐ. ችግሮች፣ መከራዎች፣ የመጨረሻው ዘመን ክፉ
    1. ማቴ. 24፡21፣ 29
    2. ማርቆስ 13፡ 19፣ 24
    3. 2ኛ ተሰ. 1፡6-9
II. የዮሐንስ አጠቃቀም
  ሀ. ዮሐንስ የተወሰነ ልዩነት አድርጓል፣ በትሊፕሲስ (thlipsis) እና ኦርጌ (orgê) መካከል ወይም ቱሞስ (thumos) (ቁጣ) በራዕይ ላይ። ትሊፕሲስ የሚለው የማያምኑ በአማኞች ላይ የሚያደርጉትን ሲሆን፣ ኦርጌ ደግሞ እግዚአብሔር በማያምኑት ላይ የሚያደርገውን ነው
    1. ትሊፕሲስ (thlipsis) - ራዕ. 1፡9፤ 2፡9-10፣ 22፤ 7፡14
    2. ኦርጌ (orgê) - ራዕ. 6፡16-17፤ 11፡18፤ 16፡19፤ 19፡15
    3. ቱሞስ (thumos) - ራዕ. 12፡12፤ 14፡8፣ 10፣ 19፤ 15፡2፡7፤ 16፡1፤ 18፡3
  ለ. ዮሐንስ ከዚህም በላይ ቃሉን በወንጌሉ ላይ፣ አማኞች በየዘመናቱ የሚገጥማቸውን መከራ አንጸባርቆበታል - ዮሐንስ 16፡33።

**5፡3፣4 “መጽናት”** ይህ ቃል “ፍቃደኝነት፣” “ንቁ፣” “ቁርጠኝነት፣” “ጽናት” ማለት ነው። ይህም ቃሉ የሚገናኘው ከሁለቱም፣ ማለትም ሰዎችን፣ እንዲሁም ሁኔታዎችን መታገሥ ነው። ልዩ ርዕስ 8፡25 ተመልከት።

5:4

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“የተፈተነ ስብዕና”** |
| **አኪጀቅ፣ አየተመት** | **“ስብዕና”** |
| **አእት** | **“የእግዚአብሔር ማጽደቂያ”** |
| **ኢመቅ** | **“የተፈተነ ስብዕና”** |

በሰባ (LXX) ዘፍ. 23፡16፤ 1ኛ ነገሥ. 10፡18፤ 1ኛ ዜና. 28፡18 ላይ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ብረታ ብረቶችን ለመቀደስና ለማትባት፣ መፈተንን (በእሳት) ለመግለጽ ነው፣ (2ኛ ቆሮ. 2፡9፤ 8፡2፤ 9፡13፤ 13፡3፤ ፊሊጵ. 2፡22፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡15፤ ያዕ. 1፡12)። የእግዚአብሔር ፈተናዎች ሁልጊዜ ለማጠንከር ነው (ዕብ. 12፡10-11)! ልዩ ርዕስ፡ ፈተና 2፡18 ተመልከት።

**5፡5 “ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ”** የተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ነው፤ በጥሬ ቃሉ፣ “የእግዚአብሔር ፍቅር ነበረ፣ እናም መፍሰሱን ይቀጥላል” ማለት ነው። ይህ ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለመንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋ. 2፡17፣ 18፣ 33፤ 10፡45 እና ቲቶ 3፡6)፣ ይህም ኢዩኤል 2፡28-29ን የሚያንጸባርቀው።
አገናዛቢው ሐረግ፣ “የእግዚአብሔር ፍቅር” በሰዋሰዋዊ አገባቡ የሚያመለክተው (1) እኛ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር፤ ወይም (2) እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡14)። ቁጥር ሁለት ብቸኛው ጽሑፋዊ አማራጭ ነው።

**▣“በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ”** ይህ የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው። ተገብሮ ግሡ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው የእግዚአብሔርን አድራጊነት ለመግለጽ ነው። ይህም የሚያመለክተው አማኞች ብዙ መንፈስ እንደማያሻቸው ነው። አንድም

*መንፈሱ ይኖራቸዋል ወይም ክርስቲያን አይደሉም* (ዝኒ ከማሁ. 8፡9)። *የመንፈሱ መሰጠት የአዲሱ ዘመን ምልክት ነበር* (ኢዮኤል 2፡28-29)፣ *አዲሱ ኪዳን* (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡22-32)።

▣ በዚህ *አንቀጽ ያሉትን ሦስቱን የሥላሴ አካላት አስተውል*፣
1. እግዚአብሔር፣ ቁ. 1፣2፣5፣8፣10
2. ኢየሱስ፣ ቁ. 1፣6፣8፣9፣10
3. *መንፈስ*፣ ቁ. 5

ልዩ ርዕስ፡ *ሥላሴ* 8፡11 *ተመልከት*።

**አአመመቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 5፡6-11**
**[6]ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። [7]ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። [8]ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። [9]ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን። [10]ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ [11]ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።**

5፡6

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | *"ገና ረዳት አልባ በነበርንበት ሰዓት"* |
| ***አኪጀቅ*** | *"ገና አቅም በሌለን ሰዓት"* |
| ***አየተመት*** | *"ገና ደካሞች በነበርንበት ሰዓት"* |
| ***አእመቅ*** | *"ገና ረዳት አልባ በነበርንበት ሰዓት"* |
| ***ኢመቅ*** | *"ረዳት አልባ እንደነበርን"* |

*ግሡ የአሁን ቦዝ አንቀጽ ነው። ይህም የሚያመለክተው የሰው ልጆችን አዳማዊ የወደቀ ተፈጥሮ ነው። ሰዎች ኃጢአትን በመቃወም ረገድ አቅመ-ቢስ ናቸው። "እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም የሚገልጸው እና ትይዩ የሆነው ገላጭ የሆነውን ስም ቁ.* 6ለ *"መልካም ያልሆነ፣" ቁ.8 "ኃጢአተኞች፣" እና ቁ.* 10 *"ጠላቶች" የሚሉትን ነው። ቁጥር* 6 *እና* 8*ከሥነ-መለኮትና ከአወቃቀር አኳያ ትይዩ ናቸው።*

▣

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ፣ አየተመት*** | ***"በትክክለኛው ሰዓት"*** |
| ***አኪጀቅ*** | ***"በተገቢው ሰዓት"*** |
| ***አእት*** | ***"እግዚአብሔር በመረጠው ሰዓት"*** |
| ***ኢመቅ*** | ***"እሱ በፈቀደው ጊዜ"*** |

*ይህ ከታሪክ አኳያ የሚያመለክተው* (1) *የሮማ ሰላም ነጻ መዘዋወርን መፍቀዱ፤* (2) *የግሪክ ቋንቋ ሁሉን አቀፍ የሆነ ባህላዊ ግንኙነት መፍጠሩ፤ እና* (3) *የግሪክና የሮማ ጣዖታት መጥፋት በመንፈስ ተስፋ አድራጊና ረሀብተኛ የሆነ ዓለም መፍጠሩ* (*ማርቆስ* 1፡15፤ *ገላ.* 4፡4፤ *ኤፌ.* 1፡10፤ *ቲቶ* 1፡3)። *ከሥነ-መለኮት አኳያ ሥጋዌ* (*የክርስቶስ ሥጋ መልበስ*)፣ *የታሰበበት መለኮታዊ ክስተት ነው* (*ሉቃስ* 22፡22፤ *ሐዋ.* 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ *ኤፌ.* 1፡11)።

**5፡6፣ 8፣ 10 "ለኃጢአተኞች ሞቶአልና"** *ይህ የተጠናቀቀ ድርጊት አመላካች ነው። እሱም የሚያሳየው የኢየሱስን ሕይወት እና ሞት እንደ አንድ ወጥ ክስተት ነው። "ኢየሱስ ዕዳችንን ከፈለ፣ እሱ ዕዳ አልነበረበትም፤ እኛ ዕዳ ውስጥ ገብተን መክፈል ያቃተንን"* (*ገላ.* 3፡13፤ 1ኛ *ዮሐንስ* 4፡10)።

*የኢየሱስ ሞት በጳውሎስ ጽሑፎች ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው። በርካታ የተለያዩ ቃላትንና ሐረጋትን የኢየሱስን የተለዋጭነት ሞት ለመጥቀስ ተጠቅሟል፡*

1. *"ደም"* (*ዝኒ ከማሁ.* 3፡25፤ 5፡9፤ 1ኛ *ቆሮ.* 11፡25፣ 27፤ *ኤፌ.* 1፡7፤ 2፡13፤ *ቆላ.* 1፡20)
2. *"ራሱን አሳልፎ ሰጠ"* (*ኤፌ.* 5፡2፣ 25)
3. *"አሳልፎ ሰጠ"* (*ሮሜ.* 4፡25፤ 8፡32)
4. *"ተሠዋ"* (1ኛ *ቆሮ.* 5፡7)
5. *"ሞተ"* (*ሮሜ.* 5፡6፤ 8፡34፤ 14፡9፣ 15፤ 1ኛ *ቆሮ.* 8፡11፤ 15፡3፤ 2ኛ *ቆሮ.* 5፡15፤ *ገላ.* 5፡21፤ 1ኛ *ተሰ.* 4፡14፤ 5፡10)
6. *"መስቀል"* (1ኛ *ቆሮ.* 1፡17-18፤ *ገላ.* 5፡11፤ 6፡12-14፤ *ኤፌ.* 2፡16፤ *ፊሊጵ.* 2፡8፤ *ቆላ.* 1፡20፤ 2፡14)
7. *"ስቅለት"* (1ኛ *ቆሮ.* 1፡23፤ 2፡2፤ 2ኛ *ቆሮ.* 13፡4፤ *ገላ.* 3፡1)

*ሁፐር* (*huper*) *የሚለው መስተጻምር በዚህ ጽሑፍ ያለው ትርጉም*

1. *ውክልና፣ "በእኛ ምትክ"*
2. *ምትክ፣ "በእኛ ቦታ"*

ተገቢው የሁፐር መሠረታዊ ፍቺ፣ ከአገናዛቢነት አኳያ "በምትክ" ማለት ነው (ሉው እና ሊንዳ)። እሱም የሚገልጸው የተወሰኑ ጠቀሜታዎች ለሰዎች መጨመራቸውን ነው (*የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት*፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 1196)። ሆኖም፣ ሁፐር (huper)፣ አንቲ (anti) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ስሜት ያለው ሲሆን፣ የሚያሳየውም "በሌላው ምትክ" ማለት ሆኖ ይህም ከሥነ-መለኮት አኳያ የሚያሳየው በሁለተኛ ሰው ምትክነት የሚገኝ ሥርየትን ነው (ማርቆስ 10፡45፤ ዮሐንስ 11፡50፤ 18፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡14፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡6)። ኤም. ጄ. ሃሪስ (ኒዶቴ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ1197)፣ "ነገር ግን ጳውሎስ ስለምን ክርስቶስ የሞተው አንቲ ሄሞን ነው በሚል ፊጽሞ አልጠቀሰም? (1ኛ ጢሞ. 2፡6 ቀረብ ያለው - አንቲሉትሮን ሁፐር ፓንቶን ይሆን)? ምናልባት ሁፐር የተባለው መስተጻምር፣ ከአንቲ በተለየ መልኩ እግረ መንገዱን ውክልና እና ምትክነቱን ስለገለጸው ይሆናል" ብሏል።

ኤም. አር.ቪንሰንት፣ የቃሉ ጥናት፣ ቅጽ 2፣ እንዲህ ይላል

"ብዙ የሚያወዛግበው ሁፐር፣ (ስለእሱ ሆኖ)፣ ከአንቲ (በምትኩ) ጋር እኩል ሊሆን ይችላል። የቀደሙት ጸሐፍት ሁኔታዎችን በማሳየት ትርጉሞቹ ተወራራሽ መሆናቸውን ያመለክታሉ... የዚህ አንቀጽ ፍቺ፣ የሆነ ሆኖ፣ በርግጠኝነት በተገቢው ማስረጃ አለመደገፉን ያሳያል። መስተጻምሩ ምናልባት ዘዬአዊ ፍቺ ሊኖረው ይችላል፣ በሙት ላይ። ማናቸውም እነዚህ አንቀጾች ወሳኝ በመሆን ሊወሰዱ አይችሉም። በእጅጉን ሊባል የሚችለው ግን፣ ሁፐር በአንቲ ፍቺ ላይ ማዋሰኑን ነው። *በዚያ ቦታ* በእጅጉን የሚያሳየው ቀኖናዊ ዳራውን ነው። በጣም ብዙው አንቀጾች ሐሳቡ በግልጽ፣ *ለእነሱ ብሎ፣ በእነሱ ምትክ* የሚል ነው። ትክክለኛው መግለጫ ሊሆን የሚችለው፣ በአንቀጾች፣ በተለይም በጥያቄ መልክ፣ እነሱም፣ ከክርስቶስ ሞት ጋር የሚገናኙት፣ እዚህ ገላ. 3፡13፤ ሮሜ.14፡15፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡18፣ እንደተጠቀሱት፣ ሁፐር ያልተወሰነና አጠቃላይ መስተጻምር ባሕርይ መያዙ ነው– ክርስቶስ በምትክ ሞተ– ያልተለመደ ሁኔታ በማሳየት፣ በምትኩ ያልተወሰነ ሆኖ፣ ብሎም በሌሎቹ አንቀጾች እልባት የሚያገኝ ነው። *በምትክ* የሚለው ፍቺ ምናልባት ታክሎበት ይሆናል፣ ይህም ግን በትርጓሜ ነው" (ገጽ 692)።

5፡7 ይህ ቁጥር የሰዎችን ፍቅር ሲያሳይ፣ ቁጥር 8 ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍቅር ያሳያል!

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**

| | |
|---|---|
| **አእት** | **"ለጻድቅ ሰው"** |
| **አየተመት** | **"ለጻድቅ ሰው"** |
| **ኢመቅ** | **"ለደጎና ሰው"** |

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ልክ እንደ ኖኅ እና ኢዮብ ጻድቅና ያለ ነውር ለሆኑ ሰዎች ባለ ሁኔታ ነው። እነሱ በዘመናቸው የነበረውን ሃይማኖታዊ መስፈርቶች ተከትለዋል። ኃጢአት አልባ ናቸው ማለትን አያሳይም። በ1፡17 ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

5፡8 **"እግዚአብሔር የራሱን ፍቅር ገልጿልና"** ይህ የአሁን የድርጊት አመላካች ነው (ዝኒ ከማሁ. 3፡5)። አብ ልጁን ላከ (ዝኒ ከማሁ. 8፡3፣ 32፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡19)። የእግዚአብሔር ፍቅር ስሜታዊ አይደለም፣ ነገር ግን በተግባር የሚታይ ነው (ዮሐንስ 3፡16፤ 1ኛ ዮሐንስ 4፡10) <u>ቋሚ</u> ነው።

5፡9 **"ይልቁንስ"** ይህ አንደኛው ተወዳጅ አገላለጹ ነው (ቁ. 10፣15፣17)። እግዚአብሔር አማኞችን ገና ኃጢአተኛ ሳሉ እጅግ በጣም ከወደደ፣ አሁን ደግሞ ልጆቹ ሲሆኑ የቱን ያህል ይወዳቸው! (ዝኒ ከማሁ. 5፡10፤ 8፡22)።

▣**"አሁንም ከጸደቁ"** ይህ የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ሆኖ አጽንዖት የሚሰጠው ጽድቅን እንደ ተጠናቀቀ ድርጊትና በእግዚአብሔር እንደሚቀዳጁት ነው። ጳውሎስ በቁ. 1 ያለውን እውነት ደግሞታል። እንዲሁም "ጸድቋል" የሚለውን (ቁ. 9) እና "ታርቋል" (ቁ. 10-11) ማስታወሻ አለ።

▣**"በደሙ"** ይህ የሚያመላክተው የክርስቶስን የመሥዋዕትነት ሞት ነው፣ (ዝኒ ከማሁ. 3፡5፤ ማርቆስ10፡45፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡ 21)። ይህ የመሥዋትነት ጽንሰ-ሐሳብ፣ ንጹሕ የሆነ ሕይወት፣ በኃጢአተኛ ሕይወት ምትክ መሰጠቱ፣ ወደ ሌዋ. 1-7 እና እንዲሁም ዘጸ. 12 (የፋሲካን በግ) የሚያመላክት ሲሆን፣ ከሥነ-መለኮት አኳያም ተግባራዊ የሆነው በኢየሱስ ላይ ነው፣ ኢሳ. 53፡4-6። የተጠናከረውም በክርስቶሳዊ ሐሳብ በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ ነው። ዕብራውያን፣ በአግባብ ብሉይና አዲስ ኪዳንን በብዙ ነጥቦች ያወዳድራል።

▣**"እንድናለን"** ይህ የድርጊት ተገብሮ አመላካች ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ.10)። ይህ የሚያሳየው የመዳረሻ ድኅነታችንን ሲሆን፣ "መክበር" በሚል ይጠራል (ዝኒ ከማሁ. ቁ.2፤ 8፡30፣ 1ኛ ዮሐንስ 3፡2)።

አኪ ድኅነትን በሁሉም ዓይነት የግሥ ጊዜያቶች ይገልጻል።

1. የተጠናቀቀ ድርጊት (ያለፈ ድርጊት)፣ ሐዋ. 15፡11፤ ሮሜ 8፡24፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ ቲቶ 3፡5
2. ያለፈ ጊዜ ድርጊት ውጤቱ አሁን ያለ (የተጠናቀቀ ድርጊት)፣ ኤፌ. 2፡5፣8
3. ቀጣይ ሂደት (የአሁን)፣ 1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡15፤ 1ኛ ተሰ. 4፡14፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21
4. ወደፊት የሚቀዳጁት (የትንቢት)፣ ሮሜ. 5፡9፣10፤ 10፡9።

ልዩ ርዕስ 10፡13 ተመልከት፡፡ መዳን የሚጀምረው በመነሻ ውሳኔ ሲሆን ግንኙነቱ እያደገ ሄዶ አንድ ቀን የምንቀዳጀው ይሆናል፡፡ ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ዘወትር በሦስት የሥነ-መለኮት ቃላት ይገለጻል፡ መጽደቅ፣ ማለትም "ከኃጢአት ቅጣት ነጻ መውጣት"፤ መቀደስ፣ ማለትም "ከኃጢአት ኃይል ነጻ መውጣት"፤ እና መክበር፣ ማለትም "ካለ ኃጢአት ነጻ መውጣት፡፡"

መጽደቅና መቀደስ የእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊቶች ሲሆኑ ለአማኙ በክርስቶስ በማመኑ የሚሰጡት ናቸው እንጂ ከምንም አይደሉም፡፡ ሆኖም አኪ. ስለ መቀደስ ሲገልጽ ሂደቱ ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚቀጥል መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህም ምክንያት ሥነ-መለኮታውያን ስለ "ማዕርጋዊ መቀደስ" እና "አዳጊ መቀደስ" ይናገራሉ፡፡ ይህም የነጻ ድኅነት ምሥጢር ሲሆን ከመልካም ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው!

▣ **"ከእግዚአብሔር ቁጣ"** ይህ ከመጨረሻው የሰው ልጆች መለኮታዊ ግብ ጋር የሚያያዝ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ታላቅ፣ የማይገባን የሆነ፣ በዋጋ የማይገመት ፍቅር ገልጾ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በኃጢአትና በአመጻ ላይ ያለውን የጸና ተቃውሞ በግልጽ ይነግረናል፡፡ እግዚአብሔር የመዳንን መንገድ እና ይቅርታውን በክርስቶስ በኩል ሰጥቷል፣ ነገር ግን እሱን የናቁ በቁጣ ሥር ናቸው (ዝኒ ከማሁ. 1፡18-3፡20)፡፡ ይህ የሰው ልጆችን ጠባይ የሚያሳይ ሐረግ ሲሆን የሚያስረዳው ግን እውነትን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቁጣ ላይ መውደቅ በጣም የሚያስፈራ ነገር ነው (ዕብ. 10፡ 31)፡፡

5፡10 **"በ... ከ... (ቢሆን)"** ይህ አንደኛ ምድብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ለጽሑፋዊ ጥቅሙ ነው፡፡ ስብእና፣ የእግዚአብሔር ዋነኛው ፍጥረት፣ ጠላት ሆነ! ሰው (ዘፍ. 3፡5) እና ሰይጣን (ኢሳ. 14፡14፤ ሕዝ. 28፡2፣ 12-17) ተመሳሳይ ችግር አለው፣ ነጻነትን መሻት፣ ለመቆጣጠር መፈለግ፣ አማልክት የመሆን ፍላጎት፡፡

▣ **"ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን... ከታረቅን"** ይህ ሁለቱም ማለት፣ የድርጊት ተገብሮ አመላካች እና የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው፡፡ "መታረቅ" የሚለው ግሥ ከመነሻው "መለዋወጥ" ማለት ነው፡፡እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በኢየሱስ ጽድቅ ለውጦታል (ኢሳ. 53፡4-6)፡፡ ሰላም ተመልሷል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 1)!

▣ **"በልጁ ሞት በኩል"** የይቅርታ ወንጌል መሠረት ያደረገው (1) የእግዚአብሔር ፍቅር፤ (2) የክርስቶስ ሥራ፤ (3) የመንፈስ መቃተት፣ እና (4) እምነት/ ግለሰባዊ የንስሐ ምላሽን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ለመሆን ሌላ መንገድ የለም (ዮሐንስ 14፡6)፡፡ የመዳን ዋስትና የተመሠረተው በሥላሴ (በእግዚአብሔር) ባሕርይ እንጂ በሰው ሥራ አይደለም! አያዎ (ፓራዶክስ) የሚሆነው የሰው ልጅ ከዳነ በኋላ ያለው ምግባር የነጻ ደኅንነቱ ማስረጃ ነው (ያዕቆብ እና 1ኛ ዮሐንስ)፡፡

▣ **"እንድናለን"** አኪ. ስለ ድኅነት የሚናገረው ባለፈ፣ በአሁን፣ እና በወደፊት ጊዜ ነው፡፡ እዚህጋ የትንቢት ጊዜው የሚጠቅሰው በዳግም ምጽአቱ የምናገኘውን የመጨረሻ ግብ፣ የተጠናቀቀ ድኅነትን ነው፡፡ ቁ. 9 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና ልዩ ርዕስ 10፡13 ተመልከት፡፡

▣ **"በሱ ሕይወት"** የዚህ ለሕይወት የተሰጠ የግሪክ ቃል ዞአ (zoa) ይባላል፡፡ ይህ ቃል በዮሐንስ ጽሑፎች ዘወትር የሚጠቀሰው ለትንሣኤ ሕይወት፣ ለዘላለም ሕይወት፣ ወይም ለመንግሥት ሕይወት ነው፡፡ ጳውሎስ በተጨማሪም ጥቅም ላይ ያዋለው በዚህ ሥነ-መለኮታዊ እሳቤ ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ አመኔታ፣ እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ ዋጋ ለአማኞች ይቅርታ ከከፈለ፣ በርግጥ በቀጣይነትም ለውጤታማነቱ እንዲሁ ነው፡፡

"ሕይወት" የሚያመላክተው አንድም (1) የኢየሱስን ትንሣኤ (ዝኒ ከማሁ. 8፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 15)፤ (2) የኢየሱስን የማስታረቅ ሥራ (ዝኒ ከማሁ. 8፡34፤ ዕብ. 7፡25፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡1)፤ ወይም (3) መንፈስ ኢየሱስን በእኛ መቅረጹ (ሮሜ 8፡29፤ ገላ. 4፡19)፡፡ ጳውሎስ የሚያስረዳው የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት እና ሞት ከዚህም በላይ ማዕርግ ያለው መንፈሳዊ ሕይወቱ፣ እነዚህ የመታረቃችን መሠረቶች ናቸው፡፡

5፡11 **"ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን"** በቁጥር 3 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

▣**"እኛም ደግሞ እንመካለን"** 5፡2 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ ይህ "መደሰት" የሚለው ቃል ሦስተኛው አጠቃቀም ነው፣ በዚህ ጽሑፍ፣ (መመካት)፡፡

1.በክብር ተስፋ መመካት፣ ቁ. 2
2.በመከራ መመካት፣ ቁ. 3
3.በመታረቅ መመካት፣ ቁ. 11

አሉታዊ የሆነ ትምክሕት በ2፡17 እና 23 ላይ ታይቷል!

▣**"አሁንም እኛ መታረቅን ተቀብለናል"** ይህ ያለፈ ድርጊት አመላካች ሆኖ፣ የተጠናቀቀ ድርጊትን የሚያሳይ ነው፡፡ የአማኞች መታረቅ እንዲሁ በቁ. 10 እና 2ኛ ቆሮ. 5፡18-21፤ ኤፌ. 2፡16-22፤ ቆላ. 1፡19-23 ላይ ተብራርቷል፡፡ በዚህ ጽሑፍ "መታረቅ"ሥነ-መለኮታዊ ተመሳሳዩ "መጽደቅ" ማለት ነው፡፡

5:12-14

[12]ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ [13]ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤ [14]ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።

5:12 "ስለዚህ" ሮሜ በርካታ ስልታዊ አገባብ ያለው "ስለዚህ" አለው (ዝኒ ከማሁ. 5:1፤ 8:1፤ 12:1)። ትርጉማዊ ጥያቄው ከምን ጋር ይዛመዳሉ የሚል ነው። እነሱ ከሁሉም የጳውሎስ የክርክር አገባቦች ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ። በርግጠኝነት ይሄኛው የሚዛመደው ከዘፍጥረት ጋር ነው፣ እና ስለዚህ ምናልባትም ወደ ሮሜ 1:18-32 ያመላክታል።

▣ "በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም እንደገባ" በቁ.12 ያሉት ሦስቱም ግሦች የተጠናቀቁ ጊዜያት ናቸው። የአዳም ውድቀት ሞትን አመጣ (1ኛ ቆሮ. 15:22)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት መነሻ እምብዛም የለውም። ኃጢአት የተከሰተው በመላእክት ግዛት ነው (ዘፍ. 3 እና ራዕ. 12:7-9)። እንዴትና መቼ እንደሆነ ርግጠኝነት የለውም (ኢሳ. 14:12-27፤ ሕዝ. 28:12-19፤ ኢዮብ 4:18፤ ማቴ. 25:41፤ ሉቃስ 10:18፤ ዮሐንስ 12:31፤ ራዕ. 12:7-9)።

የአዳም ኃጢአት ሁለት ገጽታዎችን ያጣቅሳል፣ (1) ለልዩ ትዕዛዝ አለመታዘዝ (ዘፍ. 2:16-17)፣ እና (2) ራስ-ተኮር ኩራት (ዘፍ. 3:5-6)። ይህ ዘፍጥረት 3 በተከታይ ማጣቀስ የሚጀምረው ሮሜ 1:18-32 ነው።

ይህ የኃጢአት ሥነ-መለኮት ነው ጳውሎስን ከራቢያዊ አስተምሕሮት በግልጽ የለየው። ራቢዎች (የአይሁድ መምህራን) በዘፍ. 3 ላይ አያተኩሩም፤ በአንጻሩ የሚሉት በእያንዳንዱ ሰው ሁለት "ዓላማዎች" (የትዘርስ *yetzers*) እንዳሉ ነው። የእነሱ የታወቀው ራቢያዊ አገላለጽ፣ "በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ጥቁርና ነጭ ውሾች አሉ። በሚገባ የምትመግበው ትልቅ ይሆናል" የሚል ነው። ጳውሎስ ኃጢአትን በእግዚአብሔርና በፍጥረቱ መካከል የሚገኝ ዋነኛው መሰናክል እንደሆነ ተመልክቷል። ጳውሎስ ስልታዊ የሥነ-መለኮት ሰው አልነበረም (የጀምስ ስቲዋርድ *የክርስቶስ ሰው*)። በርካታ የኃጢአት መነሻዎችን አመላክቷል (1) የአዳም መውደቅ፣ (2) ሰይጣናዊ ፈተና፣ እና (3) ቀጣዩ የሰው ልጅ ዐመጻ።

በሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ እና ትይዩ፣ በአዳምና በኢየሱስ መካከል ባለው፣ ሁለት ዓይነት ውጤቶች አሉ።

1. አዳም በርግጥ ታሪካዊ ሰው መሆኑ።
2. ኢየሱስ በርግጥ የሰው ልጅ መሆኑ።

እነዚህ ሁለቱም እውነቶች በሐሰተኛ ትምህርት አንጻር የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት ያጸናሉ። "አንድ ሰው" ወይም "ሰውየው" የሚሉት በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ እንደዋሉ አስተውል። እነዚህ ሁለት ስለ አዳምና ስለ ኢየሱስ የሚገልጹት አገባቦች በዚህ ጽሑፍ ላይ አስራ አንድ ጊዜ ተጠቅሰዋል።

▣ "በኃጢአት ምክንያት ሞት" መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ዓይነት የሞት ደረጃዎች እንዳሉ ይገልጻል (1) መንፈሳዊ ሞት (ዘፍ. 2:17፤ 3:1-7፤ ኤፌ. 2:1)፤ (2) ሥጋዊ ሞት (ዘፍ. 5)፤ እና (3) የዘላለም ሞት (ራዕ. 2:11፤ 20:6፣ 14፤ 21:8)። በአንቀጹ የተጠቀሰው ስለ አዳም መንፈሳዊ ሞት ሲሆን (ዘፍ. 3:14-19) ይህም ውጤት የሰው ልጆችን ሥጋዊ ሞት ያስከተለ ነው (ዘፍጥረት 5)።

▣ "ሞትም በሰዎች ሁሉ ላይ ሆነ" የዚህ አንቀጽ ዋነኛው ትኩረት የኃጢአት ሁለንተናዊነት ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 16-19፤ 1ኛ ቆሮ. 15:22፤ ገላ. 1:10) እና ሞት።

▣ "ሁሉም ኃጢአትን ስለ ሠሩ" ሁሉም የሰው ልጆች ከአዳም ጋር ኃጢአትን ሠርተዋል (ይህም ማለት የኃጢአትን ይዘትና የኃጢአትን ዝንባሌ ወርሰዋል።) በዚህን ምክንያት ነው እያንዳንዱ ሰው በግሉ ኃጢአትን የሚፈጽመውና የሚደጋግመው። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም የሰው ልጆች በሁለቱም በኩል፣ ማለትም በውርስም ሆነ በፍቃድ ኃጢአተኞች መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል (1ኛ ነገሥ. 8:46፤ 2ኛ ዜና. 6:36፤ መዝ. 14:1-2፤ 130:3፤ 143:2፤ ምሳ. 20:9፤ መክብብ7:20፤ ኢሳ. 9:17፤ 53:6፤ ሮሜ 3:9-18፣ 23፤ 5:18፤ 11:32፤ ገላ. 3:22፤ 1ኛ ዮሐንስ 1:8-10)።

ይህም ከጽሑፋዊ አጽንዖቱ አኳያ ሲታይ (ዝኒ ከማሁ. ቁ.15-19)፣ አንድ ድርጊት ሞትን አመጣ (አዳም) እንዲሁም አንድ ድርጊት ሕይወትን አመጣ (ኢየሱስ)። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ይህም የሰው ልጆች ምላሽ ትርጉም ያለው ገጽታ የሚኖረው፣ "በመጥፋት" እና "በመጽደቅ" ላይ ነው። የሰው ልጆች በመጻዒ ግባቸው ላይ ፍቃዳዊ ተሳትፎ አላቸው! በቀጣይነትም ኃጢአትን መምረጥ ወይም ክርስቶስን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህን ሁለት ምርጫዎች መደባለቅ አይችሉም፤ ዳሩግን በፍቃዳቸው ወደየትኛው እንደሚሆኑ ማሳየት ይኖርባቸዋል!

"ምክንያቱም" የሚለው ትርጉም የተለመደ ነው፣ ፍቺው ግን ዘወትር እንዳወዛገበ ነው። ጳውሎስ፣ ኢፍ ሆ (eph'hō) የሚለውን ቃል በ2ኛ ቆሮ. 5:4፤ ፊሊጵ. 3:12፤ እና 4:10 "ምክንያቱም" በሚል እሳቤ ተጠቅሞበታል። ይህም እያንዳንዱ የሰው ልጅ ምርጫ በግሉ የኃጢአት እና የዐመጻ ተሳትፎ በእግዚአብሔር ላይ ማድረጉን ያመለክታል። አንዳንዱ የተለየ መገለጥን በመናቅ፣ ሁሉም ደግሞ የተፈጥሮ መገለጥን በመናቅ ነው (ዝኒ ከማሁ. 1:18-3:20)።

5፡13-14 ይኸው ተመሳሳይ እውነት በሮሜ 4፡15 እና ሐዋ.17፡30 ላይ ይገኛል። እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነው። የሰው ልጆች በእነሱ ጋ ባለ ጉዳይ ብቻቸውን ኃላፊነት ይወስዳሉ። ቁጥሩ የሚናገረው ስለ ልዩ መገለጥ (ብኪ፣ ኢየሱስ፣ አኪ) ሳያካትት ሲሆን፣ የተፈጥሮ መገለጥን ግን አይደለም (መዝሙር 19፤ ሮሜ. 1፡18-23፤ 2፡11-16)።
አኪጀቅ የቁጥር 12ን ንጽጽር የሚያመለክተው በረዥም ቅንፍ መሆኑን አስተውል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 13-17) ከማጠቃለያው ከቁ. 18-21 ጋር።

5፡14

**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**

| | |
|---|---|
| **ኢመቅ** | **"ሞት ገዢ ሆነ"** |
| **አየተመት** | **"ሞት የበላይነቱን አረጋገጠ"** |
| **አእት** | **"ሞት ገዛ"** |

ሞት እንደ ንጉሥ ገዛ (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 17 እና 21)። ይህ የሞትና የኃጢአት ሰውኛ ዘይቤ እንደ ፈላጭ ቆራጭ በዚህ ምዕራፍም ሆነ በምዕራፍ 6 ላይ ቀጥሏል። ሁለንተናዊ የሞት ሥልጣን የሚያረጋግጠው የሰው ልጆችን ሁለንተናዊ ኃጢአት ነው። በቁጥር 17 እና 21፣ ጸጋ በሰውኛ ዘይቤ ተመልክቷል። ጸጋው ይገዛል! የሰው ልጆች ምርጫ አላቸው (ከሁለቱ የብኪ መንገዶች)፡ ሞት ወይም ሕይወት። ባንተ ሕይወት የሚገዛው የትኛው ነው?

▣**"እንደ አዳም ዓይነት በመሰለ የመተላለፍ ኃጢአት ባልወደቁት ላይ እንኳ"** አዳም የተላለፈው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ነው፣ ምንም እንኳ ሔዋን በተመሳሳይ መንገድ ኃጢአት ባትሠራም። ከአዳም ስለ ዛፉ ሰምታለች፣ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ባትሰማም። የሰው ልጆች ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ በአዳም ዐመጻ ተጎድተዋል! እነሱ በቀጥታ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ትዕዛዝ ላይ አላመጹም፣ ነገር ግን 1፡18-32፣ በርግጥ የዚህ ሥነ-መለኮት ጽንሰ-ሐሳብ በሆነው ሲታይ የሚያስቀምጠው እውነት፣ በውስጣቸው ባለ ብርሃን ላይ ከፍጥረታቸው እንዳመጹና፣ ይህም በእግዚአብሔር ላይ ለማመጻቸው/ ኃጢአትን ለመፈጸማቸው ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ ያሳያል። የአዳም የኃጢአት ዝንባሌ በልጆቹ ላይ ወርዷል።

▣

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ሊመጣ ላለው አምሳያው ነውና"** |
| **አእት** | **"አዳም ሊመጣ ላለው ተምሳሌቱ ነውና"** |
| **ኢመቅ** | **"አዳም ሊመጣ ላለው ቅድመ-ተምሳሊት ተደርጓል"** |

ይህ የሚያሳየው በጣም ተጨባጭ በሆነ መልኩ የአዳም-ክርስቶስን አጠቃላይ ምድብ ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡21-22፣ 45-49፤ ፊሊጵ. 2፡6-8)። ሁለቱም በዝርዝሩ ቀዳሚ ሆነው ነው የሚታዩት፣ የዘሩ መነሻዎች (1ኛ ቆሮ. 15፡45-49)። አዳም ከብኪ በተለየ መንገድ በአኪ "ዓይነት" ተብሎ የተጠራ ብቸኛው ነው። ልዩ ርዕስ፡ ቅርጽ (Tupos) 6፡17 ላይ ተመልከት።

> 5፡15-17
> **[15]ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። [16]አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። [17]በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።**

5፡15-19 ይህ ትይዩ ሐረጎችን በመጠቀም የቀጠለ ክርክር ነው። አአመመቅ፣ አየተመት፣ እና አእት አንቀጹን ቁጥር 18 ላይ ይከፍሉታል። ሆኖም ግን የተመቅሶ[4] (ዩቢኤስ)፣ አኪጀቅ፣ እና ኢመቅ የሚተረጉሙት እንደ አንድ አሀድ ነው። የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመተርጎም ቁልፉ በእያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት እንደሆነ አስተውል። "ብዙ" የሚለው ቃል ቁ. 15 እና 19 ያለው፣ "ሁሉም" ከሚለው ቁ. 12 እና 18 ከሚገኘው ጋር እንደዛው ነው። ምንም ዓይነት ሥነ-መለኮታዊ ልዩነቶች፣ (የካልቪን የተመረጠ ወይም ያልተመረጠ) በእነዚህ ቃላት ላይ መመሥረት አለበት!

5፡15 **"ነጻ ስጦታ"** ሁለት የተለያዩ ዓይነቶች የግሪክ ቃላት "ስጦታ" ለሚለው ጥቅም ላይ ውለዋል– ክሪስማ (chrisma,) ቁ. 15፣16 (6፡23) እና ዶሪአ/ዶራማ (dorea/ dorama) ቁ. 15፣ 16፣ 17 (ቁ. 3፡24 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)– ነገር ግን ተመሳሳይ ናቸው። ይህ በርግጥ ስለ ደኅንነት መልካም ዜና (ወንጌል) ነው። ከእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነጻ ስጦታ ነው (ዝኒ ከማሁ. 3፡24፤ 6፡23፤ ኤፌ. 2፡8፣9) በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ።

▣ **"በ… ከ… (ቢሆን)"** ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ ይህም ከጸሐፊው ሐሳብ ወይም ለጽሑፋዊ ጠቀሜታው አኳያ ተገቢ እንደሆነ ይገመታል። የአዳም ኃጢአት በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ሞትን አስከተለ። ይህ ከቁ. 17 ጋር ትይዩ ነው።

▣ **"የተትረፈረፈ"** ልዩ ርዕስ 15:13 ተመልከት።

**5:16 "ኵነኔ... ጽድቅ"** እነዚህ ሁለቱም ሕግነክ፣ ሕጋዊ ቃላት ናቸው። በብኪ ዘወትር የነቢያት መልአክት የሚቀርበው በፍርድ ቤት ትዕይንት አምሳያ ነው። ጳውሎስ ይሄንን ገጽታ (ሮሜ. 8:1 31-34) ላይ ተጠቅሟል።

**5:17 "በ... ከ... (ቢሆን)"** ይህ ሌለኛው አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ይህም ከጸሐፊው ሐሳብ ወይም ለጽሑፋዊ ጠቀሜታው አኳያ ተገቢ እንደሆነ ይገመታል። የአዳም መተላለፍ በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ሞትን አስከተለ።

▣ **"በጣም ብዙ የሚቀበሉ ሁሉ"** ቁጥር 18-19 በትክክል ሥነ-መለኮታዊ ሚዛኑን የጠበቀ አይደለም። ይህ ሐረግ ከሮሜ 1-8 ካለው ጽሑፍ ወጥቶ፣ እንደ ማጣሪያ ጽሑፍ ለሁለንተናዊነት (ማለት፣ ሁሉም በመጨረሻ ይድናሉ) ለሚለው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም። የሰው ልጆች በክርስቶስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ስጦታ የግድ መቀበል አለባቸው (ቁ.17ለ)። ደኅንነት ለሁሉም ተሰናድቷል፣ ነገር ግን በግል የሚቀበሉት ነው (ዮሐንስ 1:12፤ 3:16፤ ሮሜ. 10:9-13)።
የአዳም አንድ የዓመጸ ድርጊት በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ዐመጸኝነትን አስከተለ። አንዲቷ ኃጢአታዊ ድርጊት ገዘፈች! ነገር ግን በክርስቶስ አንድ የጽድቅ መሥዋዕት ገዝፎ የብዙዎችን ኃጢአት፣ ብሎም አጠቃላዩን የኃጢአት ውጤትም ለመሸፈን በቃ። ይህ "እጅግ ብዙው" የክርስቶስ ድርጊት ገነነ (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 9፣10፣ 15፣ 17)። ጸጋ ተትረፈረፈ!

**5:17፣18 "የጸጋ ስጦታ በሕይወታችን ላይ ይገዛል... የሕይወት ጽድቅ"** ኢየሱስ የእግዚአብሔር ስጦታ እና ለወደቁት ሁሉም የሰው ልጆች መንፈሳዊ ፍላጎት የተሰጠ ነው (1ኛ ቆሮ. 1:30)። እነዚህ ትይዩ ሐረጎች የሚሉት (1) ኃጢአተኛው የሰው ልጅ በክርስቶስ በኩል በተጠናቀቀ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት የመቆም መብት ያገኘ ሲሆን የዚህም ውጤት "መልካም አኗኗር" ነው፣ ወይም (2) ይህ ሐረግ ከ "ዘላለም ሕይወት" ጋር ተያያዥነት አለው። ጽሑፉ የመጀመሪያውን አማራጭ ይደግፋል። ጽድቅን በተመለከተ ለቃል ጥናት ልዩ ርዕስ 1:17 ተመልከት።

**ልዩ ርዕስ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ**

ከክርስቶስ ጋር መንገሥ የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ "የእግዚአብሔር መንግሥት" የሚለው የዋናው ሥነ-መለኮታዊ ምድብ ክፍል ነው። ይህም ከብኪ ተያይዞ የመጣ ጽንሰ-ሐሳብ ሲሆን እግዚአብሔር እውነተኛው የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ ያሳያል (1ኛ ሳሚ. 8:7)። እሱ በተምሳሌትነት ነግሧል (1ኛ ሳሚ. 8:7፤ 10:17-19) በትውልዶች ውስጥ ከይሁዳ ነገድ (ዘፍ. 49:10) እና ከእሴይ ቤተሰብ (2ኛ ሳሚ. 7)።

ኢየሱስ በብኪ ስለ መሲህ የተተነበየው ተስፋ ፍጻሜ ነው። እሱ የእግዚአብሔርን መንግሥት በቤተ ልሔም በመወለድ መርቀታል። የእግዚአብሔር መንግሥት የኢየሱስ ስብከት ማዕከላዊ ዐምድ ነው። መንግሥቱ ተጠቃሎ የመጣው በእሱ ነው (ማቴ. 10:7፤ 11:12፤ 12:28፤ ማርቆስ 1:15፤ ሉቃስ 10:9፣ 11፤ 11:20፤ 16:16፤ 17:20-21)።

ሆኖም መንግሥቱ ደግሞ መጻኢ ነው (የፍጻሜው ግብ)። አሁን አለ ነገር ግን አልተቀዳጀነውም (ማቴ. 6:10፤ 8:11፤ 16:28፤ 22:1-14፤ 26:29፤ ሉቃስ 9:27፤ 11:2፤ 13:29፤ 14:10-24፤ 22:16፣ 18)። ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ የመጣው (ኢሳ.52:13-53:12) ላይ፤ እንደ ትሑት (ዘካ. 9:9) ላይ፣ ነገር ግን የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ ይመለሳል (ማቴ. 2:2፤ 21:5፤ 27:11-14)። "መንገሥ" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ በርግጠኝነት የዚህ "መንግሥት" አካል የሆነ ሥነ-መለኮት ነው። እግዚአብሔር ለኢየሱስ ተከታዮች መንግሥቱን ሰጥቷል (ሉቃስ 12:32) ተመልከት።

ከክርስቶስ ጋር መንገሥ የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ በርካታ ገጽታዎችና ጥያቄዎች አሉት፡

1. እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለአማኞች የሰጠውን "መንግሥት" የሚያስረዱት አንቀጾች የሚያመለክቱት ስለ "መንገሥ" ነውን? (ማቴ. 5:3፣ 10፤ ሉቃስ 12:32)
2. የኢየሱስ ቃላት ለዋነኞቹ ሐዋርያት በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የአይሁድ ጽሑፍ መሠረት የሚያመለክቱት ለሁሉም አማኞች ነውን? (ማቴ. 19:28፤ ሉቃስ 22:28-30)
3. ጳውሎስ አጽንዖት የሰጠው በዚህ ሕይወት ላይ አሁን መንገሥ የሚለው ከላይ ከቀረቡት ጽሑፎች ጋር ይቃረናል ወይስ ተያያዥ ነው? (ሮሜ. 5:17፤ 1ኛ ቆሮ. 4:8)
4. መከራ መቀበልና መንገሥ እንዴት ይዛመዳል? (ሮሜ 8:17፤ 2ኛ ጢሞ. 2:11-12፤ 1ኛ ጴጥ. 4:13፤ ራዕ. 1:9)
5. ራዕይ ላይ በተደጋጋሚ የተነሣው ጭብጥ የከበረውን የኢየሱስን ንግሥና ያሳያል
   ሀ. ምድራዊ፣ 5:10
   ለ. ሺህ ዓመት (ሚሊኒየም)፣ 20:5፣6
   ሐ. የዘላለም፣ 2:26፤ 3:21፤ 22:5 እና ዳን. 714፣ 18፣ 27

5፡18-21
**[18]እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። [19]በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። [20-21]በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።**

5፡18
**አአመመቅ** *"እንዲሁም በአንድ የጽድቅ ሥራ ምክንያት ውጤቱ ሕይወትን ለማጽደቅ ለሰው ሁሉ ሆነ"*
**አኪጀቅ** *"እንዲሁም በአንድ ሰው የጽድቅ ሥራ ነጻ ስጦታው ወደ ሰው ሁሉ መጣ"*
**አየተመት** *"እናም የአንድ ሰው የጽድቅ ሥራ ወደ ጽድቅና ሕይወት ለሰዎች ሁሉ አመራ"*
**አእት** *"በተመሳሳይ መንገድ አንድ የጽድቅ ሥራ ሰዎችን ሁሉ ነጻ አውጥቶ ሕይወትን ሰጣቸው"*
**ኢመቅ** *"እናም የአንድ ሰው መልካም ሥራ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን አስገኝቶ አጸደቃቸው"*

ይህ አባባል ግን ሁሉም ይጸድቃሉ ማለት አይደለም (ሁለንተናዊነት)። ይህ ቁጥር ከሮሜ መጽሐፍ መልእክት እና ከዚሁ (ከቅርቡ) ጽሑፍ በተለየ መልኩ መተርጎም የለበትም። ይህ ለመጥቀስ የሚፈልገው ለሰው ልጆች ሁሉ የሆነውን መዳን ነው፣ በኢየሱስ ሕይወት/ ሞት/ ትንሣኤ። የሰው ልጅ ለቀረበለት ወንጌል በንሥሐና በእምነት ምላሽ መስጠት አለበት (ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣ 19፤ 20፡21)። እግዚአብሔር ዘወትር መነሻውን ይወስዳል (ዮሐንስ 6፡44፣65)፣ ነገር ግን እሱ እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ ምላሽ እንዲሰጥ ነው የመረጠው (ማርቆስ 1፡15፤ ዮሐንስ 1፡12፤ እና ሮሜ 10፡9-13)። ስጦታው አጠቃላይ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡4፣ 6፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡2)፣ ነገር ግን የበደል ምሥጢሩ ብዙዎች "እምቢ" ማለታቸው ነው።

"የጽድቅ ሥራ" አንድም (1) የኢየሱስ ሙሉ የመታዘዝ ሕይወት እና የአብ መገለጥ ወይም (2) በተለይም የሱ በኃጢአተኛ የሰው ልጅ ምትክ መሞቱ ነው። የአንድ ሰው ሕይወት ሁሉንም እንደነካቸው (የአይሁድ፣ በሥጋ ያሉት፣ ኢያሱ 7)፣ እንደሆነው የአንድ ጻድቅ ሕይወት ሁሎችንም ነክቷል። እነዚህ ሁለት ድርጊቶች ትይዩ ናቸው፣ እኩል ግን አይደሉም። ሁሉም በአዳም ኃጢአት ምክንያት ቢጎዱም ሁሉም በተጨባጭ በኢየሱስ ሕይወት ብቻ ነው የሚነኩት፤ የጽድቅን ስጦታ የተቀበሉት አማኞች ብቻ። የኢየሱስ ድርጊት ሁሉንም የሰው ልጆች ኃጢአት ነክቷል፣ ለሚያምኑትና ለተቀበሉት ያለፈውን፣ የአሁኑን፣ እና የወደፊቱን!

5፡18-19 **"ኵነኔ ለሰዎች ሁሉ… የጽድቅ ሕይወት ለሰዎች ሁሉ… ብዙዎች ኃጢአተኛ እንደ ሆኑ… ብዙዎች ጻድቅ ይሆናሉ"** እነዚህ ትይዩ ሐረጎች "ብዙዎች" የሚለውን ቃል የሚያሳዩ ሲሆኑ ክልከላ የለበትም፣ ነገር ግን የሚያካትት ነው። ተመሳሳይ የሆነ ትይዩነት በኢሳ. 53፡6 "ሁሉም" እና 53፡11፣ 12 "ብዙዎች" ላይ ይገኛል። "ብዙዎች" የሚለው ቃል፣ የእግዚአብሔርን የመዳን ስጦታ ለሰው ልጆች ሁሉ የሆነውን ክልከላ ባለው አግባብ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርበትም (የካልቪን የተመረጡት ወይም ያልተመረጡት)።
የሁለቱን ሐረጎች የተገባቦ ድምጸት (ግሥ) አስተውል። እነሱ የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ድርጊት ነው። የሰው ልጆች ኃጢአት የሚሠሩት ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር ባላቸው የጋራ ግንኙነት ሲሆን የሚጸድቁትም ከሱ ባሕርይ ጋር በሚኖር ግንኙነት ነው።

5፡19 **"የአንድ ሰው አለመታዘዝ… የአንዱ መታዘዝ"** ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ሥጋዊነት ጥቅም ላይ አውሎታል። የአንድ ሰው ድርጊት ሁሉንም ማኅበረሰብ ጎዳ (አካን በኢያሱ 7 ላይ)። የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ በፍጥረት ሁሉ ላይ ፍርድን አመጣ (ዘፍ. 3)። ሁሉም ፍጥረታት በአዳም የአመጻ መዘዝ ሳቢያ ጉዳት አገኛቸው (ዝኒ ከማሁ. 8፡18-25)። ዓለም አንድ ዓይነት አይደለም። የሰው ልጆች አንድ ዓይነት አይደሉም። ሞት የሁሉም ምድራዊ ሕይወት መጨረሻ ሆነ (ዘፍ. 5)። ይህ ዓለም፣ እግዚአብሔር ሲሆን የፈለገው አይደለም!
በተመሳሳይ ሥጋዊ አገባብ የኢየሱስ አንዱ የመታዘዝ ድርጊት፣ ቀራንዮ፣ ያስገኘው ውጤት (1) አዲስ ዘመን፣ (2) አዲስ ሕዝብ፣ እና (3) አዲስ ኪዳን ነው። ይህ ውክልናዊ ሥነ-መለኮት "የአዳም ክርስቶስ ምድብ" ይባላል (ፊሊጽ. 2፡6)። ኢየሱስ ሁለተኛው አዳም ነው። እሱም ለወደቀው የሰው ዘር አዲስ ጅማሮ ነው።

◙**"ጽድቅ አደረገ"** 1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

5፡20
**አአመመቅ** *"እናም መተላለፍም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ"*
**አኪጀቅ** *"ከዚህም በላይ መተላለፍ እንዲበዛ ሕግ ገባ"*
**አየተመት** *"ነገር ግን ሕግ ገባ፣ መተላለፍ እንዲበዛ አድርጎ"*
**አእት** *"ሕግ እንዲገባ ሆነ በደል እንዲበዛ ለማድረግ"*

*ኢመቅ* “ሕግ በመጣ ጊዜ፣ የመውደቅን አጋጣሚ እንዲበዛ አደረገው”

የሕግ ተግባር የሰው ልጆችን ለማዳን ፈጽሞ አልነበረም ነገር ግን የወደቁት የሰው ልጆች የሚያስፈልጋቸውንና አቅመ-ቢስ መሆናቸውን ለማሳየት ነው (ኤፌ. 2:1-3) እናም እነሱን ወደ ኢየሱስ ለማምጣት (ዝኒ ከማሁ. 3:20፤ 4:15፤ 7:5፤ ገላ. 3:19፣ 23-26)። ሕጉ መልካም ነው፣ የሰው ልጅ ግን ኃጢአተኛ ነው!

▣ **“ጸጋም ከመጠን ይልቅ በዛ”** ይህ በዚህ ክፍል ውስጥ የጳውሎስ ዋነኛው እምነት ነው። ኃጢአት አስፈሪና ሁሉምጋ የተሰራጨ ሲሆን፣ ነገር ግን ጸጋ፣ በሞት ተጽዕኖው ላይ በዝቶ ተትረፍርፏል! ይህ በአንደኛው ክፍለ ዘመን አዲሷን ቤተ-ክርስቲያን ለማበረታታት የሚደረግ መንገድ ነበር። እነሱ በክርስቶስ ድል አድራጊዎች ናቸው (ዝኒ ከማሁ. 5:9-11፤ 8:31-39፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:4)። ይህ ኃጢአትን ዳግም ለመፈጸም ፍቃድ አይደለም! ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ የሁፐር (*huper*) ድብልቆች አጠቃቀም 1:30 ላይ ተመልከት።

5:21 ሁለቱም “ኃጢአት” እና “ጸጋ” በሰውኛ ዘይቤ እንደ ንጉሥ ተደርገዋል። ኃጢአት የሚነግሠው በሁለንተናዊ ሞት ነው (ቁ. 14፣ 17)። ጸጋ የሚነግሠው በኢየሱስ ክርስቶስ ኃላፊነት በተፈጸመ የጽድቅ ሥራ ኃይል እና አማኞች ለወንጌል ቢያደርጉት የግል እምነትና የንስሐ ምላሽ ነው።
እንደ እግዚአብሔር አዲስ ሕዝብ፣ እንደ ክርስቶስ አካል፣ ክርስቲያኖችም ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ (ዝኒ ከማሁ. 5:17፤ 2ኛ ጢሞ. 2:12፤ ራዕ.22:5)። ይህ እንደ ምድራዊ ወይም የሺ ዓመት ንግሥና ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል (ራዕ. 5:9-10፤ 20)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ የሚናገረው ተመሳሳይ እውነት ይሄው መንግሥት ለቅዱሳን መሰጠቱን ነው (ማቲ. 5:3፣ 10፤ ሉቃስ 12:32፤ ኤፌ. 2:5-6)። ልዩ ርዕስ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መንገሥ 5:17 ተመልከት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንዲያሰላስሉ ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንዲወሰኑ አይደለም።

1. የእግዚአብሔርን “ጽድቅ” ግለጽ
2. በ “አቋማዊ መቀደስ” እና በ “ተጨማሪ ውርስ” መካከል ያለው ሥነ-መለኮታዊ ልዩነት ምንድነው?
3. የዳንነው በጸጋ ነው በእምነት (ኤፌ. 2:8-9)?
4. ክርስቲያኖች ለምን ይሠቃያሉ?
5. <u>ድነናል</u> ወይስ <u>እየዳንን ነው</u> ወይስ <u>እንድናለን</u>?
6. ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአትን ስለ ፈጸምን ነው፣ ወይስ ኃጢአት የምንሠራው ኃጢአተኛ ስለሆንን?
7. “መጽደቅ፣” “መዳን” እና “መታረቅ” የሚሉት ቃላት በዚህ ምዕራፍ እንዴት ይዛመዳሉ?
8. እግዚአብሔር ከሺ ዓመታት በፊት የነበረን የሌላን ሰው ኃጢአት እንዴት እኔን ተጠያቂ ያደርጋል (ቁ. 12-21)?
9. ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ለምን እያንዳንዱ ይሞታል፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ኃጢአት የማይቆጠር ከሆነ (ቁ. 13-14)?
10. “ሁሉም” እና “ብዙዎች” የሚሉት ቃላት ይመሳሰላሉ (ቁ. 18-19፣ ኢሳ. 53:6፣ 11-12)?

| የተየመቅሰ[4] | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢ.መቅ |
|---|---|---|---|---|
| ለኃጢአት መሞት ግን ለክርስቶስ መኖር | ለኃጢአት መሞት፣ ለእግዚአብሔር መኖር | ከኢየሱስ ጋር መሞትና መነሣት | ለኃጢአት መሞት ነገር ግን በክርቶስ መኖር | ጥምቀት |
| 6፡1-11 | 6፡1-14 | 6፡1-4 | 6፡1-4 | 6፡1-7 |
| | | 6፡5-11 | 6፡5-11 | |
| | | | | 6፡8-11 |
| | | | | ቅድስና፣ ኃጢአት እንዳይገዛ |
| 6፡12-14 | | 6፡12-14 | 6፡12-14 | 6፡12-14 |
| የጽድቅ አገልጋዮች | ከኃጢአት ባርነት ወደ እግዚአብሔር አገልጋይነት | የሁለቱም ባርነት | የጽድቅ አገልጋዮች | ክርስቲያን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ወጥቷል |
| 6፡15-23 | 6፡15-23 | 6፡15-19 | 6፡15-19 | 6፡15-19 |
| | | | | የኃጢአት ዋጋ እና የቅድስና ዋጋ |
| | | 6፡20-23 | 6፡20-23 | 6፡20-23 |

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ** (viii **ተመልከት**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

4. ሦስተኛ አንቀጽ

5. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ምዕራፍ 6፡1-8፡39 የሐሳብ ምድብ (ጽሑፋዊ አሀድ) ክርስቲያን ከኃጢአት ጋር ያለውን ግንኙነት መልክ ሰጥቶ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፣ ምክንያቱም ወንጌል የተመሠረተው በነጻና ባልተደከመባቸው

በክርስቶስ በኩል በሆነ የእግዚአብሔር ጸጋዎች በመሆኑ ነው (3፡21-5፡21) ስለሆነም፣ እንዴት ኃጢአት አማኝ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል? ምዕራፍ 6 የተመሠረተው በሁለት ታሳቢ ጥያቄዎች ላይ ነው፣ ቁ. 1 እና 15። ቁጥር 1 የሚዛመደው ከ5፡20 ጋር ሲሆን ቁ. 15 ደግሞ የሚዛመደው ከ6፡14 ጋር ነው። የመጀመሪያው የሚዛመደው ከኃጢአት ጋር እንደ ያኗኗር ዘዴ (የአሁን ጊዜ) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የግለሰብ የኃጢአት ድርጊት (የድርጊት ግሥ) ያሳያል። ቁጥር 1-14 በግልጽ የሚያሳየው አማኞች ከኃጢአት አገዛዝ ነጻ መሆናቸውን ሲሆን፣ ቁ. 15-23 ደግሞ አማኞች ቀደም ሲል ኃጢአትን ያገለግሉ እንደነበሩ፣ እግዚአብሔርን በሙሉ፣ በተሟላ እና ባጠቃላይ ልብ ያገለግሉት ዘንድ ነጻነት እንዳላቸው ነው።

ለ. ቅድስና ሁለቱም ነው፡

1. አቋም (በደኅንነት ጊዜ እንደሆነ የጽድቅ ድርሻ፣ 3፡21-5፡21)
2. ክርስቶስን በመምሰል መጓዝን

ሀ. 6፡1-8፡39 ይህንን እውነት በሥነ-መለኮታዊነት ይገልጻል

ለ. 12፡1-15፡13 በተግባር ይገልጸዋል (ልዩ ርዕስ 6፡4 ላይ ተመልከት)

ሐ. ተንታኞች የጽድቅን እና የቅድስናን ርዕሰ-ጉዳዮች ክሥነ-መለኮታዊ አኳያ ከፋፍለው ማየት ይኖርባቸዋል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺዎቻቸውን ለመገንዘብ ይረዳቸው ዘንድ። በተጨባጭ እነሱ የጸጋ ትይዩ ድርጊቶች ናቸው (አቋማዊ፣ 1ኛ ቆሮ. 1፡30፤ 6፡11)። የሁለቱም ያተገባበር ዘዴ ተመሳሳይ ነው— የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ሕይወትና ሞት የተፈጸመው፣ በእምነት የምንቀበለው (ኤፌ. 2፡8-9)።

መ. ይሄ ምዕራፍ የሚያስተምረው የሙሉ ጉልምስና እምቅ ኃይልን ሲሆን (ኃጢአት የለሽነት፣ 1ኛ ዮሐንስ 3፡6፣9፤ 5፡18) በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ልጅነት ነው። ምዕራፍ 7 እና 1ኛ ዮሐንስ 1፡8-2፡1 የሚያሳዩት የአማኞችን ቀጣይ ኃጢአተኝነት ነው።

ከይቅርታ ጋር ካለው ከጳውሎስ አመለካከት ሳቢያ አብዛኛው ክርክር የተያያዘው ከግብረ ገብነት ጉዳይ ጋር ነው። አይሁድ መልካም ሕይወትን ለማረጋገጥ ሲፈልጉ አዲስ አማኞች የሙሴን ሕግ እንዲያጸኑ ይጠይቃሉ። እንዲህ ሊሆን የቻለው አንዳንዶች የጳውሎስን አመለካከት እንደ ፍቃድ በመውሰድ ኃጢአትን ስለፈጸሙ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 1፣15፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡15-16)። ጳውሎስ የሚያምነው በውስጥ ያደረ መንፈስ እንጂ ውጫዊ የሆነ ሕግ መለኮታዊና ክርስቶስን የመሰሉ አማኞች እንደማይፈጥር ነው። በተጨባጭ ይህ ልዩነት በብሉይ ኪዳን (ዘዳግም. 27-28) እና በአዲስ ኪዳን (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝቅ. 36፡26-27)።

ሠ. ጥምቀት በቀላሉ፣ የመጽደቅና/ የመቀደስ መንፈሳዊ እውነታ አካላዊ መግለጫ ነው። በሮሜ መንታዎቹ መሠረተ እምነቶች ማለትም፣ አቋማዊ መቀደስ (መጽደቅ) እና የሕይወት-ልምድ መቀደስ (ክርስቶስን መምሰል) ሁለቱም አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል። ከእሱ ጋር መቀበር (ቁ.4) "ከእርሱ ጋር መሰቀል" (ቁ. 6) ከሚለው ጋር ትይዩ ነው።

ረ. በክርስትና ሕይወት ፈተናንና ኃጢአትን ድል ለማድረግ ቁልፎቹ፡

1. በክርስቶስ ማን መሆንህን እወቅ። እሱ ምን እንዳደረገልህ እወቅ። ከኃጢአት ነጻ ወጥተሃል! ለኃጢአት ሞተሃል!
2. በክርስቶስ ያለህን ስፍራ (አቋም) በየቀኑ የሕይወት ሁኔታህ እወቅ፣ ቁጠር።
3. እኛ የራሳችን አይደለንም! ጌታችንን ማገልገል/ መታዘዝ አለብን። የምናገለግለው/ የምንታዘዘው ከምስጋናና ከፍቅር የመነጨ ሲሆን ይህም ለወደደን ለአንዱ ነው!
4. የክርስቲያን ሕይወት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሕይወት ነው። እሱም፣ እንደ ደኅንነት፣ ከእግዚአብሔር በክርስቶስ ያገኘነው ስጦታ ነው። እሱ መነሻውም ኃይል ሰጪውም ነው። እኛም በንስሐና በእምነት ምላሽ መስጠት ይገባናል፣ በመነሻውም ሆነ በቀጣይነት።
5. በኃጢአት አካባቢ አትጫወት። እዛው እንዳለ ተወው። ከእሱ ዘወር በል፤ ከእሱ ሽሽ። ፈተና ያለበት አካባቢ ራስህን አታቅርብ።
6. ኃጢአት ሊሰበር የሚቻል ሱስ ነው፣ ነገር ግን ጊዜ፣ ጥረት፣ እና ፍቃድን ይፈልጋል።

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

6፡1-7

**[1]እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። [2]ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? [3]ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? [4]እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። [5]ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ [6]ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ [7] የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና።**

6፡1

*አአመመቅ* "ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአታችን እንቀጥል?"

አኪጆት "እንግዲህ ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአታችን እንቀጥል?"
አየተመት "ጸጋ ይበዛልን ዘንድ ኃጢአት በመፈጸም እንቀጥል?"
አእት "የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛልን ዘንድ ኃጢአትን በመሥራት ሕይወት እንቀጥል?"
ኢመቅ "ጸጋ በጣም ይጨምር ዘንድ በኃጢአት መቀጠላችን አግባብ ነውን?"

ይህ የአሁን ጊዜ ሁኔታን የሚያሳይ ነው። በጥሬ አገባቡ የሚጠይቀው፣ ክርስቲያኖች ኃጢአትን ጋር "ታግሦ መኖር ይችላሉ" ወይስ "ይቀራረባሉ" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ ተመልሶ ወደ 5:20 ይሄዳል። ጳውሎስ ይህንን ጸጋን ያግባብ መጠቀም በተመለከተ መላምታዊ ተቃውሞ (የወቀሳ ቃል) ይጠቀማል (1ኛ ዮሐንስ 3:6፣9፤ 5:18)። የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት የዐመጻን ሕይወት ለመኖር ፍቃድ እንደመስጠት አይደለም።

የጳውሎስ ወንጌል ማለትም ነጻ ደኅንነት፣ እንደ ስጦታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ጸጋ የሆነው (ዝኒ ከማሁ. 3:24፤ 5:15፣17፤ 6:23) ስለ ያኗኗር ስልት ጽድቅ ብዙ ጥያቄዎችን አስነሥቷል። ነጻ ስጦታ እንዴት አድርጎ ቀጥተኛ ግብረገብነትን ይፈጥራል? መጽደቅና መቀደስ መነጣጠል አይኖርባቸውም (ማቴ. 7:24-27፤ ሉቃስ 8:21፤ 11:28፤ ዮሐንስ 13:17፤ ሮሜ 2:13፤ ያዕቆብ 1:22-25፤ 2:14-26)።

በዚህ ነጥብ ላይ ከ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ በጳውሎስ: *ባለ ነጻ ልቡ ሐዋርያ፣* ከሚለው ልጥቀስ፣ "የክርስቲያኖች ጥምቀት ወሰኑን የሚመሠርተው በአሮጌው ባልታደሰው ማንነታቸው መካከልና በክርስቶስ ባላቸው አዲስ ሕይወት ነው፡ እሱም የሚያመለክተው ለአሮጌው ሥርዓት መሞታቸውን ሲሆን በዚህም መሠረት ለተጠመቀ ክርስቲያን በኃጢአት መቀጠል ነውርና፣ ነጻ የወጣ ባርያ ለቀድሞ ጌታው ለድጋሚ ባርነት እንደመገዛት ማለት ነው (ሮሜ. 6:1-4፣ 15-23) ወይም ባሏ የሞተባት ሴት 'ከባሏ ጋር ባለው ሕግ' እንደመታሰር ማለት ነው፣" ገጽ 281-82 (ሮሜ 7:1-6)።

በጀምስ ኤስ. ስቲዋርት መጽሐፍ፣ በክርስቶስ ያለ ሰው፣ እንዲህ ጽፏል: "ይህን መሰሉ የሐዋርያው የአስተሳሰብ ገጽታ የክስተቱ ምድብ በሮሜ 6 ላይ ይገኛል። እዚያ ላይ ጳውሎስ፣ ግሩም በሆነ ብርታትና ጥረት፣ ወደ ልቦናና ሕሊና ትምህርቱን የሚያመጣው ከኢየሱስ ጋር በሞቱ መተባበር ማለት ለአማኝ ከኃጢአት ጋር ጨርሶ መቆራረጥን ለማሳየት ነው፣" ገጽ 187-88።

6:2 **"ፈጽሞ እንዳይሆን"** ይህ የማይዘወተር የመሻት ሁኔታ አገባብ ሲሆን እሱም የሰዋሰዋዊ ሁኔታ ወይም ስልት የፍላጎት መግለጫ ወይም ጸሎት ነው። እሱም የጳውሎስ የአመላለስ ስልት ሲሆን ለመላምታዊ ተቃውሞ ምላሽ አድርጎታል። እሱም የሚገልጸው፣ ጳውሎስን ያስደነገጠውና የረበሸው የማያምኑ የሰው ልጆች የተዛባ መረዳትና ጸጋን አላግባብ መጠቀማቸው ነው (ዝኒ ከማሁ. 3:4፣6)።

▣ **"እኛ ለኃጢአት የሞትን"** ይህ የተፈጸመ ድርጊት አመላካች ሲሆን፣ ፍቺውም "ሞተናል" የሚል ነው። ነጠላ ቁጥሩ "ኃጢአት" በዚህ ምዕራፍ ሁሉ ተጠቅሷል። ለመጥቀስ የሚፈልገው ስለ እኛ "የኃጢአት ተፈጥሮ" እሱም ከአዳም የወረስነውን ነው (ሮሜ 5:12-21፤ 1ኛቆሮ. 15:21-22)። ጳውሎስ የሞትን ጽንሰ-ሐሳብ ዘወትር እንደ ዘይቤ የሚጠቀምበት፣ አማኞች ከኢየሱስ ጋር ያላቸውን አዲስ ኅብረት ለማመላከት ነው። እነሱ በቀጣይ ለኃጢአት ጌትነት ተገዥ አይሆኑም።

▣ **"በእርሱ ይኖራሉ"** ይህ በጥሬ ትርጉሙ "መራመድ" ማለት ነው። ይህ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖት ለመስጠት ሲሆን ይህም አንድም፣ የእምነት የሕይወት ዘይቤ (ኤፌ. 4:1፤ 5:2፣15) ወይም የኃጢአት የሕይወት ዘይቤ (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 4) ነው። አማኞች በኃጢአት ደስተኞች ሊሆኑ አይችሉም!

6:3-4 **"ተጠምቀናል... ተቀብረናል"** እነዚህ ሁለቱም የተጠናቀቀ ድርጊት ተገብሮ አመላካቾች ናቸው። ይህ ሰዋሰዋዊ ቅርጽ አጽንዖት የሚሰጠው በውጫዊ አካል የተጠናቀቀ ድርጊትን ሲሆን፣ እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ ነው። እነሱ በዚህ ጽሑፍ ተነጻጻሪ ናቸው።

**ልዩ ርዕስ: ጥምቀት**

ኮርቲስ ቮግሃን፣ ግብረ ሐዋርያት (Acts)፣ ገጽ 28 ላይ ማራኪ የግርጌ ማስታወሻ ይዟል።

"በግሪክ 'ጥምቀት' የሚለው ቃል ሦስተኛ መደብ አድራጊ ሲሆን፤ 'ንስሐ' የሚለው ቃል ደግሞ ሁለተኛ መደብ አድራጊ ነው። ይህ ለውጥ፣ ማለትም በእጅጉን ቀጥተኛ ከሆነው ከሁለተኛ መደብ ትዕዛዝ አንቀጽ፣ አነስ ወደሚለው ቀጥተኛ ሦስተኛ መደብ፣ 'ጥምቀት" መለወጡ የሚያመለክተው የጴጥሮስ ተቀዳሚው ጥያቄ ንስሐ መሆኑን ነው።"

ይህም ተከትሎ የመጣው የዮሐንስ መጥምቁን የስብከት አጽንዖት (ማቴ. 3:2) እና የኢየሱስ (ማቴ. 4:17) ነው። ንስሐ ሲሆን የሚችለው መንፈሳዊ ቁልፍ ሲሆን እንዲሁም ጥምቀት የዚህ መንፈሳዊ ለውጥ ውጫዊ መግለጫ ነው። አዲስ ኪዳን ስለ አልተጠመቁ አማኞች ምንም አያውቅም! ለጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን ጥምቀት ግልጽ የእምነት መግለጫ ነበር። ትዕይንቱ በሕዝብ ፊት በክርስቶስ ያለ እምነትን መግለጫ እንጂ የደኅንነት መሣርያ አይደለም! መታወስ ያለበት ነገር፣ ጥምቀት በጴጥሮስ ሁለተኛው ስብከት ላይ አልተጠቀሰም፣ ንስሐ እንጂ (ዝኒ ከማሁ. 3:19፤ ሉቃስ 24:17)። ጥምቀት በኢየሱስ የተቀመጠ ምሳሌ ነው (ማቴ. 3:13-18)። ጥምቀት በኢየሱስ የታዘዘ ነው (ማቴ. 28:19)። የዘመናዊው ጥያቄ የሆነው ለመዳን የሚያስፈልገው ጥምቀት በአዲስ ኪዳን አልተጠቀሰም፤ ሁሉም አማኞች እንዲጠመቁ ይጠበቃል። ሆኖም፣ የሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን መሣርያነት ሁሉም ሊመረምራቸው ይገባል! ደኅንነት የእምነት ጉዳይ ነው እንጂ የትክክለኛ ቦታ፣ ትክክለኛ ቃላት፣ የትክክለኛ አምልኳዊ ድርጊት ጉዳይ አይደለም!

▣ **"ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ"** የኢስ (eis) (ወደ) አጠቃቀም ትይዩነቱ ከታላቁ ተልእኮ፣ የማቲ. 28፡19፣ አዲስ አማኞች ሲጠመቁ ነው ኢስ (ወደ)፣ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም። መስተጻምሩ በተጨማሪም ጥቅም ላይ የዋለው፣ አማኞች በኢየሱስ አካል በመንፈስ መጠመቃቸውን ነው፣ በ1ኛ ቆሮ. 12፡13። ኢስ በዚህ ጽሑፍ ከኢን *ጋር* (በኢየሱስ) ተመሳሳይ ነው በቁ. 11፣ ይህም የጳውሎስ ተወዳጁ አማኞችን የማመልከቻ ዘዴ። እሱም ስፍራ አመላካች ነው። አማኞች ይኖራሉ እናም ይንቀሳቀሳሉ እንዲሁም በክርስቶስ የራሳቸው ሕላዌ አላቸው። እነዚህ መስተጻምሮች የሚያመላክቱት ይህን ወዳጃዊ ኅብረት፣ የኅብረቱን ክልል፣ ይህንን የወይንና የቅርንጫፍን ግንኙነት ነው። አማኞች የሚለዩት እና ከክርስቶስ *ጋር* የሚገናኙት በሞቱ (ዝኒ ከማሁ. ቁ.6፤ 8፡17)፣ በትንሣኤው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 5)፣ እሱ ለእግዚአብሔር ባለው የታዛዥነት አገልግሎት እና በእሱ *መንግሥት* ነው!

▣ **"በሞቱ... ከእሱ *ጋር* ተቀብረናል"** በመነከር የሚደረግ ጥምቀት ሞትንና መቀበርን *ያመለክታል* (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 5 እና ቆላ. 2፡12)። ኢየሱስ ጥምቀትን የተጠቀመበት ለራሱ ሞት ተምሳሌት ነው (ማርቆስ 10፡38-39፤ ሉቃስ 12፡50)። እዚህ*ጋ* ያለው አጽንዖት የጥምቀት መሠረተ እምነት አይደለም፣ ነገር ግን የክርስቲያን አዲስ፣ ወዳጃዊ ግንኙነት ከክርስቶስ ሞትና መቀበር *ጋር* ነው። አማኞች የሚታወቁት በክርስቶስ ጥምቀት፣ በእሱ ባሕርይ፣ በእሱ *መሥዋዕትነት*፣ በእሱ ተልእኮ ነው። ኃጢአት በአማኞች ላይ ኃይል የለውም!

6፡4 **"በሞቱ ደግሞ አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእሱ *ጋር* ተቀበርን"** በዚህ ምዕራፍ፣ እንደ ሁሉም የጳውሎስ ጽሑፎች ስልት፣ በርካታ ሱን (sun) (*ጋር*) ድብልቆች ተጠቅሟል (ምሳ. ኤፌ. 2፡5-6)።

1. ሱን (sun) + *ታፕቶ* (thaptō) = አብሮ *መቀበር*፣ ቁ. 4፤ ቆላ. 2፡12፤ እንዲሁም ቁ. 8 እይ
2. ሱን (sun) + ስታዩሮ stauroō = አብሮ *መተከል*፣ ቁ. 5
3. ሱን (sun) + አዞ azō = አብሮ *መኖር*፣ ቁ.8፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡11 (እንዲሁ አብሮ *መሞትና* አብሮ *መንገሥን* ይዟል)

▣ **"ስለሆነም እኛም በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለብን"** ይህ የድርጊት የአሁን ጊዜ ሁኔታን የሚያሳይ ነው። የሚጠበቀው የመዳን ውጤት ቅድስና ነው። አማኞች የእግዚአብሔርን ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለሚያውቁ ሕይወታቸው የተለየ መሆን አለበት። አዲሱ ሕይወታችን ደኅንነትን አያመጣልንም፣ ነገር ግን የደኅንነታችን ውጤት ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 19፤ እና ኤፌ. 2፡8-9፣10፤ *ያዕቆብ* 2፡14-26)። ይህ ግን የእምነት ነው *የሥራ* የሚል ጥያቄ አይደለም፣ ነግር ግን የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው።

**ልዩ ርዕስ፡ ቅድስና**

አኪ. የሚለው ኃጢአተኞች ወደ ኢየሱስ በንስሐና በእምነት በተመለሱ ጊዜ፣ ወዲያውኑ ይጸድቃሉ ይቀደሳሉም። ይህም በኢየሱስ ያላቸው አዲስ አቋም ነው። የሱ ጽድቅ በእነሱ ውስጥ ይመነጫል (ሮሜ. 4)። እነሱ ትክክለኛና ቅዱስ እንደሆኑ ታውጇል (የእግዚአብሔር የፍርድ ድርጊት)።

ነገር ግን አኪ. ደግሞ የሚያሳስበው ወደ ቅድስና ወይም መቀደስ ነው። ይህም ሁለቱንም፣ ማለትም *ሥነ-መለኮታዊ* አቋም በኢየሱስ ክርስቶስ በተጠናቀቀ *ሥራ* እና በዝንባሌም ሆነ በየዕለቱ የሕይወት ድርጊት ክርስቶስን የመምሰል መጠራት ነው። ደኅንነት ነጻ ስጦታ እንደሆነና የሁሉም ነገር የአኗኗር ስልት ዋ*ጋ* እንደሆነ ቅድስናም እንደዚያው ነው።

| *<u>መነሻ ምላሽ</u>* | **<u>ቀጣይ ክርስቶስን መምሰል</u>** |
|---|---|
| *ሐዋርያት ሥራ* 20፡23፤ 26፡18 | ሮሜ 6፡19 |
| ሮሜ 15፡16 | 2ኛ ቆሮንቶስ 7፡1 |
| 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡2-3፤ 6፡11 | 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡13፤ 4፡3-4፣7፤ 5፡23 |
| 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 | 1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡15 |
| *ዕብራውያን* 2፡11፤ 10፡10፣14፤ 13፡12 | 2ኛ ጢሞቲዎስ 2፡21 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 1፡1 | *ዕብራውያን* 12፡14 |
| | 1ኛ ጴጥሮስ 1፡15-16 |

▣**"ክርስቶስ ተነሥቷል"** በዚህ ጽሑፍ አብ የወልድን *ቃል* እና *ሥራ* የተቀበለበት ሁኔታ በሁለት ታላላቅ ሁነቶች ተገልጿል።

1. የኢየሱስ ከሙታን *መነሣት*
2. የኢየሱስ ማረግና በአብ ቀኝ *መቀመጥ*

▣ **"የአብ ክብር"** ለ "ክብር" ልዩ ርዕስ 3፡23 ላይ ተመልከት። ለ "አብ" ልዩ ርዕስ 1፡7 ላይ ተመልከት።

6፡5 **"በ... ከ... (ቢሆን)"** ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ለጽሑፋዊ ጥቅሙ ነው። ጳውሎስ አንባቢዎቹ አማኞች እንደሆኑ ግምት ውስጥ አስገብቷል።

▣ **"እኛም ከእሱ ጋር የምንተባበር ሆነናል"** ይህ የተፈጸመ የድርጊት አመላካች ሲሆን፣ ሲተረጎም የሚችለውም፣ "አንድ ላይ የሆነና አንድ በመሆኑ የቀጠለ፣" ወይም "አንድ ላይ የተተከለ ወይም አንድ ላይ በመተከሉ የቀጠለ" በሚል ነው። ይህ እውነት ከሥነ-መለኮት አኳያ አምሳያ የሚሆነው ዮሐንስ 15 ላይ ካለው "መኖር" ከሚለው ጋር ነው። አማኞች ከኢየሱስ ሞት ጋር ከታወቁ (ገላ. 2፡19-20፤ ቆላ. 2፡20፤ 3፡3-5)፣ ከሥነ-መለኮታዊ መታወቅ ያለባቸው ከትንሣኤው ሕይወት አኳያ ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ.10)።

ይህ፣ ጥምቀት እንደ ሞት የሚታይበት ዘይቤአዊ ገጽታ ለማሳየት የሚሻው (1) እኛ ለአሮጌው ሕይወት፣ ለአሮጌው ኪዳን ሞተናል፣ (2) እኛ የምንኖረው ለመንፈስ፣ ለአዲስ ኪዳን ነው። ስለዚህ፣ የክርስቲያን ጥምቀት፣ የመጨረሻው የብኪ ነቢይ እንደሆነው እንደ ዮሐንስ መጥምቁ ያለ ጥምቀት አይደለም። ጥምቀት የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን ለአዲስ አማኝ በሕዝብ ፊት የእምነት መግለጫ የሚሆን ምቹ ጊዜ ነበር። የጥንቱ የጥምቀት መግለጫ በተጠማቂው የሚደገመው፣ "ኢየሱስ ጌታ መሆኑን አምናለሁ" የሚል ነበር (ሮሜ. 10፡9-13)። በሕዝብ ፊት የሚደረግ ይፋ እወጃ ቀደም ሲል በልምድ የሆነውን በመደበኛ፣ በአምልኮ ሥርዓት በሆነ ድርጊት የሚፈጸም ነበር። ጥምቀት የይቅርታ <u>መሣርያ</u>፣ ደኅንነት ወይም የመንፈስ ቅዱስ መምጣት አልነበረም፣ ነገር ግን በሕዝብ ፊት፣ <u>በምቹ ጊዜ</u> የሚደረግ ምስክርነት እና ንስሐ እንጂ (ሐዋ. 2፡38)። ሆኖም ግን፣ ሌላ ተለዋጭ አልነበረውም። ኢየሱስ አዝዞታል (ማቴ. 28፡19-20)፣ እንዲሁም ምሳሌ አድርጎታል፣ (ማቴ. 3፤ ማርቆስ 1፤ ሉቃስ 3) እና እሱም የሐዋርያዊ ስብከቶች አካልና የሐዋርያት ሥራ ደንብ ነበር።

6፡6
| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ይሄንን እናውቃለን፣ እሱም አሮጌው ማንነታችን ከእሱ ጋር እንደተሰቀለ"** |
| **አኪጀት** | **"ይሄንን እናውቃለን፣ እሱም አሮጌው ሰዋችን ከእሱ ጋር እንደተሰቀለ"** |
| **አየተመት** | **"ይሄንን እናውቃለን አሮጌው ማንነታችን ከእሱ ጋር መሰቀሉን።** |
| **አእት** | **"እናም ይሄንን እናውቃለን፡ አሮጌው ማንነታችን ከክርስቶስ ጋር በእሱ መስቀል እንደሞተ"** |
| **ኢመቅ** | **"እኛ ያንን መገንዘብ ያለብን ፊተኛው ማንነታችን ከእሱ ጋር መሰቀሉን ነው"** |

ይህ የተፈጸመ ተገብሮ አመላካች ፍቺው "የእኛ አሮጌው ማንነት ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመንፈስ ተሰቅሏል" የሚል ነው። ይህ እውነት በድል ለተሞላ የክርስትና ሕይወት ወሳኝ ነው። አማኞች ከኃጢአት ጋር የሚኖራቸውን አዲስ ግንኙነት መገንዘብ ይኖርባቸዋል (ገላ. 2፡20፤ 6፡14)። የሰው ልጆች አሮጌ የወደቀ ማንነት (አዳማዊ ተፈጥሮ) ከኢየሱስ ጋር ሞቷል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 7፤ ኤፌ. 4፡22 እና ቆላ. 3፡9)። እንደ አማኞች አሁንም ስለ ኃጢአት ምርጫ አለን፣ አዳም በመጀመሪያ እንደነበረው።

▣
| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"የኃጢአት ሥጋችን ይወገድ ዘንድ"** |
| **አየተመቅ** | **"ስለዚህም የኃጢአት ሥጋችን ይደመሰስ ዘንድ"** |
| **አእት** | **"የኃጢአት ማንነት ኃይል ይደመሰስ ዘንድ"** |
| **ኢመቅ** | **"ኃጢአተኛ ሥጋን ለማስወገድ"** |

ጳውሎስ "ሥጋ" (ሶማ፣ soma) የሚለውን ቃል ለበርካታ አገናዛቢ ሐረጎች ተጠቅሞበታል።

1. የኃጢአት ሥጋ፣ ሮሜ. 6፡6
2. የሞት ሥጋ፣ ሮሜ. 7፡24
3. የሥጋ አካል፣ ቆላ. 2፡11

ጳውሎስ የሚገልጸው ስለዚህ ሥጋዊ ሕይወት የኃጢአትና የዐመጻ ዘመን ነው። የኢየሱስ የትንሣኤ አካል የአዲሱ የጽድቅ ዘመን አካል ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡17)። አካላዊነት ችግር አይደለም (የግሪክ ፍልስፍና)፣ ነገር ግን ኃጢአትና ዐመጻ እንጂ። ሥጋ ክፉ አይደለም። ክርስትና የዘላለማዊውን ግዘፍ አካል እምነት ያጸናል (1ኛ ቆሮ. 15)። ሆኖም፣ ግዘፍ አካል የፈተና፣ የኃጢአት፣ እና የእኔነት የጦር ሜዳ ነው።

ይህ የተፈጸመ ተገብሮ ሁኔታዊ ነው። "ተወግዷል" የሚለው ሐረግ ፍቺው፣ "የማይሠራ ተደርጓል፣" "ኃይል አልባ ተደርጓል" ወይም "የማይሠራ ተደርጓል" ማለት ሲሆን "ተደምስሷል" ማለት <u>አይደለም</u>። ይህ ተወዳጅ የጳውሎስ ቃል ሲሆን፣ ከሃያ አምስት ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል። ልዩ ርዕስ 3፡3 ተመልከት። ግዘፍ አካላችን ከግብረ-ገብነት አኳያ ገለልተኛ ሲሆን፣ ዳሩግን ቀጣይነት ላለው መንፈሳዊ ውጊያ የጦር ሜዳ ሆኗል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 12-13፤ 5፡12-21፡ 12፡1-2)።

**6፡7 "የሞተስ ከኃጢአት ነጻ ወጥቷል"** ይህ የድርጊት የአሁን ቦዝ አንቀጽ እና የተፈጸመ ተገብሮ አመላካች ሲሆን ፍቺውም "የሞተስ ከኃጢአት ነጻ ወጥቷል፣ በመውጣቱም ቀጥሏል።" አማኞች በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት በመሆናቸው ቀደም ሲልም ሆነ በቀጣይነት ከአዳም መውደቅ ከወረሱት የባርነትና የእኔነት ባርነት ነጻ ወጥተዋል (ዝኒ ከማሁ. 7፡1-6)።
የግሪክ ቃል "ነጻ" በሚል እዚህ የተተረጎመው በመግቢያዎቹ ምዕራፎች እንዱጋ የተተረጎመው "ጸድቋል" በሚል ነው (አመት (አሜሪካን መደበኛ ትርጉም) ASV)። በዚህ ጽሑፍ "ነጻ" በእጅጉን ስሜት ይሰጣል (በሐዋርያት ሥራ 13፡39 ጋር ተመሳሳይ አገባብ አለው)። የቃልን ፍቺ የሚወስነው አጠቃላይ ጽሑፉ እንጂ የመዝገበ-ቃላት ወይም ሞያዊ ፍቺ አለመሆኑን አስተውል። ቃላት በዓረፍተ-ነገር ፍቺ፣ ዓረፍተ-ነገሮች ደግሞ በአንቀጾች ፍቺ ይኖራቸዋል።

6:8-11
[8]*ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤* [9]*ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና።* [10]*መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል።* [11]*እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ።*

6:8 "በ... ከ... (ቢሆን)" ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ለጽሑፋዊ ጥቅሙ ነው። የአማኞች ጥምቀት ትዕይንታዊ ምሳሌነቱ የአንዱ ከክርስቶስ ጋር መሞትን ነው።

▣ "ከእርሱ ጋር ደግሞ እንኖራለን" ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው "እዚህ እና አሁን" (1ኛ ዮሐንስ 1:7)፣ ለማሳወቅ ሲሆን፣ በትንቢት መቼት ለይቶ የሚያሳይ አይደለም። ቁጥር 5 የሚገልጸው እኛ የክርስቶስን ሞት መካፈላችንን ሲሆን፣ ቁጥር 8 ደግሞ የሚገልጸው የሱን ሕይወት መካፈላችንን ነው። ይህም በተመሳሳይ የተወረሰ የሐሳብ ክርክር ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጽንሰ-ሐሳብ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚመለከት ነው። ይህም እዚህና አሁን፣ በቀጣይም ነው። ነጻ ጸጋ ራስን መግዛትን ያመጣል እንጂ ፍቃድ አይደለም።

6:9 "ከሙታን ተነሥቶ" ይህ የድርጊት ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው (6:4፣ የድርጊት ተገብሮ አመላካችን ተመልከት)።
አኪ የሚያጸናው ሦስቱም የሥላሴ አካላት በሙሉ በኢየሱስ ትንሣኤ ላይ ነበሩበት (1) መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ. 8:11)፤ (2) ወልድ (ዮሐንስ 2:19-22፤ 10:17-18)፤ እንዲሁም በጣም በመደጋገም (3) አብ (ሐዋ. 2:24፣32፤ 3:15፣26፤ 4:10፤ 5:30፤ 10:40፤ 13:30፣33፣34፣37፤ 17:31፤ ሮሜ 6:4፣9)። የአብ ድርጊት የነበረው የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትምህርቶቹን መቀበሉን ማረጋገጥ ነበር። ይህም የሐዋርያት የፊተኛው ስብከት ዋንኛው ገጽታ ነበር። ልዩ ርዕስ፡ ኬሪግማ (ጥንታዊው ስብከት) 1:2 ተመልከት።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ሞት በእሱ ላይ በቀጣይ ሥልጣን የለውም"** |
| **አኪጀት፣ አየተመቅ** | **"ከእንግዲህ ሞት በእሱ ላይ አይገዛም"** |
| **አእት** | **"ሞት ወደፊት በእርሱ ላይ ሊገዛ አይችልም"** |
| **ኢመቅ** | **"ካሁን በኋላ ሞት በእሱ ላይ ኃይል የለውም"** |

ኩሪዮ (*kurieuō*) የሚለው ግሥ ኩሪዮስ (kurios) ከሚለው ቃል የመጣና ፍቺውም "ባለቤት፣" "ጌታ፣" "ባል፣" ወይም "ጌታ፣" ማለት ሲሆን፣ ኢየሱስ አሁን በሞት ላይ ጌታ ነው (ራዕ. 1:18)። ኢየሱስ የሞትን ኃይል ለመስበር የመጀመሪያው ነው (1ኛ ቆሮ. 15)!

6:10 "**መሞትን ሞቷልና፣ ለኃጢአት ሞቷል**" ኢየሱስ የኖረው በኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ ነበር፣ እሱ ግን ኃጢአትን አላደረገም፣ ኃጢአተኛው ዓለም ሰቀለው (ዕብ. 10:10)። የኢየሱስ በሰው ልጆች ፈንታ የምትክነት ሞት መሞቱ፣ ሕግ የሚያስቀምጣቸውንና እንዲሁም የሚያስከትለውን ውጤት ሽሮታል (ገላ. 3:13፤ ቆላ. 2:13-14)።

▣ "አንዴ ለሁሉም" በዚህ ጽሑፍ ጳውሎስ አጽንዖት የሰጠው የኢየሱስን መሰቀል ነው። የእሱ የአንድ ጊዜ ለኃጢአት መሞት፣ ተከታዮቹ ለኃጢአት እንዲሞቱ አደረጋቸው።
የዕብራውያን መጽሐፍ ዋነኛውን አጽንዖት የሚሰጠው በኢየሱስ የመሥዋዕትነት ሞት ነው። ይህ አንድ ጊዜ የተደረገ ደኅንነት እና ይቅርታ ለዘላለም ተፈጽመዋል (ዝኒ ከማሁ. "አንዴ" [ኢፋፓክስ (ephapax)]፣ 7:27፤ 9:12፤ 10:10 እና "ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ" [ሃፓክስ (hapax)]፣ 6:4፤ 9:7፣26፣27፣28፤ 10:2፤ 12:26፣27)። ይህ የተቀዳጀነው መሥዋዕታዊ ማረጋገጫ ተደግሞ ነው።

▣ ነገር ግን የኖረውን ሕይወቱን፣ ለእግዚአብሔር ይኖራል" ሁለቱ ድርጊቶች ቁጥር 10ሀ ላይ ያሉት፣ ከሁለቱ የአሁን ድርጊት አመላካቾች ከሆኑት ቁ.10ለ ላይ ካሉት ጋር ይቃረናሉ። አማኞች ከክርስቶስ ጋር ሞተዋል፤ አማኞች ለእግዚአብሔር ይኖራሉ፣ በክርስቶስ በኩል። የወንጌል ግብ ይቅርታ ብቻ አይደለም (ጸድቅ) ነገር ግን ለእግዚአብሔር ማገልገል (ቅድስና) ነው። አማኞች የዳኑት ለማገልገል ነው።

6:11 "ስለሆነም ራሳችሁን ለኃጢአት እንደሞታችሁ አድርጋችሁ ቁጠሩ፣" ይህ ያሁን መካከለኛ (አረጋጋጭ) አስፈላጊ ነው። ይህ ቀጣይነት ያለው ዘወትራዊ ትዕዛዝ ነው፣ ለአማኞች። ክርስቲያኖች ክርስቶስ ለእነሱ ብሎ የሠራው ሥራ ላይ ያላቸው እውቀት ለየዕለቱ ሕይወታቸው ወሳኝ ነው። "መመርመር" የሚለው ቃል (ዝኒ ከማሁ. 4:4፣9)፣ ስሌታዊ ቃል ሲሆን ፍቺውም "በጥንቃቄ መደመር" ማለት እና፣ በዚያም እውቀት መተግበር ማለት ነው። ቀጥር 1-11 እውቅና የሚሰጡት የአንዱን በክርስቶስ ያለ አቋም (አቋማዊ መቀደስ" ሲሆን 12-13 ደግሞ አጽንዖት የሚሰጠው በእሱ መራመድን (የቅድስና ገዞን) ነው። ልዩ ርዕስ ቁ.4 ተመልከት።

6:12-14
[12]እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤ [13]ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። [14]ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።

6:12 "እንግዲህ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ" ይህ የአሁን የድርጊት ተተኳሪ በአሉታዊ ሐረጋዊ ግሥ የተመሠረተ ሲሆን፣ ዘወትራዊ ፍቺው ቀደም ሲል የተጀመረን ድርጊት ማቆም ማለት ነው። "መንገሥ" የሚለው ቃል የሚዛመደው ከ5:17-21 እና 6:23 ጋር ነው። ጳውሎስ በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቦችን ሰውኛ ዘይቤ ሰጥቷቸዋል፡ (1) ሞት እንደ ንጉሥ ነግሧል (ዝኒ ከማሁ. 5:14፣17፤ 6:23)፤ (2) ጸጋ እንደ ንጉሥ ነግሧል (ዝኒ ከማሁ. 5:21)፤ እና (3) ኃጢአት እንደ ንጉሥ ነግሧል (ዝኒ ከማሁ. 6:12፣14)። ትክክለኛው ጥያቄ በሕይወትህ የሚገዛው ማን ነው፣ ነው? አማኝ በክርስቶስ የመምረጥ ኃይል አለው! ለግለሰብም፣ ለአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያንም፣ ሆነ ለእግዚአብሔር መንግሥት አሳዛኝ የሚሆነው አማኞች ማንነትንና ኃጢአትን ሲመርጡ ነው፣ ጸጋ እንደሆነ እያስረዱ!

6:13 "የአካላችሁን ብልቶች የኃጢአት መፈጸሚያ አድርጋችሁ አታቅርቡ" የአሁን የድርጊት አትኩሮት በአሉታዊ ሐረጋዊ ግሥ የተመሠረተ ሲሆን፣ ዘወትራዊ ፍቺው ቀደም ሲል የተጀመረን ድርጊት ማቆም ማለት ነው። ይህም የሚያሳየው በአማኞች ሕይወት ያለውን የኃጢአት እምቅ ኃይል ነው (ዝኒ ከማሁ. 7:1፤ 1ኛ ዮሐንስ 1:8-2:1)። ነገር ግን የኃጢአት መሻት ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ተወግዷል ቁ. 1-11።

▣"እንደ ጦር ዕቃ" ይህ ቃል የሚያመለክተው "የወታደርን የጦር መሣሪያ" ነው። ሥጋዊ አካላችን የፈተና የጦር-ሜዳ ነው (ቁ. 12-13፤ 12:1-2፤ 1ኛ ቆሮ. 6:20፤ ፊሊጵ. 1:20)። ያደባባይ ሕይወታችን ወንጌልን ይገልጻል።

▣"ነገር ግን ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ" ይህ የተፈጸመ የአሁን ተተኳሪ (አስገዳጅ) ሲሆን ለወሳኝ ድርጊት የሚደረግ ጥሪ ነው (ዝኒ ከማሁ. 12:1)። አማኞች ይሄንን በደኅንነት ጊዜ የሚያደርጉት ሲሆን፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ማድረጋቸውን መቀጠል ይኖርባቸዋል።
የዚህን ቁጥር ይትዩ አስተውል።

1. ተመሳሳይ ግሥ እና ሁለቱም ተተኳሪ (አስገዳጅ)
2. የጦር ዕቃ ዘይቤዎች
   ሀ. የዐመጻ የጦር ዕቃዎች
   ለ. የጽድቅ የጦር ዕቃዎች
3. አማኞች አካላቸውን ለኃጢአት ወይም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መስጠት ይችላሉ

ይህ ቁጥር አማኞችን የሚመለከት መሆኑን አስተውል– ምርጫው ይቀጥላል፤ ውጊያው ይቀጥላል!

6:14 "ኃጢአት አይገዛችሁምና" ይህ የትንቢት ገቢር አመላካች ሆኖ (መዝ. 19:13) አገባቡም፣ "ኃጢአት አይገዛችሁም!" የሚል አስገዳጅ ነው። ኃጢአት በአማኞች ላይ አይገዛም፣ ምክንያቱም እሱ በክርስቶስ ላይ ስለማይገዛ፣ (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 9፤ ዮሐንስ 16:33)።

6:15-19
[15]እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአትን እንሥራን? አይደለም። [16]ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ። [17-18]ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ፥ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። [19]ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ።

6:15 ይህ ሁለተኛው ሊቀርብ የሚችል ጥያቄ (ወቀሳ) 6:1 ላይ ያለው ዓይነት ነው። ሁለቱም የተለያዩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጣሉ፣ የክርስቲያን ግንኙነት ከኃጢአት ጋር እንዴት መሆን እንዳለበት። ቁጥር 1 የሚለው፣ ጸጋ ኃጢአትን ለመፈጸም ፍቃድ አለመሆኑን ሲሆን፣ ቁ. 15 ደግሞ ክርስቲያን ግለሰባዊ የኃጢአትን ድርጊቶች መዋጋት፣ ወይም መቃወም እንደሚያስፈልገው ነው። በድጋሚም፣ በተመሳሳይ ጊዜ እግዚአብሔርን ማገልገል ይኖርበታል፣ ቀደም ሲል ኃጢአትን ያገለግልበት በነበረው ትጋት (ዝኒ ከማሁ. 6:14)።

አአመመቅ፣ አኪጀት፣
  አእት "ኃጢአት እንሥራን?"

| | |
|---|---|
| *አየተመቅ* | *"ኃጢአት መሥራት ይኖርብናል?"* |
| *ኢመቅ* | *"ኃጢአትን ለመሥራት ነጻ ነን?"* |

ዊሊያምስ እና ፊሊፕስ ትርጉሞች ሁለቱም ይህንን የድርጊት የአሁን ሁኔታን ሲተረጉመው ልክ እንደ ቁ. 1 የአሁን የድርጊት ሁኔታን አመሳስሎ ነው። ይህ ትክክለኛው ትኩረት አይደለም። አማራጭ ትርጉሞችን ተመልከት (1) ኪጀት፣ አመት፣ አኢት- "ኃጢአትን እንሥራን?"፤ (2) የምእቱ ትርጉም - "የኃጢአትን ድርጊት እንፈጽምን?"፤ (3) የተመት- "ኃጢአትን እንድናደርግ ነውን?" ይህ ጥያቄ በግሪክ አጽንዖት ያለው ሲሆን ምላሹም "አዎን" ነው። ይህ የጳውሎስ የወቀሳ ዘዴ እውነትን የሚያሳይበት ነው። ይህ ቁጥር የሚያሳየው የተሳሳተን ሥነ-መለኮት ነው! ጳውሎስ ይህንን የሚመልሰው በራሱ ባሕርይ "ፈጽሞ አይሁን" በሚል ነው። የጳውሎስ ሥር-ነቀል ነጻ የእግዚአብሔር ጸጋ የሆነው ወንጌል በብዙ ሀሰተኛ መምህራን ባግባቡ እንዳልተረዳና እንደተዛባ ነው።

6፡16 ጥያቄው "አዎን" የሚል ምላሽ ይጠብቃል። የሰው ልጆች አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ያገለግላሉ። በሕይወትህ የሚገዛው ማን ነው፣ ኃጢአት ወይስ እግዚአብሔር? ሰዎች የሚታዘዙት የሚያሳየው የሚያገለግሉትን ነው (ገላ. 6፡7-8)።

6፡17 **"ነገር ግን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን"** ጳውሎስ ዘወትር እግዚአብሔርን ያመሰግናል። የእሱ ጽሑፍ የሚፈልቀው ከጸሎቱ ነው፣ የእሱ ጸሎት ደግሞ በወንጌል ላይ ባለ እውቀቱ ነው። ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ ጸሎት፣ ምስጋና፣ እና ለእግዚአብሔር ስብሐት 7፡25 ተመልከት።

▣ **"ነበራችሁ… ሆናችሁ"** ይህ ያልተጠናቀቀ ጊዜ የ "መሆን" ግሥ ሲሆን የሚገልጸውም ቀደም ሲል የነበራቸውን ሁኔታ (የኃጢአት ባርነት) ሆኖ የድርጊት ጊዜን አስከትሎ፣ የዐመጻ አቋማቸው ማክተሙን ያስረዳል።

▣ **"ለተሰጣችሁ የትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ"** በጽሑፉ፣ ይህ የሚያመለክተው በእምነት መጽደቃቸውን ሆኖ፣ እሱም በየዕለቱ ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚያመራ መሆን ይኖርበታል። "ማስተማር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሐዋርያዊ ትምህርትን ወይም ወንጌልን ነው።

▣ **"ልብ"** ልዩ ርዕስ፡ ልብ 1፡24 ላይ ተመልከት።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ለተሰጣችሁለት ለዚያ የትምህርት ዓይነት"** |
| **አኪጀት** | **"ለተሰጣችሁለት ለዚያ አስተምህሮት"** |
| **አየተመት፣ አዓአት** | **"ለታመናችሁበት ለዚያ የትምህርት ዓይነት"** |
| **አእት** | **"በተቀበላችሁት ትምህርት ለተገኘ እውነት"** |
| **አኢመቅ** | **"ለተዋወቃችሁት ለትምህርት ዘርፍ"** |

**ልዩ ርዕስ፡ ዓይነት (ቅርጽ) (ቱፖስ *Tupos*)**

ችግሩ ቱፖስ የሚለው ቃል ነው፣ በርካታ አጠቃቀሞች ስላሉት።

1. *ሙልቶን እና ሚሊጋን፣ የግሪክ አዲስ ኪዳን መዝገበ-ቃላት፣ ገጽ* 645
   - ሀ. ፈርጅ
   - ለ. ዕቅድ
   - ሐ. የአጻጻፍ ስልት ወይም ሁኔታ
   - መ. ድንጋጌ ወይም የተከለሰ (ጽሑፍ)
   - ሠ. ውሳኔ ወይም ድንጋጌ
   - ረ. ለሚፈውስ ጣዖት በመሥዋዕትነት የተሰጠ የሰው አካል ዓይነት
   - ሰ. የሕግን አስገዳጅነት ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ግሥ
2. ሎው እና ኒዳ፣ *የግሪክ-እንግሊዝኛ ሥርወ-ቃል፣ ቅጽ* 2፣ ገጽ 249
   - ሀ. ጠባሳ (ዮሐንስ 20፡25)
   - ለ. ምስል (ሐዋ. 7፡43
   - ሐ. ማሳያ (ዕብ. 8፡5)
   - መ. ምሳሌ (1ኛ ቆሮ. 10፡6፤ ፊሊጵ. 3፡17)
   - ሠ. ዋነኛ ማሳያ (ሮሜ. 5፡14)
   - ረ. ዓይነት (ሐዋ. 23፡25)
   - ሰ. ይዘት (ሐዋ. 23፡25)
3. ሃሮልድ ኬ. ሞልቶን፣ *የግሪክ ሥርወ-ግሥ ትንታኔ የተከለሰው፣ ገጽ* 411

ሀ. ጡጫ፣ ምልክት፣ መስያ (ዮሐንስ 20፡25)
ለ. ንድፍ
ሐ. ምስል (ሐዋ. 7፡43)
መ. ቀመር፣ የሥራ ዕቅድ (ሮሜ 6፡17)
ሠ. ቅርጽ፣ ዓላማ (ሐዋ. 23፡25)
ረ. ምልክት፣ ተመሳሳይ (1ኛ ቆሮ. 10፡6)
ሰ. የሚጠበቅ መልክ፣ ዓይነት (ሮሜ 5፡14፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡11)
ሸ. ምስያ ፈርጅ (ሐዋ. 7፡44፤ ዕብ 8፡5)
ቀ. የግብረ-ገብ ፈርጅ (ፊሊጵ. 3፡17፤ 1ኛ ተሰ. 1፡7፤ 2ኛ ተሰ. 3፡9፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡12፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡3)
በዚህ ጽሑፍ ተራ ቁጥር 1 ከላይ ያለው የተሻለ ይመስላል። ወንጌል ሁለቱንም፣ ማለትም የእምነት መግለጫውና የሕይወት ስልት ተጽዕኖ አለው። በክርስቶስ ያለ የደኅንነት ነጻ ስጦታ ክርስቶስን መምሰልንም ይጠይቃል!

6፡18 **"ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ"** ይህ ያልተጠናቀቀ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ነው። ወንጌል አማኞችን ነጻ አውጥቷቸዋል፣ በክርስቶስ ሥራና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት። አማኞች ከሁለቱም ነጻ ወጥተዋል፣ ከኃጢአት ቅጣት (መጽደቅ) እና ከኃጢአት ተገዥነት (መጽደቅ፣ ቁ. 7 እና 22)።

▣ **"የጽድቅ አገልጋዮች ሆናችኋል"** ይህ ያልተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ሲሆን፣ "ለጽድቅ አገልጋይ ሆናችኋል" የሚል ነው። ልዩ ርዕስ፡ 1፡17 ተመልከት። አማኞች ከኃጢአት ነጻ የወጡት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው፣ (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 14፣ 19፣22፤ 7፡4፤ 8፡2)! የነጻ ጸጋ ግብ መልካም ሕይወት ነው። ጽድቅ ሁለቱንም፣ ማለትም ሕጋዊ አዋጅ እና ግለሰባዊ ጽድቅን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው። እግዚአብሔር ሊያድነንና ሊለውጠን ይፈልጋል፣ ሌሎችን ለማስተማር! ጸጋ በእኛ ብቻ አያቆምም!

6፡19 **"ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እናገራለሁ"** ጳውሎስ ሮም ለሚገኙት አማኞች ነው መልእክቱ። እሱ መልእክቱን የሚያስተላልፈው፣ ሰምቶት ለነበረው ለአንድ አካባቢ ችግር ማለትም (በአይሁድ አማኞችና በአሕዛብ አማኞች መካከል በተነሣው መቀናናት) ነው፣ ወይንስ ሁሉንም አማኞች ስለሚመለከት እውነት? ጳውሎስ ይሄንን ሐረግ ቀደም ሲል ሮሜ 3፡5 ላይ ተጠቅሞበታል፣ ገላ. 3፡15 ላይ እንዳደረገው ሁሉ።
ቁጥር 19 ከቁ. 16 ጋር ትይዩ ነው። ጳውሎስ ሥነ-መለኮታዊ ነጥቦቹን ለአጽንኦት ይደግማቸዋል።
አንዳንዶች ይሄ ሐረግ የሚለው ጳውሎስ የባርያን ዘይቤ መጠቀሙን ይቅርታ ለመጠየቅ ነው፣ ይሉ ይሆናል። ሆኖም፣ "ስለ ሥጋችሁ ድካም" የሚለው ለዚህ ትርጓሜ አይመጥንም። ባርነት፣ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን ኅብተሰብ፣ በተለይም በሮም እንደ ክፉ ነገር አይታይም ነበር። እንደዚሁ የጊዜው ባህል ነበር።

▣ **"ሥጋ"** ልዩ ርዕስ 1፡3 ላይ ተመልከት

▣ **"የቅድስና ውጤት"** ይህ የመጽደቅ ግብ ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 22)። አኪ ይሄንን ቃል የሚጠቀመው ለሁለት ከደኅንነት ጋር ለተያያዙ ሥነ-መለኮታዊ እሳቤዎች ነው (1) አቋማዊ መቀደስ፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነ (ተጨባጥ ገጽታ)፣ ክርስቶስን በማመን በኩል በደኅንነት ጊዜ በመጽደቅ የሚሰጥ ነው (ሐዋ. 26፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡2፤ 6፡11፤ ኤፌ. 5፡26-27፤ 1ኛ ተሰ. 5፡23፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13፤ ዕብ. 10፡10፤ 13፡12፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2) እና (2) ቀጣይነት ያለው ቅድስናም የእግዚአብሔር ሥራ ሲሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ በኩል፣ የአማኙ ሕይወት ክርስቶስን ወደ መምሰልና ወደ ሙላቱ ሲሸጋገር ነው (ተያያዥ ገጽታ፣ 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ 1ኛ ተሰ. 4፡3፣7፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡15፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡21፤ ዕብ. 12፡10፣14)። ልዩ ርዕስ፡ መቀደስ 6፡4 ላይ ተመልከት።
ሁለቱም ስጦታ እና ትዕዛዝ ነው! አቋም ነው (ተጨባጭ) እና ተግባር ነው (ተያያዥ)! እሱም አመላካች (መግለጫ) እና አስገዳጅ (ትዕዛዝ) ነው! አመጣጡ መጀመሪያ ላይ ሆኖ፣ እስከ ፍጻሜው እስኪደርስ ድረስ አያስረግጥም (ፊሊጵ. 1፡6፤ 2፡12-13)።

6፡20-23
**[20]የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና። [21]እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና። [22]አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው። [23]የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።**

6:20-21 ይህ የተቀመጠው የቁ. 18 እና 19 ተቃርኖ ሆኖ ነው። አማኞች አንድ ጌታ ብቻ ማገልገል አለባቸው (ሉቃስ 16፡ 13)።

6:22-23 እነዚህ ቁጥሮች ሕጋዊ አካሄድን ይዘው ለአገልጋይ የሚከፈልን ያሳያሉ። ይህ የኃጢአትና የአማኝ ገለጻ በጸጋ አትኩሮት ላይ ስለሚያበቃ እግዚአብሔር ይመስገን! ቀዳሚው የጸጋ ስጦታ በእኛ ተባባሪነት ሲሆን ቀጥሎም የክርስቲያን ሕይወት ስጦታ በእኛ ተባባሪነት ነው። ሁለቱም በእምነት እና በንስሐ የምንቀበላቸው ስጦታዎች ናቸው።

6:22 **"ፍሬአችሁን ታገኛላችሁ፣ ከመቀደሳችሁ የተነሣ፣ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው"** "መጠቀም" የሚለው በጥሬ ትርጉሙ "ፍሬ" ጥቅም ላይ የዋለው ቁ. 21 ላይ የኃጢአትን ውጤት የሚያሳይ ሲሆን፣ ነገር ግን ቁ. 22 ላይ እግዚአብሔርን ማገልገል ያለውን ውጤት ነው የሚገልጸው። የወዲያው ጠቀሜታው የአማኙ ክርስቶስን መምሰል ነው። የመጨረሻው ጠቀሜታው ለዘላለም ከእሱ ጋር መሆንና እሱን መምሰል ነው (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። የወዲያው ውጤት ከሌለ (የተለወጠ ሕይወት፣ ያዕቆብ 2) የመጨረሻው ውጤት የመርሕ ጥያቄ ያስነሣል (የዘላለም ሕይወት፣ ማቴ. 7)። "ፍሬ የለም፣ ሥር የለም!"

6:23 ይህ የሙሉ ምዕራፉ ማጠቃለያ ነው። ጳውሎስ ምርጫውን በግልጽ አስቀምጧል። ምርጫው የራሳችን ነው— ኃጢአትና ሞት ወይም በክርስቶስ ነጻ ጸጋ እና የዘላለም ሕይወት። ከ"ሁለቱ መንገዶች" ጋር በጣም ይመሳሰላል፣ ብኪ የጥበብ ሥነ-ጽሑፎች (መዝሙር 1፤ ምሳሌ 4፤ 10-19፤ ማቴ. 7፡13-14)።

▣ **"የኃጢአት ዋጋ"** ኃጢአት በሰውኛ የተገለጠው እንደ (1) የባሪያ አሳዳሪ፣ (2) የጦር መሪ፣ ወይም (3) ምንዳ የሚከፍል ንጉሥ (ዝኒ ከማሁ. 3፡9፤ 5፡21፤ 6፡9፣14፣17)።

▣ **"የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ የዘላለም ሕይወት ነው"** "ነጻ ስጦታ" የሚለው ቃል የተተረጎመው (ማራኪ ውበት (ክሪስማ)) ከሚለው ሲሆን ሥሩም ጸጋ (ካሪስ ነው፣ ዝኒ ከማሁ. 3፡24፤ 5፡15፣ 16፣ 17፤ ኤፌ. 2፡8-9) 3፡24 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መልካም ሥራ እና ደኅንነት እንዴት ይዛመዳሉ (ኤፌ. 2፡8-9፣10)?
2. በአማኝ ሕይወት ቀጣይነት ያለው ኃጢአት፣ ከደኅንነት ጋር እንዴት ይዛመዳል (1ኛ ዮሐንስ 3፡6፣9)?
3. ምዕራፉ ስለ "ኃጢአት-የለሽ ፍጽምና" ያስተምራልን?
4. ምዕራፍ 6 ከምዕራፍ 5 እና 7 ጋር እንዴት ይዛመዳል።
5. እዚህ ለምን ጥምቀት ማብራሪያ ተደረገበት?
6. ክርስቲያኖች ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው ይመለሳሉ? ለምን?
7. ቁጥር 1-14 የአሁን ጊዜ ግሦች የበዙበትና ቁ. 15-23 ያለፈ ድርጊት ግሦች የበዙበት ምን ውጤት አለው?

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አኪጀት | አየተመት | አእት | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከትዳር የሆነ ምሳሌ | ከሕግ ነጻ መሆን | ከትዳር የሆነ ምሳሌ | ከትዳር የሆነ መግለጫ | ክርስቲያን በሕግ አልታሰረም |
| 7:1-6 | 7:1-6 | 7:1-3 | 7:1-6 | 7:1-6 |
| | | 7:4-6 | | |
| ያደረ ኃጢአት ችግር | ኃጢአት በሕግ እንደሚሠራ | ሕጉና ኃጢአት | ሕግና ኃጢአት | የሕግ ተግባራት |
| 7:7-12 | 7:7-12 | 7:7-12 | 7:7-11 | 7:7-8 |
| | | | | 7:9-11 |
| | | | 7:12-13 | 7:12-13 |
| | ሕግ ከኃጢአት አያድንም | | | |
| 7:13-25 | 7:13-25 | 7:13 | | |
| | | ውስጣዊው ግጭት | ግጭት በሰው ውስጥ | የሚያሸልም ትግል |
| | | 7:14-20 | 7:14-20 | 7:14-20 |
| | | 7:21-25ሀ | 7:21-25ሀ | 7:21-23 |
| | | | | 7:24-25ሀ |
| | | 7:25ለ | 7:25ለ | 7:25ለ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (viii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

ሀ. *ምዕራፍ 7 መተርጎም የሚኖርበት* (1) *በምዕራፍ 6 ብርሃን፣ በተለይም ቁ.* 12-14 (*እንዲሁም* 3:20፣ 21-31፤ 4: 13-16፤ 5:20)፣ *ቢሆንም፣* (2) *እንዲሁም መያያዝ የሚኖርበት በምዕራፍ* 9-11 *በተመለከተው በሮሜ ቤተ-ክርስቲያን፣ በአማኝ አሕዛብና በአማኝ አይሁድ መካከል በነበረው ክርክር ጋር ነው። የችግሩ ትክክለኛ አፈጣጠር ግልጽ አይደለም፤ ሊሆን የሚችለው፡*
1. *በሙሴ ሕግ ላይ የተመሠረተ ሕጋዊነት፣*
2. *የይሁዲነት ተጽዕኖ፣ በሙሴ መቅደምና በኢየሱስ መቀጠል*
3. *ወንጌል ለአይሁድ እንዴት እንደሚፈጸም ያለ ያረዳድ ችግር*
4. *በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ግንኙነት በሚገባ አለመረዳት።*
5. *ሁሉንም ዓይነት የአይሁድን የአምልኮ ሥርዓት በሮም እንዳይደረግ ባገደው የንጉሡ አዋጅ ምክንያት፣ አማኝ አይሁድ አመራሮች በአማኝ አሕዛብ አመራሮች በመተካታቸው ምክንያት በተፈጠረ መቀናናት ይሆናል። በርካታ አማኝ አይሁድ ለቀው እንዲወጡም ተደርጓል።*

ለ. *ሮሜ* 7:1-6 *በምዕራፍ* 6 *የጀመረውን ዘይቤያዊ ቋንቋ ይቀጥላል፣ ይህም የክርስቲያንና ያሮጌው ሕይወቱን ግንኙነት ነው። የተጠቀመባቸው ዘይቤዎችም*
1. *ሞትና ከባርነት ነጻ ሆኖ ለሌላ ጌታ ማደር* (*ምዕራፍ* 6)
2. *ሞትና ከትዳር የመፋታት አስገዳጅነት* (*ምዕራፍ* 7)

ሐ. *ምዕራፍ* 6 *እና* 7 *ትይዩ ናቸው፤ ምዕራፍ* 6 *የሚገልጸው አማኝ ከ"ኃጢአት" ጋር ያለውን ግንኙነት ሲሆን ምዕራፍ* 7 *ደግሞ አማኝ ከሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት ነው። ምስያው፣ ሞት ባሪያን ነጻ እንደሚያወጣ* (6:12-23) *እና በንጽጽርም ሞት ከትዳር እስራት ነጻ እንደሚያወጣ ነው* (7:1-6)።

| **ምዕራፍ 6** | **ምዕራፍ 7** |
|---|---|
| 6:1 "*ኃጢአት*" | 7:1 *ሕግ* |
| 6:2 "*ለኃጢአት መሞት*" | 7:4 "*ለሕግ መሞት*" |
| 6:4 "*እኛ በአዲስ ሕይወት እንንገዝ ዘንድ*" | 7:6 "*በአዲስ መንፈስ እናገለግል ዘንድ*" |
| 6:7 "*የሞተስ ከኃጢአቱ ነጻ ሆኖአል*" | 7:6 "*ከሕግ ነጻ ወጥተናልና ለዚያ ለተያዝንበት በመሞት*" |
| 6:18 "*ከኃጢአት ነጻ መውጣት*" | 7:3 "*ከሕግ ነጻ መሆን*" |

(*ከአንደርስ ኒግሪን የወደ ሮሜ ሰዎች ሐተታ* የተወሰደ፣ ካርል ሲ. *ራስሙሰን እንደተረጎመው፣ ገጽ* 268)

መ. *ሕጉ ከነ ድንጋጌው የሞት ፍርድ ነበር። ሁሉም ሰዎች ከሕግ በታች ተኮንነዋል* (*ሮሜ* 6:14፤ 7:4፤ *ገላ.* 3:13፤ *ኤፌ.* 2:15፤ *ቆላ.* 2:14)። *ሕጉ ርግማን ነበር።*

ሠ. *ምዕራፍ* 7 *እንዴት እንደሚተረጎም አራት ዋነኛ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ*
1. *ጳውሎስ ስለ ራሱ የሚናገርበት* (*ግለ-ታሪካዊ*)
2. *ጳውሎስ የሰው ልጆችን ወክሎ የሚናገርበት* (*ውክልና፣ ቺሶስቶም* Chysostom)
3. *ጳውሎስ ስል አዳም የሕይወት ልምድ የተናገረው* (*የሞፕሱቲያው ቲዮዶር*)
4. *ጳውሎስ ስለ እስራኤል የሕይወት ልምድ የተናገረው።*

ረ. *በብዙ መንገድ ሮሜ* 7 *እንደ ዘፍጥረት* 3 *ነው፣ አገባቡ። እሱም የሚያሳየው ዐመጻ ወደ ታች ጎትቶ እንደሚጥል ሲሆን፣ ስለ እግዚአብሔር በሚገባ የሚያውቁትንም ይጨምራል። እውቀት የወደቀውን የሰው ልጅ ነጻ አያወጣም፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ፣ ንጹሕ ልብ ብቻ ነው እንደዚያ ሊያደርግ የሚችለው* (*አዲስ ኪዳን፣ ኤር.* 31:31-34፤ *ሕዝ.* 36:26-27)። ከዚያም በኋላ እንኳ ቀጣይ ትግል አለ!

**የቃልና ሐረግ ጥናት**

**7:1-3 [1]ወንድሞች ሆይ፥ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን? [2]ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና፤ ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች። [3]ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።**

**7:1 "(ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁ)"** ይህ የሚያመለክተው (1) አማኝ አይሁድን ብቻ (2) በአማኝ አይሁድና አሕዛብ መካከል በሮሜ ቤተ-ክርስቲያን የነበረው አለመግባባት፤ (3) ሕግ በአጠቃላይ መልኩ ለሁሉም የሰው ልጆች አንጻራዊ መሆኑ (ዝኒ ከማሁ. 2:14-15)፤ ወይም (4) ለአዲስ የአሕዛብ አማኞች፣ ስለ አዲሱ እምነታቸው (መሠረተ እምነት) ከብሉ ጽሑፎች በመማር ላይ ሳሉ።

▣**"ሕጉ"** ይህ የምዕራፉ ዋነኛ ጉዳይ ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 1፣2፣4፣5፣6፣ ወዘተርፈ)። ስለሆነም ጳውሎስ ቃሉን በተለያየ ዓይነት እሳቤዎች ተጠቅሞበታል። የጳውሎስ የገለጻ ቃታ ያተኮረው 6:14 ላይ ይመስላል። የእሱ አቀራረብም ከምዕራፍ 6 አወቃቀር ጋር ትይዩ ነው። ጽሑፋዊ ይዘት ሐ ተመልከት። ሕግና የሱም ግንኙነት በክርስቶስ ከሆነው አዲስ ኪዳን ጋር እንዲሁ 3:21-31 እና 4:13-16 ላይ ተብራርቷል።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ሰው በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ ሕግ የተፈጻሚነት ኃይል አለው"** |
| **አኪጀት** | **"ሰው በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ ሕጉ የመግዛት ኃይል አለው"** |
| **አየተመት** | **"ሕጉ በሰው ላይ ያስገዳጅነት ኃይል የሚኖረው ሰውየው በሕይወት ባለበት ጊዜ ብቻ ነው"** |
| **አእት** | **"ሕጉ በሰው ላይ የሚገዛው በሕይወት ሲኖር ብቻ ነው"** |
| **ኢመቅ** | **"ሕግጋት በሰው ላይ የሚፈጸሙት በሰውየው የሕይወት ዘመን ላይ ብቻ ነው"** |

ይህ በጥሬ ትርጉሙ "በእሱ ላይ ጌታ ነው" ማለት ነው (ኩሪዩ kurieuo፣ ዝኒ ከማሁ. 6:9፣14)። የሙሴ ሕግ ሁለቱንም፣ ማለትም፣ ታላቅ በረከት (መዝ. 19:119)፣ እና አስፈሪ ርግማን (ገላ. 3:13፤ ኤፌ. 2:15፤ ቆላ. 2:14)። በአካላዊ ሞት፣ የሕግ አስገዳጅነት ያከትማል። ይህ ምዕራፍ 6 ካለው አማኝ ለኃጢአት መሞቱን የሚያመለክተው ጋር ተመሳሳይ ዘይቤ ነው።

**7:2 "ያገባች ሴት"** ይህ በቁ. 1-6 ያለ የጳውሎስ ዋነኛው መግለጫ ነው። በምዕራፍ 6 ላይ ሞት የባርነት ግዴታ መቋጫ እንደሚሆን አሳይቷል። እዚህ፣ ጋብቻና ግዴታዎቹ ነው፣ ትኩረቱ። እዚህ መግለጫው ተገልብጧል፣ ምክንያቱም እንዲሞት የተደረገው ባልየው ነው፣ መበለቲቱ ድጋሚ ታገባ ዘንድ በጳውሎስ ምስያ ግን የሚሞተው አማኙ ነው፣ እናም ለእግዚአብሔር ይኖር ዘንድ።

▣**"ተፈትታለች"** ይህ ቁ. 6:6 እንዳለው ግሥ ዓይነት ነው፤ ፍቺውም "እንዳይሠራ ማድረግ፣" "ጥቅመ-ቢስ ማድረግ፣" ወይም "መወገድ" ማለት ነው። በ6:6 ላይ፣ ያለፈ ተገብሮ ነበር፣ እዚህ የተጠናቀቀ ተገብሮ ሲሆን ፍቺውም "የተለቀቀና በመለቀቁ የቀጠለ" ማለት ነው። ልዩ ርዕስ 3:3 ተመልከት።

**7:3 "አመንዝራ ተብላ ትጠራለች"** ይህ አስተያየት የሚዛመደው በአይሁድ ክርክር ማለትም በራቢያዊ ትምህርት ቤቶች፣ በሻማይ እና ሂለል መካከል በዘዳግም 24:1-4 ላይ ነው፤ በተለይም "ስለ ተወሰኑ ነውሮች።" የሂለል ትምህርት ቤት ለዘብተኛ ቡድን ሲሆን ፍቺን በሁሉም ምክንያት ይፈቅዳል። የሻማይ ትምህርት ቤት ወግ-አጥባቂ ቡድን ሲሆን ፍቺን የሚፈቅደው በአመንዝራነት ብቻ ወይም በግብረ-ሥጋ ተራክቦ ችግሮች ነው (ማቲ. 5:32፤ 19:9)።

> 7:4-6
> **[4]እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ። [5]በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ [6]አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥ ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።**

**7:4 "እናንተም ደግሞ ተገድላችኋል"** ይህ የአንቀጹ ዋነኛ ሐሳብ ነው (የምዕራፍ 6ም)። ምዕራፍ 6 ላይ ከሚገኘው፣ ክርስቶስ እንዳደረገው፣ የክርስቲያንን ለኃጢአት መሞት ከሚገልጸው ምስያ ጋር ዝምድና አለው (2ኛ ዜና. 5:14 -15፤ ገላ. 2:20)። አማኞች በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ናቸው፣ በዚህ በአዲሱ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን (2ኛ ቆሮ. 5:17)

▣ **"በክርስቶስ ሥጋ በኩል"** ይህ የቤተ-ክርስቲያንን የክርስቶስ አካል መሆን የሚጠቅሰው ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ አይደለም (1ኛ ቆሮ. 12:12፣27)፣ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ሥጋዊ አካል በ6:3-11 እንዳለው፣ ክርስቶስ ሲሞት፣ አማኞችም በጥምቀት በኩል እንደተመለከተው፣ ከእሱ ጋር እንደሚሞቱ ነው። የሱ መሞት የእነሱ ሞት ነው (2ኛ ቆሮ. 5:14-15፤ ገላ. 2:20)። የእሱ የትንሣኤ ሕይወት እግዚአብሔርንና ሌሎችን ያገለግሉ ዘንድ ነጻ አውጥቷቸዋል።

▣ **"ለእግዚአብሔር ፍሬ እናፈራ ዘንድ"** ይህም ደግሞ ከምዕራፍ 6 ጋር ትይዩ ነው፣ በተለይም ከ6:22 ጋር። አማኞች አሁን በክርስቶስ ነጻ ወጥተዋል፣ ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር ያስተሳስሩ ዘንድ። ይህ ቀጣይነት ያለው የጋብቻ ምስያ ነው። ክርስቶስ ለአማኞች እንደሞተ ሁሉ፣ እነሱም አሁን ለኃጢአት መሞት ይኖርባቸዋል (2ኛ ቆሮ. 5:13-14፤ ገላ. 2:20)።

ክርስቶስ እንደተነሣ፣ እነሱም እንዲሁ፣ በእጅጉን ተነሥተዋል በአዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሔረን ለማገለገል (ሮሜ. 6፡22፤ ኤፌ. 2፡5-6)።

7፡5
**አአመመቅ** "በሥጋ እንዳለንበት ጊዜ"
**አኪጀት** "በሥጋ በነበርንበት ጊዜ"
**አየተመት** "በሥጋ እንኖር እንደ ነበር"
**አእት** "በሰዋዊ ተፈጥሯችን እንኖር እንደ ነበር ጊዜ"
**ኢመቅ** "ከመለወጣችን በፊት"

ይህ ቁጥር የቁጥር 4 ተቃራኒ ነው። ቁጥር 4 የሚዛመደው ከአማኝ የሕይወት ልምድ ጋር ነው፣ እንደ ቁጥር 6 ሁሉ። ቁጥር 5 የሚገልጸው ከእግዚአብሔር ኃይል ውጪ ከሆነ ሕይወት ስለሚኖር "ፍሬ" ነው (ገላ. 5፡18-24፡) ሕግ ለአማኞች ኃጢአታቸውን ያመላክታቸዋል (ቁ. 7-9፤ ገላ. 3፡23-25)፣ ነገር ግን ያሸንፉት ዘንድ ኃይል ሊሰጣቸው አይችልም።

ከጽሑፍ አኳያ ይህ የሚያመለክተው የአማኞችን የወደቀ፣ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ፣ ከአዳም የተወረሰውን ነው (ዝኒ ከማሁ. 6፡19)። ጳውሎስ ይህንን ሳርክስ (sarx) የሚለውን ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞበታል (1) የኃጢአት ተፈጥሮ (አሮጌው አዳም)፣ እና (2) ሥጋዊ አካል (ዝኒ ከማሁ. 1፡3፤ 4፡1፤ 9፡3፣5)። እዚህ ላይ አሉታዊ ነው፣ ነገር ግን ሮሜ. 1፡3፤ 4፡1፤ 9፡3፣5፤ ገላ. 2፡20። ሥጋ/ግዘፍ አካል (ሳርክስ/ሶማ) በውስጡም ሆነ በራሱ ክፉ አይደለም፣ ነገር ግን እንደ አእምሮ (ኖውስ) የጦር ሜዳ ነው፣ በዚህ ዘመን በክፉ ኃይላትና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚካሄደው ትንቅንቅ ስፍራ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት የተጠቀመው በቋሚነት ከሴፕቱዋጂንት (የግሪክ የብሉይ ኪዳን ቅጅ) ጋር ነው፣ ከግሪክ ሥነ-ጽሑፍ ጋር ሳይሆን።

▣ "በሕግ ሳቢያ የተነሣ" የዚህን ገጽታ ዓይነቱ ዐመጸኛ የሰው ተፈጥሮ፣ ለተከለከለ ነገር ሁሉ የክፋት ምላሽ የሚሰጥ፣ በዘፍ. 3 እና በሁሉም ሰዎች ዘንድ በግልጽ ታይቷል። ሕጉ ገደብ ያስቀምጣል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 7-8)። እነዚህ ገደቦች የሰው ልጆችን ለመጠበቅ ናቸው፣ ነገር ግን ሰዎች እንደ ሰንሰለትና ገደብ አድርገው ነው የተመለከቷቸው። ኃጢአተኛው፣ ጥገኛ ያልሆነው መንፈስ በእግዚአብሔር ሕግ ይነቃቃል። ችግሩ ገደቦቹ አልነበሩም (ሕግ፣ ዝኒ ከማሁ. ቁ. 12-13)፣ ነገር ግን የሰው የራስ ሥልጣንና የግል ፈቃድ ነው።

7፡6 "አሁን ግን" ኒውማን እና ኒዳ፣ *የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ላይ የተርጓሚ ማስታወሻ* ፣ ላይ ግሩም አስተያየት ይገኛል።
"በቁጥር 5 እና 6 መካከል የሚገኘውን ትይዩ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፣ በተጨማሪም ደግሞ ከተከታዮቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት። ቁጥር 5 የሚገልጸው ቅድመ-ክርስትና የሕይወት ልምዶችን ሲሆን፣ ከ7.7-25 ጋር ትይዩ አለው፤ ቁጥር 6 የሚገልጸው በእግዚአብሔር ምንፈስ አመራር ሥር የሆነውን የአሁኑን የእምነት ሕይወት ሲሆን፣ በ8.1-11 ላይ ትይዩ አለው" (ገጽ 130)።

▣ "ተፈትተናል" ይህ የተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ነው። ይህም ቁ. 5 ያለው ያልተጠናቀቀ የመሐል አመላካች ነው። አማኞች በሕግ እንደተገለጸው በተደጋጋሚ በኃጢአት ተይዘዋል፣ አሁን ግን በወንጌል መልካም የምስራች በመንፈሱ በኩል ነጻ ወጥተዋል። ተመሳሳይ የሆነ ቃል ቁ. 2 ላይ ባሏ ስለሞተባት ሴት ተገልጿል።

▣ "ለዚያ ለታሰርንበት ሞተናልና" ይህ የድርጊት የአሁን ቦዝ አንቀጽ ሲሆን ያልተጠናቀቀ ተገብሮ አመላካች ተከትሎታል። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት በኩል አማኞችን ነጻ ያወጣው (1) ከብኪ ርግማን፤ እና (2) ከራሳቸው ውስጣዊ የኃጢአት ማንነት ነው። እነሱ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ፣ በተገለጠው በእግዚአብሔር ፍቃድ ላይ በማመጽ ተጠምደዋል፣ እንዲሁም በወደቀው ተፈጥሮ፣ በግል ኃጢአት፣ እና ከተፈጥሮ በላይ በሆኑ ፈተናዎች (ኤፌ. 2፡2-3)!

▣ "አዲስነት… አሮጌነት" ይህ አዲሱ መንፈሳዊ መንገድ አዲስ ኪዳንን የሚያመላክት ይመስላል (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡22-32)። የግሪኩ ቃል "አዲስ" (ኬኖስ kainos- ኬኖቲስ kainotēs) በጳውሎስ ጥቅም ላይ የዋለው

1. የሕይወት አዲስነት፣ ሮሜ 6፡4
2. የመንፈስ አዲስነት፣ ሮሜ 7፡6
3. አዲስ ኪዳን፣ 1ኛ ቆሮ. 11፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡6
4. አዲስ ተፈጥሮ፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15
5. አዲሱ ሰው፣ ኤፌ. 2፡15፤ 4፡24

"አሮጌ" የሚለው ቃል የሚያሳየው የሙሴን ሕግ ሲሆን ፍቺውም "ሙሉ ለሙሉ ያረጀ" ማለት ነው። ጳውሎስ አሮጌውን ኪዳን እና አዲሱን ኪዳን በተቃርኖ ያነጻጽራቸዋል፣ የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳደረገው ሁሉ (ዝኒ ከማሁ. 8፡7 እና 13)።

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ፣ አኪጀት | "ስለሆነም በመንፈስ መታደስ እናገለግላለን" |
| አየተመት | "ስለሆነም ለአሮጌው የተጻፈ ሕግ ባሪያዎች አይደለንም፣ ነገር ግን ለአዲሱ የመንፈስ ሕይወት እንጂ" |
| አእት | "ነገር ግን በመንፈስ በአዲሱ ሕይወት" |
| ኢመቅ | "በአዲሱ መንፈሳዊ መንገድ ለማገልገል ነጻ መሆን" |

ይህ በጥሬው፣ "በመንፈስ አዲስነት" ማለት ነው:: ይህ የሚያመለክተው የታደሰውን የሰው መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስን እንደሆነ እርግጠኛ አይደለም:: አብዛኛዎቹ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎች በጉልህ ፊደል ይጽፉታል፣ ያም ማለት መንፈስ ቅዱስን ነው፣ ይሄውም ለመጀመሪያ ጊዜ አሻሚ በሆነ መልኩ በሮሜ 8 ላይ (15 ጊዜ) ተጠቅሷል:: "መንፈስ" የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው የታደሰውንና በወንጌልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላውን የሰውን መንፈስ ሊሆን ይችላል ሮሜ. 1:4፣9፤ 2:29፤ 7:6፤ 8:15፤ 11:8፤ 12:11፤ 1ኛ ቆሮ. 2:11፤ 4:21፤ 5:3፣4፣5፤ 7:34፤ 14:15፣16፣ 32፤ 16:18::

በጳውሎስ ጽሑፎች "ሥጋ" እና "መንፈስ" ዘወትር በተቃርኖ እንደ ሁለት የተለያዩ የአስተሳሰብና የአኗኗር መንገዶች ይቀርባሉ (ዝኒ ከማሁ. 7:14፤ 8:4፤ ገላ. 3:3፤ 5:16፣17፣25፤ 6:8):: ሥጋዊ ሕይወት፣ እግዚአብሔር የሌለበት "ሥጋ" ነው፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ሕይወት "መንፈስ" ወይም "መንፈስ ቅዱስ" ነው:: የሚያድርብን መንፈስ ቅዱስ (ዝኒ ከማሁ. 8:9፣11) አማኝን በክርስቶስ ወደ ሆነ አዲስ ፍጥረት ይለውጠዋል (በአቋምም ሆነ በተሞክሮአዊ)

**ጽሑፋዊ ይዘት ሮሜ 7:7-25**

ሀ. ሮሜ 7:7-25 ሰብዓዊ እውነታን ይገልጻል:: ሁሉም የሰው ልጆች፣ ሁለቱም፣ የዳኑትም ሆነ የጠፉት፣ የጥሩውን እና የክፉውን ክርክር በነበሩበት ዓለም እና በራሳቸው ልብና አእምሮ የሕይወት ተሞክሮ አላቸው:: ትርጓሜአዊ ጥያቄው፣ "ጳውሎስ ይሄንን አንቀጽ ምን ለማስረዳት ብሎ ነው እንዲህ ያደረገው?" የሚል ነው:: ከጽሑፍ አኳያ መዛመድ የሚኖርበት ከምዕራፍ 1:18-6:23 እና 8:1-39:: አንዳንዶች በሁሉም የሰው ልጆች ላይ እንደሚያተኩር አድርገው ይመለከቱታል፣ እና ስለዚህ የጳውሎስን ግላዊ የሕይወት ልምድ እንደ ምሳሌ ይመለከታሉ:: ይህ አተረጓጎም "ግለ-ሕይወታዊ ንድፈ-ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል:: ጳውሎስ "እኔ"ን በ1ኛ ቆሮ. 13:1-3 ላይ የተጠቀመው ግላዊ ባልሆነ እሳቤ ነው:: ይህ ዓይነቱ ግላዊ ያልሆነ የ "እኔ" አጠቃቀም ከአይሁድ መምህራን ዘንድ ከዶሴ ተወስዶ ሊሆን ይችላል:: ይህም እዚህ ትክክል ከሆነ፣ ምንባቡ የሚያመለክተው የሰው ልጅን ከጥፋተኝነት ነጻ መሆን፣ ይህም በጥፋተኝነት በኩል ወደ ደኅንነት መሸጋገሩን የሚያሳይ ነው (ምዕራፍ 8) "የውክልና ንድፈ ሐሳብ::"

ሆኖም፣ ሌሎች እነዚህን ቁጥሮች የሚመለከቷቸው አማኝ ከወደቀው የሰው አፈጣጠር ጋር ከሚያደርገው መራራ ትግል ጋር አዛምደው ነው:: ልብ የሚሰነጥቀው የቁ. 24 ጩኸት የሚገልጸው ይሄንኑ ውስጣዊ ውጥረት ነው:: የድርጊትና ያልተጠናቀቀ ግሥ ጊዜያቶች ቁ. 7-13 ላይ በእጅጉን ያሉበት ሲሆን፣ በሌላ መልኩም የአሁንና የተጠናቀቀ ግሥ ጊዜያቶች የሚበዙት ቁ. 14-25 ላይ ነው:: ይህም "ግለ-ታሪካዊ ንድፈ-ሐሳብ" ለመሆኑ አመኔታ ለማግኘት ይመስላል፣ ጳውሎስ የሚገልጸው የራሱን ልምድ ሲሆን ይህም፣ ከጥፋት ነጻ፣ ወደ ጥፋተኝነት፣ ወደ ጽድቅ እና ክርክሩም ወደ ቀጣይ ቅድስና የሚያመራ ነው (ዝኒ ከማሁ. በራስ egō፣ "እኔ ራሴ፣" ዝኒ ከማሁ. ቁ. 25)::

ሁለቱም አመለካከቶች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ:: በቁ. 7-13 እና 25ለ ላይ ጳውሎስ በግለ-ታሪክ መልክ የሚያቀርብ ሲሆን ቁ. 14-25ሀ ላይ ደግሞ የራሱን የሕይወት ልምድ፣ ማለትም ከኃጢአት ጋር የሚደረገውን ውስጣዊ ትግል፣ እንደ ተዋጀ ስብዕና ተወካይ አድርጎ ያቀርባል:: ሆኖም፣ እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት ይህ ሙሉ ምንባብ ከጳውሎስ የፊት ሁኔታ፣ ዳግም ከመወለዱ በፊት የነበረበትን፣ እንደ ተሰጠ የአይሁድ ሃይማኖታዊ አኳያ መታየት አለበት:: የጳውሎስ የሕይወት ልምድ ተለይቶ የራሱ ነው::

ለ. ሕጉ መልካም ነው:: እሱም ከእግዚአብሔር ነው:: አገልግሏል፣ በማገልገሉም ይቀጥላል፣ መለኮታዊውን ተግባር (ዝኒ ከማሁ. 7:7፣ 12፣ 14. 22፣25):: ሰላም ወይም ደኅንነትን ሊያመጣ <u>አይችልም</u>:: ጀምስ ስቲዋርት *የክርስቶስ ሰው* በሚለው መጽሐፉ ላይ፣ የጳውሎስን አያዎአዊ (ፓራዶክስ) አስተሳሰብና አጻጻፍን አሳይቷል፡

"አንድን ያስተሳሰብ ሥርዓትና መሠረተ እምነት በመቃረን በተቻለ መጠን የሌላውን ባለመስማት የራሱን የቃላት ትርጉም እየተጠቀመ ከሚሄድ ሰው መቼም ቢሆን የሚጠበቀው ይሄ ነው:: በሐረጋት ላይ ዓልሞ መሪ ሐሳቡን ሲያደራጅ ልታውቁት ትችላላችሁ:: እናም በጸሐፊያችሁ አንድ ጊዜ በአንድ የተለየ እሳቤ የተጻፈ ቃል እስከ ጽሑፉ ማብቂያ ድረስ ያንኑ ይዞ መሄድ አለበት ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል:: ነገር ግን ይሄንን ከጳውሎስ መጠበቁ ቅሬታን ይፈጥርባችኋል:: አብዛኞቹ የሐረጋት አደራደር ተያያዥነትን ጠብቆ የሚሄድ እንጂ ድርቅ ያለ አይደለም... 'ሕጉ ቅዱስ ነው፣' ብሎ ጽፏል፣ 'በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛል' (ሮሜ 7:12-13) ነገር ግን በግልጽ ሌለኛው (የኖሞስ nomos) ገጽታ ሆኖ ነው፣ በሌላ ስፍራ፣ 'ክርስቶስ እኛን ከሕግ ርግማን ዋጀን ገላ. 3:13' ያለው)" (ገጽ 26)::

ሐ. "ከቁጥር 14-25 ጳውሎስ የሚጠቅሰው ለዳነ ወይስ ላልዳነ ሰው ነው?" ለሚለው ጥያቄ ጽሑፋዊ ማስረጃ እንደሚከተለው ነው

1. ያልዳነ ሰው

ሀ. ይህ የጥንታዊ ግሪክ ተናጋሪ የቤተ-ክርስቲያን አባቶች ትርጓሜ ነበር
ለ. ተከታዮቹ ሐረጎች ይህንን አመለካከት ይደግፋሉ
(1) "እኔ ከሥጋ ነኝ፣" ቁ. 14
(2) "ለኃጢአት ባርነት የተሸጥኩ፣" ቁ. 14
(3) "ምንም መልካም ነገር የሌለብኝ፣" ቁ. 18
(4) "በሰውነት ብልቶቼ በኩል የኃጢአት ሕግ እስረኛ አድርጎኛልና፣" ቁ. 23
(5) "ምንያለሁ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ለተሰጠ ሰውነት ማን ነጻ ያወጣኛል?" ቁ. 24
ሐ. አብዛኛው የሮሜ ጽሑፍ ምዕራፍ 7ን በመቀደስ ላይ የሚያተኩር ክፍል አድርጎ ይወስደዋል።
መ. ግልጽ የሆነው የግሥ ጊዜያቶች ለውጥ ካልተጠናቀቀና ካለፈ ድርጊት ቁ. 7-13 ወደ ቋሚ የአሁን ጊዜ አጠቃቀም ቁ. 14-24 መደረጉ የሚያመለክተው የጳውሎስን የተለየና አዲስ የሕይወቱን ክፍል ነው (ያም ማለት፣ መለወጥ)።
መ. አማኝ ክርስቶስን ለመምሰል በጣም ጥረት ባደረገ ቁጥር የራሱን ኃጢአተኝነት ይበልጡን እየተረዳ ይመጣል። ይህ አያዎ እዚህ ጽሑፍ ላይ ስምም ይሆናል፣ እንዲሁም በጳውሎስ ስብዕና ላይ (እናም፣ እንዲያውም በብዙዎቹ አማኞች)።
ከሄንሪ ትዌልስ ሉተራዊ ዝማሬ አንድ መስመር፡
"ሌላ ማንም፣ ጌታ ሆይ፣ ፍጹም ሰላም የለም፣
ማንም ጨርሶ ከኃጢአት ነጻ አይወጣም፤
እነዛም ዝለው የነበሩ አንተን በእጅጉን ያገለግሉሃል
ውስጣቸው ያለውን ስህተት በሚገባ ያጤኑታል።" (የደራሲው ስምና የዝማሬው ርዕስ ያልታወቀ)

7:7-12
**[7]እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ። አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። [8]ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና። [9]እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤ [10]ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤ [11]ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል። [12]ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።**

7:7 **"እንግዲህ ምን እንላለን"** ጳውሎስ ወደ ወቀሳ አጠቃቀሙ ተመልሷል (ዝኒ ከማሁ. 6:1፣15፤ 7:1፣13)።

▣ **"ሕጉ ኃጢአት ነውን"** አንደኛው የመገለጥ አያዎ፣ እግዚአብሔር የሕግን ቅዱስነትና መልካምነት እንደ መስታዎት ለኃጢአት ማሳያ ተጠቅሞ የወደቀው የሰው ልጅ ንስሐ እንዲገባና እምነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 12-13፤ ገላ. 3)። በተጨማሪም በአስገራሚ መልኩ ሕጉ ለቅድስና መሥራቱን ቀጥሏል፣ ለጽድቅ ባይሆንም!

▣ **"ይህስ ጨርሶ አይሁን"** የጳውሎስ ባሕርይ በሆነው የተሳሳቱ መረዳቶችን ማስወገድን ያሳያል (ዝኒ ከማሁ. ቁ. 13፤ 3፡ 4፣6፣31፤ 6:2፣15፤ 9:14፤ 11:1፣11፤ ገላ. 2:17፤ 3:21)።

▣ **"በተቃራኒው"** የጳውሎስ ሥነ-ጽሑፋዊ ስልት በሮሜ ላይ ነጥቦቹን ለማስቀመጥ ጠንካራ ተቃርኖዎችን ይጠቀማል (ዝ.ከ. 3:4፣6፣31፤ 6:2፣15፤ 7:13፤ 9:14፤ 11:1፣11)።

▣ **"እኔ"** በመጽሐፍ ቅዱስህ ላይ፣ "እኔ፣" "የኔ፣" ወይም "እኔን" የሚሉት ግላዊ ተውላጠ ስሞች በጽሑፉ ቁ. 7-25 ምን ያህል ጊዜ እንደተከሰቱ ተመልከት። ያስገርምሃል። ከአርባ ጊዜ በላይ ነው።

▣ **"በሕግ ካልሆነ በቀር ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር"** ይህ አንደኛው ቁልፍ ምንባብ ሲሆን የሚገልጸውም ጽንሰ-ሐሳብ የሙሴ ሕግ የግል ኃጢአትን በመግለጽ በኩል እንዴት አድርጎ እንደ መስታወት እንደሚሠራ ነው (ዝከ. 3:20፤ 4:65፤ 5: 20፤ ገላ. 3:14-29፣ በተለይም ቁ. 24)። ሕጉን አንድ ጊዜ መስበር ማለት ኪዳኑን መስበር ማለት ነው፣ እናም የሚያመጣውን ውጤት መቀበልን ያስከትላል (ዝከ. ቁ. 10 እና ያዕቆብ 2:10)!

▣ **"በሕግ ካልሆነ በቀር"** ይህ ሁለተኛ ምድብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ "ከሐቅ ጋር የሚቃረን" ተብሎ ይጠራል፣ ጳውሎስ በኃጢአቱ ጥፋተኛ በሆነበት። ይህ የሮሜ ሰዋሰዋዊ ገጽታ ብቸኛው ምሳሌ ነው። ጳውሎስ በገላ. 1:10፤ 3:21፣ እንዲሁም 1ኛ ቆሮ. 2:8፤ 5:10፤ 11:31፤ እና 2ኛ ቆሮ. 12:11 ላይ ተጠቅሞበታል።

▣ **"አትመኝ"** ይህ ከአስርቱ ትዕዛዛት የመጨረሻው ትዕዛዝ ላይ የተጠቀሰ ነው (ዘጸአት 20:17፤ ዘዳግም 5:21)። ይህ የመጨረሻው ትዕዛዝ የሚያተኩረው በተገቢ ጠባይ ላይ ሲሆን፣ በእርግጥ የሁሉም ፍሬ ሐሳብ ነው (ማቴ. 5:7)። ሕጉ ለእኛ የሚጠቀስልን "ትዕዛዝ" በሚል ነው (ዝከ. ቁ. 8፣9፣11፣12፣13)። "አትመኝ" የሚለው ቃል "ልብን በአንዱ ላይ

መጣል" ወይም "በጽኑ መመኘት" ማለት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች (ለጠፉትም ሆነ ለዳኑት) በርካታ መልካም ነገሮች በተፈጥሮ በኩል ሰጥቷቸዋል፤ ነገር ግን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስጦታ፣ እግዚአብሔር መጥኖ ከሚሰጠው በላይ ለመውሰድ ይሻሉ። "ብዙ በጣም ብዙ ለእኔ ብቻ፣ እንደምንም" ነው ዓላማቸው! እኔነት ክፉው ገዥ ነው! ልዩ ርዕስ፡ የዘጸአት ማስታወሻዎች የሚለውን 20፡17 በ13፡8-9 ላይ ተመልከት።

7፡8

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ዕድሉን ወስዶ"** |
| **አየተመት** | **"ዕድሉን በመያዝ"** |
| **አእት** | **"ዕድሉን አግኝቶ"** |
| **ኢመቅ** | **"ዕድሉን በመውሰድ"** |

ይህ ወታደራዊ ቃል ሲሆን ጥቅም ላይ የሚውለውም ገገር ቦታ ወይም የውጊያ መደብ በሚል ነው (ዝከ. ቁ. 8 እና 11)። በዚህ ጽሑፍ ሰውኛ (ዘይቤ) ተደርጓል (ዝከ. ቁ. 9፣11)። ኃጢአት እንደ ወታደራዊ ውጊያ ያለ ባሕርይ ተላብሷል (ዝከ. ቁ. 11) በወታደራዊ አዛዥ እየተመራ (ዝከ. ቁ. 11 እና 17፤ 6፡12፣ 14፣16)።

▣ **"ካለ ሕግ በስተቀር ኃጢአት ሙት ነው"** ኃጢአት በእግዚአብሔር ፍቃድ ላይ ማመጽ ነው (ሮሜ 4፡15፤ 5፡13፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡56)። በዚህ ሐረግ ላይ ግሥ የለም፤ አንድ ሊሰጠው ይገባል። አንዱ የአሁን ጊዜ ቢሰጠው፣ ውጤቱ አጠቃላይ መርሕ ይሆናል። አንዱ የተጠናቀቀ ጊዜ ቢሰጠው፣ የጳውሎስን ግላዊ ሕይወት ይመለከታል።

7፡9 **"እኔም አንጼ ሕያው ነበርኩ"** ይህ ጳውሎስን ሊያሳይ የሚችለው እንደ (1) በንጽሕና ጊዜ እንደ ሆነ ሕፃን፤ ወይም (2) የወንጌል እውነት ልቡን ሰብሮ እስከ ገባ ድረስ እንዳለ የተሰጠ ፈሪሳዊ (ሐዋ. 23፡1፤ ፊሊጵ. 3፡6፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡3)። የመጀመሪያው የሚያቀርበው "የግል ሕይወት ንድፈ-ሐሳብ) ማለትም የምዕራፍ 7 ትርጓሜ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "የተወካይ ንድፈ-ሐሳብ" ማለትም የምዕራፍ 7 ትርጉም ነው።

▣ **"ትዕዛዝ በመጣ ጊዜ፣ ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ"** የሰው ልጅ ዐመጸኛ መንፈስ በተከለከሉ ነገሮች ኃይል ያገኛል። "አታድርግ" የሚለው የእግዚአብሔር ሕግ፣ የወደቀውን ስብዕና የራስ ምሪት ኩራት ቃታውን ይስባል (ዘፍ. 2፡16-17፤ 3፡1-6)። ኃጢአት እንዴት ግላዊ እየሆነ እንደሚሄድ ተመልከት፣ በ5፡21 እና 7፡8፣11፣17፣20 እንዳለው።

7፡10 **"ለሕይወትም የተሰጠችው ትዕዛዝ፣ በእኔ ላይ ለሞት ሆነች"** ይህ ምናልባት የሚያመላክተው የሌዋ. 18፡5 የተስፋ ቃል ወይም ምናልባት ሮሜ 2፡13 ይሆናል። ሕጉ ሊፈጸም የማይችለውን የተስፋ ቃል የሰጠው፣ ኃጢአት ስለሆነ አይደለም፣ ነገር ግን ሰብአዊነት ደካማና ዐመጸኛ ስለሆነ ነው። ሕጉ የሞት ፍርድ ሆነ (ገላ. 3፡13፤ ኤፌ. 2፡15፤ ቆላ. 2፡14)።

7፡11 **"አስቶኛል በእሱም ገድሎኛል"** እነዚህ ሁለቱም የተፈጸሙ የድርጊት አመላካች ግሦች ናቸው። ይህ ቃል፣ አስቷል፣ በሴፕቱአጂንት (LXX) ስለ ሔዋን በዘፍ. 3፡13 ጥቅም ላይ ውሏል። ጳውሎስ ይሄንን ቃል በርካታ ጊዜ ተጠቅሞበታል (ሮሜ. 16፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡3፤ 2ኛ ተሰ.2፡3፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡14)። የአዳምና ሔዋን ሌላው ችግራቸው የሌላ መመኘት ነው (2ኛ ቆሮ. 11፡3፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡14)። አዳምና ሔዋን በመንፈስ የሞቱት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ነው፣ ጳውሎስም እንዳደረገው፣ ሁሉም የሰው ልጆች እንዳደረጉት (1፡18-3፡20)።

7፡12 ይህ ጳውሎስ፣ ሕግ መልካም እንደሆነ ያስረገጠበት ነው። እሱ ችግር አይደለም። ቢሆንም የጳውሎስ ንጽጽራዊ አወቃቀር፣ ማለትም "ኃጢአትን" ምዕራፍ 6 ላይ እንዲሁም "ሕግን" ምዕራፍ 7 ላይ የተጠቀመበት፣ ሕገኛ የአይሁድ አማኞችን ቅር አሰኝቷል (በድክመት 14፡1-15፡13) በሮሜ ቤተ ክርስቲያን።

> 7፡13
> **[13]እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።**

7፡13

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ኃጢአት፣ በዚህም ምክንያት ኃጢአት ይሆን ዘንድ… ኃጢአትም ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ"** |
| **አኪጀት** | **"ኃጢአትም፣ ኃጢአት ሆኖ እንዲገለጥ… ያለልክም ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ"** |
| **አየተመት** | **"ያም ኃጢአት፣ ኃጢአት ሆኖ ይታይ ዘንድ… አለቅጥ ኃጢአተኛ እንዲሆን"** |
| **አእት** | **"በዚህም ምክንያት በትክክለኛው ባሕርዩ፣ እንደ ኃጢአት ይገለጥ ዘንድ"** |
| **ኢመቅ** | **"ኃጢአት፣ ራሱን በትክክለኛው ገጽታው ያሳይ ዘንድ… ሁሉንም ኃጢአተኛ ኃይል መጠቀም ይችል ዘንድ"** |

የኃጢአት እኩይ ተፈጥሮ በግልጽ በሐቅ የሚታየው አንድን ነገር እንደ መልካም፣ እንደ ጥቅል፣ እና እንደ ሙሴ ሕግ መልካምነት በመውሰዱ ነው (መዝ. 19፡119) እንዲሁም እሱኑ ጠምዝዞ ለኵነኔና ለሞት መሣርያ ማድረጉ ነው (ኤፌ. 2፡

15፤ ቆላ. 2:14):: የወደቀው የሰው ልጅ እያንዳንዱን የእግዚአብሔርን ምልካም ስጦታ የወሰደው እግዚአብሔር ከሰጠው ልኬታ ውጭ ነው!
ሁለቱን ሂና (hina) (የተግባር) ሐረጎች አስተውል::

▣ *"አለ ልክ ኃጢአተኛ"* ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ የሁፐር (huper) ድብልቆች አጠቃቀም 1:30 ላይ ተመልከት::

> 7:14-20
> **[14]*ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ::* [15]*የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም::* [16]*የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ::* [17]*እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ::* [18]*በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም::* [19]*የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም::* [20]*የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ::***

7:14 *"ሕጉ መንፈሳዊ ነው"* የእግዚአብሔር ሕግ መልካም ነው:: እሱም ችግር አይደለም (ዝከ. ቁ. 12 እና 16ለ)::

▣ *"እኔ ግን ከሥጋ ነኝ"* ቃሉ በጳውሎስ ጥቅም ላይ የዋለው (1) በአማካኝ እሳቤ ፍች ሥጋዊ አካል (ዝከ. 1:3፤ 2:28፤ 4:1፤ 9:3፣5)፤ እና (2) በአሉታዊ እሳቤ ፍች በአዳም የወደቀ የሰው ልጅ ተፈጥሮ (ዝከ. ቁ. 5):: እዚህ ጋ እንዲጠቀስ የተደረገው ርግጠኛ አይደለም::

▣ *"ለኃጢአት ባርነት የተሸጥኩ"* ይህ የተፈጸመ ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ ፍችው "ለኃጢአት ባርነት የተሸጥኩ፣ እየተሸጥኩም ያለሁ" ማለት ነው:: ኃጢአት እዚህም ሰውኛ ሆኗል፣ እንደ ባሪያ አሳዳሪ:: የተገብሮው ድምጸት አድራጊ አይለይም:: ሰይጣን፣ ኃጢአት፣ ጳውሎስ፣ ወይም እግዚአብሔርን ያመላክት ይሆናል::
በብኪ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ወደ ራሱ የመለሰበት ዋነኛው ቃል "መቤዠት" ወይም "መዋዠት" (እንዲሁም የእነሱ ተመሳሳይ) ነበር:: በዋነኛነት የሚለው "መልሶ መግዛት" (እንዲሁም የሱ ተመሳሳይ ነው:: ልዩ ርዕስ 3:24 ላይ ተመልከት):: ተቃራኒው ጽንሰ-ሐሳብ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ሐረግ ነው፣ "አሳልፎ መሸጥ…" (ዝከ. መሳ. 4:2፤ 10:7፤ 1ኛ ሳሚ. 12:9)::

7:15-24 የእግዚአብሔር ልጅ "መለኮታዊ ተፈጥሮ" አለው (2ኛ ጴጥ. 1:4)፣ ነገር ግን እንዲሁም የወደቀ ተፈጥሮ (ገላ. 5:17):: ሊኖር ከሚችል አቅም አኳያ፣ ኃጢአት እንዳይሠራ ተደርጓል (ሮሜ. 6:6)፣ ነገር ግን የሰው ልምድ ምዕራፍ 7ን ይከተላል:: አይሁዶች፣ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ጥቁርና ነጭ ውሻ አለ ይላሉ:: ደጎና አድርጎ የሚመግበው ትልቅ ይሆናል:: ይህንን ምንባብ ሳነብ ጳውሎስ ሥቃዩን እንደገለጸው በየቀኑ የሚሆነው የሁለቱ ተፈጥሯችን ግጭት፣ እኔም ከሕይወት ልምዴ ተሰምቶኛል:: አማኞች ከወደቀው ተፈጥሯቸው ነጻ ወጥተዋል፤ ነገር ግን ወደ መታለሉ እንዳንቀጥል እግዚአብሔር ይርዳን:: በግልጽ አስገራሚ እውነት የሚሆነው የተጠናከረው መንፈሳዊ ውጊያ የሚጀምረው ከደኅንነት በኋላ ነው:: መብሰል ማለት በውጥረት የተሞላ የየቀኑ ኅብረት ከሥላሴ አንድ አምላክ ጋር ማድረግና በየቀኑ ከክፉው ጋር መዋጋት ነው::

7:16፣20 "በ... ከ... (ቢሆን)" ይህ አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ለጽሑፋዊ ጥቅሙ ነው::

7:18 "በእኔ ምንም መልካም ነገር እንደማይኖርብኝ አውቃለሁ፣ ማለት በሥጋዬ" ጳውሎስ፣ ሥጋዊ አካል ክፉ ነው እያለ አይደለም፣ ነገር ግን የወደቀው ተፈጥሮና የእግዚአብሔር መንፈስ የጦር ሜዳ ነው:: ግሪኮች ደግሞ ሥጋ፣ ከሌሎች ነገሮች ጭምር ክፉ ነው ይላሉ:: ይህም እያደገ ሄዶ ድርብ የሆነ ሃይማኖታዊ ጥርጣሬ– ግኖስጢክ ሊሆን ቻለ (ዝከ. ኤፌሶን፣ ቆላስይስ እና 1ኛ ዮሐንስ):: ግሪኮች ለመንፈሳዊ ችግሮች ሥጋን መውቀስ ያዘወትራሉ:: ጳውሎስ መንፈሳዊውን ውጊያ በዚህ መልኩ አይመለከትም:: እሱ ኃጢአትን ሰውኛ አድርጎ እንዲሁም የሰው ልጅን በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ማመጽ፣ ክፉው ዕድሉን ተጠቅሞ ሰዋዊ ተፈጥሮን እንደ ወረረ ነው፣ የሚገልጸው:: *"ሥጋ"* የሚለው ቃል በጳውሎስ ጽሑፎች ፍቺው ሊሆን የሚችለው (1) ሥጋዊ አካል ከግብረ ገብ አኳያ ገለልተኛ ነው (ዝከ. 1:3፤ 2:28፤ 4:1፤ 9:3፣5)፤ እና (2) ከአዳም የተወረሰው የወደቀው የኃጢአት ተፈጥሮ (ዝከ. ቁ. 5)::

7:20 "በእኔ ላይ የሚኖር ኃጢአት" የሮሜ መልእክት የሰውነትን ኃጢአት በግልጽ ማስቀመጡ የሚያስገርም ሲሆን፣ ነገር ግን ስለ ሰይጣን እስከ 16:20 ድረስ አልተጠቀሰም:: ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ችግር ሰይጣንን ሊወቅሱት አይችሉም:: ምርጫ አለን:: ኃጢአት በሰውኛ ዘይቤ እንደ ንጉሥ፣ ዕምባ ገነን ገዥ፣ እንደ ባሪያ አሳዳሪ ነው:: እሱ ይፈትነናል እንዲሁም ያግባባናል ከእግዚአብሔር እንለይ ዘንድ፣ ወደ ራስ አስተሳሰብ፣ በሆነ ዘዴ:: የጳውሎስ፣ ኃጢአትን ሰዋዊ ዘይቤ መስጠት የሚያያዘው የሰውን ምርጫ ነው፣ ዘፍ. 4:7 እንደ ተንጸባረቀው::

ጳውሎስ “የሚኖረው” የሚለውን ቃል በዚህ ምዕራፍ በርካታ ጊዜ ተጠቅሞበታል (ዝከ. ቁ. 17፣18፣20)፡፡ የኃጢአት ተፈጥሮ በደኅንነት ጊዜ አይጠፋም ወይም አይወገድም፣ ነገር ግን አቅሙ እንዳይሠራ ይሆናል፡፡ ቀጣይ አቅም የለሽነቱ የሚወሰነው በእኛ ካደረብን መንፈስ ጋር በሚኖረን መተባበር ነው (ዝከ. 8፡9፣11)፡፡ እግዚአብሔር፣ ለአማኞች ክፉውን ይቃወሙ ዘንድ፣ ማለትም ሰውኛ (በጥሬ ትርጉሙ) እንዲሁም ሰዋዊ (ሰይጣን እና አጋንንት) አስፈላጊውን ሁሉ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ኃይል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ነጻ የደኅንነት ስጦታ እንደተቀበልን ሁሉ፣ እንዲሁ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን፣ ብቁ ማገጃ (ክፉውን የሚያርቅ) መቀበል ይኖርብናል፡፡ ድኅነትና የክርስትና ሕይወት የየቀኑ ሂደቶች ሲሆኑ የሚጀምሩትና የሚፈጠሙት በአማኞች የየዕለት ውሳኔ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን በሙሉ ሰጥቶናል፡ መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ. 8)፣ መንፈሳዊ የጦር-ዕቃ (ኤፌ. 6፡11)፣ ራዕይ (ኤፌ. 6፡17)፣ እና ጸሎት (ኤፌ. 6፡18፡፡

ውጊያው ኃይለኛ ነው (ሮሜ 7)፣ ነገር ግን ውጊያው ድል ተነሥቷል (ሮሜ 8)፡፡

> 7፡21-25
> **[21]እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ፡፡ [22]በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ [23]ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ፡፡ [24]እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? [25]በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡ እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ፡፡**

**7፡22 “የእግዚአብሔር ሕግ”** ለአይሁድ ይሄ የሚያመላክተው የሙሴን ሕግ ነው፡፡ አይሁድ ላልሆነ ይህ የሚያመለክተው (1) የተፈጥሮ ምስክር (ሮሜ 1፡19-20፤ መዝ. 19፡1-6)፤ (2) ውስጣዊ ግብረ-ገባዊ (የሞራል) ሕሊና (ሮሜ 2፡14-15)፤ እና (3) ማኅበረሰባዊ ልማድ ወይም እሴት፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“በውስጣዊ ሰውነት”** |
| **አኪጀት** | **“እንደ ውስጥ ሰውነት”** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **“በውስጥ ማንነቴ”** |
| **አእት** | **“በውስጡ ሕልውናዬ”** |

ጳውሎስ ውጫዊውን ሰው (ሥጋዊ) ከውስጣዊው ሰው (መንፈሳዊ) ጋር እያነጻጸረ በ2ኛ ቆሮ. 4፡16 ላይ ያቀርበዋል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ ሐረጉ የሚያመለክተው እንዲያ ዓይነቱን ጳውሎስ ወይም የዳነ ሰብእና ሆኖ አጽንዖት የሚሰጠውም የእግዚአብሔርን ፍቃድና ሕግ ነው፡፡

1. “ሕጉ መንፈሳዊ ነው፣” 7፡14
2. “እኔ ለማድረግ የምፈልገው፣ “ 7፡15
3. “ከሕጉ ጋር እስማማለሁ፣ የሕጉን መልካምነት እያጸናሁ፣” 7፡16
4. “ፍላጎቱ በውስጤ ይኖራል፣” 7፡18
5. “መልካሙን እሱም የምሻውን፣) 7፡19
6. “በጣም ክፉውን አደርጋለሁ፣ የማልፈልገውን፣” (7፡19)
7. “ያንን የታሰበበትን አደርጋለሁ፣ የማልፈልገውን፣” 7፡20
8. “መልካምን ለማድረግ የሚፈልግ አንዱ፣” (7፡21
9. “ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር በደስታ እስማማለሁ፣” (7፡22
10. “ከአእምሮዬ ሕግ፣” 7፡23
11. “እኔ ራሴ ከአእምሮዬ ጋር የእግዚአብሔርን ሕግ አገለግላለሁ፣” 7፡25

ምዕራፍ 7 የሚያሳየው የእግዚአብሔርና የቃሉ እውቀታችን በቂ እንዳልሆነ ነው፡፡ አማኞች መንፈሱ ያስፈልጋቸዋል (ምዕራፍ 8)!

**7፡23** በ 6፡2፤ 8፡2 እና 7፡23 መካከል ግልጽ የሆነ ተቃርኖ አለ፡፡ ይህ ቁጥር የሚያሳየው የጳውሎስን የሕግ (ኖሞስ nomos) አጠቃቀም ሲሆን የሚያመለክተውም (1) የኃጢአት ሕግ (ዝከ. ቁ. 21፣25) እና (2) የእግዚአብሔርን ሕግ (ዝከ. ቁ. 22፣25) ነው፡፡ ቀደም ሲል በቁ. 4፣5፣6፣7፣9 እና 12 ጳውሎስ ቃሉን የተጠቀመው ለብኪ ነው፡፡ ጳውሎስ ስልታዊ የሥነ-መለኮት ሰው አልነበረም፡፡ ይሟገት የነበረው ከ “ሕግ” ጽንሰ-ሐሳብ ጋር ነበር፡፡ በአንድ በኩል የእግዚአብሔር መገለጥ ነበር፣ ለሰው ልጆች የተሰጠ አስደናቂ ስጦታ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ የነበረው ኃጢአትን መግለጥ እና ግልጽ የሆኑ ወሰኖችን ማስቀመጥ ነበር፣ ይህም የወደቀው የሰው ልጅ መጠበቅ ያልቻለውን፡፡ እነዚህ ወሰኖች የብኪ ራዕዮች ብቻ አልነበሩም፣ ነገር ግን ሁሉንም ዓይነት የግብረገብ መመሪያዎች ነው፡ የተፈጥሮ ራዕይ (መዝ. 19፤ ሮሜ 1፡18-3፡31) ወይም ማኅበረሰባዊ እሴት ወይም ልማዶችንም ነው፡፡ የሰው ልጆች ያመጹት የራሳቸውን ሕይወት ሙሉ ቁጥጥር እንዲኖራቸው በመፈለጋቸው ነው!

7፡24 ይህ ከዳነ ሰው የሆነ ቃል ነውን? አንዳንዶች፣ አይደለም ይላሉ፣ ስለሆነም ምዕራፉ የሚያመለክተው ግብረ-ገባዊ፣ ሃይማኖታዊ ሆነው ነገር ግን ያልዳኑትን ሰዎች ነው። ሌሎች ደግሞ፣ ነው፣ ይላሉ፣ ስለሆነም እሱ የሚያመለክተው የወንጌልን አከራካሪ ነጥብ ነው፣ "ገና ድሮ እና ገና አሁን" በአማኞች ሕይወት የሆነውንና የሚሆነውን ነው። የመጨረሻው ግብ መዳረሻ አሁን ገና ፍጻሜው አልተገለጠም። የበሰሉ አማኞች ይሄንን አስቸጋሪ ልዩነት በሚገባ ያጤኑታል።

▣

**አአመመቅ** **"የዚህ የሞት ሥጋ"**
**አኪጀት፣ አየተመት** **"ይሄ የሞት ሥጋ"**
**አእት** **"ይሄ ወደ ሞት የሚወስደኝ ሥጋ"**
**አኢመቅ** **"ለዚህ ለሞት ለተሰጠ ሥጋ"**

ሥጋዊ አካልና አእምሮ በውስጣቸውም ሆነ በራሳቸው ክፉ አይደሉም። እነሱ በእግዚአብሔር የተፈጠሩት በምድራችን ላይ ላለ ሕይወትና ከእሱ ጋር ለሆነ ኅብረት ነው። እነሱ የተፈጠሩት "በጣም መልካም" ሆነው ነው (ዘፍ. 1፡31)። ነገር ግን፣ ዘፍጥረት 3 የሰው ልጆችን ቀይሮ የእግዚአብሔርን ድርጊት ለወጠ። ይህ ዓለም፣ እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው አይደለም፤ እኛም፣ እግዚአብሔር እንድንሆን የፈለገው ሕዝብ አይደለንም። ኃጢአት ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ተፈጥሮን ጎድቶታል። ኃጢአት መልካም የሆነውን ወስዶ ወደ ግለኝነት ክፋት ጠምዝዞታል። ሥጋና አእምሮ የፈተናና የኃጢአት የጦር ሜዳ ሆነዋል። ጳውሎስ ውጊያውን በሚገባ ይረዳዋል! እሱ አዲሱን ዘመን፣ አዲሱን አካል፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ አዲሱን ኅብረት ይናፍቃል (ዝከ. 8፡23)።

7፡25 ይህ ጭምቅ-ሐሳብና የሮሜ 8 ላዕላይ ስፍራ መሸጋገሪያ ነው። ሆኖም፣ በምዕራፍ 8 እንኳ ቢሆን ይሄው የሐሳብ ፍጭት የሚታየው ቁ. 5-11 ላይ ነው።
በተርጓሚዎች የሚነሣው ጥያቄ የሚሽከረከረው፣ ጳውሎስ ስለ ማን እየተናገረ ነው? የሚል ነው።

1. ራሱንና በይሁዲነት ስለነበረው ልምድ
2. ሁሉንም ክርስቲያኖች
3. አዳም እንደ ሰው ልጆች አንድ ምሳሌ
4. እስራኤልና የሕግ እውቀቷ፣ ዳሩግን ለመፈጸም አለመቻሏ

በግሌ ከቁጥር 1 ላይ ነኝ (ቁ. 7-13፣25ለ) እና ቁ. 2 (ቁ. 14-25ሀ)። ሮሜ 7፡7-25 ያለውን ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት። ምዕራፍ 7 የሚገኘው ሥቃይና መከራ ከምዕራፍ 8 ግርማ ጋር ይገጣጠማል፣ ይበልጣልም!

▣ **"ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን"** የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ ምስጋና፣ ጸሎት፣ እና ውዳሴ ለእግዚአብሔር**

ጳውሎስ የምስጋና ሰው ነው። ብሉይ ኪዳንን ያውቃል። እያንዳንዱን የመጀመሪያዎቹን አራት ክፍሎች (ማለትም፣ መጻሕፍቱን) መዝሙራትና ተያያዦችን ከውዳሴዎች ጋር ያውቃቸዋል (መዝ. 41፡13፤ 72፡19፤ 89፡52፤ 106፡48)። እሱ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ያከብራልም፣ በተለያዩ በርካታ መንገዶች።

1. በመልክቶቹ የመክፈቻ አንቀጾች ላይ
   ሀ. የመክፈቻ ቡራኬ ወይም ሰላምታ (ሮሜ. 1፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡3፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡2)
   ለ. የመክፈቻ ባርኮት (ኢዩሎጂቶስ eulogētos፣ 2ኛ ቆሮ. 1፡3-4፤ ኤፌ. 1፡3-14)
2. አጭር ድንገቴ ምስጋናዎች
   ሀ. ሮሜ 1፡25፤ 9፡5
   ለ. 2ኛ ቆሮ. 11፡31
3. ውዳሴዎች (በባሕርያቸው (1) መወድስ (ማለትም፣ ምስጋና) እና (2) "ከዘላለም እስከ ዘላለም" የሚሉትን መጠቀም፤
   ሀ. ሮሜ 11፡36፤ 16፡25-27
   ለ. ኤፌ. 3፡20-21
   ሐ. ፊሊጵ. 4፡20
   መ. 1ኛ ጢሞ. 1፡17
   ሠ. 2ኛ ጢሞ. 4፡18
4. ምስጋና (ያም ማለት፣ ኢዩቻሪስቲዮ eucharisteō)
   ሀ. የመልእክት መክፈቻዎች (ሮሜ 1፡8፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡4፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡11፤ ኤፌ. 1፡16፤ ፊሊጵ. 1፡3፣12፤ 1ኛ ተሰ. 1፡2፤ 2ኛ ተሰ. 1፡3፤ ፊሊሞና ቁ. 4፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡12፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡3)
   ለ. የምስጋና ጥሪ (ኤፌ. 5፡4፣20፤ ፊሊጵ. 4፡6፤ ቆላ. 3፡15፣17፤ 4፡2፤ 1ኛ ተሰ. 5፡18)
5. አጭር ድንገቴ ውዳሴዎች

ሀ. ሮሜ 6፡17፤ 7፡25
ለ. 1ኛ ቆሮ. 15፡57
ሐ. 2ኛ ቆሮ. 2፡14፤ 8፡16፤ 9፡15
መ. 1ኛ ተሰ. 2፡13
ሠ. 2ኛ ተሰ. 2፡13

6. የመዝጊያ ቡራኬ
ሀ. ሮሜ 16፡20፣24 (?)
ለ. 1ኛ ቆሮ. 16፡23-24
ሐ. 2ኛ ቆሮ. 13፡14
መ. ገላ. 6፡18
ሠ. ኤፌ. 6፡24

ጳውሎስ ሥላሴ አንድ አምላክን ከሥነ-መለኮትም ሆነ ከሕይወት ልምድ ያውቃል። ጽሑፎቹን የሚጀምረው በጸሎትና በምስጋና ነው። በገለጻው መካከልም ድንገቴ ምስጋናና ውዳሴውን ያቀርባል። በመልእክቶቹ መደምደሚያ ላይ፣ የሚያስታውሰው መጸለይ፣ ማወደስና እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። የጳውሎስ ጽሑፎች ሽታቸው ጸሎት፣ ምስጋናና ውዳሴ ነው። እግዚአብሔርን ያውቃል፣ ራሱን ያውቃል፣ ወንጌልንም ያውቃል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ምዕራፍ 6 ከምዕራፍ 7 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
2. የብሉይ ኪዳኑ ሕግ ከአዲስ ኪዳን አማኞች ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? (2ኛ ቆሮ. 3፡1-11፤ ዕብ. 8፡7፣ 13)
3. የእኛንና የአሮጌውን ሕይወታችንን ለማብራራት ጳውሎስ በምዕራፍ 6 እና 7 ላይ የተጠቀመባቸው ሁለት መግለጫዎች እነማን ናቸው?
4. ሮሜ 7፡7-25ን ለመተርጎም በግለ ታሪክና በውክልና ንድፈ-ሐሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት በራስህ ቃል ግለጽ።
5. ሮሜ 7 የሚገልጸው የጠፋ ሰውን፣ ያልበሰለ ክርስቲያንን ወይስ ሁሉንም አማኞች?

# ሮሜ 8

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በመንፈስ ያለ ሕይወት | ከኃጢአት ማደሪያነት ነጻ መሆን | የእግዚአብሔር የማዳኑ ሥራ | በመንፈስ ያለ ሕይወት | መንፈሳዊ ሕይወት |
| 8: 1-11 | 8: 1-11 | 8: 1-4 | 8:1-8 | 8: 1-4 |
| | | በሥጋ እና በመንፈስ ያለ ሕይወት | | |
| | | 8:5-8 | | 8:5-11 |
| | | 8:9-11 | 8:9-11 | |
| | | መንፈስ እና ልጅነት | | |
| 8:12-17 | 8:12-17 | 8:12-17 | 8:12-17 | 8:12-13 |
| | | | | የእግዚአብሔር ልጆች |
| | | | | 8:14-17 |
| የሚሆነው ክብር | | | | |
| 8:18-25 | | | | |
| 8:26-30 | | | | |
| | የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር | በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ያለን መመካት | የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ ኢየሱስ | ለእግዚአብሔር ፍቅር ዝማሬ |
| | 8:31-39 | 8:31-39 | 8:31-39 | 8:31-34 |
| | | | | 8:35-37 |
| | | | | 8:38-39 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መኀዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሲገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

**ጽሑፋዊ ይዘት**

ሀ. ይህ ምዕራፍ የጳውሎስ የክርክር ነጥብ ከፍተኛ ጡዘት ላይ የደረሰበት ሲሆን ከ1፡8 ይጀምራል። እሱም፣ "ኵነኔ የለባቸውም" (ከሕግ አኳያ) ይልና "ልዩነት የለም" (በግል በሚደረግ ኀብረት) በማለት ያጠቃልላል። ከሥነ መለኮት አንጻር፣ ከቅድስና ከሆነ ፍጽምና ወደ ክብር-መቀዳጀት ይዘልቃል (ቁጥር 29-30)።

ለ. ይህ ደግሞ የጳውሎስ ሥነ መለኮታዊ እድገት፣ ማለትም እግዚአብሔር መንፈሱን ለአማኞች መስጠቱን የሚያሳይ ነው። (የዮሐንስ አቀራረብ በዮሐንስ 14፡12-31፤ 16፡7-16) መንፈስ የሚለው ቃል በቁ.14 በተደራጊ ግሥ የቀረበ ሲሆን የዛም ግንኙነት ወንጌል በወደቁት የሰው ልጆች ሕይወት ላይ እንደሚሠራ ያመላክታል። መንፈስ ከእነርሱ ጋር እና በእነሱ ውስጥ አድሮ ክርስቶስን በውስጣቸው መቅረጽ ይጀምራል። ምዕራፍ 8 ውስጥ መንፈስ የሚለውን ቃል 21 ጊዜ ሲጠቀም፣ በምዕራፍ 7 ግን ሙሉ ለሙሉ አስቀርቶ፣ (እንዲሁም ከምዕራፍ 3-6 ሳይጠቀም፣ በምዕራፍ 1-2 ሦስት ጊዜ ጠቅሷል)።

ሐ. በሕይወት ጊዜ ሁለት አመለካከቶች አሉ (ግላዊ የዓለም አተያዮች)፣ ሁለት የኑሮ ስልቶች፣ ሁለት ቀዳሚ ነገሮች፣ ሁለት መንገዶች (ሰፊው መንገድና ጠባቡ መንገድ)፣ ያም ማለት የሰው ልጆች የሚከተሉት፣ የሥጋ ወይም የመንፈስ። አንደኛው ወደ ሞት ሲያመራ ሌለኛው ወደ ሕይወት። ይህም በተለምዶ፣ "ሁለቱ መንገዶች" ተብሎ ሲጠራ፣ በብሉይ ኪዳን ጥበበ-መጻሕፍት (መዝ.1 እና ምሳ.4፡10-19።) የዘላለም ሕይወት፣ መንፈሳዊ ሕይወት ሊስተዋሉ የሚችሉ ባሕርያት አሉት– (ያም ማለት ወይም ሥጋን ተከትሎ፣ወይም መንፈስን ተከትሎ)።

ያስተውሉ፣ በዚህ ሥነ-መለኮታዊ ጽሑፍ በሙሉ፣ (ሮሜ 1-8) ሰይጣን በግልጽ አልተጠቀሰም። እሱም በሮሜ 16፡20 ድረስ አልተጠቀሰም። ትኩረት የተሰጠው የወደቀው የሰው ልጆች አዳማዊ ተፈጥሮ ነው። ይህም የጳውሎስን ዘዴ ማለትም የወደቁትን የሰው ልጆችን ሰበብ ለማስቀረት፣ ማለትም፣ ("ሰይጣን ነው እንዲህ እንድሠራ ያደረገኝ" የሚሉትን፣ በእግዚአብሔር ላይ ለማመፃቸው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይልን እንደተፈታታኝ አድርገው የሚያቀርቡትን። <u>የሰው ልጅ</u> ኃላፊነቱን ይወስዳል።

መ. ይህን ምዕራፍ በየፈርጁ ለማስቀመጥ ከበድ ይላል፤ ምክንያቱም ሐሳቡ እየተደራጀ የመጣው በርካታ የእውነት ሐረጎችን አንድ ላይ በመጠመር እና ፈርጆችን በማበጀት ሆኖ ካጠቃላይ የጽሑፉ አህዶች ያልተያያዘ በመሆኑ ነው።

ሠ. ቁጥር 12-17 ለአማኙ የሚያስረዳው ስለ ጽኑ እምነት ዋስትና ነው።
1. የመጀመሪያው በመንፈስ የምንቀዳጀውን የተለወጠ የዓለም አመለካከትና የአኗኗር ስልት ነው።
2. ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔርን መፍራታችን በመንፈስ ወደ ቤተሰባዊ ፍቅርና ስሜት መቀየሩን ነው።
3. ሦስተኛው ባደረብን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን ያለውን የልጅነት መብት ስላረጋገጥን ነው።
4. አራተኛው ደግሞ ይሄው ማረጋገጫ በዚህ በወደቀው ዓለም ችግሮችና ውጣ ውረዶች መሐል እንኳ ርግጥ መሆኑ ነው።

ረ. ቁጥር 31-39 የፍርድ ቤት ትዕይንት የሚያሳዩ ሆነው በብሉይ ኪዳን ነቢያት የታወቀ ያጻጻፍ ዘዴ ነው። እግዚአብሔር ዳኛ ነው፤ ሰይጣንም ከሳሽ ነው፤ ኢየሱስ ተከላካይ ጠበቃ፣ መላእክት ተመልካቾች፣ እንዲሁም አማኝ የሆነው ስብዕና በሰይጣን ክስ ሥር ነው።
1. በሕግ አነጋገር
   ሀ. እኛን ተቃርኖ (ቁ.31)
   ለ. ክሱ (ቁ. 33)
   ሐ. የአሳማኝነት (ቁ. 33)
   መ. የጥፋተኝነት (ቁ. 34)
   ሠ. ምልጃ (ቁ. 34)
2. የክሱ ዝርዝር "ማን" (ቁ. 31፣ 33፣ 34 [ሦስት ጊዜ]፣ 35)

3. የእግዚአብሔር እርዳታ በክርስቶስ (ቁ. 32፣ 34ለ
4. ከእግዚአብሔር አይለያይም
   ሀ. ምድራዊ ሁኔታዎች (ቁ. 35)
   ለ. ብሉይ ኪዳን ከመዝሙራት የተጠቀሰ፣ መዝ. 44፡22 (ቁ.36)
   ሐ. ድል (ቁ. 37፣ 39)
   መ. ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ኃይላት (ቁ. 37-39)

**የቃሉና የሐረጎች ጥናት**

8፡ 1-8
**[1]እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። [2]በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውየሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞትሕግ አርነት አውጥቶኛልና። [3]ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ [4]እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በባንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። [5]እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ።ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። [6]ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ [7]ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ [8]በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።**

8.1

| | |
|---|---|
| **አዲሱ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ** | **"ስለሆነም እንግዲህ አሁን"** |
| **አዲሱ ኪንግ ጀምስ እትም** | **"እንግዲህ ስለሆነም አሁን"** |
| **ቲ ኢ ቪ** | **"እንግዲህ"** |
| **አ መ ቅ** | **"ምክንያቱም እንግዲህ"** |

ይህ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ጽሑፍ የሚያጎዳኝ ነው። አንዳንዱም የሚያጎዳኘው ከ7፡24-25 ሆኖ ዳሩ ግን ወደ ኋላ መለስ ብሎ ከ3፡21-7፡25 እንደሆነ ይመስላል።

▣ **"የለም"** "የለም" በመጀመሪያ በግሪክ ዓረፍተ ነገር ነው። አጽንዖት የሚሰጥ ሆኖ፣ "ኵነኔ የለባቸውም" በክርስቶስ ላሉት (ቁ. 1-3)፣ እናም እንደ መንፈስ ለሚመላለሱ (ቁ. 4-11)። እዚህ በሁለቱም በኩል ያለውን አዲሱን ኪዳን ያሳያል። (1) ይህም በክርስቶስ ነጻ ስጦታ እንደሆነ፣ እና (2) የአኗኗር ስልት የሆነ ቃል ኪዳናዊ ምላሽ ይጠይቃል። ጽድቅ፣ ሁለቱንም ተጨባጭ (አመላካቹንና)፣ ተያያዥ (አስፈላጊውን) ማለት ነው። ሊሆን የሚገባውንና ያኗኗር ስልቱን ማለት ነው።

▣ **"መኮነን"** ይሄ ቃል ካታክሪማ ባመዛኙ በሴፕቱዋጂንት አይጠቀስም፤ ግን ዳሩግን በዘዳግም 27፡ 26 ያለውን የሕግ መጣስን የርግማን ቃል ያጣቅሳል። ይህ ማለት "ከፍርድ ውሳኔ በኋላ የሚከተለውን ቅጣት ማለት ነው።" ይህም የሕጋዊው አግባብ፣ የጽድቅ ተቃራኒ ነው። በጳውሎስ መልዕክቶች ያልተዘወተረ ነው። (5፡16፣ 18) በሌላም በአዲስ ትርጉም አይገኝም።

የኪንግ ጀምስ ትርጉም በቁጥር 1 ላይ "ሥጋን ተከትለው ሳይሆን መንፈስን ተከትለው በሚሄዱ" የሚል ይጨምራል። ይህም ሐረግ በብዙ ጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎች በቁጥር ላይ አይገኝም። ዩቢኤስ4 "ኤ" ን ያስቀረዋል (በርግጠኝነት) ። በቁጥር 4 ላይ አለ። ከሥነ መለኮት አንጻር በቁ.1 ላይ ተገቢነት የለውም። ዳሩግን ቁ. 4 በትክክል ይስማማዋል። ቁጥር 1-3 የሚያስረዱት ደረጃዊ ቅድስናን (አመላካች) ነው፤ ቁጥር 4-11 ደግሞ ባንጻሩ ተግባራዊ የሆነውን ቅድስና ወይም ክርስቶስን መምሰል ያሳያሉ። የዊሊየም አር. ኒዌልን ሮሜ ቁጥር በቁጥር (ሞዲ 1938) ከገጽ 289 ያለውን የግርጌ ማስታወሻ ተመልከት።

"አዲሱ ትርጉም በትክክል እንዳስቀረው፣ "እንደ ሥጋ ፍቃድ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ" የሚለውን። የኪንግ ጀምስ ትርጉም ከ300 ዓመት በላይ የነበረና፣ በርካታና ምርጥ እንዲሁም ትክክለኛ ጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎችን የደረሱንን፣ የተመዘገቡትን ያካተተ ነው። ልባዊና መልካም ሰዎች ቀደም ብለው በጣም አድካሚ ነገር ግን ፍሬአማ የሆነውን ሥራ እያከናወኑ፣ በሚቀዱበት ጊዜ የተፈጠሩትን ስህተቶች አርመዋል። ሁላችንም እንደምናውቀው፣ ዋነኛው የቅዱስ መጻሕፍት ጽሑፎች የሉንም፤ እግዚአብሔር ይህን ነገር ከፍጥረታት ሸሽጎ መያዙ አስደስቶታልና፣ የሰው ልጆችን አምልኮተኝነት ስለሚያውቀው።

ቁጥር 1ን "በክርስቶስ ኢየሱስ፣" በሚሉት ቃላት መዝጋት ያለብን በአራት ምክንያቶች ነው፦ (1) የግሪክ ጽሑፎች ማስረጃነት በብዛት የሚሉት፣ "ሥጋን ተከትለው ሳይሆን መንፈስን ተከትለው የሚሄዱ" የሚለውን ሐረግ ከቁጥር 1 ላይ እንዲቀር ነው። እንደ ማስረጃም በአጠቃላይ እነዚህም ቃላት ጨምሮ በቁጥር 4 መታከላቸው ነው። (2) መንፈሳዊ መለያዎችም በዚህ ይስማማሉ። በቁጥር 1 ላይ ያለው የእነዚህ ቃላት መግቢያ ደኅንነታችን የሚወሰነው በአካሄዳችን እንጂ በእግዚአብሔር መንፈስ አለመሆኑን ያሳያል። ነገር ግን ሁሉም በክርስቶስ ኢየሱስ ከኵነኔ ይድናሉ፣ በሚል በመልዕክቶች ሁሉ በግልጽ እንደሚያስተምረው። አለበለዚያማ ደኅንነታችን የሚወሰነው በአካሄዳችን እንጂ በክርስቶስ ባለን አቋም አይደለም ማለት ነው። (3) ሐረጉ በግልጽ በትክክለኛው ቦታ ላይ በቁጥር 4 መጨረሻ ላይ አለ– በዚያም

የአማኝ የአካሄድ ሁኔታ ከኩነኔ የተነሣ  ደኅንነቱ እንደማይሆን ተገልጿል። (4) ያው ከቁጥር 1 መጨረሻ ያለው ሐረግ፣ በኪንግ ጀምስ የተመለከተው (በአንዳንድ ቅጅዎች ያለው የግርጌ ማስታወሻ) የሚያሳየው፣ በዋነኞቹ ጽሑፎች ላይም መቅረቱን ብቻ አይደለም፣ አሌፍ፣ ኤ፣ ቢ፣ ሲ፣ ዲ፣ ኤፍ፣ ጂ፤ ኤ፣ ዲ፤ የተሻሉ ቅጥልጣይ የእጅ ጽሑፎች እና ጥንታዊ ጽሑፎች (Olshausen, Meyer, Alford, J.F. እና B., የDarby ግሩም ማብራሪያ በዋና ሐሳብ ጽሑፉ ተመልከቱ።) ነገር ግን እንደገና ከጽሑፉ ተመሳሳይነት አኳያ ከሕግ ፍራቻ የተጨመሩ በሌሎቹ አንቀጾችም ይገኛሉ።

እግዚአብሔር ፍቃዱ ሆኖ በዚህ መልክ እንዲተረጎምና በሥልጣን እንዲሆን ማድረጉን በአዲስ ኪዳን የግሪክ ትርጒም እና በዕብራውያን ብሉይ ኪዳን፣ ሴፕቱዋጂንት ተመልክቷል።

ስለ እነዛ ትጉሃን ሰዎች እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፣ የሕይወት ዘመናቸውን እግዚአብሔር የሰጠንን ቃሉን በማሰናዳት በአስደናቂነት እና በፍጽምና ትርጒሞችን ለእኛ ስለተውልን። እነዚህን ሊቃውንት በፍጹምነትና በዘላለማዊነት፣ "ዘመናዊ" ነን ከሚሉት ለይተን ልናያቸው ይገባል። (ወይም ደግሞ በቀድሞ ጊዜ፣ "ታላላቅ ተንታኞች" እንደሚባለው) እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ያለውን በመተው በአጉል ጥልቅ ምርምር የተጠመዱትን" (ገጽ 289)።

▣ **"በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት"** ይህ ባሕርያዊ የሆነ ሐረግ (ማለትም ድርጊቱ በግሥ የሚገለጥበት) የጳውሎስ አጻጻፍ "ግላዊ ግንኙነት" ከሚለው ዘመናዊ አገላለጽ ጋር አቻ ነው። ጳውሎስ ኢየሱስን አውቋል፣ ወድዷል፣ አገልግሏል እናም ደስ ተሰኝቷል። ወንጌል ሊታመን የሚገባው መልእክት እና እንኳን ደኅና መጣህ የሚባል ነው። በደማስቆ መንገድ ላይ ያገኘው ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ጋር ያደረገው ኅብረት የመኖር ኃይል አስገኝቶለታል። ከኢየሱስ ጋር ያሳለፈው ሕይወቱ የኢየሱስን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት አስገኝቶለታል። የሕይወት ልምዱም የተገኘው በተዘጋ ምሥጢራዊነት ሳይሆን መራር በሆነ ሐዋርያዊ አገልግሎት ነው። እሱን ማወቅ ማለት ማገልገል ማለት ነው። የበሰለ ክርስትናኑ መልእክት፣ ሥጋዌ (ክርስቶስ)፣ እና የአኗኗር ሥርዓት ነው (በ1፡5 ያለውን ማስታወሻ እይ)።

**8.2 "የሕይወት መንፈስ ሕግ… የኃጢአት ሕግና የሞት"** ይህ ሊጠቅስ የሚችለው፡ (1) በኃጢአት ሕግ (ሮሜ 7፡10፣ 23፣ 25) እና አዲሱን የእግዚአብሔርን ሕግ (ሮሜ 7፡6፣ 22፣ 25) ተቃርኖ ነው። (2) "የፍቅር ሕግ" (ያዕቆብ 1፡25፤ 2፡8፣ 12) ቁጥሮች፤ "የተቀረጹ ሕጎች" (7፡6-12)፤ (3) የአሮጌው ዘመንና የአዲሱ ዘመን ትይዩነት፤ ወይም (4) የአሮጌው ኪዳንና የአዲሱ ኪዳን ትይዩነት (ኤር. 31፡31-34፤ የአዲስ ኪዳን የዕብራውያን መጽሐፍ።)

ይህ ተቃርናዊ አገባብ የተራመደው

1. በክርስቶስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ መካከልና በኃጢአትና በሞት ሕግ፣ ቁ.2
2. በእንደ ሥጋ ፍቃድ መካከልና እንደ መንፈስ ፍቃድ ቁ.4 እና 5
3. የሥጋ ነገሮች መካከልና በመንፈስ ነገሮች፣ ቁ. 5
4. በሥጋዊ ነገሮች ላይ በተጠመደ ሐሳብ መካከልና በመንፈሳዊ ነገሮች በተያዘ ሐሳብ
5. በሥጋ በተጠመደ ሐሳብ መካከልና በመንፈስ ሐሳብ፣ ቁ. 6
6. በሥጋ እና በመንፈስ መካከል፣ ቁ. 9
7. በሥጋ ሞት እና በመንፈስ ሕይወት፣ ቁ.10
8. መሞት አለብህ እና በሕይወት ትኖራለህ፣ ቁ.13
9. የባርነት መንፈስ ሳይሆን እና በልጅነት መንፈስ፣ ቁ.15

▣

| | |
|---|---|
| **አዲሱ የአሜሪካን መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲሱ የተከለሰው ትርጒም፣መጽሐፍ ቅዱስ** | **"ነጻ አውጥቷችኋል"** |
| **አዲሱ ኪንግ ጀምስ ትርጒም፣ አእቅ** | **"ነጻ አውጥቶኛል"** |

ቁጥር 2-3 የምዕራፍ 6 ሥነ-መለኮታዊ መልእክቶች ናቸው። በርካታ የተለያዩ ተውላጠ ስሞች በጥንታዊው የግሪክ ጽሑፎች ይገኛሉ፤ "እኔ" በኤ፣ ዲ፣ ኬ፣ እና ፒ ጽሑፎች ሲገኙ፣ "አንተ" ደግሞ በ ξ(?)፣ B፣ F እና G ይገኛል። "እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም ደግሞ ወደ ኋላ በእጅ ጽሑፍ፣ Ψ ይገኛል።   መጽ.ቅ[4] አዘጋጆች "አንተ" "B" ደረጃ ይሰጡታል። (ወደ ርግጠኝነት የተጠጋ) መጽ.ቅ[4] "D" (በጣም ችግር ያለው)

ኒውማንና ኒዳ፣ በጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክት የተርጒማን ማስታወሻቸው ላይ ፣ "በUBS የግሪኩ ጽሑፍ "እኔ" የሚለው የተሰጠው ደረጃ "ሐ" የሰጡበት ውሳኔ የሚያመለክተው ከዋናው ምንባብ ከፍተኛ የጥርጥር ቅርርቦሽ እንዳለው ነው" ብለዋል። (ገጽ 145-146)

ይህም "እኛ"፣ "እናንተ"፣ "እኔ"/ "እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም ያገባብ ችግር በመደጋገም በግሪኩ ቅጂ በጳውሎስ ጽሑፍ ላይ ይገኛል።

**8.3 "ለሕግ ሥራ ያልተቻለውን"** የተቀረጸው (የሙሴ) ሕግ መልካምና ቅዱስ ነው፤ ነገር ግን ከስብእና ድካምና በኃጢአት የተሞላ ከመሆን የተነሣ፣ (7፡12፣ 16)። እዚህጋ ያለው ቅጽል በርግጥ ለማለት የፈለገው "አይቻልም" ነው፤ (ዕብራ. 6፡4፣ 18፤ 10፡4፤ 11፡6)፣ ዳሩግን "አለመቻል" ሊሆን ይችላል፣ (ሐዋ. 14፡8፤ ሮሜ 15፡1)። ሕጉ ነጻ ማውጣት አልተቻለውም። በተጻራሪው ኵነኔን፣ ሞትና ርግማንን ያመጣል!

▣ **"ከሥጋ ድካም የተነሣ"** ይህ በምዕራፍ 7 የጳውሎስ መሠረታዊ የክርክር ነጥብ ነው። የእግዚአብሔር ሕግ መልካም፣ ቅዱስ ነው፤ ዳሩግን ኃጢአተኛው፣ የወደቀው ዐመጸኛው የሰው ልጅ መስፈርቶቹን ሊያሟላ አልቻለም። ጳውሎስ ከአይሁድ መምህራን በተለየ መልኩ ለዘፍጥረት 3 ውጤት ልዩ ትኩረት ሰጥቷል።

▣ **"እግዚአብሔር ያደረገው፡ የራሱን ልጅ መላክ"** በአሮጌው ኪዳን ሥር የወደቀው የሰው ልጅ ማድረግ ያልተቻለውን፣ እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን አድርጎታልና። (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝቅ. 36፡22-36) ይህም በኢየሱስ በኩል ነው። (ኢሳ. 53፤ ዮሐ.3፡16) ከውጫዊ ሁኔታዎች ምትክ እግዚአብሔር ውስጣዊ መንፈስና አዲስ ልቦና ሰጥቷልና። ይህም አዲስ ኪዳን የተመሠረተው በሰው ልጆች ድርጊት ሳይሆን በንስሐና ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ በማመን ነው። ያም ቢሆንም ሁለቱም ኪዳናት እግዚአብሔርን የመምሰል አዲስ የአኗኗር ሕይወት ይሻሉ።

▣ **"እንደ ኃጢአተኛ ሥጋ ዓይነት"** ይሄም ተመሳሳይ እውነት በፊሊጵ. 2፡7-8 ተመልክቷል። ኢየሱስ በትክክል የሰው አካል ለብሷል (ነገር ግን ከኃጢአት ያይደለ፣ ፊሊጵ. 2፡7-8፤ ዕብራ. 7፡26፡) እሱ በርግጥ ከእኛ ጋር ነው። በብዙ መልኩ የተፈተነ ነው– አሁን እንደ እኛ ያለ ኃጢአት እንደሆንነው ማለት ነው። (ዕብራ. 4፡15)። ይረዳናል።

▣ **"ለኃጢአት መሥዋዕት እንደሆነ"** ይህ ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ በ2ኛ ቆሮ. 5፡21 እና በ1ኛ ጴጥ. 2፡24 ተመልክቷል። ኢየሱስ የመጣው ሊሞት ነው (ኢሳ. 53፡4-6፣ 10-12፤ ማር.10፡45) የኢየሱስ ፍጹምና (ያለነውር) የሆነ ሕይወት ለኃጢአት መሥዋዕት ሆነ (ዮሐ. 1፡29)።

▣ **"እሱም ኃጢአትን በሥጋ ኮነነ"** የኢየሱስ ሞት የሆነው ለሰው ልጆች የኃጢአት ተፈጥሮ ነው እንጂ (በሙሴ ሕግ እንዳለው) የእያንዳንዱን ሰው የኃጢአት ድርጊት በተመለከተ አይደለም። ይህም ሕይወቱን፣ ሞቱን እና ትንሣኤውን ብሎም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ የማዳኑን ሥራ ያሳያል። (ሐዋ. 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29) እሱም ደግሞ የሰው ልጆች ምን መሆን እንደሚችሉና መሆን እንዳለባቸው አሳይቶናል። (ዮሐ. 13፡15፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡21)

8፡4 ይህ ቁጥር ምናልባት የሚያመለክተው አዲሱን ኪዳን ነው። (ኤር. 31፡ 33 እና ሕዝቅ. 36፡26-27) እሱም የመዳናችንን ሁለት ገጽታ ያሳያል። የመጀመሪያው፣ ኢየሱስ ያሮጌውን ኪዳን መስፈርቶች ማሟላቱን እና በእሱ ላይ ያለ እምነትም ከሰው ሥራ በተለየ መልኩ ነጻ ስጦታ ሆኖ ጽድቁ ወደ አማኞች መተላለፉ ነው። ይህንንም፣ መጽደቅ ወይም የመቀደስ አቋም ብለን እንጠራዋለን። እግዚአብሔር ለአማኞች አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ይሰጣቸዋል። አሁን በመንፈስ ነው የምንራመደው፣ በሥጋ ሳይሆን። ይህም "የቅድስና እድገት" ተብሎ ይጠራል። ክርስትና አዲስ ኪዳን ሆኖ ሁለቱም መብቶች፣ (የመዳን ጸጋ) እና ኃላፊነት (ክርስቶስን የመምሰል፣ 6፡13) ያለው ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን አንዳንድ አማኞች ሥራዊና ተገቢ ያልሆነ ሕይወት ይኖራሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡1-3)።

▣**"እንደ ሥጋ ፍቃድ በማይራመዱ፣ እንደ መንፈስ ፍቃድ እንጂ"** ይህ ተመሳሳይ ተቃርኖ የሚገኘው በገላ. 5፡16-25 ነው። በፍርድ የተገኘ ጽድቅ በሕይወት የአኗኗር ሥርዓት በሆነ ጽድቅ መታጀብ ይኖርበታል። በአዲስ ኪዳን የተገኘው አዲስ ልብና አስተሳሰብ የደኅንነታችን መሠረት ሳይሆን ውጤት ነው። የዘላለም ሕይወት ሊስተዋል የሚችል ባሕርያት አሉት!

8.5 ጳውሎስ "በሥጋ" ያለ ሕይወትንና "በመንፈስ" ያለን በተቃርኖ አስቀምጦታል። በቁ. 5-8 ("የሥጋ ተግባራትን፣" ገላ. 5፡19-21 "ከመንፈስ ፍሬዎች ጋር፣" 5፡22-25)

8.6 **"አስተሳሰብ የተያዘው"** አይሁዶች ዓይንና ጆሮን ወደ ነፍስ ማስገቢያ መስኮቶች አድርገው ይወስዳሉ። ኃጢአት የሚጀምረው በሐሳብ ሕይወት ነው። የምንኖርበትን ሆነን እንገኛለን። (ሮሜ. 12፡1-2፤ ፊሊጵ. 4፡8)!
ጳውሎስ ባህላዊ የሆኑትን ራቢያዊ አስተምህሮቶች ማለትም የሰው ልጅ "ፍቃዶች" አልተከተለም። ለጳውሎስ መልካም ፍቃድ ማለት በወደቀው ሰው የማይገኘውንና በመለወጥ የሆነውን ነው። ለጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ማደር ነው ውስጣዊውን መንፈሳዊ ነውጥ የሚጀምረው (ዮሐ. 16፡7-14)።

▣ **"ሕይወት"** ይህ የሚያመለክተው የዘላለምን ሕይወት፣ የአዲስ ዘመን ሕይወትን ነው።

▣ **"ሰላም"** ይህ ቃል በመጀመሪያ የሚለው "የተሰበረውን መልሶ መጠገንን ነው።" (ዮሐ. 14፡27፤ 16፡33፤ ፊሊጵ. 4፡7) ልዩውን ርዕስ ተመልከት፣ ሰላም በ5፡1። በብሉይ ኪዳን የሰላም መግለጫ መንገዶች አሉ፦

1. በክርስቶስ ያለን ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ተጨባጭ የእውነት ሰላማችን፣ (ቆላ. 1፡20)
2. ከእግዚአብሔር ጋር ስለመሆናችን የእኛ ተያያዥ ስሜት (ዮሐ. 14፡27፤ 16፡33፤ ፊሊጵ. 4፡7)
3. አይሁድም ሆነ አሕዛብ በክርስቶስ የሆነን አንድን አዲስ ሕይወት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚተባበር (ኤፌ. 2፡ 14-17፤ ቆላ. 3፤15)

8፡7-11 ጳውሎስ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የሚርቅባቸውን በርካታ መንገዶች ይገልጣል። (1) ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ጥል፣ ቁ. 7፤ (2) ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ቁ.7፤ (3) እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አለመቻል ቁ. 8፤ እንዲሁም፣ (4)

*መንፈሳዊ ሞት፣ ይህም የዘላለም ሞትን የሚያስከትለው፣* ቁ.10-11። የሮሜ ትይዩ የሆነውን 5፡6፣ 8፣ እና 10 ተመልከት።

8.7

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አዲ.የተከ.መደ.መጽ.ቅ** | *"በሥጋ የተያዘ ሐሳብ ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ ነውና"* |
| **አዲ.ኪን. ጀምስ ትርጉም** | *"ሥጋዊ አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ ነውና"* |
| **አዲ.እን.ትርጕም** | *"ሰዎች የእግዚአብሔር ጠላት ሆኑ"* |
| **አዲ.ኢየሩ.መጽ.ቅ** | *"የተመሰቃቀለው የሰው ልጅ አፈጣጠር፣ አመለካከት ከእግዚአብሔር ጋር ተቃርኗል"* |

ይህ ሐረግ "ስለ *ሥጋ* ማሰብ ሞት ነውና" ከሚለውና በቁ.6 ከሚገኘው እና "እንደ *ሥጋ* ፍቃድ የሚመላለሱ" ከሚለው በቁ.5 ከሚገኘው ጋር ትይዩ እንደሆነ ልብ በል። እንደገናም፣ የሰው ልጅ የመውደቁ ባሕርያት የልብ ሐሳብ (የዓለም ሐሳብ) እና የሕይወት አኗኗር እንደሆነ ልብ በል (7፡5)።

▣ **"ለማድረግ እንኳ አልተቻለውም"** የወደቀው የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ለመከተል አለመወሰኑ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መከተል አለመቻሉ ነው። የወደቀው የሰው ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ሊረዳ አይችልም፣ ለመንፈሳዊ ነገሮች ምላሽ የሚሰጥ አይደለም። )ኢሳ. 53፡6፤1ኛ ጴጥ.2፡24-25) ሁልጊዜ ኃላፊነቱን የሚወስደው እግዚአብሔር ነው። (ዮሐ. 6፡ 44፣65)

**8.8 "በ*ሥጋ* ያሉትም"** ጳውሎስ ይሄንን ሐረግ በሁለት መንገዶች ተጠቅሞበታል፦ (1) ግዙፉ አካል (ሮሜ. 1፡3፤ 2፡28፤ 4፡ 1፤ 9፡3፣5)፤ እና (2) ከእግዚአብሔር ውጪ የሆነ የሰው ልጆች ጥረት (ሮሜ. 7፡5፤ 8፡4-5)። እዚህ ላይ ቁጥር 2ነው። እሱም የሚያሳየው አመፀኛውንና የማያምነውን ስብዕና ነው።

> 8፡9-11
> **9እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። 10ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። 11ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።**

**8፡9 "እንደ ሆነ"** ቅድመ ሁኔታዊ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮች መደዳውን ይገኛሉ። ቁ.9፣10፣ 11፣ 13 (ሁለት ጊዜ)፣ 17 ሁለት ጊዜ። እነዚህ ሁሉ አንደኛ ደረጃ ቅድመ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፤ ይህም ከጸሐፊው እይታ አኳያ ለአጻጻፍ ስልቱ ትክክል የሆኑ ናቸው። ጳውሎስ የጻፈላቸው አንባቢዎቹ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ናቸው። (ቁ.$9_{ሀ}$)

▣ **"የኢየሱስ መንፈስ"** ሰዎች አንድም መንፈሱ ይኖርባቸውና የሚያምኑ ይሆናሉ፤ አልያም መንፈሱ የሌለባቸው ሆነው በመንፈሳዊነት የጠፉ ሊሆኑ ይችላሉ። ስንድን መንፈስ ቅዱስን በምላት እንቀበላለን። ከዚያም ብዙ አያስፈልገንም– ራሱ ይፈልገናል እንጂ!

"መንፈስ" የሚለው አንቀጽ፣ ቁ.$9_{ሀ}$ ላይ ያለው፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ" የሚለው $9_{ለ}$ ያለው እና "የክርስቶስ መንፈስ" የሚለው $9_{ሐ}$ ያለው ተመሳሳይነት አላቸው።

**ልዩ ርዕስ፡ ኢየሱስና መንፈሱ**

በመንፈስ ሥራ እና በወልድ መካከል የመዋሀድ (የመገናኘት) ሁኔታ አለ። ጂ. ካምቤል ሞርጋን ለመንፈስ ቅዱስ ምርጡ ስም "ሌለኛው ኢየሱስ" ነው ብሏል። የሚከተለው የማነጻጸሪያ ርዕሰ-ጉዳይ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እና ርዕስ ያሳያል።

1. መንፈስ "የኢየሱስ መንፈስ" ተብሎ ወይም በተመሳሳይ አገላለጽ ይጠራል። (ሮሜ. 8፡9፤ 2ኛቆሮ. 3፡17፤ ገላ. 4፡6፤ 1ኛጴጥ. 1፡11)
2. በሁለቱም በተመሳሳይ ቃላት ይጠራሉ
   - ሀ. "እውነት"
     1. ኢየሱስ (ዮሐ. 14፡6)
     2. መንፈስ (ዮሐ. 14፡17፤ 16፡13)
   - ለ. "ጠበቃ"
     1. ኢየሱስ (1ኛ ዮሐ. 2፡1)
     2. መንፈስ (ዮሐ. 14፡ 16፣ 26፤ 15፡26፤ 16፡7)
   - ሐ. "ቅዱስ"
     1) ኢየሱስ (ሉቃ. 1፡35፤ 4፡34)
     2) መንፈስ (ሉቃ. 1፡35)

3. ሁለቱም በአማኞች ላይ ያድራሉ
   ሀ. ኢየሱስ (ማቴ. 28፡ 20፤ ዮሐ. 14፡20፣ 23፤ 15፡4-5፤ ሮሜ. 8፡10፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡5፤ ገላ. 2፡20፤ ኤፌ. 3፡17፤ ቆላ. 1፡27)
   ለ. መንፈስ (ዮሐ. 14፡16-17፤ ሮሜ. 8፡9፣ 11፤ 1ኛቆሮ. 3፡16፤ 6፡19፤ 2ኛጢሞ. 1፡14)
   ሐ. እንዲሁም አብ (ዮሐ. 14፡23፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡16)

8.10 **"ክርስቶስ በእናንተ ነው"** "እናንተ" የብዙ ቁጥር ነው፡፡ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል ደግሞ የሚያድረውን ልጁን/መንፈሱን ነው፡፡ ዮሐ. (14፡ 16-17፤ ቆላ. 1፡27) ሰዎች ልጁ/መንፈሱ ይኖርባቸዋል፣ ወይም ክርስቲያን አይደሉም፡፡ (1ኛዮሐ. 5፡12) ለጳውሎስ "በኢየሱስ" ማለት በሥነ-መለኮት "በመንፈስ" እንደ ማለት ነው፡፡

▣ **"ከኃጢአት የተነሣ በሞተው ሥጋ"** ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ከአዳም ኃጢአት፣ ከወደቀው ዓለም፣ እና ከግል 'ዐመፀኝነት የተነሣ ሥጋዊ ሞትን ይሞታሉ፡፡ (5፡12-21) ኃጢአት ሁልጊዜ ሂደቱን አያቆምም፡፡ መንፈሳዊ ሞት፣ (ዘፍጥረት 3፤ ኤፌ. 2፡1) ከሥጋዊ ሞት የተነሣ ይሆናል፡፡ (ዘፍጥረት 5፤ ዕብ. 9፡27) አማኞች እየኖሩ ያሉት፣ በሁለቱም ማለትም፣ በአዲሱ በመንፈስ ዘመን (ኢዩ. 2፡28-29፤ ሐዋ. 2፡16) እና በአሮጌው በኃጢአት እና በዐመፃ ዘመን ነው፡፡ (ቁ. 21፡35)

▣ **"ከጽድቅ የተነሣም በመንፈስ በሕይወት ይሆናል"** ይህን በተመለከተ በትርጉሞች እና በሐተታዎች መካከል አለመግባባት አለ፡፡ ማለትም፣ "መንፈስ" ያለው የሰውን መንፈስ ለማለት እንደሆነ፡፡ (አዲ. አሜ. መደ.መጽ.ቅ፣ አሜ.መደ.ትር.፣ አዲ.ዓለ.አቀ.ትር፣ የዊልየም አየሩሳሌም መጽ.ቅ)፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ (ኪ.ጀ.ትር.፣ የአሁኑ እንግ.ትርጉ፣ የተከ.እን.መጽ.ቅ፣ ካርል ባርዝ፣ ሲ.ኬ.ባረንት፣ ጆን ሙራይ፣ እና ኢቨረት ሃሪሰን)
ይህንን አጭር ሐረግ ለመረዳት ሰፋ ያሉ ጽሑፎች ግንዛቤአችንን ሊያሰፉት ይችላሉ፡፡ በክርስቶስ የሚያምኑት እንኳ በወደቀው ዓለም ውስጥ ስለሚኖሩ ይሞታሉ፡፡ ያም ቢሆን፣ በኢየሱስ ባላቸው እምነት በተገኘ ጽድቅ ቀድሞውኑ የዘላለም ሕይወት አላቸው፡፡ (ኤፌ. 2፡4-6) ይህ "ቀድሞውኑ ነው እንጂ አሁን አይደለም" የሚለው የእግዚአብሔርን መንግሥት ውጥረት ያሳያል፡፡ አሮጌው ዘመንና አዲሱ ዘመን በጊዜ ውስጥ ተነባብረዋል፡፡

▣**"ጽድቅ"** በ1፡17 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

8፡11 **"እንደ"** በቁጥር 9 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

▣**"ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ይኖራል"** የሥላሴ የትኛው አካል ነው በአማኞች ላይ የሚያድረው? አብዛኞቹ ክርስቲያኖች መንፈስ ብለው ይመልሳሉ፡፡ ይሄ በእርግጥ ልክ ነው፤ ነገር ግን በተጨባጭ የሥላሴ ሦስቱም አካላት በአማኞች ላይ ያድራሉ፡፡

1. መንፈሱ፣ ዮሐ. 14፡ 16-17፤ ሮሜ. 8፡11፤ 1ኛቆሮ. 3፡16፤ 6፡19፤ 2ኛጢሞ. 1፡14
2. ልጁ፣ ማቲ. 28፡20፤ ዮሐ. 14፡20፣23፤ 15፡4-5፤ ሮሜ. 8፡10፤ 2ኛቆሮ. 13፡5፤ ገላ. 2፡20፤ አፌ. 3፡17፤ ቆላ. 1፡27
3. አብ፣ ዮሐ.14፡23፤ 2ኛቆሮ. 6፡16

ይህ ሐረግ፣ አዲስ ትርጉም ብዙውን ጊዜ በሦስቱ የሥላሴ አካላት የሚከናወነውን የመቤዠት ሥራ ለማሳየት ግሩም የሆነ እድልን ይሰጣል፡፡

1. እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን አስነሣው፡፡ (ሐዋ. 2፡24፤ 3፡15፤ 4፡10፤ 5፡30፤ 10፡40፤ 13፡30፣ 33፣34፣37፤ 17፡ 31፤ ሮሜ. 6፡4፣9፤ 8፡11፤ 10፡9፤ 1ኛቆሮ. 6፡14፤ 2ኛቆሮ. 4፡14፤ ገላ. 1፡1፤ ኤፌ. 1፡20፤ ቆላ. 2፡12፤ 1ኛተሰ.1፡10)
2. እግዚአብሔር ወልድ ራሱን አስነሣ፡፡ (ዮሐ. 2፡19-22፤ 10፡17-18)
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን አስነሣው፡፡ (ሮሜ. 8፡11

ይሄው ተመሳሳይ ሥላሴያዊ አጽንዖት በቁ. 9-11 ይገኛል፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ**

የሦስቱም የሥላሴ አካላት ተግባርን ተመልከት፡፡ "ሥላሴ" የሚለው ቃል መጀመሪያ የወጣው ቴርቱልያን፣ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፤ ጽንሰ-ሐሳቡ ግን በየስፍራው አለ፡፡

1. ወንጌላት
   ሀ. ማቲዎስ 3፡16-17፤ 28፡19 (በትይዩነት)
   ለ. ዮሐንስ 14፡26
2. ሐዋ.-ሐዋ. 2፡32-33፣ 38-39

3. ጳውሎስ
   ሀ. ሮሜ 1፡4-5፤ 5፡1፣5፤ 8፡1-4፣8-10
   ለ. 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡8-10፤ 12፡4-6
   ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡21፤ 13፡14
   መ. ገላትያ 4፡4-6
   ሠ. ኤፌሶን 1፡3-14፣ 17፤ 2፡18፤ 3፡14-17፤ 4፡4-6
   ረ. 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡2-5
   ሰ. 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13
   ሸ. ቲቶ 3፡4-6
4. ጴጥሮስ- 1ኛ ጴጥ. 1፡2
5. ይሁዳ- ቁ. 20-21

በብሉይ ኪዳንም ጥቆማው አለ።
1. ለእግዚአብሔር የብዙ ቁጥርን መጠቀም
   ሀ. ኤሎሄም የሚለው ስም የብዙ ቁጥር ነው፣ እግዚአብሔር በሚለው ስንጠቀምበት ግን ነጠላ ግሥ ይሆናል
   ለ. "እኛ" በዘፍጥረት 1፡26-27፤ 3፡22፤ 11፡7
2. የጌታ መላእክት እንደሚታዩ የመለኮት ተወካዮች
   ሀ. ዘፍጥረት 16፡7-13፤ 22፡11-15፤ 31፡11፣13፤ 48፡15-16
   ለ. ዘፀአት 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
   ሐ. መሳፍንት 2፡1፤ 6፡22-23፤ 13፡3-22
   መ. ዘካርያስ 3፡1-2
3. እግዚአብሔርና መንፈስ ልዩነት አላቸው፣ ዘፍጥረት 1፡1-2፤ መዝሙር 104፡30፤ ኢሳ. 63፡9-11፤ ሕዝቅ. 37፡13-14
4. እግዚአብሔር (ያሕዌህ) እና መሲህ (አዶን) ልዩነት አላቸው፣ መዝሙር 45፡6-7፤ 110፡1፤ ዘካርያስ 2፡8-11፤ 10፡9-12
5. መሲህ እና መንፈስ ይለያያሉ፣ ዘካርያስ 12፡10
6. እኒህ ሦስቱም ተጠቅሰዋል፣ በኢሳ. 48፡16፤ 61፡1

የኢየሱስ መለኮትነት እና የመንፈስ ባለአካል መሆን በአንድነቱ ላይ በሚያተኩሩ የጥንት አማኞች ጥያቄ ፈጥሯል።
   1. ቴርቱሊያን- ወልድን በአብ ሥር ያደርገዋል
   2. ኦሪጅን- የወልድንና የመንፈስን መለኮታዊ ባሕርይ በሌላ ሥር እንደሆነ ያስባል
   3. አሪዮስ- የወልድንና መንፈስን መለኮትነት ይክዳል
   4. ሞናርኪያዊነት (ሥርወ-መንግሥታዊነት)- በእግዚአብሔር ተወራራሽ አገላለጥ ያምናሉ

ሥላሴ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በተገለጸው በታሪክ ሂደት መሠረት የተቀመረ ነው።
1. የኢየሱስ ፍጹም መለኮትነት፣ ከአብ ጋር መተካከሉ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባዔ ተረጋግጧል
2. የመንፈስ ፍጹም አካል እና መለኮትነት፣ ከአብና ከወልድ ጋር መተካከል በቁስጥንጥንያ ጉባዔ (382ዓ.ም) ተረጋግጧል።
3. የሥላሴ የእምነት መግለጫ በተሟላ መልኩ ሥላሴ በሚለው የአውግስጢኖስ መጽሐፍ ተብራርቷል

እውነተኛው ምሥጢር ያለው እዚህ ነው። ዳሩግን አዲስ ኪዳን እያረጋገጠ ያለው አንድን መለኮት ባሕርይ በሦስት ዘላለማዊ አካላት መገለጫዎች ነው።

▣"*ለሚሞት ሥጋችሁ ሕይወትን ሰጥቷልና*" የኢየሱስም ሆነ የተከታዮቹ ትንሣኤ ዋነኛው የእምነት ፍሬ ሐሳብ ነው። (1ኛ ቆሮ. 15፡1፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡14) ክርስትና፣ አማኞች አካላዊ ሕላዌ በዘላለማዊው እንደሚኖራቸው ያስረግጣል (1ኛ ዮሐ. 3፡2)። ክርስቶስ በመንፈስ ከተነሣ፣ ተከታዮቹም እንዲሁ (ቁ. 23)።

አዲ.አሜ.መደ.መጽ.ቅ (የተሻሻለው) ጽሑፍ፡ 8፡12-17
***[12]እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። [13]እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። [14]በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። [15]አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። [16]የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። [17]ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።***

8:12 **"ከእንግዲህ"** ጳውሎስ በቁ.1-11 ያለውን የመልእክቱን ውጤት ማሳየቱን ይቀጥላል።

▣**"ግዴታ አለብን"** ይህ የክርስትና ነጻነት ሌለኛው ጎን ነው (14:1-15:13)። ይህ በቁ.1-11 ተያይዞ የመጣውና ስለ ቅድስና የተደረገው ገለጻ ማጠቃለያ ሲሆን፣ እሱም አቋማዊ (አመላካች) እና ታዳጊ (ትዕዛዛዊ) ነው። እሱም ደግሞ በግልጽ አማኞች አሁንም ቢሆን ከአሮጌው የወደቀ ተፈጥሮ ጋር መታገል እንዳለባቸው ያሳያል (ሮሜ. 7)። ተፈጻሚ የሚሆን ምርጫ አለ፣ (መነሻ እምነት) እና ቀጣይ ተፈጻሚ ምርጫዎች (የሕይወት ኑሮ እምነት)!

8:13 **"እንደ"** በቁ.9፣10፣11፣13 (ሁለት ጊዜ)፣ እና 17(ሁለት ጊዜ) ቅድመ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች መደዳውን አሉ። እነሱም አንደኛ ምድብ ቅድመ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ሆነው፣ ከጸሐፊው የአጻጻፍ አንጻር ወይም ከጽሑፋዊ አቀራረቡ ትክክለኛ ናቸው ተብሎ ይገመታል። ጳውሎስ የጻፈላቸው አንባቢዎቹ በመንፈስ የሚኖሩ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች እንደሆኑ ተረድቷል።

▣ **"እንደ *ሥጋ* ፍቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና"** ሁለቱም በቁ.13 ያሉት ግሦች በአሁን ጊዜ ሲሆኑ ይህም በቀጣይ የሚሆን ድርጊትን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ዓይነት የሞት ደረጃዎች እንዳሉ ይገልጣል። (1) መንፈሳዊ ሞት (ዘፍ. 2:17፤ 3:1-7፤ ኤፌ. 2:1)፤ (2) አካላዊ ሞት (ዘፍ.5)፤ እና (3) የዘላለም ሞት (ራዕ. 2:11፤ 20:6፣ 14፤ 21:8)። በአንቀጹ ውስጥ እየተነገረ ያለው የአዳምን መንፈሳዊ ሞት  (ዘፍ. 3:14-19) ሲሆን የዚህም ውጤት በሰው ልጆች ሁሉ አካላዊ ሞት በማስከተሉ ነው (ዘፍ. 5)

የአዳም ኃጢአት በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ሞትን አስከተለ (ዘፍ. 5:12-21)። እያንዳንዳችን በፍቃዳችን ኃጢአትን ለመፈጸም መረጥን። በሱም ተይዘን ለመቅረት ከመረጥን "ለዘላለም" ይገድለናል (ራዕ. 20:6፣ 14፣ "ሁለተኛው ሞት")። እንደ ክርስቲያን ለኃጢአትና ለእኔነት ሞተን ለእግዚአብሔር መኖር አለብን (ሮሜ. 6)።

▣ **"በመንፈስ ግን የሰውነትን *ሥራ* ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ"** የአማኞች የመዳናቸው ዋስትና ዋጋ የሚኖረው ወይም በተግባር የሚታየው በክርስቲያናዊ የሕይወት አኗኗር ነው። (የአዲሱ ትርጉም መጻሕፍት ያዕቆብና 1ኛ ዮሐንስ)። አማኞች ይህንን ሕይወት በራሳቸው ጥረት ብቻ ሊኖሩት አይችሉም፣ ነገር ግን በመንፈሱ ረድኤት እንጂ (ቁ.14)። ስለሆነም፣ ራሳቸውን በየዕለቱ ለእሱ ቁጥጥር መስጠት ይኖርባቸዋል (ኤፌ. 5:17-18)።

በዚህ ጽሑፍ "የ*ሥጋ*ም *ሥራዎች*" በአሮጌው የኃጢአት ሕይወት አኗኗር ይታያሉ። ይህም የዘላለማዊ አካላዊ ሕላዌን መጣል የሚያመለክት አይደለም፣ (8:23) ዳሩግን (የአዲሱ ሕይወት) በሆነው በመንፈስ ማደሪያነትና (በአሮጌው ሕይወት) በኃጢአት መካከል ያለውን ትግል ያሳያል እንጂ።

8:14 **"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና"** ይህ የአሁን የተፈጸመ ጊዜ ሆኖ ቀጣይነት ያለውን የመንፈስን ምሪት ያመላክታል። መንፈስ እኛን ወደ ክርስቶስ ያቀርበናል፣ ከዚያም ክርስቶስን በውስጣችን ያደራጃል (ቁ. 29)። ከውሳኔው ይልቅ እጅግ ክርስትና ይኖራል። ውሳኔውን ተከትሎ ቀጣይነት ያለው ደቀ መዝሙርነት በርግጥ ይኖራል። ይህም የሚያመለክተው የተለዩ ሁኔታዎችን፣ ጊዜያትን፣ ወይም አገልግሎትን ሳይሆን የየዕለት ተግባራትን ነው።

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች"** ይህ የብዙ ቁጥራዊ ሐረግ በብሉይ ኪዳን ጥቅም ላይ የሚውለው ለመላእክት እና አልፎ አልፎም ለሰዎች ነው። ነጠላ ቁጥሩ ለአዳም፣ ለእስራኤል፣ ለንጉሢና ለመሲኂ መለያ ሆኗል። እዚህ የሚያመላክተው ለአማኞች ሁሉ ነው። በቁ. 14 የግሪኩ ቃል *huioi ሁሆይ (ወንዶች ልጆች)*  ቁ.16፣ ቴክና (ልጆች) በሚል ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህ ጽሑፍም በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል።

8:15 **"መንፈስ"** ይሄ ቁጥር እንደ ቁ.10 ሁሉ አሻሚነት አለው። ሊጠቀስ የሚችለውም በክርስቶስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ የዋጀውን የሰው ልጅን አዲሱን መንፈስ ነው። ሁለቱም በቁጥር 16 ይገኛሉ።
በጳውሎስ ጽሑፎች በብዙ ስፍራ ሰዋሰዋዊ አመሠራረቱ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ግለሰብ የሚፈጥረውን ይገልጻል።

1. ይህም፣ "የባርነት መንፈስ ሳይሆን፣" "የልጅነት መንፈስ፣ ቁ.15
2. "የየውሃት መነፈስ፣" 1ኛቆሮ. 4:21
3. "የእምነት መንፈስ (ታማኝነት)፣ 2ኛ ቆሮ.4:13
4. "የጥበብና የመገለጥ መንፈስ፣" ኤፌ. 1:17

ብዙ ቦታዎች፣ በተለይም 1ኛ ቆሮንቶስ፣ ጳውሎስ ራሱን ለመግለጽ *pneuma (ኑማ)* ይላል፣ (1ኛቆሮ. 2:11፤ 5:3፣ 14፤ 7:34፤ 18:8፤ እና ቆላ. 2:5)። በዚህ ጽሑፍ ቅኝት ቁ. 10 እና 15 ለዚህ ምድብ በእጅጉ ይስማማሉ።

▣ **"እንደገና ወደ ፍርሃት የሚመራ የባርነት"** የአሮጌው ተፈጥሮ ባሕርይ ፍርሃት ነው። የአዲሱ ተፈጥሮ ባሕርይ ቁ. 14-17 ተገልጿል።

▣ **"እንደ ልጆች ከሆንን"** በሮማውያን ሕግ ማደጎነት በጣም አስቸጋሪ ነው፣ አንድ ጊዜ ከሆነ በኋል ግን ጽኑ ነው። (ገላ. 4: 4-6)። ይሄ ዘይቤ *ሥነ-መለኮታዊ* እውነት የሆነውን የአማኝን ደኅንነት ያጠናክራል። ያብራክ ክፋይ ልጅ ከውርስ ሊታገድ ሲችል፣ የማደጎን ግን አይቻልም። ይህ ነው የጳውሎስ ተወዳጁ ቤተሰባዊ ዘይቤ፣ ደኅንነትን የሚገልጽበት። (ቁ.

15፣23)። ዮሐንስና ጳውሎስም ተዛማጅ የሆነ ቤተ-ሰባዊ ዘይቤ፣ "ዳግም መወለድ" ይጠቀማሉ። (ዮሐንስ 3፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡3፣23)።

▣ "አባ" ይህ አራማዊ ቃል ልጆች አባታቸውን እቤት ("አባበይ" ወይም "አባ" ) እንደሚጠሩት ያለ ነው። ኢየሱስና ሐዋርያት ይናገሩ የነበሩት አራማዊ ነው። አማኞች አሁን ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር የሚቀርቡት በክርስቶስ ደም በኩል፣ ባደረባቸው መንፈስ በጽኑ እምነት እና በቤተሰባዊ ተማምኖነት ነው። (ማርቆስ 14፡36፤ ገላ. 4፡6)። የወደቀው ሰብእና እግዚአብሔርን፣ አብን ሲጠራ የሚገርም አይሆንም፣ ይልቁንም ዘላለማዊ ቅዱሱ ይህንን ሲፈልገው! ልዩ ርዕስ የሆነውን፡ አባት በ1፡7 ላይ ተመልከት።

**8፡16 "መንፈስ፣ እሱ ራሱ"** የግሪኩ ቃል መንፈስ *ኒውተር* ነው፣ ስለሆነም ኪ.ጀ.ት. ይህን ሲተረጉመው "መንፈስ፣ ራሱ፣" ብሎ ነው፣ ነገር ግን መንፈስ አካል ነው፤ ሊያዝን ይችላል (ኤፌ. 4፡30፤ 1ኛ ተሰሎ. 5፡19)፣ ስለዚህ "እሱ ራሱ" የተሻለ ትርጉም ነው።

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል"** በቁ. 13 ላይ እንደተመለከተው፣ የአማኞች የእምነት ዋስትና አንዱ ገጽታ የተለወጠና እየተለወጠ የሚሄድ ሕይወት ነው። (የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያዕቆብና 1ኛ ዮሐንስ)። ሌለኛው የዋስትና ገጽታ ደግሞ የሚያድርብን መንፈስ የእግዚአብሔር ፍራቻችንን ወደ ቤተሰባዊ ፍቅር መተካቱ ነው። ማስታወሻ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም እና አዲስ የተከለሰው መደበኛ መጽ.ቅ ትርጉሞችና ሥርዓተ ነጥቦች፣ "አባ! አባት! ብለን ስንጮኽ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን መንፈሱ ከመንፈሳችን ጋር ምስክርነቱን ይሰጣል" (ገላ. 4፡6)። ይህም የሚያመለክተው ዋስትናው የሚመጣው አማኞች እግዚአብሔርን ፣ አባት፣ ብለው በመንፈስ ሲጠሩት ነው።
ውስጣዊው የመንፈስ ምስክርነት የሚደመጥ ሳይሆን ተግባራዊ ነው።

1. ጥፋተኝነት በኃጢአት ላይ
2. ክርስቶስን የመምሰል ፍላጎት
3. ከእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጋር የመሆን ፍላጎት
4. ለእግዚአብሔር ቃል ያለ ረሀብ
5. ወንጌላዊነትን ለመተግበር የመሻት ስሜት
6. ክርስቲያናዊ መሥዋዕትነት ለመክፈል የመሻት ስሜት

እነዚህ የመለወጥ የእምነት ማስረጃ የሆኑ የውስጣዊ መሻት ዓይነቶች ናቸው።

የመዳን ዋስትና ወደ ሃይማኖታዊ ወገንተኝነት ጉዳይ ተቀየረ፡

1. የሮማ ካቶሊክ ሥነ-መለኮታዊ አስተምህሮት በዚህ ሕይወት ላይ ሊገኝ የሚቻለውን ዋስትና ክዶ ዳሩ ግን "የእውነተኛ" ቤተ-ክርስቲያን አባል በመሆን የትምምን መሠረቱን አጸና።
2. ጆን ካልቪን (በተሐድሶ ባህል) የዋስትና መሠረትን በመመረጥ (ቀድሞ በተወሰነ) ላይ አጸና፤ ዳሩ ግን አንዱ ፍጹም በርግጠኝነት ከዚህ ሕይወት በኂላ በፍርድ ቀን ካልሆነ በቀር ሊያውቀው አይችልም።
3. ጆን ዌስሊ (በሜቶዲስት ባህል) የዋስትና መሠረትን በፍጹም ፍቅር ላይ አጸና። (ከሚታወቅ ኃጢአት በላይ በመኖር)
4. አብዛኞቹ መጥምቃውያን (ባፕቲስት) የዋስትና መሠረትን ነጻ ጸጋ በሆነው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የተስፋ ቃል በማድረግ (ማስጠንቀቂያዎቹንና ተግሣጾቹን ችላ ይሏቸዋል።)

የክርስቲያን ዋስትናን በተመለከተ ከአዲስ ኪዳን አይአዎአዊ (ፓራዶክስ) አቀራረብ በተያያዘ ሁለት ዓይነት አደጋዎች አሉ፡

1. "አንድ ጊዜ የዳነ፣ ሁሌም ድኗል" የሚለውን ከሚገባ በላይ ማጋነን
2. ለደኅንነት የሰዎችን የክዋኔ ድጋፍ ከሚገባ በላይ ማጋነን

ዕብራውያን 6 በግልጽ እንደሚያስተምረው፣ "አንድ ጊዜ የወጣ ሁሌም ወጥቷል።) የሰው ጥረት (መልካም ተግባራት) የአማኞችን መዳን አያስጠብቅም፣ (ገላ. 3፡1-14።) ነገር ግን መልካም ተግባራት የክርስቲያናዊ ሕይወት ግቦች ናቸው። (ኤፌ. 2፡10።) እነርሱም እግዚአብሔርን የመገናኘት እና ያደረብንን መንፈስ ተፈጥሯዊ ውጤት ናቸው። የእውነተኛ መቀየር ትክክለኛ ማስረጃዎች ናቸው።
ዋስትና፣ የመጽሐፍ ቅዱስን የቅድስና ጥሪ ማለዘብ ማለት አይደለም! በሥነ-መለኮታዊ ቋንቋ ዋስትና የተመሠረተው በእውነተኛው አምላክ ባሕርይና ተግባር ላይ ነው፡

1. የአብ ፍቅርና ምሕረት
2. የወልድ የተጠናቀቀ መሥዋዕታዊ ሥራ
3. የመንፈስ ወደ ክርስቶስ ማቅረብ፣ ከዚያም ኢየሱስን ንስሐ በገባው አማኝ ውስጥ ማስረጽ

የዚህ መዳን ማስረጃው የተለወጠ የዓለም አተያይ፣ የተለወጠ ልብ፣ የተለወጠ የሕይወት አኗኗር እና የተለወጠ ተስፋ ነው! የሕይወት አኗኗር ማስረጃ የሌለውና ባለፈው ስሜታዊ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ሊሆን አይችልም። (ያም ማለት፣ ፍሬ፣ ማቴ. 7፡15-23፤ 13፡20-22፤ ዮሐ. 15።) ዋስትና እንደ ደኅንነት፣ እንደ ክርስትና ሕይወት ሁሉ ለእግዚአብሔር ምሕረት ምላሽ በመስጠት ይጀምርና ያንኑ ምላሽ፣ ሕይወትን በሙሉ መቀጠል ነው። እሱም የተለወጠና በመለወጥ ላይ ያለ የእምነት ሕይወት ነው!

▣ **"ይመሰክራል"** ይህም ሌለኛው ድብልቅ ቃል ነው። የመንፈስና የአማኙ መንፈስ የተቀናጀ ምስክርነት። ጳውሎስ ይሄንን ድብልቅ ቃል በ2:15፤ 8:16 እና 9:1 ተጠቅሞበታል።

**8:17 "እንደ"** በቁ.9፣10፣11፣13 (ሁለት ጊዜ)፣ እና 17(ሁለት ጊዜ) ቅድመ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች መደዳውን አሉ። እነሱም አንደኛ ምድብ ቅድመ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ሆነው፣ ከጸሐፊው የአጻጻፍ አንጻር ወይም ከጽሑፋዊ አቀራረቡ ትክክለኛ ናቸው ተብሎ ይገመታል። ጳውሎስ የጻፈላቸው አንባቢዎቹ በመንፈስ የሚኖሩ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች እንደሆኑ ተረድቷል።
▣ በዚህ ቁጥር ላይ ሦስት ድብልቅ ቃላት በተመሳሳይነት ማለትም "በተቀናጀ የጋራ ተሳትፎ" አሉ። አማኞች ከክርስቶስ ጋር የወራሽነት መብትን ይጋራሉ፤ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መከራን ይካፈላሉ፤ እናም አማኞች ከክርስቶስ ጋር ክብርን ይካፈላሉ። በተጨማሪም ተመሳሳይ ድብልቆች በቁ. 22 (ሁለት ጊዜ)፣ 26እና28። ኤፌ. 2:5-6 እንዲሁ ሦስት ተመሳሳይ ድብልቆች የአማኝን በክርስቶስ ያለ ሕይወት ይገልጻሉ።

▣ **"ወራሾች"** ይህም ሌላው ቤተሰባዊ ዘይቤ ሲሆን አማኞችን የሚገልጽ ነው። (ቁ. 4:13-14፤ 9:8፤ ገላ. 3:29።) የሚከተለውን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ: የአማኞች ውርስ**

*መጻሕፍት፣ አማኞች ብዙ ነገሮችን እንደሚወርሱ፣ ይህም የሁሉም ነገር ወራሽ ከሆነው ከኢየሱስ ጋር ባላቸው ግንኙነት የተነሣ እንደሆነ ይገልጻሉ። (ዕብ. 1:2)፣ እናም እነሱም አብረው ወራሾች እንደሆኑ (ሮሜ. 8:17፤ ገላ. 4: 7) የ*

1. *የመንግሥቱ* (ማቴ. 25:34፣ 1ኛ ቆሮ. 6:9-10፤ 15:50)
2. የዘላለም ሕይወት (ማቴ. 19:29)
3. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል (ዕብ. 6:12)
4. የእግዚአብሔር ለተስፋ ቃሉ ያለው ጥበቃ (1ኛ ጴጥ. 1:4፤ 5:10)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ከእርሱ ጋር በእርግጥ መከራ እንቀበላለን"** |
| **አየመመቅ** | **"ከእርሱ ጋር መከራን እንቀበላለን"** |
| **አእቅ** | **"የክርስቶስን መከራ የምንካፈል ከሆንን"** |
| **ኢመቅ** | **"መከራውን ከተካፈልን** |

በወደቀው ዓለም ላይ የአማኞች መከራን መቀበል የተለመደ ነው። (ማቴ.5:10-12፤ ዮሐ. 15:18-21፤ 16:1-2፤ 17: 14፤ ሐዋ.14:22፤ ሮሜ. 5:3-4፤ 8:17፤ 2ኛ ቆሮ. 4:16-18፤ ፊሊጵ. 1:29፤ 1ኛ ተሰሎ. 3:3፤ ያዕቆብ 1:2-4፤ 1ኛ ጴጥ. 4:12-19።) ኢየሱስ መንገዱን አወጣ (ዕብ. 5:8።) የዚህ ምዕራፍ ቀጣይ ይህን ጭብጥ ያጎላዋል።

▣**"ከእርሱ ጋር እንከብራለን"** በዮሐንስ ጽሑፎች ኢየሱስ ስለ ሞቱ በተናገረ ጊዜ ሁሉ፣ "ከበረ" ይለዋል። ኢየሱስ በመከራው ከብሯል። አማኞችም፣ በአቋምም ሆነ በልምምዳቸው የኢሱስን የሕይወት ሁነቶች ይካፈላሉ። (ሮሜ. 6) ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡ በእግዚአብሔር *መንግሥት መንገሥ*፣ ቁ. 5:17-18 ላይ።

8:18-25
**[18]ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። [19]የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። [20]ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ [21]ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። [22]ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። [23]እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። [24]በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? [25]የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።**

**8:18 "አስባለሁ"** ይህ በጥሬ ትርጕሙ "በላዩ መጨመር" ነው። ይህ *አመላካች መካከለኛ የአሁን* ጊዜ ነው። ጳውሎስ በማከታተል የክርስቲያን መከራ ውጤትን ከግምት ውስጥ ያስገባል። ይህ ቀመራዊ (ሒሳባዊ) የሆነ ቃል በጥንቃቄ ወደ ተጠና ድምዳሜ ያደርሳል። ይህ ደግሞ የተነሣ በሮሜ ላይ ያለ ጭብጥ ነው። (በ2:3 ያለውን ማስታወሻ ተመልከቱ) አማኞች በተረዱት በመንፈሳዊ እውነት ብርሃን መኖር አለባቸው።

▣ **"በመከራዎች"** ክርስቶስን በማገልገል ሳቢያ ሊመጣ ስለሚችለው መከራ ጥቂት ሐሳቦችን (ከ1ኛ ቆሮ.4፡9-12፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡7-12፤ 6፡4-10፤ 11፡24-27፤ ዕብ. 11፡35-38) አግኝተናል።

▣ **"በዚህ በአሁኑ ጊዜ"** አይሁድ የዓለም ታሪክ በሁለት ዘመናት እንደሚከፈል ያምናሉ– የአሁኑ ክፉ ዘመንና ሊመጣ ያለው የጽድቅ ዘመን:: (ማቴ. 12፡32፤ ማር. 10፡30::) ብሉይ ኪዳን፣ የሚመጣው መሲሕ ይህንን የአዲስ ዘመን ጽድቅ ያጎናጽፋል ብሎ ተስፋ ያደርጋል። ሆኖም ሁለቱም የክርስቶስ ምጽዓቶች፣ ማለትም፣ አንደኛው (*ሥጋ* እንደለበሰ) አዳኝ፣ እና ሁለተኛው በጌትነቱ (ዳግም ምጽዓቱ)፣ የእነዚህን ሁለት ዘመናት መደራረብ አስከትሏል። አማኞችም፣ "በሆነው" እና "በሚሆነው" የእግዚአብሔር መንግሥት መካከል ባለ ውጥረት ይኖራሉ። ልዩ ርዕስ፡ ዘመኑ እና መጪው ዘመን የሚለውን በ12፡2 ያለውን ተመልከት።

▣**"የሚጠቅም…ክብር"** እነዚህ ሁለት ቃላት የብሉይ ኪዳን የክብደት ጽንሰ-ሐሳብ ከሆኑት– ከከባድና ጠቃሚ ጋር ይዛመዳሉ። "ጠቃሚ" የሚለው ከንግድ ጋር የተያያዘ ቃል ሲሆን፣ "በሚቻለው ሁሉ ከባድ መሆን" ማለት ነው። የዕብራይስጡ ቃል "ክብር" ሌላው ሥርወ-ቃሉ "ከባድ መሆን" ማለት ሆኖ፣ ዋጋ ያለው ሆኖ መገኘት የሚል ስሜት አለው፣ እንደ ወርቅ። በ3፡23 ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከቱ።

በጳውሎስ ጽሑፎች "ክብር" የሚለው ቃል የመጨረሻውን ግብ አመላካች ነው። የሚያመላክተውም በግርማውና በኃይሉ የተሞላውን የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ክብርና ሞገስ ነው። (ቆላ. 3፡4). ልዩ ርዕስ፡ ክብር በ3፡23 ተመልከት።

▣ **"ለእኛም የሚገለጠው ክብር"** ተገብሮ የሆነው ሐረግ ባለቤትነቱን የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ወይም የመንፈስን ውክልና ነው (በቁጥር 20)። አማኞች በዚህ ዘመን የሚኖሩት በእምነት ነው እንጂ በማየት አይደለም (ቁ. 24 እና 1ኛ ቆሮ. 2፡9፤ 13፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡7 እና ዕብ. 11፡1)።

**8፡19 "ፍጥረት በሐሳብና በናፍቆት በጉጉት ይጠብቃል"** ግዙፉ ፍጥረት በሰውኛ ዘይቤ ተመስሎ አንገቱን እያቀና አድማሱን ይፈልጋል። ፍጥረት በክፉ ጎኑ ተጎድቷል፣ አዳምና ሔዋን ካመጹ በኋላ (ዘፍ. 3፡17-19)። ፍጥረት ሁሉ በመጨረሻ የሚዋጅ ይሆናል (ከዐመጹ መላእክት፣ ከማያምኑ ሰዎች፣ ተለይተው የሚሆኑበት የተሰናዳ ቦታ፣ ብሩስ ኮርሊ እና ኩርቲስ ቫውጋን፣ ሮሜ ገጽ 95፣ የግርጌ ማስታወሻ 46 ተመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ፡ የተፈጥሮ ሀብቶች**

I. *መግቢያ*
   - *ሀ.* ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን የፍቅር ጉዳይ የሚያሳይ የመድረክ ትዕይንት ነው።
   - ለ. ውድቀቱን ይካፈላል (ዘፍ. 3፡17፤ 6፡1፤ ሮሜ. 8፡18-20።) በተጨማሪም የመጨረሻውን መቤዠት ይካፈላል (ኢሳ. 11፡6-9፤ ሮሜ. 8፡20-22፤ *ራዕይ* 21-22።)
   - ሐ. በኃጢአት የተሞላው፣ የወደቀው የሰው ልጅ በከፋ ራስ ወዳድነት የተፈጥሮ አካባቢውን አበለሻሽቶታል። የሚከተለው፣ *የዌስትሚኒስቴር ቅዱስ ቃል (መርህ)* ከሚለው የኤድዋርድ ካርፔንተር የተጠቀሰ ነው።

     *"…የሰው ምሕረት የለሽ አደጋ ጣይነት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአካባቢው ባለ ዓለምና ሥነ ፍጥረታት ላይ– ያም ማለት በእግዚአብሔር ፍጡር ላይ– በዓየር ላይ በመበከል እና በማጥፋት፤ የተፈጥሮ የውኃ መፋሰሻዎችን በመበከል፤ መሬቱንም እየመረዘ (አሲድ እያደረገ)፣ ደኖችን ቆርጦ እየጣለ፣ ዘላቂውን ባላስተያየ ማስተዋል በጎደለው ግብረ ገብነት በሌለው ጥፋት እያወደመ ይገኛል። ይህም ጥቃት ጥቂት በጥቂት የሆነና መረን የወጣ ነው። ለተፈጥሮ ሚዛን የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፤ አንደኛው ትውልድ ለሌለኛው በሚያወርሰው ነገር ላይም እንዲሁ ጥቂት የኃላፊነት ስሜት ብቻ ነው ያለው።"*

   - *መ.* አሁን እያጨድን ያለነው ፕላኔታችንን የበከልነውንና ያጠፋነውን ብቻ አይደለም፤ መጪው ትውልድም ብዙ መከራ ያጭዳል፣ ተመልሶ ሊስተካከል የማይችል ጥፋት።

I. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገሮች*
   - *ሀ.* ብሉይ ኪዳን
     1. ዘፍጥረት 1-3
        - *ሀ.* ተፈጥሮ ልዩ በሆነ ስፍራ በእግዚአብሔር የተፈጠረና ከሰው ልጆች ጋር ላለው ኅብረት ነው የሚሆን ነው። (ዘፍ. 1፡1-25።)
        - ለ. ተፈጥሮ መልካም ነው (ዘፍ. 1፡4፣ 10፣ 12፣ 18፣ 21፣ 25)፣ አዎን፣ በጣም መልካም (ዘፍ. 1፡ 31።) ይህም ማለት ለእግዚአብሔር ምስክር እንዲሆን ነው (*መዝ*. 19፡ 1-16)።
        - ሐ. ሰውነት የተፈጥሮ ዘውድ የመሆን ዓላማ ነው (ዘፍ. 1፡ 26-27።)
        - *መ.* ሰውነት ማለት በሥልጣን መሥራት ነበር (በዕብራይስጥ፣ "መነገድ" የእግዚአብሔር ወኪል እንደ መሆን ነው (ዘፍ. 1፡28-30፤ *መዝ*. 8፡3-8፤ ዕብ. 2፡6-8።) እግዚአብሔር አለ፣ በፈጣሪነቱም ይቀጥላል /በአስቀጣይነቱ /በተቤዥነቱ/ በፍጥረታት ጌትነቱ (ዘጸ. 19፡5፤ ኢዮ. 37-41፤ *መዝ*. 24፡1-2፤ 95፡3-5፤ 102፡25፤ 115፡15፤ 121፡2፤ 124፡8፤ 134፡3፤ 146፡6፤ ኢሳ. 37፡16።)

*ሠ.* የሰው ልጅ የተፈጥሮ አዛዥነት በዘፍ. 2፡15 ይታያል፣ "ያበጃት እና ይንከባከባት ይጠብቃትም ዘንድ" (ሌዋ. 25፡23፤ 1ኛ ዜና. 29፡14፡፡)

2. እግዚአብሔር ፍጥረታትን ይወዳል፣ በተለይም እንስሳትን፡፡
   *ሀ.* የሙሴ ሕግጋት ለእንስሳት ተገቢውን አያያዝ ያዛሉ
   *ለ.* ያሕዌህ የፈጠረው ዘንዶ ይጫወታል (*መዝ.* 104፡26)
   *ሐ.* እግዚአብሔር ለእንስሳት ይጠነቀቃል (ዮናስ 4፡11)
   *መ.* የተፈጥሮ የመጨረሻ ግብ በሆነ ሕላዌ (*መናር*) (ኢሳ. 11፡6-9፤ *ራዕይ* 21-22)
3. ተፈጥሮ በአንድ መልኩ እግዚአብሔርን ያከብራል፡፡
   *ሀ. መዝሙር* 19፡1-6
   *ለ. መዝሙር* 29፡1-9
   *ሐ.* ኢዮብ 37፡41
4. ተፈጥሮ ማለት በአንድ መልኩ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ያለውን ታማኝነት አመላካች ነው፡፡
   *ሀ.* ዘዳግም 27-28፤ 1ኛ *ነገሥት* 17
   *ለ.* በትንቢታት ውስጥ ሁሉ

*ለ.* አዲስ ኪዳን

1. እግዚአብሔር በፈጣሪነቱ ታይቷል፡፡ አንድ ፈጣሪ ብቻ አለ፣ እውነተኛው እግዚአብሔር (ኤሎሄም፣ ዘፍ. 1፡1፤ *መንፈስ*፣ ዘፍ. 1፡2፤ እና ኢየሱስ፣ በአዲስ ኪዳን፡፡) ከእነዚህ ውጭ ያሉት ፍጡራን ናቸው፡፡
   *ሀ.* ሐዋ. 17፡24
   *ለ. ዕብራውያን* 11፡3
   *ሐ. ራዕይ* 4፡11
2. ኢየሱስ በተፈጥሮ ላይ የእግዚአብሔር ወኪል ነው
   *ሀ.* ዮሐንስ 1፡3፣10
   *ለ.* 1ኛ ቆሮንቶስ 8፡6
   *ሐ.* ቆላስያስ 1፡16
   *መ. ዕብራውያን* 1፡2
3. ኢየሱስ በትምህርቱ ላይ እግዚአብሔር ለተፈጥሮ ያለውን ጥንቃቄ በተዘዋዋሪ መንገድ ገልጿል
   *ሀ.* ማቴዎስ 6፡26፣ 28-30፣ የሰማይ አእዋፋትና የምድር ዕፅዋት
   *ለ.* ማቴዎስ 10፡29፣ ድንቢጦች
4. ጳውሎስ እንደሚለው ሁሉም የሰው ልጆች እግዚአብሔርን በማወቅ ተፈጥሯዊ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ (ማለትም፣ በተፈጥሮ የተገለጠው፣ ሮሜ. 1፡19-20፤ *ራዕይ*21-22፡፡)

II. *መደምደሚያ*

*ሀ.* በዚህ ተፈጥሯዊ ሥርዓት ተገደናል!

*ለ.* በኃጢአት የተሞላው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ተፈጥሮ ለመጥፎ ነገር አውሎታል፣ እንደ ሌሎቹ የእግዚአብሔር መልካም ስጦታዎች፡፡

*ሐ.* ይህ የተፈጥሮ ሥርዓት ጊዜያዊ ነው፡፡ ሊያልፍ ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡7፡፡) እግዚአብሔር ዓለማችንን ወደ ታሪካዊ ጉድኝቶች እያንቀሳቀሰው ነው፡፡ ኃጢአትም ጉዞውን ይቀጥላል፣ እግዚአብሔር ግን ወሰኑን ቆርጦለታል፡፡ ፍጥረት ይቤዣል (ሮሜ. 8፡18-25፡፡)

▣ **"ለመገለጥ"** ይሄ ቃል የሚለው "መጋረጃውን ወደ ኂላ መግለጥ" ሲሆን መግለጥ ወይም ማስታወቅ እንደ ማለት ነው፡፡ እሱም ደግሞ የሐዲስ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ "የራዕየ ዮሐንስ" ርዕስ ነው፡፡ ዳግም ምጽዓቱ ሁሌ የሚጠቀሰው የምጽዓቱ መገለጥ ተብሎ ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡7-8፤ 1ኛ ጴጥ. 17፣13)፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች"** ይህ የተለመደው ቤተሰባዊ ዘይቤ ክርስቲያኖችን ለመግለጽ ይውላል፡፡ (8፡14፣16፡፡) እሱም ስለ እግዚአብሔር እንደ አባት ስለ ኢየሱስም አንድያ ልጁ ስለመሆኑ ይናገራል፡፡ (ዮሐንስ1፡18፤ 3፡16፣18፤ ዕብ. 1፡2፤ 3፡6፤ 5፡8፤ 7፡28፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡9፡፡)

በብ.ኪ. እስራኤል የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፡፡ (ሆሴዕ 11፡1)፣ ነገር ግን ደግሞ ንጉሡም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፡፡ (2ኛ ሳሙ. 7)፡፡ ይህ ጽንሰ-ሐሳብ በመጀመሪያ የተጠቀሰው በሐ.ኪ. በማቴ. 5፡9 ሲሆን (እንደገና በዮሐንስ 1፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡18፤ ገላ. 3፡26፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡1፣10፤ *ራዕ.* 21፡7 ነው፡፡

▣8፡20

**አ.አ.መደ.መ.ቅ፣ አ.ኪ.ጀ.ት**

| | |
|---|---|
| **አ.የተ.መደ. ትር.** | **"ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቷልና"** |
| **የአሁ.እ.ትር.** | **"ፍጥረት ጥቅመ-ቢስ ይሆን ዘንድ ተኮንኗልና"** |

ኢየ. መ.ቅ. **"በተፈጥሮ በኩል በሆነ ምንም ዓይነት ስህተት አይደለም፣ ተግባሩን በተገቢው እንዲያከናውን ያላስቻለው"**

ይህ "ከንቱነት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በቅዱሳት መጻሕፍት በርካታ ተመሳሳይ ስሜቶች (ተመሳስሎዎች) ጥቅም ላይ ይውላል– ትርጕመ ቢስ፣ ጥቅመ ቢስ፣ ረብ የለሽ፣ የሀሰት አማልክት (ጣዖታት)፣ እና ባዶነት። ፍጥረት ሁሉ ጥቅመ ቢስ ሆነ፣ ለእግዚአብሔር የተግባር ሐሳብ (ዘፍ. 3፡17-19)፣ እግዚአብሔር ግን አንድ ቀን የመውደቅን ርግማን ያስወግዳል (ራዕ. 22፡3፡፡) ይህ እግዚአብሔር ሊሆን የሚፈልገው ዓለም አይደለም!

▣ **"ነገር ግን በእሱ ምክንያት ሁሉን ባስገዛለት፣ ተስፋ በማድረግ"** ግሡ ተገብሮ የሆነ (መፈጸሙን ወይም መቀጠሉን የማያመላክት) በአጠቃላይ ግን ስለ እግዚአብሔር የሚያመላክት ነው። (አ.አ.መደ.መ.ቅ፣ አ.ኪ.ጀ.ት፣ የአሁ.እ.ትር.) ግዑዙን ተፈጥሮ ለከንቱነት አስገዛው።

1. በሰው ልጆች ዐመጽ ምክንያት
2. የሰው ልጆችን ወደ ራሱ ለማዞር እንደ መሞከር (ዘዳግም 27-29)

ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ ከንቱነት የሚሆነው ለጊዜው ነው። የሰው ልጆችን መቤዠት ለወደፊቱ ግዘፋዊ ተስፋ ያለው ነው (አካል እና ዓለም፡፡)

እግዚአብሔር የአዳምን ዐመጽ ቀደም ብሎም ያውቀዋል። የወደቀው ሰው በወደቀው ዓለም ላይ እንዲሆንና እንዲሠራ ፍቃዱና ምርጫው ሆነ። ይህ ግን እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው ዓለም አይደለም። ይህ አንድ ጊዜ ወደፊት የሚሆነው ዓለም አይደለም። (2ኛ ጴጥ. 3፡10፤ ራዕ. 21፡1-3)። "ተስፋ" የሚለውን 5፡2 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

8፡21 **"ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነጻ ይወጣል"** ተፈጥሮ የዘላለማዊ አካል ይሆናል፣ (ኢሳ. 11፡6-10)። ሰማይም አዲስ ከተፈጠረው ዓለም ጋር ተመልሶ ይመጣል (ማቲ. 5፡18፤ 24፡35፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡10፤ ራዕ. 21፡1)። መጪው ወደ ኤደን ደስታ መመለስ ይሆናል፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ኅብረት፣ ሰዎች ከሰዎች፣ የሰው ልጅ ከእንስሳት፣ የሰው ልጅ ከምድር ጋር! መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በእግዚአብሔር፣ በሰው ልጅ፣ እና በእንስሳት በገነት ስፍራ በኅብረትና በስምምነት ነው (ዘፍ. 1-2) እናም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያበቃውም በተመሳሳይ መልኩ ነው (ራዕይ 21-22)።

▣**"መበላሸት"** ልዩ ርዕስ 1፡23 ተመልከት።

▣ **"የእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን የክብር ነጻነት"** በቁ. 14 አማኞች "የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች" ተብለው ነው የሚጠሩት፤ በቁ. 16 "የእግዚአብሔር ልጆች"፤ በቁ. 17 ደግሞ "የእግዚአብሔር ወራሾች፡፡" በቁ.18 የመጨረሻውን የእግዚአብሔር ክብር ለአማኞች ይገልጻል። እንግዲህ በ19 ፍጥረት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል፤ ምክንያቱም የእነሱን የፍጻሜ ክብር ተካፋይ ስለሚሆን ነው (ቁ.21)። ይህ የፍጥረት መታደስ፣ በተለይም የሰዎች፣ የተፈጥሮን ዋነኛ ግብ ተፈጻሚ ያደርገዋል– እግዚአብሔር እና በአምሳሉ የሠራው የሰው ልጅ ወዳጃዊ በሆነ ኅብረት።

8፡22 **"ፍጥረት ሁሉ እየቃተተ"** ይህ ሌለኛው የጳውሎስ ተመሳሳይ ድብልቅ (ዓረፍተ ነገር)፣ "አብሮ እየቃተተ" ይላል። ብዙዎች ቃላትን ተጠቅሟል። በተለይም ከኤር.12፡4፣ 11 (ዘዳግ. 27-27)፣ ጠቅሷል፤ የእስራኤል ምድር በሰው ልጆች ኃጢአት ምክንያት ሰው የማይኖርበት በመሆኑ እንዳዘነ ያሳያል።

▣ **"የምጥ ሥቃይን መቀበል"** በአይሁድ ዙሪያ ይህ ጽንስ ሐሳብ በተለምዶ "የአዲሱ ዘመን የምጥ ሥቃይ" (ማር. 13፡8) በሚል ይታወቃል። የአዲስ ቀን የጽድቅ ጎሕ ያለ ችግር አይሆንም። የዚህ የወደቀ ዓለም የግብረ ገብና መንፈሳዊ ሁኔታዎች እየከፋ እየባሰበት ይሄዳል (2ኛ ተሰ. 2፡1-12፤ እና እንዲሁም ሰባቱ ማኅተሞች፣ መለከቶች፣ እና የራዕይ ሰፊ ክፍል (bowels) 5-18 ያመላክታል።

ሦስት ዓይነት "መቃተቶች" በዚህ ጽሑፍ ይገኛሉ፡ (1) ፍጥረት (ቁ.22)፤ (2) አማኞች (ቁ.23)፤ እና (3) ማላጅ የሆነው መንፈስ (ቁ. 26)፣ እነዚህ ሦስቱም በዘፍ. 3 ምክንያት (ዘይቤው ከቁ.16 የመጣ ነው።

8፡23 **"እኛ እራሳችን… እኛ እራሳችን… ራሳችን"** ተውላጠ ስሞቹ አጽንኦታዊና የተደጋገሙ ናቸው።

▣ **"የመንፈስ በኵራት"** ይህ ቃል በዘመናዊ ግሪክ "የመተጫጨት ቀለበት" ለሚለው ይውላል። ይህም ተምሳሌት "የመንፈስ ማኅተም" በ2ኛ ቆሮ. 1፡22 ያለ ነው፤ ደግሞም "የመንፈስ ቃል ኪዳን" በ2ኛ ቆሮ. 5፡5፤ እና ኤፌ. 1፡14።

በኵራት በብ.ኪ. የመጪው መከር ተስፋ ነበሩ። እነርሱም የእግዚአብሔርን የሁሉም መከር ባለቤትነት ምሳሌ ያደርጋሉ። ኢየሱስ የትንሣኤ በኵራት እንደ ሆነ ሁሉ መንፈስም የአዲሱ ዘመን በኵራት ነው። (1ኛ ቆሮ. 15፡20)። አማኞች እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ በአሁን ጊዜ እንኳ በእነሱ ላይ ባደረውና በሆነው መንፈስ አማካኝነት አንዳች ሰማያዊ የሆነ ደስታን ይለማመዳሉ። ይህ "ገና ድሮ" ነገር ግን "አሁን ገና" መካከል ያለ የሐሳብ ግጭት፣ የአይሁድን ሁለቱን ዘመናት ያሳያል። አማኞች በምድር ላይ የሚኖሩ የሰማይ ዜጎች ናቸው!

▣ **"እኛ ራሳችን፣ በውስጣችን እንቃትታለን"** ይህ ክርክራዊ አግባብ "ገና ድሮ" እና "አሁን ገና" በሚለው መካከል ያለ የሐሳብ ግጭት፣ የአይሁድን ሁለቱን ዘመናት ያሳያል። የእግዚአብሔር መንግሥት ደርሷል ዳሩግን አልተጨረሰም።

አማኞች የትንሣኤ ሕይወት አላቸው፣ ግን ገና ሥጋዊ ሞትን ይሞታሉ። (2ኛ ቆሮ. 5፡2-4)። ድነናል። ነገር ግን ኃጢአትን እንፈጽማለን (ሮሜ.7)።

▣ **"የእኛን ልጅነት በጉጉት እየተጠባበቅን"** ልጅነት የጳውሎስ ተወዳጁ ቤተሰባዊ ዘይቤ፣ ደኅንነትን የሚገልጽበት ነው (ቁ.15)። የአማኞች ደኅንነት ሂደት መነሻው የንስሐ ውሳኔ እና እምነት ሲሆን ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚያድግ ነው። አማኞች እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ሙሉ ለሙሉ አይድኑም። (ቁ. 30 እና 1ኛ ዮሐ. 3፡2)።

"ልጅነት" የሚለው ቃል በአንዳንድ የግሪክ ጽሑፎች ተገድፏል (MSS P46, D,F,G, እና በአንዳንድ የላቲን ቅጅዎች። ቢሆንም፣ በX, A,B,C, በተወሰኑ በላቲን፣ በቫልጌት፣ ሲሪያዊ፣ ኮፕቲክ፣ እና አርማንያዊ ቅጅዎች። ዩቢኤስ ተጨማሪውን እንደ "A"።

▣**"የአካላችንን መቤዠት"** ይህ ቃል "መልሶ መግዛት" ማለት ነው። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በብ. ኪ. አገልግሎት ላይ የሚውለው በዘመዱ ከባርነት ነጻ የወጣውን ሰው ያመለክታል። ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው የወደቀውን የሰው ልጅ ከኃጢአት ባርነት እግዚአብሔር እንደተቤዠው ለማሳየት ነው። የተከፈለውም ዋጋ ሥጋ የለበሰው ያለ ኃጢአት የሆነው ወልድ ነው። ልዩ ርዕስ 3፡24 ላይ ተመልከት።

ክርስትና እንደ ይሁዲነት (ኢዮብ 14፡14-15፤ 19፡25-26፤ ዳን.12፡2)፣ አማኞች አካላዊ፣ (ዳሩግን ሥጋዊ የማይሆን 1ኛ ቆሮ. 15፡35-49) ዘላለማዊ አካል እንደሚኖራቸው ያስረዳል። የአማኞች መንፈሳዊ አካላት በአዲሱ ዘመን በፍጽምና ይዘጋጃል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጃዊ ኅብረት ያለው።

**8፡24 "በተስፋ ድነናልና"** ይህ አመላካች ተገብሯዊ ያልተጠናቀቀ ቃል ነው። በቁ. 23 እንደተመለከተው ቀጣዩን ደኅንነታችንን፣ ቁ.24 ደግሞ በመንፈስ አማካኝነት ያለፈውን ደኅንነታችንን ያሳያል። አ.ኪ. በርካታ የግስ ጊዜያቶችን ደኅንነታችንን ለመግለጽ ይጠቀማል።

1. ተገብሮ ግስ፣ ሐዋ. 15፡11 (ሮሜ. 8፡24፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ ቲቶ3፡5፤ እና ሮሜ. 13፡11 ያልተጠናቀቀውን ተገብሯዊ ግስ ከወደፊት ጊዜ ጋር ይደባልቀዋል።
2. የተጠናቀቀ ድርጊት (ተገብሮ)፣ ኤፌ. 2፡5፣8
3. የአሁን ጊዜ፣ 1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2፤ 2ኛ ቆሮ.2፡15፤ 1ኛ ጴጥ.3፡21፤ 4፡18
4. የወደፊት ጊዜ (በግስ ጊዜ ወይም በጽሑፋዊ አገባብ)፣ ሮሜ. 5፡9፣10፤ 10፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡15፤ ፊሊጵ. 1፡28፤ 1ኛ ተሰሎ.5፡8-9፤ ዕብ፡ 1፡14፤ 9፡28።

ስለሆነም፣ ደኅንነት በመነሻ የእምነት ውሳኔ ጀምሮ በተከታይ ሂደት በአኗኗር ዘይቤአዊ እምነት አንድ ቀን በፊት ለፊት የሚከወን ይሆናል (1ኛ ዮሐ. 3፡2)።

**8፡25 "ተስፋ"** ከበታች ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ

**ልዩ ርዕስ፡ ተስፋ**

ጳውሎስ ይህን ቃል በተለያዩ ነገር ግን ተመሳሳይነት ባላቸው መልኮች አዘውትሮ ይጠቀማል። ብዙውን ጊዜም ከአማኞች እምነት መደምደሚያ ጋር ይያያዛል (ለምሳሌ 1ኛ ጢሞ. 1፡1)። በዚህም ሊገለጽ የሚችለው እንደ ክብር፣ የዘላለም ሕይወት፣ የደኅንነት ግብ፣ ዳግም ምጽዓት፣ ወዘተ ነው። የፍጻሜው መደምደሚያ ርግጥ ነው፣ የጊዜው ጉዳይ ግን መጻኢና የማይታወቅ ነው። ይህም ብዙውን ጊዜ የሚያያዘው "ከእምነት" እና "ከፍቅር" ጋር ነው (1ኛ ቆሮ. 13፡13፤ 1ኛ ተሰሎ.1፡3፤ 2ኛ ተሰሎ. 2፡16)። የጳውሎስ አጠቃቀም የከፊሉ ዝርዝር፡

1. ዳግም ምጽዓቱ፣ ገላ.5፡5፤ ኤፌ.1፡18፤ 4፡4፤ ቲቶ. 2፡13
2. ኢየሱስ ተስፋችን ነው፣ 1ኛ ጢሞ. 1፡1
3. አማኝ ለእግዚአብሔር ይሰጣል፣ ቆላ. 1፡22-23፤ 1ኛ ተሰሎ. 2፡19
4. ተስፋ ያለው በሰማይ ነው፣ ቆላ. 1፡5
5. በወንጌል መታመን፣ ቆላ. 1፡23፤ 1ኛ ተሰሎ. 2፡19
6. የመጨረሻ ደኅንነት፣ ቆላ. 1፡5፤ 1ኛ ተሰሎ. 4፡13፤ 5፡8
7. የእግዚአብሔር ክብር፣ ሮሜ. 5፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡12፤ ቆላ. 1፡27
8. የአሕዛብ ክርስቶስ መዳን፣ ቆላ. 1፡27
9. የመዳን ዋስትና፣ 1ኛ ተሰሎ. 5፡8
10. የዘላለም ሕይወት፣ ቲቶ 1፡2፤ 3፡7
11. የክርስቲያን እድገት ውጤቶች፣ ሮሜ. 5፡2-5
12. የፍጥረት ሁሉ መቤዠት፣ ሮሜ. 8፡20-22
13. የልጅነት መደምደሚያ፣ ሮሜ. 8፡23-25
14. የእግዚአብሔር ማዕርግ፣ ሮሜ. 15፡13
15. የጳውሎስ መሻት ለአማኞች፣ 2ኛ ቆሮ. 1፡7
16. ብ.ኪ. ለሐ.ኪ. አማኞች እንደ መመሪያ፣ ሮሜ. 15፡4

▣ **"በመቀጠል"** ይህ ቃል እስከ መጨረሻው መቀጠልን እያሳየ በ5:3 እና 15:4-5 ጥቅም ላይ ውሏል። የአማኞች ድኅነት በሂደት በሚገኝ ፍጽምና ሆኖ አንድ ቀን የምንቀዳጀው ነው። መቀጠል (ራዕ. 2:8፣ 11፣ 17፣ 26፤ 3:5፣ 12፣ 21፤ 21:7) ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን መጠበቂያ አስፈላጊ የሆነው የመጥምቃውያንን (ባፕቲስት) "አንድ ጊዜ የዳነ ሁሌም ድኗል" የሚለውን የተጋነነ ቃል ለማመላከት ነው። አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች የሚገለጡት አከራካሪ በሆኑ ጥንድ ሐሳቦች ነው።

| |
|---|
| 8:26–27<br>**[26]እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤[27]ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።** |

8:26 **"በተመሳሳይ መልኩ"** ይህ የመንፈስን የምልጃ አገልግሎት "ከመቃተትና ተስፋ ከማድረግ" ጋር የሚያገናኝ ሲሆን ቁ. 23-25 ተጠቅሷል።

▣ ***"መንፈስም ደግሞ ያግዘናል"*** ይህ የአሁን ጊዜ መካከለኛ አመልካች ነው። እሱም ድርብ ድብልቅ ሆኖ ከ(ቁ. 28) ጋር ተመሳሳይ እና ተጻራሪ ነው። የተሻለ ትርጓሜው "ይይዘናል" ነው። ይህ ቃል የሚገኘው እዚህ ብቻ እንዲሁም ሉቃስ 10፡40 ላይ ነው። ሞላው እውነተኛ እግዚአብሔር ለአማኞች ነው። አብ ወልድን ለሰው ልጆች ብሎ ይሞት ዘንድ ሳከው፣ እሱ አሁን ስለእኛ ይማልዳል (ቁ. 34፤ 1ኛ ዮሐ. 2:1)። መንፈስ የወደቀውን የሰው ልጅ ወደ ክርስቶስ ያመጣና ክርስቶስን በውስጣቸው ያደርጋል (ዮሐ. 16:8-15)። ቢሆንም "ርዳታ" የሚለው ቃል "አንድ ሰውን መደገፍ" ሆኖ ትርጉሙም አማኞችም የመንፈስን ርዳታ ባግባቡ መያዝ ላይ እንዳለባቸው ያመለክታል (ምልጃን)።

**ልዩ ርዕስ፡ በተስፋ የመቀጠል አስፈላጊነት**

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮዎች ከክርስትና ሕይወት ጋር የተጎዳኙት ከማስረዳት አስቸጋሪ ናቸው ምክንያቱም በተለይ በምዕራባውያን አከራካሪ ጥንድ ሐሳቦች በመቅረባቸው ነው። እነዚህ ጥንዶች የሚቃረኑ ይመስላሉ፣ ዳሩግን ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። የምዕራብ ክርስቲያኖች አንደኛውን እውነት እየተቀበሉ ሌለኛውን አንጻራዊ እውነት መተው ወይም ችላ ማለት ያዘወትራሉ። እስቲ ላብራራው።

1. ደኅንነት ኢየሱስን በማመን በሚደረግ መነሻ ውሳኔ ወይስ በሕይወት ዘመን መሰጠት ባለ ደቀ መዝሙርነት?
2. ደኅንነት ከሁሉን ቻይው እግዚአብሔር በሚሆን የጸጋ መመረጥ ወይስ በሰው ልጆች ማመንና ንስሐ መግባት የሚሆን መለኮታዊ መሥዋዕት ምላሽ?
3. ደኅንነት አንድ ጊዜ ከተቀበሉት ሊያጡት የማይቻል ነው ወይስ ቀጣይነት ያለው ትጋት ያሻዋል?

የመቀጠል ጉዳይ ቀጣይነት እንዳለው በቤተክርስቲያን ታሪክ ሁሉ ተመልክቷል። ችግሩ የሚነሣው በሐ. ኪ. ባሉ አከራካሪ አንቀጾች ሁሉ ነው፡

1. በዋስትና ላይ ባሉ ጽሑፎች
   - ሀ. የኢየሱስ ንግግሮች (ዮሐ.6:37፤ 10:28-29)
   - ለ. የጳውሎስ ንግግሮች (ሮሜ. 8:35-39፤ ኤፌ. 1:13፤ 2:5፣ 8-9፤ ፊሊጵ. 1:6፤ 2:13፤ 2ኛ ተሰሎ. 3:3፤ 2ኛ ጢሞ. 1:12፤ 4:18)
   - ሐ. የጴጥሮስ ንግግሮች (1ኛ ጴጥ. 1:4-5)
2. ስለ ቀጣይነት አስፈላጊነት ያሉት ጽሑፎች
   - ሀ. የኢየሱስ ንግግሮች (ማቴ. 10:22፤ 13:1-9፣ 24-30፤ 24:13፤ ማር. 13:13፤ ዮሐ. 8:31፤ 15:4-10፤ ራዕ. 2:7፣ 17፣ 20፤ 3:5፣ 12:21)
   - ለ. የጳውሎስ ንግግሮች (ሮሜ. 11:22፤ 1ኛ ቆሮ. 15:2፤ 2ኛ ቆሮ. 13:5፤ ገላ. 1:6፤ 3:4፤ 5:46:9፤ ፊሊጵ. 2:12፤ 3:18-20፤ ቆላ. 1:23)
   - ሐ. የዕብራውያን ጸሐፊ ንግግሮች (2:1፤ 3:6፣ 14፤ 4:14፤ 6:11)
   - መ. የዮሐንስ ንግግሮች (1ኛ ዮሐ. 2:6፤ 2ኛ ዮሐ.9)
   - ሠ. የአብ ንግግር (ራዕ. 21:7)

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድኅነት የሚነሣው ከፍቅር፣ ከምሕረት፣ እና ከጸጋ ሆኖ ከእውነተኛ አምላክ ነው። መንፈስ ካላሳሰበው በቀር ማንም ሰው ሊድን አይችልም (ዮሐ. 6:44-65)። መለኮት ቀድሞ መጥቶ አጀንዳውን ያኖራል፤ ነገር ግን የሰው ልጆችን የእምነትና ንስሐ የመግባት ምላሽ ከመነሻውም ሆነ በቀጣይነት ይፈልጋል። እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የሚሠራው ኪዳናዊ በሆነ ግንኙነት ነው። መታደልም ሆነ ኃላፊነት ሁለቱም አሉ!

ደኅንነት ለሁሉም የሰው ልጆች የተሰጠ ነው። የኢየሱስ ሞት የሆነው በወደቀው ፍጥረት ኃጢአት ችግር ምክንያት

ነው:: እግዚአብሔር መንገዱን ሰጥቶ በአምሳሉ የፈጠራቸው ሁሉ በኢየሱስ ለገለጠው ፍቅሩ ምላሽ እንዲሰጡ ይሻል:: በዚህ ርዕሰ ጉዳይ በተጨማሪ ለማንበብ ከፈለጉ፣ ካልቫኒያዊ ካልሆነ አስተሳሰብ፣ ቀጣዩን ይመልከቱ፣

1. *ዳሊ ሞዲ፣ የእውነት ቃል፣* ኤርድማንስ፣ 1981 (*ገጽ* 348-365)
2. *ሃዋርድ ማርሻል፣ በእግዚአብሔር ኃይል መጠበቅ፣* ቤታኒያ ኅብረት፣ 1969
3. *ሮበርት ሻንክ፣ በወልድ ያለ ሕይወት፣* ዌስትኮት፣ 1961

*መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ አካባቢ ሁለት የተለያዩ ችግሮችን ያመለክታል:* (1) *ዋስትናን ፍሬ የሌለው ሕይወት ለመኖር እንደማረጋገጫ መውሰድ፣ የግለኝነት ሕይወት እና* (2) *ከአገልግሎትና ከግል ኃጢአት ጋር የሚታገሉትን ማበረታታት:: የዚህ ችግር ስህተተኛ ቡድኖች የተሳሳተ መልዕክት ወስደው በተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጾች ላይ*

▣ **"*መንፈስም ራሱ በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ይማልድልናል*"** *አማኞች በውድቀታቸው ሲያዝኑ መንፈስ ደግሞ ስለእነሱ በመቃተት ይማልዳል:: በተዋጁት ውስጥ መንፈስ ስለእነሱ ይለምናል፣ ኢየሱስም በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ ስለእነሱ ይለምናል (ቁ.* 27፣ 34፤ *ዕብ.* 9:24፤ 1*ኛ ዮሐ.* 2:1)*:: ምልጃው፣ አማኙ ይጸልይ ዘንድ ኃይል ይሰጠዋል (ቁ.* 15፤ *ገላ.* 4:6)*:: ይህ አንቀጽ በጽሑፉ የሚያመለክተው በልሳን ስለ መናገር መንፈሳዊ ስጦታ ሳይሆን ነገር ግን አማኙን ወክሎ መንፈስ ወደ አብ የሚያደርገውን ምልጃ ነው::*

▣ **"*ይማልዳል*"** *ልዩ ርዕስ: የጳውሎስ ሁፐር* (Huper) *ድብልቅን በ*1:30 *ተመልከት::*

**8:27 "*ልብንም የሚመረምረው*"** *ይህ ድጋሚ የሆነ ጭብጥ በብ.ኪ.* (1*ኛ ሳሙ.* 2:7፤ 16:7፤ 1*ኛ ነገሥ.* 8:39፤ 1*ኛ ዜና.* 28:9፤ 2*ኛ ዜና.* 6:30፤ *መዝ.* 7:9፤ 44:21፤ *ምሳ.* 15:11፤ 20:27፤ 21:2፤ *ኤር.* 11:20፤ 17:9-10፤ 20:12፤ *ሉቃ.* 16:15፤ *ሐዋ.* 1:24፤ 15:8)*:: እግዚአብሔር በእርግጥ ያውቀናል ይወደናልም (መዝሙር* 139)*::*

▣ **"*ስለ ቅዱሳን ይማልዳል*"** *የመንፈስ ተግባራት በዮሐንስ* 16:2-15 *በግልጽ ተቀምጧል:: አንደኛውም መማለድ ነው:: "ቅዱሳን" የሚለው ቃል ሁልጊዜ በብዙ ቁጥር ነው፣ ፊሊጵ.* 4:21 *ካለው በቀር፣ እሱም ቢሆን ስለ ሁሉም አማኞች የሚያመላክት ነው:: ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት፣ የክርስቶስ አካላት፣ በግለሰብ አማኞች የተገነባው አዲስ ቤተመቅደስ ናቸው:: ይህ እንግዲህ ከምዕራብ (የአሜሪካ) ግለሰበኝነት ጋር ሥነ መለኮታዊ ሚዛን የሚያሻው ነው:: ልዩ ርዕስ: ቅዱሳን* 1:17 *ይመልከቱ::*

**ልዩ ርዕስ: የመንፈስ አካላዊነት**

ይህ በመጀመሪያ የተጠቀሰው "የመንፈስ ቅዱስ" አካልነት ሲሆን፣ በሮሜ (ስሞቹ የተጠቀሱት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይሆን፣ ቁ. 5:5፤ 9:1፤ 14:17፤ 15:13፣16):: በብ.ኪ. "የእግዚአብሔር መንፈስ" (ማለትም፣ ruach) የያህዌህን ተግባር የመቀዳጀት ኃይል ሲሆን፣ ነገር ግን አካላዊ ለመሆኑ ምንም ፍንጭ የለም (ያም ማለት በብ.ኪ. አንድ መሆን (ዋህድነት):: ቢሆንም፣ በሐ.ኪ. የመንፈስ ሙሉ አካል እና አካላዊነት ማስረጃ ይገኛል::

1. የማይገባ ቃል ይናገሩት ይሆናል (ማቴ. 12:31፤ ማር. 3:29)
2. ያስተምራል (ሉቃስ 12:12፤ ዮሐ.14:26)
3. ምስክርነት አለው (ዮሐንስ 15:26)
4. ይፈርዳል፣ ይመራል (ዮሐንስ 16:7-15)
5. "ማን" ተብሎ ይጠራል (ያም ማለት hos) (ኤፌ. 1:14)
6. ሊያዝን ይችላል (ኤፌ. 4:30)
7. ዝም ሊል ይችላል (1ኛ ተሰሎ. 5:19)

ሥላሴያዊ ጽሑፎች ደግሞ ስለ ሦስቱ አካላት ይገልጻሉ

1. ማቴ. 28:19
2. 2ኛ ቆሮ. 13:14
3. 1ኛ ጴጥ. 1:2

መንፈስ ከሰዎች እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘ ነው

1. ሐዋ. 15:28
2. ሮሜ. 8:26
3. 1ኛ ቆሮ. 12:11
4. አፌ. 4:30
5. 1ኛ ተሰሎ. 5:15

በሐዋርያት ሥራ ገና ከመነሻው ጀምሮ የመንፈስ ሚና አጽንዖት ተሰጥቶታል:: ጰንጠቆስጤ የመንፈስ ሥራ መጀመሪያ ሳይሆን አዲስ ምዕራፍ ነው:: ኢየሱስ ሁሌም መንፈሱ አለው:: የእሱ መጠመቅም የመንፈስ ሥራ መጀመሪያ ሳይሆን አዲስ ምዕራፍ ነው:: ሉቃስ ቤተክርስቲያንን ለስኬታማ አገልግሎት አዲስ ምዕራፍ ያዘጋጃል:: ኢየሱስ አሁንም ተተኳሪ ነው፣ መንፈስም የስኬታማነት አግባብ፣ የአብ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ እና በአምሳሉ የፈጠራቸው የሰው ልጆች ሁሉ መመለስ ግብ ነው!

8፡28 ***"ነገር ሁሉ"*** የጥንታዊ ግሪክ የእጅ ጽሑፎች ሀ እና ለ "እግዚአብሔር ለሁሉም ነገር ምክንያት ነው" የሚል አላቸው፡፡ የወረቀት የእጅ ጽሑፎች ፒ[46] "እግዚአብሔር" "አብሮ እንደሚሠራ" ባለቤት ነው፡፡ በሰዋሰዋዊ አግባብም በቁ. 28 ያለው "መንፈስ" የሚለው ባለቤት የሚቻል ነው (ቁ. 27 እና አ.እ.መ.ቅ እና የተ.እ.መ.ቅ)፡፡ ይህ ቁጥር "ሥቃዮች" ከሚለው በቁ. 17-18፤ እና "መቃተቶች" ከሚለው ቁ. 23 ጋር ይዛመዳል፡፡ ገድ፣ ዕጣ እና ዕድል የሚሉት ነገሮች ከአማኞች ጋር ግንኙነት የላቸውም፡፡

▣ ***"ሁሉም ለበጎ እንዲደረግ"*** ይህ የአሁን ጊዜ አመላካች ነው፡፡ ይህም ድብልቅ እና "ተመሳሳይ" (syn) ነው (ቁ. 26፡፡) ስለሆነም፣ በጥሬ ትርጉም ሲታይ "ሁሉም ነገር በቅንብር አንዱ ካንዱ ተጣጥሞ ለበጎ እንዲቀጥል" የሚል ነው፡፡ በክፉና በሥቃይ ዓለም ይህ ጽንሰ ሐሳብ አስቸጋሪ ነው፡፡ (ሁለት ደጋፊ መጻሕፍት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ፣ *የእግዚአብሔር መልካምነት* በዌንሃም እና በሐናህ ዊዛል ስሚዝ *የክርስቲያን ደስተኛ ሕይወት ምሥጢር) ናቸው፡፡ "መልካም" በሚል እዚህ የሚገለጸው ቁ.29 ላይ* "የልጁን መልክ እንዲመስሉ የወሰናቸውን" ነው፡፡ ክርስቶስን መምሰል ብልጽግና፣ ዝና፣ ጤንነት ማለት ሳይሆን፣ ሊለወጥ የማይቻል ለእያንዳንዱ አማኝ የሆነ የእግዚአብሔር እቅድ ነው፡፡

▣ ***"እግዚአብሔርን ለሚወዱት፣ እንደ ሐሳቡም ለሚጠሩት"*** እነዚህ ሁለት የአሁን ጊዜ ድርጊትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ናቸው አማኝ በቀጣይነት ሕይወትን እንዲያይና በዙሪያው ያለውን በመልካም ብርሃን እንዲመለከት የሚያስችሉት (ቁ. 15)፡፡ በድጋሚ መንታዎቹን ኪዳናዊ ገጽታዎች የሰው ልጅን ነጻነት ("ፍቅር") እና የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ("የጠራቸውን") የሚለውን አስተውል፡፡

8፡28–30

**[28]እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡[29]ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰኖአልና፤ [30]አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው፡፡**

8፡29-30 በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ያሉት የገቢር የአሁን አመላካች ግሶች ናቸው፡፡ ቀደም ካለው ጊዜ አንሥተው ማለቂያ እስከ ሌለው ጊዜ ሰንሰለታዊ ትስስር ይዘዋል፡፡ እግዚአብሔር ያውቀናል እንዲሁም ለእኛ ነው እኛም ከእሱ ጋር እንድንሆን ይሻል፡፡ ይህ እንግዲህ የተጠቃለለ እንጂ ግለሰባዊ ጽሑፍ አይደለም፡፡ የመጨረሻው የክብር ድርጊት ወደፊት ነው፣ ነገር ግን በዚህ ጽሑፍ ላይ እንደተቀዳጁት ክስተት ቀርቧል፡፡

8፡29 "አስቀድሞ ***ያወቃቸው"*** ጳውሎስ ይህንን ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅሟል፣ እዚህና 11፡2 ላይ፡፡ በ11፡2 ላይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ቀድሞ የነበረውን ኪዳናዊ ፍቅር ያሳያል፡፡ "ያወቀው" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ጓደኝነትን፣ ግለሰባዊ ቅርርብን ያሳያል እንጂ ስለ አንድ ግለሰብ ያለ እውነታን አያመለክትም (ዘፍ. 4፡1፤ ኤር. 1፡5)፡፡ እዚህ በሁነቶች ሰንሰለት ተካትቷል (ቁ. 29-30) ፡፡ ይህ ቃል ቀድሞ ከተወሰነው ጋር ይገናኛል፡፡ ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር ቀድሞ አዋቂነት የመመረጥ መነሻ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲያ ቢሆን ኖሮ ምርጫ በወደቀው ሰው መጻዒ ዕድል ማለትም በሰው ሥራ ይሆን ነበር፡፡ ይህ ቃል በሐዋ. 26፡5፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡ 2፣ 20 እና 2ኛ ጴጥ. 3፡17 ላይ ይገኛል፡፡

▣ ***"ቀድሞ የታወቀ"*** "ቀድሞ የታወቀ" ወይም "ቀድም የተወሰነ" የሚሉት ቃላት ሁለቱም "በፊት" ከሚለው መስተጻምር ጋር ድብልቆች ናቸው፤ ስለሆነም "ቀድሞ ማወቅ" በሚል መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡ "ወሰኑን ቀድሞ ማከናወን" ወይም "ፈቱ አመልክቶ መጨረስ" ማለት ነው፡፡

የተወሰኑት አንቀጾች ቀድሞ መወሰንን በተመለከተ በአ.ኪ. ሮሜ. 8፡28-30፤ ኤፌ. 1፡3-14 እና ሮሜ. 9 ናቸው፡፡ እነዚህ ጽሑፎች በግልጽ እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ እሱ የሁሉም ነገሮች አጠቃላይ ተቆጣጣሪ ነው፣ የሰዎችንም ታሪክ ጭምር፡፡ አሁን መለኮታዊ የመዋጀት እቅድ አለ፣ ቀደም ባለው ጊዜ ይሠራ የነበረ፡፡ ቢሆንም ይህ እቅድ አሻሚ ወይም መራጭ አይደለም፡፡ መሠረት ያደረገውም በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ቀድሞ አዋቂነት ላይ ሳይሆን ነገር ግን በእሱ የማይለወጥ ባሕርያዊ ፍቅር፣ ምሕረት እና የማይገባን ጸጋ ነው፡፡

እኛም ከምዕራባዊ (አሜሪካ) ግለሰበኝነት ወይም ወንጌላዊ ቅንዓት ይህን አስደናቂ እውነት እንዳንቀይረው (እንዳንኩለው) ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጽንፈኝነት ታሪካዊነትን ከመያዝ፣ ከሥነ መለኮታዊ ግጭቶች ማለትም በአውግስቲንና በፔሊገስ ወይም በካልቫኒያዊነትና በአርሜኒያዊነት መካከል ካሉት ነቅተን ልንጠበቅ ይገባል፡፡

ቀድሞ የታወቀ ማለት፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ጸጋ፣ እና ምሕረት የመወሰን አስተምህሮት ማለት አይደለም፤ ወይም ደግሞ ከወንጌል ጥቂት መቀነስ ማለት አይደለም፡፡ እሱ ማለት አማኞችን ለማጽናት የዓለም አመለካከታቸውን ለመቅረጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሁሉም የሰው ልጅ ነው (ዮሐ. 3፡16፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡4፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡9)፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በመቆጣጠር ላይ ነው፡፡ ከእሱ ማን ወይም ምን ሊለየን ይችላል (ሮሜ. 8፡31-39)? ቀድሞ የታደለ፣ ሕይወትን ለማየት አንድና ሁለት መልኮችን ይይዛል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ታሪክ አሁን እንደሆነ ይመለከታል፡፡ ሰዎች በጊዜ የተወሰኑ ናቸው፡፡ የእኛ አስተሳሰብና የአእምሮ ችሎታዎች የተወሰኑ ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ተቃርኖ የለም፡፡ ኪዳናዊ መዋቅር ነው፡፡ ይህም ሌለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ምሳሌ ሆኖ ክርክራዊነት

ያለው ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ብዙውን ጊዜ የሚቀርቡት ከተለያየ ያስተሳሰብ አንጻር ነው። ብዙ ጊዜ አያዎአዊ ሆነው ነው የሚቀርቡት። እውነት፣ በእነዚህ ተቃራኒ መሰል ጥንዶች መካከል ያለውን ሚዛን ይጠብቃል። አንዱን እውነት ብቻ መዝዘን በማንሣት ልዩነቱን ማስቀረት የለብንም። የትኛውንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በመነጠል በራሱ ክፍል ማድረግ የለብንም።

እዚህ ላይ መጨመር የሚገባው ጠቃሚ ነገር የመመረጥ ግብ ስንሞት ወደ መንግሥተ ሰማያት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን አሁንም ክርስቶስን መምሰል ነው (ኤፌ. 1:4፤ 2:10)! እኛ የተመረጥነው "ቅዱስና ያለ ነውር" እንድንሆን ነው። እግዚአብሔር የመረጠን ሊለውጠን፣ በዚያውም ሌሎች ለውጡን አይተው በክርስቶስ ለእሱ በእምነት ምላሽ እንዲሰጡ ነው። ቅድመ እውቅና ግለሰባዊ ሞገስ ሳይሆን ኪዳናዊ ኃላፊነት ነው!

▣ **"የልጁን መልክ ይመስሉ ዘንድ አስቀድሞ ወስኗል"** ይህ የዚህ አንቀጽ ዋነኛው እውነት ነው። ይህ የክርስትና ግብ ነው (ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 4:13)። ቅድስና የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ለእያንዳንዱ አማኝ። የእግዚአብሔር ምርጫ ክርስቶስን ለመምሰል ነው (ኤፌ. 1:4)፣ ሌላ አቋም አይደለም። የእግዚአብሔር አምሳል ለሰዎች በተፈጥሮ የተሰጠው (ዘፍ. 1:26፤ 5:1፣ 3፤ 9:6) ሊመለስ ነው (ቆላ. 3:10)። በ8:21 ያለውን ማስታወሻ እና ልዩ ርዕስ፡ መጠራትን 1:6 ላይ ይመልከቱ።

▣ **"እሱ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ"** በመዝሙር 89:27 "በኩር" ለመሲሕ የተሰጠ ማዕርግ ነው። በብ.ኪ. የበኩር ወንድ ልጅ ቀዳሚ መብትና ሞገስ አለው። ቃሉ በቆላ. 1:15 ኢሱስ የፍጥረት በኩር መሆኑን ያሳያል፣ ደግሞም ቆላ. 1:18 እና ራዕ. 1:5 የኢየሱስን የትንሣኤ ልዕልና ያሳያል። በዚህ ጽሑፍ አማኞች በእሱ በኩል ወደእሱ ክብር መጥተዋል!

ይህ ቃል የኢየሱስን ስጋ መልበስ አያመላክትም፣ ነገር ግን የአዲሱ ዘር ራስ መሆኑን እንጂ (5:12-21)፣ የቀጣዮቹ የመጀመሪያ፣ የእምነታችን መፈተኛ ነበልባል፣ የአብ የበረከት መስመር ለእምነት ቤተሰቦች! ቀጥሎ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ።

**ልዩ ርዕስ፡ ብኩርና**

ይህ "ብኩርና" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ የተለያዩ አግባቦች ጥቅም ላይ ውሏል።

1. ብ. ኪዳናዊ ዳራው የሚያመለክተው የበኩር ልጅ በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ቅድመ አመላካችነት ነው (መዝ. 89:27፤ ሉቃስ 2:7፤ ሮሜ. 8:29፤ ዕብ. 11:28)
2. በቆላ. 1:15 ያለው አግባብ ኢየሱስ የፍጥረት በኩር እንደሆነ የሚገልጸው በብ.ኪ. ምሳ. 8:22-31፣ ወይም በመፍጠር ላይ የእግዚአብሔር ወኪል (ዮሐንስ 1:3፤ 1ኛ ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:15-16፤ ዕብ. 1:2) በመጥቀስ ይሆናል።
3. በቆላ. 1:18፤ 1ኛ ቆሮ. 15:20 ያለው አግባብ (እና እዚህ) የሚያሳየው ኢየሱስ ከሙታን በመነሣት በኩር መሆኑን ነው።

እሱ የብ.ኪ. ማዕርግ ሆኖ ለመሲህ የተሰጠ ነው (መዝ. 89:27፤ ዕብ. 1:6፤ 12:23)። እሱም የኢየሱስን ቀዳሚነትና ማዕከላዊነት በርካታ ገጽታዎች የሚያዋሕድ ነው። በዚህ ጽሑፍ ቁ.3 እና ቁ.4 ይበልጥ ይስማማዋል።

8:30 "ከበረ" እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የሚገለጸው "ክብር" በሚለው ቃል ነው። ሥርወ- ቃሉ የመጣው ከንግድ ሲሆን ትርጉሙም "ከባድ" ሆኖ እንደ ወርቅ ያለ ውድነትን ያሳያል። በ3:23 ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ። ከሥነ-መለኮት አንጻር እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ልጅ እየዋጀ ያለው በቁ. 29-30 በተዘረዘሩት ተከታታይ ደረጃዎች ነው። የመጨረሻው ደረጃም "ክብር" ነው። ይህም የአማኞች ፍጹም ድኅነት ይሆናል። በትንሣኤ ቀንም ይከሰታል፣ አዲሱን መንፈሳዊ አካል ሲጎናጸፉ (1ኛ ቆሮ. 15:20-58) እናም ከእውነተኛው አምላክና እርስ በርሳቸውም ሙሉ አንድነት ይኖራቸዋል (1ኛ ተሰሎ. 4:13-18፤ 1ኛ ዮሐ. 3:2)።

8:31–39

**[31]እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?[32]ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?[33]እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?[34]የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።[35]ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?[36]ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።[37]በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።[38]ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥[39]ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።**

**8:31 "እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን"** ይህ የጳውሎስ ተወዳጅ ሐረግ ሲሆን ካቀራረቡ ከረር ማለትን ያንጸባርቃል (ቁ. 3:5፤ 4:1፤ 6:1፤ 7:7፤ 9:14፣30)። ይህ ጥያቄ ቀደም ሲል ከተሰጡት እውነታዎች ጋር ይገናኛል። ምን ያህል ወደ ኋላ እንደሚያጣቅስ አይለይም። ከ3:21-31 ወይም 8:1 ወይም 8:18 ያጣቅስ ይሆናል። "እንግዲህ" የሚለውን 8:1 ስለ ተጠቀመ እና በጽሑፉም፣ 8:18 ምናልባት ጥሩ ግምት ይሆናል።

▣ **"ከ"** ይህ 1ኛ ደረጃ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን እውነትነቱ ሊታይ የሚችለው ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ከጽሑፋዊ አግባቡ ሊሆን ይችላል። የሚገርመው፣ ከኃጢአት ጋር በምናደርገው ትግል ሁሉ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ነው!

▣ **"ማን ይቃወመናል"** "ማን" የሚለው ተውላጠ ስም በቁ. 33፣34 እና 35 ተደግሟል። የሚያመለክተውም እስከ 16:20 ድረስ በስሙ ያልተጠቀሰውን ሰይጣንን ነው። ይህ አንቀጽ፣ ከ31-39፣ የብ.ኪ. የነቢያትን የአጻጻፍ ስልት፣ ማለት የፍርድ ቤት ጉዳይን ያሳያል (ሚክ. 1 እና 6)። ያህዌ ሕዝቡን በመንፈሳዊ ምንዝርናቸው ወደ ፍርድ ቤት ሲያቀርብ። ከኢሳ. 50:8-9 ጋር ይጣቀሳል።

የፍርድ ቃላት የሆኑትን: "ተቃውሞ" ቁ.31፤ "ክስ" ቁ.33፤ "ከወንጀል ነጻ" ቁ.33፤ "ጥፋተኝነት" ቁ.34፤ እና "መማለድ" ቁ.34 ያጢኑ። ክርስቶስ ተከላካይ ጠበቃ ነው። ሰይጣን ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ነው (ነገር ግን ጸጥ ብሏል።) መላእክት ፍርድ ቤቱን እንደ ታዛቢ ሞልተውታል (1ኛ ቆሮ. 4:9፤ ኤፌ. 2:7፤ 3:10)።

▣ **"ለገዛ ልጁ እንኳ ያልራራለት"** እግዚአብሔር አብ ለወደቀው የሰው ልጅ ምርጡን ነው የሰጠው። አሁንም አማኞችን አይተዋቸውም ወይም አሳንሶ አይሰጣቸውም (ዮሐንስ 3:16፤ ሮሜ. 5:8)። እዚህ ጋ ያለው በደንብ መረዳት ያልተቻለው ጽንሰ ሐሳብ የብ. ኪ. እግዚአብሔር ጨካኝነትና የኢየሱስ አፍቃሪነት ነው! ይህ የመጨረሻ ጸጋ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው ቃል በዘፍ. 22:12፣ 16 ላይ ተንጸባርቋል። ራቢዎች (የአይሁድ መምህራን) ይህንን የብ.ኪ. አንቀጽ ለአብርሃም ዘሮች ተለዋጭ መታረቂያ (ካሳ) መስጠት ለሚለው አስተምህሮአቸው ማጠናከሪያ ያውሉታል።

▣ **"ነገር ግን ስለ ሁላችንም አሳልፎ ሰጠው፣"** በዚህ ጽሑፍ "ሁሉም" የሚለው ቃል ዋና ነው። ኢየሱስ የሞተው ለዓለም ኃጢአት ነው (ሉቃስ 2:10-11፤ ዮሐንስ 3:16፤ 4:42፤ 11:51፤ 1ኛ ጢሞ. 4:10፤ 1ኛ ዮሐንስ 2:2፤ 4:14)። እሱም የአዳም-ኢየሱስን ምድብ በ5:12-21 ያለውን ያንጸባርቃል። የኢየሱስ ሞት የኃጢአትን ችግር አስወግዷል። አሁን ያለው የ"እመንና ተቀበል" ችግር ነው።

▣ **"ሁሉንም ነገር በነጻ ሰጠን"** ይህ ግስ ከግሪክ ሥረወ-ቃል ሲሆን ጸጋ ማለት ነው። "ሁሉም ነገር" የሚያመላክተው ቁ.17ን ነው፣ በ3:24 ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

**8:33-34 "ክስ... ከክስ ነጻ... ጥፋተኛ... መማለድ"** እነዚህ ሁሉ ሕጋዊ ቃላት ናቸው። ቁጥር 31-39 በሰማይ ያለውን የፍርድ ቤት ትእይንት ያሳያል። ይህም ምናልባት ከኢሳይያስ 50:8-9 ጋር ይጣቀሳል።
**8:33 "በእግዚአብሔር የተመረጠ"** ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ሲሆን ለሰው ልጆች የተሰጠ ነው (ባርዝ)። በዚህ እውነት ግልጽ እና የተሟሉት አንቀጾች በብ.ኪ. ኤፌ. 1:3-4፤ እና ሮሜ. 9:14-26 ናቸው። እግዚአብሔር ኢየሱስን መረጠው የሰው ልጆችን ሁሉ ይመርጥ ዘንድ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር "አዎ" ነው፣ ለወደቀው የሰው ልጅ "አሉታ!

**ልዩ ርዕስ: መመረጥ /ቅድመ መታደል እና የሥነ-መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት**

መመረጥ የሚያስደንቅ መሠረተ እምነት ነው። ቢሆንም በልዩ ውዴታ የሆነ ጥሪ አይደለም፣ ነገር ግን መተላለፊያ መስመር ለመሆን፣ ለሌሎች የመዋጀት እቃ ወይም ምክንያት ለመሆን ነው! በብሉይ ኪዳን ቃሉ በመጀመሪያ ለአገልግሎት፤ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በቅድሚያ ከአገልግሎት ለሚወጣ ደኅንነት ይውላል። መጽሐፍ ቅዱስ ተቃርኖ መሰሉን በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለውን አያስታርቅም፣ ሁለቱንም ያስረግጣቸዋል እንጂ! ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርክሮች ጥሩ ምሳሌ፣ ሮሜ 9 በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እና ሮሜ 10 በሰው ልጆች ምላሽ አስፈላጊነት (10:11፣13) ናቸው።

የዚህ ሥነ-መለኮታዊ ክርክር ቁልፉ ምናልባት ኤፌሶን 1:4 ላይ ይገኛል። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ሲሆን እናም ሁሎችም በእሱ በኩል ይመረጣሉ (ካርል ባርዝ)። ኢየሱስ ለወደቀው የሰው ልጅ መሻት "አዎ" ነው፣ (ካርል ባርዝ)። ኤፌሶን 1:4 ደግሞ ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ይረዳል፣ ቀድሞ መታወቅ መንግሥተ ሰማያት እንዳልሆነ በመግለጽ ነገር ግን ቅድስና (ክርስቶስን መምሰል) እንደሆነ። ብዙውን ጊዜ በወንጌል ጠቀሜታዎች እየተማረክን ኃላፊነትን እንዘነጋለን! የእግዚአብሔር ጥሪ (ምርጫ) ለአሁን ጊዜም ሆነ ለዘላለምም ጭምር ነው!

አስተምህሮዎቹ ከሌሎቹ እውነቶች ጋር ይገናኛሉ፣ በተናጠል ሳይሆን፣ በማይዛመዱ እውነቶች። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ኅብረ ከዋክብትና ነጠላ ኮከብ ነው። እግዚአብሔር እውነትን የሚያሳየው በምስራቃዊ እንጂ በምዕራባዊ የጽሑፍ ዘውግ አይደለም። በክርክራዊ ተቃርኖ መልክ የቀረቡትን አይአዎአዊ ጥንድ መሠረተ እምነት ነክ እውነቶች ልናስወግዳቸው አይገባም:

1. ቀድሞ መታወቅ እና የሰው ነጻ ፍቃድ

2. የአማኞች ደኅንነት እና የጥረት አስፈላጊነት
3. የውርስ ኃጢአት እና የፍቃድ ኃጢአት
4. ኃጢአት አልባነት (ፍጽምና) እና በጥቂት ኃጢአት መፈጸም
5. መነሻ የወዲያውኑ ጽድቅና እና ቅድስና እና ቀጣይነት ያለው ቅድስና
6. ክርስቲያናዊ ነጻነት እና ክርስቲያናዊ ኃላፊነት
7. የእግዚአብሔር ወሰንየለሽነት እና የእግዚአብሔር የተለየ ግዛት (?)
8. የእግዚአብሔር መጨረሻ አይታወቄነት እና እግዚአብሔር በቃሉ መታወቁ
9. የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንደሆነ እና ወደፊት የምንቀዳጀው
10. ንስሐ እንደ እግዚአብሔር ስጦታ እና ንስሐ እንደ አስፈላጊ የሰዎች ኪዳናዊ ምላሽ
11. ኢየሱስ እንደ መለኮት እና ኢየሱስ እንደ ሰው
12. ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ እና ኢየሱስ እንደ አብ ረዳትነት

የ "ኪዳን" ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ የሚያስተባብረው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ሁልጊዜ መነሣሣቱንና ጉዳዩን የሚያነሣው እሱ በመሆኑ) እና ከሰዎች የሚጠበቀውን ፍቃደኝነትና ቀጣይነት ያለው የንስሐ፣ የእምነት ምላሽ ነው። የጽሑፉን አያዎ አንዱን ጎን ብቻ ከማረም እና ሌላውን ከማንኳሰስ ይጠበቁ! የራስዎን ተወዳጅ መሠረተ እምነት ወይም የሥነ መለኮት ሥርዓት ብቻ አይመልከቱ!

8:34 ይህ ቁጥር የኢየሱስን አብዛኛዎቹን አገልግሎቶች ይዘረዝራል (1) ሞቷል፣ (2) ተነሥቷል፣ (3) በእግዚአብሔር ቀኝ ነው፣ እናም (4) ስለ አማኞች ያማልዳል።
የኢየሱስ ሞት የእኛን የኃጢአት ዕዳ ከፍሏል (ኢሳይያስ 53፤ ማርቆስ 10:45፤ 2ኛ ቆሮ. 5:21)። የኢየሱስ ትንሣኤ የሚያሳየው አብ የወልድን አገልግሎት መቀበሉን ሲሆን በስደትና በሞት ላይ ተስፋን ይፈነጥቃል። የኢየሱስ መክበር በአብ ቀኝ መቀመጥ እና ለአማኞች መማለድ የእምነትን መልካም ተጋድሎ ያደርጉ ዘንድ ብርታትን ይሰጣቸዋል።

▣ **"በእግዚአብሔር ቀኝ"** ይህ ሥነ-ሰዋዊ ዘይቤ ነው። እግዚአብሔር ግዘፍ አካል የለውም። "መንፈስ" ነው። ይህ ዘይቤ የሚያሳየው የኃይልን ስፍራ ፣ ሥልጣንና ልዕልናን ነው። ጳውሎስ ገለጻውን አዘውትሮ አልተጠቀመም (ኤፌ. 1:20፤ ቆላ. 3:1)። ጳውሎስ ምናልባት ከጥንት ክርስቲያን ጸሎተ ሃይማኖት ላይ ጠቅሶት ይሆናል፣ ቁጥር 34 (ፊሊጵ. 2:6፤ 1ኛ ጢሞ. 3:16)።

▣ **"ይማልዳል"** የኢየሱስ አገልግሎት ቀጥሏል። ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል (ዕብ. 4:4-16፤ 7:25) መንፈስ እንደሚያደርገው (ቁ. 26-27)። ይህ "ጰራቅሊጦስ" ከሚለው ቃል ነው፣ ማለትም ለመንፈስ ከተጠቀሰው በዮሐንስ 14:16 እና ስለ ወልድ በ1ኛ ዮሐንስ 2:1 ከተጠቀሰው። ይህም ሌለኛው ጠቃሽ ዘይቤ፣ መከራ የሚቀበለውን አገልጋይ መዝሙር (ኢሳ. 53:12) ያመለክታል።

8:35 **"የክርስቶስ ፍቅር"** ይህ ተሳቢ ወይም ባለቤት ነው። ይህም ወይም (1) ክርስቶስ ለአማኞች ያለውን ፍቅር ወይም (2) አማኞች ለክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር ሊሆን ይችላል። ቁጥር 1 በዚህ ጽሑፍ ይበልጥ ይስማዋል (እናም 2ኛ ቆሮ 5:14) ምክንያቱም የአማኞች ፍቅር ለክርስቶስ ይኖራልም አይኖርምም፣ ነገር ግን ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር ርግጠኛና የጸና ነው።

እዚህጋ የግሪክ የብራና ጽሑፍ አለ ከዚህ ሐረግ ጋር በተለየ መልኩ የሚገናኝ። የጥንታዊው ግሪክ ጽሑፍ ያለው "የእግዚአብሔር ፍቅር" (MS ?) ነው። አንድ ጥንታዊ ጽሑፍ አንድ ላይ ያጣምራቸዋል፣ "በክርስቶስ ያለ የእግዚአብሔር ፍቅር" (MS B)። ዩቢኤስ አዋሐጆች "የኢየሱስ ፍቅር" እና "A" ርግጠኝነትን ያሳያል። እሱም በMSS C,D,F,G, እና በአብዛኛው የድሮ የላቲን ቅጂዎች እና ቫልጌቲ እና ፔሺታ ላይ ይገኛል።

▣ **"መከራ፣ ወይም ጭንቀት፣ ወይም ስደት ቢሆኑ"** ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ችግሮች ይገጥማቸዋል፣ ዳሩግን እነዚህ ችግሮችም ሆኑ የክፉ ኃይላት ከእግዚአብሔር ሊለዩአቸው አይችሉም። ልዩ ርዕስ፡ መከራን በ5:3 ላይ ይመልከቱ።

8:36 ይሄ ጥቅስ ደግሞ ከመዝ. 44:22 ነው። በዚህ መዝሙር እግዚአብሔር የተጎዳ ሕዝቡን እንዲታደግ ይጠራል።

8:37

| | |
|---|---|
| አ.አ.መደ.መ.ቅ፣ | **"ነገር ግን በዚህ ሁሉ ሳይቋቋሙን አሸንፈናል"** |
| አ.ኪ.ጀ.ት | **"በዚህ ሁሉ ግን ከአሸናፊዎች እንበልጣለን"** |
| አ.የተ.መደ. ትር. | **"አይደለም፣ በዚህ ሁሉ ግን ከአሸናፊዎች እንበልጣለን"** |
| የአሁ.እ.ትር. | **"አይደለም፣ በዚህ ሁሉ ግን በእሱ በኩል ፍጹም ድልን ተቀዳጅተናል"** |
| ኢየ. መ.ቅ. | **"እነዚህን ፈተናዎች አልፈን ነው ያሸነፍነው"** |

ይህ ነው "ማሸነፍ" ለሚለው ቃል የተጠናከረ መልኩ። ጳውሎስ ይህንን ቃል የወጣው (huper + nikao) ነው። ይህ አስደናቂ ድብልቅ ዘይቤ ነው፣ "አሸናፊ በጎች።" አማኞች በክርስቶስ አሸናፊዎች ናቸው (ዮሐንስ 16፡33፤ 1ኛ ዮሐንስ 2፡13-14፤ 4፡4፤ 5፡4)። ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ የሁፐር (Huper) ድብልቅ አጠቃቀም 1፡30 ይመልከቱ።

▣**"በእርሱ በወደደን"** ይህ ተውላጠ ስም አብን ወይም ወልድን ያመላክታል።

**8፡38 "ተረድቻለሁ"** ይህ የአሁን ጊዜ ገቢር አመልካች ሲሆን፣ ትርጉሙም "ቀደም ሲልም አሁንም እየተረዳሁ ነኝ" ነው።

▣**"መላዕክት"** ራቢዎች (የአይሁድ መምህራን)፣ መላዕክት በእግዚአብሔር ፍቅር እና ለሰው ልጆች ባለው አትኩሮት ይቀናሉ ብለው ያስባሉ፤ ስለሆነም በእሱ ደስ አይሰኙም። የግኖስቲክ የሐሰት መምህራን ደግሞ ደኅንነት ሊገኝ የሚችለው በተለየ የይለፍ ቃል በባላንጣ መላእክት ክልል ነው ይላሉ (ቆላ. እና ኤፌ.)።

ጳውሎስ ስለ መላእክት በተጠቀመባቸው ቃላት ላይ፣ ጆርጅ ኢልደን ላድ ደኅና ማጠቃለያ ፣ *የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት* በሚለው ላይ ይገኛል፡

"ጳውሎስ ጥሩ እና መጥፎ መላእክት በማለት ብቻ ሰይጣንንና አጋንንትን አይገልጽም፤ ሌሎች ቃላትንም የመላዕክታዊ መናፍስትን ማዕርግ ለመለየት ይጠቀማል። ቃላቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡

'ገዢ' [ሊቀ] 1ኛ ቆሮ. 15፡24፤ ኤፌ. 1፡21፤ ቆላ. 2፡10

'ገዢዎች' [ሊቆች፤ የተ.መደ.ትር፣ "ገዢዎች"]፣ ኤፌ. 3፡10፤ 6፡12፤ ቆላ. 1፡16፤ 2፡15፤ ሮሜ. 8፡38

'ባለ ሥልጣን' [? ፤ ]፣ 1ኛ ቆሮ. 15፡24፤ ኤፌ. 1፡21፤ ቆላ. 2፡10

'ሥልጣናት' [? ፤ የተ.መደ.ትር፣ "ሥልጣናት"]፣ ኤፌ. 3፡10፤ 6፡12፤ ቆላ. 1፡16፤ 2፡15

'ኃይል' [ኃይል] 1ኛ ቆሮ. 15፡24፤ ኤፌ1፡21

'ኃይላት' [ኃይላት]፣ ሮሜ. 8፡38

'ዘውዶች' [? ] ቆላ. 1፡16

'ጌትነት' [? ፣ የተ.መደ.ትር፣ "ግዛት"]፣ ኤፌ 1፡21

'ጌቶችነት' [? ]፣ ቆላ. 1፡16

'የዚህ የጨለማ ዓለም ገዢዎች፣' ኤፌ. 6፡12

'በሰማያዊ ስፍራ ያለ የክፋት መንፈሳዊ ሠራዊት፣' ኤፌ. 6፡12

'የጨለማው ባለ ሥልጣናት፣' ቆላ. 1፡13

'የተሰየመ ስም ሁሉ' ኤፌ. 1፡21

'ሰማያዊ፣ ምድራዊ፣ እና ከሚታወቀው በላይ የሆኑ ፍጥረታትንም፣' ፊሊጵ. 2፡10" (ገጽ 401)።

የወደቁ የብ.ኪ. መላእክት ከሐ.ኪ. አጋንንት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ቀጥተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የለም። ብዙዎች ፍጹም ተመሳሳይ እንደሆኑ ያስባሉ። ሆኖም በአይሁድ የትንቢት ሥነ-ጽሑፍ፣ አጋንንት የኒፊሊም መንፈስ የሆኑት በዘፍጥረት 6 የሚገኙትና ግማሽ መላእክት ግማሽ ሰው የሆኑት ናቸው። አካላቸው በጥፋት ውኃ ወድሟል። ስለሆነም አካላቸውን ይሻሉ! ይህ እንግዲህ መላምት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት መጀመሪያ ያሉብንን ጥያቄዎች በሙሉ አይመልስልንም፤ የእሱ ተግባር የሰው ልጆችን መዋጀት እንጂ ሁሉን ማሳወቅ አይደለም።

▣ **"ሥልጣናት... ኃይላት"** ይህ የሚያመለክተው (1) የዚህ ዘመንን የክፉ መላእክት ወይም የአጋንንት ኃይላት (ኤፌ. 2፡2፤ 6፡12፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡24፤ ቆላ. 1፡16)፣ ወይም (2) የወደቀውን ዓለም አካላዊ መዋቅር ይሆናል (ሃይማኖት፣ መንግሥት፣ ትምህርት፣ ሕክምና ወዘተ)፣ ይህም የወደቀውነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ውጭ እንደ ወደደው እንዲሆን (ሄንድሪከስ ቢርክሆፍ፣ *ሥልጣናትና ኃይላት*) በ13፡1 ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ።

**ልዩ ርእስ፡ አርኬ ARCHE**

"ግዛት" የሚለው ቃል የግሪኩን ቃል አርኬ (ARCHE) ማለት ሲሆን፣ ትርጉሙም የአንድ ነገር "መጀመሪያ" ወይም "ጥንት" ማለት ነው።

1. የፍጥረታት የአጀማመር ሥርዓት (ዮሐንስ 1፡1፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡1)
2. የወንጌል መጀመሪያ (ማርቆስ 1፡1፤ ፊሊጵ. 4፡15)
3. የመጀመሪያዎቹ የዓይን ምስክሮች (ሉቃስ 1፡2)

1. የመጀመሪያ ምልክቶች (ዮሐንስ 2፡11)
2. የመጀመሪያ መርሖዎች (ዕብ. 5፡12)
3. የመጀመሪያ ዋስትና/መተማመኛ (ዕብ. 3፡14)

ይህም "ግዢ" ወይም "ሥልጣን" በሚል ጥቅም ላይ ውሏል።

1. በሰው ልጆች ላይ የሚገዙ አለቆች
   ሀ. ሉቃስ 12፡11
   ለ. ሉቃስ 20፡20
   ሐ. ሮሜ 13፡3፤ ቲቶ 3፡1

2. የመላእክት ሥልጣናት
ሀ. ሮሜ. 8፡38
ለ. 1ኛ ቆሮ. 15፡24
ሐ. ኤፌ. 1፡21፤ 3፡10፤ 6፡10
መ. ቆላ. 1፡16፤2፡10፣15

እነዚህ የሐሰት ምምህራን ሁሉንም አለቆች ይዘልፋሉ፤ ምድራዊዎቹንም ሆነ ሰማያዊዎቹን። እነሱ ለሞራል ግድ የሌላቸው ናቸው። ራሳቸውንም ሆነ ፍላጎታቸውን ከእግዚአብሔር፣ ከመላእክት፣ ከሲቪል ባለሥልጣናት እና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስቀድማሉ።

8፡9 **"ከፍታም ቢሆን ዝቅታ"** እነዚህ ቃላት ጥቅም ላይ የሚውሉት የክዋክብትን ከፍታና ዝቅታ ለማመልከት ሲሆን፣ የሰዎችን ሕይወት የሚቆጣጠሩ አማልክት እንደሆኑ ይታመኑ ነበር (በሥነ-ፈለግ) (በሐሳበ- ክዋክብት)። ቆይቶም ሞያዊ ቃላት ሆነው የግኖስቲዝም የሃይማኖት ሕጸጽ (ጉድለት) ኃጢአታዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚያመጡ ለመላእክት ደረጃዎች፣ ከቅዱስ ጣዖት እና ከአናሳ ጣዖት መሐል ያለውን ያሳያል።

▣ **"ሌላም ፍጥረት ቢሆን"** ይህ በጥሬ ትርጉሙ "ሌላ ዓይነት ፍጥረት" ማለት ነው። ጽሑፉ የሚያስፈልገው ለመላእክት ኃይላት ተጨማሪ ማጣቀሻነት ነው። በግሪክ መስተጻምር መካከል *heteros*፣ አንደኛው ልዩ ዓይነት ሲሆን፣ ደግሞም *allos*፣ ሌላው ተመሳሳይ ሆኖ ከኮኒ ግሪክ ከአገልግሎት ውጭ ሆኗል፤ ዳሩግን ይህ ጽሑፍ የተወሰኑ ልዩነቶች እንዳሉ ያሳያል።

▣ **"ቢሆን... ወይም... ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም"** እንዴት ያለ ለዋስትና የሆነ ከባድ ቃል ነው። ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው ኩነኔ የለም በሚል ሆኖ የሚደመድመው ደግሞ አይለየንም በሚል ነው። የአማኝን ደኅንነት ማንም ሊወስድ አይችልም። ቢሆንም ማንም ቢሆን ሁለቱንም መነሻውን (3፡21-31) እና ቀጣይነትን (ምዕራፍ 4-5) መገንዘብ ይኖርበታል። መንፈስ ቁልፉ ሲሆን፣ ነገር ግን የታዘዘ ሁኔታዊና ኪዳናዊ ኃላፊነት አለ። ንስሐ እና እምነት ያስፈልጋሉ (ማርቆስ 1፡15፤ ሐዋ. 3፡16፣19፤ 20፡21)፣ እንደ መታዘዝና መቀጠል!

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ሐተታ ነው፣ ያም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግል ከመተርጎም አኳያ ራሱ ተርጓሚው ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል። እያንዳንዳችን ባለን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። እርስዎ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ በትርጓሜው ቅድሚያ ናችሁ። ይህን በሐተታ አቅራቢው ልዩ ትርጉም መያዝ አይኖርብዎትም።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንዲያጤኑ እንዲረዳዎት ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንዲያሰላስሉ ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንዲወሰኑ አይደለም።

1. ምዕራፍ 8 ከምዕራፍ 7 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
2. ኩነኔ የማይኖር ከሆነ፣ ኃጢአት በአማኞች ሕይወት እንዴት ተጽዕኖ ይኖረዋል?
3. መንፈስ ወይም ኢየሱስ በአማኞች ላይ ያድራሉን (ቁ.9)?
4. ፍጥረት እንዴት በሰው ኃጢአት ሊጎዳ ይችላል (ቁ. 19-22)? ፍጥረት የመንግሥተ ሰማያት አካል ይሆናልን (ኢሳ. 11፡6-10)?
5. መንፈስ እንዴት ስለ እኛ ይማልዳል (ቁ.26-27)? ይህም "በልሳናት መናገርን" ያመለክታልን?
6. መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በዚህ በክፉ ዓለም ነገሮች ሁሉ ለበጎ ይሆናሉ ይላል (ቁ. 28)? "በጎ" የሚለውን (ቁ. 29) ያለውን አብራራ።
7. መቀደስ፣ ከሥነ- መለኮታዊ ሁኔታዎች ቅደም ተከተል በቁ. 30 ከተመለከቱት ለምን ሊወጣ ቻለ?
8. በቁ. 31-39 ያለው ለምን የፍርድ ቤት ትዕይንት ተባለ?
9. በቁጥር 34 ስለ ኢየሱስ የተባሉትን አራት ነገሮች ዘርዝር።

## ሮሜ 9

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ምርጫ | የእስራኤል መሲሁን መቃወም | የእስራኤል አለማመን | እግዚአብሔር እና የራሱ ሕዝብ | የእስራኤል መብት |
| 9:1-5 | 9:1-5 | 9:1-5 | 9:1-5 | 9:1-5 |
| | የእስራኤል መቃወም እና የእግዚአብሔር አላማ | የእግዚአብሔር መሐላ ለእስራኤል የሚሻር አይደለም | | የእግዚአብሔር ኪዳኑን ይጠብቃል |
| 9:6-13 | 9:6:13 | 9:6:13 | 9:6-9 | 9:6-13 |
| | የእስራኤል መቃወም እና የእግዚአብሔር ፍርድ 9: | የእግዚአብሔር ትክክለኛ ምርጫ | | እግዚአብሔር ፍርድን አያጣምም |
| 9:14-18 | 14-29 | 9:14-18 | 9:14-18 | 9:14-18 |
| የእግዚአብሔር መቅሰፍት እና ምህረት | | | የእግዚአብሔር ቁጣ እና ምህረቱ | |
| | | | 9:19-21 | 9:19-21 |
| 9:19-29 | | | | |
| | | 9:27-29 | | |
| እስራኤል እና የምስራቹ ወንጌል | እስራኤል ያለችበት የጊዜው ሁኔታ | ጽድቅ በእምነት በኩል ይገኛል | እስራኤል እና የምስራቹ ወንጌል | በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትንቢት |
| | | | | 9:25-29 |
| 9:30-10:4 | 9:30-33 | 9:30-10:4 | 9:30-10:4 | |
| | | | | 9:30-33 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምእራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. የመጀመሪያው ምንባብ

2. ሁለተኛው ምንባብ

3. ሦስተኛው ምንባብ

4. ወ.ዘ.ተ

**ሮሜ ምዕራፍ 9-11 እና ከ1-8 ያላቸው ዝምድና**

ሀ. ሁለት የማስረጃ መንገዶች እንመልከት፡-

1. ርዕስ ጉዳዩ የተለየ መሆኑ እና የስነመለኮት ትንታኔውን መመልከት ዝምድናውን ለመለየት ያስችላል፡፡
   - ሀ. ይህ ግልፅ የሆነ ተነፃፃሪነት አለው፤ይህም የሀሳብ ፍሰቱ ሙሉ ለሙሉ አይገናኝም ለምሳሌ ሮሜ 8፡39 እና 9፡1 ይመልከቱ፡፡
   - ለ. በሮም ቤተክርስቲያን የአሕዛብ እና የአይሁድ ክርስቲያኖች በምኩራብ የነበረው ውጥረት በዚህ የአሕዛብ ክርስቲያኖች አመራር እያደገ መምጣት ያመለክታል::
   - ሐ. የሐዋሪያው ጳውሎስ ትምህርት ስለ እስራኤል ስለሕግ እና ለአህዛብ ሐዋሪያ ስለመሆን ትንታኔ ስቷል፡፡
2. የሐዋሪያው ጳውሎስ ለወንጌል ያለው አቀራረብ፡-
   - ሀ. በምዕራፍ 8 ሐዋሪያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ፍቅር ማን ይለየናል ይላል፤ይህ እምነት ስለሌላቸው ይሰራ ይሆን?
   - ለ. ሮሜ 9-11 ስለማያምኑ እስራኤሎች የተነገረውን ቃል ነው፡፡
   - ሐ. ሐዋሪያው ጳውሎስ በመልዕክቶቹ ትኩረት የሰጣቸው ጉዳይዎች እንመልከት ሮሜ 1፡3, 3,16, 3፡21,31 እና 4፡11፡፡
   - መ. ሐዋሪያው ጳውሎስ እግዚአብሔር የታመነ እንደሆነ ይናገራል፤ የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖች ተሽረዋል?

ለ. ንጽፈ ሐሳቡን የመከፋፈል ዘዴ:-

1. ጳውሎስ የተጠቀመበት መንገዶች እንመልከት:-
   - ሀ. ሮሜ 9፡14
   - ለ. ሮሜ 9፡19
   - ሐ. ሮሜ 9፡30
   - መ. ሮሜ 11፡1
   - ሠ. ሮሜ 11፡11
   - ረ. ሮሜ 9፡6
2. ሮሜ 9፡11 አጠቃላይ ትርጉሙን ለማወቅ የምዕራፎቹን አከፋፈል ዘዴ እንመልከት፡፡
   - ሀ. 9፡1-29 በእግዚአብሔር ሉአላዊት ላይ ያተኩራል፡፡
   - ለ. 9፡30-10፡21 የሰው ሃላፊነቱ ያመለክታል፡፡
   - ሐ. 11፡1-32 በእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ ላይ ያተኩራል፡፡
3. ከምንባቡ ዋና ርዕስ የሚሆነውን ማወቅ የአዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም የተሻለ ይሆናል፡፡
   - ሀ. የእስራኤል ወሲሁን መቃወም ሮሜ 9፡1-5፡፡
   - ለ. የእስራኤል የእግዚአብሔርን አላማ መቃወም ሮሜ 9፡6-13 ፡፡
   - ሐ. የእስራኤል የእግዚአብሔርን ፍትህ መቃወም ሮሜ 9፡14-29 ፡፡
   - መ. የእስራኤል ነባራዊ ሁኔታ ሮሜ 9፡30-33 ፡፡
   - ሠ. እስራኤል እና ወንጌል ሮሜ 10፡14-21 ፡፡
   - ረ. የእስራኤል ቅሬታዎች ሮሜ 11፡1-10 ፡፡
   - ሸ. ለእስራኤል ይራራል ሮሜ 11፡11-36 ፡፡

ሐ. ይህ ክፍል ከልብ ወደ እግዚአብሔር የተደረገን ልመና ያሳያል፤ ነገር ግን እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ አመፀች፤ ሆሴ 11፡1-4፣8-9፡፡ በብዙ መንገድ የህጉ መልካምነት እና ክፉነት በዚህ ክፍል ላይ ተጠቅሷል ሮሜ 9ን ከሮሜ 7 እና 10 ጋር ያነፃፅሩ፤ሐዋርያው ጳውሎስ ግን የህጉ ክፍና መልካም መሆን ሞት እንደሚያመጣ በተሰበረ ልብ ገልጿል፡፡

መ. ሐዋሪያው ጳውሎስ ከሮሜ ምዕራፍ ዘጠኝ እስከ አስራ አንድ ሃያ አምስት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በመጥቀስ የቀድሞውን የተስፋ ቃል ለእስራኤል ያስገነዘበበት ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን የአብርሃም ዘሮች የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች ሆነዋል ሐዋ 7 እና ነህ 9 አንብቡ፡፡

ሠ. ኤፌ 1፡3-14 ይህ የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል የእግዚአብሔርን የዘላለም ምርጫ የሚያስገዝብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቀድሞ የመረጣቸው እንዳሉም የሚናገር ይመስላል (ካልቪኒዝም)፤ ነገር ግን ትኩረቱ በግለሰብ ላይ ሳይሆን የእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድን የሚናገር መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፤ ዘፍ 3፡15፣ ሐዋ 2፡23 3፡18፤ 4፡28፤ እና 13፡29፡፡

*የጀሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ ይህንን ሲያስቀምጠው ሐዋርያው ጳውሎስ ግለሰቦችን በማወዳደር ላይ ያተኮረ ሳይሆን፤ነገር ግን የሁሉም ድነት የሚወስነው በእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ መሆኑን ለማመልከት የተጠቀመበት ነው* (የ318)፡፡

**የምዕራፍ ዘጠኝ አውድ እይታ**

ሀ. በምዕራፍ ስምንት እና ዘጠኝ ያለውን ልዩነት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

ለ. የዚህ ምዕራፍ ክፍፍል ከስነ መለኮት ትንተና ረገድ ሲታይ፡-

1. በደህንነት መሰረት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡
2. በእግዚአብሔር የዘላለም ምርጫ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡
3. የእግዚአብሔር ታማኝነት እና የእስራኤል አለመታመን፡፡
4. በኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢያት ስርየት ለሰው ልጆች ሆንዋል፡፡

ሐ. ይህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ሉአላዊነት የሚናገር የአዲስ ኪዳን ምንባብ ነው፡፡ በእርሱ መመረጥ ኤፌ 1፡3-14 ፤ነገር ግን ምዕራፉ ነፃ ምርጫ ለሰው ተሰቷል (እያንዳንዱ ቁ.4) ("ማንም" ቁ11፣13) ("ሁሉም" ቁ 12)፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ እነዚህን ቃሎች ለማስታረቅ አልሞከረም ምክንያቱም ሁሉም ትክክል ስለሆኑ ነው፤ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮቶች በዚህ መልስ ይስማማሉ፡፡ እነዚህ በዚህ ሁኔታ የተቀመጡ ጥቅሶች አንድን እውነት ያስተላልፋሉ፡፡ የኦገስቲያኒዝም እና ካልቪኒዝም ከሰሚ ፔልጋኒዝም እና ኦሪያኒዝም ትምህርቶቻቸውን ስንመለከት እውነታንም ብሎም ስህተቶችንም የያዙ እንደሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ያልተመለሱ የሚያወዛግቡ ጥያቄዎችን ለመፋታት የአውደ ንባብ፣ አጠቃላይ ሃሳቡን፣ አመክናዮቹን መመልከት ወደ ቀረበው ወይም ወደ ትክክለኛው ትርጉም ይመራናል፡፡

መ. ሮሜ 9፡30-33 የዚህ ምዕራፍ ማጠቃለያ እና የምእራፍ 10 ዋና ሀሳብ የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

9፡1-5
**ብዙ ሃዘን የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ አልዋሽምም ህሌናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል፡፡ በስጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንደምሆን እፀልይ ነበርና፡፡ እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና ልጅነትና ክብር ኪዳንም የህግም መስጠት የመቅደስም ስርአት የተስፋውም ቃላት ለእርሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በስጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን፡፡**

9፡1-2 በግሪክ አንድ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ለሚገኙ ክርስቲያኖች እውነትን እንዲያውቁ የተለያዩ አስረጂዎችን ያቀርብላቸዋል፡፡

1. የእርሱ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ቁ.1
2. የህሊናው ምስክርነት ቁ.1
3. ለእስራኤል ያለው ልባዊ ናፍቆት ቁ.2

9፡1 "በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ አልዋሽም" ይህ የጳውሎስ የተለመደ ንግግሩ ነው (2 ቆሮ 11፡10፤ ገላ 1፡20፤ 1ጢሞ 2፡7 ሮሜ 1፡9፤ 2ቆሬ 1፡23፤ 11፡31 ፊሊጰ. 1፡8፤ 1ተሎ 2፡5፣10) እነዚህ በስብከቶቹ፤በአስተምህሮቶቹ መሃከል የሚያስገባ የራሱ ዐረፍተ ነገር ነበር፡፡ ይህም ታማኝነትን በሰው ልብ ለመፍጠር የሚጠቀምበት ነበር፡፡

▣ "ሕሊናዬ" ይህ እግዚአብሔር ለሰዎች ህይወታቸውን እንዲመሩበት እንዲያመዛዝኑበት የሰጠው ስጦታ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ሰምተን በአይምሮአችን ፈቅደን ምልሳሽ የምንሰጥ መሆኑንም ያስገነዝባልና (1ጢሞ 1፡5፤ 19)፡፡ የማያምኑ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ መስጠት የማይችሉት ህሊናቸው በሌላ የተገዛ ስለሆነ ነው 1ጢሞ 4፡2

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት..."** |
| **አየመመቅ** | **"የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ..."** |
| **አእቅ** | **"በመንፈስ ቅዱስ ምሪት..."** |
| **ኢመቅ** | **"በመንፈስ ቅዱስ አንድነት..."** |

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ እና ትዕዛዝ የተረዳ ሰው ነው፤ሐዋ 9፡1-22፣ ገላ 1፡1፤ የሐዋሪያነት ስልጣን ነበረው 1ቆሮ 7፡25፡40፡፡ የእግዚአብሔርን ሐዘን በማያምኑ ላይ እና በህዝበ እስራኤል ላይ ገልጿል ቁ.2፡፡ የእስራኤልን ተጠቃሚ መሆን አሳይቷልቁ 4-5፤
9-3

▣
**አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም**

አየመመቅ "እመኛለሁ…"
አእቅ "ስለ እርሱ እመኛለሁ…"
ኢመቅ "ሁል ጊዜ ፈቃደኛ ነኝ …"

ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለተወለደበት ህዝብ ስለ እስራኤል የጋለ ፍላጎት እንዳለው እና ሁሉን ለማድረግ ፈቃደኛ እንደሆነ ይገልፃል ቁ.3 ይህ ጥቅስ ጠንካራና የሰዋሰው ስርአትን የተከተለ ነው። በመሆኑም ጳውሎስ የራሱን ጥልቅ ፍላጎት የገለፀበት ቦታ ነው። የጳውሎስ ፀሎት ከሙሴ ምልጃ ጋር መመሳሰል ይታይበታል፤በተለይ ሐጢያት ለሰሩ ለእስራኤል መጸለዩ ዘፀ 32፡30-35።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ የምልጃ ፀሎት**

I. መግቢያ
  ሀ. ፀሎት አስፈላጊ ነው፤ምሳሌውን ከኢየሱስ እንማር፡-
    1. የግል ፀሎት ማርቆ 1፡35 ሉቃ 3፡21
    2. መቅደሱን ማንፃት ማቴ 21፡13 ማርቆ 11፡17
    3. የፀሎት ምሳሌነት ማቴ 6፡5-13 ሉቃ 11፡2-4
  ለ. ፀሎት እምነታችን በተጨባጭ እንዲታይ የሚረዳ መሳሪያ ነው።
  ሐ. እግዚአብሔር የህዝቡን ፀሎት እንዳይመልስ የሚያደርጉ ጉዳዮች (ያዕቆ 4፡2)።
  መ. የፀሎት ዋናው አላማ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ነው።
  ሠ. ክርስቲያኖች በየትኛውም ርዕስ ላይ መፀለይ ይችላሉ በተደጋጋሚም መፀለይ ይችላሉ።
  ረ. ፀሎት የያዛቸውን አስፈላጊ ነጥቦችን እንመልከት፡-
    1. ምስጋና ፤ ስግደት
    2. ውዳሴ፣ ህብረት
    3. ንስሃ መግባት (የቀድሞውንም የጊዜውንም)
    4. የውስጥ ፍላጎታችንን ልመና ማቅረብን ይመለከታል።
    5. ምልጃ (ይህ ለራስም ለሌሎች የሚጠቅም የፀሎት አይነት ነው።

II. ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን
  ሀ. ብሉይ ኪዳን
    4. የምልጃ ፀሎት ምሳሌዎች፡-
      ሀ. አብርሃም ስለ ሰዶም ማለደ ዘፋ 18፡22
      ለ. ሙሴ ስለእስራኤል ልጆች ማለደ፤ከሚከተለው ጥቅሶች ይመልከቱ፡-
        1. ዘፀ 5፡22-23
        2. ዘፀ 32፡31
        3. ዘዳ 5፡5
        4. ዘዳ 9፡18
      ሐ. ሳሙኤል ለእስራኤል ልጆች ማለደ፡-
        1. 1ሳሙ 7፡5-6፣ 8-9
        2. 1ሳሙ 12፡16-23
        3. 1ሳሙ 15፡11
      መ. ዳዊት ስለ ልጁ ማለደ 2ሳሙ 12፡16-18።
    2. እግዚአብሔር ማላጆችን ይፈልጋል ኢሳ 59፡16።
    3. ንስሃ ያልተገባበትን ሃጢያት እንቅፋት ይፈጥራል።
      1. መዝ 66፡18
      2. ምሳ 28፡9
      3. ኢሳ 59፡1-2፤ 64፡7
  ለ. አዲስ ኪዳን
    1. ልጁ እና መንፈሱ ይማልዳሉ፡-
      ሀ. ኢየሱስ (ልጅ)
        1. ሮሜ 8፡34
        2. ዕብ 7፡25
        3. 1ዮሐ 2፡1
      ለ. መንፈስ ቅዱስ ይማልዳል ሮሜ 8፡26-27
    2. የሐዋርያው ጳውሎስ የምልጃ አገልግሎት

ሀ. ለአይሁድ የተደረገ ፀሎት፡-

1. ሮሜ 9፡1
2. ሮሜ 10፡1

ለ. ለአብያተ ክርስቲያናት የተደረገ ፀሎት፡-

1. ሮሜ 1፡9
2. ፊሊ 1፡16
3. ፊሊ 1፡3 -4፤9
4. ቆላ 1፡3፤9
5. 1ተሰሎ 1፡2-3
6. 2 ተሰሎ 1፡11
7. 2ጢሞ 1፡3
8. ፊሊ ቁ 4

ሐ. ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዲፀልዩለት ጠየቀ፡-

1. ሮሜ 15፡30
2. 2ቆሮ 1፡11
3. ኤፌ 6፡19
4. ቆላ 4፡3
5. 1 ተሰሎ 5፡25
6. 2 ተሰሎ 3፡1

3. የቤተክርስቲያን የምልጃ አገልግሎት እንደሚከተለው ነው፡-

ሀ. እርስ በእርስ መፀለይ

1. ኤፌ 6፡18
2. 1ጢሞ 20 2፡1

ለ. የፀሎት ጥያቄ ማቅረብ፡-

1. ለጠላቶቻችን ማቴ 5፡44
2. ለክርስቲያን ሰራተኞች ዕብ 13፡18
3. ለገዥዎች 1ጢሞ 2፡2
4. ለታመሙ ያዕቆብ 5፡13-16
5. በእምነት ለደከሙ 1ዮሐ 5፡16

ሐ. ፀሎት ለወንዶች ይደረጋል 1 ጢሞ 2፡1

III. እንዴት እንፀልይ

ሀ. ከክርስቶስ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት በማድረግ፡-

1. በእርሱ በመኖር መፀለይ ዮሐ 15፡7
2. በስሙ እንፀልይ ዮሐ 14፡13፣15፡16
3. በመንፈስ እንፀልይ ኤፌ 6፡18፣ ይሁዳ 20
4. እንደፈቃዱ እንፀልይ ማቴ 6፡10, 1 ዮሐ 3፡22

ለ. የውስጥ ፍላጎታችንን ለመግለፅ መፀለይ ያለብን፡-

1. በእምነት መፀለይ
2. በንስሃ መፀለይ
3. ለጥቅማችን ብቻ መፀለይን ማስወገድ
4. ራስ ወዳድነትን በማስወገድ መፀለይ

ሐ. ሌሎች ጉዳዮች

1. ትዕግስት

ሀ. ሉቃ 18፡1-8
ለ. ቆላስ 4፡2
ሐ. ያቆ 5፡16

2. መሰመን

ሀ. ማቴ 7፡7-8
ለ. ሉቃ 11፡5-13
ሐ. ያዕቆ 1፡5

3. የራስን ቤት ችግር ማስወገድ አስፈላጊ ነው 1 ጴጥ 3፡7
4. ከኃጢያት ነፃ መሆን

ሀ. መዝ 66፡18
ለ. ምሳ 28፡9

| |
|---|
| ሐ. ኢሳ 59:1-2<br>መ. ኢሳ 64:7<br>IV. የስነ-መለኮት ትንታኔ<br>ሀ. ለክርስቲያኖች መብት እድል፣ሃላፊነት ተሰጥቷል።<br>ለ. ኢየሱስ ምሳሌአችን ነው፣መንፈስ ቅዱስ መሪያችን ነው፣ እግዚአብሔር አባታችን ጠባቂአችን ነው።<br>ሐ. ቤተሰብህ፣ባልንጀሮችህ፣አንተ ወደ አዲስ ህይወት ትቀየራላችሁ። |

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ, | " ከክርስቶስ ተለይቶ መረገም..." |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "መረገም ከክርስቶስ..." |
| አየመመቅ | "መረገም እና ከክርስቶስ መለየት" |
| አእቅ | "በእግዚአብሔር እርግማን ስር መሆን እና ከክርስቶስ መለየት..." |
| ኢመቅ | "ፈቅደን መረገም እና ከክርስቶስ መለየት..." |

ቅዱስ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው፤ እንዲሁ መረገም ለአንድ ነገር ወይም ለአንድ ሰው ቃሉ ሊያገለግል ይችላል እነዚህ ጥቅሶች አንብበው ይረዱ፡- ዘሌዋ 27:28፣ ሉቃ 21:5፣ ኢያ 6:7፣ ሮሜ 9:3)። ይህ ከላይ በዝርዝር የሚታዩት ጥቅሶች የቃሉ ፊቺ እንደ አውዱ የሚወሰን ይሆናል።

| |
|---|
| **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ እርግማን (አናቲማ)**<br>የእብራይጥ ቋንቋ እርግማንን የተለያዩ ቃሎች ይገልጡታል "ሂረም" ለእግዚአብሔር አንድን ነገር፤ መስጠት ያመለክታል በግሪኩ አናቲማ ጥፋት ማለት ነው (ዘዳ 7:26፣ አያ 6:17-18፤ 17:12) ቅዱስ ጦርነት የሚል ትርጉምም ይሰጣል እግዚአብሔርም ከነአናውያንን እና ኢያሪኮን ፈጥማቹ አጥፋ አላቸው።<br>በአዲስ ኪዳን "አናቲማ" የተለያዩ ትርጉሞች ተሰተውታል፡-<br>1. ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስጦታ ሉቃ 21:5<br>2. የሞት መሐላ ሐዋ 23:14<br>3. መራገም ማርቆ 14 :71<br>4. ኢየሱስን መራገም<br>5. አንድን ሰው ለእግዚአብሔር እርግማን አሳልፎ መስጠት ሮሜ 9:3፣ 1ቆሮ 10:22፣ ገላ 1:8-9 |

9:4-5 የሰሞች በቅደም ተከተል መቀመጥ እስራኤል ባለመብት መሆኗን የሚያስረዳ ነው ሉቃ 12:48።

9.4 **"እስራኤላውያን"** ይህ ለአብርሃም ዘሮች የተሰጠ ስያሜ ነው፣በተለይ ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ከታገለ በኂላ የተሰጠ ስም ነው፤ ዘፍ 32:18 ይህ ስያሜው የአይሁድ ህዝብ ስም ሆኖ ተሰይሟል።

▣ **"ልጆች"** በብሉይ ኪዳን ለመላእክቶች የተሰጠ ስያሜ ነው፡- (ኢዮ 1:6፣ ኢዮ 2:1፣ ኢዮ 38:7፣ ዳንኤ 3.25፣ መዝ 29:1፤89፡ 6-7)።

የነጠላ ስያሜው እንደሚከተለው ነው፡-

1. የእስራኤል ንጉስ 2ሳሙ 7:14
2. ለህዝብ ዘፀ 4:22
3. ለመሲሁ መዝ፣ 2:7
4. ለሰው ልጆች ዘዳ 32:5፣ ሕዝ 21፣ ሆሴ 1:10

ሐዋርያው ጳውሎስ የድነትን ሃሳብ ለመግለጥ "ልጅ ማድረግ" የሚል ቃል ተጠቅሟል። ሐዋርያው ጴጥሮስ እና ዮሐንስ "ዳግም መወለድ" በሚል ቃል ተጠቅመዋል። ይህ የአይሁድ የንግግር ምሳሌ አይደለም፣ነገር ግን ከሮማውያን የተወሰደ ሀሳብ ነው። በሮም የሃገሪቱ ነዋሪ እንዲሆን መብት የተሰጠው ሰው ዳግም እንደተወለደ ይቆጠራል፤ይህ ማለት የነዋሪነት ፈቃድ ያገኛል ማለት ነው። ይህን ሀሳብ ወደ መንፈሳዊ ተቀይሮ እንመለከታለን።

▣ **"ክብር"** የእብራይስቱ "መክበድ" የሚል ትርጉም ተሰቶታል። (1) የእግዚአብሔር በተራራው ላይ ክብሩን መግለጡ ዘፀ 19:18-19 (2) የደመናው አምድ እስራኤሎችን በምድረ በዳ ይመራ ነበር (ዘፀ 40:34-38)። ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በልዩ መንገድ የተገለጠበት መንገዱ ነበር። ይህ የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ነበር። 1 ነገ 8:10-11፣ ዕዝ 1:28፣

▣ **"ቃል ኪዳን"** P46 B & D በእነዚህ የጥንት የግሪክ ጽሁፎች ላይ ቃልኪዳን የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ተቀምጧል። ነገር ግን በMSS and C እና በጥቂት የጥንት ላቲን ጽሁፎች ላይ እና ቨልጋት እና ኮብቲክ እትሞች ላይ ቃልኪዳን

የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር አስቀምጠውታል፡፡ ዩቢኤስ በግማሹ በብዙ ቁጥር አስቀምጦታል፡፡ በብሉይ ኪዳን ቃልኪዳን የሚለው ቃል ለብዙ ቁጥር መግለጫ አልዋለም፡፡

ምሳሌ፡- አዳም፣ ኖህ፣ አብርሃም፣ ሙሴ እና ዳዊትን መመልከት ይቻላል፡፡ የሚከተለው የህጉ መሰጠት ቢጠቅስም ነገር ግን የአብርሃም ቃልኪዳን መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ እርሱም ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ መሰረት የተጠቀመበት መሆኑን ከሚከተለው ዝርዝር እንመልከት፡፡ ሮሜ 4:1-21 ገላ. 3:16-17 ዘፍ፣ 12,15,17 ቃኪዳን ማለት እውነተኛ አምላክ ከሰው ፍጥረት ጋር የሚያደርገው መልካም ግንኙነትን ያመለክታል፡፡ አንዳንድ ቃልኪዳኖች በእግዚአብሔር ባህሪ፣ ድርጊት እና አላማ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ : "ቃል ኪዳን"**

የብኪ. ቃል የሆነው ቤሪዝ፣ ኪዳን፣ ለመግለጽ ቀላል አይደለም፡፡ በዕብራይስጥ የሚገጥም ግሥ የለውም፡፡ ሥርወ ቃላዊ ፍች ለማምጣት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የማያሳምኑ ሆነዋል፡፡ ሆኖም፣ የጽንሰ ሐሳቡ
ማዕከላዊነት የቃሉን አጠቃቀም ይመረምሩ ዘንድ ሊቃውንትን አስገድዷቸዋል፣ ተግባራዊ ፍችውን ለመወሰን፡፡

ኪዳን አንዱ እውነተኛው አምላክ ከእሱ ፍጡር ከሆነው ሰው ጋር የሚደረግ ውል ነው፡፡ የኪዳን ጽንሰ ሐሳብ፣ ውል፣ ወይም ስምምነት የመጽሐፍ ቅዱስን መገለጥ ለመረዳት ወሳኝነት አለው፡፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለው ክርክር በኪዳን ጽንሰ ሐሳብ በግልጽ ይታያል፡፡ አንዳነድ ኪዳናት የተመሠረቱት በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ድርጊት፣ እና ዓላማ ላይ ነው፡፡

1. ተፈጥሮ ራሱ (ዘፍ. 1-2)
2. የአብርሃም መጠራት (ዘፍ. 12)
3. ከአብርሃም ጋር ኪዳን (ዘፍ. 15)
4. የኖህ መጠበቅና ተስፋ (ዘፍ. 6-9)

ሆኖም፣ የኪዳን ዋነኛ ባሕርዩ ምላሽን መፈለጉ ነው

1. በእምነት አዳም እግዚአብሔርን መታዘዝና በኤደን ገነት መሐል ከሚገኘው ዛፍ መብላት የለበትም (ዘፍ. 2)
2. በእምነት አብርሃም ወገኖቹን ትቶ፣ እግዚአብሔርን መከተል፣ እንዲሁም ስለ መጪው ዝርዮቹ ማመን ነበረበት (ዘፍ. 12:15)
3. በእምነት ኖህ ትልቅ መርከብ ገንብቶ፣ ከውሃ ራቅ ያለ፣ እንስሳትን ማሰባሰብ ነበረበት (ዘፍ. 6-9)
4. በእምነት ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ የተወሰኑ መመሪያዎችን፣ ለሃይማኖታዊና ለማህበራዊ ሕይወት የሚሆኑ፣ የበረከትና የርግማን ተስፋዎችን መቀበል ነበረበት (ዘዳ. 27-28)፡፡

ተመሳሳይ የሆነ ክርክር እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት "በአዲስ ኪዳን" ተመልክቷል፡፡ ክርክሩ በግልጽ የሚታየው ሕዝ. 18 ን ከሕዝ. 36:27-37 ጋር በማወዳደር ነው፡፡ ኪዳኑ የተመሠረተው በእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊት ነውን ወይስ ለሰው በተሰጠ የውክልና ሃላፊነት? ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፣ በብሉይ ኪዳን፣ በአዲሱም ጭምር፡፡ የሁለቱም ግቦች ተመሳሳይ ናቸው፡ (1) የጠፋው ህብረት መመለስ፣ ዘፍ. 3 እና (2) የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ጻድቅ ሕዝብ መመሥረት፡፡

የኤር. 31:31-34 አዲስ ኪዳን ክርክሩን ያቃልላል፣ የሰዎችን ድርጊት ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገውን በማስቀረት፡፡ የእግዚአብሔር ሕግ ውስጣዊ መሻት ሆነ፣ ውጫዊ ድርጊት መሆኑ ቀርቶ፡፡ መልካም፣ ጻድቅ ሕዝብ የመሆን ግብ በተመሳሳይ መልኩ ነው የሚቀረው፣ ነገር ግን ዘዴው (አገባቡ) ነው የተቀየረው፡፡ የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ነጸብራቅ ከመሆን ብቃት እንደሌለው ተረጋግጧል (ሮሜ 3:9-18)፡፡ ችግሩ ኪዳኑ አልነበረም፣ ነገር ግን የሰው ሃጢአተኝነትና ድካም ነው (ሮሜ 7፤ ገላ. 3)፡፡

ተመሳሳይ ክርክር በብኪ. ሁኔታዊ ያልሆነና በሁኔታዊ ኪዳናት መካከል እንዳለ ይኖራል፣ በአኪ፡፡ ደህንነት በፍጹም ነጻ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ፣ ነገር ግን ንስሐና እምነትን ይጠይቃል (ሁለቱንም በመነሻነትም ሆነ በቀጣይነት)፡፡ እሱም ሁለቱም፣ ሕጋዊ ሥልጣናዊ አዋጅና ክርስቶስን ወደ መምሰል መጠራት፣ አመላካች መግለጫ ለተቀባይነትና አስፈላጊ ቅድስና! አማኞች በራሳቸው ድርጊት የዳኑ አይደሉም፣ ነገር ግን በመታዘዝ (ኤፌ. 2:8-10)፡፡ እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የመዳን ማስረጃ ነው እንጂ የመዳን ምክንያት አይደለም፡፡

▣ **"የሕጉ መሰጠት እና የመቅደስ ስርዓት"** (1) ሙሴ ሕጉን ተቀበለ ዘፀ 19-20 (ዳዊት የመቅደሱን ስርዓት በአግባቡ አካሄድ) (2) የመገናኛው ታቦት በምድረዳ መሄድ (ዘፀ 25-40 እና ዘሌዋ)

**"ቃል ኪዳኑ"** የእግዚአብሔር የወደፊቱን እቅዱን ለሰው ልጆች ይናገራል (ሐዋ 13:32፣ ቲቶ 1:2፣ ዕብ 1:1)፡፡ የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖች የሚያመለክቱን የመሲሁን መምጣት ነው፤ (ዘፍ 15:12-21፣ ኢሳ 7:14፣ ዳንኤ 7:13፣27 ሚክ 5-2)፡፡

9.5 **"የቀደሙ አባቶች"** አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ ናቸው ዘፍ 12-50
ሮሜ 11:28

▣ **"ኢየሱስ የመጣበት ወገን"** ይህ ኢየሱስ የመጣበትን የዘር ግንድ ያመለክታል፤በመሆኑም በስጋ ከአይሁድ ዘር የሆነ መሲህ ነው ሮሜ 1:3፡፡ በእግዚአብሔር የተሾመ የእግዚአብሔር ምርጥ ነው፡፡ የሚከተለውን አገልግሎቶቹን እንመልከት፡-

(1) የነገስታት ንጉስ ነው (2) ሊቀ ካህን ነው (3) ነብይ፣ እነዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለማከናወን እግዚአብሔር የሚመርጣቸው አገልግሎቶች ናቸው። ኢየሱስ ሶስቱንም አገልግሎቶች ያገለግል ነበር። ዕብ 1:2-3 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሙሉ ህልውናው መገለጫ ነው፤እርሱ በስጋ ተገለጠ እንጂ አምላክ ነው፡ ሚክ 5:2 ተሰሎ 1:13-30 ኢሳ 7:14 ኢሳ 9:6

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በወንጌል በስጋ የዳዊት ዘር ስለ ተወለደ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"የክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት"** |
| **አየመመቅ** | **"የመሲሁ መምጣት "** |
| **አእቅ** | **"ክርስቶስ የሰውን መልክ ይዞ መምጣት"** |
| **ኢመቅ** | **"የክርስቶስ መምጣት እርሱም ከሁሉ ይበልጣል"** |

ሁሉን በሁሉ ያደረገ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት ማቴ 28:19 ሮሜ 1:15-20

▣ **"ለዘላለም"** ይህ ለግሪኮች በተለምዶ "እስከ እድሜ መጨረሻ" ማለት ነው፤ሉቃ 1:23 ሮሜ 1:25፣ ሮሜ 11:36፣ ገላ 1:5፣ 1ጢሞ 1:17።

▣ **"እስከ እድሜ መጨረሻ"** የሚከተለውን ጥቅሶች ተመልከት ማቴ 21:19 ማርቆ 11:14፣ ሉቃ 1:55

▣ **…ከዘላለም እስከ ዘላለም** አፌ 3:21 ይህ መድረሻ የሌለው ፍፃሜ ያልተበጀለት መሆኑን ያስረዳል ሮሜ. 9:6-13። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለም እነዚህ ከእስራኤል የሚወዱ ሁሉ የእስራኤል አይደሉምና፤ የአብርሃምም ዘር ስለ ሆነ ሁላቸው ልጆች አይደሉም ነገር ግን በይስሐቅ ዘር ይጠራሃል ታባለ። ይህም የተስፋ ቃል ልጆች ሆነው ይቆጠራሉ እንጂ እነዚህ የስጋ ልጆች የሆኑ የእግ/ር ልጆች አይደሉም።

**9:6 የእግ/ር ቃል** ይህ የብሉይ ኪዳንን ቃል ኪዳን የሚያሳይ ነው። የእግ/ር መሃላ (ዘኅ 23:19፣ ኢሳ 40:8፣ ኢሳ 59:21)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አየመመቅ, አእቅ, ኢመቅ** | **"ይሻላልን"** |
| NKLV | **"አይቀየርም"** |

ይህ ቃል በግሪክ ekpipto ተብሎ አገልግሎቱም ለአንድ ነገር ኢሳ 6:13 ወይም የአንድ ሰው ውድቀትን የሚያመለክት ቃል ነው፤ ኢሳ 14:12

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከእስራኤል ያልሆኑ እነርሱ የእስራኤል ዘር አይደሉም"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ከእስራኤል ያልሆነ እነርሱ እስራኤሎች አይደሉም"** |
| NRSU | **"ከእስራኤል ያልሆነ የእስራኤል ወገን አይሆኑም"** |
| **አእቅ** | **"የእስራኤል ህዝብ ያልሆኑ የእግዚአብሔር ህዝብ ይሆናሉ"** |
| **ኢመቅ** | **"የእስራኤል ዘር የሆነ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለም"** |

የእስራኤል የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የተለያዩ ትርጉሞቹን እንመልከት፡- (1) እስራኤል - የያዕቆብ ዘሮች ዘፍ 32:32 (2) እስራኤል - የተመረጠ ሕዝብ (3) እስራኤል - ቤተ/ክርስቲያን ገላት 6:16 1ጴጥ 2:8 ራዕ 1:6

**9.7** ሁለተኛው የዚህ ጥቅስ፡ ዐርፋተ ነገር የተወሰደው ከዘፍ 21:12 ላይ ነው። የአብርሃም ልጆች የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ዘሮች ናቸው ዘፍ 12:1-3 ዘፍ 15:1-11፣ 17፣1-21፣ 18-15፣ ገላት 4:23

**9.8** ሐዋርያው ጳውሎስ "ስጋ" የሚለውን ቃል ዘርን ለማመልከት ተጠቀሞበታል (ሮሜ 1:3፣ 4:1፣ 9:3፣5)

**9.9** ይህ ከዘፍ 18:10,14 የተወሰደ ነው ይህ ዘር ከሳራ የሚመጣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቅድመ ፍላጎት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል።

**9.10** የአባቶች መሃን ሚስቶች መውለዳቸው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነቱን ነው።

**9.11-12** ይህ በግሪኩ አንድ አረፍተ ነገር ነው፤የተወሰደው ከዘፍ 25:19 በእግዚአብሔር ምርጫ መሲሁ ለሁሉም መሰጠቱን ያመለክታል። ነገር ግን ነፃ ምርጫ ለሁሉም ተሰቷል። አርም 31:31 ሕዝ 36:22-36

**9.11** **"አላማ"** ይህ ጥምር ቃል በግሪኩ pro እና titrem; ይህ ማለት፡-

1. ሮሜ 3፡25
    ሀ. ሕገ ደንብ ማውጣት
    ለ. ቅድመ እቅድን ለማመልከት
2. እቅድን ማቀድ
    ሀ. ሮሜ 1፡13 (ለጳውሎስ)
    ለ. ኤፊ. 1፡9 (ለእግዚአብሔር)

አላማ የሚለው ቃል የወል ስሙ pro thesis ማለት “ቀድሞ ማቀድ ማለት ነው”

1. ማቴ 12፡4 ማርቆ 2፡26
2. ቅድመ ዕቅድን ለማመልከት ሮሜ 8፡28፣ ሮሜ 9፡11፣ኤፌ 1፡5፣ 2ጢሞ 1፡9,3፡10

ሐዋሪያው ጳውሎስ “ቀድሞ” የሚለው ቃል በሮሜ ምዕራፍ 8 እና 9 እና በኤፌ1 ላይ ተጠቅሞ እንመለከታለን።

1. ፕሮጂኒስኮ (ቀድሞ ማወቅ) ሮሜ 8፡29
2. ፕሮዞ (ቀድሞ ማቀድ) ሮሜ 8፡29, ኤፌ 1፡5,11
3. ፕሮቲሲስ ( ቀድሞ የተወሰነ) ሮሜ 9፡11
4. ፕሮአቶሚዞ (ቀድሞ የተመለከተ) ሮሜ 9፡23
5. ፕሮሌጊዮ ( የቀድሞ የተነገረ) ሮሜ 9፡29
6. የሌኢሊፐዞ ( የቀድሞ ተስፋ የተጣለበት) ኢፊ 1፡12

**9-12** ይህ የተጠቀሰው ከዘፍ 25፡23 ስለ ኤሳውና ያዕቆብ ነው።

**9፡13** ነገር ግን ኤሳውን ጠላሁ ሚል 1፡2-3 መጥላት የዕብራይስጥ ቃል ነው። የሚከተሉት ጥቅሶች ይመልከቱ ዘፋ 29፡ 31-33, ዘዳ 21፡15, ማቴ 10፡37-38, ሉቃ 14፡26 እና ዮሐ 12፡25 እጠላለሁ እና እወዳለሁ የሚለው ቃል አንድ ሰውን መጥላት መውደድ ሳይሆን ነገር ግን መሲሁ የሚመጣበትን መምረጡን ያሳያል። ያዕቆብ የቃል ኪዳን ልጅ ነው ዘፋ 25፡ 33 ነገር ግን ኤሳው የኤዶም አለቃ ነው ሚል 1፡2-3።

9፡14-18
**እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ አመፃ አለ ወይ አይደለም ለመሴ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ይላልና። እንግዲህ ምህረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም ለሙሴ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና እንግዱህ ምህረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም ከሚምር ከእግ/ር ነው እንጂ መፅሐፍ ፈርኦንን ሃይሌን በአንተ ላይ አሳይ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ለዚህ አስነጣሁህ ይላልና።**

**9፡14** “ ምን እንላለን”? ይህ ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚጠቀምበት የተለመደ
ዓረፍተ ነገር ነው። ሮሜ 3፡5 ሮሜ 4፡1 6፡1 8፡31 ወዘተ…

▣ “በእግዚአብሔር ዘንድ አመፃ አለ ወይ”? እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ሲችል ለሰው ልጆች ነፃ ምርጫን ሰቷል። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ያለ አግባብ በአመፀ ስልጣኑን እንደማይጠቀም ነው።
እግዚአብሔር ቀድሞ በተመለከተው ውስጥ ነው የሰው ዘር ሁሉ የሚገባው እንጂ ሰው ቀድሞ ባቀደው አይደለም 1ዜና 1፡ 2፤እግዚአብሔር ግን በእምነት ወደ እርሱ የሚጠጉትን ይመርጣቸዋል። እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ነገር ግን በምህረት እና በቃል ኪዳን ሰዎችን ወደ እራሱ ያስጠጋል።

▣ “በፍፁም አይደለም ” ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀምበት ዐረፍተ ነገር ነው የሚከተሉን ጥቅሶችን ይመልከቱ (ሮሜ 3፡4,6,31, 6፡2,15፣ 1ቆሮ፣ 6፡15፣ ገላ 2፡17፣ ገላ 3፡21,6፡14)።

**9፡15** የተወሰደው ከዘፀ 33፡19 መሴ ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመቀበል ባይፈልግም እግዚአብሔር ግን ለማዳን መፈለጉን የሚያሳይ ክፍል ነው። ሙሴ ራሱ ገዳይ ነበር (ዘፀ 2፡11-15 የእግ/ር ምዕረት ቁልፍ ጉዳይ ነበር ሮሜ 16,78-23፣ 11፡30,31,32)።

**9፡15-16** “ምዕረት” የግሪኩ “ኢሊዮስ” ሮሜ 15,16,18-23 ይህም ማለት “ለቃል ኪዳን መታመን” ማለት ነው።እንግዲህ የእግዚአብሔር ምርጫ ለሁሉም ነው፤ ማለት፡- ለአይሁድ ወይም ለይሳሃቅ ነገር ግን ለአረቦች አይደለም። ቃልኪዳኑ ለእስራኤልና ለያዕቆብ ነው፤ነገር ግን ለኤሳውና ለኤዶም አልነበረም፣ ነገር ግን አሁን ላመኑ አይሁድ እና ለአህዛብ ሁሉ የሚሠራ ሆኖዋል። በቀድመው ምዕራፍ በሮሜ 9-11 የማይቀየረው የእግዚአብሔር ምዕረት ብቻ ነው። ሮሜ 9፡ 15,16,18,2311፡30,31,32 ምህረት ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ አይነተኛ መንገድ ነው።

**9፡17-18** የተወሰደው ከዘፀ 9፡16 ላይ ነው። የፈርኦንን ልብ አጠናከረ ዘፀ 8፡15,32፡9፡34 እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ እንደሚያጠነክረው ተናገረ። ይህም ፈረኦን እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን እንዲያሳይ የተጠቀመበት ንጉስ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የተጠቀመው በፈርኦን ልብ ደንዳናነት እና በአስቸጋሪ ባህሪው ነበር፤ ሮሜ 9፡18።

እግዚአብሔር ለማዳን ፈርኦን ላይ ያደረገውን እንመልከት፡-

1. እግዚአብሔር ታላቅ ሃይሉን አሳይቷል (ይህም ከአማልክቶች የበላይ መሆኑን)፡፡
2. ግብፃውያን እግዚአብሔር እንዲያውቁት አድርጓል፡፡

እግዚአብሔር ላልዳነው አለም ማዳኑን ሊያሳይ ሲፈልግ ፈርኦንን መረጠው፡፡ እግዚአብሔር ሉአላዊ አምላክ መሆኑ በብዙ ማስረጃዎች አሳይቷል፡፡

1. ኢዮብ መከራ ተቀብሏል በእግዚአብሔር ፈቃድ በሰይጣን ክስ መሰረት የሚከተለውን ምዕራፎች ተመልከቱ(ሉአላዊነቱን ያመለክታል)፡- (ኢዮ 1 እና 2)፡፡
2. በአካን ሃጢያት ምክንያት እስራኤል ተሸነፈ (ኢያሱ 7)፡፡
3. ከዳዊት ሃጢያት የተነሣ የዳዊት ልጅ መሞት (2 ሳሙ 12፡15)፡፡

እግዚአብሔር ሉአላዊነቱን በእነዚህ ሰዎች ላይ በቀጣትና ለማስተማሪያም ሊያደረግ ይታያል፡፡

**ሮሜ.** 9፡19-26
***እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል? ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው? ትለን ይሆናል ነገር ግን አንተ ሰው ሆይ እግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ስራ ሠሪውን ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን? ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ስልጣን የለውም? ነገር ግን እግ/ር ቁጣውን ሊያሳይ ሃይሉንም ሊገልጥ ወደ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምዕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለ ጣዓላት ይገልኝ ዘንድ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግስት ከአይሁድ ብቻ አይደሉም ነገር ግን ከአህዛብ ደግሞ የጠራን እኛን ነው፡፡እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ፡፡ ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብዬ፥ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ እጠራለሁ፤እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለላቸውም ስፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ ይላል፡፡***

9፡19 **"*ማን ይቃወመዋል*"** *ይህ አረፍተ ነገር የሚያሳየው ቀጣይነት ያለው ነገር እንደሆነ ነው ከ2ቆሮ* 20፡6, *ኢዮ*. 9፡12 *መዝ* 135፡6 *ዳንኤ* 4፡35 *ያመሳክሩ በዚህ ክፍል ላይ ሁለት የተለያየ አይነት ነገሮች ይታያሉ፡፡*(1) *እግዚአብሔር ለሰዎች ያዘጋጀው ደህንነት፡- ይህ ዕቅድ የማይታጠፋ ዘላለማዊ ሆኖ ይኖራል፡፡*(2) *እግዚአብሔር ሰዎችን ለራሱ አላማ ይጠቀማል ለመልካም ሙሴን፤ለክፉ ፈርኦንን-* (*ዘፀ* 3፡7-9 *እና* 10)፡፡

9፡20-21 *ይህ የተወሰደው ከኢሳ* 29፡16, 45፡9-13 *እና ኤር* 18፡1-12 *ነው፤የሸክላ ሰሪው የተመሰለው በእግዚአብሔር ነው የሰው ልጆች ደግሞ ሸክላ ተብለዋል ዘፋ* 2፡7 *ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር ሉአላዊ ምርጫ ላይ ሦስት ሃሳቦችን ያነሣል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቁ.* 20 *ላይ ሲገኙ የሦስተኛው ግን በቁ* 21 *ላይ ይገኛል እርሱም፡-*(1) *ይስሃቅ እና እስማኤል ሮሜ* 8-9(2) *ያዕቆብ እና ኤሳው ሮሜ* 10-12(3) *ሕዝብ እስራኤል እና ሕዝበ ኤዶም ሮሜ* 9፡13

9፡22 **በጭቃ ላይ ስልጣን የለውምን"** *ይህ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ለማሳየት ፀሐፊው የተጠቀመበት ቋንቋ ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ምህርቱ ብዙ ነው ዘዳ* 5፡9-10 *ለፍጥረቱ ሩህሩህ ነው ህዝ* 18 *ክፉን ለራሱ ስራ ይጠቀማል፣ ሰይጣንን፣ ፈርኦንን፣ አሴርን፣ ናቡከደነጾርን ቂሮስን ወዘተ...*

▣

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | **"ቁጣውን ሊያሳይ ፈቃደኛ ሆኖአል"** |
| ***አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*** | **"ቁጣው ሊያሳይ ፈልጓል"** |
| ***አየመመቅ*** | **"ፍላጎት መቅስፍቱን ሊገለኝ"** |
| ***አእቅ*** | **"ፍላጎቱን ቁጣውን ሊገልኝ"** |
| ***ኢመቅ*** | **"ቁጣውን ሊገልጥ ተዘጋጀ'** |

*እግዚአብሔር ቁጣውን የሚያሳየው ሀይሉ እና የክብሩ ባለጠግነት እንዲታወቅ ነው፤ነገር ግን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የማዳን አላማ አለው፡፡*

▣ **የቁጣው *መጠቀሚያ*** - *ይህ እግዚአብሔር የማያምኑትን ለራሱ ክብር እንደሚጠቀምባቸው የሚያመለክት ነው፡፡*

▣

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*** | ***"የተዘጋጀ"*** |
| ***አየመመቅ*** | ***"የተሰራ"*** |
| ***አእቅ*** | ***"የተወሰነ"*** |
| **NSB** | ***"የታቀደ"*** |

*እነዚህ ዝርዝር ቃላቶች የሚያስረዱት በጅማሪው የፋፃሜን እንዲያመለክቱ የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው፡፡*

▣ **"ጥፋት"** *ልዩ ርዕስ በሚለው* 3፡3 *ተመልከቱ፡፡*

**9:23 "አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው"** ሮሜ 8:29-30 እና ኤፌ. 1:4,11 ይመለከቱ። በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ነው በዘፍ 9:8-17 እና 15:12-21 ላይ የሚገኙት ገደብ የማይሰራላቸው ቃል ኪዳኖች ናቸው፤ነገር ግን ሌሎች ቃል ኪዳኖች የሚፀኑት ሕጉን በማክበር ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል (የእግዚአብሔር ምርጫ ሮሜ 9 እና የሰው ነፃ ምርጫ ሮሜ 10)

እግዚአብሔር የራሱ ምርጫ ብቻ ነው ያለው? ሌሎችን ተቃውሞ ወይስ ሰው የራሱ የሆነ ብቻ ምርጫ አለው ሮሜ 9:30-10:21) (ኦገስቲን-ፒለገዮስ) እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ ነፃ ምርጫን ይሰጣል ምክንያቱም ሁሉም በእርሱ አምሳል ተፈጥረዋልና (ዘፋ 1:26,27)

▣ **"ክብር"** ሮሜ 3:23 ተመልከቱ።

**9:24** ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር የሁሉ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፤እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ምህረቱን ያደርጋል፤ዘፋ 3:5 ምክንያቱም በግልፅ እንደሚታየው እስከ ዘፋ 12 አይሁዶች አልነበሩም፤እስራኤል ለካህናት መንግስት እንደሆኑ የተጠየቁት በዘፀ 19:5-6 አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ ፍቃዱ ተገልጣል ኤፌ 2:11-3: ገላ 3:28 ቆላ 3:11
ሐዋርያው ጳውሎስ የጠቀሳቸው የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች፦

1. ቁ 25 ሆሴ 2:23
2. ቁ 26 ሆሴ 1:10
3. ቁ 27 ኢሳ 10:2 እና ሆሴ 1:10
4. ቁ 28 ኢሳ 10:23
5. ቁ 29 ኢሳ 1:9

**9:25-26** ይህ አውድ በቀጥታ ከግሪኩ የተወሰደ ነው። የሚያመለክተውም አስሩን የሰሜን ነገዶች ነው። ነገር ግን ጳውሎስ ለአህዛብ ተጠቅሞበታል የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የብሉይ ኪዳኑን ቃለ መሃላዎች የአዲስ ኪዳን ፍፃሜ እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል 2ቆ 6:16 ቲቶ፣ 2:14፣ 1ጴጥ 2:5-9 በመሆኑም የሆሴዕ ምንባብ እምነት የሌላቸውን እስራኤሎችን የሚያመለክት ሆኖአል። እግዚአብሔር ለእነዚህ አስር ነገዶች ምህረትና ፍቅሩን ካሳየ ለአህዛብም ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ፍቅሩን ያሳያል የሚል ህሳቤ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር እናያለን።

> **ሮሜ.** 9:27-29
> ***ኢሳያስም የእስራኤል ልጆች ቁጥር ምንም እንደ ባህር አሸዋ ቢሆን ቅሬታው ይድናል ጌታ ነገሩን ፈጽሞና ቆርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኸል ኢሳያስ እንዲሁ ጌታ ፀባኦት ዘር በላስቀረልን እንደ ሰዶም በሆነን ገምራንም በወስልን ነበር። ብሎ አስቀድሞ ተናገረ።***

9.27
**አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም**
**አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም, ኢመቅ** **"ምንም እንኳን"**
**አእቅ -** **"እንኳን"**

**9:27-28** ይህ በግሪክ ፅሑፍ ላይ የሌለ ዓረፍተ ነገር ነው። ነገር ግን በኋላ የተጨመረ ነው፤ ነገር ግን ከኢሳ 10:23 መጨረሻ ላይ የተወሰደ መሆኑ ግልፅ ነው።

▣ **"እንደ ባህር አሸዋ ቢሆን"** ይህ ለአብርሃም የተነገረውን የተስፋ ቃል ለምሳሌ ለማመልከት ፀሐፊው የተጠቀመበት ዓረፍተ ነገር ነው።

▣ **"ዘር ባለስቀረልን ነበር"** ይህ የእስራኤልን ልጆች ወደ ምርኮ የተወሰዱትን በሕይወት የተረፋትን ለማመልከት የተጠቀመበት ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ብዙዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባልሆኑ ጊዜ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በፈቃዳቸው የሚያመልኩ ቅሬታዎች ተብለዋል ኢሳ 1:10-20

> **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ ቅሬታዎች**
> **ሦስት አብይ ነገሮችን እንመልከት፦**
> 1. ቅሬታዎቹ ከምርኮ የተረፋት ያመለክታል ኢሳ 10:20-23
> ኢሳ 17:4-6 ኢሳ 37:31-32
> 2. ለእግዚአብሔርን ታማኝ የሆኑትን ያሳያል፤ (ኢሳ 4:1-5፣ ኢሳ 11:11,16፣ ኢሳ 28:5-21፣ ኢዩ 2:32, አምፅ 5:14-15)።
> 3. ለምፅአቱ ራሳቸው በንጽህና የጠበቁትን ያመለክታል አሞፅ 9:11-15

9.29 ይህ ከግሪኩ በቀጥታ የተወሰደው ከኢሳ1፡9 የሚናገረውም የእስራኤልን ሃጢያት ነው፡፡

▣ **"የሰንበት ጌታ"** ይህ የብሉይ ኪዳን ለያሕዌ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ በተለምዶ የፍጥረት ጌታ ያዕ 5፡4 ከአንድ አውድ ከሌላኛው አውድ ቃሉ አጠቃቀም ሊለያይ ይችላል "የስራዊቶች አለቃ" ሊሆንም ይችላል ኢያሱ 5፡13-15 በተለይ የባቢሎናውያን አምላኮች በሠማይ ሠራዊት ይመሰላሉ፡፡ ዘፍ 1፡16, መዝ 8፡3, መዝ147፡4 ኢሳ 40፡20 ያመሳክሩ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ -** | **"ቅሪትን ባልተወልን ነበር"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ዘርን ባላስቀረልን ነበር"** |
| **አየመመቅ** | **"የተረፋትን ባልተወልን ነበር"** |
| **አእቅ -** | **"ዝሪያን ባልተወልን ነበር…"** |
| NSB | **"ጥቂት የተረፋትን ባልታወስን ነበር"** |

በዕብራይስጥ ኢሳ 1፡9 "ቅሬታ" በግሪክ ደግሞ ዘር ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ቀጣይነት ያላቸው ሁለት ነገሮች፡- (1) ቅሬታ፣ (2) የመሲሁ ዘር፡፡

▣ **"ሰዶም እና ገሞራ"** ቁ.28 የእግዚአብሔር ፍርድ ለማመልከት ይረዳል፡፡ እነዚህ ሁለት የአሕዛብ ከተሞች በእግዚአብሔር ፍርድ የጠፉ ከተሞች ናቸው ዘፋ 19፡24-26 ከዚህ ቀድሞ ያልታየ የእግዚአብሔር ፍርድ የታዩባቸው ከተሞች ናቸው፡፡ (ዘዳ 29፡34፣ ኢሳ 13፡19፣ ኤር 20፡16፣ ኦም 4፡11፣ ኤር 50፡40)

**9፡30-33 እንግዲህ ምን እንላለን? ፅድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ፅድቅን አገኙ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ፅድቅ ነው፡፡ እስራኤል ግን የፅድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ህግ አልደረሱም ይህም ስለ ምንድንነው? በስራ እንጂ በእምነት ፅድቅን ስላልተከተሉ ነው እነሆ በፅዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፋርም…"**

9-30-31 ይህ የሚያስደንቅ የእግዚአብሔር የምርጫ ዕቅድ የተገለጠበት ቦታ ነው፡፡ ቁ 30-33 የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ እና የምዕራፍ አስር ማስጀመሪያ ሃሳብ ነው፡፡ መንገዳቸው ያስተካከሉ አሕዛብ እንጂ አይሁድ ሁሉ የእግዚአብሔር ወገን ላይሆን ይችላል፣ የሰው ዘር ሁሉ የሚድነው፡-(1) በእግዚአብሔር ሉአላዊነት (2) በክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ስራ (3) በግለሰቡ እምነት

▣ **"ፅድቅ"** ሮሜ 1፡17 ይመልከቱ፡፡

9፡32 "በስራ"፡- ሕግ የሚለው ቃል በኃላ በፀሐፊው የተጨመር ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በህግ ስራ የሚል ሐረግ አይጠቀምም (ሮሜ 3፡20,28፣ ገላ 2፡16፣ ገላ 3፡2,5,10፣

በጥንት ግሪክ ፅሑፍ A,B,F እና G የለውም፡፡ ፅድቅ የማግኛው መንገድ የክርስቶስ የመስቀል ስራ እንጂ የሰው የተሻለ የሚባል ጥረቱ አይደለም ሮሜ 3፡21-31 ነገር ግን ሰው ሁሉ ሊቀበለው የተገባ ነው፡፡
(ሮሜ 9፡33፣ ዮሐ 1፡12፣ ሮሜ 4፡1፣ ሮሜ 10፡9-13፣ ኤፌ 2፡8-9)፡፡

ደርጅ ኤልደን ቲዎሎጂ ኦፋ ዘ ኒው ቴስታመንት በተሰኘው መፃፍ ላይ "ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሕግ ያለው አመለካከት በግዜው የነበረውንም ሕግ በማዛመድ ነው፡፡" የሚል ትንተና ይሰጣል፡፡
እንግዲህ ሐዋርያው ጳውሎስ በጊዜው የነበረውን ሃሳብ በማጣቀስ ወደ መንፈሳዊ ሃሳብ በመቀየር ለጊዜው ለነበረው ለተየለ ሁኔታ ስለ መለኮታዊ ህግ ትንታኔ የሰጠበት መንገድ ይታያል፡፡

9፡33 ይህ የተወሰደው ከኢሳ 28፡16 ላይ ነው፡፡
"እንሆ ለፅዮን ድንጋይ አኑሬአለሁ" ኢሳ 28፡16
"የማስናከያ አለት" ኢሳ 8፡14
"በእርሱ የሚያምን አያፋርም" ኢሳ 28፡16
እነዚህን ጥቅሶች በእንዲህ መልክ በማሰባሰብ ቃሉ ከአዎንታዊ ወደ አሉንታዊ ትርጉሙን ሲያመጣው ይታያል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይን ቃላት ለራሱ አላማ እንደሚጠቀምበት ያመለክታል፡፡

1. የሚጠቀመው ትርጉም ( የግሪኩ,የዕብራይስጡ ወይም የራሱን)
2. ሃሳቦችን ይቀይራል ለምሳሌ (ባቢሎንን ወደ አህዛብ)
3. አውዶችን ያገናኛል
4. ርዕሶችን እና ተውላጠ ስሞችን ይቀይራል ለምሳሌ፡- ያህዌን ወደ ኢየሱስ

▣ **"በእርሱ የሚያምን አያፋርም"** ከኢሳ 28፡16 የተወሰደ ነው በሮሜ 10፡11 ላይ ይገኛል ከአዮ 2፡32 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ይህም በሮሜ 10፡13 ተፅፏል ይህም የደህንነት ቁልፋ፡- (1) የማዕዘኑ ድንጋይ (2) የአንድ ግለሰብ እምነት (በእርሱ የሚያምን)፡፡

▣ "አለት" ይህ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ነው። (መዝ 18፡1-2,3፣ ዘዳ 32፡18፣ 1ሳሙ 2፡2፣ መዝ 28፡1፣ መዝ 31፡3፣ ይህ ስያሜ ለመሲሁም ተሰቷል፦ ዘፋ 49፡24፣ መዝ 118፡22፣ ኢሳ 8፡14)።ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አልተረዱም 1ቆሮ 1፡23 በተጨማሪም አይሁዶች መሲሁን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የዘላለም ቃል ኪዳን በአጠቃላይ አልተረዱም። ኢሳ 8፡14 ሉቃ 2፡34 ላመኑት ሁሉ ግን የሚከተለውን ጥቅስ ይመልከቱ፦ ኢሳ 28፡1 1ጴጥ2፡6-16

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ "የማዕዘን ድንጋይ"**

I. የብሉይ ኪዳን አጠቃቀም
   ሀ. የማይሻርን ኪዳን ለማመልከት መዝ 18፡1
   ለ. መሲሁን ለማስታወስ ዘፋ 49፡24, መዝ 118፡22
   ሐ. በመሲሁ በኩል የሚመጣውን የእግዚአብሔር ፍርድ ለማመልከት (ኢሳ 8፡14፣ ዳን 2፡34-35
   መ. ተምሳሌያዊ ንግግር
      1. የመሠረት አለት ወይም የቤት መጋጠሚ ዋና የማዕዘን ድንጋይ ከላይ ያለው የመጋጠሚያ ድንጋይ ዘካ 4፡7፣ ኤፌ 2፡20,21)
      2. "ካፕስቶን" ዕብራይስጡ ራሽ" ማለት ራስ የሚል ትርጉም አለው፤
      3. ዋና ድንጋይ ሁሉን አጋጣጥሞ የሚያስተሳስር

II. የአዲስ ኪዳን አጠቃቀም
   1. ኢየሱስ መዝ 118 በተደጋጋሚ ይጠቅስ ነበር (ማቴ 21፡41-46፣ ማርቆ 2፡10-11፣ ሉቃ 20፡17)።
   2. ሐዋርያው ጳውሎስ የእስራኤልን አመፀኝነት ገልጾበለታል (ሮሜ 9፡33)።
   3. ቁልፍ ድንጋይ ወይም ዋና ድንጋይ (ኤፌ 2፡20-22)።
   4. ሐዋርያው ጴጥሮስ የጠቀሰው ኢየሱስ የማዕዘን ራስ ነው ደግሞም ሕዝቡ ደግሞ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው በማለት ነው (1ጴጥ 2፡1-10፣ 1ቆሮ 6፡19)

   ነገር ግን አይሁዶች የሕይወት መሠረት የሆነውን እግዚአብሔር መቃወማቸው ሁሉን እንዲያጡ አድርጓቸዋል።

III. ስነመለኮታዊ ሃተታ
   ሀ. ያህዌ ዳዊትን እና ሠለሞንን በመቅደሱ ስራ ውስጥ እንዲሳተፋ አደረጋቸው፤ቃል ኪዳኑን ቢጠብቁ መቅደሱ እንደሚጠበቅ ነገር ግን ኪዳኑን ባይጠብቁ መቅደሱ እንደሚፈርስ ተናገረ።1 ነገ 9፡1-9
   ለ. የአይሁድ ሃይማኖት በስርአታቸው ላይ ያተኩራሉ እግዚአብሔር ግን የግል ህብረትን ይፈልጋል።
   ዘፋ 1፡26-27 ሉቃ 20፡17-18
   ሐ. ኢየሱስ የመቅደስን ምሳሌ በሰውነቱ መሰለ መሲሁን መወቅ እግዚአብሔር እንደማወቅ መሆኑን አስተማረ።
   መ. ደህንነት ማለት የፈረሰውን ሕብረት እንደገና ማደስ ነው። የክርስትና ቁልፍ ሃሳብ ክርስቶስን መምስል ነው።
   ሠ. ኢየሱስ የእምነታችን መሠረት ነው። (አልፋ እና አሜጋ ነው) ነገር ግን ለማያምኑ የማስናከያ አለት ነው። እርሱን ማጣት ሁሉን እንደማጣት ይቆጠራል።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን። እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም።

እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉን ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው።

1. በምዕራፍ 9 ላይ ያለው አስቀድሞ ወስኗል እና በምዕራፍ 10 ላይ ለሰው ነፃ ምርጫ ተሰቷል የሚለውን ተወያዩበት።
2. የምዕራፍ 9፡1-29 ዋናው ጭብጥ ምንድነው?
3. እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳን ሽሯልን?
4. እስራኤሎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ዕድሎች ዘርዝር።
5. ሁሉም አይሁድ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ናቸው ለምን ሆኑ? ለምን አይደለም (9፡6)?
6. የእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ ሰው እንዲፈፅም ከተገደደ ኃላፊነቱን ተወቷል ማለት ይችላልን?
7. ምህረት የሚለው ሃሳብ በእግዚአብሔር አስቀድሞ ወሳኝነት ያለው ድርሻ ምንድነው

# ሮሜ 10

## በዘመናችን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እስራኤልና ወንጌል | እስራኤል ወንጌል ያስፈልጋታል | ፅድቅ በእምነት ነው | እስራኤልና ወንጌል | እስራኤል እግዚአብሔርን ከማመን ተሰናከለች |
| | | 9:30-10:4 | 9:30-10:4 | |
| 9:30-10:4 | | | | |
| | 10:1-13 | | | 10:1-4 |
| ድነት ለፍጥረት | | እስራኤል ሃላፊነቱን ወስዳለች | ድነት ለፍጥረት | |
| 10:5-13 | | | 10:5-13 | 10:5-13 |
| | እስራኤል ወንጌልን አልተቀበለችም | | | የሙሴ ምስክርነት |
| 10:14-21 | 10:14-21 | 10:14-17 | 10:14-17 | 10:14-17 |
| | | 10:18-21 | 10:18-21 | 10:18-21 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ፤በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. ምንባብ አንድ

2. ምንባብ ሁለት

3. ምንባብ ሦስት

4. ወ.ዘ.ተ

**የአውዱ ዳሰሳ**

ሀ. ምዕራፍ አስር እስራኤል ከእግዚአብሔር የተሰጣትን የደህንነት በረከቶች ያሳያል፤ ምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ እግዚአብሔር አይሁድን መምረጡ ሰውን ሁሉ ለማዳን ያዘጋጀው መሆኑን ያሳያል፤ ነገር ግን አይሁዶች ተቃወሙት፡፡

ለ. ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን መፅሐፋትን ለአዲስ ኪዳን ማጠናከሪያ ይጠቅሳል ይህም “ኬሪጋም” ይባላል ማለት “እወጃ” ማለት ነው፡፡

ሐ. እውነቶቹ እንደሚከተሉት ናቸው ሮሜ 9:30-40
1. ሕህዛብ በእምነት በክርስቶስ የሚገኘውን ፅድቅ ያገኛሉ፡፡
2. አይሁዶች ያለ እምነት የፅድቅ ተካፋይ አይሆኑም፡፡
3. ሕጉ ሰውን አይፀድቅም፡፡

መ. ብሩስ እና ኩራትስ የመመሪያ መፃፋቸው ላይ የሚከተለው ዝርዝር አለ፡- ገፅ 115-116 (ስለ አይሁድ አጢያት)

1. የሐይማኖት አክራሪነት ሮሜ 10፡2
2. መንፈሳዊ ዕውርነት ሮሜ 10፡2,3
3. ራስን ማፅደቅ ሮሜ 10፡3
4. የልብ ጠማምነት ሮሜ 10፡4

በምዕራፍ ዘጠኝ እና አስር ላይ ማጠቃለያ ተሰቷል፤ይህም ድነት የሚገኘው በመስቀሉ ስራ ብቻ ነው፡፡ 1ተስሎ 1፡4-10 በመሆኑም ወንጌልን መስበክ የእግዚአብሔርን ዓላማ የማስፈፀሚያ ዋና መንገድ ነው፡፡

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

| |
|---|
| ሮሜ 10፡1-4<br>**ወንድሞች ሆይ የልቤ በጎ ፋቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲደኑ ነው፡፡ በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመክራቸዋለሁ፡፡ የእግ/ርን ፅድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ፅድቅ ሊያቆሙ ሲፈለጉ ለእግዚአብሔር ፅድቅ አልተገዙም፡፡ የሚያምኑ ሁሉ ይፀድቁ ዘንድ ክርስቶስ የህግ ፋፃሜ ነውና፡፡** |

10፡1 **"ወንድሞች"** የሐዋርያው ጳውሎስ የተለመደ ንግግሩ ነው (1፡13፣ 7፡1,4፣ 8፡12)፡፡

▣ **"የልቤ ፍላጎት ለእነርሱ ሁሉ እንዲድኑ ነው"** ሐዋርያው ጳውሎስ ለአይሁድ ስለድነት የሚፀልየ ፀሎት እንደሚሰማ አምኗል፡፡

የግሪኩ ትርጉም "ለእነርሱ" የሚለው ለእስራኤል በሚል ተክቶታል፡፡

10፡2 **"ለእግዚአብሔር ቀንተዋል"** ታማኝነት እና የጋለ ፍላጎት ብቻ በቂ አይደለም (ሮሜ 3-4፣ ሐዋ 9፡1፣ ገላ 1፡14፣ ፊሊ. 3፡6)፡፡

▣ 10፡2-3 **"በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለ"** ማወቅ የሚለው ቃል (epiginosko) ተብሏል፡፡ ለሁለት ትርጉም ያገለግላል፡- (1) አይሁድ ነፃ የሆነውን ወንጌል አልተረዱም፣ (2) አይሁድ በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር አልተዛመዱም፡፡ ዕብራይስጡ "ማወቅ" ዘፋ 4፡1, ኤር 1፡5 ይመልከቱ ፡፡

10፡3 **"የእግ/ር ፅድቅ"** ሮሜ 9-11 የእግዚአብሔር አቋም ይጠቁማል ይህም በፍቅሩ, በምህረቱ, በተከናወነው የመስቀል ስራ በንስሃ፣ በእምነት፣ ቀጣይነት ባለው መታዘዝ እና በመፅናት ብቻ ይከናወናል፡፡

አይሁድ የእግዚአብሔርን ፅድቅ በተሳሳተ መረዳት ተረድተውታል ለህግ መታዘዛቸው ዘዳ 4፡28-6፡3,17,24-25 እውነትን እና ንስሃን ያማከለ ሊሆን ይገባል ዘዳ 5፡29-30,6፡5፡፡

▣ **"ለእግዚአብሔር ፅድቅ እራሳቸውን አላስገዙም"** ይህ የወታደራዊ ቃል ነው፤ ትርጉሙም ለአንድ አለቃ ራስን አለማስገዛት ማለት ነው፡፡ አይሁድ የእግዚአብሔርን ፅድቅ በስራ ማግኘት ፈልገው አልቻሉም፤ ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ሮሜ 3፡24,5፡15 ኤፊ 2፡8-9 ይህንን ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ በግልፅ ተመልክቶታል፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ መገዛት** (Heptoses)

የግሪኩ ቃል አስር የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃሎችን ለዚህ ቃል ይጠቀማል በብሉይ የነበረው የዚህ ቃል ትርጉም "ትዕዛዝ ወይም "ትክክለኛ ትዕዛዝ" በሚል ተተርጉሟል፡-

1. እግዚአብሔር ያዛል ዘሌ 10፡1 ዮና 2፡1
2. ሙሴ ያዛል ዘፀ 36፡6 ዘዳ 27፡1
3. ነገስታት ያዛሉ 2ዜና 31፡13

በአዲስ ኪዳን ሐዋርያቶች ይጠቀሙብታል ሐዋ 10፡48

1. በጎ ፈቃደኝነትን ለመግለጽ
2. ኢየሱስ ራሱን ለአብ ማስገዛት ኤፌ 5፡22-24 ቆላ 3፡28
3. አማኞች ለባህሉ ራሳቸውን ስለ ወንጌል ሲሉ ማስገዛት አለባቸው፡፡
   ሀ. አማኞች ሁሉ (ኤፌ 5፡21)፡፡
   ለ. የአማኝ ሚስቶች (ኤፌ 5፡22-24,ቶላ 3፡28(፡፡
   ሐ. አማኞች ለማያምኑ ነገስታት (ሮሜ 13፡1-7 1ጴጥ 2፡13)፡፡

አማኞች ለእግዚአብሔር ፤ለክርስቶስ ፤ለእግዚአብሔር መንግስት እና ለሌሎች ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

10:4

*አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*

NRኢ *መ ቅ* — *"ክርስቶስ የሕግ ፍፃሜ ነው"*

*አእቅ* — *"ክርስቶ የሕግ ፋፃሜን አምኘቷል"*

*ኢመቅ* — *"አሁን ሕግ በክርስቶስ ወደ ፋፃሜው መቷል"*

*ማቴ* 5:17-8 *ይመልከቱ። የሕግ አላማ እና ፋፃሜ ደህንነት አይደለም፤ ነገር ግን ስርዓት ማስጠበቂያ ነው* (*ገላ* 3:24-25፣ *ገላ* 3:1-29)።

*ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን ጥቅሶች ሲጠቀም እንደ አወዱ ትርጉማቸውን ሲለዋወጣቸው ማጤን ተገቢ ነው፤ ይህም በብሉይ የተነገሩት ንግርቶች እና ቃላት ከአዲሱ ዘመን ጋር ለማጣጣም የሚደረግ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሕግ ያለውን አመለካከት ይመልከቱ ሮሜ* 13:9

▣

*አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* — *"የሚያምን ፅድቅን ያገኛል*

NSV — *"ስለዚህ ለሚያምኑ ሁሉ ፅድቅ ይሆንላቸዋል"*

*አእቅ* — *"የሚያም ከእግዚአብሔር ጋር መንገዱን አስተካክሏል"*

N*ኢመቅ* — *"የሚያምን ይፀድቃል"*

*ምዕራፋ ዘጠኝ እና አስር በአንድ ላይ መተርጎም ያለባቸው ምዕራፎች ናቸው፤ ምዕራፋ* 9 *ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ሉአላዊትን እናያለን፣ ምዕራፋ* 10 *ላይ ለሰው ሁሉ የተደረገውን ጥሪ ያሳያል።*

*የእግዚአብሔር የማዳን አላማ ዘፋ* 3:15 *እና* 12:3 *እና ዘፀ* 19:5-6 *ይመልከቱ። እግዚአብሔር በአምሳሉ በተፈጠሩ መሃከል አያዳላም። እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ወደ ደህንነት ይጠራል?* (*ዮሐ* 3:16፣ 1*ዮሐ* 2:2-4፣ 1*ጢሞ* 2:4፣ 2*ጴጥ* 3:9) *ማመን የሚለው ቃል* (Pasteur) *በሦስት የእንግሊዘኛ ቃሎች ተተርጉሟል* Believe፣ Faith ፣Trust *እነዚህ በአማርኛ ተመሳሳይ ትርጉም ይኖራቸዋል፤የተፃፍትም በአሁን ጊዜ አመልካች ቃል ነው።*

---

*ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ የግሪኩ ቃል "ድነት"*

*ድነት የሚፈጠር ሳይሆን ግንኙነት ማድረግን የሚያሳይ ነው፤ ከተሰራው የላቀ ስራ የተነሣ ደህንነትን መቀበል ይቻላል፡፡ደህንነት የተጠናቀቀ ስራ ነው፤ የሚከተሉት ጥቅሶችን ይመልከቱ።*

- *ሐዋ* 15:11
- *ሮሜ* 8:24
- 2*ጢሞ* 1:9
- *ቲቶ* 3:5
- *ሮሜ* 13:11

*ደህንነት ሙሉነት ነው የሚከተለውን ጥቅስ በአግባቡ ይመልከቱ፡-*

- *ኤፌ* 2:5-8

*ደህንነት ቀጣይነት ያለው ነው የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከሩ፡-*

- 2 *ቆሮ* 1:18:15:2
- 2 *ቆሮ* 2:15

*ደህንነት የወደፊቱንም የሚያሳይ ነው ሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከሩ፡-*

- *ሮሜ* 5:9-101
- *ቆሮ* 3:15
- *ፊሊ* 1:28
- *ዕብ* 1:14
- *ማቴ* 10:22

---

*ሮሜ* 10:5-13

***ሙሴ ከህግ የሆነውን ፅድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ፅፎአልና ከእምነት የሆነ ፅድቅ ግን እንዲህ ይላል በልብህ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል። አትበል ይህ ክርስቶስን ለማውረድ ነው ወይም በልብህ ወደ ጥልቁ ግን ይወረዳል? አትበል ይህ ክርስቶን ከመታን ለማወጣት ነው ነገር ግን ምን ይላል? በአፋህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፊህ ብትመሠክር እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል በአፋ መስክሮ ይድናልና መፅሐፋ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፋርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።***

**10:5** ከዘሌ 18:5 የተወሰደ ነው፡፡ ሉቃ 10:28, ገላ 3:12 ችግሮቹ ሮሜ 3:9,10-18, 19,23 ሃጢያትን የምታደርግ ነፍስ ትጠፋለች ዘፋ2:17, ዘዳ 30:18,ሕዝ18:4,20 አሮጌው ኪዳን አልፏል፤ የሞት ቅጣት ሮሜ 7:10, ገላ 3:13, ቆላ 2:14
**10:6-8** ዘዳ 30 11-14 ይመልከቱ ለሙሴ የተነገረ ቃል ነው፡፡ ነገር ግን የኢየሱስን ሞት እና ትንሳኤ ለመግለፅ አገልግሏል ኤፌ 4:9-10 ዘዳ 30:15-20 (ከሙሴ የተለየ የሕግ አተረጓጎም)

▣ **"ከእምነት የሆነ ፅድቅ"** ጳውሎስ ስለ ሃጢያት እና ሰለ ፀጋ ተናገረ፤ፅድቅ በእምነት በኩል ብቻ የሚከናወን ነው፡፡ ሮሜ 10:6-8

▣ **"መውጣት መውረድ"** የሰው ልጅ ክርስቶስን ፈልጋ የትም መሄድ አይችልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ክርስቶስን በሚታይ መልኩ ለሰው ሁሉ ይገልጸዋል፡፡

▣ **"ልብ"** ማንነትን የሚገልፅ ብልት ነው፡፡

**10:9 "እንደሆነ..."** የወደፊት አመልካች ቃል ነው፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ : መመስከር**

ሀ. ለዚህ ቃል ሁለት የተለያዩ የግሪክ ትርጎሞች ተሰተውታል "Homologue እና exomologeo:- home "አንድ አይነት" እና logeo "መናገር"

ለ. የእንግሊዘኛው ፍቺ
1. ማመስገን
2. መስማማት
3. ማወጅ
4. መተንበይ
5. መመስከር

ሐ. የቃሉ ሁለት አይነት አጠቃቀም
1. ማመስገን (እግዚአብሔርን)
2. በሐጢያትን መፀፀት

የእግዚአብሔር ቅድስና እና የሰውነ ሐጢያተኝነትን የሚገልፅ ቃል ነው፡፡

መ. በአዲስ ኪዳን የቃሉ አጠቃቀም የሚከተለው ነው፤
1. ቃል ኪዳን
2. መስማማት ዮሐ 1:20,ሉቃ 22:6
3. ማመስገን ማቴ 11:25, ሉቃ 10:21
4. መስማማት
   ሀ. ለግለሰብ (ማቴ 10:32፣ ሉቃ 12:8፣ ዮሐ 9:22)
   ለ. ለእውነት (ሐዋ 23:8፣ 2ቆሮ 11:13፣ 1ዮሐ 4:2)
5. በሰዎች ፊት ማወጅ (የራስን እምነት ለመግለፅ) ሐዋ 24:1 1ጢሞ 6:13)
   ሀ. ከበደለኝነት ነፃ መሆን (1ጢሞ 6:12, ዕብ 10:23)
   ለ. ከመበደል ነፃ አለመሆን (ማቴ 3:6፣ ሐዋ 19:18፣ ዕብ 4:14፣ ዕብ 5:16)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እየሱስ እርሱ ጌታ ነው"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ጌታ ኢየሱስ"** |
| **NRኢ መ ቅ ,አእቅ,ኢመቅ** | **"ኢየሱስ ጌታ ነው"** |

ይህ በጥንቷ ቤተክርስቲያን የሚደረግ የእምነት መግለጫ እና የጥምቀት ስርዓት ማስኬጃ አረፋተነገር ነው፡፡ (አዩ 2:32፣ ሐዋ 2:32-33,36፣ ፊሊ. 2:6-11)

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ የጌታ ስም**

ይህ የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን መገኘት እና እግዚአብሔር እንደሚሰራ ለማመልከት የሚጠቅም ቃል ነው፡፡ ፊሊ. 2:11 ይመልከቱ፡፡

1. በጥምቀት ጊዜ ሰዎች የሚናገሩት ቃል፡- (ሮሜ 10:9-13፣ ሐዋ 2:38,8:12,16,10:48,19:5,22:16፣ 1ቆሮ 1: 13,15፣ ያዕ 2:7)
2. አጋንቶች ሲወጡ፡- (ማቴ 7:22፣ ማርቆ 9:38፣ ሉቃ 9:49
3. በፈውስ ጊዜ፡- (ሐዋ 3:6፣ ያዕቆ 5:14)

4. በአገልግሎት ጊዜ፡- (ማቴ 10፡42፣ ማቴ 18፡5፣ ሉቃ 9፡48)
5. ቤተክርስቲያን በምትቀጣ ጊዜ፡- (ማቴ 18፡15-20)
6. ለአሕዛብ ወንጌል ሲሰበክ፡- (ሉቃ 24፡47፣ ሐዋ 9፡15)
7. ለፀሎት ፡- (ዮሐ 14፡13፣ ዮሐ 15፡2,16፣ 1ቆሮ 1፡2)
8. የክርስትናን እምነት ለመግለፅ፡- (ሐዋ 26፡9፣ 1 ቆሮ 1፡10፣ 2ጢሞ 2፡19)

▣ **"በልቡ አምኖ"** ማወጅ የሚለው አቻ ቃሉ ነው፡፡ ማመን (pistils) ማለት፡- (1) የግል እምነት (ዕብራይስጥ) (2) በዕውቀት የተመረኮዘ (ግሪኮች) (3) መሰጠት ዘዳ 30፡20

በጥንት ጊዜ "ልብ የሚለው የሰው ምላተስብዕና ለማመልከት የሚያገለግል ነበር ዘዳ 30፡20፡፡

▣ **10፡10 "ፅድቅን ማግኘት"** የእግዚአብሔር ዓላማ ሰዎችን መንግስተ ሰማይ ማስገባት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሰው ሁሉ ክርስቶስን (ልጁን) እንዲመስል ነው፡፡ የተመረጡ ሰዎች በጽ ድቅ ሊኖሩ ይጠየቃሉ ዘዳ 30፡15-20

ቁ.10 ይህ ቁጥር የታላቁ ተልኮን ያሳያል ማቴ 28፡19-20 ያንብቡ፤ ደህንነት (ሰዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ) እና ፅድቅ (ሰዎችን ለማስተማር መዘዝ) ኤፊ 2፡8-9 ነፃ ምርጫ በፀጋ እና ጥሪን ያመለክታል፡፡ ኤፊ 2፡10

**10፡11** ከኢሳ 28፡16 ተወስዶ ሐዋርያው ጳውሎስ "ማንም ሆነ ማንም" የሚለው ቃል ጨምሯል፤ኢሳያስ በእምነት መሲሁን ማግኘት እንደሚቻል ተነበየ እርሱም እግዚአብሔር የማዕዘን ድንጋይ ነው ሮሜ 9፡32-33 "እያንዳንዱ" ቁ4 እና "ማንም" እና "ሁሉም" እነዚህ የምዕራፋ 9 ዋና ቃላቶች ናቸው፡፡

▣ **"በእርሱ የሚያምን"** 1ጢሞ 1፡16 ይመልከቱ፤ ማመን የአንድ ጊዜ ክርስትና ሳይሆን ነገር ግን ወደ ፊትም የሚቀጥል ሂደት ነው ሦስት ነገሮችን ማጤን አለብን እነርሱም፡- የወንጌል እውነት ዘወትር መኖር አለበት፣ ሰው ወንጌልን በቀጣይነት ማመን አለበት፣ ሰው ወንጌልን በቀጣይነት መኖር አለበት፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ,አእቅ** | **"አትከፋም"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም, አየመመቅ** | **"አታፋርም"** |
| **ኢመቅ** | **"በምክንያት አታፋርም"** |

**10፡12 "እንግዲህ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች መሃከል ልዩነት የለም"** ሮሜ 3፡22, 29, ኤፌ. 2፡11, ቆላ 3፡11 እግዚአብሔር የጠፋውን አለም እንደገና ዋጅቷል፡፡ በግሪክ እና በአይሁድ መካከል ልዩነት የለም፡፡ በአይሁድ እና በሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፡፡ በሰው ልጆች መሃከል መለኮት አያዳላም አዩ 2፡28-29 ፊሊ 4፡19 ቆላ 1፡27,2፡2፡፡

**10፡13** ከኢዮ 2፡32 ይህንን የጳውሎስን ምንባብ ሁለቱን አጠቃቀሙን እንመልከት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ያሕዌ የሚለሙን ስያሜ በሮሜ መፅሐፋ ውስጥ ተጠቅሚል ፤ጴጥሮስ ደግሞ ኢየሱስ በሚል ተክቶታል ሐዋ 2፡21, ዮሐ 12፡41, ኢሳ 6፡9-10 ፊሊ 2፡9 እና ኢሳ 45፡22-25, ሮሜ 9፡33 እና ኢሳ 8,13-14፣ አዳኝ ወይም ነፃ አውጪ ይህ የሚያመለክተው ይቅርታን እና የዘላለምን ሕይወት ነው ፤በዚህ መልክ ስሙን መጥራት እምነትን የመግለጫ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ፡- (ሐዋ 7፡59,9፡14,21፣ 1 ቆሮ 1፡2፣ 2 ጢሞ 2፡22)

**ልዩ ርዕስ፡ ኢየሱስ የናዝሬቱ**

በርካታ የተለያዩ የግሪክ ቃላት አሉ፣ ማለትም አኪ በተብራራ መልኩ ኢየሱስን የሚገልጽበት

ሀ. የአኪ ቃላት

1. ናዝሬት - በገሊላ ያለች ከተማ (ሉቃስ 1፡26፤ 2፡4፣39፣51፤ 4፡16፤ ሐዋ. 10፡38)፡፡ ይህች ከተማ በተጓዳኝ ምንጮች አልተጠቀሰችም ነገር ግን በቅርብ ጊዜ ጽሑፎች ላይ ተገኝታለች፡፡
   ኢየሱስ ከናዝሬት መሆኑ አሻሚ አይደለም (ዮሐንስ 1፡46)፡፡ በኢየሱስ መስቀል ላይ የተደረገው የዚህ ስፍራ ምልክት ስም ለአይሁድ የንቀት ማሳያ ነው፡፡
2. ናዛሪዮስ - የሚያመለክተው ደግሞ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን ነው (ሉቃስ 4፡34፤ 24፡19)፡፡
3. ናዛራዮስ - የሚያሳየው ከተማን ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ደግሞ በዕብራይስጡ መሲሐዊ ቃል "ብራንች" ጨዋታን (ትርዒትን) ያሳያል (ኒዘር፣ ኢሳ. 4፡2፤ 11፡1፤ 53፡2፤ ኤር. 23፡5፤ 33፡15፤ ዘካ. 3፡8፤ 6፡12)፡፡ ሉቃስ ይሄንን ለኢየሱስ ይጠቀምበታል በ18፡37 እና ሐዋ. 2፡22፤ 3፡6፤ 4፡10፤ 6፡14፤ 22፡8፤ 24፡5፤ 26፡9፡፡

ለ. በአኪ ውጪ ታሪካዊ አጠቃቀሙ፡፡ ይህ ሹመት ሌላም ታሪካዊ አጠቃቀም አለው፡፡

1. እሱም የሚያሳየው የአይሁድን (ቅድመ ክርስትና) የመናፍቃን ወገንን ነው፡፡
2. እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በአይሁድ ማህበረሰብ በኢየሱስ የሚያምኑትን ለመግለጥ ነው (ሐዋ. 24፡5፣ 14፤ 28፡22)፡፡
3. እሱም በሶርያ (የአራምኛ) ቤተ ክርስቲያናት አማኞችን ለማመልከት ነው፡፡ "ክርስቲያን" በግሪክ አብያተ

ክርስቲያናት የሚያመለክተው አማኞችን ነው።

4. አንዳንዴ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ፣ ፈሪሳውያን በጃሚና ዳግም ተደራጅተው በቤተ ክርስቲያንና በምኩራብ መካከል ይፋ የሆነ ልዩነት አስቀምጠዋል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆንም የውግዘት ቀመር ክርስቲያኖችን በመቃወም "በአስራ ስምንተኛው ቃለ ቡራኬ" ከባርኮት 28ለ-29ሀ አማኞችን "ናዝራውያን" የሚል ተገኝቷል።

"ናዝራውያን እና መናፍቃን ወዲያውኑ ይጥፉ፤ ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ እንዲሁም ከታመኑት ጋር አይጻፉ።"

ሐ. የጸሐፊው አስተያየት

በቃሉ በርካታ ሆሄያት መኖር እገረማለሁ፣ ይህም በብኪ ያልተሰማ ቢሆንም እንደ "ኢያሱ" በርካታ ሁሄያት በዕብራይስጥ አሉት። ይህም፣ የሆነበት ምክንያት (1) ከመሲሐዊው ቃል ከ "ብራንች" ጋር ባለው የቀረበ ትስስሮሽ፤ (2) ከአሉታዊ ትርጉም ጋር በመደበላለቁ፤ (3) ጥቂት ወይም ምንም ተጓዳኝ ማረጋገጫ ከገሊላዋ የናዝሬት ከተማ ጋር መኖሩ እርግጠኛ እንዳልሆን አድርጎኛል፣ ትክክለኛውን ፍች ለማግኘት፤ እንዲሁም (4) በመለኮታዊ መልኩ ከአጋንንት አፍ ወጥቷል (ማለትም፣ "ልታጠፋን መጣህን?")።

ለዚህ ቃል ምድብ ለሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት፣ የነጻ ትምህርት የኮሊን ብራውን (አዘጋጅ)፣ *አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት*፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 346 ተመልከት።

10:14-15
**እንግዲህ ያላመኑበት እንዴት አድርገው ይጠሩታል ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምስራች የሚያወሩ አግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተፃፈ ካላመኑ እንዴት ይሳብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምስረቹ ቃል አልታዘዙም።**

10:14-15 እስራኤሎች ለመሲሁ ምላሽ አልሰጡም ነህ 9 እና ሐዋ 7 ነገር ግን ነብያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰባኪዎችን አስተማሪዎችን ልኮላቸዋል በኢሳ 52:7 መሰረት እነዚህ ሁሉ የወንጌል ሰባኪዎች ተብለዋል።

በዚህ የመዳን እምነት የሰው ድርሻ ምንድነው? (1) መልዕክቱን ማመን (2) መታዘዝ (3) መቀበል (4) ንስሃ መግባት መታገስ።

10:15 በዚህ ጥቅስ መሰረት ለማዳን ወንጌል ሰባኪዎች ተልከዋል።

ሮሜ 10:16-17
**ነገር ግን ሁሉ ለምስራቹ ቃል አልታዘዙም ኢሳያስ ጌታ ሆይ ምስክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።**

10:16 ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእስራኤል የተጠቀመበትን ንግግር የመሲሁ መልእክት እንዲሆን አድርጓል እስራኤል የያሕዌን መልእክት እንዳልተቀበለች እንዲሁ አይሁድም የጳውሎስን መልእክት አልተቀበሉም ኢሳ 6:9-13

10:17 ወንጌል መልእክት ነው ገላ 3:2 የክርስቶስ ወንጌል ያመለክታል፤ ቆላ 3:15-16

▣ **"የክርስቶስ ወንጌል"** ስለ ክርስቶስ የሚነገር ወንጌል ነው፤የግሪኩ ፅሑፋ የክርስቶስ ቃል ወይም የእግዚአብሔር ቃል ይላል። ቆላ 3:16 ልዩ አጠቃቀም ይመልከቱ። (ሉቃ 3:2፣ ዮሐ 3:34፣ ኢፌ 6:17፣ ዕብ 6:5፣ ዕብ 11:3)

10:18-21
**ዳሩ ግን ባይሰሙ ነው ወይ እላለሁ በእውነት ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ መጣ ነገር ግን እስራኤል ባያውቁ ነው ወይ? እላለሁ ሙሴ አስቀድሞ በእኔ ሕዝብ በማይሆነው አስቀናችኋለሁ በማያስተውልም ሕዝብ አስቀጣችኋለሁ ብሎአል ኢሳይያስ ደፍሮ ላልፈለጉኝ ተገኘሁ ላልጠየቁኝም ተገለጥሁ አለ። ስለ እስራኤል ግን ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና ወደሚቃወም ህዝብ እጆቼን ዘረጋሁ ይላል።**

10:18 አይሁድ ወንጌልን መስማት ብቻ ሳይሆን መቀበላቸውን ተናግሯል ሮሜ 1:2 ጳውሎስ ይህንን ቀይሮታል። (1) አለማቀፋዊ ምስክርነት (ለምድር) (2) በአገልጋዮቹ መልእክቱን አስተላልፏል (ኢፌ 4:11፣ መዝ 19:8-14)።

10:19-20 አይሁድ ሙሴን እና የእግዚአብሔር ወንጌል ሰምተዋል ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ምዕራፋ አሕዛብ በእምነት የእርሱ ተካፋይ መሆናቸውን ይናገራል።

ዘዳ 32:21, ኢሳ 65:1-2 የአህዛብ የደህንነት ተካፋይ መሆን አይሁዶችን ለእምነት አነሳስቷቸዋል።

10፡21 ከግሪክ መፃፋ ሙሉ ለሙሉ የተወሰደ ነው፡፡ ኢሳ 65፡2 ሕህዛብ የእግዚአብሔር መልእክት ባይቀበሉም እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነበር፤ እስራኤል ግን ታማኝ አልነበረችም፡፡ የእነርሱ ያለመታመን ወደ ጊዜያዊ ፋርድ አምጥቷቸዋል ደግሞም እስከ መጨረሻ ያለመታመን ወደ ዘላለም ፋርድ ያደርሳል፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡*

*እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉ ዋና አብይ ጉዳዮችን ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡*

1. እግዚአብሔር ይመርጣል ከተባለ ጳውሎስ መፀለዩ ምን ለውጥ ያመጣል? (10፡1 ሮሜ 10፡9-13) ለምን የሰው ምላሽ ተፈለገ?
2. ቁ 4 ምን ማለት ነው?
3. ሮሜ 10፡9-10 በዝርዝር አስረዳ
4. ለምን ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሳል?
5. ምዕራፋ 10፡11-13 እና ምዕራፋ 9 ዝምድናቸው ምንድነው?
6. ምዕራፍ 10፡14-15 እና አለማቀፋ ሚሲዮናዊነትን የሚያዛምደው ምንድነው?
7. የሰው ነፃ ምርጫ በሰው ደህንነት ላይ እንዴት ይገለፃል ምዕ 10?

# ሮሜ 11

**በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል**

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእስራኤል ቅሬታ | የእስራኤል መቃወም | የእስራኤል መቀወም | የእግዚአብሔር ምህረት | የእስራኤል ቅሬታ |
| 11:1-10 | 11:1-10 | 11:1-10 | 11:1-6 | 11:1-10 |
| | | | 11:7-10 | |
| ድነት ለአህዛብ | የእስራኤል መቃወም | | | |
| 11:11-12 | 11:11-36 | 11:11-12 | 11:11-12 | 11:11-15 |
| | | | የአህዛብ ድነት | |
| 11:13-16 | | 11:13-16 | 11:13-15 | |
| | | | 11:16-18 | 11:16-24 |
| | | የወይራ ዘይት ዛፍ ምሳሌ | | |
| 11:17-24 | | 11:17-24 | | |
| አዲስ ኪዳን ለእስራኤል | | እስራኤል ሁሉ ይድናል | የእግዚአብሔር ምህረት በሁሉ ላይ | የአይሁድ መቀየር |
| 11:25-32 | | 11:25-32 | 11:25-32 | 11:25-27 |
| | | | | 11:28-29 |
| | | | | 11:30-32 |
| | | | እግዚአብሔር ይመስገን | ለእግዚአሔር ምህረትና ጥበብ መዝሙር |
| 11:33-36 | | 11:33-36 | 11:33-36 | 11:33-36 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

**የአውዱ ትንተና**

ሀ. ምዕራፍ አስራ አንድ ስለ ምርጫ እና ስለ ወንጌል ይናገራል፡፡ የብሉይ ኪዳን ምርጫ ለአገልግሎት ሲሆን የአዲስ ኪዳን ምርጫ ለድነት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች በብሉይ ኪዳን አገልጋዮች የሚል ስያሜ ተሰጥቷል፣ ይህ ምዕራፍ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት እና ስለ ሰው አመፀኝነትም ነው፡፡

ለ. ምዕራፍ ዘጠኝ ስለ እግዚአብሔር ሉአላዊነት እና ስነፃ ምርጫ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ አይሁድ ለመቀበልም ለመቃወምም ምርጫ እንደተሰጣቸው ፅፏል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ አስራ አንድ የእግዚአብሔር ታማኝነት ፀንቶ የሚኖር መሆኑ ያሳያል ዘዳ 8፡፡

ሐ. በእምነት ፀንተው የኖሩ አይሁድ ነበሩ፣ ጳውሎስ አንዱ አይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ አይሁድ መሲሁን ባይቀበሉም ነገር ግን (1) አህዛብ አማኞች በመሆናቸው ደህንነት ለሁሉ መሆኑን አረጋገጡ (2) የእግዚአብሔር ልጅነት ሃሳብ የተሟላ ሆነ፡፡

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

11:1-6
**እንግዲህ እግዚአበሔር ህዝቡን ጠላቸውን እላለሁ አይደለም እኔ ደግመ እስራኤላዊና አብርሃም ዘረ ከብንያምም ወገን ነኝና እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጠላቸውም መፅሐፍ ስለ ኤልያስ በተፃፈው የሚለውን በእግዚአብሔር ፊት እስራኤልን እንዴት እንደሚክስ አታውቁምን ጌታ ሆይ ነብያትህን ገድሉ፡፡ መሰዊያዎችህንም አፈረሱ እኔም ብቻዬን ቀረሁ ነፋሴንም ይሸታል ነገር ግን አምላካዊ መልስ ምን አለው ለበአል ያልሰገዱትን ለባዳል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች አስቀርችአለሁ፡፡ እንዲሁም በአሁን ዘመንደ ደግሞ በፀጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ፡፡ በፀጋ ከሆነ ግን በስራ መሆኑ ቀርቷል ፀጋ ያለዚያ ፀጋ መሆኑ ቀርቷልና፡፡**

11:1 **"እግዚአብሔር ህዝቡን ጣላቸውን?** ምላሽን የሚልግና ጥያቄ አይደለም፡፡ በዚሁ ምእራፍ ቁ. 1-10 ያንብቡ፡፡ ምእራፍ በሕዝብ ፈንታ "ዘር" በሚል ተተክቷል **"እላለሁ"** ሐዋሪያው ጳውሎስ ጥያቄውን ምላሽ የማይፈልግ መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡ ሮሜ 3፡4፣6

▣ **"እኔ እስራኤላዊ ነኝ"** ሐዋሪያው ጳውሎስ አይሁድ ሆኖ አማኝ መሆኑን ለማሳወቅ ይህ አረፍተ ነገር ተጠቀመ፡፡ ፊል 3፡5

▣ **"እግዚአብሔር ህዝቡን አልጣለም** " ከብሉይ የተጠቀሰው መዝ 94፡ 14 ዘዳ 31፡6 1ሳሙ 12፡22፣ 1ነገ 6፡13፣ ሰቆ 3፡31-32

▣ **"ቀድሞ ያወቃቸውን"** የእግዚአብሔርን ምርጫ ያመለክታል፡፡ የእግዚአብሔር በጎነት እና ምርጫ እንጂ የእስራኤል ቀና ልብ አይደለም፡፡ ሕዝ. 36፡ 22-32

▣ **"መፅሐፍም"** 1ነገ19፡10 ለመተረክ ነው፡፡

11፡4 **"ለበአል ያልሰገዱ ሰባት ሺህ ሰዎች ለኔ አስቀርቼአለሁ"** "ለእኔ" በዕብራይስጡ ፅሑፍ ላይ አይገኝም 1ነገ 19፡18 ሐዋሪያው ጳውሎስ ከዕብራይስጥም ፅሑፍ አልጠቀሰም ነበር ነገር ግን ስለእግዚአብሔር ምርጫ ለመናገር የራሱን ትንተናዊ አጠቃቀም አድርጓል፡፡
የሐዋሪያው ጳውሎስ ሃሳብ ይህ ቃል የሚመለከት በዚያም ዘመን ሲሆን ቅሬታዎች እንደነበሩ በእርሱም ዘመን ከአይሁድ መሃከል ቅሬታዎች እንዳሉ ለመግለፅ ነው፡፡

▣ **"በአል"** የጣኦት ስም ነው፡፡ የተቀመጠውም በወንድ ስም ነው፡፡ በአይሁድ ባህል የሴትን ስም መጥቀስ የተከለከለ ነው፡፡

11፡5-6 ይህ ቁልፍ ጥቅስ ነው፡፡ የብሉይ ኪዳንን ሃሳብ ከአሁን ጊዜ ጋር ያገኛዋል፡፡ ምርጫ በእግዚአብሔር ነው 1ሮሜ 9፡ 15፣ 16፣ 18 ሮሜ 11፡30፣ 31፣ 32) የእግዚአብሔር ፀጋ ቀዳሚ ነው፣ ነገር ግን የሰው እምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ማርቆ 1፡15፣ ሐዋ 3፡16፣ 19፣ 20፣ 21 ኤፌ 2፡8-9 2ጢሞ 1፡9፣ ቲቶ 3፡5.

11፡6 **"ከሆነ"** የፀሐፊው ሐሳብ ነው፣ ደህንነት በእግዚአብሔር ፀጋ ነው ሮሜ 3፡24፣ 6፡23 ኤፌ 2፡8-9
Kኢ መ ቅ ቁ. ስድስትን ጨምሯል "ነገር ግን ከሥራ ከሆነ ጸጋ አያስፈልግም" ይህ በግሪኩ ፅሑፍ ላይ አይገኝም፡፡

**ሮሜ 11: 7-10**
**እንግዲህ ምንድነው እስራኤል የሚፈልጉትን አላገኙትም የተመረጡት ግን አገኙት ሌሎቹም ደነዘዙ እንደሁም አይኖቻቸው እንዳያዩ ጆሮአቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከዛሬ ሰጣቸው ተብሎ ተፅፏል ዳዊትም፡- ማዕዳቸው ወጥመድና አሽክላ ማሰናከያም ፍፃሜ ይሁንባቸው በአይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ ጀርባቸውንም አጉብኝ ብሎአል፡፡**

11:7 *"እንግዲህ ምንድነው? እስራኤል የሚፈልጉትን አላገኙትም"* ይህ አይሁድ በሃይማኖት ስርዓት እግዚአብሔርን ማግኘት አለመቻላቸውን የሚጠቁም ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ 1ቆሮ 1:29 ኤፌ 2:9

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | *"ነገር ግን የተመረጡ ያገኙታል"* |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | *"ነገር ግን ምርጦች ያገኙታል"* |
| አየመመቅ | *"ነገር ግን የተመረጡ አግኝተውታል"* |
| አእቅ | *"እግዚአብሔር የመረጣቸው ጥቂቶች ያገኙታል"* |
| ኢመቅ | *"ነገር ግን የተመረጡ ብቻ"* |

ይህ የብሉይ ኪዳን የ1000 ቅሬታዎች ሃሳብ የሚያመለክተው 1ነገ 19:18 ሰው በሃይማኖት፣ በጥረት፣ በዘር ከእግዚአብሔር መታረቅ አይቻልም ነገር ግን በፀጋ ብቻ ነው ኤፌ 1:3-14

▣ *"**ሌሎቹም ደነዘዙ**"* 2 ቆሮ 3:14 እግዚአብሔር ልባቸውን አደነዘዘው 2ቆሮ. 4:4 መደንዘዝ የሕክምና ቃል ነው፡፡ ይህም "ከመታወር ጋር" የቀረበ ትርጉም አለው ሮሜ 11:25፣ 2ቆሮ 3:14 ኤፌ 4:18፣ ማርቆ 6:52 የግሪኩ ቃል የተለየ ትርጉም ይሰጣል ስቬልኑሮ የምህረት ተቃራኒ ማለት ነው፡፡ ዕብ 3:8፣ 15፣ 4:7
ሮሜ 11:1-6 ይመልከቱ የተመረጡ አምነዋል፤ የደነዘዙ አላመኑም ይህ ጥቅስ ከሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር በማዛመድ የሚነበብ እና የሚተረጎም መሆን አለበት፡፡

11:8-10 የተወሰደው ከኢሳ 29:10 (ቁ.8) ዘዳ 29:4 የዕብራይስጡ እና የግሪኩ ፅሑፍ ይህ የለውም፡፡ ኢሳያስ የሕዝቡን አመፅ ለመግለፅ የተጠቀሙበት ሐተታ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ አደንዝዞ ነበርና ጳውሎስም የሚለው በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ ነው፡፡ ሮሜ 13፣ 15፣ 17
ሮሜ 11:8

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | *"እግዚአብሔር ያለመንቃትን መንፈስ ሰጣቸው* |
| አየመመቅ, ኢመቅ | *"እግዚአብሔር የለዘመበን መንፈስ ሰጣቸው* |
| አእቅ | *"እግዚአብሔር ልባቸውንና አይመሮአቸው አደነዘዘ"* |

11:10 *"አይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ ጀርባቸውንም ዘወትር አጉብጥ ብሎአል"* ይህ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት እና የሰው ልጅ ምላሽ መሰጠት እንዳለበት እንመለከታለን ለማመን ልባቸውን የሚያጠናክሩ ይደነዝዛሉ፡፡

11:11-16
**እንግዲህ የተሰናከሉ እስኪወድቁ ነውን? እላለሁ አይደለም ነገር ግን እነርሱን ያስቀናቸው ዘንድ በእርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ ዳሩ ግን በደላቸው ለዓለም ባለ ጠዓላት መሸነፋቸውም ለህዝብ ባለ ጠዓላት ከሆነ ይልቁንም መሙላታቸው እንዴት ይሆን?**
**ለእናንተም ለአህዛብ እናገራለሁ እኔ የአህዛብ ሐዋርያ በሆንሁ መጠን ሰጋዬ የሆኑትን አስቀንቼ ምናልባት ከእነርሱ እንዳንዱን አድን እንደ ሆነ አገልግሎቴን አከብራለሁ፡፡ የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ ከሙታን የሚመጣ ህይወት በቀር መመለሳቸው ምን ይሆን? በኩራቱ ቅዱስ ከሆነ በሆነው ደግሞ ቅዱስ ነው ስሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው፡፡**

11:11 *"እንግዲህ" የተለመደ ንግግር ነው፡፡ በቀጣይም ጳውሎስ የሰነ መለኮት ትንተናውን ይቀጥላል፡፡ እስራኤል ሁሉ አይጣሉም* ሮሜ 11:11-24

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | *"የተሰናከሉት እንዲወድቁ አይደለም ነውን?"* |
| NKኢመቅ, አየመመቅ | *"የተሰናከሉት እንዲወድቁ አይደለም ነውን?"* |
| አእቅ | *"አይሁድ ሲሰናከሉ ወድቀው እንዲጠፉ ነውን?"* |
| ኢመቅ | *"አይሁድ ለዘለዓለም ይጠፋሉን?"* |

መልሱ የሚሆነው አይጠፋም ወይም አይደለም የሚል ይሆናል

▣
አአመመቅ "ቢመተላለፋቸው"
አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም "በውድቀታቸው ውስጥ"
አየመመቅ "በክፋታቸው"
አእቅ "በሐጢያታቸው ምክንያት"
ኢመቅ "በውድቃታቸው"
ይህ የሚያመለክተው አይሁድ ኢየሱስን (መሲሁን) አልተቀበሉተም ሮሜ 11፡12

▣ "ለአሕዛብ ድነት ሆነ" በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ለነበሩ አይሁድ የሚከብድ ንግግር ነው፡፡ (ሮሜ 11፡12፣ ሐዋ 13፡46፣ ሐዋ 18፡6፣ ሐዋ 22፡21)

▣ "እነርሱን ለማስቀናት" የእግዚአብሔር እቅድ አህዛቦችን የደህንነት ተካፋይ እንዲሆኑ ያደረገበት ምክንያት፡- ድነት ለሁሉም እንደሆነ ለማሳየት፣ እምነት የግል መሆኑን ለመግለፅ ሮሜ 11፡12-14 የአይሁድ አለማመን እና የአሕዛብ ማመን ሮሜ 12,14,15,16,17,18,21,24 ሮሜ 11፡12፡፡

▣
አአመመቅ "ስኬታቸው የበለጠ ይሆን ነበር
አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም "ሙላታቸው እንዴት ይልቅ"
አእቅ "መባረካቸው እንዴት አይበዛ ሁሉም አይሁድ ቢሆኑ"
ኢመቅ "ሁሉም ቢቀየሩ የበለጠን ይሆን ነበር"
NRSN "የተሟላ ቢሆን እንዴት ከሁሉ ይልቅ"
የክሩክስ ትርጉም ስለ ሙላት" (1) አይሁድ እየዳኑ ነው ሮሜ 11፡14,26 (2) የአይሁድ እና የአሕዛብ መዳን በቁጥር ቢሰላ ምን ያህል ይሆናል

11፡13 "ለእናንተም ለአሕዛብ እናገራለሁ" ምዕ 9 እና 10 ያንብቡ:: አይሁዶች ለምን መሲሁን ተቃወሙ ለምን? ሐዋርያው ጳውሎስስ ለዚህ ጉዳይ ለምን ትኩረት መስጠት ፈለገ? ምክንያቱም በሕዛብ እና በአይሁድ መሐከል የነበረውን መለያየት ለማስቀረት ነበር፡፡

"እኔ የአሕዛብ ሐዋርያ ነኝ" ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር የመደበለትን ቦታ በሚገባ ያወቀ ይመስላል ፡- (ሐዋ 9፡15, 22፡21፣ ሮሜ 1፡5,15፡16፣ ገላ 1፡16,2፡7,9፣ 1ጢሞ 2፡7፣ 2ጢሞ 4፡17)፡፡

▣
አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም "አገልግሎቴን አተልቃለሁ
NRኢ መ ቅ "አገልግሎቴን አከብራለሁ
አእቅ "በአገልግሎቴ እመካለው"
ኢመቅ "በአምላኬ እመካለሁ"
አተልቃለሁ የሚለው ቃል፡-(1) አመሰግናለሁ (2) እመካለሁ (3) ከሁሉ አስበልጣለሁ የሚሉ ቃሎች ይተኩታል፡
በተጨማሪም ጳውሎስ ይህን ያለበት ምክንያት ነበረው፡- (1) አህዛብን ማገልገል ስለሚያስደስተው፡፡ (2) አይሁዶችን (3) ለማስቀናት ይህም ወደ ደህንነት የሚያደርስ ነውና ሮሜ 11፡11,14 እና 9፡1-3

11፡14 "በእነርሱ አንዳንዱን አድን እንደሆነ" ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ ጥሪ ነው፡፡ 1ቆሮ 1፡21, 1ቆሮ 9፡22

11፡15 አይሁድ ሁሉ አለመዳናቸው የእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ ነበር ይህም ድነት ለሁሉም መሆኑን አመላካች ነው አይሁድ መሆን፣ ሃይማኖተኝነት፣ እንዲሁም አሕዛብ መሆን ወደ እግዚአብሔር አያስጠጋም፡፡

▣ "ለዓለም መታረቅ ከሆነ..." ካታ እና አላሶ ማለት የመሰዊያ ለውጥ ወይም መለወጥ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ እድሳት በሁሉ አቅጣጫ ሮሜ 5፡11,11፡15, 2ቆሮ 5፡18፡19 እግዚአብሔር በኤደን ገነት ከሰው ጋር የነበረው ግንኙነት ለመመለስ የተፃፈ ቃል ነው፡፡

11፡16 "አንዱ ቅርንጫፉ ቅዱስ ቢሆን" ዘኁ 15፡17-21 ይህ በብሉይ ኪዳን የበኩሩን ፍሬ ለእግዚአብሔር ይሰጥ የሚለውን ያስተውሰናል ፤ቅሬታ የሆኑት አይሁዶች ለአለም ህዝብ ለመዳን ምክንያቶች መሆናቸው የማይካድ ነው፡፡ "ቅርንጫፎቹ" እና ስሩ የሚለውን ሀሳብ ከሚከተለው ጥቅስ ይመልከቱ ኤር11፡16-17፡፡

ሮሜ 11፡17-24

ነገር ግን ከቅርንጫፎቹ አንዳንድ ቢሰበሩ አንተም የበረሃ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚመጣሙ ስር ተካፋይ ከሆነህ በቅርንጫፎቹ አትመካ ብትመካባቸው ግን ስሩ አንተን ይሸክምሃል እንጂ ስሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም እንግዲህ እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል፡፡
መልካም እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል፡፡ ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩበት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራሳቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና፡፡ እንግዲህ የእግ/ር ቸርነትና ጭከና ተመልከት ጭከናው በወደቀት ላይ ነው በቸርነቱ ግን ፀንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው የለዚያ አንተ ደግሞ ትቁርጣለህ፡፡ እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ፀንተው ባይኖሩ በዛፍ ውስጥ ይገባሉ እግዚአብሔር መልሶ ሊያገባቸው ይችላልና አንተ በፍጥነት የበረሀ ከነበረ ወይራ ተቁርጠህ ወይራ ከገባህ ይልቁንስ እነዚየ በፍጥረታቸው ያሉት ቅርንጫፎች በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?

11፡17 “ቅርንጫፎች ተሰበሩ” ይህ የማያምኑ እስራኤሎችን ያመለክታል፡፡
ሮሜ 11፡18,19

“የበረሃ ወይራ ለወንጌል ምላሽ የሰጡ አሕዛብን ያሳያል

▣ “መገረዝ” በዋናው ወይራ ላይ መተከልን ያመለክታል “የወይራ ዛፋ” እስራኤልን ያመለክታል ሮሜ 11፡24 (መዝ 52፡ 8፣ መዝ 128፡3፣ ኤር 11፡16 ሆሴ 14፡6)

11፡18 “የቅርንጫፎች ላይ በደል አትስራ ይህ በቤተክርስቲያን በአይሁድና በሕዛብ መካከል የነበረውን አለመግባባት ያመለክታል፡፡

11፡19-20 በእግዚአብሔር አሕዛቦች ስለተወደዱ አይሁዶች አልተጠሉም ነገር ግን ባለማመናቸው ምክንያት ሊመረተጡ አልቻሉም፡፡

11፡20

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | “በእምነታቹ ቆማችሁ” |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | “እና በእምነት ቆማችኋል” |
| NRኢ መ ቅ | “ነገር ግን በእምነታቹ ብቻ በኩል ፀንታችኋል” |
| አእቅ | “በመፅናት የሆናችሁት በእምነት ነው” |
| ኢመቅ | “ፀንታችሁ ብትኖሩ እምነታችሁ መመስገን አለበት” |

ለመፅናታችን እምነታችን ከሆነ፡- (1) የመዳን መንገድ ላይ ነን፡፡ (2) እምነት አለን፡፡ (3) በሂደት የሚያድግ እምነት አለን፡፡ (4) ወደ ፍፃሜ የሚያመጣ እምነት አለን፡፡

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | “አታጋንን ነገር ግን ፍራ” |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | “አትኩራ ነገር ግን ፍራ” |
| አየመመቅ | “አትበይን ነገር ግን በፍርሃት ቁም” |
| አእቅ | “ፍራ እንጂ የትቢትን ነገር አታስብ” |
| ኢመቅ | “በመኩራት ፍንታ ፍርሃትን አድረግ” |

11፡21 “ለአንተ ደግሞ አይራራልህም” እስራኤል ባለማመኗ ለእግዚአብሔር የተቆረጠች ሆናለች እንዲሁ ቤተ ክርስቲያን ባታምነው ትቆረጣለች፡፡

11፡22 “የእግዚአብሔር ቸርነት እና ጭከና” እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ባሕሪያት ናቸው ኢሳ 55፡8-11 ሰው በምርጫው ከሁለት አንዱ ይሆንበታል፡፡

▣ “በቸርነቱ ግን ፀንተህ ብትኖር” በእምነት ፀንቶ መኖርን ያመለክታል ፊሊ 2፡12-13 የግል እና የጋራ ገላ 6፡9 ራዕ 2፡ 7,17 የእግዚአብሔር የዘላለም ቃል ኪዳን እና የሰው ምላሽ በእኩል የሚታዩ ነገሮች ናቸው፡፡

11፡23 አይሁድ ንስሃ ቢገቡ ይቅር ይባላሉ፤በተቃራኒው አሕዛብ ማመናቸውን ቢያቆሙ ተቀባይነታቸው ይቆማል፡፡
ሮሜ 11፡25-32

11፡5-32
*ወንድሞች ሆይ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ይህን ምስጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድርስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል እንዲህ ብሎ እንደ ተፃፈ፡- መድሃኒት ከፅዮን ይወጣል ከያዕቆብም ሃጢተኝነትን ያሰወግዳል። ሃጢያታቸውንም ስወስድላቸው ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው።*
*በወንጌልስ በኩል ለእናንተ ጠላቶች ናቸው በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸሁ እግዚአብሔር በፀጋው ስጦታና በመጥራቱ አትምና እናንተም ቀድሞ ለእግ/ር እንዳልታዘዛችሁ አሁን ግን ከአመታዘዛቸው የተነሣ ምህረት እንደገኛችሁ እንዲሁ ለተማራችሁበት ምህረት እነርሱ ደግሞ ምህረትን ያገኙ ዘንድ እነዚህ ደግሞ አሁን አልታዘዙም እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን ባለመታዘዝ ዘግቶታልና።*
*እግ/ር ባለጠግነት እና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርድ እንዴት የማይመርመር ነው ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።*

11፡25 *"ወንድሞች ሆይ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ* ሮሜ 1፡13 1ቆሮ 10፡1,2 ቆሮ 1፡8, 1ተሰሎ 4፡13 ይመልከቱ፣ ሐዋርያው አዲስ ምዕራፍ ለመጀመር የሚጠቀምበት ሐረግ ነው።

▣
*አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*

| | |
|---|---|
| *አየመመቅ* | *"የተደበቀ"* |
| *አእቅ* | *"ሚስጥር"* |
| *ኢመቅ* | *"የተደበቀ ምክንያት ለዘህ ሁሉ"* |

*ልዩ ርዕስ፡ የተደበቀ/ሚስጥር*
የእግዚአብሔር ዕቅድ ተገለጠ ዘፋ 3፡15, 12፡3, ዘፀ 19፡5-6 አሁን የእግዚአብሔር ምስጥር ተገለጠ 1ቆሮ 2፡6-8 የኢየሱስ እና የመንፈስ ቅዱስ የተስፋ ቃል መፈፀም ከዚህም ባለፈ የድነት ስራ 1ቆሮ 4፡1, ኤፌ 6፡19 ቆላ 4፡3, 1ጢሞ 1፡9 እነዚህ ጥቅሶች አውዳቸውን ጠብቀው የሚነበቡ ናቸው።
1. የአይሁድ ልብ መጠንከር ለአሕዛብ መዳንን አመጣ ሮሜ 11፡25-32
2. ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ታወቀ መዳን በክርስቶስ መሆኑ ሮሜ 16፡25-27 ቆላ 2፡2
3. አማኞች በዳግሞ ምፅአት ሌላ አካል ይለብሳሉ 1ቆሮ 15፡5 1ተሰሎ 4፡13-18
4. ክርስቶስ የሙላት መጨረሻ ነው ኤፌ 1፡8-11
5. አሕዛብ እና አይሁድ በአንድነት ይወርሳሉ ኤፌ 2፡11-3፡13
6. በክርስቶስ እና በቤተክርስቲያን መሃከል ያለው ግንኙነት የጋብቻ ተምሳሌነት አለው ኤፌ 5፡22-23
7. አሕዛቦች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ወደ ክርስቶስ ሙላት መድረሰባቸው እግዚአብሔር ሰውን ከሃጢያት ውድቀት እያነሣው መሆኑን አመላካች ነው።
8. የመጨረሻው ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ይነሣል 2ተሰሎ 2፡1-11
9. የሚስጥሩ መታወቅ 1ጢሞ 2፡1-11

▣

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ* | *"እስራኤል በከፊል ድንዛዜ ሆነባቸው"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"በጥቀቱ በእስራኤል ድንዛዜ ሆነ"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"ድንዛዜ በተወሰኑ እስራኤሎች ላይ ሆነ"* |
| *አእቅ* | *"እስራኤል አለመታዘዝ ለዘላለም አይደለም"* |
| *ኢመቅ* | *"የእስራኤል አንድ ወገን የታወረ ሆነ"* |

ይህ ሃተታ ከምዕራፋ አስራ አንድ ጋር ተዛማጅነት አለው። ያመኑም ያላመኑም አይሁድ መኖራቸውን የሚያስገነዝብ ነው። እግዚአብሔር ለሁሉ ድነትን ሰቷል ዘፋ3፡15 አብርሃምን መርጧል ዘፋ 12፡3 እስራኤልን መረጠ ዘፀ 19፡5-6 ነገር ግን እስራኤል ከእምነት ተሰናከለች ፤በመሆኑም በእምነት በሆነ ዕድቅ ሰው ሁሉ ድነትን ያገኝ ዘንድ በክርስቶስ ደህንነትን አመጣ ሮሜ 11፡30-31 አዝ 36፡22-38 ያንብቡ።

▣ *"የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድርስ ሉቃ* 21፡24 ያንብቡ ይህ ስለእግዚአብሔር የዘላለም የቀድሞ ዕቅድ እና ስለምርጫ የሚያስገነዝቡ ዐረፋተ ነገሮች ናቸው።

**11:26 "እስራኤል ሁሉ ይድናል"** ሁለት የተለያዩ ትርጎሞች ተሰታውታል፡፡ (1) በታሪክ እስራኤል የተባለችውን ነገር ግን እያንዳንዱ አይሁድን ላይሆን ይችላል፡፡ (2) መንፈሳዊዋን እስራኤል ቤተክርስቲያንን ያመለክታል፡፡ አንዳንድ ማብራሪያ የሚሰጡ መፅሐፋቶች እስራኤል ማለት ብሔራዊ ሕልውና ያላት እስራኤል የሚሉ አሉ ምክንያቶቹም፡- (1) የምዕራፋን አውድ መመልከት ሮሜ 9-11 (2) የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይገኝበታል ሮሜ 11:26-27 (3) ግልፅ ዓረፋተ ነገር አለው (ሮሜ 11:28)፡፡

▣ **"እንደተፃፈው"** ከግሪኩ ሁለት ጥቅሶችን ወስዷል ኢሳ 59:20-21 እና ኢሳ 27:9 የመዳን መንገድ አንድ ነው የሚል ብረቱ ቃል ነው፡፡ ዮሐ 10:7-18ዮሐ 11:25-29
ዮሐ 14:6፡፡

**11:27** ኢሳ 27:9 ያንብቡ ስለተሃድሶ የሚገናገር ጥቅስ ነው፤ አዲሱ ቃል ኪዳን እርሱም ወንጌል አሕዛብን እና አይሁድን በአንድ ማደሪ የሚያሳድር ነው ኤፌ 2:11-3:13, ሕዝ 36:22-36፡፡

**11:28** ሁለት አይነት ምርጫዎች፡- (1) በእግዚአብሔር ለአገልግሎት መመረጥ በብሉይ ኪዳን (2) በእግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት እና ለዘላለም ሕይወት መመረጥ

**"ከአባቶች የተነሣ እናንተ ተወዳችኋል"** የዘፀ 20:5-6 ቃል ኪዳን ነው፤ እስራኤል ከአባቶች እምነት የተነሣ መመረጧን ያመለክታል (ዘዳ 4:37፣ ዘዳ 7:8፣ ዘዳ 10:15)፡፡ መሲሁ ከይሁዳ ነገድ መምጣት በረከት ነው 2ሳሙ7 ቢሆንም እምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ሕዝ 36:22-36 የግል እምነት, የቤተሰብ እምነት, የሚከተለውን ጥቅስ ይመልከቱ (1ቆሮ 7:8-16 ሮሜ 11:29)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | |
| አየመመቅ | "የፀጋ ስጦታው እና ጥሪ የማይቀየር ነው |
| አእቅ | "እግዚአብሔር ስለምርጫውና ስለበረከት ሃሳቡን አይቀይርም" |
| ኢ መ ቅ | "እግዚአብሔር ከምርጫው የሚመልሰው የለም" |

ይህ የመንፈሳዊ የፀጋ ስጦታን አያመለክትም ነገር ግን ሰለ እግዚአብሔር የፅድቅ የደህንነት ጥሪ የሚያመለክት ነው፡፡

**11:30-32** የእግዚአብሔርን ፅድቅ የሚያሳይ ምንባብ ነው (1) እግዚአብሔር መሃሪ አምላክ ነው ሮሜ 9:15,16,18,23 (2) እግዚአብሔርበሁሉ ላይ ይፈርዳል ሮሜ 3:9,19,23 (3) እግዚአብሔር ምህረቱን ለማሳየት ሰውን ይጠቀማል ሮሜ 11:22

**11:30** እና **31 "ነገር ግን አሁን"** እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ኢየሱስ በማመን እንድትጠጋ ፀሐፊው ያሳስባል ሮሜ

> 11:33-36
> **የእግዚአብሔር ባለጠግነት፤ጥበብ፤እወቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው ለመንገዱም ፍለጋ የለውም፡፡ጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው ወይስ አማካሪው ማን ነበር ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን፡፡**

**11:33-36** ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ በምልክት ልዩ ምስጋና የሚያቀርብበት መንገድ ነው፡፡

**11:33 "ባለጠግነት"** (ሮሜ 2:4, 9:23፣ ሮሜ 10:12፣ ኢፌ 1:7,8:2:7፣ ኤፌ 3:8,16)

▣ **"እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው"** አብን ይመለከታል 1ቆሮ 11:12 ለክርስቶስም በተመሳሳይ አባባል 1ቆሮ 6:6 ቆላ 1: 16 ዕብ 2:10፡፡

**11:34** ከኢሳ 40:13-14 ከግሪኩ የተወሰደ ነው ፤እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባሕድ ምድር ይታደጋል፡፡ 1ቆሮ 2:16 ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን አዳኝነት ገልፃበታል፡፡

**11:35** ከኢዮ 35:7 ወይም ከ41:11 የተወሰደ ነው፡፡

**11:36 "ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን"** (1) እግዚአብሔር አብን ለመግለፅ 1ቆሮ 3:21 ፊሊ 4:20 1ጢጥ 4:11 ይሁዳ 25 ራዕ 5:13,7:12 (2) በተመሳሳይ መልክ ሰለ ልጁ 1ጢሞ 1:17, 2ጠሞ 4:18 2ጴጥ 3:18 ራዕ 1:16

▣ **"አሜን"** - የፕሮግራምን መዝጊያ ለማመልከት ይህ ቃል ይጠቅማል

*የመወያያ ጥያቄዎች*

*ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡*

*እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉን ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡*

1. እስራኤል የደህንነትን መንገድ እንዴት አጣች?
2. እስራኤል ፈፅም አልተጣለችም ለሚለው ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠውን ሁለቱን ምክንያቶች ዒፋ
3. እግዚአብሔር ለምን የአይሁድን ልብ አደነደነህ?
4. ቅሬታ የሚለውን ቃል አብራራ?
5. ሚስጥር የሚለውን ቃል አብራራ?
6. ሮሜ 11፡26 ምን ማለት ነው?ከምዕ 9፡6 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
7. ሐዋርያው ጳውሎስ ለአሕዛብ አማኞች የሚያስጠነቅቃቸው ምንድነበር ሮሜ 11፡17-24?

# ሮሜ 12

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በክርስቶስ አዲስ ህይወት | ለእግዚአብሔር ህያው መስዋት | የተቀደሰ ህይወት | የአገልግሎት ህይወት | መንፈሳዊ አምልኮ |
| 12:1-2 | 12:1-8 | 12:1-2 | 12:1-2 | 12:1-2 |
| | | | | መራራት እና እርዳታ |
| 12:3-8 | | 12:3-8 | 12:3-8 | 12:3-8 |
| የክርስትና ህይወት መመሪያ | እንደ ክርስቲያን መኖር | መለየት | | ጠላቶቻችንንም መርዳት |
| 12:9-21 | 12:9-21 | 12:9-13 | 12:9-13 | 12:9-13 |
| | | 12:14-21 | 12:14-16 | 12:14-21 |
| | | | 12:17-21 | |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወ.ዘ.ተ

**የአውድ የአጠቃላይ እይታ ከቁጥር 1-8**

ሀ. ብዙዎችን የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች የተለያዩ መሠረታዊ የክርስትና መመሪያዎቸ የያዙ ናቸው ከዚያም ባለፈ የተነሱ ችግሮችን አልባት ለመስጠት የተፃፍም ናቸው፡፡

ለ. ክርስትና እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚኖር ኑሮ ነው ማቴ 7:24-27, ዮሐ 13:17 ሮሜ 2:13 ሐዋርያው በፀጋ ስለሚገኝ ድነት ያስተምራል፡፡

ሐ. ሮሜ 12:1-2 በመንፈስ የተሞላ ኑሮ መኖርን ያመለክታል፡፡

መ. ሮሜ 12፡3-8 በመንፈሳዊ ስጦታ መባረክ ማለት ለክርስቶስ ራስን መስጠት ነው፡፡ ዘዳ 6፡4-5 ማቴ 22፡37 እና ለሌሎች ዘሌ 19፡18 ማቴ 19፡19

***የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት***

> 12፡1-2
> ***እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔር ን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታች ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፈፀምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለውጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡***

▣ *"**እንግዲህ**" በሮሜ መፅሐፉ ውስጥ ዋና የመሸጋገሪ ቃል ሆኖ ያገለግላል፡፡ በምዕራፍ አምስት በዕምነት ስለሚገኝ ፅድቅ ምዕራፍ ስምንት አማኞች ከሐጢያት ጋር ስላላቸው ግንኙነት በምዕራፍ አስራ ሁለት በየቀኑ ስለሚኖረን ኑሮ ይናገራል፡፡*

12፡1

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | ***"አበረታችኋለሁ"*** |
| ***አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*** | ***"እለምናችኋለሁ"*** |
| ***አየመመቅ, አእቅ*** | ***"እማፀናችኋለሁ*** |
| ***ኢመቅ*** | ***"እለምነችኋለሁ*** |

*ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ተገቢውን ኑሮ እንዲኖሩ ፅፏል፡፡* ሮሜ 12፡1, 5፡30, 1ቆሮ 1፡10, 2ቆሮ 2፡8 ኤፌ 4፡ 11 ፊሊ 4፡2, 1ተሰሎ 4፡10, 1ጢሞ 1፡3, ፊሊሞ 9-10

▣ *"**ወንድሞች**" አዲስ ሃሳብን ለመጀመር ጳውሎስ ይጠቀምበታል፡፡*

▣ *"**የእግዚአብሔር ርህራሄ**" ዘፀ* 34፡6 *ምዕረት* (ojkieiro እና eleeo) *ይህ እግ/ር በሐጢያት ውድቀት የደረሰበትን ሰውን የሚያገኝበትን መንገድ ያሳያል* (ኤፊ 1፡4፣ ኤፌ 2፡10፣ ኤፌ 2፡8-9)፡፡

▣ *"**ታቀርቡ ዘንድ**" መሰዋት ለመሰጠት ሲፈለግ የሚጠቅም ቃል ነው፡፡ ሮሜ* 6፡13, 16,19 *ይመልከቱ ለእግዚአብሔር ወይም ለሰይጣን ሰዎች እራሳቸው አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ* (2 ቆሮ 5፡14-15፣ ገላ 2፡20፣ 1 ዮሐ 3፡16)፡፡

▣ *"**ሰውነታችሁን**" ክርስትና ከግሪክ እምነት ይለያል ከሚለይባቸው አንዱ ሰውነትን ለእግዚአብሔር መስጠት የሚል ትምህርት ስላለው ነው ግሪኮች ሰውነት ክፉ ነው ይሉ ነበር፡፡ ሰውነት የሚለው "አእምሮ" በሚል ተተክቷል ሮሜ* 12፡2 *በመሆኑም አማኞች የትኛውንም ነገራቸው ለእግዚአብሔር መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡ዘዳ* 6፡51 *ቆሮ* 6፡20፡፡

▣ *"**ሕያው**" ይህ ለጣኦት ከሚቀርበው መስዋት ፈፅሞ የተለየ ነው* (ሮሜ 6፡13፣ ገላ 2፡20)፡፡
*ይህ ከብትህና* ( asceticism) *የተለየ ኑሮ የሚጠይቅ መሆኑን ለመግለፅ የሚገለግል ቃል ነው፡፡*

▣ *"**ቅዱስ መሰዋት**" ቅዱስ ማለት "የተለየ" ማለት ነው በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ቅዱስን ለመጠቀም እንደሚፈለግ ያሳያል፡፡*

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: ቅዱስ**

I. የብሉይ ኪዳን አጠቃቀም

ሀ. ጥሬ ትርጉም "መክፈል" (kadosn) ይህም ከከነዳናውያን መለየት የሚል ትርጉም አለው፡፡(ዘዳ 7፡6፣ ዘዳ 14፡2,21፣ ዘዳ 28፡19)

ለ. ከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከሰው ጋር ዝምድና አለው በዘፀአት, የዘሌላውያን እና በዘኃልቁ መፅሐፎች ላይ ሙሴ ተጠቅሞበታል፡፡

ሐ. የእግዚአብሔርን ባህሪ ይገልፃል ኢሳ 6፡3

መ. ምህረት እና ቅዱስ የሚለው ሃሳብ የብሉይ ኪዳን ተደጋጋሚ ቃላቶች ናቸው

II. የአዲስ ኪዳን አጠቃቀም

ሀ. ከሉቃስ በስተቀር ሁሉም የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የግሪክ ባህል እና ቋንቋ ተጠቃሚዎ ናቸው በመሆኑም በብሉይ ኪዳን የግሪክ ፅሐፎች ተፅኖ አለባቸው

ለ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ቅዱስ ነው ሉቃ 1፡35, ሐዋ 3፡14, 4፡27 እርሱ ቅዱስ እና ፃድቅ ሐዋ 3፡14, 22፡14 ኢየሱስ ሐጢያት የለበትም ዮሐ 8፡46, 2ቆሮ 5፡21 ዕብ 4፡15, 7፡26 1ጴጥ 1፡19, 2፡22 1ዮሐ

ሐ. እርሱ ቅዱስ ነውና ልጆቹ ደቅሞ ቅዱሳን ናቸው ዘሌ 11፡44-45 ማቴ 5፡48, 1ጴጥ 1፡16 ኢየሱስ ቅዱስ ስለሆነ ተከታዮቹም ቅዱስ ናቸው ሮሜ 8,28-29 2ቆሮ 3፡18, ገላ 4፡19 ኤፌ 1፡4, 1ሰሎ 3፡13, 4፡3 1ጴጥ 1፡15 ተቀባይነት ያለው "ልከኛ መስዋት መቅረብ አለበት ሮሜ

▣ "**ከወቀሳ ነፃ የሆነ**" የሚል ትርጉም አለው (ዘፍ 6፡9፣ ዘፍ 17፡1፣ ዘዳ 18፡13፣ ኢዮ 1፡1)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"መንፈሳዊ አገልግሎታችሁ ነው"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"አሳማኝ አገልግሎታችሁ ነው"** |
| **አየመመቅ** | **"መንፈሳዊ አምልከአችሁ ነው"** |
| **አእቅ** | **"እውነተኛ አምልኮታችሁ ነው"** |
| **ኢመቅ** | **"እውነተኛ አስተሳሰባችሁ ነው"** |

ሎጂኮሶ ኮሎጂዘሚያ ማለት ምክንያታዊ ማለት ነው፤ ማርቆ 11፡31, 1ቆሮ 13፡11 ፊሊ 4፡8 በዚህ አውድ አምልኮታችው በአመክኖ የተደገፈ እንደሆነ ለመግለፅ ነው፡፡

12፡2 "**አትምስሉ**" ፊሊ 2፡6-8 ይመልከቱ የሚታየው "ስኬማ" እና የማይታየው የማይለወጠው "ምርፋ" ፊሊ 6-7 ነገር ግን አማኞች የማይለወጠውን መያዝ አለባቸው፡፡

▣ "**ይህን አለም**" ማለት ዘመን የሚል ቃል ይተካዋል ማቴ 12፡32, ማርቆ 10፡30 ሉቃ 20፡34-35 አይሁድ ሁለት ዘመንን ለማመልከት ይጠቀሙበታል፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: ዘመን እና የሚመጣውን ዘመን**

የብሉይ ኪዳን ነብያቶች የሚመጣውን ዘመን ቀጣይ እንደሆነ ያስቡ ነበር፤ እነርሱ የእስራኤል ሕዝብ እንደ አገር ሉአላዊ የምትሆበትን ጊዜ አመልክተዋል ኢሳ 68፡17, 66፡22 1 ሄኖክ 6 ዕዝራ 2 ባቡክ በተለይ እነዚህ መፅሐፍቶች ሁለቱን ዘመኖች ይናገራሉ፡፡ የአሁኑ ዘመን በሰይጣን እና በወደቀው መላአክ ተሰጥቶአል ነገር ግን የሚመጣው ደግሞ የፅድቅ እና መሲሁ የሚመጣበት እንደሆነ ለማመልከት ይጠቀሙበታል፡፡

መፅሐፋ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆነው ነገር ይናገራል ደግሞም ሰለሁለቱ ዘመኖች ተፅፎ እናገኛለን፤ የሚከተሉትን ንፅፅሮች እንመልከት፡-

| ኢየሱስ | ጳውሎስ | ዕብራውያን |
|---|---|---|
| ማቴ 12፡32 | ሮሜ 12፡2 | 1፡2 |
| ማቴ 13፡22-29 | 1ቆሮ,12፡20,2፡6,8 | 6፡5 |
| ማርቆ 10፡30 | 2ቆሮ 4፡4 | 11፡3 |
| ሉቃ 16፡8 | ገላ 1፡14 | |
| ሉቃ 18፡30 | ኤፌ 1፡21,2፡1,7 | |
| ሉቃ 20፡34-35 | 2ጢሞ 6፡17 | |
| | 2ጢሞ 4፡10 | |
| | ቲቶ 2፡12 | |

በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነብያቶች ስለ ሁለቱ የመሲሁ መምጣቶች ተናግረዋል የመሲሁ በስጋ መገለጥ እና እንደፈራጅ ሆኖ በመጨረሻ ስለሚገለጠው መሲህ ኢሳ 53, ዘካ 9፡9, ራዕ 19

▣ "**ተለውጡ**" አማኞች ከአንድ ክብር ወደ ሌላ ክብር መለወጥ እንዳለባቸው የሚያስገነዝም ቃል ነው፡፡ ይህ ለውጥ የሚያቆም አይደለም፡፡ በተመሣሣይ ሕዝ 18፡31 ያንብቡ (የሰውን መስጠት) ሕዝ 36፡26-27 (የእግ/ር ስጦታ)፣ ኢየሱስ

በተራራው ላይ ተለውጧል ማቴ 17:2፣ የእርሱ እውነተኛ ተፈጥሮው 2ጺጥ 1:3-4፣ እያንዳንዱ አማኝ መቀየር አለበት 2ቆሮ 3:18 ኤፌ 4:13

▣ "**በልባችሁ መታደስ ተለወጡ** ግሪክ (ኬኖስ) ማለት የተሻለ አዲስ ማለት ነው፡፡ ለአይሁድ የነብስ በሮች የሚባሉ አይን እና ጆሮ ናቸው በእነዚህ በኩል አዳዲስ ነገሮች ይገኛሉ በመሆኑም አማኝ በእነዚህ በሮች በኩል አዲስ የተለወጠ አሳብ ሊገኝ ይገባል የሚል እምነት አላቸው ኤፌ 4:13,23, ቲቶ 3:5

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: መታደስ**

በግሪኩ ሁለት ትርጎሞች ተሰተውታል

1. አንድ ነገር አዲስ ወይም ከቀድሞ የተለየ ማድረግ ሮሜ 12:2
2. ወይም የበፊቱን ማደስ 2ቆሮ 4:16 ዕብ 6:4-6

ሞልተን እና ሚልጂን በፃፉት በግሪኩ መዝገብ ቃላት ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ከመፃፉ በፊት በግሪኩ ስነፅሁፍ የታወቀ ነው፡፡

ፍራንስ ስቴጅ የአዲስ ኪዳን ስለመለኮት ተንታኝ፡-

ዳግም መውለድ እና መቀየር የእግዚአብሔርስራ ብቻ ነው፡፡

2ቆሮ 4:16 የውስጥ ሰውነት ዕለት ዕለት የሚቀየር ነው (ቆላ 3:10)፡፡

▣ "**የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጉና ደስ የሚያሰኝ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ**" በግሪክ የሚተካው ቃል "ዶኦኬማዞኦ" ማለት የቃሉ ፍቺ **በማየት ፈትኖ ማሻሻል ማለት ነው**፡፡ ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ድነት እንድናገኝ ነው ዮሐ 6:39-40, ክርስቶስን እንድንመስል ነው ሮሜ 8:28-29 ገላ 4:19, ኤፌ 1:4 የክርስቲያን እርግጠኝነት የተመሠረተው፡-

1. በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ነው፡፡
2. የመንፈስ ቅዱስ ማደሪ በመሆኑ ነው ሮሜ 8:14-16፡፡፡
3. የሚቀየር ሕይወት ስላለው ክርስቲያን ከእግ/ር እርግጠኛ ይሆናል (ማቴ 13:1-9፣ ማቴ 19-23)

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: የእግዚአብሔር ፈቃድ** (thelema)

**የዮሐንስ ወንጌል**

- ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ሊያደግ መጣ ሮሜ 4:34
- አባት ለልጅ ሁሉን ሰጠው ሮሜ 6:39
- ሁሉም በእርሱ እንደያምኑ ሮሜ 6:29,40
- እንደፈቃዱ የሚፀለዩ ፀሎቶች ይመለሳሉ ሮሜ 9:31

**ሦስቱ ወንጌላት**

- የእግዚአብሔር ፈቃድ ማድረግ አስፈላጊ ነው ማቴ 7:21
- የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈፀም የኢየሱስ ወገን ያደርጋል ማቴ 12:50
- ማንም እንዲጠፋ የእግ/ር ፈቃድ አይደለም ማቴ 18:14 1ጢሞ 2:4
- ቀራኒዮ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማቴ 21:41, ሉቃ 22:42

**የጳውሎስ መልእክቶች ደብዳቤዎች**

- የአማኞች እድገትና አገልግሎት ሮሜ 12:1-2
- አማኞች ከዚህ ክፉ አለም ይድናሉ ገላ 1:4
- የእግዚአብሔር ፈቃድ የማዳን ዕቅድ ነው ኤፌ 1:5,9,11
- አማኞች በመንፈስ የተሞላ ሕይወት መኖር አለባቸው ኤፌ 5:17-18
- አማኞች በእውቀት መሞላት አለባቸው ቆላ 1:9
- አማኞች ሙሉ መሆን አለባቸው ቆላ 4:12
- አማኞች መንፃት አለባቸው 1ተሰ 4:3
- አማኞች ስለ ሁሉ ማመስገን አለባቸው 1ተሰሎ 5:18

**የጴጥሮስ መልዕክቶች ደብዳቤዎች**

- አማኞች ትክክል መሰረት አለባቸው (ለስልጣን መገዛት) 1ጴጥ 2:15
- አማኞች መከራ ያገኛቸዋል 1ጴጥ 3:17,4:19
- አማኞች ራስ ወዳድ መሆን የለባቸውም 1ጴጥ 4:2

**የዮሐንስ መልእክቶች ደብዳቤዎች**

- አማኞች ማደሪያ አላቸው 1ዮሐ 2:17
- አማኞች ለፀሎት ምላሽ ያገኛሉ 1ዮሐ 5:14

"በጎና እና ደስ የሚያሰኝ" አማኞች ከደህንነት በኂላ እንድንለብስ ይፈልጋል ማቴ 5:48

**"ፍፁም"** ማለት ያደገ የበሰለ የተጠናቀቀ ማለት ነው ይህ ማለት ከሃጢያት ነፃ የሆነ ለማለት አይደለም ይህ በሌላ ምሳሌ፡- (1) የተሰበረ እጅ እና እግር ነገር ግን ተጠግኖ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ (2) የተበጣጠሰ የአሳ ማጥመጃ መረብ ነገር ግን ተጠግኖ እንደገና ለማጥመድ የሚያገለግል ነው፡፡ (3) የዶሮ ጫጩት ከአደረ በኂላ ለዕርድ እንደሚቀርብ እነዚህ ምሳሌዎች ፍፁም የሚለው ቃል ለመተንተን የሚረዱ ቀላል ምሳሌዎች ናቸው፡፡

> ሮሜ 12:3-8
> **እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነት መጠን እንደካፈለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ አለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ፀጋ እናገራለሁ በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ስራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን እርስ በእርሳችንም እያንዳንዳችን የሌለው ብልቶች ነን እንደተሰጠንም ፀጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ የሚገዛ በትጋት ይግዛ የሚምር በደስታ ይማር፡፡**

12:3 **"አዲስ አይምሮ"** ፡ የአስተሳስብ አይነቶችን ይመልከቱ የተጋነነ ማሰብ, በአግባብ ማሰብ, በአላማ ማሰብ, በሃዘን ማሰብ፡፡

▣ **"በተሰጠኝ ፀጋ"** መንፈሳዊ ስጦታን ያመለክታል ሮሜ 15:15, 1ቆሮ 3:10 ገላ2:9, ኤፌ3:7-8, ፅድቅ ሰጣታ አይደለም ሮሜ 4 ይህ ጳውሎስ ለአሕዛብ የሚናገረውን መልእክት ይመለከታል፡፡
(ሐዋ 9:15፣ ሮሜ 1:1,5፣ ገላ 1:15-16,2:7-8)

▣ **"ለእያንዳንዶቹ እናገራለሁ"** እያንዳንዱ ክርስቲያን እንጂ ለመሪዎች ብቻ አለመሆኑን ይገልፃል፡፡

▣ **"ከሚገባው አልፎ ማንም በትዕቢት እንዳያስብ"** ከፋ ያለ አለመኑሩን ለማስገንዘብ የተፃፈ ነው፡፡

▣ **"ለእያንዳንዱ በተሰጠው ፀጋ"** አማኞች ፀጋ የሚሰጣቸው በእግ/ር ምርጫ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል 1ቆሮ 12:11 ኤፌ 4:7

▣ **"የእምነት መጠን"** እምነት በስጦታዎች ውስጥ ትልቁን ሰፋራ ይይዛል ገላ 5:22-22(ፋሬዎቹን ይመልከቱ)

12:4 በሰው አካል የቀረበ ምሳሌ 1ቆሮ 12:12-27ኤፌ 1:23 ቆላ 1:18,24,2:19፡፡ ይህ የሚያሳየው የክርስትና ሕይወት መገለጫዎች በግል እና በጋራ (በሕብረት) መሆኑን የሚገልፀ አስረጂ ጥቅሶች ናቸው፡፡

▣ 12:5 **"ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን"** የልዩነት አንድነትን የሚያሳይ ዓረፋተ ነገር ነው 1ቆ 13, 1ቆሮ 12 እና 14 ክርስቲያኖች የሚወዳደሩ ሳይሆን የሚረዳዱ መሆን አለባቸው፡፡

12:6-8 ግሪኩ በአንድ ቃል ጠቅሶታል "እንጠቀም" በሚል ሀረግ

12:6-8 **"ስጦታ ፀጋ... ስጦታ"** (ካሪዝማ) እና ፀጋ (ካሪዝ) በሚል ስርው ቃላቸው ተመመሳሳይ ናቸው፡፡ እርሱም "በነፃ የተሰጠ ማለት ነው ሮሜ 3:24 መንፈሳዊ ነፃ ስጦታዎች ይመልከቱ 1ቆሮ 12,ሮሜ 12, አፌ 4 እና 1ጴጥ 4፡፡

▣ **"ቢሆን"** ማለት "ቢሆንም የሚል ተመመሳሳይ ትርጉም አለው 1ቆሮ 3:22, 2ቆሮ 5:10 1ቆሮ 12:26, 2ቆሮ 1:6

▣ **"ትንቢት"** ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ጋር የሚዛመድ አይደለም ነገር ግን ከእግዚአብሔር እውነት ዕወጃ ጋር በቀጥታ የተገናኛ ትርጉም አለው ሐዋ 11:27-28 21:10-11, 1ቆሮ14:1,39 እና የተለየ የመንፈሳዊ ሰጣታ 1ቆሮ 12:28 1ቆሮ 14: 29, ኤፌ 4:11

> **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: የአዲስ ኪዳን ትንቢት**
> I. ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ጋር አይመሳስልም ነገር ግን ከእግ/ር በቀጥታ የተነገራቸውን ፅፈዋል፡፡
> ሀ. ሙሴ ነብይ ነበር ዘዳ 18:15-21
> ለ. የታሪክ መፅሐፋት (ኢያሱ-ነገስት ሌሎችንም መመልከት ይቻላል፤ ከሩት በስተቀር) ነብያቶች ተብለዋል ሐዋ 3:24

ሐ. ነብያቶች የሊቀ ካናቱን ቦታ ይተኩ ነበር ኢሳያስ እና ሚልክያስ
መ. በዕብራውያን መፅሐፍ ላይ የነብያት መፀሐፋት የሚባል አለ።
(ማቴ 5፡17፣ ማቴ 22፡40፣ ሉቃ 16፡16፣ ሮሜ 3፡21)

II. አዲስ ኪዳን ስለ ትንቢት የተሰጠ ማብራሪያ
ሀ. የብሉይ ኪዳንን መፅሐፋት ይጠቅሳል ማቴ 2፡23 ሮሜ 1፡2
ለ. ለግለሰቦች ትንቢት ሊመጣ ይችላል።
ሐ. መጥመቁ ዮሐንስ ማቴ 11፡9, ሉቃ 1፡26 ኢየሱስም ስለመንግስት ተናገረ ማቴ 13፡57, ሉቃ 4፡24
መ. ሌሎች ነብያት
I. በሉቃስ ወንጌል ላይ የተፃፈው የኢየሱስ ሕይወት እንመልከት።
ሀ. ኤልሳቤጥ ሉቃ 1፡41,42
ለ. ዘካሪያስ ሉቃ 1፡67-79
ሐ. ስምኦን ሉቃ 2፡25-35
መ. ሃና ሉቃ 2፡36
II. ዮሐ 1፡51 (የሚከናወን ትንቢት)
ሠ. ወንጌል ሰባኪ 1ቆሮ 12፡28-29 ኤፌ 4፡11
ረ. ለቤተክርስቲያን የተሰጠው ፀጋማቴ 23፡24ሐዋ 13፡1 ሐዋ 15፡32 ሮሜ 12፡6 1ቆሮ 12፡10 ኤፌ 4፡11
ሸ. የራዕይ መፅሐፋ የትንቢት መፅሐፍ ነው ራዕ 1፡3፣ ራዕ 22፡7,10,18,19

III. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች
ሀ. የአዲስ ኪዳን ነብያቶች መፅሐፋ ቅዱስ እንደገና በእግዚአብሔር የሚቀበሉ አይደሉም ሐዋ 6፡7,13,8
(ገላ 1፡23,3፡33፣ ፊሊ 1፡27፣ ይሁዳ 3፡20)
በአዲስ ኪዳን መፅሐፋቶች ውስጥ አንዳንድ የሚያወዛግቡ ትርጉሞች ይገኛሉ። ነገር ግን አማኞች በእምነት ብቻ የሚያረጋግጧቸው ናቸው። የመገለጥ ሦስትዮሽ፡-
1. እግዚአብሔር በዘመናት ራሱን ገልጧል
2. እግዚአብሔር በፀሐፊዎች ራሱን ገልፃን
3. እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አብርሆትን ሰቷል
ለ. በአንዳንድ መንገድ የአዲስ ኪዳን እና የብሉይ ኪዳን ነብያቶች ይመሣሠላሉ።
1. የወደፊቱን በመተንበይ ሐዋ 27፡22, ሐዋ 11፡27-28 ሐዋ 20፡23
2. ፍርድን ይናገራሉ ሐዋ 13፡11, 28፡25-28
3. ሊሆን ያለውን ማንኛውንም ክስተት ይናገራሉ ሐዋ 21፡11
ሐ. ወንጌልን በትንቢት መልክ ይናገራሉ ይሐ 11፡27-28, 20፡23,21፡10-11፣ 1ቆሮ14፡24,39
መ. ስለነባራዊው ሁኔታ ይናገራሉ 1ቆሮ 14፡3
ሠ. በመጀመሪያው ምዕተዓተም የእግ/ር ዋና አገልጋዮች ነበሩ። 1ተሰሎ 5፡20፣ 1ቆሮ 11-4-5፣ ኤፌ 2፡20

IV. በአዲስ ኪዳን የፀጋ ስጦታዎች መስራት አቁመዋልን?
ሀ. የፀጋ ስጦታ የሚሰጥበት ምክንያቶቹ ዛሬ አሉ ወይ ብሎ መጠየቅ ጥያቄውን ለመመለስ ይረዳል።
ለ. በቤተክርስቲያን ታሪክ ይህ ጥያቄ ተመሶ ይሆን? በአዲስ ኪዳን የፀጋ ስጦታዎች ግዚያዊ ናቸው የሚል ግነዛቤ አናገኝም 1ቆሮ 13፡8-13 ይህንን የመፅሐፋ ቅዱስ ጥቅስ ያለአግባብ ሰዎች ሲጠቀሙበት ይታያል።
ሐ. የአዲስ ኪዳን መፅሐፋቶች ከቤተክርስቲያን ታሪክ ይልቅ የፀጋ ስጦታ አስፈላጊነታቸውን ቢናገሩ ታአማነነት ይኖረዋል።
መ. ፀጋ ስጦታዎችን አንዳንድ አማኞች ይቀበላሉ ሌሎች ደግሞ አይቀበሉም ሮሜ 14፡1-15፡3 1ቆሮ 8-10ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱ ሁለት መንገዶች
1. እያንዳንዱ አማኝ በብርሃን እና በእምነት መላለስ ይገባል። እግዚአብሔር ሃሳባችንን ይመዝናል
2. እያንዳንዱ አማኝ ሌላኛው አማኝ በደረሰበት በእምነት እንዲመላለስ መፍቀድ አለበት፤
ሠ. ክርስትና የእምነት እና የፋቅር ኑሮ ነው

▣ "እንደ እምነታችንም መጠን" ኤፊ 4፡7 አማኞች እንዴት አድርገው የተሰጣቸውን ስጦታ መጠቀም እንዳለባቸው ያስረዳል ገላ 5፡22፣ ሮሜ 12፡7)

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የሚያገለግል"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም , አየመመቅ** | **"መቆም አገልግሎት ለአገልግሎት እንጠቀምበት)** |
| **አእቅ** | **"አገልግሎት ከሆነ ማገልገል አለብን"** |
| **ኢመቅ** | **"አስተዳደር ከሆነ በማስተዳደር እንትጋ"** |

ለግሪኩ (ዲያኮና) ለሚለው ቃል አቻ የእንግሊዘኛ ቃል አይገኝም ነገር ግን ሁለት ፋቺ ተገኝቶለታል፡፡ (1) በተግባር የሚታይ አገልግሎት (2) አገዛዝ ሐዋ 6፡1 1ቆሮ 12፡5,28 ለተሻሻለው የግሪክ ትርጉም ደግሞ ይህ ቃል "የሚሰራ አገልግሎት እና "ቢሮ" በሚል ተተርጉሟል (ሮሜ 12፡7, 1ቆሮ 12፡5 ቆላ 4፡17 2ጢሞ 4፡5)

▣ **"የሚያስተምር በማስተማር"** "በግሪኩ "ዲዳስክ" 1ቆሮ 12፡28 እና 1፡4፡26 ይህ ስጦታ ከስብከት፣ በትንቢት፣ ከመንጌላዊነት ተመሳሳይ መሠረት አለው ነገር ግን የማስተማሪየው ዘዴ የተለየ ነው፡፡

**12፡8 "የሚመክር በምክሩ"** ማለት በግሪክ "ፐራካሊዮ" ከማስተማር ጋር ይዛመዳል 1ጢሞ 4፡13 ኤፊ4፡15,16 እውነትን በፋቅር መናገር ይጠይቃል፡፡ የሚሰጥ በነፃነት ይሰጥ ቀጣዩን ተመልከት

| |
|---|
| **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: ቸርነት ማድረግ (ሃፐሎቶስ)**<br>ሃፐሎቶስ ሁለት ትርጉም አለው፡- መራራት እና የተከበር ማለት ነው፤ ምሳሌያዊ አገላለፅ አለው፡- 1. ትዕቢተኛ (የማይራራ) ዘዳ 15፡9 እና ምሳ 23፡6፣ 2. ቅን ምሳ 22፡9 ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ተጠቅሟል ይህም ማለት፡- ንፁህ, የተከበረ እና ቀለል ያለ 2ቆሮ 1፡12 ኤፌ 6፡5 ቆላ 3፡22 እና 2. ነፃነት ሮሜ 12፡8, 2ቆሮ 8፡2)፡፡ |

▣ **"የሚገዛ በትጋት ይግዛ"** የክርስቲያን አመራርን ይመለከታል፡፡

▣ **"የሚምር በደስታ ይማር"** ይህ የተቸገሩትን መርዳትን ያመለክታል ወንጌል ሰዎችን እንድናገለግላቸው ያዘናል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች 1-8**

ይህ የጥናት መመሪያ ነው በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው በጥልቀት የማጥናት ሃላፊነት አለበት መፅሐፋ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ያለው ሁሉ ወደ እውነት ይደርሳል፡፡

1. ራስን ሕያው መስዋት አድርጎ መስጠት ምንን ያጠቃልላል?
2. እያንዳንዱ አማኝ የፀጋ ስጦታ ተሰቶታልን? 1ቆሮ 12፡7
3. የፀጋ ስጦታዎች አላማ ምንድነው?
4. መፅሐፋ ቅዱስ የዘረዘራቸው የፀጋ ስጦታዎች አሉን?
5. አንድ አማኝ እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ እንዴት መለየት ይችላል?

**የአወድ አጠቃላይ እይታ ቁ 9-21**

ሀ. የክርስትና መመሪያ እርስ በእርስ ስለሚኖር ግንኙነት ይናገራል፡፡ ማቴ 5-7 1ቆሮ 13 እና 1ዮሐ 3፡18,4፡7-21፡፡

ለ. ሮሜ 12 እና 1ቆሮ 12-13 ተመሳሳይ ጭብጥ አላቸው ከመንፈሳዊ ስጦታ ትንተና በኂላ ማስጠንቀቂ እንመለከታለን፡፡

ሐ. አውዱ የሚናገረው፡-
   1. ከክርስቲያኖች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት 1ሮሜ 12፡9-13 1ቆሮ 8፡1
   2. ከማያምኑ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት ሮሜ 12፡14-21
   3. የሚደራረቡ ግንኙነቶች አሉ፡፡

መ. በመስቀል ላይ በተሰራው ያለቀ ስራ ድነት ይገኛል፡፡ ነገር ግን የሚጠይቀው ሕይወት ዋጋ ያስከፋላል ሉቁ 6፡46፡፡

ሠ. ክርስቲያኖች ከእስራት ተፈተዋል፡፡

ረ. ክርስትና የተከፈተ አይምሮ፣ የተከፈተ ልብ፣ የተከፈተ እጅ፣ የተከፈተ በር ሊኖረው ይገባል፡፡ ያዕቆ 2

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

| |
|---|
| ሮሜ 12፡9-13<br>**ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን ክፋውን ነገር ተፀየፋት ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ ለስራ ከመትጋት አትለግሙ በመንፈስ የምታቀጠሉ ሁሉ ለጌታ ተገዙ በተስፋ ደስ** |

**ይበላችሁ በመከራ ታገሱ በፀሎት ፅኑ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።**

12:9 "ፍቅራች ያለግብዝነት ይሁን" በግሪኩ ላይ አገናኝ ግሶችን እናገኝም ነገር ግን በዚህ አረፍተ ነገር ባልተለመደ ሁኔታ እናነባለን ይህ ምናልባት የዕብራይስጡ ሰዋሰው ነፀብራቅ ነው። ከማቴ 5 ጋር ያንፃፅሩ

"ግብዝነት" ማለት ጭንብል መልበስ ማለት ነው በእውነተኛ ፋቅር ጭንብል ማጥለቅ አይቻልም 2ቆሮ 6:6 ዮሐ 13:34-35, ዮሐ 3:11 ፋቅር የእግ/ር ባህሪ ነው።

▣ "ክፋውን ተፀያፋ" አማኞች ክፋውን መፀየፋ አለባቸው 1ተሰሎ 5:21-28

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "ከበጎ ጋር ተጣበቁ" |
| አየመመቅ | "በጎውን ያዙ" |
| አእቅ | "ከመልካሙ ጋር ተጣበቁ" |
| Nኢመቅ | "ከመልካሙ ጋር ተጣበቁ" |

የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ ዘፋ 2:24, ሐዋ 8:29 እና ፊሊ 4:8 1ተሰሎ 5:21-22

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "በወንድማማች ፍቅር ተዋደዱ" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "በፍቅርና በትህትና እርስ በእርስ ተዋደዱ" |
| አየመመቅ | "እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ" |
| አእቅ | "እርስ በእርሳችሁ እንደ ክርስትያን ተዋደዱ |
| ኢመቅ | "ወንድማማች እንደሚያደርጉት እርስ በእርስ ተዋደዱ" |

በግሪኩ ፊሎ ስቶረጅ ማለት "የወንድማማች ፍቅር ወይም የቤተሰብ ፍቅር ማለት ነው። ይህ ሃሳብ በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው ያለው ምክንያቱም ክርስቲያኖች አንድ ቤተሰብ ናቸውና ተሰሎ 4:9

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "እርስ በእርሳችሁ ጥልቅ አክብሮት ተሰጣጡ" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "አንዱ ሌላውን |
| አየመመቅ | "አንዱ ለሌላው ክብርን ይስጠው" |
| አእቅ | "እርስ በእርስ በመከባበር ትጉ" |
| ኢመቅ | "አንዱ ለሌላው ክብር ይኑረው" |

እያንዳንዱ ክርስቲያን ሌላውን ለመንከባከብ የተዘጋጀ መሆን አለበት ኤፌ 4:2 ፊሊ 2:3

12:11

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "በትጋት ላይ አትለግሙ" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "ለስራ አትለግሙ" |
| አየመመቅ | "በቅናት ውስጥ አትለግሙ" |
| አእቅ | "ጠንክራቹ ስሩ ነገር ግን አትሰነፋ" |
| ኢመቅ | "በልባች በመማር ለጌታ ስሩ" |

እውነተኛ ፍቅር ታላቅ ሃይል አለው ገላ 6:9

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "በተነሣሣ ልብ" |
| አየመመቅ | "በሚቀጣጠል ልብ |
| አእቅ | "በልበ ሙሉነት የተሰጣችሁ ሁኑ" |
| ኢመቅ | "በጓጓ መንፈስ" |

ይህ የመንፈስ ቅዱስን በአማኝ ልብ ውስጥ ማደር የሚያመለክት ቃል ነው ሐዋ 18:25, ራዕ 3:15-16

▣ "ለጌታ አገልግሉ የግሪኩ ለጌታ የሚለውን በጌታ ውስጥ ብሎታል ዮሐ 9:4 ኤፌ 5:16 የቀድሞው የግሪክ ትርጉም ጌታን ማገልገል" በሚል ገለፃታል።

12:12 "በተስፋ ደስ ይበላችሁ" ተሰፋ የሚለው ቃል የዳግሞ ምፅአት ጋር የተገኘት ቃል ነው ሮሜ 5:2 በእንግሊዘኛው ተስፋ ወይም ምኞት የሚል ትርጉም ይሰጣል። በአዲስ ኪዳንም መጽሀፍቶች ውስጥ ከወደፊቱ ዓለም ጋር የተገናኛ ቃል የሚል ትርጉም ይሰጣል።

▣ “*ታገሱ*” ማለት ፈቃደኛ በመሆን መረጋጋት መሸከም ቦታን አለመልቀኑ ያሳያል የአሁኑ ጊዜ ሰዋሰው ተጠቅሟል

▣ “**በመከራ**” ሮሜ 5፡3-5 የአማኝ መንገድ ማቴ 5፡10-16 ሐዋ 14፡22 ሮሜ 8፡1, 2ጢሞ 3፡12 1ጴጥ 4፡12፡፡

▣ “**በፀሎት ፅኑ**” በአሁኑ ጊዜ ግስ ተጠቅሟል እግዚአብሔር ልጆቹ ወደ እርሱ እንዲፀልዩ ተናግሯል ሐዋ 1፡14, ሐዋ 2፡ 42 ኤፌ 6፡18-9

12፡13

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አየመመቅ** | **“የተቸገሩ ቅዱሳንን በችግራቸው እርዱ”** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **“ያላችሁን ለተቸገሩ ቅዱሳን አከፋፈሉ”** |
| **አእቅ** | **“ለተቸገሩ ክርስቲያኖች ያላችሁን አካፋሉ”** |
| **ኢመቅ** | **“ለተቀደሱ ለእግዚአብሔር ቅዱሳን በችግራቸው እርዳታ አድርጉ”** |

የግሪኩ ግስ “ኮኖኖዮ” ማለት ህብረት ማድረግን ጳውሎስ ለተለያየ ትርጉሞች ይህንን ቃል ይጠቀምበታል ገላ 6፡6 ለክርስቶስ ስቃል ፊሊ.3፡8-10 1ጴጥ 4፡13 ፊሊ. 4፡14

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ ህብረት (ኮኖኒያ)**

1. ከአንድ ሰው ጋር ባልንጀራ መሆን፡-
   ሀ. ከልጁ ጋር 1ዮሐ 1፡6, 1ቆሮ 1፡9
   ለ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር 2ቆሮ 13፡13 ፊሊ. 2፡1
   ሐ. ከአባት ጋር 1ዮሐ 1፡3
   መ. ከወንድሞች እና ከእህቶች ጋር 1ዮሐ 17 ሐዋ 2፡42 ገላ 2፡9
2. ከአንድ ነገር ጋር ወይም ቡድን ጋር ህብረት ማድረግን ያመለክታል
   ሀ. ከወንጌል ጋር ሕብረት ማደረግ ፊሊ. 1፡5, ፊሊሞ 6
   ለ. ከክርስቶስ ደም ጋር ሕብርት ማድረግ 1ቆሮ 10፡16
   ሐ. ከጨለማ ጋር ሕበረት ማድረግ 2ቆሮ 6፡14
   መ. ከመከራ ጋር ሕብረት ማድረግ ፊሊ. 3፡10 1ጴጥ 4፡13
3. ስጦታ ማድረግ፡- ሮሜ 12፡13፣ 2 ቆሮ 8፡42ቆሮ 9፡13፣ ፊሊ. 4፡15፣ ዕብ 13፡16
4. የእግዚአብሔር ስጦታ በክርስቶስ በኩል ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ሕብረት እንዲያደርግ ነው፡፡

▣ “*እንግዶችን ለመቀበል ትጉ*” ትርጉሙ መስተንግዶን ማድረግ እንዳለብን የሚጠቁም ነው፡፡ ሮሜ 14፡9 1ጢሞ 3፡2, ቲቶ 1፡8, ዕብ 13፡2, 1ጴጥ 4፡9 በጥንቷ ቤተክርስቲያን የተለመደ ነው

**ሮሜ 12፡14-21**
***የሚያሳድዷቹን መርቁ መርቁ እንጂ አትርገሙ ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተሰማሙ የትዕቢትን ነገር አታሰቡ ነገር ግን የትህትናን ነገር ለመስራት ትጉ ልባሞች የሆናችሁ አይምስላችሁ ለማንም ስለ ክፋ ፈንታ ክፋን አትመልሱ በሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተፅፎአልና ጠላትህ ግን በራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፋም ትከምራለህና ክፋውን በመልካም አሸንፋ እንጂ በክፋ አትሸነፋ፡፡***

12፡14 “*የሚያሳድዷቹን መርቁ*” የእግሊዘኛው አዲስ ትርጉም “መባረክ” የሚል ፍቺ ሰጥቶታል፡፡ ማቴ 5፡44, ሉቃ 6፡28 1ቆሮ 4፡12 ያዕቆ 3፡9-12 1ጴጥ 3፡9

“*አትርገሙ*” የእግዚአብሔርን በቀል በፀሎት ስለመጥራት ይመለከታል 1ቆሮ 12፡3, ኤፌ 4፡29, 1ጴጥ 3፡9

12፡15 “*ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱ ጋር አልቅሱ*” ክርስቲያኖች ቤተሰቦች ናቸው ሮሜ 12፡14-21 ይመልከቱ

12፡6

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **“አንድ አይነት አሳብ ይኑራችሁ”** |
| **አየመመቅ** | **“በአንድ ሃሳብ ተስማምታችሁ ኑሩ”** |
| **አእቅ** | **“አንድ አይነት ትኩረት ይኑራችሁ”** |
| **ኢመቅ** | **“ሁሉንም በእኩል መመልከት ይሁንላችሁ”** |

ቁ.16 *ያለመግባባትን ይመለከታል፡- (1) በሮሜ ቤተክርስቲያን በአይሁድ እና በአህዛብ መሃከል ያለመግባባት ነበር ሮሜ 11፡13-14 (2) በባለጠጎች መሃከል የነበረ የከረመ ግጭት ነበር (3) መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይለያዩ ነበር (4) በባሕል ውስጥ ያለ የራስ ልምምድ ነበር*

▣ **"የትዕቢትን ነገር አታስቡ ነገር ግን የትዕትናን ነገር ለመስራት አስቡ"** *አስቡ የሚለው ሁለቱን ፃታ የሚመለከት ነው፡፡*

▣ **"ልባሞች የሆናችሁ አይምስላችሁ"** *አማኝ በሌለው አማኝ ላይ የበላይ ለመሆን መጣር የለበትም ከዚህም ባለፈ ያለአግባብ በአህዛቦችም ላይ የበላይ ለመሆን መፈለግ የለበትም፡፡*

12፡17 **"ለማንም ስለ ክፋ ፈንታ ክፋን አትመልሱ"** *የእግዚአብሔር ድርሻ እና የሰውን ድርሻ የሚለይ አይነተኛ ጥቅስ ነውምሳ* 26፡22 *ምሳ* 24፡29 *ማቴ* 5፡38-48 *ሉቃ* 6፡27 1*ተሰሎ* 5፡15, 1*ጴጥ* 3፡9

▣ **"በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ"** *ይህ ከምሳሌ መፅሐፋ የተወሰደ ነው ምሳ* 3፡4 (*በግሪኩ ላይ ይገኛል*) *አማኞች ሌሎችን ለወንጌል ለመድረስ መልካሙን ማሰብ ይጠበቅባቸዋል፡፡* 1*ቆሮ* 9፡19-23, 2*ቆሮ* 8፡21, 1*ተሰሎ* 5፡22 *እና* 1*ጢሞ* 3፡7 *ይመልከቱ፡፡*

12፡18 **"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ"** *ይህ ማለት አማኞች ሁል ጊዜ ይህንን ላይፈፅሙ ይችላሉ ነገር ግን ይህ ጥቅስ በሰላም መኖር እንደሚቻል ይናገራል ማርቆ* 9፡50 2*ቆሮ* 13፡11 1*ሰሎን* 5፡13

12፡19 **"ራሳችሁ አትበቀሉ"** *እግዚአብሔር በወሰነው ቀን ራሱ ብድራቱን ይመልሳል ማለት ነው፡፡*
**"ተብሎ ተፅፏልና"** *የብሉይ ኪዳንን መፅሐፋት የሚያመሳክር ቃል ነው፡፡* 1*ቆሮ* 14፡21 *እና* 2*ቆሮ* 6፡17 *ይህ የተጠቀሰው ዘዳ* 32፡35
12፡20 **"ጠላትህን ግን"** *ጠላቶች ለሁል ጊዜ መኖራቸውን በሚያመለክት የጊዜ መደብ ተጠቅሟል፡፡*

**"በራሱ ላይ የእሳት ፋም ትከምራለህ"** *የተወሰደው ከምሳሌ* 25፡21-22
1. *ይህ ትርጉሙም ከግብፆች የተወሰደ ባህል እርሱም ትህትና ጠላትን የማሸነፊያው አይነተኛ መንገድ ነው የሚል ነበር ይህንን ክርስቲያኖች ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ማቴ* 5፡44
2. *"የእሳት ፍም" የሚያመለክተው የአንድን ሰው አግባብ ያልሆነ ክፋ ስራ በሌላኛው ወገን ላይ ሲደረግና ይቅርታን ባለማድረግ ሲለይን ያመለክታል (ጀሮም እና አገስቲን)*
3. *የክርስቲያኖች ትሁት መሆን እግዚአብሔር ለበቀል በአመፀኞች ላይ ያስነሣዋል (ኦሪገን እና ክሪሰስቶም)*

12፡21 **"ክፋውን በመልካም አሸንፋ እንጂ በክፋ አትሸነፋ"** *በውስጣችን ያለው ሰላም እና ደስታ ሌሎችን ለመርዳት አይነተኛ መሳሪያ ነው ምሬት የመንፈሳዊ ህይወት ካንሰር ነው፡፡*

▣ **"ክፋ"** *ክፋ የሚለው ቃል ፃታ የለሽ ቃል ነው በመሆኑም ለሁሉ ያገለግላል በአዲስ ኪዳን ፅሑፎች የተለመደ ነው ማቴ* 5፡37,6፡13 *ዮሐ* 17፡15 2*ተሰሎ* 3፡3 1*ዮሐ* 2፡13-14

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

*ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡*

*እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፋን ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡*

1. *ከምዕራፋ* 12፡ *ከቁ.* 19-21 *አፋራሽ ሃሳቦችን በማወጣት ተወያዩ*
2. *ከዚህ ምዕራፋ ውስጥ ያሉትን ትዕዛዛቶች በመዘርዘር ተወያዩባቸው*
3. *ክርስቲያኖችን መርዳት እና የማያምኑትን (አሕዛቦችን) መርዳት የሚሉ ጥቅሶችን ለይታችሁ ተወያዩ*

# ሮሜ 13

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ለገዢዎች መታዘዝ | ለመንግስት መገዛት | ክርስቲያን እና መንግስት | ለመንግስት ማድረግ የሚገባን | ለስልጣን መገዛት |
| 13፡1-7 | 13፡1-7 | 13፡1-7 | 13፡1-5 | 13፡1-7 |
| | | | 13፡6-7 | |
| የወንድማማችነት ፍቅር | ልነጀራህን ውደድ | ፍቅር የህግ ፍፃሜ ነው | አንዱ ለሌላው | ፍቅር እና ጦርነት |
| 13-8-10 | 13፡8-10 | 13፡8-10 | 13፡8-10 | 13፡8-10 |
| ወደ ክርስቶስ ቀን መቅረብ | ክርስቶስን መልበስ | ዳግም ምፃት | | የብርሃን ልጆች |
| 13፡11-14 | 13፡11-14 | 13፡11-14 | 13፡11-13 | 13፡11-14 |
| | | | 13፡14 | |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**

*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሦስት
4. ወዘተ

**የአውድ አጠቃላይ እይል ሮሜ ከቁጥር 1-7**

ሀ. ከዚህ ቀደም የነበረው ምዕራፍ 12 ክርስቲያኖች እርስ በእርስ ስላላቸው ሕብረት ይናገራል ምዕራፍ 13 ስለ ክርስቲያን ሕይወት ከመንግስት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ይናገራል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቲያኖች የአለም ሮት እንዴት ባለ ሁኔታ መሆን እንዳለበት እያሳየ ነው፡፡

ለ. አማኞች ስለ መንግስት ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡ በቃየል ዘር ውስጥ ይህ ይታያል ዘፋ 4፡16-22 የባቢሎን ግንብ ዘፋ 11 (የራገስ አስተዳደር ምሳሌ) በብሉይ ኪዳን ነገስታቶች ከእግ/ር በተቀበሉት ስልጣን ህዝቡን ይመሩ ነበር፡፡ ኢየሱስ የተናገረውን በማቴ 22,21 እና ማርቆ 12፡17 ሐዋርያቶች ከመንግስታት ጋር ለመስማማት ብርቱ ጥረት ያደርጉ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ በመንግስት ይጠበቅም ይሰደድም ነበር ዮሐንስም በራዕይ 17 መንግስታት ታላቅ እንደሆነ ፅፏል 2 ተሰሎ 2፡6-7 ያንብቡ፡፡

ሐ. አስፈላጊ ጥቅሶችን ያንብቡ ቲቶ 3፡1 እና 1ጴጥ 2፡13-17
መ. አይሁዳዊነት በሮማ መንግስት የሚታወቅ ሃይማኖት ነበር ነገር ግን ክርስትና እንደ አንድ ቡድን የስህተት ሃይማኖት ለዓመታት ይፈጅ ነበር፡፡ ሐዋ 18፡12-16 ነገር ግን ክርስቲያኖች በሮም መንግስት ላይ በአመፅ የሚነሱ አልነበሩም 1ጢሞ 2፡1-2 ያንብቡ፡፡

ሠ ይህ ምንባብ ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ተሞክሮ በመጥቀስ የፃፈውም ነው፡፡ ይህ ምንባብ አስፈላጊ የሆነው፡-
1. በሮሜ ቤተክርስቲያን ከመንግስት ጋር የነበረውን ቅራኔ ለማስቀረት ነው ሐዋ 18፡2
2. ወንጌል በመስበክ በሮማ ግዛት የነበረውን አለመረጋጋት ለማስወገድ ነበር፡፡

**የቃል እና የጥምር ቃላት ጥናት**

**ሮሜ 13፡1-7**
**ነፋስ ሁሉ በበላይ ባለ ባለስልጣኖች ይገዛ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ስልጣን የለምና ያሉትም ባለ ስልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ባለ ስልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ስርዓት ይቃወማል የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ፡፡ ረዥሞች ለክፉ ባለ ስልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና በከንቱ ግን ሰይፋ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፋራ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድርገውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡ ስለዚህ ስለ ቁጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ህሊና ደግሞ ትገብራላችሁና በዚህ ነገር የሚታጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፡፡ ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ ግብር ለሚገባው ግብርን ቁርጥ ለሚገባው ቀረጥን መፋራት ለሚገባው መፋራትን ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ፡፡**

**13፡1 "ነፋስ ሁሉ በበላይ ባለ ስልጣኖች ይገዛ"** ቲቶ 3፡! 1ጴጥ 2፡13 "ተገዙ" የወታደራዊ ቃል ነው ኤፌ 5፡21፡፡ "መገዛት" አፋራሽ ቃል ተደርጉ ይወሰዳል ነገር ግን ከሌሎች ጋር በትህትና ለመኖር እግ/ርን ለማክበር የሚጠቅም መሆኑን መገንዘብ አለብን (1) ለወላጆች መገዛት ሉቃ 2፡51 (3) ለእግዚአብሔር አባት መገዛት 1ቆሮ 15፡28

▣ "ባለ ስልጣናት" "ኤክሰሺያ" ማለት የመላክት ስልጣን በቀዳሚነት የሰይጣንን ኃይለ ስልጣን ያመለክታል ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ቃል ለሌላ አውድ ተጠቅሞበት እናያለን ሮሜ 8፡38 ቆላ 1፡16 ኤፊ 1፡21 3፡10 እዚህ ቦታ "የመንግስት ስልጣንን ገልፃበታል 1ቆሮ 2፡6-8 ቲቶ 3፡1, 1ጴጥ 2፡13

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: የሰው መንግስት**

I. መግቢያ
   ሀ. ትርጉም፡- መንግስት ማለት በሰው የተዋቀረ የሰውን ጉዳይ ለማስፈፀም የቆመ ተቋም ነው፡፡
   ለ. አላማ፡- እግዚአብሔር ትዕዛዛትን ያወጣል
      1. የሙሴ ሕግጋት ለህዝቡ ህግ እንዲሆን የእግ/ር ፈቃድ ነው
      2. በመፅሐፋ ቅዱስ ውስጥ የምድር ነገስታት የሚመሩበትን እያንዳንዱን ሕግ አልተፃፈም ዲሞክራሲም ካፒታሊዝም የመፅሐፋ ቅዱስ አጀንዳ አይደለም ነገር ግን ክርስቲያኖች በዚህ ስርዓት ውስጥ ሲኖሩ ወንጌል እና አገልግሎት እንጂ አብዮት አላማቸው ሊሆን አይገባም፡፡
   ሐ. የሰው መንግስት መገኛ
      1. የሮም ካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን የሰው መንግስት በተፈጥሮ የሚገኝ ፀጋ ነው የሚል እምነት አላቸው አርስቶትል ከዚህ ሃሳብ ጋር ይሰማማል "political animal" ነው "መንግስት ለመልካም ኑሮ የሚታገል መሆን አለበት"
      2. የፕሮቴስታንቱ ተሃድሶ አምጪ ማርቲን ሉተር "መንግስት ከሃጢያት ውድቀት በኋላ የመጣ ነው በመሆኑም እግዚአብሔር "አመፀኞችን ለመቆጣጠር ክፋ ሰዎችን ይሾማል፡፡
      3. ካርል ማርክስ መንግስት ማለት ጥቂት የተማሩ በብዙሃን ባልተማሩ ላይ ስልጣን የሚይዙበት ነው (ሃይማኖትም እንዲሁ ነው)
II. የመፅሐፋ ቅዱስ አስተምሮት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
      1. የአምላክ ገዥነት በብሉይ ኪዳን የታወቀ ነው ያሕዌ ንጉስ ነው 1ሳሙ 8፡4-9
      2. የእግዚአብሔር ሉአላዊነት በሰው መንግስት ውስጥ ይሰለጥናል፡፡
         ሀ. ኤርም 27፡6 ዕዝ 1፡1
         ለ. 2 ዜና 36፡22
         ሐ. ኢሳ 44፡28
         መ. ዳንኤ 2፡21
         ሠ. ዳንኤ 2፡44

ረ. ዳንኤ 4፡17,25
ሸ. ዳንኤ 5፡28
3. የእግዚአብሔር ሕዝብ በጊዜው ያለውን መንግስት ማክበር ይገባቸዋል፡፤
ሀ. ዳንኤ 1-4 ናቡክደነፃር
ለ. ዳንኤ 5, ብልጣሶር
ሐ. ዳንኤ 6, ዳሪዮስ
መ. ዕዝ እና ነህምያ
4. የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመንግስት መፀለየ አለባቸው
ሀ. ኤርም 28፡7
ለ. አዲስ ኪዳን
1. ኢየሱስ ነገስታቶችን አክብሮአል
ሀ. ማቴ 17፡24-27 (የቀረጥ ክፋያ)
ለ. ማቴ 22፡15-22
ሐ. ዮሐ 19፡11 "እግዚአብሔር ለመንግስት ስልጣን ሰቷሰል"
2. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መንገስት ያለው ግንዛቤ
ሀ. ሮሜ 13፡1-7 (አማኞች ለመንግስት መገዛት አለባቸው)
ለ. 1ጢሞ 2፡1-3 (አማኞች ለመንግስት መፀለየ አለባቸው)
ሐ. ቲቶ 3፡1 (አማኞች ለመንግስት ተጠረ መሆን አለባቸው)
3. ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለመንግስት ያለው ግንዛቤ
ሀ. ሐዋ 4፡1-31,5፡29 ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በሸንራ ፊት
ለ. 1ጴጥ 2፡13-17 አማኞች ስልጣንን ማክበር አለባቸው
4. ሐዋርያው ዮሐንስ ስለመንግስት ያለው ግነዛቤ
ሀ. ባቢሎን የሰው መንግስት ተምሳሊት ሆኖ እግዚአብሔር መንግስት ተቃዋሚ ነው፡፡
III. መደምደሚያ
ሀ. የሰው መንግስት የሚሻረው በእግዚአብሔር ነው፡፡
ለ. አማኝ ለመንግስት መታዘዙ የማክበር ምልክት ነው፡፡
ሐ. አማኞች ቀረጥ እና ፀሎት ማድረግ አለባቸው
መ. የሰው መንግስት የእግዚአብሔር መጠቀሚያ ነው
ሠ. የሰው መንግስት ጊዜያዊ ነው ኦገስቲን የእግዚአብሔር ከተማ በሚል መፅሐፋ ልይ ስለ ጊዜያዊ እና ስለዘላለማዊ መንግስት ጠቅሷል፡፡
ረ. አማኞች በመንግስት የስልጣን ቢሮ እንዲሰሩ ማበረታታት ይኖርብናል፡፡
ሸ. ሕብረተሰብ ሚቀየረው ግለሰቦች ሲለወጡ መሆኑን መገንዘብ አለብን የሰው መንግስት ከእግዚአብሔር እርዳታ ስር ካልሆኑ ለብዙ ስህተት የሚሸነፋ ይሆናሉ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በአሁኑ ጊዜ ያሉት በእግዚአብሔር የተመሠረቱ ናቸው"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ያሉት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"የተደራጁት በእግዚአብሔር ነው"** |
| **አእቅ** | **"የተቀመጡት በእግዚአብሔር ነው"** |
| **Nኢመቅ** | **"የተሾሙት በእግዚአብሔር ነው"** |

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ የሰው መንግስት ላይ ሉአላዊ መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡ ዮሐ 19፡11 እግዚአብሔር እያንዳንዱን ነገር ማዘዝ ይችላል፡፡

**13፡2 "ስልጣንን የሚቃወም"** ይህ ማለት በመንግስት ህግ ላይ ተቃውሞ ማንሳት ይመለከታል ሐዋ 18፡6, ያዕ 5፡6 ኢየሱስ ለቤ/ክርስቲያንና ስለመንግስት ተናገረ ማርቆ 12፡17, ሐዋ 5፡25-32

▣ **"ይቃወማል የሚቃወሙትም"** እግዚአብሔር ያዘዘው ትዕዛዝ በሐጢያት ለወደቀው አለም እውነተኛ መገዛትን ነው፤ እግዚአብሔር ለሾመው መገዛት መሆኑን መገንዘብ አለብንአለ ሮሜ 13፡4,6

▣ **"ፍርድን ይቀበላሉ"** Kኢ መ ቅ መግዛት ከ1611 AD በኂላ ይህ ቃል "ፍርድ" በሚለው ተተክቷል፡፡ በዚህ የአውድ ይህ ቃል፡- (1) የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመለክታል፡፡ (2) የፍርድ ቤት ቅጣትን የመለክታል፡፡
እነዚህ ሰዎች መንግስትን በመቃወም ፍርድን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ ዮሐ 3፡17-21 ይመልከቱ፡፡

**13፡3** 1ጴጥ 2፡14 ይመልከቱ፡፡

▣ "**ስልጣን** "በሕዝብ ላይ ገዥ መሆን ማለት ነው።

13፡4 "**መልካም ነገር ለማድረግ ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና**" መንግስት አመፀኞችን ይቀጣል። አማኞች በዚህ ሁኔታ የበቀል ምላሽ መስጠት አይገባቸውም ሮሜ 12፡17-19 ሉተር እንደተናገረ "መንግስት በእግ/ር ዕቅድ አመፀኞችን ለመቆጣጠር የሚሾም ነው"

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ያለአላማ ሰይፋን አይታጠቅምም"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በከንቱ ሰይፋን አይታጠቅምም"** |
| **አየመመቅ** | **"ባለስልጣናት በከንቱ ሰይፋን ያለአላማ አይታጠቁም"** |
| **አእቅ** | **"ስልጣናቸው ለመቅጣት ነው"** |
| **ኢመቅ** | **"ባለስልጣናት ሰይፋ የሚታጠቁት ለከንቱ አይደለም"** |

"ሰይፋ" ሮማውያን ለቅጣት የሚጠቁሙበት መሣሪያ ነው። ሐዋ 12፡2 ሮሜ 8፡35 እና ሐዋ 25፡11 የሞት ፍርድን ለማመልከት ተጠቅሷል ዘፋ 9፡6 ይመልከቱ።

▣ "**የሚበቀል የእግ/ር አገልጋይ ነውና**" በቀል በብሉይ ኪዳን የሚታወቅ ቃል ነው። ዘሌ 19፡18 ያንብቡ አንድ ሰው የባልንጀራውን አይን በማወቅም ባለማወቅም ቢያጠፋ አይኑ እንዲጣፋ ይደረግ ነበር (የደም ካሳ ይሉታል) ሐዋርያው ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን የምድር መንግስት ለመቅጣት በዚህ ተሹሚል የሚል ትርጉም ሰቶታል።

13፡5 "**መግዛት ግድ ነው**" ሁለት ምክንያቶችን እንመልከት፡- (1) ከቅጣት ለማምለጥ (ከእግ/ር እና ከመንግስት)፣ (2) ከህሊና ክስ።

▣ "**ስለ ህሊና**" በግሪኩ ላይ አይገኝም የዕብራይስጡ "ብረስት" የራስ ዕውቀት የውስጥ ተነሳሽነት የሚል ነው። በግሪኩ ህሊና አምስቱ የስሜት ህዋሳትን የሚወክል ብቻ ነው። የውስጥ ስሜት ሮሜ 2፡15, ሐዋ 23፡1 እና 24፡16 1ቆሮ 4፡4 ሕሊና የአማኝን የውስጥ ማንነት የሚመዘንበት ነው፡- (1) ስለ መፅሐፋ ቅዱስ ያለው ግነዛቤ (2) ከመንፈስ ቅዱስ ያለው ዝምድና (3) የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት

13፡6 "**ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁ**" የክርስቲያን ሃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

13፡7

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የሚገባውን ትገብራለችሁ ቀረጥ ይህ እንደልማድ፣ በፍርሃት፣ በማክበር"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"የሚያስፈልገውን ትገብራላችሁ ቀረጥን በደንቡ፣ በፋርሃት እና በማክበር"** |
| **አየመመቅ** | **"ቀረጣችሁን ክፋሉ በማክበር እና በሚገባ ክብር"** |
| **አእቅ** | **"ከምታገኙት ቀረጥን መክፈል ክብር መስጠታችሁን ያመለክታል"** |
| **ኢመቅ** | **"መንግስት ለሚጠይቀው አግባብ ለሆነው ሁሉ ቀረጥን ክፈሉ በቁረጥ መልክ ወይም በሌላ መልክ በማክበር እና በፋርሃት"** |

ክርስቲያኖች ለመንግስት መገዛት እና ቀረጥ መስጠት መዘንጋት የለባቸውም ማቴ 22፡15-22
ቀረጥ እና ግብር የተለያየ ትርጉሞች አላቸው ቀረጥ ማለት ለአሸናፊው መንግስት ገንዘብ ሲሰጥ ነው ሉቃ 20፡22 ግብር ከሰራነው ስራ ለመንግስት ስጦታችንን ስናበረክት ነው ማቴ 17፡25,17,19

**የአውድ አጠቃላይ እይታ ሮሜ 13፡8-14**

ሀ. ከቁ 1-7 መረዳት የሚያዳግት አይሆንም ቁ.8 ላይ ምንባቡ ሌላ ስሜት ሲኖረው ይታያል አማኞች ለመንግስት እና ለሰው ዘር ሁሉ መልካም ልብ ሊኖራቸው እንዲሚገባ ማወቅ አለብን።

ለ. ከቁ 8-10 ተመሳሳይ ሃሳብ እናገኛለን ከምዕራፋ 12 የቀጠለ የክርስቲያን ለሌላው ያለውን ሃላፊነት የሚያሳይ ነው።

ሐ. ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች በንፅህና መኖር እንዳለባቸው ያመለክተናል። ይህንን ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች ተጠቅሰዋል

1. ኢየሱስ የተናገረው ቃል
2. የመንፈስ ቅዱስ ምሪት
3. ብሉይ ኪዳን
4. የመምህራን ስልጣና

5. የግሪኮች ትምህርት

ሌላም መገለጫው፡-

መ. ከቁጥር 11-14 ስለመጨረሻው ዘመን የሚናገር ክፍል ነው፡፡ በዮሐንስ እና በሐዋርያው ጳውሎስ ፅፁፍ ላይ የመጨረሻው ዘመን የሚጠቅስ ቃል መጠቀማቸው የተለመደ ነው፡፡ 1ተሰሎ 5፡1-11 ያንብቡ፡፡

ሠ. ከቁጥር 13-14 የሰነ መለኮት ሰው የሆነው አገስቲን "ይህን ከአነበብኮ በኂላ ሌላ ተጨማሪ አልፋልግም" አለ

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

> ሮሜ 13፡8-10
> **እርስ በእርሳችሁ ከመሃደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ህግን ፈፅሞታልና አታመንዝር አትነደል አትስረቅ በውሸት አትመስክር አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትዕዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህ እንደ ነፋስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፋ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነው፡፡**

13፡8 **"ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ"** ቀረጥን ያመለክታል 13፡6-7 የሰው የሆነ ማንኛውም ነገር በእጃችን እንዳይገኝ መፅሐፋ ቅዱስ ያስጠንቅቃል በመሆኑም እርስ በእርስ መዋደድ አለብን ምክንያቱም በቃል ኪዳን ወንድማማች ነን ማቴ 22፡39-40, ዮሐ 13፡34-35 ሌላው እንደ ሰው ከሌለው ጋር ቅንጅት መፍጠር አለብን ማቴ 5፡42, ገላ 6፡10፡፡

**"ከፍቅር በስተቀር"** ቁልፋ ሃሳብ ነው ቁ 8-10 ዮሐ 13፡34 ሮሜ 12፡10 1ቆሮ 13, ፊሊ 2፡3-4 1ተሰሎ 4፡9 ዕብራ 13፡1, 2ጴጥ 1፡7 1ዮሐ 3፡11,4፡7, 11-12

"ሌላውን የሚወድ" የአሁን ጊዜ አመልካ ግስ ተጠቅሟል በመሆኑ ወቅታዊ ሳይሆን ሌላውን መውደድ የሕይወታችን መርህ ማድረግ አለብን፡፡"

"ሌላውን" ባልንጀራ ወይም ሌላ የተለየ" የሚል ትርጉም ተሰታውታል፡፡ በዚህ አውድ በጎረቤት የሚኖርን ይመለከታል፡፡ በሌላ ትርጉም አማኝ  እና የሚያምኑንም ይጨምራል ሉቃ 12፡4-21, 10፡25-37

ማንኛውንም ክርስቲያን ሌላውን ክርስቲያ መውደድ አለብን 1ቆሮ 12፡7

▣

**አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም**

| | |
|---|---|
| **አየመመቅ** | **"ሕግን ፈፅምታል"** |
| **አእቅ** | **"ሕጉን ታዞቷል"** |
| **ኢመቅ** | **"ትህዛዞቹን ተግብራችኋል"** |

የግሪኩ (pletoo) "የነበረ ደግሞ የሚቀጥል" ይላል፡፡ (ገላ 5፡14, 62) ያንብቡ፡፡ ሮሜ 13፡9 የሙሴን ሕግ ባልተለመደ ሁኔታ የሐዋርያው ጳውሎስ የቃል አጠቃቀም ይመልከቱ ዘፀ 20፡13-17, ዘዳ 5፡17-21 እና ዘሌ 19፡18 ሐዋርያው ጳውሎስ ከአስርቱ ትዕዛዝ አንዱን በመውሰድ ክርስቲያኖች ሲያበረታታ ይታያል (ኤፌ 6፡2-3 1ጢሞ 1፡9-10 ኢየሱስ ስለ ህግ ተናገረ ማቴ 5፡17)፡፡

> **ልዩ ርዕስ፡ የሐዋርያውን ጳውሎስ የሙሴ ህግ ዕይታ**
>
> ሀ. ከእግ/ር ነው ሮሜ 7፡!2-16
>
> ለ. ሕግ በመጠበቅ ሰው አይፀድቅም ገላ 3
>
> ሐ. ሕግ ለክርስቲያኖች የእግ/ር ፈቃድ ነው
>
> መ. አማኞች በብሉይ ኪዳን መፅሐፋት እንዲጠቀሙ መፅሐፋ ቅዱስ ያዛል ሮሜ 4፡23-24, 15፡4, 1ቆሮ 10፡6,11, ሐዋ 15 ሮሜ 4
>
> ሠ. በአዲስ ኪዳንም ሕጉ ይሰራል
>
> 1. ከሃጢያት ነፃ መሆን ገላ 3፡15-29
> 2. በሕብረተሰቡ መሃከል መመሪያ ይሆናል
> 3. ክርስቲያኖች የታነፃ ኑሮ እንዲኖር ያደርጋል
>
> ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግ ቅዱስ ነው ይላል ሮሜ 7፡12,22 በሌላው አቅጣጫ ክርስቶስ እርግማን ዋጅቶናል ይላል ገላ 3፡13፡፡

**ልዩ ርዕስ፡ ዘፀ 20፡3 “መግደል”**

**መግደል**

I. ዓውዱ
   ሀ. የእግ/ር በፍጥረቱ ላይ የበላይ መሆኑን የሚሳይ ህግ ነው ሕግ/ር ሕግ አውጪ አምላክ እንደሆነ የታየበት ቦታ ነው ይህም እግ/ር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ያሳያል፡፡
   ለ. ማዕበረሰብ እንዴት መኖር እንደሚገባው የሚመራ ሕገ ደንብ የታየበት ያውድ ነው
II. የቃል ጥናት
   ሀ. “መግደል”
      1. ይህ ቃል “ራሻ” ማለት “ሕይወትን መውሰድ 46 ጊዜ በብሉይ ኪዳን ተጠቅሷል ሁለት አስፈላጊ ቃላቶችን እንመልከት
         ሀ. “ሃርግ” 165 ጊዜ ተጠቅሷል
         ለ. “ሄሚት” 201 ጊዜ ተጠቅሷል
      2. “ራሻ” የሚለው ሌላው ትንተናው
         ሀ. በቀል የሚል ትርጉም ይሰጣል ዘኍ 35፡30-34, ዘሌ 24፡13-23 አይን ለአይን ተብሏል፡፡ ዘፉ 9፡5-6 ያንብቡ
         ለ. በማወቅ የተደረገ ድርጊት ዘፀ 21፡12-14 ዘኍ 35፡11 ዘዳ 28፡24
         ሐ. የሚቤዥን ሰው ደም ለመመለስ የተደረገን ድርጌት ይህ ቃል ይጠቅሳል፡፡ ሆሴ 4፡2, ኤርም 7፡9
      3. በአገር ደረጃ የሚሰጠውን የሞት ፍርድ ወይም ጦርነት አይመለከትም
      4. አዲስ ዘመናዊ ትርጉሙ “አስቦ መግደል” የሚል ትርጉም ሰቶታል፡፡
III. የአውድ እይታ
   ሀ. ስድስተኛው ሰባተኛው እና ስምንተኛው ትዕዛኦች በሁለት የዕብራይስጥ ቃሎች ተቀምጠዋል፡፡
   ለ. ሕይወት የእግ/ር ነው፡፡
IV. የአዲስ ኪዳን
   ሀ. ኢየሱስ
      1. ትዕዛዛቶች ለሕይወታችህ መሠረት ናቸው ማቴ 5፡21-26
      2. ኢየሱስ በድርጊት ምሳሌ የሚሆን አስተማሪ የሚናገረውን ያደርግ ነበር
   ለ. ዮሐንስ
      1. 1ዮሐ 3፡15 መጥላት ግድያ ነው
      2. የግሪኩ ማቴ 5፡21 እና 1ዮሐ 3፡15 የተለያዩ ናቸው ነገር ግን ትርጉማቸው እንድ ነው
      3. አሉታዊ ሃሳብ አለው 1 ዮሐ 4፡19-21
V. ከዚህ ምን እንማራለን
   ሀ. የሰውን ደም ያፈሰሰ ወደ መማፀኛ ከተማ ቢሸሽም የዘሪው ያጭዳል ዘኍ 35, ኢያ 20
   ለ. ይህ ጥቅስ እራስን መግደል የሚል ትርጉም የለውም ነገር ግን በሌላ አካል የእግዚአብሔርን መልክ ማጥፋትን ያመለክታል
   ሐ. ይህ ጥቅስ፡- (1) ስለሞት ቅጣይ አይናገርም (2) ስለ ጦርነት አይናገርም እስራኤላውያን ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱም ድርጊቶች ያደርጉ ነበር፡፡
   መ. ይህ ጥቅስ የሚናገረው ነፋስን ስለመግደል ነው፡፡ የሰው ሃላፊነት ስለ ሰውነቱ፣ስለማዕበረሰቡ፣ ስለ ስነልቦና መሆኑን ይህ ጥቅስ ያሰራዳናል፡፡

**ዘፀ 20፡14- “ዝሙት”**

I. ዓውድ
   ሀ. የእግ/ር ሕግ የሌላውን ቤት፣ ሚስት፣ ንብረት ከመጠበቅ አኳያ ነው ኤርም 5፡8
   ለ. ይህንን እውነት ለእያንዳንዳችን የማስጠንቀቂ መልዕክትም ነው፡፡
   ሐ. ለማዕበረሰብ መሠረት የሆነው ለቤተሰብ ታማኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡
   መ. እግ/ር በተቀራኒ ፃታ መሃከል ያለውን ግንኙነት የበላይ ተቆጣጣሪ መሆኑን ያሳያል
   ሠ. ይህ ትዕዛዝ መሠረት ያደረገው ዘፉ 2፡24 ላይ ነው፡፡
II. የቃል ጥናት
   ሀ. “ዝሙት” በጥንት ዕብራውያን፡-
      1. “ሴሰኝነት” ሌላው ትርጉሙ ነው በጋብቻ ሆኖ ከሌላ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግን ይመለክታል ምሳ 29፡3 ምሳ 31፡3
      2. እግ/ር ጋብቻ ላይ ትኩረት የሚያደርገው በቃል ኪዳን የታሰረ ስለሆነ ነው፡፡

3. ከሙሴ ዘመን በፊት ዝሙተኝነት ተነቅፏል
4. ዝሙት ሃጢያት ነው
ሀ. በባልንጀራህ ላይ ዘፀ 20፡14, ዘዳ 5፡18
ለ. በጋብቻ ላይ ዘሌዋ 18፡20
ሐ. በእግ/ር ላይ ዘፋ 20፡1-13, ዘፋ 28፡7-11
5. ዝሙት የሞት ቅጣት ያመጣል፡፡
ሀ. ዘሌ 20፡16
ለ. ዘዳ 22፡22-24
ሐ. ሕዝ 16፡40
መ. ምሳ 1-9

III. በአዲስ ኪዳን ዕይታ
ሀ. ኢየሱስ የዘሌ 19፡18 ቃል ተጠቅሟል ለቃ 10፡27 ያንብቡ፡፡
ለ. ኢየሱስ ስለ ሕግ አስፈላጊነት ተናገረ፡፡ ማቴ 5፡28

IV. እኛ ምን እንማራለን
ሀ. ጋብቻ የዕድሜ ሙሉ ቃል ኪዳን ነው፡፡ ሚል 2፡14
ለ. ትዳር መረጋጋት እና ታማኝነት የሚጠይቅ ኑሮ ነው
ሐ. የግብ ስጋ ግንኙነት ፋላጎት ከእግ/ዚ/ር የተሰጠ ስጦታ ነው ነገር ግን ሰው ለክፋ ተግባር ተጠቀሙበት
መ. የግብረስጋ ግንኙነት የተቀደሰ ሊሆን ይገባል፡፡ ነገር ግን በሃጢያት የወደቀው ሰው ፍላጎት ወደራሱ የሚያዘነብል ነው፡፡

ዘፀ 20፡15 “መስረቅ”

I. አጠቃላይ መረጃ
ሀ. የእግ/ር ቃል ኪዳን የምንጠብቀው በአጠገባችን ያለውን ሰው ሃብቱን ካልተዘረፋን ነው፡፡ 1ዮሐ 4፡20-21
ለ. በመንፈሳዊ ሕይወታችን የባልንጀራን ሃብት አለመንካት ሰሞችን ወደ እግ/ር የመማረኪያ መንገድ መሆኑን መገንዘብ አለብን

II. የቃልና የጥምር ቃል ጥናት
ሀ. ይህ ቃል “መስረቅ” በዕብራይስጥ በሁለት ቃል ብቻ ተቀምጧል
ለ. ይህን የሚደግፋ ሃሳብ እንመልከት፡፡
1. ከዚህ ትዕዛዝ በፊት የሚቀድሙት ሁለት ትዕዛዞች ከዚህ ትዕዛዝ ጋር ይዛመዳሉ
2. ከዘፀ 21፡16 ተመሣሣይ ነው፡፡ ዘዳ 24፡7 እና ዘፋ 37 ያንብቡ፡፡
ሐ. ለምን ተፃፈልን?
1. ሕይወታችንን እንድንመራበት ይረዳናል
2. እውቀታችንን እንድናሰፋ ያደርጋል
3. ስርቆት አፀያፊ መሆኑን ለማመልከት ዘፀ 22፡1
4. ከኢየሱስ ትምህርቶች አንዱ መሆኑን ለማስገንዘብ ማቴ 19፡18
መ. በቀድሞ ዘመን መስረቅ የሞት ቅጣት ወይም ሰላሣ ጊዜ ካሳ የሚያስከፈል ነበር፡፡
ሠ. ተመሣሣይ ጥቅሶች እንመልከት፡፡
1. ዘፍ 19፡1-18 እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ”
ሀ. ሕይወታችን የእግ/ር ሕይወት ማንፀባረቅ አለበት
ለ. በየዕለቱ ኑሮኦችን የሚገለጥ ሕይወት መሆን አለበት፡፡
ሐ. ለባልንጀራችን መራራት አለብን፡፡
2. አምፅ 8፡4-7 እግ/ር ብዝበዛን ይጠላል፡፡
3. ሚክ 6፡6-8 እግ/ር ስርቆትን ይጠላል፡፡
4. ዘፀ 22፡1 ሃጢያት ዋጋ ያስከፋላል፡፡

III. እውነተኛ ተግባራት
ሀ. የእኛ የሆነው ሁሉ የእግ/ር መሆኑን ማወቅ አለብን ነገር ግን አንድ ነገር ለማግኘት የማይጥር ወደፊት ምንም ሊኖረው አይችልም” ጆይ ዲሲድ ማን፡፡
ለ. ስርቆት በሃጢያት የወደቀው ሰው ባህሪ ነው አሮጊው ሰው ይወስዳል አዲሱ ሰው ይሰጣል ኤፊ 4፡28
ሐ. እግዚአብሔር ማክበራችን የሚታወቀው ሌላውን ስናከብር ነው፡፡
መ. ዘመናዊው ሰው በስርቆት የተካነ መሆኑ ያሳዝናል

የመወያያ ጥያቄዎች
1. ዘመነኛው ሰው ስርቆትን ለምን ይለማመዳል?

2. ካሳ እና ንስሃ ዝምድናቸው ምንድነው?
3. አትስረቅ የሚለው ቃል በካፒታሊዝም አስተሳሰብ እንዴት ይታያል፡፡

ዘፀ 20፡17 "መመኘት"

I. መግቢያ

ሀ. የመጨረሻዎቹን አምስት ትዕዛዛት ዝምድናቸውን እንመልከት

1. ዘጎ 6,7 እና 8 (ባልንጀራ ላይ ጉዳት ማድረስ)
2. ዘኂ 9 ባልንጀራን በንግግር መጉዳት ክልክል ነው
3. ዘኂ 10 ባልንጀራን በሃሳብ መበደል አስፈላጊ አይደለም

ለ. የምኞት ሃሳብ ወደ ድርጊት ስለሚቀየር ባልንጀራን ማሳዘኑ የማይቀር ነው፡፡

ሐ. ምሳ 23፡7 እና ያዕቆ 1፡14-15 ይመልከቱ ክፉ ምኞት ወዳልተፈለገ ድርጊት ይመራል፡፡ ዘዳ 7፡25፤ አያ 7፡21 ሚክ 2፡2 ይህንን ቃል በእስራኤል ህግጋት እንጂ በቅርብ ምስራቅ ይህ ቃል አይታወቅም የሚል አስተምሮሆት ያላቸው አሉ ይህ ሃሳብ ግን ስህተት ነው፡፡

መ. የእግ/ር ህግ ለህይወት ስለሆነ ህጉ በፍጥረት መጀመሪያ መምጣቱ አስፈላጊነቱን ያሳያል፡፡ በኢየሱስ የተራራው ስብከት ትኩረት አግኝቷል ማቴ 6፡33 "የእግ/ርን መንግስት ፈልጉ ሌላው ይጨመርላችኂል

II. የቃል እና የጥያር ቃል ጥናት

ሀ. ዘፀ 20፡7 እና ዘዳ 5፡21 መሠረታዊ ሃሳቡን ይመልከቱ፡፡

1. ሚስት ለወንድ እንደሆነች ተገለፀ ዘፀ 20 ነገር ግን ቅድሚያ ተስቷትም ይታያል ዘዳ 5
2. ዘፀ 20 የዕራይስጡ ቃል ለምኞች "ፍላጎትን ማግኘት" ተብሏል፡፡ ዘዳ 5 ሁለተኛ ትርጉሙ "ፍላጎት እንዲሁም ምኞት ተብሏል
3. ዘፀ 20 የእስረኤል ልጆች ምድረበዳ ነበሩ ዘዳ 5 ከነአን ገብተዋል ነገር ግን ለሁለቱም ጊዜዎች ይህ ሕገ እግዚ/ር ይሰራ ነበር፡፡

ለ. ምኞት መልካምም ለማሰብ ቃሉ ያገለግላል መዝ 19፡10, 1ቆሮ 12፡31

ሐ. ክፉ ምኞች ከአጋንነት እና ከስጋ የሚመነጭ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ ክፉ ምኞት ጋር ታግሏል ሮሜ 7፡7-8 ምኞት ባጠቃላይ ያለመርካትን ያሳያል

መ. የአዲስ ኪዳን በርካታት ምንባቦች ስለ ምኞት ይናገራሉ

1. የሰው ያለመርካት እና ስስታምነት ሉቃ 12፡15 1ጠሞ 6፡8-10
2. ኢየሱስ ከነቀፈው መሃል ምኞት አንዱ ነው ማርቆ 7፡17-23 1ቆሮ 5፡10, ኤፌ 5፡5, ቆላ 3፡5

III. ተግባራዊ እውነቶች

ሀ. ያለመርካት እና ክፉ ምኞት የሚሸነፋት

1. በፍቅር ሮሜ 13፡8-10
2. በመርካት ዕብ 13፡5, ፊሊ 4፡11-13

ለ. በክርስቶ ብቻ እናሸንፋለን፡፡

ሐ. እግ/ር ልባችንን ያውቃል

1. 1 ዜና 28፡9
2. ምሳ 20፡27
3. መዝ 139፡1,23
4. ኤር 17፡10
5. ሮሜ 8፡27
6. ራዕ 2፡23

መ. ሁሉም ነገር ክፉ አይደለም ነገር ግን ከእግ/ር በላይ ስናደርጋቸው ሃጢያት ይሆኑብናል

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ምኞት ምንድነው?
2. ሰው ለምን ይመኛል?
3. ሃሳባችን ሁሉ ሃጢያት ነውን?
4. ለክርስቲያን ህይወት ሃሳብን መቆጣጠር ለምን አስፈላጊ ሆነ?
5. ዘፀ 20፡7 ከዘዳ 5፡21 የሚለይበትን ዘርዝር

▣ **"በዚህ"** አስሩን ትዕዛዛት ያመለክታል፡፡ በግሪክ እና በዕብራይስጡ ፅሑፎች ላይ የዘፀ 20 እና የዘዳግ 5 በጥቀቱ አመዚጋገቡ የተለየ ነው፡፡

▣ **"ከሌላይቱ ትዕዛሁ ሁሉ ጋር"** ሙሴ ለህዝቡ ያዘዘውን ሌሎቹን ትዕዛዞች እና ደንቦችን ይመለከታል ወይም በአጠቃላይ ሌላ "ህግን" ለማለት ተፈልጎ ነው"

▣ **"በሚለው ቃል ተጠቅልሏል"** ዘሌዋ 19፡18 ይመልከቱ በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ማቴ 5፡43, ማቴ 19፡19,22፡39 ማርቆ 12፡31 እና ሉቃ 10፡27 ኢየሱስ ሁለተኛ ከሁሉ የምትበልጥ ብሏል፡፡ ገላ 5፡14 እና ያዕቆ 2፡8 ያንብቡ፡፡

▣ **"ባልንጀራህን እንደነፋስህ ውደድ"** አማኞች ሌሎችን ከመውደሰደዳቸው በፊት እግዚአብሔር እና ራሳቸውን መውደድ አለባቸው አግባብነት ያለው እውነተኛ ፍቅር በፍቃድ እንጂ በህግ እና በግድ አይሆንም፡፡

ሮሜ 13፡11-14
**ከእንቅልፋ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሶ ዘመኑን እወቁ ከመንሩበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና ሌሊቱ አልፎአል ቀኑም ቀርቦአል እንግዲህ የጨለማውን ስራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር በአግባብ እንመላለስ በዘፈንና በስካር አይሁን በዝሙትና በመዳራት በክርክርና በቅናት አይሁን ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈፅም ለስጋ አታስቡ**

13፡11

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "ይህንን አድርጉ" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "እና ይህንን አድርጉ" |
| አየመመቅ | "በተጨማሪ ይህን" |
| አእቅ | "ይህን ማድረግ አለባቹ" |
| ኢመቅ | "በተጨማሪ" |

ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ ይህ ማለት የተግባር ሰው መሆን ለክርስቲያን የሚጠበቅ ሕይወት ነው፡፡

▣ **"ዘመኑን እወቁ"** ግሪኩ ኬሮስ ልዩ ወቅትን የሚያመለክት ነው፡፡ ነገር ግን የተለመደው የቀን አቆጣጠር "ኬሮኖስ" አይደለም፡፡

**"ስዓት አሁን እንደደረሰ"** "ሰኖት" የእግ/ርን የድነት እቅድ ያመለክታል፡፡ ሮሜ3፡26, 1ቆሮ 7፡29,10፡11, ያዕቆ 5፡8 1ጴጥ 4፡7, 2ጴጥ 3፡9-13, 1ዮሐ 2፡18, ራዕ 1፡3,22፡10 የኢየሱስን መስቀል እና ዳግሞ ምፃት ያመለክታል፡፡

▣ **"እንቅልፋ"** መንፈሳዊ ድንዛዜ ያመለክታል ኤፌ 5፡8-14 "ተሰሎ 5፡6 ይህ አውዱን የጠበቀ ትርጉሙ መሆንን መገንዘብ አለብን፡፡

▣ **"መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና"** ደህንነት የአንድ ጊዜ ውሳኔ እና ቀጣይነት ያለ ሕይወት ነው፡፡ 1ዮሐ 3፡2, 1ተሰሎ 4፡13-18, ዕብ 9፡28 1ጴጥ 1፡5 በስነ መለኮት ትንተና "ክብራችን" ተብሏል ሮሜ 8፡30 ሉቃ 21፡28 እና 1ሰሎን 4፡15

▣ **"ከመንንበት ጊዜ"** እምነት የአንድ ጊዜ የግል ውሳኔ ሲሆን መቀደስ፣ የፅድቅ ኖሮ፣ መለወጥ፣ በንፅህና መኖር በሕይወታችን ዘመን በሂደት የሚታይ መሆኑን ያስገነዝበናል ዮሐ 1፡12,3፡16 ሮሜ 10፡9-13

**13፡12 "ሌሊቱ አልፎአል"** ክፋ ዘመን ማለፍን እና በአዲስ መተካቱን የሚያበስር ቃል ነው 1ቆሮ 7፡29 ያዕቆ 5፡8, ኤፌ 5፡8,14 2ዮሐ 2፡17-18, 1ዮሐ 4፡7, ራዕ 1፡3, ራዕ 22፡10

▣ **"ቀኑም ቀርቧል"** ይህ የመጨረሻውን ዘመን የሚያመለክት ነው፡፡ ፊሊ 4፡5, ያዕቆ 5፡9 የኢየሱስን መመለሻ ቀን ያመለክታል፡፡

▣ **"አውጥተን... እንልበስ"** እናንተ ራሳችሁ የጨለማን ስራ ማስወገድ የሚል ትርጉም አለው የእግ/ር እና የሰውን ድርሻ በግልፅ የሚያስረዳ ነው፡፡ አማኞች እንቅልፋቸውን ማስወገድ ሃላፊነታቸው ነው ኤፌ 4፡22-(16) ቆላ 3፡10

▣ **"የብርሃንን ጋሻ ጦር"** ከኢሳ 59፡17 ተመሣሣይ ነው፡፡ አማኞች መንፈሳዊ ልብስ መልበስ አለባቸው 2ቆሮ 6፡7 ኤፌ 6፡11-13 ነገር ግን አማኞች ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች አሉ

1. ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል
2. እግዚአብሔር ለሁሉ እንደሚሰጥ ማወቅ አለባቸው
3. በየቀኑ በሕይወታችን መለማመድ ይኖርብናል

**13:13 “በአግባቡ እንመላለስ”** *ዕብራይስጡ “መሄድ” ይላል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስላሣ ሦስት ጊዜ ተጠቅሞበታል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሃጢያቶች በሦስት ጥንድ በሁለት ትርጉም ተቀምጠዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በትርጉም ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት ስለሚገኙበት ነው፡፡*

*ይህ የተፃፈው በቤተክርስቲያን የነበረውን የአይሁድን እና የአህዛብን ውዝግብ ለመፋታት ነው፡፡ ይህም፡-*

1. *የአሕዛብ ክርስቲያኖች (አማኞች) የቀድሞ የጣኦትን አምልኮታቸውንና ክፋ ስራቸው ባለመተዋቸው ነበር*
2. *የአህዛብ ክርስቲያኖች በግልፅ የሚያሳዩት አግባብ ያልሆነ ባህሪ በተለይ በአይሁድ ክርስቲያን መሪዎች እና በስርዓታቸው ላይ ይዘባበቱ ነበር ይህም የኔሮ መንግስት አይሁዶችን መንቀፋ ተከትሎ የሆነ ነበር፡፡*

▣ **“በዘፈን እና በመጠን አይሁን** *በጨለማ ለጣኦት የሚሰዋን የዝሙት መሰዋትን ያመልክታል፡፡ የስጋ ስራ ነው ገላ* 5፡21

▣ **“በዝሙትና በመዳራት”** *የተመሣሠለ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ሁለተኛው ቃል በአዲስ ኪዳን የተለመደ ነው ማርቆ* 7፡22, 2ቆሮ 12፡21” *ገላ*5፡19, *ኤፌ* 4፡19, 1ጴጥ4፡3, 2ጴጥ 2፡7

▣ **“በክርክርና በቅንአት”** *በሰዎች መሃከል ያለን ክርክር ያመለክታል ገላ*5፡20 *ይህም ከተበላሸ ባህሪ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡* 1ቆሮ 3፡3, ቆላ 3፡8 *ይመልከቱ፡፡ በዚያ ጊዜ ይህ ባህሪ የጣኦት አምላኪዎች መገለጫ ነበር በመሆኑም ክርስቲያኖች ይህንን ባህሪ መለማመድ እንደሌለባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው፡፡*

**13:14 “ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልብሱት** *ይህ ክርስቲያን የክርስቶስን ሕይወት መላበስ አለበት ማለት ነው፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ ተንታኞች ይህ ልብስ በጥምቀት ጊዜ የምንለብሰው መንፈሳዊ ልብስ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በሮሜ* 14፡12 *በክርስቶስ አዲስ መሆንን ያሳያል* (*ኤፌ* 4፡22-24, *ቆላ* 3፡8, *ገላ* 3፡27)፡፡

*እኛ በክርስቶስ አሁን ያለን ቦታ እና በእርግጥ ደግሞ ያንን ቦታ የምንይዝበት ጊዜ የተለያዩ በመሆናቸው አሳቦቹ በሁለት ተከፍለዋል እኛ ዛሬ ቅዱሳን ተብለናል ነገር ግን ወደ ቅድስና ሙላት መድረስ ደግሞ ሌላ ነው ክርስቶስን በማመን ደህንነት አግኝተናል ነገር ግን አሁንም ክርስቶስን እንድንመስል ተናግሮናል በመሆኑም እነዚህ ሁለት አሳቦች የሚገጫጩ ይመስላሉ*

*“አይሁን” በሂደት ላይ ያለን እንቅስቃሴ ማቆምን ይመለከታል፡፡ በሮም የነበሩት ክርስቲያኖች የባህድ አምሎኮታቸውን እንዲያቆሙ ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡*

*በአዲስ ኪዳን ትምዕርት ስጋዊ ሰውን ለመግፅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን ግልፅ በሆነ መንገድ ያልዳነ ወይም የነዳ የሚል ጠንካራ ትርጉም የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ሲሰጡ ይታያል ሐዋርያው ሰዎችን በሦስት ሲከፋላቸው መመልከት ይቻላል፡፡*

1. *ተፈጥሮአዊ ሰው ቆሮ* 2፡14
2. *መንፈሳዊ ሰው* 1ቆሮ 3፡1
3. *ስጋዊ ሰው* 1ቆሮ 3፡1

▣ **“ምኞቱን እንዲፈፅም ለስጋ አታስቡ”** *ሐዋርያው ጳውሎስ በሃጢያት ምክንያት ስጋ አዳማዊ ባህሪ እንደሚያስቸግረው በግልፅ የተናገረበት ቦታ ነው፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ (ሮሜ* 7 *ኤፌ* 2፡3)፡፡ *ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለእግ/ር ክብር እንዲሆን ኃይል እንደሚሰጠን ተስፋ አለን ሮሜ* 6 *ነገር ግን ቀጣይ ትግልም ይታያል ሮሜ* 8፡5-7, 1ዮሐ 3፡6-9

***የመወያያ ጥያቄዎች***

*ይህ የጥናት* <u>*መመሪያ*</u> *ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ትርጓሜዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብህም፡፡*

*እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉ ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡*

1. *ሐዋሪያው ጳውሎስ መንግስት የሚለውን ሐተታ ትኩረት መስጠት ለምን አስፈለገ?*
2. *ክርስቲያኖች ለማንኛውም አይነት መንግስት መገዛት ይኖርባቸዋልን?*
3. *ክርስቲያኖች መንግስት ላወጣቸው ህጋዊ ህጎች መገዛት ይገባቸዋልን?*
4. *ሮሜ* 13፡1 *ነገስታቶች በመለኮት ምርጫ የሚመረጡ መሆናቸውን ያስረዳልን?*
5. *ሐዋርያው ጳውሎስ አዲስ ስነ መለኮት ያመጣ ነው ወይስ በኢየሱስ ትምህርት ውስጥ የነበረ ነበር?*
6. *ክርስቲያኖች ለህግ አለመገዛት ትክክለኛ ያረጋቸዋልን? ሐዋ.*5፡25-32?

7. ሮሜ 13፡4 ከሞት ቅጣተ ጋር ያለው ዝምድና ምንድን ነው?
8. የክርስቲያኖች ህልና ሁል ጊዜ ትክክል ሊሆን ይችላልን?
9. በሮሜ 13፡8 መሰረት ክርስቲያን ብድር ሊበደር ይችላንን? ለቲያክርስ
10. በሮሜ 13፡8 ላይ ያለው ቃል ለክርስቲያኖች ወይስ ለሁሉም የሚኖረንን ፍቅር ያሳያል?
11. ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ላይ የሀጢያት ዝርዝሮችን መዘርዘር ለምን አስፈለገው?
12. ክርስቶስን እንዴት መልበስ ይቻላል?

# ሮሜ 14

## በዘመናችን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ አከፋፈል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| አትፍረድ | ነፃ የሚያወጣ ህግ | ሌሎችን መውደድ | ሌሎችን አትወንጅል | ለሌሎች ምዕረት አድርግ |
| 14፡1-12 | 14፡1-13 | 14፡1-4 | 14፡1-4 | 14፡1-12 |
| | | 14፡5-6 | 14፡5-12 | |
| | | 14፡7-9 | | |
| | | 14፡10-12 | | |
| ለወንድምህ እንቅፋት አትሁን | ፍቅር ይኑርህ | | በሌሎችን ተንኮል አትስራ | |
| 14፡13-23 | 14፡14-23 | 14፡13-23 | 14፡13-18 | 14፡13-15 |
| | | | 14፡19-23 | 14፡22-15 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ትርጓሚዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምእራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. ምንባብ አንድ
2. ምንባብ ሁለት
3. ምንባብ ሶስት
4. ወ.ዘ.ተ

**የዓውዱ እይታ ሮሜ 14፡1-12**

*ሀ.* ይህ ምዕራፍ የክርስቲያን ነፃነትን እና ሃላፊነቶችን ለማዛመድ ይጥራል፡፡

*ለ.* በአይሁድና በአህዛብ አማኞች መሃከል የነበረውን የነገር ውጥረት ለማጥፋት የተፃ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜን መጽሐፉ ሲጽፍ በቆሮንቶስ ሆኖ ነበር፡፡ በቆሮንቶስ ያለው ችግር መከፋፈል ሲሆን በሮም ያለው ችግር ደግሞ የተለያዩ አይነት አማኞች መሆናቸው የበለጠ ችግሩን ማባባስ ችሏል፡፡

*ሐ.* አማኞች የራሳቸውን ልምምድ የሌላው እንዲሆን ማስገደድ የለባቸውም 2ቆሮ 10፡12 ነገር ግን አማኞች በተረዱበት መረዳት እግ/ርን ማምለክ አለባቸው አማኞች በምንም በደል ቢገኙ ፍቅርን ማሳየት ይጠበቅብናል ቆሮ 13፡12፤

መ. አማኞች የውስጥ ሃሳባቸውን ማስተካከል ሌላውን ለመርዳት ይጠቅማቸዋል። እያንዳንዱ ክርስቲያን በፍርድ ወንበር ፊት ይጠየቃል 2ቆሮ 5:10

ሠ. ማርቲን ሉተር "ክርስቲያን በሁሉ ለጌታ የሚገዛ ነው ሌላ ተጠሪ የለውም ነገር ግን የሁሉ አገልጋይ ነው"

ረ. ሮሜ 14:1-15:13፤ 1ቆሮ 8:10 እና ቆላ 2:8-23 ይህ አስፈላጊ ሊጠኑ የሚገቡ ክፍሎች ናቸው።

ሸ. እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚበረታበት እና የሚደክምበት የህይወት ክፍል አለው። 1ቆሮ 13:8-13

ቀ. ሐዋርያው ጳውሎስ ደካማ እና ጠንካራ የሚል ቃል ተጠቅሟል ይህ መውደድ እና ጥላቻውን እየገለፀ አይደለም።

በ. የሚከተሉትን ለግንዛቤ እንመልከት
1. እግዚአብሔርእንደተቀበለን እርስ በእርሳችን እንቀባበል ሮሜ 14:1,3፤15:7
2. እግዚአብሔር ፈራጅ ስለሆነ በማናም ላይ አትፍረድ ሮሜ 14:3-12
3. ፍቅር ከግል ነፃነት ይበለጠ ሃይል አለው ሮሜ 14:13-23
4. የኢየሱስን ምሳሌ በመከታተል የራስን ነገር ለሌሎች መተው የሚያንጽና መልካም ስራ መሆኑን መገንዘብ አለብን ሮሜ 15:1-13

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

> **ሮሜ 14:1-4**
> **በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት በአሳቡም ላይ አትፍረዱ። ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የመረበለ የማይበላውን አይናቀው፤ የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ እግ/ር ተቀብሎታልና፤ አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ሲቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው። ነገር ግን እግ/ር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።**

**14:1**

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ* | *"አሁን ተቀበሉ"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"ተቀበሉት"* |
| *አየመመቅ,አእቅ* | *"በደስታ ተቀበሉት"* |
| *ኢመቅ* | *"በሰላምታ ተቀበሉት"* |

ይህ የሚያሳየው በሮም ቤተክርስቲያን በእርግጠኝነት በአህዛብና በአይሁድ መሃከል የመቀባበል ችግር መኖሩን እና የተለያየ ምልዓተ ስብእና ያላቸው ሰዎች እንዳሉም የሚያመለክት ነው።

▣

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"በእምነት የደከመውን"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም , አእቅ* | *"በእምነት የደከሙትን"* |
| *ኢመቅ* | *"አንዱ አማኝ ጠንካራ ካልሆነ"* |

በግሪኩ ጽሑፍ "በእምነቱ የደከመ" ተብሏል በእምነት የደከመው ወንድም በሶስት መገለጫ ተገልፃል። (1) በሙብላቱ የሚወቀስ ሮሜ 14:2,6,21 (2) ተስፋ በመቁረጡ ሮሜ 14:5-6 (3) በጠጪነቱ ይወቀሳል እናንብብ፦ (ሮሜ 15:1፣ 1ቆሮ 8፤9-13፣ 1ቆሮ 9:22)።

የክርስቲያኖች ክፍፍል ብርቱና ደካማ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አግባብ አይሆንም ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው የሚደክምበት እና የሚበረታበት የሕይወት ክፍል ስላለው ነው። የሐዋርያው ጳውሎስ አተያየት የተለየ ነው፤ ገላ 4:9-10 እና ቆላ 2:16-23 ይመልከቱ።

> **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: ድካም**
>
> ደካማ "አስቴኒዮ" ማለት ነው። በደካማ እና በመመካት መሃከል ያለውን ልዩነት በሁለቱ በቆሮንቶስ መጽሃፍቶች ውስጥ እንመልከት።

| *መመካት* | *ደካማ* |
|---|---|
| 1ቆሮ 1:29፣31 | 1ቆሮ 1:25,27 |
| 3:21 | 2:3 |
| 4:7 | 4:10 |
| 1ቆሮ 5:6 | 1ቆሮ 8:7፣9፣10፣11፣12 |

| | |
|---|---|
| 1ቆሮ 15፡16 | |
| 2ቆሮ 1፡12,14 | 9፡22 |
| 2ቆሮ 5፡12 | 1ቆሮ 11፡30 |
| 2ቆሮ 7፡4,14 | 12፡22 |
| 2ቆሮ 8፡24 | 15፡43 |
| 2ቆሮ 9፡2,3 | 2ቆሮ 10፡10 |
| 2ቆሮ 10፡8,13,15,16,17 | 11፡21,29,30 |
| 2ቆሮ 11፡12,16,17,18,30 | 12፡5,9,10 |
| 2ቆሮ 12፡1,5,6,9 | 13፡3,4 |

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ድካም የተጠቀመበትን የተለያዩ መንገዶችን እንመልከት፡፡

1. የእግ/ር ድካም 1ቆሮ 1፡25
2. የአለም ደካሞች 1ቆሮ 1፡27
3. የጳውሎስ ድካምና ፍርሃት 1ቆሮ 2፡3፣ 2ቆሮ 11፡29,30
4. ጳውሎስና የሚሲዮናዊ ቡድኑ 1ቆሮ 4፡10፣ 2ቆሮ 11፡21
5. ደካማ አማኞች ሮሜ 14፡1-15-13፣ 1ቆሮ 8፡7,9,10,11,12
6. የሰውነት ህመም 1ቆሮ 11፡30
7. የሰው የሰውነት ብልቶች 1ቆሮ 12፡22
8. የሰው ሰውነት
9. የሐዋርያው የሰውነቱ አቅም እና የንግግሩ ችሎታ 2ቆሮ 10፡10
10. የሐዋርያው ጳውሎስ ድካም የእግ/ርን ጥንካሬን አመጣ፣ 2ቆሮ 12፡9,10 2ቆሮ 13፡4,9
11. የክርስቶስ መልአክ በጳውሎስ ሲተሳሰፍ 2ቆሮ 13፡3
12. የክርስቶስ አካል 2ቆሮ 13፡4

▣

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | ***"አላማቹ በሃሳቡ ላይ ለመፍረድ አይሁን"*** |
| ***አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*** | ***"የጠረጠራችሁትን ሁሉ አትፍረዱበት"*** |
| ***አየመመቅ*** | ***"በሃሳቡ ላይ ግጭትን አትፍጠሩ"*** |
| ***አእቅ*** | ***"ስለ ግል ሃሳባቸው ሙግት አትግጠሙ"*** |
| ***ኢመቅ*** | ***"ክንትርክ ነፃ ሁኑ"*** |

አማኞች የሌላውን የአኗኗር ስልት ያለ አግባብ መንቀፍ አይጠበቅባቸውም ይህ ከተደረገ ነፃነትን ማሳጣት ይሆናል፡፡

14፡2 በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ምግብ ስለ ሃይማኖት እንጂ ስለ ጤና የተፃፈ አይደለም፡፡ ይህ ችግር ከሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይገባል፡፡ (1) አይሁድ የምግብ ስርአት አላቸው ዘሌ 11 (2) ስጋ በተለምዶ ለጣኦት የሚሰጥ በመሆኑ ነው 1ቆሮ 8፡10 ኢየሱስ በትምህርቱ ሰው በሚበላው እንደማይረክስ አስተምሯል ማቴ 15፡10-20፣ ማርቆ 7፡14-23፣ ሐዋ 10

14፡3 **"የሚበላ የማይበላውን አይናቀው"** "የማይጠቅም አድርጎ አይቁጠረው" የሚል ትርጉም አለው ሮሜ 14፡10, ሉቃ 18፡9, 1ቆሮ 6፡4፤ 2ቆሮ 10፡10 ገላ 4፡14, 1ተሰሎ 5፡20 ጠንካራ እምነት ያለው በፍጹም ደካማ እምነት ያለውን ሊንቀው አይገባም፡፡

▣ **"እግዚአብሔር ተቀብሎታል"** "ተቀብሎታል" አማኞች እርስ በእርስ በቀባበል ያለባቸው በክርስቶስ በተደረገው የመስቀል ስራ መሆን አለበት፡፡ ሮሜ 15፡7

14፡4 **"ማን ነህ?"** ግሪኩ "ደካማ" ለማለት የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡

▣ **"አገልጋዩን"** "ኦቶኬትስ" ከ "አኪዮስ" ይህ ማለት "ቤት" ሙሉ ትርጉሙ **የቤቱን አገልጋይ** ሉቃ 16፡13፣ ሐዋ 10፡7፣ ሮሜ 14፡4፣ 1ጴጥ 2፡18 በግሪኩ ጽሑፍ ላይ የተመሳሰሉ ጥቅሶችን አሉ ዘፍ 9፡25,27፡37,44፡16 ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታ አገልጋይ መሆኑን አበክሮ ይናገራል፡፡ 2ቆሮ 5፡10

▣ **"ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው"** ሐዋርያው ጳውሎስ ለሁለቱም መልዕክቱን የሚያደርስ ይመስላል፡፡ አማኞች ለጌታ የመሰላቸውን ነገር ያደርጋሉ (ማቴ 7፡1-15)፡፡

▣ **"ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ያቆማል"** ይህ አስደናቂ ቃል ኪዳን ነው፤ ሮሜ 5፡1-2፣ ይሁዳ 24-25, አማኝ ሁሉ በእግ/ር ይደገፋል (1ቆሮ 15፡1-2)፡፡

**ሮሜ 14፡5-9**
**ይህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል ያ ግን ቀን ሁሉ አንድ እንደ ሆነ ያስባል እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል የሚባለም እግዚአብሔርን ያመሰግናልና። ለጌታ ብሎ ይባላል የማይበላም ለጌታ ብሎ ይበላል የማይበላም ለጌታ ብሎ አይበላም እግ/ርንም ያመሰግናልና። ለጌታ ብሎ ይባላል የማባልም ለጌታ ብሎ ይባላል። የማይባልም ለጌታ ብሎ አይባልም እግ/ርንም ያሰግናል። ከእኛ አንድስ እንኳን ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም።**
**በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራንና ብንሞተም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በህይወት ሆነን ብንኖር ወይም እንሞት የጌታ ነን። ስለዚህ ነገር ሙታንንም ህያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶልናልና፤ ህያውም ሆኖአልና።**

14.5 **"ይህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል"** በርካታ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ለማክበር የቀን መቁጠሪ ይጠቀማሉ። ገላ 4፡10 ቆላ 2፡16-17 ነገር ግን ቀኖች ሁሉ የእግ/ር መሆናቸው እንጂ ልዩ የሚባል ቀን እንደሌለ መገንዘብ አለብን።

▣ **"በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ"** አማኞች አንድ ነገር አጥብቀው መረዳት ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ መሆን አለበት።

14፡5 **"ለጌታ"** ለግል ጥቅም ያልሆነ ለማለት ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ጊዜ ተጽፏል በቁ 6 እና 8። ሁለቱን የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ (ኤፌ 6፡7 እና ቆላ 3፡23)።

14፡7 **"ከእኛ ለራሱ የኖረ የለም"** ለክርስቶስ መኖርን ያመለክታል ወይም የቤተሰብነት ኑሮን የሚያሳይም ነው (1ቆሮ 10፡ 24፣27-33)።

14፡8 **"ብንኖርም፣ ብንሞትም"** "ራስን መስጠት ያመለክታል ኤፌ 6,7፤ ቆላ 3፡23

14፡9 **"ሙታንና ሕያውያንን ሊገዛ ባለው"** የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት ሞት እና ትንሳኤውን ማገልገል ይጠበቅባቸዋል ሮሜ 6 አማኞች የግል ፍላጎታቸውን በመግታት የፍቅር አምላክ የሆነውን ማገልገል ይጠበቅባቸዋል 2ቆሮ 5፡14-15፤ ገላ 2፡20 1ዮሐ 3፡16

**ሮሜ 14፡10-12**
**አንተም በወንድምህ ላይ ትፈዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና። እኔ ሕያው ነኝ ይላል ጌታ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ተብሎ ተጽፎአልና። እነግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግ/ር መልስ እንሰጣለን።**

14.10 **"አንተም"** ፊት ለፊት ለመናገር የተጠቀመበት ቃል ነው። በቁጥር አስር ውስጥ የሚታየው ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች ፈራጅ እና የሚፈረድበት እንዳለ እንመለከታለን። በመሆኑም ሁለት ነገር መገንዘብ ይቻላል። (1) የእግዚአብሔርን ፈራጅነት ዘንግተዋል (2) ፍርዳቸው ሁሉን በማወቅ ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ያሳያል።

▣ **"ሁላችንም በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን"** 2ቆሮ 5፡10 ተመሳሳይ ቃል እናነባለን፤ አማኞች በአምላካቸው ፊት በግል የሚቆሙበት ቀን አለ በዚህ ቀን ስለ ሰሩት ስራ መልስ ይመልሳሉ። ማቴ 25፡31-46

14፡11 **"ተብሎ ተጽፏል"** የብሉይ ኪዳንን መጽሀፍት ያመለክታል፤ ከኢሳ 45፡23 የተወሰደ ነው። ፊሊ 2፡10-11 ያንብቡ።

▣ **"እኔ ህያው ነኝ"** የእግዚአብሔር የኪዳን ስም ነው። ዘፀ 3፡14 ያህዌ ለዘላለም የሚኖር፣ ብቸኛ ዘላለማዊ ነው። ስለዚህ በህያውነቱ መሃላ ሲያደርግ እንመለከታለን፤

14፡12 **"እንግዲህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግ/ር መልስ እንሰጣለን"** ክርስቲያኖች ይፈረድባቸዋል 2ቆሮ 5፡10። የግሪኩ "እግ/ር" የሚለው የለውም።

**የአውዱ አጠቃላይ እይታ ሮሜ 14፡13-23**

ሀ. አማኞች የሌላውን ድካም በመሸከም ክርስቶስ እንደተቀበላቸው ሊቀባበሉ ይገባል። የአንዳንድ አማኞች የቤተሰብ ሃይማኖተኝነት፣ የግል የኑሮ ደረጃ፣ የግል ልምምድ ለእግዚአብሔር ምንም እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

ለ. በክርስቶስ ያለ ፍቅር ወንድማቾችን ያቀራርባል እርሱም ንፁህ ፍቅር ተብሏል ኢየሱስ እራሱ ለወዳጆቹ እንደሰጠ እንዲሁ ለወዳጆቻችን ራሳችንን ልንሰጥ ይገባል፤ 2ቆሮ 5፡13-14፣ ዮሐ 3፡16 ይህ የክርስትና መሰረታዊ ትምህርት መሆኑን እንገነዘብ፡፡

ሐ. የአለም ማንኛው ነገር ጠፊ መሆኑን መገንዘብ አለብን ነገር ግን አማኞች በየእለት ሮአቸው ውስጥ ይህንን ማስተዋል ይገባቸዋል፡፡ ሮሜ 14፡14, 20 1ቆሮ 6፡12,10፡25-26

መ. በክርስቶስ ያገኘነው ነፃነት ሌሎችን ለመበደል ልንጠቀምበት አይገባም ምክንያቱም የሚጠቅም የምንለው የሌላውን ህሊና ሊጎዳ ይችላልና እጅግ ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ (1ቆሮ 6፡12, 1ቆሮ 10፡23)፡፡

ሠ. ሐዋርያው ጳውሎስ ደካማ የሚባሉ ወንድሞች ብርቱዎች የሚሆኑበት ቀን የሚመጣ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ምንባብ ስለ ፀጋ ሳይሆን እርስ በእርስ ስለሚኖር ፍቅር ያስገነዝባል የአማኞች ቀዳሚ ስራ ሌሎችን መውደድ እንጂ መለወጥ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር አለምን ሁሉ እንደወደደ ልጁን ኢየሱስን ለሁሉ እንደሰጠ እናውቃለን እንዲሁም እኛም ሰዎች ከመለወጣቸው በፊትም ልንወዳቸው ይገባል፡፡

**የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት**

**ሮሜ 14፡13-23**
**እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በእርሳችን አንፈራረድ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቁረጡ፡፡ በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደ ሌላ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቼአለሁም፡፡ ነገር ግን ምንም እርኩስ እንዲሆን ለሚቀጥር ለእርሱ ርኩስ ነው፡፡ ወንድምህንም በመብልህ አተጥፍው፡፡ እንግዲህ ለእናንተ ያለው መልካም ነገር፤ አይስደብ የእግዚአብሔር መንግስት ፅድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና፡፡ እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔር ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው፡፡ እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን ስራ አታፍርስ፡፡ ሁሉ ንፁህ ነው፡፡ በመጠራጠር የተበላ እንደ ሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፉ ነው፡፡ ስጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወነድምህም የሚሰናከለበትን አለማድረግ መልካም ነው፡፡ ለአንተ ያለህ እምነት በእግ/ር ፊት ለራስህ ይሁንልህ፡፡ ፈትኖ መልካም እንዲሆን በሚቀጥረው ነገር በራሱ ላይ የማይፈረድ ብፅዕ ነው፡፡ የሚጠራጠረው ግን ቢበላ በእምነት ስላልሆነ ተኮንኖአል በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ሃጢያት ነው፡፡**

14፡13 **"እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በእርሳችን አንፈራረድ"** ይህ ማስጠንቀቂያ ሳይሆን ነገር ግን ፊፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ ሮሜ 14፡16 ይመልከቱ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ቃል አምስት ጊዜ ተጠቅሞበት ይስተዋላል፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: ክርስቲያኖች እርስ በእርስ ሊፈራረዱ ይገባልን?**
በሁለት መንገዶች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የመጀመሪያው ክርስቲያኖች በሌላው ላይ ሊፈረዱ አይገባም ማቴ 7፡1-5 ሉቃ 6፡37፣ 42 ሮሜ 2፡1-11 ያዕቆ 4፡11-12 በሌላ በኩል አማኞች መሪዎችን ይወቅሳሉ ማቴ 7፡6፣ 15-16 1ቆሮ 14፡ 29፤ 1ተሰሎ 5፡21፣ 1ጢሞ 3፡1-13 እና 1የሐ 4፡1-6 ይመልከቱ፡፡
**ግምገማ ለማድረግ የሚጠቅሙ መሰረታዊ ሃሳቦችን እንመልከት**
1. ግምገማ ለማበረታታት መሆን አለበት 1ዮሐ 4፡1
2. ግምገማ በንፁህ መንፈስ መካሄድ አለበት ገላ 6፡1
3. ግምገማ ግለሰብን የሚጎዳ መልክ መሆን የለበትም ሮሜ 14፡1-23፣ 1ቆሮ 8፡1-13፣10፡23-33
4. ግምገማ በአግባብ የማይሄዱትን መሪዎች ለመምረጥ ይረዳል 1ጢሞ 3

▣ **"ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት"** 1ቆሮ 8፡9 ይመልከቱ፡፡ ይህ ማለት አንዱ አማኝ ለሌላው ጠባቂው፣ ረዳቱ፣ ባልንጀራው እና የሚያበረታታው መሆን አለበት እንጂ በመንገዱ የሚያሰናክለው መሆን የለበትም፡፡

14፡14

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | "አውቄአለሁ ደግሞም ተረድቼአለሁ በጌታ በኢየሱስ" |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "አውቄአለሁ ደግሞም ተረድቼአለበት በጌታ በኢየሱስ" |
| አየመመቅ | "አውቄአለሁ ደግሞም አምኜአለሁ በጌታ በኢየሱስ" |
| አእቅ | "ከኢየሱስ ጋር ያለኝ አንድነት አረጋግጦልኛል" |
| ኢመቅ | "አሁን እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን ስለ ኢየሱስ እናገራለሁ" |

ይህ ማለት አምኜአለሁ ደግሞም እያመንኩ እኖራለሁ የሚል ትርጉም ይሰጣል አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረታቸው እየጠነከረ ሲሄድ መንፈሳዊ መረዳታቸው እያደገ ይሄዳል።

▣ **"በራሱ እርኩስ ነገር እንደሌለ"** ሐዋ 10፡9-16 ያንብቡ። ፍጥረታት፣ ነገሮች ሁሉ ክፉ አይደሉም ሮሜ 14፡20፣ ማርቆ 7፡18-23፣ 1ቆሮ 10፡25-26፣ 1ጢሞ 4፡4፣ ቲቶ 1፡15)

▣ **"ነገርግን ለእርሱ እርኩስ አድርጎ ለሚቆና ሁሉ ነገር እርኩ ነው"** ይህ በሃይማኖት ወግ ሲታይ እርኩስ ነው። አማኞች ህሊናቸውን ማዳመጥ አለባቸው ሮሜ 14፡5፤22 ነገር ግን በሌላው ህሊና ሊፈረዱ አይገባቸውም።

14፡15 "ወንድምህን በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆነህ" ፀሐፊው ትኩረት የሰጠው ለወንድም ነው፡፤ ለመብት ሳይሆን ለፍቅር; ለነፃነት ሳይሆን ነገር ግን ለሃላፊነት ቅደም መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል።

ሁለቱን ነጥቦች ያዛምዱ፣ የአይሁድ የምግብ ስርዓት ለሌዋ 11፣ ለጣኦታት የስጋ መስዋት ይሰጥ ነበር 1ቆሮ 8-10

▣ **"እንግዲህ በፍቅር አልተመላለሳችሁም"** "የፍጽምና ህግ" ይባላል ያዕቆ 1፡15 ያዕቆ 3፡12 ወይም የንጉስ ህግ" ይባላል ያዕቆ 2፡8 ወይም የክርስቶስ ህግ "ተብሏል ገላ 6፡2 እነዚህ የአዲስ ኪዳን ግዴታዎች እና መመሪያዎች ናቸው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ክርስቶስ የምተለትን በምትበላው ምግብ አታሰናክለው"** |
| **አየመመቅ** | **"የሚያስናክል ምግብ በመብላት ክርስቶስ የምተላትን አታሰናክል"** |
| **አእቅ** | **"የምትበላው ክርስቶስ የሞተለትን ማሰናከል የለበትም"** |
| **ኢመቅ** | **"የተፈለገውን ሁሉ መብላት አትችልም ብትበላ ክርስቶስ የሞተለትን እንደማሰናከል ይቆጠራል"** |

ይህ ማለት የክርስቲያን ነፃነት ሌላኛውን ወገን እንደሚያሳዝን ያሳያል። ምናልበት ደህንነትን ላያሳጣ ይችላል ነገር ግን ሰላምን ሊረብሽ እና አገልግሎት ሊያጠፋ ይችላል።

ግሪኩ "ሊያጠፋ" ማለት ሃዘን እና ህመም" ተብሏል። ሐዋርያው ጳውሎስ ቃሉን ተጠቅሟል (2ቆሮ፣ ሮሜ 2፡2,4፣5፤ 6፡10፤7፡8፤9፤11፣ ሮሜ 14፡16)።

14፡16

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በናንተ ያለው መልካም ነገር ክፉ እንደሆነ አይነገር"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም,አየመመቅ** | **"መልካሙ እንዲ ክፉ አይነገር"** |
| **አእቅ** | **"መልካም ነገር በክፉ ስም አይጠራ"** |
| **ኢመቅ** | **"የተሰጣችሁን መብት አታመቻምቹ"** |

"መልካም ነገር" የተባለው በአውዱ ብርቱ ወንድሞች የሚያደርጉትን ስራ ለማመልከት ነው። ስለዚህ ይህ መልካም ስራ በሌሎች ደካማ ተብሎ እንዳይጠራ ሐዋርያው ጳውሎስ ያሳስባል።
ይህ ጥቅስ በግልጽ የሚያስቀምጠው አማኞች በአብሮነት ኑሮ ውስጥ እርስ በእርሳቸው በመጠባበቅ መኖር እንዳለባቸው የሚያስተምር አይነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ነው።

14፡17 **"የእግዚአብሔር መንግስት"** በሮሜ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ተፃፈ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ መሃከለኛ ትምህርት ነው ማቴ 6፡8-10።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርእስ : የእግዚአብሔር መንግስት**

በብሉይ ኪዳን ይህዌ የእስራኤል ንጉስ የሚል አስተሳሰብ ነበር። 1ሳሙ 8፡7 መዝ 16፡16 መዝ 24፡7-9 ኢሳ 43፡15፤ 44፡4-6 እና የሚመጣው መሲሁ ንጉስ ተብሏል መዝ 2፡6 የእግዚአብሔር መንግስት በአዲስ ቃል ኪዳን መታለች ኤርም 31፡31-34፤ ሕዝቅ 36፡27-23 ዮሐንስ መጥምቁ አዋጅ ማቴ 3፡2 ማርቆ 1፡15 ኢየሱስ ስለ መንግስተ ሰማይ አስተማረ ማቴ 4፡17፤ 23 ማቴ 9፡3፤ ማር 26፡28 ማርቆ 24፡14፤ 26፡29 ማርቆ 9፡1 ሉቃ 21፡31፤ 22፡16፣ 18 የእግዚአብሔር መንግስት የምትመጣ ናት ማቴ 16፡28 ማቴ 24፡14 ማርቆ 9፡1 ሉቃ 21፡31፤ 22፡16፣18

ከወንጌላት መሃከል በማርቆስ እና በሉቃስ ወንጌል ላይ በቀጥታ "የእግዚአብሔር መንግስት" የሚል ጥምር ቃል እናገኛለን። ማቴዎስ "መንግስተ ሰማይ" ብሏል ምክንያቱም አይሁድ የእግዚአብሔር ስም መጥራት ለሃይማኖታቸው ክብርን አለመስጠት እንደሆነ ስለሚያስቡ ነው፤ ነገር ግን ማርቆስና ሉቃስ ጽሑፋቸውን ለአህዛቦች ስለፃፈ የእግዚአብሔርን ስም ተጠቅመው እንመለከታለን በዮሐንስ ወንጌል ላይ "የዘላለም ህይወት" የሚል ይህንን ቃል የሚተካ ቃል እናገኛለን።

የብሉይ ኪዳን ትኩረት የመሲሁ መምጣት ላይ ሲሆን የአዲስ ኪዳን ደግሞ ምፅአቱንም ያጠቃልላል ኢሳ 53፣ ዘካ 9፡9 እነዚህ ሁለቱ ለብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አንባቢዎች ለነበሩት አይሁድ ሊቀበሉት ያስቸገራቸው መሆኑን እንገነዘባለን። ነገር ግን "የተፈፀመች" እና "የምትመጣ" መንግስት እንዳለች መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣለን።

▣ “ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት” እነዚህን ነገሮች ሊሰጥ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች የተሰጠ ውጫዊና ውስጣዊ መረከቶች ናቸው፡፡
“ፅድቅ” ሮሜ 3፡21 ; 31፡4 ይመልከቱ በማመን ፅድቅን ማግኘት ይቻላል፡፡

14፡18 አማኞች ስለደካሞች ወንድሞቻቸው የየራሳቸው ፍላጎት መገደብ ይኖርባቸዋል፤ ይህ የሞተላቸውን ጌታ ማክበራቸውን ያሳያል፡፡

▣ “በሰው ዘንድ የተመሰገነ” ለወንጌል በር የሚከፍት መሰረታዊ ዓረፍተ ነገር ነው 2ቆሮ 8፡21፣ “ጴጥሮ 2፡12 በማዕበረሰቡ መሃከል ያለው እዎንታዊ ምላሽ ለወንጌል አመቺ መድረክ ይፈጥራል፡፡

14፡19 “እንከተል” ግሪኩ “ኪያኮ” ማለት “በትጋት መከተል” “ለማግኘት መጣር” በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ የተለመደ አባል ነው ሮሜ 9፡30-31 ሮሜ 12፡13 ነገር ግን በሮሜ 12፡14 በስደት ለነበሩ አማኞች ተነገረ 1ቆሮ 4፡12፤ 2ቆሮ 4፡9 ገላ 1፡13፤23 ፊሊ. 3፡6

አማኞች አጥብቀው መፈለግ ያለባቸውን በዝርዝር እንመልከት

1. እንግዶችን መቀበል ሮሜ 12፡13
2. ሌላውን የሚያንፅ ሮሜ 14፡19
3. ፍቅርን መከተል አለባቸው 1ቆሮ 14፡1
4. ክርስቶስን መምሰል ፊሊ. 3፡12-14
5. መልካምነትን ዘሌዋ 5፡15
6. ፅድቅን፣ እግዚአብሔር መምሰል እምነትን ፍቅርን 1ጢሞ 6፡11
7. ጽድቅን፣ እምነት፣ ፍቅርን፣ ሰላምን መከታተል 2ጢሞ 2፡22

▣ “እንግዲህ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በእርሳችን የምንታነጽበትን እንከተል” አማኞች ለማንኛውም ለሚያደርጉት ነገር አላማ ሊኖራቸው ይገባል መዝ 34፡14 እብ 12፡14 የአንድ አማኝ የላቀ ትምህርት እና መረዳት ለመታነጽ ምክንያት ይሆናል (ሮሜ 15፡2፣ 1ቆሮ 6፡12፣ 1ቆሮ 14፡26፣ ኤፌ. 4፡12)፡፡

14፡20 “የእግ/ርን ስራ አታፍርስ” በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ሶስት ጊዜ ይህ አረፍተ ነገር ተጠቅሷል 2ቆሮ 5፡1 እና ገላ 2፡18፡፡

▣ “የእግ/ር ስራ” በዚህ ዐውድ ውስጥ መንፈሳዊን ስራ በተለይ በደካማ ክርስቲያኖች ያለውን ያመለክታል፡፡ በዚህ ምንባብ እና በ1ቆሮ 8-10 አንዱ ቡድን ሌላውን እንዲረዳ ሐዋርያው ጳውሎስ ያዘዘበት ብቸኛ ምንባብ ነው፡፡

▣ “ሁሉ ንፀህ ነውን” ቁ.14 ይመልከቱ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ነገር ግን በመጠራጠር ለሚበላ ሰው ከፉ ነው፤** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **“በጥርጣሬ ለሚበላ ክፉ ነው”** |
| **አየመመቅ** | **“በሰራኸው ስህተት ሌሎች መሰናክል የለባቸውም በተለይ በምትበለው”** |
| **አእቅ** | **“ሌላውን የሚያሰናክል መብላትህ ስህተት ነው”** |
| **ኢመቅ** | **“በምትበላው ምግብ ሌላው ቢሰናከል በደል ይሆንብሃል”** |

ይህ ቁጥር ለዚህ ምዕራፍ ዋና መልእክት ነው (1ቆሮ 10፡25-26፣ ቲቶ 1፡15)፡፡

ይህ ምግብ የሚያመለክተው ለጣኦት የታረደን ነው፤ (1ቆሮ 8-10)፡፡

ስለ ስጋ መልካምነት እና ክፋት ሳይሆን ደካማ ህሊና ያለው ወንድም የሚሰናከል ከሆነ ስለህሊናው ሲባል ስጋ መብላት እንደ ክፉ ኃጥያት መታየት መቻሉ ስለወንድም ያለን ግንዛቤ ከፍተኛ መሆን እንዳለበት የመላከት ቃል ነው፡፡
በርካታ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች “ደካማው ወንድም” በብርቱው ወንድም እውን ተጽኖ እንደሚደረግበት ይገልፃል፡፡ በካቶሊኮች አዲስ ትርጉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ “ሂሊና የማይቀበለውን ምግብ መብላት ትክክል አይደለም” ይላል፡፡

14፡21 የተፃፈው “ለብርቱ ወንድሞች” ይህ ከምግቦች “አጠቃላይ መታቀብ” እንዲያደርጉ የተናገረበት ቦታ ነው፡፡

መብላት እና መጠጣት ክልክል አይደለም ነገር ግን አስናካይ ከሆነ ስለወንድም ሲባል ገደብ ሲደረግለት ይታያል 1ቆሮ 8-10 14፡22

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ያለህ እምነት ለአንተ ለራስህ ይሁን ራሱን ማይከንን ደስተኛ ነውና”** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **“እምነት ካለህ ለራስህ ይሁን ራሱን የማይኮንን ደስተኛ ነውና”** |

| | |
|---|---|
| *አየመመቅ* | *"ያለህ እምነት ላንተ ለራሰህ ይሁን ራሳቸውን የናወቅሴ ሰዎች እንዴት የተባለኩ ናቸው።"* |
| *አእቅ* | *"ያለህን እምነት አጥብቀህ ያዝ የበደለኝነት ስሜት የማይሰማቸው ሰዎች ህሊናቸው ንጹህ ነው"* |
| *ኢመቅ* | *"እምነትህን ያዝ እርሱም በአንተ እና በእግዚአብሔር መሃከል ነው ይህም ህሊናህን ንፁ ያደርገዋል።* |

*አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ብርሃንና በቅዱስ ቃሉ ራሱን ህሊናውን እየጠበቀ ሊኖር ይገባል በተሰጠው ብርሃን መሄድ አለበት ቁ*22፣ *"ብርቱ አማኝ" ቁ* 23 *"ደካማ አማኝ "የሚለውን ደግመው ይመልከቱ" ሮሜ* 2:18 *ይመልከቱ*

14:23 **"ነገር ግን የሚጠራጠር"** *ከመጠን ያለፈ ተጣራጣሪ ክርስቲያን አለ።*

▣ ***"ክፉ ነው ወይም የተወገዘ ነው"*** *በግሪኩ ጹሁፍ ላይ "ካርታ እና ካረና" ማለት "በደለኝነት" በአዲሱ እትም የግሪክ ጽሁፍ ደግሞ "ከፍርድ ቀጥሎ የሚመታ ቅጣት" ሮሜ* 5:16-18 *ሮሜ* 8:1 *ያንብቡ በተጨማሪ በአዲስ ኪዳን የግሪክ መዝገበ ቃላት ገጽ* 328 *የአንድን ሰው ህሊና መጉዳት እና በውጤቱም የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳን የሚያመለክት ነው"*

▣ **"ቢበላ"** *ሶስተኛ ነጠላ መደብን ያመለክታል፤*

▣ ***"በእምነት ያልሆነ ሁሉ ሃጢያት ነው"*** *ሃጢያት የህሊና ጥሰት እንጂ የሕግ ጥሰት ብቻ አይደለም። አማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቃቸው የሚያደርጉት ድርጊት ትክክለና እንደሆነ ያደርገዋል።*

▣ *አንዳንድ የግሪክ ጽሁፎች ሮሜ* 16:25-27 *ለሮሜ* 14 *መጨረሻ እንደመዝጊያ ሲጠቀሙበት ይታያል ሌሎቹ ደግሞ በሁለቱም ምዕራፎች መጨረሻ አንድ አይነት ማጠቃለያ ምስጋና ሲጽፉ እንመለከታለን። በተለያየ የግሪክ ጽሁፎች ላይ ስድስት ጊዜ ተጽፋል ይህን የሮም አገር ባህል አባባል ነው።ለተጨማሪ ገለፃ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ኦሪገን ማርከዮን የሮሜን የመጨረሻዎቹን ሁለት ምእራፎች ስላስወገዳቸው የመዝጊያው ሰላምታ በምእራፍ አስራ አራት መጨረሻ ተፃፈ በማለት ተናግሯል።* (1) *ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ቤተክርስቲያን ከምዕራፍ* 1-14 *ከፃፈ በኋላ አስፈላጊነቱን ሲመለከት ለኤፌሶንም ይህንኑ መጽሐፍ ሁለት ምእራፍ ጨምሮበት መፃፉን በመሆኑም ረጅም የመዝጊው ሰላምታ የተፃፈው ለኤፌሶን መሆኑ ይገመታል* (2) *በምእራፍ አስራ ስድስት ላይ ያለው ሰላምታ ወደ ሮም ለሚሄዱ በኤፌሶን ለነበሩ ክርስቲኖች እንጂ ለሮም ቤተክርስቲያን አይደም ምክንያቱም አቂላ እና ድርሰቅላ በኤፌሶን ነበሩ። የእነርሱን ወደ ሮም መመለስ መጽሀፍ ቅዱስ አይናገርም።*
*ሰላምታ በፀሐፊው የተፃፈ አይደለም ነገር ግን ለሃይማኖት ስርየት ለቤተክርስቲያን ለህዝብ አገልግሎት ጠቃሚ በመሆኑ የተጨመረ ነው።*

***የመወያያ ጥያቄዎች***

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን። እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ትርጓሜዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብህም።*

*እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉ ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው።*

1. *"ደካማ ወንድም" የሚለውን አስረዳ ሐዋርያው ጳውሎስ ያልበሰሉ ናቸው ብሏልን*
2. *ስለ ክርስቲያን ነፃነት እና ሃላፊነቶች ትንተና ስጥ፤*
3. *በተፈጥሮ ሁሉ ነገር ንፁህ ነውን ተወያዩበት ሮሜ* 14:14፤20
4. *ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን "ምግብ" የሚለው ርዕስ ለምን አስፈላጊ ሆነ "ቆሮ* 8:10) *ሐዋርያው የሮሜን መፅሐፍ ሲጽፉ ከቆሮንቶስ ሆኖ ነበር።*
5. *በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የእውቀትን የነፃነትን እና የፍቅርን ዝምድና እናሳይ።*
6. *በቤቴክርስቲያን ህብረታችን መመስረት ያለበት በምን ላይ ነው፤*
7. *አማኞች የግል ምርጫች መሰረት ማድረግ ያለበት ማንን ነው*
8. *የአማኞች ድርጊት በምን መንገድ የሌላውን ህሊና እንደሚጎዳ አስረዳ፤ ከእኛስ ምን ማድረግ ይጠበቃል*
9. *የክርስትናን ስነ ምግባር እንዴት ማስተካከል ይቻላል*
10. *ክርስቲያን በመንፈሳዊ ህይወቱ ሲበስል ክፉ ነገሮችን በመቃወም ደግሞ ለእግዚአብሔር የሚሆነውን ይቀበላል ማለት ምን ማለት ነው.*

# ሮሜ 15

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ባልንጀሮች ሆይ እናንተን አይደለም | የሌሎችን ሸክም ተሸከሙ | የሌላውን ሸክም አንሸከም | ሌሎችን እናንተን አይደለም | (14:22-15:6) |
| 15:1-6 | 15:1-6 | 15:1-6 | 15:16 | |
| ወንጌል ለአህዛብ እና ለአይሁድ | እግዚአብሔር እናክብር | | ወንጌል ለአህዛብ | ስለ አንድነት ተጠየቅ |
| 151-13 | 15:7-13 | 15:7-13 | 15:7-12 | 15:7-12 |
| | | | 15:13 | 15:13 |
| የጳውሎስ የሚሲዮናዊ ተልኮ | ከእየሩሳሌም እስከ ምድር ዳርቻ | የግል ማስታወሻ | የጳውሎስ የጽሁፍ ስራ | መግቢያ |
| 15:14-21 | 15:14-21 | 15:14-21 | 15:14-21 | 15:14-16 |
| | | | | 15:17-21 |
| የጳውሎስ እቅድ ሮምን ለመጎብኘት | ሮምን ለመጎብኘት የጳውሎስ ዕቅድ | | የጳውሎስ እቅድ ሮምን ለማየት | የጳውሎስ ዕቅድ |
| 15:22-29 | 15:22-23 | 15:22-29 | 15:22-29 | 15:22-29 |
| 15:30-33 | | 15:30-33 | 15:50-33 | 15:30-33 |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ትርጓሜዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምእራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ፡፡

1. ምእራፍ አንድ
2. ምእራፍ ሁለት
3. ምእራፍ ሶስት
4. ወ.ዘ.ተ

**የአውዱ አጠቃላይ እይታ ከቁ.1-13**

ሀ. የክርስቲያን ነፃነት እና ሃላፊነት በዚህ ምዕራፍ ላይ ውይይቱ ቀጥሏል::
ለ. አጠቃላይ ውይይቱ ሮሜ 14:1-15:3::

1- በእግዚአብሔር እንደተቀበለን እርስ በእርሳችን እንቀባበል ሮሜ 14፡1፣3 ሮሜ 15፡7::
2- እርስ በእርሳችን አንፈራረድ ምክንያቱም ፈራጁ ክርስቶስ ነው፡፡
3- ፍቅር ከግል ነፃነት ይበልጣል ሮሜ 14፡13-23::
4- የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል ለሌሎች መኖር መጀመር አለብን ሮሜ 15፡1-13::

ሐ. ሮሜ 15፡5-6 በሮሜ 14፡1-15፡3 ያለውን ሃሳብ ሶስት እጥፍ አላማውን ጠቅልሎ የያዘ ምንባብ ነው፡፡
1. እርስ በእርስ በመስማማት እንኑር::
2. የኢየሱስን ምሳሌ እንከተል::
3. በአንድ ልብ ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርብ ::

መ. የግል ነፃነት እና የጋራ ኃላፊነት የሚለውን ተመልከቱ 1 ቆሮ 8፡10::

**የቃል እና የጥም ቃል ጥናት**

> **ሮሜ 15፡1-6**
> ***እኛም ሃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል እያንዳንዳችን እንድናንፀው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ፡፡ ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኝምና ነገር ግን አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብ እንደ ተፃፈ ሆነበት፡፡ በመፅናትና በመፃህፋት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆናልን፤ ዘንድ አስቀድሞ የተፃፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና፡፡ በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስን ክርስቶስ አባት ታከብሩ ዘንድ የትዕግስትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ አባት ታከብሩ ዘንድ የትግስትና የመጸናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በእርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ፡፡***

15፡ 1

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ* | *"ብርቱዎች ደካሞችን ሊሸከሙ ይገባል"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"ብርቱዎች የሆንን የደከሞችን ከባድ ሸክም ልንሸከም ይገባል"* |
| *አየመመቅ* | *"ብርቱዎች የደካሞችን ሸክም ማንሳት ይገባቸዋል"* |
| *አእቅ* | *"በእምነት ጠንካሮች የሆንን የሌሎችን ድካም ልንሸከም ያስፈልጋል"* |
| *ኢመቅ* | *"ብርቱዎች ደካሞችን ድካም መሸከም አለባቸው"* |

*ይህ በሮም ቤተ ክርስቲያን እና በአብያተ ክርስቲያናት መሃከል ያለውን ውጥረት ለማርገብ ሐዋርያው ጳውሎስ በማያሻማ ሁኔታ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን "ከብርቱዎቹ" ምድብ አድርጎት ይታያል፡፡*

*በአዲሱ የእንግሊዘኛ መደበኛ ትርጉም "ብርቱዎች" የሚባሉ በሃይማኖት ስርአት እና ህግ ያልተያዙ ነገር ግን ራሳቸውን ነፃ ያደረጉ ናቸው፡፡ ብርቱዎች የሚለው አመለካከት በሃይማኖት እና በሃይማኖት ልምምዶቻችን ከሌላው በልጠን መገኘት አንችልም የሚል አመለካከት ነው፡፡*

*ደካማ "አዱኔስት" ማለት መልፈስፈስ" ሮሜ 8፡3 "ከአስቴኒዮ"*

*ይለያል፤ ሮሜ 14፡1፣21 1ቆሮ 8፡7,10,11,12 1ቆሮ 9፡22*

*እያንዳንዱ ክርስቲያን የሌለውን አማኝ ሸክም ሊሸከም እንጂ ሊቆጣጠረው በፈፀም አይገባም፡፡ "መሸከም" የሚለውን ቃል የሚያብራራ ጥቅሶችን ይመልከቱ (ዮሐ 19፡17፣ ሉቃ 14፡27)፡፡*

▣ "*እራሳችንን ደስ እንዳናሰኝ ይገባል" ራስ ወዳድነት ያለመብሰል ምልክት ነው፤ የኢየሱስ ምሳሌ እንከተል ፊሊ* 2፡1-11፣ ሮሜ 14፡1, 14,21,27 *ለደካሞች የተፃፈውን እናንብብ* ሮሜ 14፡3,20,23 ሮሜ 15፡5-6,7

▣

| | |
|---|---|
| *አአመመቅ* | *"እንዲታነጽ"* |
| *አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* | *"ወደ መታነጽ ምራቸው"* |
| *አየመመቅ* | *"ለባልንጀራህ መልካም መታነጽ"* |
| *አእቅ* | *"በእምነት እንዲገለብቱ"* |
| *ኢመቅ* | *"ጠንካራ ክርስቲያን እንዲሆኑ እርዳቸው"* |

*ይህ ሃሳብ የምዕራፉ ዋና መልእክት ነው፡፡ ሮሜ* 14፡6,19 *የመንፈሳዊ የፀጋ ስጦታ የሚሰጡበት አላማ ለማነጽ ነው፤* 1ቆሮ 10፡23 1ቆሮ 12፤7፣ 14፡26 ኢፌ 4፡29

*የሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት የሚያተኩረው ሌላውን በማገልገል; በማነጽ እና ለሌላው መኖር መሆኑ በደብዳቤዎቹ ጽሁፎች በግልጽ ተቀምጦ እናገኛለን፡፡ በማፅበርመታነጽ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የሚያስረዱ ጥቅሶችን እንመልከት፡፡* (1ቆሮ 14፡12፣ ኤፌ 4፡12፣ ሮሜ 14፡19)

> **ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርእስ: "ማነጽ"**
> *ማነፅ* "Oikdomeo" *"ማለት "ቤት መገንባት" ማቴ 7፡24 ነገር ግን በምሳሌነት ቃሉ ለሌሎች ትርጉሞች ያገለግላል፡፡*

1. የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) (1ቆሮ 3፡9፣ ኤፌ 2፡21፣ ኤፌ 4፡16)
2. *መገንባት*
   *ሀ. ደካማ ወንድሞችን ሮሜ* 15፡1
   *ለ.* ባልንጀራን ሮሜ 15፡2
   *ሐ.* እርስ በእርስ ኤፌ 4፡29፣ 1ተሰሎ 5፡11
   *መ. ቅዱሳንን ኤፌ* 4፡11
3. እኛ ራሳችን እንታነፃለን
   *ሀ.* በፍቅር ቆሮ 8፡1፣ ኤፌ 4፡16
   *ለ.* የግል ነፃነታችንን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት 1ጢሞ 1፡4
   *ሐ. ያልተሟላን ግንዛቤን ማስወገድ* 1ጢሞ 1፡4
   *መ.* የቤተክርስቲያንህን የመድረክ ተናጋሪዎችን ወሰን አድርግ 1ቆሮ 14፡3-4፣12
4. *ሁሉ ለማነጽ ይሁን*
   *ሀ.* የሐዋርያው ጳውሎስ ስልጣን 2ቆሮ 10፡8፣ 2ቆሮ 12፡19፣ **92 | ገጽ**፣ 2ቆሮ 13፡10
   *ለ.* የማጠቃለያ ሐተታ ሮሜ 14፡19፣ 1ቆሮ 14፡26

**15፡3 "ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና"** ክርስቶስ እውነተኛ ምሳሌአችን ነው፡፡ ፊሊ 2፡1-11፣ 1ጴጥሮስ 2፡21፣ 1ዮሐ 3፡16

▣ **"ተብሎ እንደተፃፈ"** *የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት ያመለክታል፡፡ ቃሉ የተወሰደው መዝ* 69፡9፡፡ *ሐዋርያው ጳውሎስ* የክርስቶስን ህይወት እና፣ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት ሁለቱ ትላልቅ ማስረጃዎቹ ነበሩ፡፡

**15.4 "አስቀድሞ የተፃፈው ለትምህርታችን ተጽፏል"** የብሉይ ኪዳን መጽሐፉ ለአዲስ ኪዳን አማኞች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ሮሜ 4፡23-24 1ቆሮ 9፡10 1ቆሮ 10፡6፣11፡፡ ለአዲስ ኪዳን አማኞች የሚጠቅም ነው፡፡ 2ጢሞ 2፡15 2 ጢሞ 3፡16-17፡፡

▣ **"በመጽናት እና መጽሐፍት በሚሰጡት መጽናናት"** *የአማኞች መጽናትና የእግዚአብሔር ቃል ውህደት ለህይወት መልካም ውጤት እንደሚያስገኙ ያመለክታል:: ይህ ጽናት ኢየሱስ ለሚወጣበት ቀን ለክብር የሚያበቃ ነው፡፡*

▣ **"ተስፋ ይሆንልን ዘንድ"** በአዲስ ኪዳን "ተስፋ" *ዳግም ምፃትን ያመለክታል፡፡* ሮሜ 8፡30፣ 1ዮሐ 3፡2፡፡
*ሐዋሪያው ጳውሎስ "ተስፋ" የሚለውን ቃል ለተለያየ ሃሳብ ተጠቅሞበታል: ነገር ግን የሚዛመድ ሃሳብ ነው፡፡* የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ፡- (1ቆሮ 13፡13፣ 1ተሰሎ 1፡3፣ 2 ተሰሎ 12፡16)፡፡
*ሐዋርያው "ተስፋ" የሚለውን ቃል የተጠቀመበትን ጥቅሶች እንመልከት፡-*

1. *ግም ምፃት ገላ* 5፡5፣ ኤፌ 1፡18፣ ኤፌ 4፡4፣ ቲቶ 2፡13
2. ኢየሱስ ተስፋችን ነው፤ 1ጢሞ 1፡1
3. በወንጌል *ማመን* ቆላ 1፡23
4. ድነት ቆላ 1፡5፣ 1ተሰሎ 4፡13፣ 1ተሰሎ 5፡8
5. የእግዚአብሔር ክብር ሮሜ 5፡2፣ 2 ቆሮ 3፡12፣ ቆላ 1፡27
6. የድነት እርግጠኝነት 1 ተሰሎ 5፡8፣
7. የዘላለም ሕይወት ቲቶ 1፡2፣ ቲቶ 3፡7
8. የፍጥነት *መዋጀት* ሮሜ 8፡20
9. እምነት ሮሜ 8፡23-25፣ ሮሜ 15፡4
10. የእግዚአብሔር ስም ሮሜ 15፡13
11. የጳውሎስ ምኞት ለአማኞች 2ቆሮ 1፡7

**15.5 "እግ/ር .... ይስጣችሁ"** ምኞት እና ፀሎትን ያመለክታል ልመናዎቹ ሁለት ናቸው፡፡ (1) አንድ ልብ ይሁንላችሁ፡፡ ሮሜ 12፡16፣ 2ቆሮ 13፡11፣ ልሊ 2፡2 (2) በአንድ ላይ እግዚአብሔርን *ማመስገን* ሮሜ 15፡6,7,9

▣ **"የትዕግስት እና የመጽናናት አምላክ"** የእግዚአብሔር የስሙ *መገለጫ* ነው፤ ሮሜ 15፡13, 1ቆሮ 1፡3

**15.6 "እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት ታከብሩ ዘንድ"** ይህ የአዲስ ኪዳን ሙሉ ስሙ ነው፤ 2ቆሮ 1፡3፣ ኤፌ 1፡3፣ 1ጴጥ 1፡3፡፡ ይህ እግዚአብሔር በፍልስፍና የሚገኘው አምላክ ሳይሆን በመገለጥ የሚታወቀው አምላክ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሉስ በፀሎቱ ሁለቱን የእግዚአብሔርን ስም *መገለጫዎች* ይጠቅሳል እነርሱም፡- (1) የትዕግስትና የመጽናናት አምላክ (2) የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ

**ሮሜ 15፡7-13**
**ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደተቀበለችሁ እንዲሁ እርስ በእርሳቹ ተቀባበሩ፡፡ ለአባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል ያፀና ዘንድ ደግሞም ስለዚህ በአህዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ ስምህም እዘምራለሁ ተብሎ አንደ ተፃፈ አህዛብ ስለምህረቱ እግዚአብሔር ያከብሩ ዘንድ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ ከህዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል፡፡ ደግሞም፡፡**
**እናንተ አህዛብ ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ**
**ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል፡፡ ደግሞም ኢሳያስ፡-**
**የእሴይ ሥር አህዛብንም ሊገዛ የሚነሣሙ ይሆናል፡፡ በእርሱ አህዛብ ተስፋ ያደርጋሉ ይላል የተስፋ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይመለባችሁ፡፡**

**ሮሜ 15፡7**
*አአመመቅ,* *አእቅ* **"እርስ በእርስ ተቀባበሉ"**
*አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* **"አንዱ ሌላውን ይቀበለው"**
*አየመመቅ* **"እርስ በእርስ ተቀባበሉ"**
*ኢመቅ* **"እንደባልንጀራ እርስ በእርሳችሁ ተቀባበሉ"**

አማኞች እርሱ በእርሳቸው ሊቀባበሉ ይገባል ሮሜ 14፡1 እግዚአብሔር አህዛቦችን ተቀበለ 15፡9-12 ሮሜ 1፡12፣ 12፡ 5፣10፣16 ሮሜ 13፡8፤14፡13፣19 ሮሜ 15፡5፡7፣14 ሮሜ 16፡6፤

▣ **"ክርስቶስ እንደተቀበለን"** ሮሜ 14፡3 ይመልከቱ የአማኞችን ተግባር የሚገልጽ ነው፡፡ ምዕራፍ 14 የሚያተኩረው በሚከተሉት ላይ ነው፡፡ (1) ክርስቶስ እንደ ጌታ እና ፈራጅ፡፡ ሮሜ 14፡1-12 (2) ክርስቶስ ራሱን በመስጠት ምሳሌአችን ነው፡፡ ሮሜ 14፡13-23

▣ **"ለእግ/ር ክብር"** ሮሜ 3፡23 ይመልከቱ፡፡

**15.8 "ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር የመገረዝ አገልጋይ ሆነ፡፡"** ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍፃሜ ነው ማቴ 15፡24፡፡ ይህ ሃሳብ በሮም ቤተክርስቲያን በአይሁድ እና በአህዛብ አማኞች መሃከል የነበረ አከራካሪ አጀንዳ ነበር፡፡

▣
*አአመመቅ,* **"እግዚአብሔር እውነት ለሚነጋጋኝ እርሱም የአባቶችን ቃል ኪዳን"**
*አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም* **"እግዚአብሔር እውነት ለማረጋገጥ ይህም ከአባቶች ጋር የተደረገውን ኪዳን"**
*አየመመቅ* **"ለአባቶች የተነገረውን ቃል ኪዳን የእግዚአብሔር እውነት ለመፈጸም ነው "**
*ኢመቅ* **"እግዚአብሔር ለአባቶች ስለገባው ኪዳን ታማኝ ነው"፡፡**

ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለህዝበ እስራኤል የገባውን ኪዳን ያስታውሰናል፤ ሮሜ 4፡16 ከዚህም በተጨማሪ ለፍጥነት የተገባውን ቃል ኪዳንም ያመለክታል፡- ዘፍ 3፡15፣ ኢሳ 2፡2-4ዘፍ 12፡3፣ ኢሳ 66፡18-24ዘፀ 19፡5-6፣ ኢሳ 56፡ 7፡፡

የአዲስ ኪዳን መልእክት የብሉይ ኪዳን ትንቢት መፈፀም እንጂ አዲስ የተለየ መልዕክት አለመሆኑን መረዳት አለብን፡፡ (1) ለእስራኤል የተገባው ቃል ኪዳን መፈፀም (2) ለአህዛብ የወንጌል በር መከፈቱ ሮሜ 3፡29-30፤ 29-30
ሮሜ 10፡11-12 ሮሜ 11፡25,32 ኤፌ 2፡1-3፡21 እስራኤል ለወንጌል ተልእኮ አስቸጋሪ ስትሆን እግዚአብሔር አዲስቱ እስራኤል በመንፈስ እንዳስነሳ እንመልከት፤ገላ 6፡16፣ ማቴ 28፡19-20፣ ዮሐ 3፡16፡፡

▣ **"ያፀና"** ሮሜ 4፡16

**15፡9-12** "በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ አሕዛብ እንዳሉ የሚያመልክት ጥቅስ ነው፤
ሮሜ 10፡10-20፣ ዘዳ 32፡43፣ መዝ 18፡49፣ መዝ 117፡1፣ 2ሳሙ 22፡50፣ ኢሳ 11፡1,10

15፡9 **"ስለምህረቱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ"** የእግ/ር ምህረት የዘላለም ዕቅድ ውስጥ የተጠቀለለ መሆን ለማስገንዘብ ይረዳል ሮሜ 9፡15፣16፣18፣23 አሕዛብ ተጠቃለሉ ሮሜ 11፡30፣31፤32 ሮሜ 15፡9፡፡ የእግዚአብሔር ምህረት አይሁድንና አሕዛብን ያድናል፡፡ ይህ ማዳን ከሰው ፍላጎት የመጣ አይደለም ሮሜ 9 እግ/ር አይቀየርም ዘፀ 34፤6፣ ነህ9፡17፣ መዝ 103፤8፣4፣ ኢዮ 2፡13)፡፡

▣ **"የተስፋ አምላክ"** ይህ በተለምዶ የመዝጊያ ሰላምታ ላይ የሚቀርብ አረፍተ ነገር ነው፡፡

**15.13 "ደስታና ሰላም ሁሉ ይሙላባችሁ"** የጳውሎስ ፀሎት ነው (ሮሜ 5፡ 1-2፣ ሮሜ 14፡17)፡፡
▣
*አአመመቅ, አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም*

*አየመመቅ* "በጣመን"
*አእቅ* "በእርሱ በኩል ባላችሁ እምነት"
*ኢመቅ* "በእምነታችሁ"

የአንድ አማኝ በህይወት መፅናት የሚታወቀው በክርስቶስ ባለው እምነት፣ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል እና በግል ባለው ሰላም እና ደስታ መሆኑን መገንዘብ አለብን። እምነት ደግሞ በኑሮአችን ሁሉ በምናሳየው ጽናት ይመዘናል።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ : መትረፍረፍ "Perissevo"**
ይህንን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀመበትን ቦታዎች እንመልከት።

1. የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከተትረፈረፈ ስለ ምን በእኔ ዳግም እንደ ሃጢያተኞች ገና ይፈርዱብኛል። ሮሜ 3፡7
2. ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም ሮሜ 5፡15
3. የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ ሮሜ 15፡13
4. መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም ባንበላም ምንም አይጎድለንም ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም 1ቆሮ 8፡8
5. እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ 1ቆሮ 14፡12
6. የእግዚአብሔር ስራ የሚበዛላችሁ ሁኑ 1ቆሮ 15፡58
7. የክርስቶስ ስቃይ በእኛ ላይ እንደበዛ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ ይበዛልናል 2ቆሮ 3፡9
8. የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይጣልጣልና 2ቆሮ 3፡9
9. በብዙዎች በኩል የተትረፈረፈው ፀጋ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋናን ያበዛ ዘንድ ሁሉ ስለ እናንተ ነውና 2ቆሮ 4፡15
10. በብዙ መከራ ተፈትነው ሳለ የደስታቸው ብዛት እና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸው ባለ አግነታቸው አብዝቶአል 2 ቆሮ 8፡2
11. ነገር ግነ በነገር ሁሉ በእምነትና በቃል በእውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደ ተረፋችሁ በዚህ ቸር ስራ ደግሞ ትረፉ 2ቆሮ 8፡7
12. ለበጎ ስራ ትበዛ ዘንድ ጸጋ ሊያበዛላችሁ ይችላል 2ቆሮ 9፡8
13. ነገር ግን ደግሞ በብዙ ምስጋና ለእግ/ር ይበዛል 2ቆሮ 9፡12
14. ፀጋውን በጥበብና በእምሮ አበዛልን አለ 1፡8
15. ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ከፊት ይልቅ እያደገ እንደ በዛ ይህን እፀልያለሁ ፊሊ 1፡9
16. በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችም ጋር እንድቆይ አውቃለሁ። ፊሊ 1፡26
17. መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ በእያንዳንዱ ነገር መነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብና መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ፊሊ 4፡12
18. በሃይማኖት ጽኑ ምስጋናም ይብዛላችሁ ቆላ 2፡7
19. ጌታ እርስ በእርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ይብዛ ይጨምርም 1ተሰሎ 3፡12
20. ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ በጌታ በኢየሱስ እንለምናችኋለን ተሰሎ 4፡1
21. ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ ተሰሎ 4፡10

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግ/ርን ፀጋ የሚገልጽበት ቋንቋ "የተትረፈረፈ" መሆኑ እግ/ር ለሰው ያለውን ትእግስትና ፍቅር ለማመልከት የተጠቀመበት ነው።

▣ "**በመንፈስ ቅዱስ ሃይል**" በአዲስ ኪዳን የሚሰራውን የእግዚአብሔርን ስራ ለመግለጽ የሚጠቅም ቃል ነው። በዚህ በመጨረሻው ዘመን ያለ መንፈስ ቅዱስ ምንም ማድረግ አይቻልም የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ። (ሮሜ 15፡19፣ 1ቆሮ 2፡4፣ 1ተሰሎ 15)።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን። እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ትርጓሜዎች መሆናቸውን መዘንጋት የለብህም።

እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉ ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው።

1. የሮሜ 14፡1-15-13 ዋና መልዕክት ምንድ ነው?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 15፡9-12 የጠቀሰው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ፈይዳው ምንድ ነው? ከዚያስ ምን እውነታን እናስተውላለን?

የአውዱ አጠቃላይ እይታ ሮሜ 15፡14-33

ሀ. የዚህ ደብዳቤ መክፈቻና መዝጊያ ተመሳሳይ ነው፤ 1፡8-15
  1. ሐዋርያው ጳውሎስ እምነታቸውን አደነቀ ሮሜ 1፡8
  2. ጳውሎስ ለአህዛብ እንደተጠራ አረጋገጠራ ሮሜ 1፡13 -14
  3. ጳውሎስ ሊጎበኛቸው ፍላጎት እንዳለው ገለፀ ሮሜ 1፡10፣13
  4. የጳውሎስ ያልተሳካ የጉብኝት ፍላጎቱን የሚያመለክት ሃሳብ ነው፤ ሮሜ 1፡13

ለ. በአይድሁና በአህዛብ አማኞች መሃከል የነበረውን መለያየት ያመጣው ችግር በምዕራፍ 9፡11 እና በምዕ 14፡1-15፡3 ተጠቅሷል።

ሐ. ሌላው በሐወርያው ጳውሎስ ሐዋርያዊ ስልጣን ላይ ጥያቄ ተነስቷል። በዚህም የመከላከያ ሃሳብ አቅርቧል ሮሜ 15፡15-19፣ ሮሜ 1፡2

መ. ምንባቡ ሁለት ርዕስ ጉዳዮችን አሉት።
  1. የጳውሎስ ሐዋርያዊ አገልግሎት፣ የወንጌል አገልግሎት እና አህዛብን እንዲያገለግል መሾሙን ይጠቅሳል ሮሜ 15፡14-21
  2. ሐዋርያው ጳውሎስ አላማውን ለማስፈፀም እስከ ሮም መምጣት አስፈልጎት ነበር። ሮሜ 15፡22-23

የቃል እና የጥምር ቃል ጥናት

> ሮሜ 15፡14-21
> **እኔም ራሴ ደግሞ ወንድሞቼ ሆይ በበጎነት ራሳችሁ እንደ ተሞላችሁ እውቀትም ሁሉ እንደ ሞላችሁ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሰፁ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ። ነገር ግን አህዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መስዋዕት ለሆኑ ለእግዚአብሔር ወንጌል እነደ ካህን እያገለገልሁ ለአህዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ በእግዚአብሔር በተሰጠኝ ፀጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፈረት ፃፉሁላችሁ። እንግዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር በክርስቶ ኢየሱስ ትምክት አለኝ። አህዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በስራ በምልክትና በድንቅ ነገር ሃይል በመንፈስ ቅዱስም ሃይል በእኔ አድርጎ ከሰራው በቀር በምንም ልናገር አልደፍርም ስለዚህ ለኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ። እንዲሁም በሌላው ሰው መሰረት ላይ እንዳልሰራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ ነገር ግን፡- ስለ እርሱ ያልተወራላቸው ያያሉ ያልሰሙም ያስተውላሉ ተብሎ እንደ ተፃፈ ነው።**

15፡14

| | |
|---|---|
| አአመመቅ | “ወንድሞቼ እኔ ስለ እናንተ እተማመናለሁ” |
| አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | “አሁን እኔ ስለ እናንተ በጎላት በድፍረት መናገር እችላለሁ” |
| አየመመቅ | “ወንድሞቼና እህቶቼ እኔ ስለ እናንተ ምልካምነት በድፍረት እናገራለሁ” |
| አእቅ | “ባልንጀሮቼ አሁን እኔ ራሴ ስለ እናንተ እመካለሁ” |
| ኢመቅ | “እኔ ስለ እናንተ አልጠራጠርም፤ ወንድሞቼና እህቶቼ፤ ነገር ግን ሙሉ እምነቴን በእናንተ ላይ እጥላለሁ።” |

“እኔ የሚለው ቃል “all to ego” በግሪክ አገናኝ ቃል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሶስት ርእስ ጉዳዮችን ስለ ሮም ቤተክርስቲያን ጠቅሷል። (1) የሮም ቤተ ክርስቲያን በመልካምነት የተሞሉ መሆናቸውን አሞግሷል። (2) የሮም ቤተ ክርስቲያን በእውቀት የተሞሉ መሆናቸው ጠቅሷል። (3) የሮም ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን እርስ በእርስ የሚከባበሩ መሆናቸው ጽፏል።

▣ “በበጎነት ራሳችሁ እንደተሞላችሁ” በግሪክ “እንደተሞላች” በሴት ስያሜ ቀርቧል” ትርጉሙም “ሙሉ የሆነ ያልጎደለ”ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ቃል በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል ሮሜ 1፡29 እና 15፡4።

“መሞላት” ፐሊሮ የሚለውን ቃል ጳውሎስ በተለያየ ቦታ ተጠቅሞበታል ሮሜ 1፡29 ሮሜ 8፡4 ሮሜ 15፡13፣ 14፡19። “ፐሊሮማ” የሚለው ግን ሌላ ትርጉም አለው የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት በሮሜ 11፡12፣25፣ ሮሜ 13፡10፣ ሮሜ 15፡29 በገላጭ ግስ የተቀመጠ አይደለም።

▣ **"እውቀትም ደግሞ እንዲሞላባችሁ"** ይህንን ቃል ለመረዳት የሚረዱ ሁለቱን መንገዶች እንመልከት፡፡ (1) ይህንን ቃል ለመረዳት ወደ ቀደመው ምንባብ መሄድ ይጠበቅብናል እርሱም ሮሜ 14፡1-15፡13 ይሄውም አማኞች እርስ በእርስ የሚኖራቸውን የመተሳሰብና ፍቅር የሚያመለክት ነው፡፡ (2) ሌላው "እውቀት" የሚለው የወንጌልን እውነት፣ እምነታቸውን፣ ትክክለኛውን ትምህርት እና ስህተትን መለየታቸውን ያመለክታል፤

15.5 **"በድፍረት ፃፍኩላችሁ"** ሐዋርያው ጳውሎስን የሮሜን መጽሐፍ የፃፈው ቆሮንቶስ ሆኖ ነበር፡፡ በመሆኑም ጳውሎስን በድፍረት እንዲጽፉ ያደረገው በቤተክርስቲያኒቱ የነበረው በግዜው የተፈጠረው ችግር ነበር፡፡ 2ቆሮ 10፡2፣12 2ቆሮ 11፡21፤

▣ **"ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ፀጋ ምክንያት"** ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔርን ፀጋ እውቅና የሰጠበት ቦታ ነው፡፡ ሮሜ 1፡5 ሮሜ 12፡3 1ቆሮ 3፡10 1ቆሮ 15፡10 ገላ 2፡9 እና ኤፌ 3፡7-8፡፡ ይህ ፀጋ እርሱን እንዳዳነው፣ ስጦታ እንደሰጠው እና ለአህዛብ ወንጌል ሰባኪ እንዳደረገው በዝርዝር የተናገረበት ቦታ ነው፡፡ ሮሜ 11፡13 ሮሜ 15፡16፡፡

15፡16 **"አገልጋይ .... እያገለገልሁ... መስዋት .... የተወደደ"** ቁ.16 እና ቁ.17 በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ቋንቋዎችን ናቸው "አገልጋይ" የሚለው ቃል የክህነት አገልግሎት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ የክርስቶስን አገልግሎት የሚያመላክት ነው፡፡ ዕብ 8፡2፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ላይ ራሱን "ካህን" ብሎ ሲጠራ እንመለከታለን ፊሊ 2፡17 ይሄውም አህዛብን እንዲያገልግል የተሰጠው ሹመት ነው፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል ህዝብ የተሰጠ ኃላፊነት ነበር፤ ዘፀ 19፡5-6፣ ኢሳ 66፡20 በአዲስ ኪዳን ለቤተክርስቲያን የማስታረቅ የወንጌል አገልግሎት ተሰቷታል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ለተጨማሪ መረዳት አንብቧቸው ፡፡ (ማቴ 28፡18-20፣ ሉቃ 24፡47፣ 1ጴጥ 2፡5፣9፣ ራዕ 1፡6)፡፡

▣ **"በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው"** ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር የመቀድስ ስራ እናዳለው በዚህም ስፍው አህዝብ ለእግ/ር መንግስት ተቀባይነት እነደማኖራቸው ተናገረ፡፡ በተጨማሪም በአህዛብና በበአይድ መሃስል፤ የላበረውን ልዩነት ለመፋታት የተጠቀመበት አይነተኛ የማስታረቅያ ሃሳብ ነው 1ቆሮ 6፡11፡፡

15፡17-19 **"ስላሴ"** የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል ተጽፎ ባይገኝም ነገር ግን በሶስት አካልና በስም ተጠርተው በዚህ ክፍል እንመለከታለን፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች ለተጨማሪ ግንዛቤ አንብቡ፡፡ ማቴ 3፡16-17፣ 1ቆሮ 12፡4-6፣ ሐዋ 2፡33-34፣ 2ቆሮ 1፡21፣ ሮሜ 8፡9-10፣ ኤፌ 1፡3-14፣1ቆሮ 12፡4-6፣ ቲቶ 3፡4-6)፡፡

15፡18-19 ሐዋርያው ጳውሎስ በአህዛብ መካከል ያለው አገልግሎቱ ውጤታማ የሆነበትን መንገድ እንደሚከተለው ገለፃታል፡- (1) በቃል (2) በስራ (3) በምልክት (4) በድንቅ (5) በመንፈስ ሃይል

በመንፈስ ሃይል የሚለውን ሌሎች የግሪክ ጽሁሮች "መንፈስ ቅዱስ" ወይም "የእግዚአብሔር መንፈስ" በሚል ይለወጡታል፡፡

15፡18 **"አሕዛብ እንዲተዘዙ"** የእግዚአብሔር ፍላጎት አህዛብ ሁሉ የእርሱን ባሕሪ እንዲመስሉ ነው፡፡ የኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት አላማ የእግ/ርን የቀድሞው መልክ ለሰው ለመመለስ ነው ዘፍ 3፡፡ የክርስትና ዋናው አላማ ከመለኮት ጋር ሕብረት መፍጠር እና ክርስቶስን መምሰል ነው፡፡

▣ **"በቃል እና በሥራ"** የሐዋርያው ጳውሎስን አገልግሎት የሚያመለክት እንጂ በሮም የነበሩ ክርስቲያኖችን ታዛዥነት የሚያመሪክት አይደለም፡፡

15፡9 **"በምልክትና በድንቅ ብርሃይል"** በሐዋርያት ስራ መጸሐፍ ውስጥ እነዚህ ሁለት ቃላቶች እናገኛለን ሐዋ 14፡8-10፣ ሐዋ 16-18፣25-26 ሐዋ 20፡9-12፣28፡8-9 የእግዚአብሔርን ሀይል በወንጌል ስራው ውስጥ ያመለክታል፡፡

▣ **"ክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ"** ሐዋርያው ጳውሎስ በምስራቅ ሚዲትራኒያ የነበረውን አገልግሎቱን ማጠናቀቁን የተናገረበት ቦታ ነው፡፡

▣ **"እስከ እልዋሪቆን"** የሮም ግዛት ሆና "የአልማታ" ትባላለች፤ ከአድሪያቲካ ባህር በስተምስራቅ ከሚቄደንያ በሰሜን ምእራብ ትገኛለች፡፡ የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ሐዋርያው ጳውሎስ በእልዋሪቆን የነበረውን አገልግሎት አልዘገበም፡፡ "እስከ" የሚለው ምናልባት" "እስከ ከተማው ወሰን" ወይም "በዛሪያው ያሉትን" የሚያመለክት ይሆናል፡፡

15፡20 **"እንዲሁም በሌላው ሰው መሰረት ላይ እንዳልሰራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ፡፡** ይህ የጳውሎስን የወንጌል አገልግሎቱን አገልግሎት ዘዴውን ያመለክታል፤ 1ቆሮ 3፡10፣ 2ቆሮ 10፡15-16 ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል ፈጽመው ያልሰሙትን ነገር ግን ጣኦትን የሚያመልኩ ሰዎችን ለመድረስ ፍላጎቱን አሳይቷል፡፡

15፡21 ከግሪኩ የተወሰደ ነው፡- ኢሳ 52፡15 ይመልከቱ ሐፍ የው ጳውሎስ ይህንን የብሉይ ኪዳን ትንቢት ለወንጌል ስብከት ዕቅዱ ሲጠቀምበት እንደመለከታለን፡፡

**ሮሜ 15:22-29**
**ስለዚህ ደግሞ ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ። አሁን ግን በዚህ አገር ስፍራ ወደ ፊት ስለ ሌለኝ ከብዙ ዓመትም ጀምሮ ወደ እናንተ ልመጣ ናፍቆት ስላለኝ ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ እናንተን እንዳይ አስቀድሜ ጥቂት ከጠግባችሁ ወደዚያ በጉዙዬ እነድትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ። መቄደንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና። ወደዋልና የእርሱም ባለእዳዎች ናቸው። አህዛብን በእርሱ መንፈሳዊ ነገርን ተካፋዮች ከሆኑ በስጋዊ ነገር ደግሞ ያገለግሏቸው ዘንድ ይገባቸዋልና። እንግዲህ ይህን ፈጽሜ ይህን ፍሬ ከተምሁላቸው በኋላ በእናንተ በኩል አልፌ ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት ሙላት እንድመጣ አውቃለሁ።**

15:22 **"ስለዚህ ደግሞ"** ጳውሎስ ምክንያቱን ለመግለጽ የተጠቀመት ቃል ነው።

**"ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከላከልሁ"** ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ ተከልክሏል ሮሜ 1:13። ሐዋርያውን የከለከለው ሰይጣን፣ እግዚአብሔር ፣ ክፉ ሰዎች ወይም ሌላ የወንጌል ስብከት አገልግሎ ሊሆን ይችላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ በነበረ ጊዜ ለሮም ቤተክርስቲያን የሚያስፈልጋቸውን መልዕክት ጽፎላቸዋል። ነገር ግን በቆሮንቶስ ወንጌል በአግባቡ፤ እንዳይሰብክ ከወንድሞች ተቋውሞ ደርሶበታል። በመሆኑም ጳውሎስ ተከለከልሁ ያለበት ምክንያቱ ይህ ሳይሆን አይቀርም።

15:23 **"አሁን ግን በዚህ አገር ስፍራ ወደ ፊት ስለሌለኝ"** በትንሹ እስያ እና በምስራቅ ሚድትራኒያ ያለውን ቦታ የሚጠቅስ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ አካባቢ ባሉ አገሮች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል አላስተማረም ነበር። በጥቂት ቦታዎች ላይ ወንጌልን አድርሷል።

▣ **"በብዙ ዓመትም ጀምሮ ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ እናንተን እንዳይ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮም ሄዶ ለማገልገል ያለውን ፋላጎት የገለፀበት ቦታ ነው፤ ሮሜ 1:10-15፣ ሐዋ 19:21፣ ሐዋ 23:11
በግሪኩ ስነ ጽሑፍ ላይ "ብዙ" Polus) የሚለው ትርጉሙ "ከተለያዩ ጊዜያት" (ikanos) በሚል ተተክቷል።

15:24 **"ወደ እስፔን በሄድሁ ጊዜ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ምዕራብ የሮም ግዛት መሄድ ጓጉቷል፤ 2ቆሮ 10:16። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከሮም እስር ተላቆ አራተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞውን ለማድረግ እየተዘጋጀ ያለበት ጊዜ ነው። ይህንን ለመረዳት 1ጢሞ እና 2ጢሞ ማንበቡ አስፈላጊ ነው።

ይህ ታሪክ በቀጥታ ሊመሳከር የሚችለው ከ2ጢሞ 4:10 ጋር ነው። የግሪኩ ጽሑፍ የሚያረጋጥመው ጳውሎስ እስከ ባህሩ ዳርቻ ድረስ በመጓዝ ወንጌልን እንዳገለገለ ተጽፎ እናገኛለን።

▣ **"በጉዞዬ እንድትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ"** ይህ ዓረፍተ ነገር በመጀመሪያው ዓመተ ምህረት አገልጋዮች ለቀጣይ አገልግሎት ለመሰማራት የሌሎችን እገዛ የሚጠይቁበት መንገድ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች በአግባቡ ይመልከቱ፡- (ሐዋ 15:3፣ 2ቆሮ 16:6፣ 2 ቆሮ 1:16፣ ቲቶ 3:13)።

15:26 **"በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና"** ሐዋርያው ጳውሎስ የገንዘብ እርዳታ ከብዙዎቹ ተቀብብሏል። በዝርዝር እንመለከት፡- (1) ከገላትያ እና ከትንሽ እስያ ቤተ ክርስቲያን 1ቆሮ 6:1-4 (2) ከሚቄዶንያና ከአኪያ አብያተ ክርስቲያናት 2ቆ 8-9 ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የገንዘብ ማሰባሰብ ልምምድ ያገኘው ከአንፆኪያ ካለች ቤተክርስቲያን ነበር ሐዋ 11:30 ሐዋ 12:25 ሐዋርያው ጳውሎስ የገንዘብን እርዳታ የሚያደርግበት ዓላማ በአይሁድና በአህዛብ መሃከል ያለውን መለያየት ለማስወገድ ነው።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ : ክርስቲያን እና ረሃብ**

I. *መግቢያ*
*ሀ. ረሃብ የሐጢያት ውድቀት ውጤት መሆኑን መገንዘብ አለብን፤*
*ለ.* ከበርካታ ችግሮች ማሃከል ረሃብ የሰውን ዘር ማንነት የሚጎዳ መሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን በግብርና ስራ ይባርክ ነበር ነገር ግን በተቀራኒው ሲቀጣ እርሻቸው መብልን እንዳይሰጡ ያዝዝ ነበር ዘዳ 27-28 ያንብቡ። ይህ በአዲስ ኪዳን ላለን አማኞች በቀጠታ ትርጉም ላይኖረው ይችላል፤ ማቴ 5:45 በማንበብ ተጨለማ ግልጽ ትንተና አግኝ።
*ሐ.* የረሃብ አይነተኛ ምሳሌዎቹ የሰው ስስታምነት እና እራስ ወዳድነቱ ነው። ረሃብ ለምግብ ብቻ ሳይሆን ሰው

በተፈጥሮ የውስጥ ሰውነቱ ይራባል፡፡ እግዚአብሔር ቸርነቱን ለሰዎች የሚገልጽበት መንገድ አንዱ በረሃብ ፈንታ በረከቱን ሲሰጥ ነው፡፡

II. ሁለቱ ኪዳኖች ስለ ረሃብ የሚሉትን እመልከት

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1.በሙሴ ዘመን

ሀ. ለእግ/ር ከሚሰጡ ስጦታዎች አንዱ ለደሃ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡ ዘዳ 14:28-29

ለ. የብሉይ ኪዳን ህግ ለድሆች ትኩረት እንዲሰጥ ያዛል (ዘፀ 23:11, ለሌዋ 19:10, ዘሌዋ 23:22, ዘዳ 24:19-22)::

ሐ. የብሉይ ኪዳን ህግ ለድሆች በዋጋ ቅናሽ የሆነ መስዋት ወደ መቅደስ እንዲያመጡ ይፈቅዳል (ዘሌዋ 14: 21)::

መ. የቀደሙት እስራኤላውያን ስለ ድሆች የጠለቀ ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ (ዘዳ 15:7-11፣ አዮ 29:16፣ አዮ 30: 25፣ አዮ 31-10-23)

2. የቃሉ ፍቺ በስነ ግጥም መጽሐፍቶች እንመልከት

ሀ. በመንፈሳዊው ዓለም ደሆችን የሚረዱ ልዩ ስፍራ አላቸው፡፡ መዝ 41:1

ለ. ድሆችን መርዳት እግዚአብሔርን እንደመርዳት ይቆጠራል፡፡ ምሳ 14:31፣ ምሳ 17:5፣ ምሳ 19:17)፡፡

3. የቃሉ ፊቺ በነብያት መጽሐፎች

ሀ. በእግ/ር ህግ መሃል አንዱና ዋነኛው የድሆችን መብት ማስጠበቅ የሚል ነው (ኢሳ 58:6-7፣ ሚክ 6:8)

ለ. ወንጌል ለድሆች ይሰበካል፤

ሐ. የእግ/ር ነብያቶች በህዝብ መሃከል ያለን አድልዎ ይቃወማሉ (አርም. 2:6-8፣ አርም. 5:10-13)

ለ. አዲስ ኪዳን

1. በወንጌላት መጽሀፍት

ሀ. ድሆችን መርዳት አለብን (ማር 10:21፣ ሉቃ 3:11)

ለ. እያንዳንዱ ክርስቲያን ባልንጀራውን መውደድ አለበት እኛ ሌሎችን መርዳታች ኢየሱስን እንደ ማገልገል ነው፤ ማቴ 25:31-46

ሐ. የማርቆ 14:7 ሃሳብ በብዙዎ ዘንድ የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቶት ይታያል ነገር ግን ኢየሱስ ለድሆች ያለውን ስፍራ የሚያሳይ ነው፡፡

መ. የእግዚአብሔርን መልእክት ድሆችን እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ (ኢሳ 61:1-2፣ ሉቃ 4:18፣ ሉቃ 7: 22፣ ሉቃ 14:21)

2. ሐዋርያው ጳውሎስ ረሃብ የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፤

ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስ በአንፆኪያ በነበረ ጊዜ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ድሆች ገንዘብ በማሰባሰብ ፍቅሩን ገልጧል፡፡ (ሮማ 15:26፣ 1ቆሮ 16:1፣ 2ቆሮ 8:4,6,19፣ 18-ገላ 2)

ለ. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ፀጋ፣ እምነት እና ስራ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ አስተምሯል ኤፌ 2:8-10

3. መጽሀፈ ያዕቆብ (የአዲስ ኪዳን የስነ ግጥም መጽሀፍ)

ሀ. በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት የሚገለጠው ለወዳጆቻችን ባለን ፍቅር ነው ያዕቆ 2:14-17

ለ. እምነት ያለ ስራ የሞተ ነው፡፡ ኢሳ 61:1-2

4. የቃሉ ፍቺ በዮሐንስ መጽሐፋት

ሀ. እንደ 1ዮሐንስ መጽሐፍ የክርስትና ኑሮ በእምነት የተቀየረ ኑሮ እና ሌሎችን የሚያገለግል ሕይወት እንደሆነ ይናገራል (1ዮሐ 3:17-18)፡፡

III. ***ማጠቃለያ***

ሀ. የፍጥረት መከራ የሃጢያት ውድቀት ውጤት ነው፡፡ ለረሃብ መንስኤ የሚሆኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡

1. የስነ ምግባር ብልሹነት ምሳ 19:15
2. የእግዚአብሔር ቅጣት ዘዳ 27-28
3. መንፈሳዊ አገልግሎት 2 ቆሮ 11:27
4. የባህል ተጽኖ
5. የተፈጥሮ አደጋዎች ድርቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወዘተ)

ለ. እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ይወዳል፡፡ እግዚአብሔር የራሱን ፍጥረት በእኩል ዓይን ይመለከታል፡፡

ሐ. እግዚአብሔር ለመረጠው ሕዝቡ ለጥያቄአቸው ምላሽን ይሰጣል (ለስጋ እና ለመንፈሳዊው)

1. በግል ለሚጠየቁ ጥያቄዎች እግዚአብሔር መልስ አለው
2. በሃገርና በቤተክርስቲያን ደረጃ ለሚለመኑ ፀሎቶች እግዚአብሔር ምላሽ አለው
3. ስለ ሃገር ፖለቲካ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች እግዚአብሔር መፍትሔ አለው፡፡

መ. የራሳችንን ባህልና የግል ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ቃል መመርመር ተገቢ ነው (2 ቆሮ 8-9)፡፡

ሠ. አቅም ላነሳቸው ሁሉ አይናችንን፣ ጆሮአችንንና፣ ልባችንን እና እጃችንን ለእርዳታ ልንከፋት ይገባናል፡፡

ረ. ሰዎችን ስንረዳቸው የታላቁ ተልእኮ ዋና ተግባር መሆኑን በማወቅ መሆን አለበት፡፡
(እርዳታው በስጋዊውም በመንፈሳዊውም መሆን አለበት፡፡) ማቴ 28:18-20

15፡27 "ከሆኑ" ፀሐፊው ግምቱ ትክክል እንደሆነ ለመግለጽ ይህንን ቃል ተጠቅሟል፡፡ አውዱን መመልከት ይረዳል፡፡ ይህ ማለት አህዛብ ከአይሁድ መንፈሳዊ ነገርን ተጠቃሚ ከሆኑ በኢየሩሳሌም ያላቸውን ቤተ ክርስቲያን መርዳታቸው ተገቢ ይሆናል፡፡

15፡28

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ይህንን ካሳመርኩ በኋላ ማዕተሜን በፍሬአቸው ላይ አኖራለሁ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ይህንን በስራሁ ጊዜ ፍሬውን አትንላችኂለሁ"** |
| **አየመመቅ** | **"ይህንን በማጠናቀቅ ጊዜ የተሰበሰበውን እሰጣቸዋለሁ"** |
| **አእቅ** | **"ይህንን ተግባር ሳጠናቅቅ ለእነርሱ የተሰበሰበውን ገንዘብ እሰጣቸዋለሁ"** |
| **ኢመቅ** | **"ለእነርሱ የተሰበሰበውን ገንዘብ በማስረጃ አስረክባቸዋለሁ"** |

ይህ በጊዜው የነበረውን በማዕተም ታሽጎ ሽልማትን የመስጠት ባህልን የሚያመለክት ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልክ ገንዘብ ይቀበልና ይሰጥ እንደነበር ጠቀሽ ሃሳብ ነው፡፡ ይህም ታአማኒነትን ለመፍጠር የሚጠቅም አይነተኛ መንገድ ነው፡፡

15፡29 የታደገመ ቃል ነው ሮሜ 15፡14 ይመልከቱ

> ሮሜ 15፡30-33
> **ወንድሞች ሆይ ስለ እናንተ ወደ እግዚአብሔር እየፀለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንደ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃደ በደስታ ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋ እንዳርፍ በይሁዳ ካሉት ከማይታዘዙ እድን ዘንድ ለኢየሩሌምም ያለኝ አገልግሎቴ ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ ፀልዩ፡፡ የሰላምም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡**

15፡30 "**እየፀለያቹ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ**" ይህ በግሪኩ  ጽሁፍ ሁለት ጥምር ቃል ነው "ሳን" ማለት "በህብረት" አጎናዘሚያ" ማለት "መታገል፣ መዋጋት" ማለት ነው፤ ይህንን በሮሜ 12፡1 እና በጌተ ሰማኒ ኢየሱስ የታገለውን ትግል ለመግለጽም ያገለግላል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎቱ ይበርታ ዘንድ ከልቡ የሌሎችን ፀሎት የፈለገበት ቦታ ነው፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቧቸው፤ 2ቆሮ 1፡11፣ ኤፌ 6፡18-20፣ ቆላ 4፡3፣ 1ተሰሎ 5፡25፣ 2 ተሰሎ 3፡1)፡፡

15፡30-33 ሐዋርያው ጳውሎስ የሌሎችን ፀሎት አጥብቆ የፈለገበት ምክንያቶቹ ሶስት ናቸው፡፡ (1) የመጀመሪያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በሃጢያተኞች እጅ እንደሚሰጥ ስለተረዳ ነበር፡፡ ሐዋ 20፡22-23 (2) ሁለተኛው ከአህዛብ ክርስቲያኖች የተላከውን የገንዘብ ስጦታ በኢየሩሳሌም ያለች ቤተክርስቲያን ያለ አንዳች ቅሬታ እንድትቀበለው ነው፡፡ (3) ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ እስፔን በሚያደርገው ጉዞው በሮምም ለሚኖረው ቆይታው የሌሎችን ፀሎት መፈለጉን እንረዳለን፡፡

15፡31 "**የማይታዘዙ**" እነዚህ አንዳንድ የጳውሎስን አገልግሎት የማይቀበሉ ሃይማኖተኞች አይሁዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ የማይታዘዙ ናቸው በማለት በከንቱ ስማቸውን አላጎደፈም (ሮሜ 11፡30፣ 31)፡፡

15፡32 ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት የፀሎት ርዕሶችን አቅርቧል፡፡ (1) ጳውሎስ በልብ ደስታ ወደ እነርሱ እንደሚወጣ ፈልጓል፤ (2) ጳውሎስ ከማይቀበሉት ጋር በሚኖረው ጊዜ የእረፍት ጊዜ እንዲኖረው ምኞቱን ተናግሯል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በተለምዶ ከመንፈሳዊ ሰዎች ጋር በመሆን እረፍት የሚፈልግ ሰው ነበር፡፡ ተከታዮቹን ጥቅሶች ለተጨማሪ ግንዛቤ እናንብብ (2ቆሮ 4፡7-12፣ 2ቆሮ 6፡3-10፣ 2ቆሮ 11፡23-33)፡፡ ነገር ግን ይህ ሐዋርያው በእረፍት ፋንታ በርካታ ስቃይና እስር የገጠመው ስለመሆኑ ህይወቱ ህያው ምስክር ነው፡፡

15፡33 "**የሠላም አምላክ**" ይህ አስደናቂ የእግዚአብሔር ስያሜ ነው (ሮሜ 6፡20፣ 2ቆሮ 13፡11፣ ፊሊ 4፡9፣ 1ተሰሎ 5፡ 23፣ 2ተሰሎ 3፡16፣ ዕብ 13፡20)፡፡

▣ "**አሜን**" "ይሁን" ማለት ነው፡፡ ሮሜ 1፡25 ይመልከቱ፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

እንግዲህ የመወያያ ጥያቄዎች የምዕራፉ ዋና አብይ ጉዳዮች ለማስታወስ የሚጠቅሙና ለማወያየት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው።

1. የብሉይ ኪዳን መጽሐፎች ለአዲስ ኪዳን መጽሐፍቶች በምን መንገድ ጠቃሚዎች ይሆናሉ። (ሮሜ 15:4-5፣ 1ቆሮ 10:6፣ 11)?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን ጥቅስ በሮሜ 15:19-22 ለምን ተጠቀመ? እናንተስ ከዚያ ምን ትማራላችሁ?
3. በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የአይሁድ እና የአህዛብ ክርስቲያኖች መከፋፈል የታየው በየትኛው ቦታ ላይ ነው?
4. በየትኛው የሮሜ መጽሐፍ ምዕራፍ ላይ የሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋሪያው አገልግሎቱ ላይ ጥያቄ ተነሳ?
5. ሐዋርያው ጳውሎስ ከአህዛብ ክርስቲያኖች በሮም ላለች ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያሰበሰበበት ምክንያት ምንድነው (15:15-29)?
6. የሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌል ስርጭት ዘዴ እንዴት ነበር? ለምን ወደ እስፔን መሄድ አስፈለገው?
7. ሐዋርያው ጳውሎስ የካህንን ስራ እየሰራ እንደሆነ መግለጹ ያስፈልጋል? ሮሜ 15:16  እስራኤል የካህናት መንግስት ናት ከሚለው ጋር አዛምዱት ዘፀ 19:15-6 ወይም ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ጋር 1ጴጥ 2,5,9 ራዕ 1:6
8. እግዚአብሔር የጳውሎስን የፀሎት ጥያቄ መልሷልን? ሮሜ 15:30-33

# ሮሜ 16

## በዘመናችን የምገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የአንቀጽ ክፍፍል

| ዩቢኤስ | አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | አየመመቅ | አእቅ | ኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰላምታ | | ሠላምታ | የግል ሰላምታ | ሰላምታና መልካም ምኞት |
| 16፡1-2 | 16፡1-2 | 16፡1-2 | 16፡1-2 | 16፡1-2 |
| | የሮሜ ቅዱሳንን ሰላምታ | | | |
| 16፡3-16 | 16፡3-16 | 16፡3-16 | 16፡3-5 | 16፡3-5 |
| | | | 16፡5-7 | |
| | | | 16፡8-11 | |
| | | | 16፡12-15 | |
| | | | 16፡16 | |
| | ችግር የሚፈጥሩትን አስወግዱ | | የመጨረሻው ጥፋት | ማስጠንቀቂና አንደኛ ማጠቃለያ |
| 16፡17-20 | 16፡17-20 | 16፡17-20 | 16፡17-20 | 16፡17-20 |
| | | | 16፡20-21 | |
| | | | | የመሰናበቻ ሰላምታና ሁለተኛ ማጠቃለያ |
| | | 16፡21 | | 16፡21-23 |
| | | 16፡22 | | |
| | | 16፡23 | | |
| ማመስገን | ከጳውሎስ ባልንጀሮች ሰላምታ ቡራኬ | | የማጠቃለያና የምስጋና ፀሎት | |
| 16፡25-27 | 16፡25-27 | 16፡25-27 | 16፡25-26 | |

**የንባብ ዑደት ሦስት (ገጽ 3 ይመልከቱ)**
*የጸሐፊውን የሀሳብ ፍሰት በአንቀጽ ደረጃ ለመመልከት ሞክሩ*

ይህ የጥናት መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው የራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመስጠት ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መሄድ አለብን፡፡ እንግዲህ አንተ፣ መጽሀፍ ቅዱስ እና መንፈስ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለብህም፡፡

በመጀመሪያ ምእራፉን በማንበብ ጭብጡን ለዩ በተለይ አውዱን በሙሉ በማንበብ የፀሀፊውን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ አውድ አንድ መልዕክት ብቻ እንደሚያስተላልፍ እንገንዘብ።

1. ምእራፍ አንድ
2. ምእራፍ ሁለት
3. ምእራፍ ሶስት
4. ወ.ዘ.ተ

**አጠቃላይ የአውድ እይታ ሮሜ 16፡1-27**

ሀ. በዚህ በመጨረሻው የሮሜ መፅሐፍ ላይ የተፃፍት ሴቶች ከጳውሎስ ጋር አብረው ወንጌልን የሚያገለግሎ ነበሩ እነርሱም ቁ.1 ፊበን፣ ቁ.3 ጳርስቅላ፣ ቁ.6 ማርያም፣ ቁ.7 ዩልያን፣ ቁ.2 ለእናቱ፣ ቁ.15 የዩልያ፣ እና ቁ.15 ለእህቱ በጳውሎስ ዘመን የሴቶች አገልግሎት ሰፊውን ቦታ እንደያዘ ከዚህ ክፋል መረዳት ይችላል። አማኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ፀጋን ያገኛሉ 1ቆሮ 12፡7,11፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችም ይሆናሉ ኤፊ 4፡12 መፅሐፋ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ የወንድን የበላይነት ብቻ አያስተምርም ነገር ግን ሴቶችም በእግዚአብሔር ስራ ውስጥ ያላቸውን ተግባር ያብራራል አዩኤ 2፡28፣ ሐዋ2፡16-21 በመሆኑም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጋጩ የሚወስሉ ሃሳቦችን እንዴት ማብራራት እንደምንችል ማወቅ አለብን 1ቆሮ 11፡4-5 ከ1ቆሮ 14፡34 አነፃፅሩ።

ለ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስሞች መገለጫ እንመልከት
1. የአይሁድ አማኞች ስሞች፡- አቂላ፣ ጳርስቅላ፣ ማርያም (መሪማ) አንዲራኒቆን፣ ዩልያ
2. የሮማውያን የመሳፍንት ቤተሰብ ስሞች፡- ድርስቅላ፣ ጳልያጠ፣ ኤጤሌ፣ ንርቀሱ፣ ፍሌጎን፣ ዩልያ።
3. የአይሁድ የመሳፍንት ቤተሰብ ስሞች፡- ሄሮዲ ዮና ፣ አርስጣባሉ

ሐ ሮሜ 16 የሚከፋፈለው በሦስት ክፍል ነው
1. ከቁ 1-16 ሐዋርያው ጳውሎስ የግል ስላምታውን ለበርካታ ሰዎች ማድረጉን ያሳያል።
2. ከቁ 17-20 ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ያስጠነቅቃቸዋል
3. ከቁ. 21-23 በቆሮንቶስ ያሉ ሚሲዮናዊያን ስላምታ የላኩበት ክፍል ነው።

መ. በዚህ ምዕራፍ ላይ ያሉትን የስም ዝርዝሮች ለማጥናት ከገፅ 266-284 ያንብቡ።

ሠ. የሮሜ መፅሐፍ የሚጠናቀቀው በየትኛው ምዕራፍ እንደሆነ አልተረጋገጠም ምክንያቱም በዕብራይስቱ ፅሑፋ ላይ በምዕራፋ 14 እና 15 ላይ የመዝጊያ የስላምታ ፅሑፍ እና በአስራ ስድስተኛው ላይ የመዝጊያ ስላምታ ይነበባል። ነገር ግን የጥንቲቱ ቤተክርስቲያን የሮሜን መፅሐፋ ማጠቃለይ ስላምታ አድርጋ የምትወስደው ሮሜ 16፡25-27 ነው። ለተጨማሪ ግንዛቤ Bruce M.metzger,A textual commentary on the Greek new testament page 533-536

**የቃል እና የጥምር ቃል (የሐረግ) ጥናት**

> **ሮሜ 16፡1-2**
> **በክንክራኦስ ባለች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የምትሆን እህታችንን ፊቤንን አደራብያችኊለሁ በቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሉአት እርስዎ ለብዙዎች በጌታ ተቀበሉአት እርስዎ ለብዙዎች ለእኔም ለራሴ ደጋፊ ነበረችና ከእናንተም በምትፈልገው በማናቸወም ነገር እርድአት።**

16፡1 "አደራ ብያችኊለሁ" ሐዋርያው ጳውሎስ ለዲያቆን ፊቤን የድጋፋ ደብዳቤ መፅሐፍን ያመለክታል። ሌሎችም በርካታ የደብዳቤ መግቢያ አፃፎችንና የድጋፋ ደጋዳቤዎችን ዓይነት በአዲስ ኪዳን መመልከት እንችላለን። ሐዋ 18፡27, 1ቆሮ 16፡ 3 2ቆሮ 3፡1, 2ቆሮ 8፡18 ፡24 እና ፊሊ 2፡19-30)

▣ "ፊቤን" የስሟ ትርጉም "የሚያበራ" ወይም "የሚያንፀባርቅ" ማለት ነው

▣
አአመመቅ,አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም "የቤተክርስቲያን አገልጋይ ለምትሆን"

| | |
|---|---|
| አየመመቅ | "የቤተክርስቲያን ዲያቆን" |
| አእቅ | "ቤተክርስቲያን ለምታገለግል" |
| ኢመቅ | "በጽቁና ቤተክርስቲያንን" |

ዲያቆን የሚለው "ዲያኮናስ" በነጠላ የሴት ፃታ የተቀመጠ ቃል ነው። የግሪኩ ቃል ሲተረጎም "አገልጋይ" የሚል ትርጉም ይሰጣል። ቃሉ ለክርስቶስ ለመገለጫ አገልግሏል (ሮሜ 15፡8 እና ኤፌ 3፡7 ቆላ 1፡23, 25)።

የዲያቆናት አገልግሎት በስፋት የታወቀው በአዲስ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ከተፃፈ በኂላ በነበረችዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር። የመብላት ሴቶች ድርሻ በቤተክርስቲን ከፍተኛ ነበር 1ጢሞ 3፡11 1ጢሞ 5 MR Vincent word studies, vo 12= 8p 752 and 1196 በዚህ በፅሐፋ ላይ እንደተብራራው በተለይ በሁለተኛ መጨረሻ እና በሦስተኛው መጀመሪያ ምዕተ ዓመት ላይ የተደነገገው የሐዋርያት ህገ ደንብ የሴቶችን ስራ እና በቤተክርስቲያን ሴቶች ያላቸውን እገዛ ለይቶ ያስቀመጠ ህግ ነበር።

1. ዲያቆናት (የሴት ዲያቆናት)
2. መበላቶች (1ጢሞ 3፡11 1ጢሞ 5፡9-10)
3. ደናግልት (ሐዋ 21፡9 እና 1ቆሮ 7፡34)

የሴቶች ስራዎች የሚያካትቷቸው፦

1. የታመሙትን መንከባከብ
2. በስደት ሰውነታቸው ለተጎሳቀለ እርዳታ መስጠት።
3. በእምነታቸው ምክንያት በእስር ቤት ያሉትን መጎብኘት።
4. አዳዲስ አማኞች ማስተማር
5. በቅዱስ ጥምቀት ጊዜ ሴት ተጠማቂዎች መንከባከብ።
6. ሴት የቤተክርስቲያን አባሎችን መንከባከብ መጎብኘት።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ ሴቶች በመፅሐፋ ቅዱስ ውስጥ ያላቸው ድርሻ**

I. በብሉይ ኪዳን

ሀ. በብሉይ ኪዳን ባህል ሴቶች ዕቃ ተደርገው ይታዩ ነበር።

1. ሴቶች ከእቃ ዝርዝር መሃከል ተደርገዋል (ዘፀ 21፡17)
2. የሴት ልጅ ባርነት እንክብካቤ በብሉይ ኪዳን (ዘፀ 21፡7-11)
3. የሴት ልጅ መሐላ በማዕበረሰቡ ኃላፊነት ባለው ወንድ ይወሰናል (ዘኃ 30)
4. ሴቶች የጦር ምርኮኞች ይሆናሉ ዘዳ 20፡10-14, 21፡10-14)

ለ. ሴቶችና ወንዶች የጋራ ጥቅም አላቸው

1. ወንድና ሴት በእግ/ር አምሳል ተፈጥረዋለው። (ዘፋ 1፡26-27)
2. አባትህን እና እናትህን አክብር። (ዘፀ 20፡12,ዘዳ 5፡16)
3. አባትህን እና እናትህን ፍራ። (ዘሌዎ 19፡3, 20፡9)
4. ወንዶች እና ሴቶች ለእግዚአብሔር  የተለዩ ይሆናሉ። (ዘኃ 6፡1-2)
5. ሴት ልጆች የመውረስ መብት ተስቷቸዋል። (ዘኃ 27፡1-11)
6. ሴቶች የቃል ኪዳን ሕዝብ ወገን ናቸው (ዘዳግ 29፡10-12)
7. የአባትን እና የእናትን ምክር በእኩል መስማት። (ምሳ 1፡8, 6፡20)
8. የኤማን ሴት ልጆች በዝማሬ በመቅደሱ ያገለግሉ ነበር (1ዜና 25፡5-6)
9. ወንዶችና ሴት ልጆች በመጨረሻው ዘመን ትንቢት ይናገራሉ። (አዩኤ 2፡28-29)

ሐ. የሴቶችን ሚና በመሪነት አገልግሎት

1. የሙሴ እህት ማርያም ነብይ ተብላለች። (ዘፀ 15፡20-21)
2. የመገናኛውን ድንኳን እንዲስሩ ለሴቶች ኃላፊነት ተስቷል (ዘፀ 35፡25-26)
3. ዲቦራ ነብይ ነበረች (መሳ4፡4) መሪ ሆናለች መሳ 4፡4-5
4. ሕልዳና ነብይ ነበረች። (2 ነገ 22፡14, 2ዜና 34፡22-27)
5. እግ/ር የምትፈራዋ ሩት የዳዊት አያት ነች።
6. ንግስት አስቴር በባቢሎን ሕዝቧን አገልግላለች።

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. በአይሁድና በግሪኩ ሮማ ባህል ውስጥ ሴቶች እንደሁለተኛ ዜጋ ስለነበር መብቶቻቸውም እንዲሁ ውስን ነበሩ።

ለ. ሴቶች በአመራር ስልጣን የሚኖራቸው ሚና ምንነው

1. ኤልሳቤጥ እና ማርያም የእግዚአብሔር ዓላማ ማስፈፀሚ ነበሩ። (ሉቃ 1-2)
2. ሃና በቤመቅደስ የምታገለግል ሴት ነበረች። (ሉቃ 2፡36)
3. ሊዲያ አማኝና በቤቷ ያለውን ቤተክርስቲያን የምትመራ ነበረች (ሐዋ 16፡14-40)
4. ፊሊጾስ አራት በትንቢት ስጦታ የሚያገለግሉ ሴት ልጆች ነበሩት (ሐዋ 21፡8)
5. ፊበን በክንክራኦንስ ባለች ቤተክርስቲያን ዲያቆን ነበረች። (ሮሜ 16፡1)

6. ጶርስቅላ (አቂላ) የጳውሎስ አጋር የወንጌል ሰራተኞች ነበሩ፡፡ (ሐዋ 18፡26 ሮሜ 16፡3)
7. ማርያም፣ ፕሮሰምና፣ ጢሮፊምሳ፣ ዩልያ፣ ሰኒርያ እህት፣ እነዚህ እና ሌሎችም ከጳውሎስ ጋር የወንጌል አጋር ሠራተኞች ነበሩ ሮሜ 16፡6-16
8. ዩልያ (kኢ መ ቅ ) ሐዋርያ እንደሆነች ይናገራል፡፡ (ሮሜ 16፡7)
9. ኤዎድያን፣ ሲንጤኮንን ከጳውሎስ ጋር ወንጌልን የሚያገለግሉ ነበሩ (ፊሊ 4፡2-3)

III. አማኞች የመፅሐፋ ቅዱስን ምሳሌዎች እንዴት ከአሁኑ ዘመን ጋር ማዛመድ አለባቸው?

ሀ. የቀድሞውን ታሪክና ባህልና በመመልከት የእግ/ርን ቃል ከአሁኑ ዘመን እውነት ጋር እንዴት ማዛመድ ይቻላል?

1. የፀሐፊውን የመጀመሪያ የውስጥ ሃሳብ ከፅሑፋ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡
2. ፅሑፋ የተዛፈበትን ዘመን ታሪክ ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡
   ሀ. ስርዓቱን ማወቅ ሐዋ 15, ገላት 3
   ለ. ስለ አይሁዳዊነት ማወቅ
   ሐ. የሐዋርያው ጳውሎስ ታሪክ ጠቃሽ ዓረፋተ ነገሮች
      1. የሮማውያን ሕግ (1ቆሮ 6)
      2. ባሪያ መሆን (1ቆሮ 7፡20-24)
      3. ጃንደርባነት (1ቆሮ 7፡1-35)
      4. ድንግልና (1ቆሮ 7፡36-38)
      5. ለጣኦት የሚቀረብ መስዋት (1ቆሮ 10፡23-33
      6. በጌታ እራት ስርዓት ላይ የሚያዩ አላስፈላጊ ግድፈቶች (1ቆሮ 11)
3. እግዚአብሔር በአንድ በተወሰነ ባህል እራሱን መግለጡን መረዳት አስፈልጊ ነው፡፡ ፅሑፍ የተፃፈበትን ዓላማ በአጠቃላይ ልንወስደው እንችላለን፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን ታሪካዊ ክርስታት ትኩረት መስጠት ላይኖርብን ይችላል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተፃፈውን ከአንድ ባህል ህዝብ እና በተወሰነ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ አለብን፡ ፡

ለ. መፅሐፍ ቅዱስ ሲተረጎም በፀሐፊው ትክክለኛ ሃሳብ ላይ መመስረት መሆን አለበት፡፡ ፀሐፊውን ለነማን ምን እያለ ነበር? ይህ ጥያቄ መፅሐፋ ቅድስን ለመተርጎም መሠረታዊ ጥያቂ መሆኑን መገንዘብ አለብን በቀጣይም ለእኛ የሚሆነውን ወደ እኛ ሁኔታ መተርጎም ያስፈልጋል፡፡ እንግዲህ መፅሐፋ ቅዱስን ስንተረጉም የሴቶችን አገልግሎት በተለይ ከመሪነት አገልግሎታቸው ይልቅ የድቁና አገልግሎታቸውን በማጉላት ነገር ግን ዲያቆናት በጊዜው መሪዎች አድረገን ልነተረጎም እንችላለን፡፡ ሮሜ 16፡1 ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 14፡34-35 እና በ1ጢሞ 2፡9-15 ሴቶች በማዕበር እንዳይናገሩ አዟል ይህንን ቃል ለእኛ እንዴት እንተረጉመዋለን፡፡ ይሄ በጳውሎስ ባህል እና ጊዜ የተፃፈ በማለት ብቻ መናቅ አይገባም የመፅሐፋ ቅዱስን ስልጣን መቃወም አስፈላጊ አይደለም፡፡

ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 16 ላይ የሴቶችን መሪነት ጠቅሶ እናገኛለን፡፡ በ1ቆሮ 11-14 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ማዕበር አምልኮ በተገቢው መንገድ ፅፏል፡፡ በ1ቆሮ 11፡5 ላይ ሴቶች ፀጉራቸውን ሸፈነው መስበክ እና መፀለይ እንደሚችሉ ተጠቅሷል በሉላ በኩል ደግሞ የሴት ዲያቆናት መኖራቸው ተጠቅሷል (ሮሜ 16፡1) እና ትንቢት የሚተነብይ ነበሩ (ሐዋ 21፡9) እንግዲህ ይህ የተለያየ ዝርዝር ሃሳብ በኤልሶንና በቆሮንቶስ የሴቶች አገልግሎት ውስጥ ለምን ሆነ የሚል ጥያቄ አንድናነሣ ነፃነት ይሰጠናል፡፡ በሁለቱም አብያተ ክርስትያናት የሴቶች ነፃነት ወንጌልን በማስፋት አንፃር ችግር እንዳለው እንመለከታለን ነገር ግን ወንጌል እንዲሰፋ የሴቶችን ነፃነት መገደብ እንዳለባቸው በራሳቸው አውድ እና ለተለየ ችግራቸው የተጠቀሙበት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

የእኛ ዘመን የጳውሎስ ዘመን ተቃራኒ መሆኑ ግልፅ ነው በተቃራኒው ሴቶች ወንጌልን ባይናገሩ ወንጌል በፍጥነት የመስፋቱ ፍጥነት ሊገደብ ይችላል ሴቶች ለወንጌል አስፈላጊዎች ናቸውና፡፡ የማዕበር አምልኮ ዓላማው ወንጌልን ላልዳኑ ለማድረስ እና ደቀ መዝሙርትን ለማፍራት ነው፡፡ እግ/ር መሪ በሚሆኑ ሴት እህቶቻችን ይደስታልን? መፅሐፋ ቅዱስ በጥቅሉ የሚደግፋ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የኔ የስነ መለኮት ትምህርት በጳውሎስ ትምዕርት ላይ መሠረት ያደረገ ነው በመሆኑም በአሁኑ ዘመን ባለው የሴቶች የበላይነት በሚለው አለማቀፋዊ እንቅስቃሴ (feminism) የጳውሎስ ትምህርት አይቀየርም ነገር ግን ቤተክርስቲያን ለባሪያንግድ፣ ለዘረኝነት፣ ለጠበኝነት በፃታ ግንኙነት የወንድ የበላይነት ማስወገድ የሚሉና ሌሎችንም ርዕስ ጉዳዮች በአሁኑ ጊዜ መረዳቱን እየተቀበለች ነው፡፡ በተመሳሳይ የሴቶችንም ድርሻ በቤተክርስቲያን ሙሉ መረዳት እንደምናገኝ የያዝነው መንገድ አመላካች ነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ባሪያ የለ ጨዋ፣ ወንድ ያለ ሴት ነፃ አድርጓናል፡፡ ነገር ግን የባህል ተገዥ በመሆን ሰዎች ለዘመናት ተስቃይተዋል፡፡

የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በፀጋ ስታጠ የተባረከች ቤተክርስቲያን በትሆንም ነገር ግን በርካታ ችግሮችም የነበሩበት ቤተክርስቲያን ነበረች ሴቶች በእነዚህ ሁኔታ ውስጥ አንድ የቤተክርስቲያኒቱ አካል ነበሩ በኤፊሶንም ሃሰተኛ አስተማሪዎች ሴቶችን የሃስት ትምዕርታቸውን ለማስፋፋት ይተቀሙባቸው ነበር (1 እና 2 ጢሞ)፡፡

▣ **"ቤተክርስቲያን" ቀጥሎ ያለውን ተመለከቱ፡፡**

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ: "ቤተክርስቲያን" (ኤክሌሺያ)**
ኤክሌሺያ በግሪኩ የሁለት ጥምር ቃል ነው "መውጣት" እና "መጣራት" በመሆኑም ቃሉ ሲተረጎም "በመለኮት ተጠርቶ የመጣ" ማለት ነው። የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቃል የማያምኑ ከሚባሉት የወሰደችው ነው። ሐዋ 19:32,39,41) በግሪኩ ፅሑፉ ላይ ይህንን ቃል የእስራኤል "ማዕበር ተብሏል (ዘኃ 16:3 ዘኃ 20:4) የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ መሰባሰብ ነው። (አይሁድ የብሉይ ኪዳን አባቶች ቀጣይ ትውልድ መሆናቸውንም ለማመልከት ይህንን ቃል ይጠቀሙበታል። እርሱ አዲሲቱ እስራኤል ናቸው። (ሮሜ 2:28-29, ገላ 6:16, 1ጴጥ 2:5,9,ራዕ1:6) የእግዚአብሔር አለም አቀፋዊ ዕቅድ ማስፈፀሚያ 1ዘፋ 3:15,ዘፋ 12:3, ዘፀ 19:5-6 ማቴ 28:18-20 ሉቃ 24: 47,ሐዋ 1:8)
ቤተክርስቲያን በወንጌላትና በሐዋርያት ስራ መፅሐፉ የተለያዩ ትርጉሞች አለው
1. በማያምኑ ሰዎች ከተማ የተደረገ ስብሰባ ሐዋ 19:32,39,41
2. በክርስቶስ የዳኑ በአለም ያሉትን ሁሉ ያመለክታል ማቴ 16:18 እና ኤፌሶንን አንብቡ
3. የክርስቶስ አማኞች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉት ስብሰባ ማቴ 18:17 ሐዋ 5:11 (በኢየሩሳሌም የነበረች ቤ/ክርስቲያን)
4. የእስራኤል ሕዝብ ስብስባ በአጠቃላይ ሐዋ 7:38 (የእስቲፋኖስን ስብከት እናንብብ)
5. በየአገሩ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተክርስቲያን ተብለዋል ሐዋ 8:3

▣ "ክንክራኦስ" ቆሮንቶስ ካላት ሁለት የባህር በር አንዱ ነው። ይህ የባህር በር የሚገኝ በስተምስራቅ ነው። ሐዋ 18:18

▣ 16:2 "ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሉአት" ማለት እንደ እንግዳ በአግባቡ ክርስቲያኖችን መቀበል እንዳለብን ያስገነዝበናል። ፊሊ. 2:29 ሐዋርያው ጳውሎስ ይህችን ክርስቲያን አገልጋይ እህት እንደ እርሱ እሷን እንዲቀበሏት እና በሚያስፈልጋት እንደረዷት ይጠይቃል።

▣ "ቅዱሳን" ፍቺው የተቀደሰ" ነው ቅዱሳን የሚለው ቃል ሁለት ነገሮችን የሚገልፅ ነው የመጀመሪያው አማኞች በክርስቶስ ስላለቸው ስልጣን ያመልክታል ሁለተኛው በክርስቶስ የተገኘውን አዲሱን የቅዱሳን ህይወት የሚያመለክት ነው። ቅዱሳን የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ስሞችን የሚያመለክት ነው። ነገር ግን በፊሊ 4:21 ላይ ብቻ በነጠላ ቁጥር ስም ተሰቶት እንመለከታለን ይህ የሚያመለክተው ክርስቲያን መሆን ቤተሰብ፣ አካል ወይም ከሌላው ጋር አንድ መሆንን የሚያመለክት ነው ነገር ግን የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን በተለይ በምዕራብ ዓለም የወንድሞችንና የእዕቶችን ሕብረት ዝቅ ያለ ዋጋ በመስጠት እውነተኛውን የወንጌልን ቃል መተላለፏ አግባብነት የሌለው መሆኑን ማወቅ አለብን።

▣ "ከእናንተ በምትፈልገው በማናቸውም ነገር እርዱአት" ለሁለት ነገር ጥሪ የተደረገበት ቦታ ነው የመጀመሪያው "ለመርዳት መዘጋጀትን" ያመለክታል። ሁለተኛው ፍላጎቷን አሟሉላት" የሚል መልዕክት ይሰጣል። 2ቆሮ 3:1
በግብፅ ትርጉሙ ለወንጌል አገልጋዮች እርዳታ መስጠት እንዳለበት የሚያመለክት የመፅሐፉ ቅዱስ ክፍል ነው። ይህን እርዳታ ለመቀበል የጥንቷ ቤተክርስቲያን ለአገልጋዩ የማረጋገጫ ደብዳቤ እንዲፃፍለት ማድረጓ ለታአማነነት የሚረዳ እንደነበር ከታሪክ መገንዘብ ይችላል።

▣

| | |
|---|---|
| አአመመቅ,አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም | "የብዙዎች ረዳት" |
| አየመመቅ | "ለብዙዎች ጥቅም ስታለች |
| አእቅ | "እሷ ራሷ የብዙዎች ባልንጀራ ነበረች" |
| ኢ መ ቅ | "የብዙ ሰዎች ተንከባካቢ ነበረች" |

ይህ እርዳታ በገንዘብ እና በቁሳቁስ መሆኑ የቃሉ ፈቺና የቃሉ አመሠራረት ያመለክታል። ፊበን ወደ ሮም በመሄድ እና ብዙዎችን መርዳቷ በሁሉ ዘንድ የሚያስመሠግናት እና ለብዙዎች ለምሳሌነት የምትጠቀስበት መልካም ስራ ሆኖአል።

16:3-16
**በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጳርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ እነርሱ ስለ ነፋሴ ነፋሳቸውን ለሞት አቅረቡ የአህዛም አብያት ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው። እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም በቤታቸውም ባለች ቤተክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ ከእስያ ለክርስቶስ በኩራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ስለ እናንተ ብዙ ለደከመች ለማርያም ሰላምታ አቅርቡልኝ በሐዋርያት መሃከል ስመ ጥሩዎች ለሆኑ ደግሞም ክርስታን በማመን ለቅደሙኝ አብረውኝም ለታሠሩ ለዘመዶቼ ለአንዲራቆንና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡልኝ በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ። በክርስቶስ መሆኑ ተፈትኖ ለተመሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ ከአርስጣባሉ ቤተ ሰዎች ላሉት ሰዎች ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ ለዘመዱ ለሄሮድዮና ሰላምታ አቅርቡልኝ ከንርቀሱ ቤተ ሰዎች በጌታ ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ በጌታ ሆነው ለሚደክሙ ለፕሮልማናና ለጢሮልምሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ በጌታ እጅግ**

**ለደከመች ለተወደደች ለጣርሲዳ ስላምታ አቅርቡልኝ በጌታ ሆኖ ለታወቀ ለሩፎን ለእኔና ለእርሱም እናት ስላምታ አቅርቡልኝ ለአስቀረጠንና ለአፋላሶንጳ ለሄሮሜንም ለጳጥሮስም ለሄር ማንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ወንድሞች ስላምታ አቅርቡልኝ። ለፍሌጎንና ለቶልያ ለኔርያና ለእህቱም ለአልንጠንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ቅዱሳን ሁሉ ስላምታ አቅርቡልኝ። በተቀደሰ አሳሳም እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ የክርስቶስ አብያት ክርስቲያናት ሁሉ ስላምታ ያቀርቡላችኋል።**

**16:3 ጵርስቃን አቂላ** ባለመድሃኒቱ ሉቃስ "ጵርስቅላ" ብሏታል። ይህች ሴት ስሟ ባልተለመደ ሁኔታ ከባሏ ጋር ተመሳሳይነት አለው (ሐዋ 18:18፣ 1ቆሮ 16:19፣ 2ጢሞ 4:19)።

ይህች ሴት የሮማውያን መሳፍንት ወገን እንደሆነችና ከዚህም ባለፈ በአጠገቧ ባሉ ሰዎች ሁሉ ላይ በጎ ተፅኖ የምታሳድር ጠንካራ ሴት በድንኳን መስፋን ስራ ተሰማርቶ በነበረ ጊዜ ጰርስቅላ እና አቂላ የስራ ባልደረቦቹ እና የወንጌል አጋሮቹ እንደነበሩ በሐዋርያት ስራ መፅሐፍ ላይ ተፅፎ እናገናለን።

**16:4 "ስለ ነፋሴ ነፋሳቸውን አቀረቡ"** መፅሐፋ ቅዱስ ጳውሎስ ለማለት የፈለገውን በዝርዝር አላስቀመጠም ነገር ግን ይህ ማለት የክርስቲያኖች በሌሎች በክፋ መፈለግ ነገር ግን አቂላና ጳርስቅላ ይህንን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች እንደሆኑ የሚገልፅ ዓረፍተ ነገር ነው።

▣ **"የአህዛብ አብያት ክርስቲያናት የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እነጂ እኔ ብቻ አይደለሁም"** ሐዋርያ ጳውሎስ እነዚህን ባለ ትዳሮች ስለ ባልንጀርነታቸውና ስለ እርዳታቸው ያመሠግናቸዋል ጳውሎስ በእነርሱ አገልግሎት ስለተማመነ አገልግሎታቸውን ለአህዛብ አብያተክርስቲያናት በመናገር የማረጋገጫ ምስጋና ለሁሉ ሲፅፋ እናነባለን። ሐዋ 18:24-28

**16:5 "ቤተክርስቲያን"** ይህ የሚያመለክተው በሕንፃውን ሳይሆን ሕዝቡን ነው። ቤተክርስቲያን የሚለው `"ተጠርቶ የወጣ" ማለት ነው። የብሉይ ኪዳኑ የግሪኩ ፅሑፋ ወደ ዕብራይስጡ ሲተርጎም "ካሃል" ማለት "ስብስብ" የሚል ትርጉም ይሰጣል። በመሆኑም በአዲስ ኪዳን የነበሩ እስራኤሎች ራሳቸውን የብሉይ ኪዳን አባቶች ተከታይ በማድረግ "የእስራኤል ማዕበር" በማለት ራሳቸውን ይጠሩ ነበር።

▣ **"በቤታቸው ላለች"** የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን በአብዛኛውን ጊዜ አምልኮ የምታደርገው በግለስቦች ቤት እንደነበር የሚጠቅስ ቃል ነው። የወንጌል ስርጭቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰሞች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ቢያመጣም ነገር ግን እስከ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት የቤተክርስቲያን ህንፃ አልተገነባም ነበር።

▣ **"አጤኔጦ"** የስሙ ትርጉም ምስጋና ማለት ነው።

▣ **"ለክርስቶስ በኩራት ለሆነው"** ይህ የእስቲፋኖስ ቤተስብ ስለሆነ በኩራት ተብሏል ለተጨማሪ ማብራሪያ ቀጣዩን ጥቅስ አንብቡ። 1ቆሮ 16:15

▣ **"ከእስያ"** ይህ የአለም ክፍል የሮማውያን ግዛት ነበር በአሁኑ ጊዜ በምዕራብ ቱርክ የሚገኘው አንድ ሦስተኛውን ክፍል ነው።

**16:6 "ለደከመች ለማርያም ስላምታ አቅርቡልኝ"** በዚህ ክፍል ላይ ስለምትገኛው ስለዚች ሴት ግልፅ የሆነ ትንታኒ የልም ነገር ግን ከሮም ቤተክርስቲያን የተላከች ሚስዮናዊ እንደምትሆን መለምት አለ። በርካታ ለእግዚአብሔር መንግስት ሕይወታቸውን የሰዋ ሰዎች አሉ እነዚህን ሁሉ እኛ ላናውቃቸው እንችላለን ነገር ግን በእግዚአብሔር የታወቁ ናቸው።

**16:7 "አብረውኝም ለታስሩ"** የመፅሐፋ ቅዱስ ምሁራን መታሰር የሚለውን በዚህ ቦታ የተጠቀሰውን ለመተንተን እርግጠኛ አይደሉም ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዕምነቱ መከራ ደርሶበታል የሚከተለውን የመፅሐፋ ቅዱስ ጥቅስ ሁሉንም በማንበብ አጠቃላይ መረዳት ማግኘት ይችላል (2ቆሮ 4:8-11፣ 2ቆሮ 6:4-10፣ 2ቆሮ 11:25-28)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊሊጲስዩስ በቂሳርያ፣ በሮም እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ስለ ወንጌል ተጋድሎ በሚያደርግበት ጊዜ እስር በርካታ ጊዜ ገጥሞታል። የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ። (ኤፌ መፅሐፋ በሙሉ፣ 1ቆሮ 15:32፣ 2ቆሮ 1:8)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከሐዋርያት መሃከል ለተመሠገኑት"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"ከሃሐርያት መሃከል ለታወቁቱ"** |
| **አየመመቅ** | **"ከሃሐርያት መሃከል ዋና ለሆኑት"** |
| **አእቅ** | **"ከሃሐርያት መሃከል እጅግ ታዋቂ ለሆኑት"** |
| **Nኢመቅ** | **"ለተመሰገኑት"** |

ሐዋርያት የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስራ ሁለቱን ወይም የተለያዩ የአገልጋዮችን ስብሰባ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁለቱ ከእነርሱ መሃከል የታወቁ ናቸው የሚከተሉትን ጥቅሶች ለማንበብ አውዶቹ ከሚሰጡት የተለያዩ ትርጉሞች ግንዛቤ እናገኛለን (ሐዋ 14:14,14,18:5፣ 1ቆሮ 4:9፣ ገላ 1:9፣ ፊሊ 2:25፣ 1ተስሎ 2:6፣ ኤፌ 4:11)።

▣ **"ክርስቶስን በማመን ለቀደሙኝ"** ሐዋርያው ጳውሎስ አማኝ ከመሆኑ በፊት ሌሎች በእምነት የቀደሙት እንዳሉ ለመጥቀስ የሚያመለክት አረፍተ ነገር ነው፡

16:8-16 በዚህ የመፅሐፋ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰዎች ምሁራን ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እና በጳውሎስ የተወደዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን መፅሐፋቶች ውስጥ የተወደደው ስራቸው አልተፃፈም ከተፃፋት ሰዎች መሃከል ሮማውያን የሚሰጡት የባሪያ ሰሞች፣ የሮም መሳፋንት ስሞችና እና አይሁዳውያን ስሞች ይገኙበታል፡፡ ይህ ስብሰባ የወንዶችና የሴቶች ነበር፡፡ ከእነዚህ መሃከል የታወቁ ባለጠጎችና ሰባኪዎች ይገኙበት ነበር ከሌሎች ሃገሮችም ከፔርሺያ የመጡ ሁሉ በአንድነት የክርስቶስን ቤት ክርስቲያን ያገለግሉ ነበር (ሮሜ 3:22,10:12፣ ኢዩ 2:28-32፣ ሐዋ 2:14-21፣ 1ቆሮ 12:11፣ ገላ 3:28፣ ቆላ 3:11)፡፡

16:8 **"ጳልያጦ"** ይህ እንደ "ዩልያ" እና "ጵርስቅላ" የታወቀ የሮማውያን ቤተሰብ ስያሜ ነው፡፡

**"በጌታ ለምወደው** ይህ ቃል እግዚአብሔ ልጁን ኢየሱስን ስለመውደዱ የተጠቀመበት ቃል ነው ማቴ 3:17 እና 17:5 በተጨማሪ ከኢሳያስ መፅሐፋ የተወሰደ ነው ማቴ 12:18, ኢሳ 42:1 ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ለአማኞች ፍቅሩን ለመግለፅ ተጠቅምበታል (ሮሜ 1:7, 16:8,9 1ቆሮ 4:14,17:15:58፣ ኤፌ 6:21፣ ፊሊ 2:12፣ ቆላ 4:7,9,14)፡፡

16:9 "ኢሩባኖ" የሰሙ ትርጉም "የከተማ ነዋሪ"

▣ **"በክርስቶስ"** የተደጋገመ ቃል ነው የሚያመለክተው አማኞች ሁሉ አንድ ቤተሰብ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

▣ **"ስንጣክ"** ይህ ያልተለመደ ስም ነው፡፡ የስሙ ትርጉም "ጆሮ" ማለት ነው የቅሪት አካል ተመራማሪዎች ይህ ስም የቄሳር ቤተሰብ ስም መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

16:10 "በክርስቶስ መሆኑ ተፈትኖ የተመሰገን" ይህ በእምነቱ በርካታ ፈተና የደረሰበት ነገር ግን የፀናን ሰው ለማመልከት አባቶች የሚጠቀሙበት ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

▣ **"ቤተሰዎች"** ይህ ቃል እንደ መፅሐፋ ቅዱስ ምሑራን ምልክታ በቤት ውስጥ ባሪያዎች የሆኑትን እንጂ የቤተሰብ አባል ማለት እንዳይደለ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ለተጨማሪ ግንዛቤ ሮሜ 16:11 መመልከት ይችላል፡፡

▣ **"ከአርስጣባሉ"** አንዳንድ የመፅሐፋ ቅዱስ ምሑራን ይህንን ስም ላይትፋት በማለት ይጠሩታል በተጨማሪም ይህ ሰው የሄሮድስ አግሪጳ ወንድም እንደሆነ ይገምታሉ፡፡ ይህ አግሪጳ ሐዋርያው ያዕቆብን የገደለው ነው (ሐዋ 12) ይህ የሚያሳየው ወንጌል ወደ ንጉስ ቤተሰቦች ዘልቆ እንደገባ ነው፡፡

16:11 **"ሄሮድዮና"** ይህ ሰው የሄሮድስ ቤተሰብ ባሪያ እንደሆነ ይገመታል፡፡

▣ "የንርቀሱ ቤተ ሰዎች" የንጉስ ነገስቱ የገላውዲዎች ታማኝ ባሪያ እንደነበር ይገመታል፡፡ ይህ እውነት ከሆነ ወንጌል በቤተመንግስት ውስጥ እንደገባ አመላካች ነው፡፡

16:12 **"ፕሮፊሞና"** የስሙ ትርጉም ለስላሳ ወይም ለስለሰ ያለ ማለት ነው፡፡

▣ **"ለጢሮልምሳ"** የሰሙ ትርጉም "ስልካካ ማለት ነው እነዚህ ሁለት መንትያ እህትሟማቶች መሆናቸው ይገመታል፡፡

▣ **"በስራ ለሚደክሙ"** በድካምና በጥረት የሚደክሙትን ለማሞገስ የሚጠቅም ቃል ነው፡፡

▣ **"ጠርሲዳ"** የአሦር አገር ሴት ነች፡፡

16:13 **"ሩፎ"** የስሙ ትርጉም "ቀይ" ወይም ቀይ, ቡናማ ወይም ብርቱካናማ የፀጉር ቀለም የተቀባች ሴት ማለት ነው፡፡ በሮማውያን ዘንድ ይህ ትርጉም የተለመደ ነው፡፡ (ማር 15:21)፡፡ በእርግጥ ይህ ሰው ፀጉሩን ቀለም መቀባቱን መፅሐፋ ቅዱስ አይናገርም ነገር ግን የስሙ ትርጉም እንደሚያመለክተው ፀጉሩን ቀለም የተቀባ ሰው መሆኑን የመፅሐፋ ቅዱስ ምሑራን ይናገራሉ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በጌታ ለተመረጠ ሰው"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም,አየመመቅ** | **"በጌታ ለተመረጠ"** |

አእቅ "በጌታ አገልግሎት ስመጥር የሆነ"
ኢመቅ "የተመረጠ የጌታ አገልጋይ"

ጥሬ ቃሉ ሲተርጎም የተመረጠ ማለት ነው የእግ/ርን ምርጫ ብቻ ሳይሆን የሰውንም የሕይወት ጎዳና የሚያመለክ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እናቱ ትንከባከበውና ታስብለት እንደነበር የሚጠቅስ የመፅሐፉ ቅዱስ ጥቅስ የሚገኘው በዚህ ክፍል ነው።

16:14 **"ሄርመስ"** ይሄ ስያሜ ለጣኦት የተሰጠ ስም ነበር የጣኦቱም ስም "መልካም ዕድልን የሚናገር ጣኦት በመባል ይታወቃል።

16:15 **"ቅዱሳን ሁሉ"** ሮሜ 1:7 ጋር ያመሳክሩ።

16:16 **"በተቀደሰ አሳሳም** ለዚህ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም አናገኝም ምክንያቱም ማን ማንን መሳም እንዳለበት እና መቼ እና የት መሆን እንዳለበት የሚያብራራ ማስረጃ የለም ነገር ግን ወንዶች ወንዶችን ሴቶች ደግሞ ሴቶችን ጉንጭ ለጉንጭ እንዲሳሳሙ ታዘው እንደነበር እናነባለን: አሳሳም በቤተክርስቲያን በዚያ ጊዜ የተዛባ መረዳትን በማያምኑ ሰዎች ዘንድ አምጥቶ ነበር።

> **ሮሜ** 16:17-20
> *ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰሞች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ እንዲህ ያሉ ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቁላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ። መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአልና እንግዲህ በእናንተ ደስ ይለኛል ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፋም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ: : የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።*

16:17 ይህ የማስጠንቀቂያ ቃል በዓውዱ ውስጥ ባልተለመደ ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው ነው። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚያደርጉት ድርጊት በዝርዝር ተፅፎ እናገኛለን ከቁ 17-18 እናንብብ።

1. በሕዝቡ መሃከል መከፋፈል እንዲኖር ያደርጋሉ
2. በአማኞች ሕይወት እንቅፋትን ያስቀምጣሉ
3. ቤተክርስቲያን የምታወጣውን ህገ ደንብ ሰዎች እንዲቃወሙ ያለአግባብ ያነሣሣሉ።
4. ሐሰተኛ አስተማሪዎች የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ያስተምሩ ነበር።
5. ሌላው የሐሰተኛ አስተማሪዎች ድርጊት በሚያባብልና በቁልምጫ ቃል የዋሆችን ያታልሉ ነበር።

ይህ ዝርዝር ከደካማና ከብርቱ ክርስቲያኖች አማኞች ከሚለው ዝርዝር ጋር የማይነፃፀር ነው።

▣ **"ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ"** የአረፍተ ነገሩ የአሁን ጊዜ አመልካች ነው ይህ የተደጋገመ ዋና ሃሳብ ነው (ገላ 1:8-9, 2ተሰሎ 3:6,14 2ዮሐ 10)

16:18
**አአመመቅ, አየመመቅ**
**አእቅ** **"ለምግብ ፍላጎታቸው"**
**አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** **"ለሆዳቸው"**
**ኢመቅ** **"ስለ ስግብግብነታቸው**

ይህ ቀጥተኛ ትርጉሙ "ሆዳሞች" የሚል ትርጉም ይሰጣል። (ፊሊ 3:9፡ቲቶ 1:12)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የትኛውንም ነገር ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ነው የሚያደርጉት።

▣ **"በመልካም እና በሚያቆለባብጥ ንግግር"** ሐሰተኛ አስተማሪዎች ተክለ ሰውነታቸው የሚስብና የሰውን አዕምሮ የሚማርክ ስብዕና አላቸው (ቆላ 2:4) ሐሰተኞች አቀራረባቸው ምክንያታዊ ነው ነገር ግን ምክንያቶቹ ሐሰት የሞላባቸው ናቸው መፅሐፋ ቅዱስ ነቅተን የሐስተኞች ትምህርት እንድንለይ ያስጠነቅቀናል (ዘዳ 13:1-5 ዘዳ 18:22 ማቴ7፡ፊሊ 3:2-3,8-19, 1ዮሐ 4:1-9

▣ **"ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ"** ዓረፋተ ነገሩ የአሁን ጊዜ አመልካች መሆኑ በዚህ ጊዜ እየተታለሉ ያሉ ስዎች እንደነበሩ ያመለክታል። በግዜው ለነበረው ለስህተት ትምርቶች ይጋለጡ የነበሩት አዳዲሱ አማኞችና የዋህ እና ታማኝ አማኞች ነበሩ።

16:19 **"መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቷል"** ከሮሜ 1:8 ጋር ያዛምዱ የሐዋርያው ጳውሎስ የግነት ንግግርን ያመለክታል።

▣ **"ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፋም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ"** የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት የሚያንፀባርቅ ነው። ማቴ 10፡16, ሉቃ 13፡20)።

**16፡20 የሰላም አምላክ"** ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ (ሮሜ 15፡33, 2ቆሮ 13፡16, ፊሊ. 4፡9 1ተሰሎ 5፡23, እና ዕብ 13፡20)

▣ **"ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል"** ከዘፋ 3፡15 የተወሰደ ነው። አማኞች ከመሲሁ ጋር ያላቸው ግንኙነት ጠላትን ድል እንዲያደርጉት አድርጓቸዋል 1ዮሐ 5፡18-20) ይህ ውድ የሆነ ቃል ኪዳንና ኃላፊነትም ጭምር ነው፡ ፡ በዚህ ዓውድ ላይ ሠይጣን የሃሰት አስተማሪዎችን በመጠቀም የቤተክርስቲያንን አንድነት ለማበላሸት የቤተክርስቲያንን የወንጌል ተልኮ ለማደጋቀፋ እንደማይተኛ የሚያብራራ ክፍል ነው። ከአስተኞች አስተማሪዎች ትምህርት በስተጀርባ አጋንንቶች አሉ። ነገር ግን የወንጌል ብርሃን ክፋውን ጨለማ የማስወገድ ሃይል አለው ለተጨማሪ ግንዛቤ "three crucial bastions about spiritual warfare" by Clinton E. Arnold" ይህ መፅሐፋ ጠቃሚ መረጃት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ይሰጣል።

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡ ጠላትነት**

ይህ ርዕስ ከተለያዩ ምክንያት የተነሳ በቀላሉ መልሱን መመለስ አይችልም።

1. የብሉይ ኪዳን መፅሐፋት ሁሉ ጠላትነትን በመልካም አይገልፁትም ነገር ግን ይህ ጠላት የሰውን ዘር ወደ ሌላ የስህተት መንገድን ይመራል በተጨማሪም ሰውን ሁሉ ስለፅድቅ ይከሳዋል።
2. የሰይጣን ክፋ ስራ በስፋት ይነገር የነበረው እስራኤሎች በፋርስ መንግስት ቅኝ ግዛት ስር በሩብሩ ጊዜ ነበር። ከመፅሐፋ ቅዱስ ውጪ በሆኑ ፅሑፎች ውስጥ በብዛት ተፅፎ ይገኛል። ይህ ትምህርት የአይሁድን መምህራን ከእምሮ የተቆጣጠረ አስተምርወት ነበር።
3. አአዲስ ኪዳን መፅሐፋት የብሉይ ኪዳንን መፅሐፋቶች ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ዋና የሚባሉትን ጭብጦች ወስደዋል።

በስነ መለኮት ትንተና ስለ "ክፋ ወይም ስለ ጠላትነት ስናጠና የመፅሐፎቹን ፀሐፊ፣ የመፅሐፋን አውድ ተንትኖ ማጥናት ትክክለኛውን የዓውድ ትርጉም ልናገኝ እንችላለን።

በመሆኑም አንድ ሰው ከመፅሐፋ ቅዱስ ሌላ የንባብ ፅሐፋ በመጠቀም ወይም የአለም ሐይማኖቶችን ወይም የምስራቅ ሃይማኖቶችን ፅሐፎች በማንበብ ስለ "ጠላትነት" ወይም ሰለ "ክፋ ቢያጠና የአዲስ ኪዳን መፅሐፋቶች ስለ ጠላትነት ወይም ስለ "ክፋ ሠይጣን" የሚሰጡት ትንታኔ የፋርስ ሃይማኖት (Persian dualism) እና የግሪኩ ሮማ የመንፈስ አለም ፍልስፍና (spiritism) ትምህርት ተፅኖ ጥላውን አጥልቶ በበርካታ የአዲስ ኪዳን መፅሐፋቶች ውስጥ ይታያል።

ነገር ግን ማንም አማኝ የአዲስ ኪዳንን መፅሐፋት ስልጣንና ትምህርት ጠንቅቆ የሚያወቅ ራሱን ከአይሁዱ እውነት መሳይ ተረቶችና ከምዕራባውያን የተሳሳተ ግንዛቤ ካላቸው መፅሐፋት መጠንቀቅ ይገባዋል። እግ/ር ስለ ክፋ ስራ ሁሉንም ገልጦ አላሳየንም ነገር ግን መሸነፋን ገልጠልናል።

በብሉይ ኪዳን ሰይጣን ወይም ከሳሽ ከሶስት ተነፃፃሪዎች ጋር እንመልከት

1. የሰው ከሳሾች (1ሳሙ 29፡4, 2ሳሙ 19፡22, 1ነገ 11፡14,23,25 መዝ 109፡6)
2. የመልአኩ ክስ (ዘኃል 22፡21-23, ዘካ3፡1)
3. የሰይጣን ክስ (1ዜና 21፡1, 1ነገ 22፡21, ዘካር 13፡2

በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ላይ የተጠቀሰው እባብ "ሰይጣን" የሚለውን ስያሜ ያገኘው የጨለማ ኪዳን ዘመን በሚባለው ጊዜ ነው (የጥበብ መፅሐፋ 2፡23-24, 24 ሄኖክ 31፡3) ይመልከቱ። **"የእግዚአብሔር ልጆች"** ተብሎ መፅሐፋ በዘፍጥረት ስድስ ላይ የተጠቀሰው በ1ሄኖክ 54፡6 ላይ መላዕክት ተብለዋል።

ይህ መጠቀሱ የስነ መለኮት ትንተናውን ለማውገዝ ሳይሆን ነገር ግን የሃሳብ ትንታኔ ለመስጠት ብቻ ነው። በብሉይ ኪዳን ስለ ክፋ የተሰጡ ስያሜዎች በአዲስ ኪዳን ለክፋ መላእክቶች" ተሰቶ እንመለከታለን ወይም ሠይጣን) 2ቆሮ 11፡3, ራዕ 12፡9

በብሉይ ኪዳን ሰይጣንን ማንነት እና ስራውን መለየት አስቸገሪ ነው። እስራኤል የሚያመልከው አንድ አምላክ ነው 1ነገ 22፡20-22 መክ 7፡14, ኢሳ 45፡7, አም 3፡6)። በብሉይ የሚፈጠሩት ጥፋቶች የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት መገለጫ ናቸው (ኢሳ 43፡11 ኢሳ 44፡6,8,24 ኢሳ 45፡5-6,14,21,22)።

ስለ "ሠይጣን" የተጠቀሱ የመፅሐፋ ቅዱስ ምንጮችን እንመልከት ኢዮብ 1-2 ስይጣን በዚህ ክፍል ላይ የእግዚአብሔር ልጆች በተባሉት መላዕክት መሃከል አንዱ ነበር። በኢሳያስ 14 እና በሕዝቅኤል 28 ሰይጣንን በምስራቅ ነገስታቶች በባቢሎንና በጢሮስ መስለውት እናነባለን። ሕዝቅኤል የኤደንን ገነት ምሳሌን ለጢሮስ ንጉስ እንደ ሰይጣን መመስል ብቻ ሳይሆን የግብፅንም ንጉስ መልካምና ክፋ በምታስታወቀው ዛፋ መስሎት እናነባለን። (ሕዝቅ 31)። ኢሳያስ በምዕራፋ 14፡12-14 መልአኩ ማመፁን አመልክቷል። እግ/ር ስለሠይጣን ፍጥረት፣ የክፋትን ጅማሬ ሁሉን አመልክቶን ቢሆን የብሉይ ኪዳን መፅሐፋት ትንተና፤የአውድ ትርጉም፤የፀሐፊውን ሐሳብ እና ዘመን ጥናት የሚሉ እና ሌሎችንም ትንተና ባላስፈለገን ነበር።

Alfred Ecersheim (the life and times of Jesus the messiah, vol 2, appendices xill (pp 748-763) and xvl (pp 770-776) በዚህ መፅሐፋ ላይ የአይሁድ መምህራን በፍርስ ሃይማኖት እና ስለ አጋንንት በተሳሳተ አመለካከት ተይዘው ነበርና በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ እውነተኛ ትምህርት የላቸውም ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ ከሚያስተምሩት የተለየ ትምህርት ያስተምር የነበረው አንዱ ምክንያት ከዚህ የተነሣ ነበር፡፡

የአይሁድ መምህራን ስለ መጽሀፍት እና ለሙሴ በሲና ስለተሰጠው ህግ ያላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ለሰይጣን በር መክፈት እንደሆነ አላስተዋሉም፡፡

ይህም ለሁለቱ ኃያላን ለሚባሉ የኢራንያ ጣኦቶች በር የከፈተ ነበር፡፡ የኢራንያ ዞራስትሬን ወይም ዱዋሊዝም ናቸው ሁለቱ የአለም ሃያላን ሃይላት በእኩል አለምን

ይገዛሉ ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ከሁለቱ ዱዋሊዝም ለአይሁድ ሁለቱ ሃያላን ያሕዌና ሠይጣን ናቸው የሚል ትርጉም አመጣ፡፡የአዲስ ኪዳን መፅሐፋ ሠይጣንን በማብራራት ግልፅ የሆነ ትምዕርት እንዲኖር አድርገዋል ለምሳሌ በሰማይ ጦርነት ሆነ፤የሰይጣን ከሰማይ መውደቅ፤ሌሎችንም እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡በራዕይ መፅሐፋ ላይ ይህ ርዕስ ተተንትኖአል (ራዕ 12፡4,7, 12-13) ሰይጣን የተሸነፈና የተጣለ መላክ ቢሆንም ነገር ግን የያህዌ አገልጋይ ሆኖ እንመለከታለን ማቴ 4፡1 ሉቃ 22፡31-32 1ቆሮ 5፡5, 1ጢሞ 1፡20)፡፡

እያንዳንዱ ሰው ለፈተና የሚያስገድደው ነገር ይገጥመዋል ነገር ግን እግዚአብሔር ወይም ሰውየው ለዚህ ጉዳይ ከሁለት አንዱ ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን ድነትን ከማግኘቱ በፊት ወይም በኃላ መንፈሳዊ ጦርነት ሊያጋጥመው ይችላል፡፡

▣ **"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ከእናንተ ጋር ይሁን"** *ሐዋርያው ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ ማጠቃለያ ላይ የሚጠቀምበት የመዝጊያ ንግግሩ ነው፡፡ (1ቆሮ 16፡23, 2ቆሮ 13፡14, ገላ 6፡18, ፊሊ. 4፡23, ቆላ 4፡18 1ተሰሎ 5፡28, 2ተሰሎ 3፡18 እና ራዕ 22፡21)፡፡ ይህ ፅሑፋ በሐዋርያው ጳውሎስ እጅ ቃል በቃል የተፃፈ ነው፡፡ በመሆኑም የሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ (2ተሰሎ 3፡17, 1ቆላ 16፡21, ቆላ 4፡18)፡፡*

**ሮሜ 16፡21**
**አብሮኝ የሚሠራ ጠዋቴዎስ ዘመዶቼም ሉቂዮስና ኢያስን ሱሲ ጴጥሮስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፡፡**

**16፡21-23** ይህ ምንባብ በተጨማሪነት የተፃፈ ፁሁፍ ነው፡፡ የጳውሎስ የቅርብ ወዳጆቹ የላኩት የሰላምታ ቃል ነው፡፡

**16፡21 "ሉቂዮስ"** ይህን ስም በተመለከተ ሶስት መላምቶች አሉ፡ (1) ባለመዳኒቱ ሉቃስን ሊሆን ይችላል (ቆላ 4፡14)፡፡ ወይም ለሊቅ ሰው የሚሰጥ ቅጽል ስም ይሆናል፡፡ (2) የቀሬናው ሉክዮስ ማለት ይሆናል ሐዋ 13፡1)፡፡ ወይም ስሙ ያልተጠቀሰ የአንድ ክርስቲያን ስም ይሆናል፡፡

▣ **"ኢያሶ"** ይህ ሰው በተሰሎንቂ ወደ ቤቱ ሐዋርያው ጳውሎስን ተቀብሎታል (ሐዋ 17፡5-9)፡፡

▣ **"ሱሲ ጳጥሮስ"** ይህ ሰው የቤርያ ከተማ ነዋሪ ነው (ሐዋ 20፡4)፡፡

**ሮሜ 16፡22**
**ይህን መልእክት የፃፍኩ እኔ ጤርጥዮስ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ**

**16፡22 "ይህን መልእክት የፃፍኩ እኔ ጤርጥዮስ"** ሐዋርያው ጳውሎስ ፀሐፊ እንደነበረው ያሳያል 1ቆሮ 16፡21፣ ገላ 6፡11 ቆላ 4፡18 2ተሰሎ 3፡17)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የማየት ችሎታው ዝቅ ያለ በመሆኑ በሚያንስ ፊደል በፓፒረስና በብራና ላይ መጻፍ አይችልም የሚል መላምት አለ በመሆኑም ፀሀፊ አስፈልጎት ነበር፡፡ እንደምሳሌ በጉልህ የማይታይ ጽሁፍ የሚባሉት አንዱ በገላ 6፡18 እንመልከት፡፡

**ሮሜ 16፡23-24**
**የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አስተናጋጅ ጋዮስ ሰላምታ የቀርብላችኋል፡፡ የከተማው መጋቢ ኤስጦስ ወንድማችንም ቁአስጥሮስ ስላምታ ያቀርቡላችኋል፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን፡፡**

**16፡23 "ጋይዮስ"** የዚህን ስም መላምቶች እንመልከት፡፡ (1) በሐዋርያት ስራ 18፡7 ላይ የሚገኘው ሰው ሊሆን ይችላል (2) ጋዮስ የደርቤ ከተማ ሰው ለሆን ይችላል ሐዋ 19፡29፣ 1ቆ 1፡14 (3) ወይም ጋዮስ ሶስተኛ የሐንስ ላይ ቁጥር አንድ ላይ የተፃፈው ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አስተናጋጅ"** ይህ ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን መስተንግዶ የሚገልጽ ነው፡፡ በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚያርፍበትን እና የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ለማሟላት ክርስቲያኖች

ፈቃደኛ ይሆኑ ነበር፡፡ በዚህ ምንባብ ላይ የተገለፀው ሰው ቤቱን ለአምልኮ መሰብሰቢያነት የሰጠ ነበር፡፡ የቤት ለቤት ያለች ቤተ ክርስቲያን ከመቶ አመታት በላይ እድሜን አስቆትራለች፡፡

▣ **"የከተማው መጋቢ ኤርስጦስ"** ሐዋ 19፡22፣ 2ጢሞ 4፡20 ተመልከቱ፡፡ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር በመዞር ወንጌልን የሰበከ ሰው ነው፡፡

▣ **"ቁአስጥሮስ"** በላቲን **"አራት"** ማለት ነው፡፡ ቁአስጥሮስ የጤርጥዮስ ወንድም ነው፡፡ ጤርጥዮስ በላቲን "ሶስት" ማለት ነው፡፡ (ሮሜ 16፡22)፡፡

16፡24 ይህ ጽሑፍ በግሪኩ መጽሐፍ ላይ አልተፃፈም ነገር ግን በሌሎች የግሪክ ጽሑፎች ላይ በምዕራፉ 16፡23 በኂላ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ይህ የሚያሳየው የመጀመሪያ የግሪክ ጽሁፍ ላይ እንዳልተፃፈ ነው፡፡ በተጨማሪም በ አአመመቅ አየመመቅ አእቅ እና Nኢመቅ ትርጉሞች ላይም አልተፃፈም፡፡ በዩቢኤስ ትርጉም ላይም በመጠኑ የተቆረጠ ሃሳብ ይታያል፡፡ ይህ በግሪኩ ጽሑፍ ላይ የደብዳቤውን መዝጊያ ለማድረግ ከመጨረሻዎቹ ሶስት ምዕራፎች በአንዱ ላይ እንደሆነ ያለመታወቁ ያመጣው ችግር እንዲሆን ያሳያል፡፡

> ሮሜ 16፡25-27
> **እንግዲህ እንደ ወንጌል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰበከ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጽሐፍ የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአህዛብ ሁሉ የታወቀው ምስጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን፡፡**

16፡25-27 ይህ ቀጥታ ከግሪኩ ጽሑፍ የተወሰደ ምንባብ ነው፡፡ ይህ የማጠቃለያ ጽሁፍ በምዕራፍ አስራ አራት እና አስራ አምስት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ዓውድ የመጽሐፉን ዋና ጭብጥ የሚናገር ክፍል ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በራሱ እጁ ጽሁፍ የፃፈው ነው፡፡

የተለያዩ አማኞች ስለዚህ የማጠቃለያ ጽሁፍ የተለያየ ምልከተ አለም አላቸው (views)

1. ይህ የማጠቃለያ ደብዳቤ ለኤፌሶን አብያተ ክርስቲያናት የተላከ ነው፡፡ በኤፌሶንም በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተነበበ ነው፡ የሚል አመለካከት አለ፡፡
2. ደብዳቤው ወደ ሮም ለሚሄዱ ሰዎች የተሰጠ ነበር፡፡ የሚከተሉትን ምክንያቶች እንመልከት፡፡
   ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮም ሳይሄድ ለሃያ ስድስት ሰዎች ሰላምታ አቅርቧል፡፡
   ለ. አስራ ስድስተኛው ምዕራፍ ስለ ሀሰተኛ አስተማሪዎች የሚጠቅስ ነው፡፡
   ሐ. ይህ የማጠቃለያ ጽሑፍ በግሪኩ ጽሁፍ ላይ የተለያየ ስፍራዎች ተጽፎ ይገኛል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ከምዕራፍ አንድ እስከ አስራ አራት ለሮም ቤተክርስቲያን እና ከምእራፍ አንድ እስከ አስራ ስድስት ያለው ለኤፌሶን እንደፃፈ ይነገራል፡፡ ሶስት ምክንያቶችን እንመልከት፤ (1) በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ከቦታ ቦታ ለራሳቸው የግል ስራ ይዟዟሩ ነበር፡፡ (2) በግሪኩ ጽሁፍ ላይ ሮሜ ምዕራፍ አስራ ስድስት ተጽፎ ይገኛል፡፡ (3) ሐሰተኛ አስተማሪዎች በምዕራፍ አስራ አራት ላይ ተጽፈው እናገኛለን ሮሜ 14፡1-15

16፡25 **"ለያበረታቹ ለሚችለው"** ይህ አስደናቂ የሆነ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ነው፤ በአዲስ ኪዳን ሶስት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ኤፌ 3፡20 ይሁዳ 24

▣ **"ሚስጥር"** እግዚአብሔር በሃጢያት ለወደቀው ለሰው ልጅ እንደገና የመዋጀትን ስራ ለሰው ዘር ሁሉ አዘጋጅቷል ዘፍ 3፡፡ ይህም እቅድ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍቶች ተገልጦ እንመለከታለን ዘፍ 3፡15፤ ዘፍ 12፡3፣ ዘፀ 19፡5-6 እና በነብያት መፅሐፍት ላይ ተጽፏል፡፡ ምንም እንኳን የእግ/ር ሙሉ አጀንዳው በዝርዝር ባይቀርብም 1ቆሮ 2፡6-8፡፡ ነገር ግን የመሲሁና የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ነገሩን አብራርቶታል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ "ሚስጥር" የሚለው ቃል የሚጠቀመው የእግዚአብሔርን የድነት ዕቅድ ለመግለጽ ነው 1ቆሮ 4፡1 ኤፌ 2፡11-3 13፤6፡19፤ ቆላ 4፡3 1ጢሞ 1፡9 ነገር ግን እንደ አውዱ የተለያየ ትርጉሞች ተሰቶት እንመለከታለን ጥቂቶቹን ከዚህ በታች እንመልከት፡፡

1. የእስራኤል ልብ ደንዳናነት አህዛቦች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመምጣት በር ከፈተ፡፡ ሮሜ 11፡25-32
2. የወንጌል ሚሥጥር ለሰው ዘር ሁሉ ተገለጠ፣ ይህም በክርስቶስ ውስጥ ተጠቃሎአል ሮሜ 16፡25-27፣ ቆላ 2፡2
3. የአማኞች አዲስ አካል መልበስ በዳግም ምጽአት 1ቆሮ 15፡5-57፤ 1ተሰሎ 4፡13-18
4. በክርስቶስ ሁሉን መጠቅለል የእግዚአብሔር እቅድ ነው፡፡ ኤፌ 1፡8-11
5. አይሁድና አህዛብ የእግዚአብሔርን መንግስት ይወርሳሉ ኤፌ 2፡11-3፡13
6. በክርስቶስ እና በቤተክርስቲያን መሃከል ያለው ግንኙነት በጋብቻ ቃል ኪዳን ተመስሏል (ኤፌ 5፡22-33)፡፡
7. አህዛቦች በቃል ኪዳኑ ሕዝብ ጋር ተቆጠሩ ደግሞ በክርስቶስ መንፈስ ተጠመቁ ይህም ክርስቶስን የሚወስን ህይወት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር በሐጢያት የወደቀውን የሰው ዘር የራሱን መልክ እንዲመስሉ አድርጓል፡፡ (ዘፍ 6፤5፤11-13፤ 8-21) ሰው በእግ/ር አምሳል ተፈጠረ (ዘፍ 1፡26-27፤ ዘፍ 5፡1 ዘፍ 9፡6 ቆላ 1፡26-28)፡፡

8. በመጨረሻም ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ይገለጣል (2 ተሰሎ 2፡1-11)፡፡
9. በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሚስጥሩ ተገልጧል (1ጢሞ 1፡160፡፡

**16፡26 "ሚስጥር እንደተገለጠ"** የተሰወረ የተባለው የእግዚአብሔር የዘላለም አጀንዳ የነበረው የምስራች ወንጌል መገለጡን የሚያበስር አዋጅ ነው፡፡ ኤ 2፡11-3፡13

▣ **"በመጽሐፍት"** ይህንን የዘላለም ዕቅዱን እግዚአብሔር የገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት እና በመስቀሉ ስራ ነው ይህም በብሉይ የተነገረው የትንቢት ፍፃሜ ነው፡፡ በመሆኑም የአህዛብና የአይሁድ አብያተ ክርስቲያናት መመስረታቸው የእግዚአብሔር እቅድ እንጂ የሰው አይደለም፡፡ (ዘፍ 3፡15፣ 12፡3፣ ዘፀ 19፡5-6፣ ኤር 31፡31-34)

**ልዩ ትኩረት የሚያሻው ርዕስ፡- "ዘላለም"**
"ዘላለም" ወይም "alonios" የሚለው ገላጭ ከአርባ ጊዜ በላይ በአዲስ ኪዳን ተፅፎ ይገኛል፡፡ በተለይ የዘላለም ህይወት በሚል ሃረግ እግ/ር ለሰዎች ሁሉ በምድርም በሰማይም እንዲኑሩ የሰጠቸው ትልቅ ሰጦታ እንደሆነ መፅሐፋ ያስተምረናል የሚከተሉተን ጥቅሶች አንብቡ

ሮሜ 16፡26
ዕብ 9፡12,13፡20
ሮሜ 16፡25,2 2ጢሞ 1እና 9 ቲቶ 1እና 2 ማቴ 18፡8,25,41 የዘላለም ቅጣት , ማቴ 25-46 የዘላለም ፍርድ በዚህ ምዕራፍ ላይ ዘላለም የሚለው ቃል ማጠቃለያን፣ የአለም ፍፃሜን፣ መጨረሻ መሆኑን፣ የሰዎች ዕድል ፈንታ የሚታወቅበት መሆኑን የሚያብራራ ነው እኛ ሁላችን ስለ ወደፊቱ የምናወቀው በጣም ጥቂት ነው በእርግጥ የሰው ልጅ ወደማይታየው የዘላለም ዓለም ይሄዳል በመሆኑም በእግዚአብሔር ቃል ላይ መጨመርም መቀነስም ስህተት ነው፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር የዘላለም ቅጣት በግልፅ

በመፅሐፋ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎ እናገኛለን በመሆኑም እግዚአብሔር በክርስቶስ ያዘጋጀውን የፍቅር መንገድ በመከተል ነገር ግን አንድ በጥልቀት ልናብራራው የማንችለው ጨለማ እንዳለም ማወቅ ይገባናል:: PP 318-319

▣ **"ለአህዛብ ሁሉ የታወቀው"** ይህ በግሪኩ ፅሑፋ ላይ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ነው እግ/ር ለሰው ልጆች እንዲታወቅ ያደረገው ወንጌልን ነው ይህም የእግ/ር የዘላለም አላማው ነው፡፡ ዘፋ 3፡15

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ወደ እምነት መታዘዝ የሚመራ"** |
| **አዲሱ ክንግ ጀምስ ትርጉም** | **"በመታዘዝ ወደ እምነት"** |
| **አየመመቅ** | **"ወደ እምነት መታዘዝ የሚያደርስ"** |
| **አእቅ** | **"ወደ እምነት መታዘዝ የሚመራ"** |
| **ኢመቅ** | **"ወደ እምነት መታዘዝ የሚያመጣቸው"** |

እነዚህን ሃረጎች ለመረዳት የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ ሐረጎቹ የሚያመለክቱት፡- (1) ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት (2) በክርስቶስ ስለመታመን (3) ያለሚቋረጥ ለወንጌል ስለመታዘዝ መታዘዝ ተግባራዊ የሚሆነው በንስሃ እና በእምነት መሆኑን የመፅሐፋ ቅዱስ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ማርቆ 1፡15 ሐዋ 3፡16,19,20፡21

**16፡27 "ብቻውን ጥበብ ላለው** እግዚአብሔር ይህ ከዘዳግም መፅሐፋ የተወሰደ እግ/ር አንድ አምላክ እንደሆነ የሚናገር የመፅሐፋ ቅዱስ ዐረፍተ ነገር ነው ዘዳ 6፡4-5 የክርስትና ሃይማኖት እንደ ይሁዲነት አንድ አምላክን የሚያመልክ ሃይማኖት ነው ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ስላሴ ወይም ሦስት አካል አንድ አምላክ የሚለውን ትርጉምን በመሰጠት ክርስቲያኖች የእምነታቸው መግለጫ በማድረግ ሃይማኖታቸውን መስርተውበታል፡፡

▣ **"እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን"** ከሮሜ 3፡23 ጋር ያዛምዱ

▣ **"አሜን"** ልዩ ትኩረት ከሚለው 1፡25 ይመልከቱ

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን ያሉትን በርካታ ሰዎች ወደ ሮም ሳይሄድ እንዴት አወቃቸው?
2. የሴት ዲያቆናት እንደ ነበሩ የመፅሐፋ ቅዱስ ማስረጃ ይኖራልን? (ሮሜ 16፡1፣ 1ጢሞ 3፡11፣ 1ጢሞ 5፡3-16)
3. በዚህ በመጨረሻው ምዕራፋ ላይ የበርካታ ሴቶች ስም ተጠቅ እናገኛለን አስፈላጊነቱ ምንድነው?
4. የሐሰተኛ አስተማሪዎች ትምዕርታቸውን እና የማስተማር ዘዴአቸውን አብራራ ሮሜ 16፡17-18

# ተጨማሪ መግለጫ አንድ

## የግሪክ ሰዋሰዋዊ ቃላት አጭር መግለጫዎች

የኮኔ ግሪክ፣ ዘወትር ሔለናዊ ግሪክ የሚባለው፣ በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል አካባቢ ከታላቁ አሌክሳንደር ጀምሮ (336-323 ቅልክ) ዋነኛ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል፤ ለ800 ዓመታት ገናና ሆኖ አክትማል (300 ቅልክ – 500 ዓም)። እሱም ቀለል ያለ የጥንታዊ ግሪክ አልነበረም፣ ነገር ግን በብዙ መንገዶች አዲሱ ግሪክ ሆኖ በጥንታዊው ቅርብ ምስራቅና በሜዲትራኒያን የዓለም ክፍል ሁለተኛ ቋንቋ ሆኖ ነበር።

የግሪኩ አዲስ ኪዳን በአንዳንድ መንገዱ የተለየ ነበር፣ ምክንያቱም ተጠቃሚዎቹ ከሉቃስና ከዕብራውያን ጸሐፊ በተቀር፣ ምናልባት አራማዊን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጠቅመው ይሆናል። ስለዚህ፣ ጽሑፎቻቸው የአራማዊ ፈሊጦችና መዋቅራዊ ቅርጾች ስላሉባቸው ነው። በተጨማሪም፣ ከሴፕቱዋጊንት (የግሪኩ የብሊ ትርጉም) ያነቡም ይጠቅሱም ነበር፣ ይህም ደግሞ በኮኔ ግሪክ የተጻፈው። ነገር ግን ሴፕቱዋጊንት ደግሞ የተጻፈው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ግሪክ ባልሆነ የአይሁድ ሊቃውንት ነው።

ይህም አዲስ ኪዳንን ወደ ጥብቅ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ወዳለው እንዳንገፋው እንደ ማስታወሻ ያገለግላል። እሱ የተለየ ያልሆነና ብዙ የሚጋራው ያለው ነው (1) ሴፕቱዋጊንት፤ (2) የግሪክ ጽሑፎች ለአብነትም የጆሴፈስ፤ እና (3) በግብፅ የተገኘው የወረቀት ጽሑፍ። ታዲያ እንዴት አድርገን የአዲስ ኪዳንን ሰዋሰዋዊ ትንታኔ እናካሂዳለን?

የኮኔ ግሪክ ሰዋሰዋዊ ባሕርይና የአዲስ ኪዳን ኮኔ ግሪክ ተወራራሽ ናቸው። በብዙ መንገዱ ሰዋሰውን በቀላል መልክ የማቅረብ ጊዜ ነበር። ጽሑፉ ዋነኛው መመሪያችን ይሆናል። ቃላቶች ትርጉም የሚኖራቸው በሰፊ ጽሑፍ ነው፤ ስለሆነም፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅርን መረዳት የሚቻልበት ብርሃን (1) የጸሐፊው የተለየ ያጻጻፍ ስልት፤ እና (2) የተለየ የጽሑፍ አካል ነው። በግሪክ ቅርጾችና መዋቅሮች ላይ ለድምዳሜ የሚሆን ተስማሚ መግለጫ የለም።

ኮኔ ግሪክ በመጀመሪያ ግሣዊ ቋንቋ ነበር። ዘወትር ለትርጓሜው ቁልፉ የግሡ ዓይነትና ቅርጽ ነው። በብዙ ዋነኛ ሐረጎች ግሡ በመጀመሪያ ይመጣና፣ ዋነኛ ጠቀሜታውን ያስከትላል። የግሪክን ግሥ ለመተንተን ሦስት የሚሆኑ መረጃዎች የግድ ያሻሉ፡ (1) መሠረታዊ አጽንኦት የሰጠው ጊዜ፣ ድምጸት (ገቢር/ተገብሮ) እና ሁኔታው (ገጠመኙ ወይም የግሡ ርባታ)፤ (2) የተለየው ግሥ መሠረታዊ ፍቺ (ሥርወ ቃል)፤ እና (3) የጽሑፉ አወራረድ (አገባብ)።

I. ጊዜ

ሀ. ጊዜ ወይም ገጽታ የሚያካትተው የግሥን የተጠናቀቀ ድርጊትና ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ግንኙነት ነው። ይህም ዘወትር “የተጠናቀቀ” እና “ያልተጠናቀቀ” በመባል ይታወቃል።

1. የተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የድርጊትን መከናወን ነው። አንድ ነገር ከመሆኑ ውጪ ተጨማሪ መረጃ አይሰጥም! አጀማመሩ፣ አካሄዱ ወይም ማብቃቱ አይካተትም።
2. ያልተጠናቀቀ ጊዜ የሚያተኩረው የአንድን ድርጊት ቀጣይነት ነው። linear action (ተሸጋጋሪ ድርጊት፣ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊት፣ ቀጣይ ድርጊት፣ ወዘተ።

ለ. ጊዜያቶች፣ ጸሐፊው ድርጊቶች እንዴት እንደተካሄዱ በተመለከተበት አግባብ ሊመደቡ ይችላሉ

1. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ ግሥ
2. ሆኖአል እናም ውጤቱም ይገኛል = የተጠናቀቀ
3. ባለፈው ጊዜ ተጠናቋል እናም ውጤቱ ይኖራል፣ አሁን ግን አይደለም = በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ
4. እየሆነ ነው = የአሁን
5. ሆኗል = ያልተጠናቀቀ
6. ይሆናል = የወደፊት

እነዚህ ጊዜያቶች ለትርጓሜ እንዴት እንደሚረዱ ተጨባጭ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው “መዳን” የሚለው ቃል ነው።እሱም በበርካታ የጊዜያት ዓይነቶች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሂደቱንም ሆነ ፍጻሜውን ያመላክታል።

1. የድርጊት ግሥ – “ድኗል” (ሮሜ. 8፡24)
2. የተጠናቀቀ – “ድኗል እናም ውጤቱ ይቀጥላል” (ኤፌ. 2፡5፣8)
3. የአሁን – “የዳነ” (1ኛ ቆሮ. 1፡18፤ 15፡2)
4. የወደፊት (የትንቢት) – “ይድናል” (ሮሜ. 5፡9፣ 10፤ 10፡9)

ሐ. በግሥ ጊዜያቶች ላይ በማተኮር፣ ተርጓሚዎች፣ ዋናው ጸሐፊ ራሱን ለመግለጽ የመረጠበትን ምክንያት ይቃኛሉ። መደበኛው “ከስም በፊት የሚመጣቅ ግሥ” ጊዜያቱ ያልተጠናቀቀ የተግባር ግሥ ነበር። እሱም መደበኛው “ያልተወሰነ፣” “ያልተለየ፣” ወይም “ዘወትር ከስም በፊት” የሆነ ግሥ ነው። በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ጽሑፉ በሚወስነው መሠረት። እሱም አንድ ነገር መሆኑን ያሳያል። የኃላፊ ጊዜው ገጽታ

ጥቅም ላይ የዋለው በአመላካች ተግባር ነው። ሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋለ አንድ ልዩ ነገር አጽንዖት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ግን ምን?

1. የተጠናቀቀ ጊዜ። ይህ የሚናገረው የተጠናቀቀ ድርጊትን ከሚኖረው ውጤት ጋር ነው። በአንዳንድ አገባቦች ያልተፈጸመ ጊዜ (የድርጊት ግሥ) እና የአሁን ጊዜን የደባለቀ ነው። ብዙውን ጊዜ የሚያተኩረው የተገኘው ውጤት ላይ ወይም የድርጊት መጠናቀቅ ላይ ነው። ለምሳሌ፡ ኤፌ. 2፡5 እና 8፣ "ድናችኋል፣ በመዳናችሁም ቀጥላችኋል።"
2. በኃላፊ ጊዜ የተጠናቀቀ። ይህም እንደ ተጠናቀቀ ጊዜ ሆኖ የሚኖረው ውጤት ያበቃበት ነው። ለምሳሌ፡ "ጴጥሮስ ከበሩ በስተውጭ ቆሞ ነበር" (ዮሐንስ 18፡16)።
3. የአሁን ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ያላበቃለት ወይም ያልተጠናቀቀ ድርጊትን ነው። ትኩረቱም ብዙውን ጊዜ በሁኔታው ቀጣይነት ላይ ነው። ለምሳሌ፡ "በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን በመሥራት አይቀጥልም፣" "ማንም ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን በመፈጸም አይቀጥልም" (1ኛ ዮሐንስ 3፡6 እና 9)።
4. ያልተጠናቀቀ ጊዜ። በዚህ ጊዜ ከአሁን ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ከተጠናቀቀ እና በኃላፊ ጊዜ ከተጠናቀቀው ጊዜ ጋር ያለው ግንኙነት ተመሳሳይ ነው። ያልተጠናቀቀው የሚያሳየው ያላበቃለትን ድርጊት ማለትም ተጀምሮ አሁን ያበቃለትን ወይም ባለፈው ጊዜ የነበረውን ድርጊት መጀመሪያ ነው። ለምሳሌ፡ "ከዚያም ሙሉው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣታቸውን ቀጠሉ" ወይም "ከዚያም ሞላው ኢየሩሳሌም ወደ እሱ መውጣት ጀመሩ" (ማቴ. 3፡5)።
5. የትንቢት ጊዜ። ይህ የሚያሳየው ዘወትር በመጪው ጊዜ የሚፈጸምን ንድፍ አመላካች ነው። የሚያተኩረውም አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠር በሚችለው ላይ ነው። ዘወትር የሚናገረውም የሁኔታዎቹን እውንነት ነው። ለምሳሌ፡ "ብፁዓን ናቸው… እነሱ ወደፊት…" (ማቴ. 5፡4-9)።

II. የግሥ ጊዜያት (ድምጸት)

ሀ. የግሥ ጊዜያት የሚገልጸው የግሥን ድርጊትና የባለቤቱን ግንኙነት ነው።

ለ. የአሁን ጊዜ ተራ፣ የሚጠበቅ፣ ያልተጋነነ መንገድን ይዞ ለማለት የሚፈልገውን ባለቤቱ የግሡን ድርጊት ሲከውን ነው።

ሐ. ተገብሯዊ ጊዜ ማለት ባለቤቱ የድርጊቱ ተቀባይ ሲሆን ማለት በውጭ አካል የተደረገውን። በውጭ አካል የሚፈጸመው ድርጊት በግሪክ አኪ ሲመለከት በሚከተለው መስተጻምራት እና አግባቦች ላይ ይታያል፡

1. ቀጥተኛ ሰዋዊ አድራጊ በ(hupo) ሲፈጸምና በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሰከሰት (ማቴ. 1፡22፣ ሐዋ. 22፡30)።
2. ሰዋዊ መካከለኛ ፈጻሚ በ(dia) በስም፣ በተውላጠ ስምና በቅጽል የሚታይበት አግባብ ሲከሰት (ማቴ. 1፡22)።
3. ሰዋዊ ያልሆነ ፈጻሚ፣ ዘወትር በ(en) በቁሳቁሳዊ አግባብ።
4. አንዳንድ ጊዜ በሰዋዊ ሆነ ሰዋዊ ባልሆነ ፈጻሚ፣ በቁሳዊ አግባብ ብቻ።

መ. መካከለኛ ጊዜ ማለት ባለቤት የግሡን ተግባር ሲፈጽም እና እንዲሁም በቀጥታ በግሡ ድርጊት ላይ በቀጥታ ሲገባ ነው። ዘወትር ከፍ የተደረገ ሰዋዊ ፍላጎት የግሥ ድምጸት ተብሎ ይጠራል። ይህ አወቃቀር በተመሳሳይ መንገድ ለሐረጉ ወይም ለዓረፍተ ነገሩ ባለቤት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ አወቃቀር በእንግሊዝኛ አይገኝም። እሱም ሰፋ ያለ የግሪክ ፍቺ እና ትርጉም አግባብ አለው። ለዚህ ዓይነት የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎች፡

1. አነጻጻሪ – የባለቤቱ ቀጥተኛ ድርጊት በራሱ ላይ። ምሳሌ፡ "ራሱን ሰቀለ" (ማቴ. 27፡5)።
2. የታሰበበት – ባለቤት ድርጊቱን ለራሱ ይፈጽማል። ምሳሌ፡ "ሰይጣን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ ይለውጣል" (2ኛ ቆሮ. 11፡14)።
3. ባለ ሁለት ወገን – የሁለት ባለቤቶች ውስጣዊ ድርጊት። ምሳሌ፡ "እርስ በርሳቸው ተመካከሩ" (ማቴ. 26፡4)

III. አኳኋን (ወይም አገባብ)

ሀ. በኮኔ ግሪክ አራት አገባቦች አሉ። እነርሱም የግሥን እውነታዊ ግንኙነት ይጠቁማሉ፣ ይሄውም በተቻለ መጠን ጸሐፊው በራሱ ሐሳብ። አገባቦች በሁለት ሰፋፊ ምድቦች ይከፈላሉ፤ እውነታን የሚጠቁሙ (ጠቋሚ) እና በውስጥ ያለ አቅም ጠቋሚዎች (መሻታዊ ሁኔታ (አጠራጣሪ)፣ ትዕዛዝ አንቀጽ እና አማራጫዊ ናቸው።)

ለ. አመላካች አገባብ ሁነኛ አገባብ ሲሆን የተከናወነን ወይም ተከናውኖ የነበረን ማለትም ቢያንስ በጸሐፊው ልቦና የነበረን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው። ይህም <u>ብቸኛው</u> የግሪክ አገባብ ሆኖ ትክክለኛን ጊዜ የሚገልጽ ነው፣ እዚህም ቢሆን ይህ ገጽታ ሁለተኛ ነው።

ሐ. ተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በምናልባታዊ የትንቢት ድርጊት ነው። አንድ ነገር ገና አልሆነም፣ ነገር ግን የመሆን ዕድል አለው። ከትንቢታዊ አመላካች ጋር በርካታ የሚጋራው አለው። ልዩነቱ መሻታዊው የሚገልጸው የተወሰነ ደረጃ ያለው አጠራጣሪነትን ነው። በእንግሊዝኛ ይህ ዘወትር "ይችላል፣" "ነበር፣" "ምናልባት፣" "ምናልባት።"

መ. አማራጫዊ ሁኔታ የሚገልጸው በንድፈ ሐሳባዊ ደረጃ ሊሆን የሚችለውን ነው። ከመሻታዊው አንድ ደረጃ ከእውነታ ቀደም ብሎ ይገኛል። አማራጫዊው አጠራጣሪነትን የሚገልጸው በተወሰኑ ሁኔታዎች ነው። አማራጫዊው በአዲስ ኪዳን አልፎ አልፎ ነው የሚገኘው። በጣም የታወቀው ድግግሞሻዊ አጠቃቀሙ የሚገኘው በታወቀው የጳውሎስ ሐረግ፣ "እንዲህስ አይሁን" (ኪጀቅ፣ "እግዚአብሔር አያርገው")፣ የሚለው አስራ አምስት ጊዜ (ሮሜ. 3፡4፣ 6፣ 31፤ 6፡2፣ 15፤ 7፡7፣ 13፤ 9፡14፤ 11፡1፣ 11፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡15፤ ገላ. 2፡17፤ 3፡21፤ 6፡ 14) ጥቅም ላይ ውሏል። ሌሎች ምሳሌዎችም ተሰ. (?) 1፡38፣ 20፡16፣ ሐዋ. 8፡20፣ እና 1ኛ ተሰ. 3፡11።

ሠ. ትዕዛዛዊ ሁኔታ አጽንዖት የሚሰጠው ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ ላይ ሆኖ አጽንዖቱ ግን በተናጋሪው ፍላጎት ላይ ነው። እሱም በፍቃድ ላይ የተመሠረተውን ብቻ አማራጭ አመላክቶ እንዲሁም በሌላው ሁኔታዊ አማራጭ ላይ ነው። ትዕዛዛዊ ሁኔታ በጸሎት እና በሦስተኛ መደብ ጥያቄዎች ላይ ልዩ አጠቃቀም አለው። እነዚህ ትዕዛዛት በአኪ የሚገኙት በአሁን እና በግብር ግሦች ነው።

ረ. አንዳንድ ሰዋሰዎች ቦዝ አንቀጽን እንደሌለኛው ሁኔታዊ ዕይነት ይመድቧቸዋል። እነዚህም በግሪክ አኪ የተለመዱ ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ግሳዊ ቅጽል በሚል። ከሚቀራረቡት ከዋናው ግሥ ጋር ተጣምረው ይተረጎማሉ። ቦዝ አንቀጽን ለመተርጎም የተለያየ ሰፋ ያለ አማራጭ አለ። እዚህ ላይ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎችን መቃኘቱ ይበጃል። *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤክር የታተመው ደኅና አድርጎ ይረዳል።

ሰ. የድርጊት አንቀጽ አመላካች፣ ሁነኛ ወይም "ያልተለየ" አንድን ሁኔታ (ድርጊት) ለመመዝገብ ይሆን ነበር። ማንኛውንም ጊዜ፣ ድምጸት ወይም የተለየ ትርጓሜያዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ይህም ዋነኛው ጸሐፊ ለማለት የፈለገውን ነው።

IV. የግሪክኛ ችሎታ ለሌለው ሰው የሚከተሉት የጥናት መርጃዎች አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ፡

ሀ. ፍሪበርግ፣ ባርባራ እና ጢሞቲ። *የተተነተነ የግሪክ አዲስ ኪዳን*። ግራንድ ራፒድስ፡ ቤክር፣ 1988።

ለ. ማርሻል፣ አልፍሬድ። *ኢንተርሳይነር (መስመራዊ) የግሪክ እንግሊዝኛ አዲስ ኪዳን። ግራንድ ራፒድስ*፡ ዞንደርቫን፣ 1976።

ሐ. ሞውንሲ፣ ዊሊየም ዲ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ቃላታዊ ትንታኔ። ግራንድ ራፒድስ*፡ ዞንደርቫን፣ 1993።

መ. ጭምቅ ሐሳቦች፣ ሬይ. *የግሪክ አዲስ ኪዳን ጠቀሜታዎች።* ናሽቪሊ፡ ብሮድማን፣ 1950።

ሠ. በከፍተኛ ትምህርት ተቀባይነት ያለው የኮኔ ግሪክ የተልእኮ ኮርስ ከሞዲ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም፣ ቺካጎ፣ IL ይገኛል።

V. ስሞች

ሀ. ከአገባብ አኳያ፣ ስሞች የሚመደቡት በየጉዳዩ ነው። ጉዳዩ ከስሙ አኳያ መልኩ የተቀየረ ሲሆን ይህም ከግሡ እና ከሌሎቹ የዓረፍተ ነገሩ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። በኮኔ ግሪክ ብዙዎቹ የጉዳዮ ተግባራት የሚጠቆሙት በመስተጻምሮች ነው። የጉዳዩ መልክ የተለያዩ በርካታ ግንኙነቶችን እንደመግለጡ መጠን፣ መስተጻምሮች ለእነዚህ ተግባራት የሚሆኑ ግልጽ መለያዎችን ያስቀምጣሉ።

ለ. የግሪክ ጉዳዮች በሚከተሉት ስምንት መንገዶች ይመደባሉ፡

1. ሳቢዎቹ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት ለስያሜ ሲሆን ዘወትርም የዓረፍተ ነገሩ ወይም የሐረጉ ባለቤት ይሆናሉ። በተጨማሪም ስም አመልካች ግሦችን እና ቅጽሎችን ከአያያዥ ግሦች ጋር "የመሆን" ወይም "የመኖር" ለመጠቀም ያስችላል።
2. አገናዛቢ ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውሉት የተለየ ባሕርይ ወይም ይዘት ለቃሉ እና ከእሱም ጋር ለተጎዳኙት የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ ነው። "ምን ዓይነት?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "የ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
3. የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ተመሳሳይ የሆነ መልኩ የተቀየረ እንደ አገናዛቢ ያለ ይጠቀማል፣ ነገር ግን መለያየትን ነው የሚያሳየው። ዘወትር የሚገለጸውም በጊዜ፣ በቦታ፣ በምንጭ፣ በመነሻ ወይም በደረጃ ያለውን ልዩነት ለማሳየት ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ከ"ን በመጠቀም ይታወቃል።
4. ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ (የስም) ጥቅም ላይ የሚውለው ግላዊ መሻትን ነው። ይህም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታዎችን ያሳያል። ይህም ዘወትር ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ነው። ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "ወደ"ን በመጠቀም ይታወቃል።

5. አቅጣጫዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ተመሳሳይ የስም፣ የተውላጠ ስምና የቅጽል ጉዳዮች ዓይነት ሲሆን፣ ነገር ግን የሚያሳየው አቅጣጫን በቦታ፣ በጊዜ፣ ወይም በአመክኖአዊ ወሰን ነው:: ብዙውን ጊዜም በእንግሊዝኛው መስተጻምር "በውስጥ፣ በላይ፣ በ፣ በመሐል፣ በጊዜ፣ በ፣ በላይ እና በላይ"ን በመጠቀም ይታወቃል::
6. መገልገያዊ ጉዳይ ቀጥተኛ ካልሆነው ተሳቢ እና ለመገልገያዊ ጉዳዮች መልኩ የተቀየረ ተመሳሳይ ነው:: እሱ የሚገልጸው ምንነቱንና መስተጋብሩን (ተያያዥነቱን) ነው:: ብዙውን ጊዜም የእንግሊዝኛውን መስተጻምር "በ"ን ወይም "ጋር"ን በመጠቀም ይታወቃል::
7. ቀጥተኛ ባለቤታዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉት የአንድን ድርጊት ድምዳሜ ለመግለጽ ነው::ዋናው ጠቀሜታው ለቀጥተኛ ባለቤት ነው:: "ምን ያህል ሩቅ?" ወይም "እስከ ምን ድረስ?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል::
8. የስም መልኮች ጉዳይ ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥተኛ ባለቤትን ነው::

VI. መስተዋድድ እና አያያዦች

1. ግሪክ በጣም ቁልጭ ያለ ቋንቋ ነው፣ ምክንያቱም በርካታ አያያዦች ስላሉት:: እነሱም ሐሳቦችን ያያይዛሉ (ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮች፣ እና አንቀጾችን):: በጣም የተለመዱ ስለሆኑ፣ በሚቀሩበት ጊዜ በተለይ በትንታኔ ጊዜ ትርጉም ይኖረዋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ መስተዋድዶች እና አያያዦች የጸሐፊውን ሐሳብ አቅጣጫ ያመላክታሉ:: ብዙውን ጊዜ ጸሐፊው በትክክል ምን ለማለት እንደፈለገ ለመወሰን በጣም ጠቃሚ ናቸው::
2. ከዚህ ቀጥሎ የጥቂት መስተዋድዶች እና አያያዦች እና ትርጉሞቻቸው ይቀርባል፣ (ይህ መረጃ ባብዛኛው የተገኘው ከ ኤች. ኢ. ዳና እና ጆሊየስ ኬ. ማንቲ *የግሪክ አዲስ ኪዳን የሰዋሰው መመሪያ)* ላይ ነው::

*ሀ.* ጊዜ አያያዦች

1) epei, epeid e, hopote, hote, hotan (ተሳቢ) - "*መቼ*"
2) *hoes*, - "በ… ጊዜ"
3) *hotan, epan* (ተሳቢ) — "*መቼም* ቢሆን"
4) *hoes, achiri, mechri* (ተሳቢ) — "እስከ… *መቼ*"
5) *priv* (ንዑስ አንቀጽ) - "በፊት"
6) *hos* - "ከ… ጀምሮ" "*መቼ*" "እንደ"

ለ. አመክኖአዊ አያያዦች

1) ተግባር
   a) *hina* (ተሳቢ), *hopos* (ተሳቢ), hos - "እንደ…መሆኑ" "እንደ"
   b) *hoste* (አቀላጣፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
   c) *pros* (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) ወይም eis (አቀላጠፊ ንዑስ አንቀጽ ተሳቢ) "እንደ"
2) ውጤት (በሰዋሰዋዊ ቅርጾች ተግባርና ውጤት መካከል የቀረበ ተወራራሽነት አለ)
   a) (ንዑስ አንቀጽ ይህ በጣም የተለመደ ነው) - "እንደ…መሆኑ" "እንደ"
   b) *hiva* (ተሳቢ) - "ስለሆነም"
   c) *ara*- "ስለዚህ"
3) መንሥኤ ወይም ምክንያት
   a) (ምክንያት/መነሻ ወይም ሳቢያ/ድምዳሜ) — "ለ፣" "ምክንያት"
   b) *dioti, hotiy* - "ምክንያቱም"
   c) *epei, epeide, hos*- "ከ… ጀምሮ"
   d) (ከ ተሳቢ) እና (አቀላጣፊ ተሳቢ ንዑስ አንቀጽ) "ምክንያት"
4) ተገቢ አስተያየት
   a) *ara, poinum, hoste*-"ስለሆነም"
   b) *dio* (ጠንካራው ምርመራዊ ተገቢ አስተያየት) — "በዚህም ምክንያት)
   c) *oun* "ስለሆነም" "ስለዚህ" "ከዚያም" "በዚህም ሳቢያ"
   d) *toinoun* "በመሠረቱ"
5) ተጻራሪ ወይም ተቃርኖ
   a) *alla* (ጠንካራ ተቃርኖ) - "ግን፣" "በተቀር"
   b) *de* - "ግን፣" "ቢሆንም፣" "ገና፣" "በሌላ በኩል"
   c) *kai* - "ግን"
   d) *mentoi, oun* - "ቢሆንም"
   e) *plên* "ቢሆንም ግን" (በአብዛኛው ሉቃስ ላይ)
   f) *oun* - "ሆኖም"
6) አወዳዳሪ
   a) *hôs*, (አወዳዳሪ ሐረጎችን ያሳያል)

b) *kata* (በድብልቆች katho, kathoti, kathôsper, kathaper)
c) *hosos* (በዕብራይስጥ)
d) ê — "ከ…ይልቅ"

7) ተከታታይ ወይም ተለጣጣቂ
a) *de* - "እና" "አሁን"
b) *kai* - "እና"
c) *tei* - "እና"
d) *hina, oun* - "እንደ"
e) *oun* "ከዚያም" (በዮሐንስ)

ሐ. ግነታዊ አግባብ

1) *alla* - "በርግጠኝነት" "አዎን" "በእውነቱ"
2) *ara* - "በርግጥ" "በእውነቱ " "በርግጥ "
3) *gar* - "ግን በርግጥ" "በርግጠኝነት" "በርግጥ "
4) *de* - "በርግጥ"
5) *ean* - "እንኳን"
6) *kai* - "እንኳን" "በርግጥ" "በእውነቱ "
7) *mentoi* "በርግጥ"
8) *oun* "በርግጥ" "እንደ ምንም"

VII. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች

ሀ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሐረጎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ለትርጓሜ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም እሱ ነባሩ ግሥ ድርጊቱን ያደረገበትን ወይም ያላደረገበትን ሁኔታዎች፣ ምክንያቶች ወይም መንሥኤዎች ስለሚያሳይ ነው፡፡ አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ አካሄዳቸውም ከጸሐፊው አስተሳሰብ ወይም ሊል ለፈለገው እውነት ወደ ሆነው መሻት ነው፡፡

ለ. አንደኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር የሚገልጸው ድርጊትን ወይም ከጸሐፊው አስተሳሰብ አኳያ  ትክክል ይሆናል ተብሎ የሚታመንበትን ወይም ሊል ከፈለገው አንጻር ነው— ምንም እንኳ "እንደሁ" በሚል ቢገለጥም፡፡ በብዙ ጽሑፎች "ከ… ጀምሮ" በሚል ቢተረጎምም (ማቲ. 4፡3፤ ሮሜ.8፡31)፡፡ ቢሆንም ይህ ግን ሁሉም አንደኛ መደቦች ከእውነታ ጋር ትክክል ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት አንድን ነጥብ በክርክራዊ መንገድ ወይም ስህተት ያለበትን አጉልቶ በማሳየት ነው (ማቲ. 12፡27)፡፡

ሐ. ሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር ብዙውን ጊዜ "ከሐቅ ጋር ተጻራሪ" በመባል ይታወቃል፡፡እሱም ነጥቡን ለመጥቀስ ትክክል ያልሆነን ነገር ወደ እውነት ያመጣል፡፡ ለምሳሌ፡

1. "በርግጥ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ አይደለም እንጂ፣ ማን እና እንዴት ያለች ሴት እንደያዘችው ባወቀ ነበር፣ ግን አይደለም" (ተሰ. 7፡39)፡፡
2. "ሙሴንስ ብታምኑት፣ አታምኑትም እንጂ እኔን ታምኑኝ ነበር፣ ግን አታምኑም" (ዮሐንስ 5፣46)፡፡
3. "ሰዎችን ባስደስት ኖሮ ግን፣ አላደርገውም እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጨርሶ ባልሆንኩን ነበር፣ ነገር ግን ነኝ" (ገላ. 1፡10)

መ. ሦስተኛ መደብ ሊሆን የሚችል የትንቢት ድርጊትን ያመላክታል፡፡ ዘወትር የድርጊቱን የመሆን ግምት ያስቀምጣል፡፡ ዘወትርም ሊደርስ የሚችልን ያሳያል፡፡ የነባሩ ግሥ ድርጊት ርግጠኛ ባልሆነ መልኩ በሐረጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ምሳሌዎች ከ1ኛ ዮሐንስ፡ 1፡6-10፤2፡4፣6፣15፣20፣21፣24፣29፤ 3፡21፤ 4፡20፤ 5፣14፣16፡፡

ሠ. አራተኛው መደብ ሊደርስ ከሚችል ራቅ ያለ ነው፡፡ በአኪ. እምብዛም አይገኝ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የተሟላ አራተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገር አይገኝም፣ ሁለቱንም የሁኔታዊ ክፍሎች መግለጫ ሊያሟላ የሚችል፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ ምሳሌ የሚሆን የመክፈቻ ሐረግ በ1ኛ ጴጥ. 3፡14፡፡ ለከፊል አራተኛ መደብ መዝጊያ ሐረግ የሚሆን ምሳሌ ሐዋ. 8፡31፡፡

VIII. ክልክሎች

ሀ. የአሁን ጊዜ ያልተጠናቀቀ፣ እኔ በሚል አገባብ (ግን የተለየ ያልሆነ) በሂደት ላይ ያለ ድርጊት መቆሙን አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ጥቂት ምሳሌዎች፡ "ሀብታችሁን በምድር ላይ ማከማቸታችሁን አቁሙ…" (ማቲ. 6፡19)፤ "ስለ ሕይወታችሁ መጨነቃችሁን አቁሙ…" (ማቲ. 6፡25)፤ "ሥጋችሁን ለኃጢአት በመስጠት ክፉ የመፈጸሚያ መሣርያ አታድርጉ…" (ሮሜ. 6፡13)፤ "የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ማሳዘን አይኖርባችሁም…" (ኤፌ. 4፡ 30)፤ እና "በወይን ጠጅ አትስከሩ…" (5፡18)

ለ. ያልተጠናቀቀ ድርጊት እኔ በሚል አገባብ "አንድን ድርጊት ወይም አትጀምር ወይም አትፈልም" ለሚለው አጽንዖት ይሰጣል። ምሳሌዎች፡ "እንደዛለማድረግ እንኳ አታስቡ..." (ማቲ. 5፡17)፤ "አትጨነቁ..." (ማቲ. 6፡31)፤ "አሳፋሪ መሆን አይኖርባችሁም..." (2ኛ ጢሞ. 1፡8)።

ሐ. ጥንድ አሉታ በተያያዥ አኳኋን የሚገለጠው በእጅጉን አጽንዖታዊ አሉታ ነው። "ፈጽሞ በፍጹም" ወይም "በምንም ምክንያት ቢሆን" ምሳሌዎች፡ "እሱ ፈጽሞ፣ በፍጹም ሞትን አያይም" (ዮሐንስ 8፡51)፤ "እኔ በፍጹም፣ ፈጽሞ..." (1ኛ ቆሮ. 8፡13)።

IX. መስተአምር

ሀ. በኮኔ ግሪክ የተወሰነ መስተአምር "ው" (the) ከእንግሊዝኛው ጋር ተመሳሳይ ጠቀሜታ ነው ያለው። ዋነኛው ተግባሩ "አመላካችነት" ሆኖ ለሚመለከተው ቃል፣ ስም ወይም ሐረግ አጽንዖት ማሰጠት ነው። አጠቃቀሙ በአዲስ ኪዳን ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያል። የተወሰነው መስተአምር ለሌሎች ተግባራትም ሲውል፡

1. እንደ አመላካች ተውላጠ ስም ለተቃርኗዊ አግባብ፤
2. ቀደም ሲል ለተጠቀሰ ባለቤት ወይም ሰው እንደ ማጣቀሻ ምልክት
3. የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት በአያያዥ ግሥ በሚገልጽ በሆነ መንገድ። ምሳሌዎች፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣" ዮሐንስ 4፡24፤ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣" 1ኛ ዮሐንስ 1፡5፤ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣" 4፡8፣16።

ለ. የኮኔ ግሪክ እንደ እንግሊዝ "አንድ" (a እና an) ዓይነት የተወሰነ መስተአምር የለውም። የዚህ ያልተወሰነ መስተአምር አለመኖር ማለት፣

1. በአንድ ነገር ባሕርይ ወይም ዓይነት ላይ ያተኩራል።
2. በአንድ ነገር ምድብ ላይ ያተኩራል።

ሐ. የአኪ ጸሐፍት በስፋት የሚለያዩት በመስተአምር አጠቃቀማቸው ነው።

X. በግሪክ አዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚታዩባቸው መንገዶች

ሀ. በአዲስ ኪዳን አጽንዖት የሚሰጥባቸው ስልቶች ከጸሐፊ ጸሐፊ ይለያያሉ። ከሁሉም የተሻሉት ቋሚ እና መደበኛ ጸሐፍት ሉቃስ እና የዕብራውያን ጸሐፊ ናቸው።

ለ. ቀደም ሲል ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች መደበኛና ለአጽንዖት ያለተለየ ዳሩግን ሌላ ማንኛው ግሥ፣ ድምጸት ወይም አኳኋን ትርጉማዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተመልክተናል። ይህም ማለት ያልተጠናቀቀ ድርጊት የአሁን አመላካች ተገቢያዊ በሆነ የሰዋሰው ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡ ሮሜ. 6፡10 (ሁለት ጊዜ)

ሐ. በኮኔ ግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል

1. የኮኔ ግሪክ ተለዋዋጭ የሆነ የቃላት ቅርጽ ያለው ቋንቋ ሲሆን እንደ እንግሊዝኛው የቃላት ሥርዓት ሳይሆን ራሱን የቻለ ነው። ስለዚህም ጸሐፊው መደበኛውን የቃላት ቅደም ተከተል እነዚህን ለማሳየት ይለዋውጠዋል...
   ሀ. ጸሐፊው ለአንባቢው አጽንዖት እንዲሰጥ የፈለገውን
   ለ. ጸሐፊው ለአንባቢው ያስገርማል ብሎ ያሰበውን
   ሐ. ጸሐፊው በጥልቀት የተሰማውን ጉዳይ
2. ተገቢው የግሪክ የቃላት ቅደም ተከተል ጉዳይ ገና እልባት አላገኘም። ቢሆንም፡ ይሆናል የብሎ የታሰበው ተገቢ ቅደም ተከተል
   ሀ. ለአያያዥ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ማሟያ
   ለ. ለተሻጋሪ ግሦች
      (1) ግሥ
      (2) ባለቤት
      (3) ተሳቢ
      (4) ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ
      (5) መስተጻምራዊ ሐረግ

ሐ. ለስማዊ ሐረጎች
    (1) ስም
    (2) አጎላማሽ
    (3) መስተጻምራዊ ሐረግ
3. የቃላት ሥርዓት ለማብራራት (ለትርጓሜ) ፍጹም ጠቃሚ ነጥብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡
   ሀ. "ለእኔና ለበርናባስ የኅብረት ቀኝ እጃቸውን ሰጡን" (ገላ. 2፡9)፡፡ "የኅብረት ቀኝ እጃቸውን" ተከፍሎ ጠቀሜታውን ለማመልከት ከፊት ለፊት ሆኗል፡፡
   ለ. "ከክርስቶስ ጋር" (ገላ. 2፡20)፣ ከፊት ሆኗል፡፡ ሞቱ ማዕከላዊ ነው፡፡
   ሐ. "ጥቂት በጥቂት እና በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ነበር" (ዕብ. 1፡1)፣ ከፊት ሆኗል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠ ነው አከራካሪ የሆነው እንጂ የመገለጥን እውነት በመቃረን አይደለም፡፡
      መ. ዘወትር የተወሰነ መጠን ያለው አጽንዖት ያሳያል
1. የተውላጠ ስሞች መደጋገም፣ በግሡ በተለያየ መልኩ ቀደም ሲል የነበረው፡፡ ምሳሌ፡ "እኔ፣ ራሴ፣ ከእናንተ ጋር በርግጥ እሆናለሁ…" (ማቴ. 28፡20)፡፡
2. በቃላት፣ በሐረጋት፣ በዐቢይ ሐረጋት ወይም በዓረፍተ ነገሮች መካከል መኖር የሚገባው መስተጻምር ወይም ሌሎች አያያዥ ቃላት አለመኖር፡፡ ይህም (asyndeton) ("ያልታሰረ") በመባል ይታወቃል፡፡ አያያዡ ቃል እንዲኖር ተጠብቆ መቅረቱ ትኩረትን ይስባል፡፡ ለምሳሌ፡
   ሀ. የብፁአን ትሩፋቶች (ሰባቱ)፣ ማቴ. 5፡3 (ዝርዝሩን ለማግነን)
   ለ. ዮሐንስ 14፡1 (አዲስ ርዕስ)
   ሐ. ሮሜ. 9፡1 (አዲስ ክፍል)
   መ. 2ኛ ቆሮ. 12፡20 (ዝርዝሩን ለማግነን)
3. በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ የቃላት ወይም የሐረጎች መደጋገም፡፡ ምሳሌ፡ "ለክብሩ ምስጋና" (ኤፌ. 1፡6፣ 12 እና 14)፡፡ ምስጋናው ጥቅም ላይ የዋለው የእያንዳንዱን የሥላሴ አካል ሥራ ለማሳየት ነው፡፡
4. ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ወይም ቃል (ድምጽ) በቃላት በካከል የሚኖረው ሚና
   ሀ. ተለዋጭ ቃል - ስም አይጠሬ ቃላትን ቀይሮ በሌላ መጠቀም ለምሳሌ "እንቅልፍ" ን ለሞት (ዮሐንስ 11፡ 11-14) ወይም "እግሮች" ለወንድ ብልት (ሩት 3፡7-8፤ 1ኛ ሳሙ. 24፡3)፡፡
   ለ. ኅናዊ አገላለጽ - ለእግዚአብሔር ስም ቃላትን መለወጥ፣ ምሳሌ "የሰማይ መንግሥት" (ማቴ. 3፡21) ወይም "ከሰማይ የሆነ ድምፅ" (ማቴ. 3፡17)፡፡
   ሐ. ዘይቤያዊ አገላለጾች
      (1) የማይቻል ግነት (ማቴ. 3፡9፤ 5፡29-30፤ 19፡24)፡፡
      (2) የተለዩ ግነታዊ አገላለጾች (ማቴ. 3፡5፤ ሐዋ. 2፡36)፡፡
      (3) ሰዋዊ ዘይቤዎች (1ኛ ቆሮ. 15፡55)፡፡
      (4) ውስጠ ወይራ (ገላ. 5፡12)
      (5) ቅኔያዊ አንቀጾች (ፊሊ. 2፡6-11)፡፡
      (6) በቃላት መካከል ያሉ ድምፆች
         (ሀ) "ቤተ ክርስቲያን"
            i. "ቤተ ክርስቲያን" (ኤፌ. 3፡21)
            ii. "ጥሪ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
            iii. "የተጠራ" (ኤፌ. 4፡1፣4)
         (ለ) "ነጻ"
            i. "ነጻ ሴት" (ገላ. 4፣31)
            ii. "ነጻነት" (ገላ. 5፡1)
            iii. "ነጻ" (ገላ. 5፡1)
   መ. ዘይቤአዊ ቋንቋ - ብዙውን ጊዜ ባህላዊ እና የተለየ ቋንቋን (ዘዬ) የሚያሳይ ነው፡
      1) ይህ የ "ምግብ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 4፡31-34)፡፡
      2) ይህ የ "መቅደስ" ዘይቤአዊ አጠቃቀም ነበር (ዮሐንስ 2፡19፤ ማቴ. 26፡61)፡፡
      3) ይህ የዕብራይስጥ የማወዳደሪያ ፈሊጥ ነው፡ "ጠላ" (ዘፍ. 29፡31፤ ዘዳ. 21፡15፤ ተሰ. 14፡36፤ ዮሐንስ 12፡25፤ ሮሜ. 9፡13)
      4) "ሁሉም" ወይም (በተቃርኖ) "ብዙ፡፡" ኢሳ. 53፡6 ("ሁሉም")ን ከ53፡11 እና 12 ("ብዙ") ጋር አነጻጽር፡ ፡ ቃላቶቹ እንደ ሮሜ. 5፡18 እና 19 እንደታየው ተመሳሳይነትን ያመለክታሉ፡፡
5. በነጠላ ቃል ምትክ ሙሉ ሐረጋዊ ቋንቋ መጠቀም፡፡ ምሳሌ፡ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡"
6. የስሞች፣ የቅጽሎች፣ የተውሳከ ግሦች (የርስ በርሱ) ልዩ አጠቃቀም
   ሀ. መስተአምሩ (ጠባያዊ ቦታ) ሲይዝ "አንድ ዓይነት" በሚል ይተረጎማል፡፡
   ለ. ያለ መስትአምር (በአንቀጹ ቦታ) ሲይዝ አረጋጋጭ አገናዛቢ ተውላጠ ስም በሚል ይተረጎማል– "ራሱ፣" "ራሷ፣" ወይም "ራሱ፡፡"

ሠ. *ግሪክኛ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ አጽንዖትን በተለያየ መንገድ ሊረዳ ይችላል፡*

1. በትንተናዊ *ቃላት* አጠ*ቃቀም*፣ ማለትም በግሪክኛውና በእንግሊዝኛው ጽሁፍ በየመስመሩ በተጻፈው።
2. የእንግሊዝኛን ትርጓሜዎች በማነጻጸር፣ በተለይም ከተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች አኳያ። ምሳሌ፡ "የቃል በቃል" ትርጓሜዎችን በማነጻጸር (ኪጀት፣ አኪጀት፣ አመት፣ አአሶመቅ፣ የተመት፡ አየተመት) ከ "ታደሰው አቻ" (ዊሊያምስ፣ አዓአት፣ አእመቅ፣ የተእመቅ፣ ኢበቅ፣ አኢመቅ፣ TEV ?እት)። ሻል ያለ ማብራሪያ ደግሞ *መጽሐፍ ቅዱስ በሃያ ስድስት ትርጉሞች* በቤከር የታተመው ላይ ይገኛል።
3. ባለ *አጽንዖታዊ መጽሐፍ ቅዱስ* በጆሴፍ ብራያንት ሮዘርሃም (ክሪገል፣ 1994)
4. የጥሬ ትርጉም አጠቃቀም
   ሀ. *የአሜሪካ መደበኛ ትርጉም* የ1901
   ለ. *ለወጣቶች ተስማሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም* በሮበርት ያንግ (ጋርዲያን አሳታሚ፣ 1976)።

ለተገቢ ትርጓሜ ሰዋሰዋዊ ጥናት አስፈላጊ ነው፣ አስቸጋሪ ቢሆንም። እነዚህ አጠር ያሉ መግለጫዎች፣ አስተያየቶች እና ምሳሌዎች የተፈለጉት ግሪክኛ አንባቢ ያልሆኑ ሰዎችን ለማበረታታትና በቅጹ ውስጥ የተመለከቱትን ሰዋሰዋዊ መግለጫዎች እንዲያገናዝቡ ነው። በርግጥ እነዚህ መግለጫዎች ቀለል ብለው ነው የቀረቡት። ቀኖናዊና ሊተጣጠፍ በማይችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም፤ ዳሩግን ወደ አዲስ ኪዳን አገባብ የተሻለ መረዳት የሚወስዱ ደረጃዎች ናቸው። እነዚህ መግለጫዎች አንባቢዎች የሌሎችን የጥናት መርጃዎች አስተያየቶችን ለምሳሌም፣ የአዲስ ኪዳን ስልታዊ ሐተታዎችን ለመረዳት ያስችሏቸዋል።

የራሳችንን ትርጓሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኛቸው ጽሑፎች ላይ በመመሥረት ልንመረምረው ይገባል። ሰዋሰው በጣም ከሚረዱን ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው፤ ሌሎች ዓይነቶች ደግሞ እንደ ታሪካዊ መቼት፣ ሥነጽሑፋዊ ጽሑፎች፣ የየዘመኑ የቃላት አጠቃቀም፣ እና አቻዊ አንቀጾች ይገኙበታል።

# ተጨማሪ መግለጫ ሁለት

# ጽሑፋዊ ትንተና

ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ መልኩ የቀረበው በዚህ ሐተታ ውስጥ የሚገኙትን ጽሑፋዊ ማስታወሻዎች ለማብራራት ነው:: ቀጣዩ ማውጫ ጥቅም ላይ ይውላል::

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   ለ. ሐዲስ ኪዳን
II. "የመለስተኛ ትንተና" ወይም "ጽሑፋዊ ትንተና" ተብሎ የሚጠራው ንድፈ- ሐሳባዊ ችግሮች አጭር ማብራሪያ
III. ለተጨማሪ ንባብ የተጠቀሱ ምንጮች

I. የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ጽሑፋዊ ምንጮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ማሶረቲክ ጽሑፍ (ማጽ) - የዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ የተቀናበረው በራቢ አቂባ በ100 ዓ.ም ነው:: አናባቢው የሚያመለክተው የአነጋገር ዘዬን፣ የህዳግ ማስታወሻዎችን ሥርዓተ- ነጥብ እና አስረጅ ነጥቦች ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም መካተት ተጀምሮ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የተጠናቀቀው ነው:: የተከናወነውም የአይሁድ ሊቃውንት ክፍል ከሆኑት ማሶራተስ በሚባሉት ነው:: የተጠቀሙበትም የጽሑፍ ዓይነት፣ በሚሽናህ፣ ታልሙድ፣ ታርጉምስ፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት አንድ ዓይነት ነው::
2. ሴፕቱዋጊንት (ሰባ) - ከባህል አኳያ ሴፕቱዋጊንት የተጻፈው በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ሲሆን በ70 ቀናት ለአሌክሳንደሪያ ቤተ-መጻሕፍት ሆኖ በንጉሥ ፕቶለሚ 2ኛ (285-246 ቅ.ል.ክ) ነው:: ትርጉሙ የተዘጋጀው ምናልባት በአሌክሳንደሪያ በሚኖሩ የአይሁድ መሪዎች ጥያቄ ሊሆን ይችላል:: ይህ ልምድ የመጣው፣ "ከአሪስታስ መልእክት" ነው:: ሰባ የተመሠረተው በተደጋጋሚ ከዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ባህል ከራቢ አቂባ (ማጽ) በተለየ መልኩ ነው::
3. የሙት ባሕር ጥቅሎች (ሙባጥ) - የሙት ባሕር ጥቅሎች የተጻፉት በሮማ ቅ.ል.ክ ባለው ጊዜ (200 ቅ.ል.ክ እስከ 70 ዓ.ም) ሲሆን በአይሁድ የተለዩ ክፍሎች በሆኑ "ኤሰንስ" በተባሉ ተለይዎች ነው:: የዕብራይስጥ የብራና ጽሑፎች የተገኙት፣ በሙት ባሕር አካባቢ በበርካታ ቦታዎች ሲሆን፣ ከሁለቱም ማለት ከማጽ እና ከሰባ በተለየ መልኩ የዕብራይስጥ ጽሑፋዊ ቤተሰብ ናቸው::
4. የእነዚህ ጽሑፎች ንጽጽር፣ ተርጓሚዎች ብሉይ ኪዳንን እንዲረዱት እንዴት እንደሚረዳ ጥቂት የተወሰኑ ምሳሌዎችን ስንመለከት
   ሀ. ሰባው ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሰባ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በእሱ</u> ይደነቁበታል::"
      (2) ማጽ በኢሳ. 52፡14፣ "ብዙዎች <u>በአንተ</u> ይገረሙ ነበር"
      (3) በኢሳ.52፡15 ተውላጠ ስሙ ልዩነቱ በሰባ ላይ ያለው ተረጋግጧል
         (ሀ) ሰባ፣ "ስለሆነም ብዙ ሕዝቦች በእሱ ይደነቁበታል"
         (ለ) ማጽ፣ "እሱ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል"
   ለ. ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ተርጓሚዎችንና ሊቃውንትን ማጽ (ማሲኒክ ጽሑፍ) ይገነዘቡ ዘንድ ረድተዋቸዋል
      (1) ሙባጥ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ነቢዩ ጮኸ፣ በቆምኩበት መጠመቂያው ማማ…"
      (2) ማጽ በኢሳ. 21፡8፣ "እናም ጨኸኩ አንበሳው! ጌታዬ፣ ሁልጊዜ በመጠበቂያው ማማ ላይ ቆሜያለሁ ቀኑን…"
   ሐ. ሁለቱም ሰባ እና ሙባጥ ኢሳ. 53፡11ን ለማብራራት ረድተዋል
      (1) ሰባ እና ሙባጥ፣ "ከነፍሱ መከራ በኋላ ብርሃንን ያያል፣ ይደሰታል"
      (2) ማጽ፣ "ያያል… ከነፍሱ መከራ በኋላ፣ ይደሰታል"

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ከ5,300 በላይ የእጅ ጽሑፎች ከግሪክ አዲስ ኪዳን በሙሉ ወይም በከፊል ጠፍተዋል:: 85 የሚሆኑት በፓፒረስ የተጻፉ ሲሆኑ 268 ደግሞ በቁም ጽሕፈት የተጻፉ የብራና ጽሑፎች ናቸው:: ቆይቶም፣ ወደ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ቅጥልጣይ ጽሑፍ እየተስፋፋ መጣ:: የግሪክ ጽሑፎች የተጻፉት በቁጥር 2700 ይሆናሉ:: በተጨማሪም 2100 የሚሆኑ ቅጂዎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ዝርዝር ለአምልኮ የሚሆኑ ሌክሽናሪስ ብለን የምንጠራቸው አሉ::
2. 85 የሚሆኑት የግሪክ የእጅ ጽሑፎች የአዲስ ኪዳንን የተወሰኑ ክፍሎች የያዙትና በፓፒረስ ላይ የተጻፉት ሙዝየሞች ውስጥ ተቀምጠዋል:: አንዳንዶቹ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ያስቆጥራሉ፣ ነገር ግን አብዛኞቹ የሦስተኛውና የአራተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ናቸው:: ከእነዚህ ጽሑፎች አንዳቸውም የተሟላ አዲስ ኪዳንን አልያዙም:: እነዚህ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ናቸው ማለት ግን በራሱ ጥቂት ልዩነት አላቸው ማለት

አይደለም። አብዛኞቹ የእነዚህ ቅጂዎች ለአካባቢው ጥቅም ይውሉ ዘንድ በችኮላ የተጻፉ ናቸው። በሂደቱ ላይ ጥንቃቄ አልነበረም። በመሆኑም ብዙ ልዩነቶች አሏቸው።

3. ኮዴክስ ሲናይቲከስ፣ በዕብራይስጥ ፊደል ( ) (አሌፍ) ወይም (01) በመባል የሚታወቀው፣ በቅዱስ ካተሪኒ ገዳም በሲና ተራራ በቲስቼንዶርፍ ተገኝቷል። ዓመቱም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም ሲሆን በውስጡም የብኪን ሰባ እና የግሪክን አኪ. ይዟል። እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው።
4. ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ፣ "ሀ" ወይም (02) በመባል የሚታወቀው፣ የ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተገኘው፣
5. ኮዴክስ ቫቲካነስ፣ "ለ" ወይም (03) በመባል የሚታወቀው፣ በሮም በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ሲሆን፣ ዓመቱም ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓ. ም እኩሌታ ነው። በውስጡም የብሉይ ኪዳን ሰባ እና የግሪክን አዲስ ኪዳን ይዟል። እሱም "የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ" ዓይነት ነው።
6. ኮዴክስ ኤፍራሚ፣ "ሐ" ወይም (04) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ በከፊል የተበላሸው፣
7. ኮዴክስ ቤዜ፣ "መ" ወይም (05) በመባል የሚታወቀው፣ የአምስተኛ ወይም የስድስተኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ነው። "የምዕራብ ጽሑፍ" ተብሎ ከሚጠራው ዋንኛው አስረጅ ነው። በውስጡም በርካታ ተጨማሪዎች የያዘ ሲሆን እንዲሁም ዋነኛው የግሪክ እማኝ ሆኖ በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ አገልግሏል።
8. የአኪ. MSS በሦስት ሊመደብ ይችላል፣ እንዲያውም በአራት፣ አንዳች ባሕርይ በሚጋሩ።

(ሀ) የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ ከግብፅ

(1) ገ$^{75}$፣ ገ$^{66}$ (200 ዓ.ም አካባቢ)፣ ወንጌላት የተጻፉበት
(2) ገ$^{46}$ (225 ዓ.ም አካባቢ)፣ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉበት
(3) ገ$^{72}$ (ከ225-250)፣ የጴጥሮስና የይሁዳ መልእክቶች የተጻፉበት
(4) ኮዴክስ ለ፣ ቫቲካነስ የሚባለው (325 ዓ.ም)፣ ሙሉውን ብኪ. እና አኪ. የያዘ
(5) ከዚህ የጽሑፍ ዓይነት የተጠቀሱ ምንጮች
(6) ሌሎች MSS የዚህን የጽሑፍ ዓይነት የሚያሳዩት ?፣ C፣ L፣ W፣ 33፣

(ለ) ከሰሜን አፍሪካ ምዕራባዊ ጽሑፍ

(1) ከሰሜን አፍሪካ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ተርቱሊያዊ፣ ሲሪያዊ፣ እንዲሁም የጥንታዊ ላቲን ትርጉሞች
(2) ከኤሪናዩስ የተጠቀሱ
(3) ከቲታን እና ከጥንታዊ ሲሪያ ትርጉሞች የተጠቀሱ
(4) ኮዴክስ መ "ቤዚ" የዚህን ጽሑፍ ጻይነት የሚከተል

(ሐ) ከኮንስታንቲኖፕል የምዕራብ ባይዛንታይን ጽሑፍ

(1) የዚህ ጽሑፍ ዓይነት ከ80% በላይ የሚሆነውን የ5300 MSS ያንጸባርቃሉ
(2) በአንቲሆች በሶርያ የቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሰ፣ ካፓዶቅያ፣ ክሪሶስቶም፣ እና ቴሮዶሬት
(3) ኮዴክስ ሀ፣ በወንጌላት ብቻ
(4) ኮዴክስ ሠ (ስምንተኛ ክፍለ ዘመን) ለሙሉ አኪ.

(መ) አራተኛው ሊሆን የሚችል ዓይነት "ቂሳሪያዊ" ከፓልስታይን

(1) በቅድሚያ የታየው በማርቆስ ብቻ ነው
(2) ጥቂት አስረጅዎች ገ$^{45}$ እና W

II. "የመለስተኛ ትንታኔ" ወይም "የጽሑፋዊ ትንታኔ" ንድፈ ሐሳባዊ ችግሮች

ሀ. ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ?

1. ሳይታወቅ ወይም በድንገት (አብዛኛው ሰፊ ክፍል የተፈጠረበት)
   ሀ. በዓይን የተፈጠረ ስህተት፣ ማለትም በእጅ በሚጻፍበት ጊዜ ሁለት ተመሳሳይ ፊደላት ላይና ታች መስመር ይዘው ሲመጡ ሁለተኛውን ጽፎ በመጀመሪያው መስመር ላይ ያሉትን ቃላት እንዳለ መግደፍ (ሆሞቲሉቶን)
      (1) የዓይን መሳሳት ጥንድ ቃላትን ወይም ሐረግ መግደፍ (ሀፕሎግራፊ)
      (2) የሐሳብ መሰረቅ ሐረግን ወይም መስመርን ሲደግሙ፣ የግሪክ ጽሑፍ (ዲቶግራፊ)
   ለ. የጆሮ ስህተት፣ በቃል ሲነገር በተጻፈ ወቅት የተሳሳተ ንባብ ሲቀርብ የሚፈጠር (ኢታሲዝም)። ብዙውን ጊዜ ይህ የተሳሳተ ንባብ ተመሳሳይ ድምፅ ባላቸው የግሪክ ቃላት ይፈጠራል።
   ሐ. የቀድሞዎቹ የግሪክ ጽሑፎች ምዕራፍም ሆነ የስድ ንባብ ክፍሎች አልነበራቸውም፣ ጥቂት ወይም ምንም ሥርዓተ ነጥብ ነበራቸው፣ በፊደልና ፊደል መካከልም ክፍተት አልነበረም። እናም መልእክቶቹን በተለያየ ቦታ መክፈልም ሆነ ሌሎች ቃላትን መመሥረት ይቻል ነበር።
2. ሆንተብሎ
   ሀ. የሚቀዳውን ጽሑፍ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ለማሻሻል ሲባል ይደረጉ የነበሩ ለውጦች

ለ. ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ጋር አረጋጋጭ እንዲሆኑ ይደረጉ የነበሩ ለውጦች (የአቻዎች ኅብር)

ሐ. ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ የተለያዩ ምንባቦችን ወደ አንድ ወጥ ጽሑፍ ለመቀየር ሲባል የተደረጉ ለውጦች፣ (ድብለቃ)

መ. በጽሑፉ ውስጥ ስህተት ያለ መስሎ ሲታሰብ ለማስተካከል የተደረጉ ለውጦች (1ኛ ቆሮ. 11:27 እና 1ኛ ዮሐንስ 5:7-8

ሠ. ከተጨማሪ መረጃ፣ ከታሪካዊ አቀማመጥ ወይም ከተገቢ ትርጓሜ አንጻር በአንድ ጸሐፊ የሰፈረ በግርጌ ማስታወሻ በሌለኛው ጸሐፊ ደግሞ በጽሑፉ ውስጥ እንዲካተት ሲደረግ (ዮሐንስ 5:4)

ለ. *የጽሑፋዊ ትንታኔ መሠረታዊ መርሖዎች* (በዋንኛው የጽሑፉ ንባብ ላይ ልዩነቶች ሲኖሩ ለመወሰን የሚሆን *አመክኖአዊ መመሪያ*)

1. በጣም አስቸጋሪው ወይም ሰዋሰዋዊ አገባቡ እንግዳ የሆነው ዋነኛው ጽሑፍ ሊሆን ይችላል
2. ቅልጥፍ ያለው ጽሑፍ ዋነኛው ሊሆን ይችላል
3. ከዋናው ጋር በታሪክ ይቀራረባል ስለሚሰጠው ብዙ ክብደት የሚሰጠው ለጥንታዊው ጽሑፍ ነው፣ ሌላው እኩል ሆኖ
4. MSS በመልክዓ ምድራዊ የሚለያዩት ብዙውን ጊዜ ዋነኛውን ምንባብ ይዘዋል
5. ደከም ያሉት የእምነት መግለጫዊ ጽሑፎች፣ በተለይም ከዋናዎቹ የሥነ-መለኮት ማብራሪያዎች ጋር የሚገናኙት የእጅ ጽሑፎቹ ጊዜ ሲለወጡ፣ እንደ ሥላሴ ያሉት ፣ በ1ኛ ዮሐንስ 5:7-8 የተመለከቱት ይመረጣሉ።
6. የዋናውን ጽሑፍ በተሻለ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ ሌሎች ጽሑፎች
7. እነዚህን አስቸጋሪ ልዩነቶች ሚዛን ለመጠበቅ የሚረዱ ማሳያ ሁለት ጥቅሶች

   *ሀ.* የጄ. ሃሮልድ ግሪንሊስ መጽሐፍ፣ *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣ "ማንኛውም የክርስቲያን መሠረተ እምነት በአከራካሪ ጽሑፍ መሆን የለበትም፤ የአኪ ተማሪም ጽሑፉ፣ ተመስጧዊ ከሆነው ከዋናው ጽሑፍ የተሻለ ቀጥተኛና ከመሠረተ እምነት አኳያ የጠነከረ እንደሆነ ከመፈለግ መጠበቅ ይኖርበታል"* (ገ. 68)

   ለ. ደብልዩ. ኤ. ክሪስዌል ለጌርግ *ጋሪሰን የበርሚንግሃም ኒውስ* ሲናገር እሱ (ክሪስዌል) የመጽሐፍ ቅዱስ *ቃላት ሁሉ ተመስጧዊ ናቸው ብሎ አያምንም፣ "ቢያንስ ቢያንስ ሁሉንም ቃላት ለዘመናዊው ሰው የቀረበው በምዕት ዓመታት ተርጓሚዎች" አለ ክሪስዌል፤ "በጽሑፋዊ ትንታኔ በጣም የማምን ነኝ። ይህ እንግዲህ፣ እንደማስበው፣ የማርቆስ 16ኛ ምዕራፍ የመጨረሻው አጋማሽ አጠራጣሪ ነው፤ ተመስጧዊ አይደለም፣ የተደባለቀ ፈጠራ ነው… እነዚያን የእጅ ጽሑፎች ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ብታነጻጽሩ እንደ ማርቆስ ወንጌል መደምደሚያ ያለ አታገኙም። አንዱ ጨምሮት ይሆናል።*

   *የበቁ* የSBC አባቶች እንደሚከራከሩት ከሆነ "ተጨማሪ" *ነገሮች መኖራቸውን በዮሐንስ* 5 *ያለው በቤተሳይዳ መጠመቂያ የኢየሱስ ሁኔታ ማስረጃ ነው። ሁለቱንም የተለያዩ የይሁዳን የራሱን መግደል ሁኔታዎች የገለጸበት* (ማቴ. 27 እና ሐዋ. 1)፡ *"ይህ የተለየ ዓይነት ራስን የመግደል ሁኔታ ነው፣" ይላል ክሪስዌል። "በመጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ፣ ለዚህ መግለጫ በኖረው ነበር። እናም ሁለቱ የይሁዳ ራሱን የመግደል ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፣" ክሪስዌል ጨምሮም፣ " ጽሑፋዊ ትንታኔ በራሱ አስደናቂ ጥበብ ነው። ጊዜያዊ አይደለም። ተዳፋሪነትም አይደለም። በእንቅስቃሴ ላይ ያለና ማዕከላዊ ነው…"*

III. የእጅ ጽሑፍ ችግሮች (ጽሑፋዊ ትንታኔ)

*ሀ.* ለተጨማሪ የንባብ ምንጮች ጥቆማ

1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ፡ ታሪካዊ፣ ሥነጽሑፋዊ እና ጽሑፋዊ፣* በአር. ኤች. ሃሪሰን
2. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ፡ አስተላለፉ፣ ጥፋቱ እና ዳግም መመለሱ* በብሩስ ኤም. ሜዝገር
3. *የአዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ትንታኔ መግቢያ፣* በጄ. ኤች ግሪንሊ

# ተጨማሪ መግለጫ ሶስት

# የቃላት ፍቺ

**ልጅነት መወከል፦** ይህ ጥንት የነበረ አስተሳሰብ ሲሆን ኢየሱስ ከመለኮታዊነት ጋር የነበረውን ህግኙነት ያጣቅሳል። ፅንሰ ሃሰቡ መሰረት የሚያደርገው ኢየሱስ በማንኛውም መንገድ ሰው ሲሆን ልጅነትን ያገኘው በእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ማለትም በጥምቀቱ /በማቴ 3፡17፤ ማርቆስ 1፡11/ ወይም /በሮሜ 1፡4/ በተመለከተው መሰረት ነው። ኢየሱስ ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ በዚህ ዓይነት እንደኖረ እግዚአብሔርም በአንዳንድ ሁነቶች /በጥምቀትና በትንሳኤ/ እንደ ገዛ ልጁ እንደሆነው /ሮሜ 1፡4 ፊሊጵ 2፡9/ በተመለከተው መሰረት ያሳያል። ይህ የእምነት መግለጫ በ8ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የአናሴ ቤተ-ክርስቲያን ጥስታዊ አስተሳሰብ የነበረ ነው። አምለሰክ ሰው ሆነ /ስጋዌ/ ከማመልከት ይልቅ ገለባብጦ ሰው እንዴት አምላክ እንደሆነ ያመላክታል።

ኢየሱስ አምላክ የሆነው ወለድ ቀድሞ መለኮት ምሳሌያዊ ሕይወት በመኖሩ እግዚአብሔር አከበረው ብሎ በቃላት ለማስረዳት ይቸግራል። እሱ ከቀድሞ ጀምሮ አምላክ ከሆነ እንዴት ክብርን ይሸለማል? እሱስ ቀድሞ የነበረ መለኮታዊ ክብር እያለው እንዴት ተጨማሪ ክብር ይሰጠዋል? እርግጥ ይህን ልንደርስበት በርግጥ ይቸግረናል፤ ማለትም አብ ኢየሱስን በተለየ መልኩ የአባቱን ፍቃድ በመፈጸሙ መከበሩን ለማሳየት ይሆናል።

**የአሌክሳዳሪያ አስተምህሮት፦** ይህ ዓይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ አግባብ በግብፅ አሌክሳንደሪያ በ2ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ ነው። መነሻ ያደረገውን መሰረታዊውን ፊሎአዊ የፍቺ መርህ ተከታይ የሆነው ጀሎን ያመላክታል። ተምሳሌታዊ ዘዴ በመባል የታወቃል። እስከ ተሃድሶ ዘመን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሲሰራበት ኖሯል። የተርጓሚው ሊቃውንት ሲረገንና አውስጢኖስ ናቸው። /ለተጨማሪ መረጃ የMoises Silva "ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን አሳስታ ተርጉማው ይሆን?" የሚለውን አንብብ /1987 ዓ.ም/።

**አሌክሳዳሪያ፦** ይህ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በአሌክሳዳሪያ የተገኘ የግሪክ /ቅርፅ/ የብራና ፅሑፍ ሲሆን፣ በውስጡም ብሉይ ኪዳን፣ የራዕይና አብዛኛውን ሐዲስ ኪዳን ያካተተ ነው። ፅሁፉ የግሪኩን አዲስ ኪዳን ቅጂ በተመለከተ ዋናኛው ማጣቀሻ ነው። /ከማቴዎስ፣ ከዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ክፍሎች እና ከሁለተኛ ቆሮንቶስ በቀር/ይህ ጽሑፍ ማለትም ልዩ ስሙ "ሀ" የተባለውና የቫቲካሉ ጽሑፍ ልዩ ስሙ "ለ" የተባለው በንባብ ላይ ሲሰማ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች አማካኝነት በብዙ አገባቦች እንደ ዋነኛ ተደርገው ይወሰዳሉ።

**ተምሳሌታዊ፦** ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በመጀመሪያ የተስፋፋው በአሌክሳንደሪያ የአይሁድ እምነት ነው። እያገነነ የመጣው በአሌክሳንደሪያው ፊሎ ነው። የመሰረታዊ እምነቱም ፍላጎት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደየሰው ባህል፣ ፍልስፍናና ስርዓት በማጣጣም የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ መቼት /ቦታና ጊዜ/ ስነጽሁፋዊ ይዘት በመተው ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የተሸሸጉትን እያንዳንዳቸውን ትርጓሜዎች በመመርመር ላይ ያተኩራል። ኢየሱስ በማቴስ 13 እንዲሁም ጳውሎስ በገላትያ 4 እውነትን ለመግለጽ የተጠቀሙበትን ተምሳሌት ያመላክታው። ዳሩ ግን ይህ ተምሳሌታዊ ሳይሆን ጽሑፋዊ መልክ የያዘ ነው።

**ስርወቃላዊ ትንታኔ፦** ይህ አንደኛው የምርምር ዘዴ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን የግሪክ ስርወ ቃላት ለመለየት ይረዳል። በግሪክ የፊደል ተራ መሰረት ቅርጹና ዋናው መግለጫ /ትርጓሜ/ የያዘ ነው። ግሪክኛን ለሚያነሱ አማኞች ሰዩ ትርጓሜ አያይዞ በማስቀመጥ የግሪክን የሐዲስ ኪዳን ሰዋሰውና ስነጽሑፋዊ አገባብ ለመረዳት ያስችላል።

**የቅዱሳት መጻሕፍት ተመሳስሎ፦** ይህ ሐረግ ለማስረዳት የሚሻው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና እርስ በርሱ የሚቃረን ሳይሆን የሚደጋገፍ እንደሆነ ለማመላከት ነው።

ይህ አይነቱ በውል የተቀመረ አቀራረብ ቃሉን መሰረታዊ በሆነ መልኩ በንጽጽር በማስቀመጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ይተረጉማል።

**አሻሚ ትርጓሜ፦** ይህ የሚያመላክተው አሻሚ ትርጓሜ ያላቸውን የጽሑፍ ሰነዶችን ሲሆን ሁለትና ከዚያም በላይ ፍቺ ሲኖር፤ ወይም ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ነገሮች በአንድ ጊዜ በማጣቀሻነት ሲቀርቡ የሚከሰት ነው። ዮሐንስ ሆን ብሎ በዚህ ዘዴ ተጠቅሟል /ማለትም በእጥፍ አገባብ/

**ሰዋዊ ምዕላድ፤** ይህ አይነቱ ፍቺ ከሰው ልጆች ጋር የተያያዘውን ሲማመላክት ጥሬ ቃሉም ሃይማኖታዊ ቋንቋዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቁርኝት ነው። ስርወ ቃሉ ከግሪክኛ የመጣ ሲሆን የሰው ልጅ ማለት ነው። ፍቺውም እኛ ስለ እግዚአብሔር የምንናገረው በሰውኛ ዘይቤ ማለት ነው። እግዚአብሔር በአካላዊ፣ በማህበረሰባዊ፣ በስለልቦናዊ ቃላት ከሰው ልጆች ጋር በተጓዳኝ /ዘፍ 34፤ 1ኛ ነገስት 22፡19-23/ እንደተጻፈው ሲነገር ማለት ነው። እርግጥ ይሄ ተመሳስሎ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ከሰው ልጆች በቀር ልንጠቀምበት የምልኝልበት ምድብ ወይም ቃል የለም። ስለሆነም ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት እውነትን ተንተርሶ ውስንነት እንዳለው ያመላክታል።

**የአንቲሆች አስተምህሮት**፡- ይህ አይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ዘዴ በአንቲሆች ሶሪያ በ3ኛው ክፍለ ዘመን የተንሰራፋ ሲሆን የአሌክሳንደሪያ ግብጽን ተምሳሌታዊ ዘዴ የሚቃረን ነው። መሰረታዊ እምነቱን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ትርጓሜ ላይ ያተኩራል። መጽሐፍ ቅዱስን እንደማንኛውም የሰው ልጆች ስነጽሑፍ ይተረጉማል። ይህ አስተምህሮት ከክርስቶስ ክልዔ /ሁለት/ ባሕርይ አለው ከሚለው /ንስጥሮሳዊ/ አስተምህሮትና ወይም ደግሞ አንድ ባሕርይ አለው /ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው/ ከሚለው አስተምህሮት መሐል በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ኂላም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተነቅፎ እንደመናፍቅ ስለተወሰደ ወደ ፋርስ ሊሄድና ድጋሚ ሊቋቋም ቢሞክርም ውል ያለው አቋም ሳይዝ ቀርቷል። መሰረታዊ የአተረጓም መርሆቹ ግን ለትርጓሜ አግባብ ይሆኑ ዘንድ ለሉተርፐ ለካልቪን የፕሮቴስታንት የተሀድሶ አራማጆች ጥቅም ላይ ሊውል ችሏል።

**አንቲቴትካል**፡- ከሶስቱ አንደኛው ዓይነት ገላጭ ጽሑፋዊ ዘዴ ሲሆን የእብራይስጥን የቅኔ ሐረጎች ተዛምዶ ያመላክታል። ፍቺያቸው የማይገጣጠሙትን የቅኔ ሐረጎች/ዘውጎች ተዛምዷቸውን ይመለከታል/ምሳሌ 10፡1፤15፡1/።

**ራዕያዊ ስነጽሑፍ**፡- ይህ በአብዛኛው፤ በተለየ መልኩ የአይሁድ የስነጽሑፍ ዘውግ ነው። ይህ ዓይነቱ ምስጢራዊ ጽሑፍ ከአዩዳውያን በውጭ ኃያላት ይወረሩና ሲገዙ የሚዘወተር ነው። በጽሑፉ ይዘትም እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ፣ ሙላዋ የሱ እንደሆነችና መበገቴት እንደሚችሉ አመላክቶ ለእስራኤልም የተለየ ዓላማ እንደሚጠነቀቅለት ያሳያል። ስነ ጽሑፉ የመጨረሻው ድል የሚገኘው በእግዚአብሔት ልዩ ክንድ እነደሆነ አጽንዖት ይሰጣል።

ጽሑፉ በጣም ተምሳሌታዊና ምስል ከሳች ምስጢራዊ ቃላት ይበዙበታል። ብዙውን ጊዜ እውነትን በቀለማት በቁጥሮች በምስል ከሳች ሁኔታ በሕልሞች በመላእክታዊ ክስታ በምስጢራዊ ቃላት የሚገለጽ ሆኖ ጊዜ በሰናይና በክፉ መሐል በመንታዊ ሰይፉ ከፍሎ ያልፋል።

የዚህ ዘውግ አነዳንድ ምሳሌዎች 1ኛ በብሉይ ኪዳን ሕዝቅኤል/36-48/ ዳንኤል /ምዕ 7-12/ ዘካሪያስ እና ዘርፍ ሲሆን ደግሞ ማቴ 2 ማር 13 2ኛ ተሰሎ 2 እና ራዕይ ናቸው።

**አፖሎጅስት**፡- ይህ የግሪክ ስርወ ቃል ሕጋዊ ተከላካይ የሚል ነው። ከስነ-መለኮት አንደኛው የትምህርት ንዑስ ዘርፍ ሲሆን ለክርስትና እምነት ተገቢ የመከራከሪያ ማስረጃና አመክኗዊ የክርክር አግባብን ይቀምራል።

**ቀዳማይ**፡- ይህ ቃል ቀደም ሲል ከተሄደበት አግባብ ጋር ጥብቅ መሰረታዊ ቁርኝት ያለው ነው። የሐሳብ አወራረዱም ቀደም ሲል ከወጡትና ከተቀበልናቸው ትርጓሜዎች መርሆች ወይም አቋሞች በመመስረት እንደ እውነት በመቀበል መቀጠል ነው። ያለ ምንም ተጨማሪ ምርምርና ትንታኔ የምንቀበላቸውን ማለት ነው።

**አርዮሳዊነት**፡- አርዮስ በአሌምሳንደሪያ ግብፅ ፕሬስቤታሪያን ቤተ-ክርስትያን በ3ኛ እና በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረ ነው። አጽንዖት ሰጥቶ የሚከራከረው ምሳሌ 8፡22-31 ያለውን ቃል ሲሆን እየሱስ ቀድሞ እንደነበረ ቢቀበልም መለኮትነቱ ክዷል። /ከአብ ጋር መስተካከል የለበትም ባይ ነው።/ ከአሌክሳንደሪያው ጳጳስ ተቋውሞ የገጠመው ሲሆን ይህም ከ318 ዓ.ም አንስቶ ለብዙ ዓመታት የቆየ ክርክር ነው። አርዮሳዊነት በተለይ የምስራቅ ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነት ተደርጎ ተወስዶ ነበር። በ325 ዓ.ም በአቅያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት አርዮስን አውግዘውና ነቅፈው ተወልድን የተካከለ መለኮትነት አጽንተዋል።

**አርስጣጣሊስ**፡- የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ ሲሆን የፕላቶ ተማሪና የታለቁ እስክስድር /አሌክሳንደር መምህር ነው። የሱ ተጽዕኖ እስካሁን ድረስ በዘመናዊው ጥናትና አስተምህሮት ላይ የጸና ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በማስተዋልና ምደባዊ ፊር በያዘ የማስተማር። ስልት አጽንዖት በመስጠቱ ነው። ይህም አንደኛው የሳይንሳዊ ምርምር ዘዴ እንደሆነ ይታወቃል።

**አውቶግራፐር**፡- ይህ ለጥናታዊውና ወጥ ለሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች የተሰጠ ስያሜ ነው። እነዚህ ጥንታዊ ወጥ የብራና ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። የቅጂ ቅጂ ብቻ ነው ያለው ይህም የጽሑፋዊ ይዘት ልዩነቶችን በዕብራይስጥና በግሪክ የብራና ጥንታዊ ጽሑፎች መሐል ሲፈጥር ችሏል።

**ቤዛ**፡- ይህ የ6ኛው ክፍለ ዘመን የግሪክና የላቲን ጽሑፍ ነው። የሚል መለያ ሲኖረው ወንጎላትንና ግብረ-ሐዋርያትን እንዲሁም አንዳንድ መልዕክቶችን አካቷል። ከዚህም በላይ ሌሎት በርካታ ስንክሳሮችን /ጽሑፎችን/ ይዟል። በኪንግጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ወስጥ መካተት ስላለባቸው መሰተር ጥሏል። /እንደ መነሻ ሆኗል።

**አድልዖ**፡- ይህ ቃል የሚያመለክተው በአንድ ነገር ወይም አመለካከት ላይ ቀደም ተብሎ የተያዘ አድሏዊ ግትር አቋምን ነው። አእምሮ በአንድ ነገር ከተያዘ ማድላቱ የማይቀር መሆኑል ያሳያል። ቀደም ብሎ የተያዘ ፍርደ-ገምድላዊ አቋምን ያመላክታል።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት**፡- ይህ ቃል በተለተ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ይህም ማለት የመጀመሪያው ፀሐፊ በዘመኑ ምን ለማለት እንደፈለገና አሁን በዘመናችን በምን መልኩ ተግባራዊ እንደምናደርገው ያለውን ያካትታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ቃሉን ስልጣናዊ መመሪያ አድርጎ መውሰድ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ የትርጓሜ መዛባት እንዳይከሰት የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ በታሪካዊና በሰዋሰዋዊ ዘዴ ብቻ መወሰኑ ይበቃል፡፡

**ደንብ**፡- ይህ ቃል በተለይ ተመስጧዊ በሆነ ሁኔታ በተመስጧዊ የሆኑትን ጽሑፎች ይመለከታል፡፡ ይህም ሁለቱንም የብሉይና የሐዲስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያካትታል፡፡

**ማዕከለ ክርስቶስ**፡- ይህ ቃል የኢየሱስን ማዕከላዊነት ያመላክታል፡፡ ቃሉን ለመጠቀም የተፈለገው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጌትነቱን የሚያሳየውን ጽንሰ ሐሳብ ለማሳየት ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን ወደ እሱ አመላካች ነው፡፡ እሱም የቃሉ ፍጻሜና ግብ ነው /ማቴ 5፡17-48/

**ሐተታ ትርጓሜ**፡- ይህ የተለየ ዓይነት የሐተታ መጽሐፍ ነው፡፡ ለመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ዳራ ያስነብባል፡፡ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ክፍልን ትርጓሜ ለመስጠት ይሞክራል አንዳንዶች በተግባራዊ አያያዝ ላይ ሲያተኩሩ ሌሎች ደግሞ በጽሑፍ ቴክኒካዊ አግባብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት በጣም ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ዳሩ ግን ከእነሱ በፊት አጥኚው ግለሰብ የራሱን ጥናት መካሄድ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት ሐተታዎችን መቀበል የሚገባው በወል መርምሮ መሆን ይገባል፡፡ ለዚሁም የተለያዩ ትርጓሜዎችን ከተለያየ ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶች አቋም አኳያ መመልከቱ ተመራጭ ነው፡፡ ቃላት ዝርዝር ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምርምራዊ መጽሐፍ ነው፡፡ በብሉይም ሆነ በሐዲስ ያሉትን ቃላት ሁሉ በየአገባባቸው በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ በብቁ መንገድ እገዛ ያደርጋል፡፡ 1/ እያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቃል ምነ መሆን እንዳለበት ከዕብራይስትና ከጽርዕ/ግሪክ/ እንደሆነ ያመላክታል 2/አንቀጾችን በማነጻጸር የመሳሳይ የሆነ የግሪክ ወይም የዕብራይስጥ ቃል ጥቅም ላይ መዋሉን ለማወቅ ያስችላል፡፡ 3/ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ቃላት በተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ቃል ተርጉመው እንደሆነ ያመላክታል፡፡ 4/ቃላቶች በምን ያህል ድግግሞሽ በየትኞቹ መጻሕፍትና ጸሐፋት እነደተፈረጉ ያሳያል፡፡ 5/ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተጠቀሰው ቃል አመላካች የሆነ አንቀፃ ያሳያል /ዋልተር ክላርክ የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ እንዴት ጥቅም ላይ እነደዋለ የጥናት መረጃ መጽሐፍ ገጽ 54-55፡፡

**የሙት ባሕር ጥቅሎች**፡- ይህ የሚያመለክተው የጥንታዊ ጽሑፍ ጥቅሎች የሆኑ በዕብራይስጥና በአረሚክ የተፃፉ ሙት ባሕር አጠገብ በ1947 የተገኙትን መጻሕፍትን ነው፡፡ እናዚህ ጥቅሎች ሃይማኖታዊ ቤተ-መጽሐፍት ሲሆኑ የይሁዳነት ክፍል የሆኑ በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ነው፡፡ የሮማ የግዛት መስፋፋትና በ60ዎቹ የተካሄዱት የቀናኢነት ውጊያዎች ገዳም በመሰሉና በዋሻዎች ውስጥ በሸክላ ታሽገው እንዲቀመጡ እንዳስገደደ ይገመታል፡፡ ጥቅሎች የ1ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጤምን ታሪካዊ መቼቶችን እንድንገነዘብና ማሰራዊ ጽሑፎች የሚባሉትን ትክክለኛነት እንድንረዳ /ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን/ አስችለውናል፡፡ በአድሕሮት በመባል ይታወቃሉ /ሙ/ባ/ጥ/ የሙት ባሕር ጥቅሎች፡፡

**ዲዳክተር**፡- ይህ አይነቱ ተአመክንዮ አገባብ ከአጠቃላይ መርሕ ተነስቶ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ የሚገባ ሎጂካዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ከአንደክቲቭ አስተሳሰብ ተቃራኒ ነው፡፡ ማለትም ሳይንሳዊ የሆነውን ከዝርዝር አስተውሎች በመነሳው ወደ አጠቃላይ ንድፈ ሃሳብ የሚያደርሰውን፡፡

**ዲያሌክቲካዊ**፡- ይህ አይነቱ የአስተሳሰብ ዘዴ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች ያስቀምጥና /አይዎ/ በሁለቱም በኩል ያለውን ተቃርኖና ተዛምዶ የሚመረምር ነው፡፡ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቶች ዲያሌክታካዊ ጥንዶች አሏቸው፡፡ ለአብነትም ቀድሞ የተወሰነና - ነጻ ፍቃድ ደሕንነት - ጥረት እምነት ስራ ውሳኔ ስርዓታዊት ክርስትያናዊ ነጻነት ክርስትያናዊ ሐላፊነት፡፡

**ዲያስፖራ**፡- ይህ ቃል የግሪክ ሲሆን ከነዓናዊ አይሁዶች አገራቸው ውጭ ያሉትን ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከተስፋይቱ ምድ ዳርቻ ወጭ የሚኖሩትን አይሁዳውያን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ነው፡፡

**ፍጹማዊ አቻነት**፡- ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጓሜ ሐሳብ ሲሆን ትርጓሜዎቹም ቃል በቃል አቻ እና አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዕብራይስጥም ሆነ ከግሪክ አቻውን አግኝተው መተርጎም የሚገባው ሲሆን ይህ ከልሆነም በሐረግ መልክ ሐሳብ በጥንቃቄ ከምንጩ ሳይዛባ እንዲተረጎም ይደረጋል፡፡ በእነዚህ ሁለት ንድፈ ሐሳቦች መሐል ፍጹማዊ አቻነት መነሻ ጽሑፉን አተኩሮ ይዚ በዘመናዊ ሰዋሰውና ፈሊጥ መተርጎም ይኖርበታል ይላል፡፡ የእነዚህ የትርጓሜ ንድፈ ሐሳቦች ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱሳን እንዴት በመረዳት እናንብብ ገጽ 35 በሚለው ሰፊ እና ስታዋርት መጽሐፍ ላይ /ሮበርት ባራቸር/ መግቢያ በሰጡበት እናገኘዋለን፡፡

**ኤሌክቲክ**፡- ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የመጽሐፉን ቅኝት ለማከናወን ብቻ ነው፡፡ ጠቀሜታውም የተለያዩ ንባቦችን ከግሪክ ጽሑፎች ውስጥ በመምረጥና በመመርመር ዋነኛውን ወጥ ጽሑፍ ጋር ለመድረስ የሚያስችል ነው፡፡ ከግሪክ ጽሑፎች መሐከልም ዋነኛውን ተንተርሰው በግል አስተያየት መልክ የተሰጡትን አይቀበልም፡፡

**ኤሲጀሲስ፡-** ይህ የኤክሰሳይስ ተቃራኒ ነው። ማለትም ኤክሲጂሰሲ ከዋነኛው ጸሓፊ ሐሳብ ያፈነገጠ /የወጣ/ ከሆነ ኤሲጀሲስ ደግሞ ባዕድ ሐሳብ ወይም አስተያየት ውስጥ ማጨቅን/በብዛት መግባትን ማስገባትን/ ይመለከታል።

**ስርወቃል፡-** ይህ የስርወ ቃላት የማጥኛ ዘዴ ሆኖ መነሻው ከምን እንደሆነ ይመረምራል። ከቃሉ ስር ፍቺ በመነሳትም ቃሉ እንዴት እቅም ላይ እነደዋለ ለማወቅ ያስችላል። በትርጓሜ ጊዜ ግን ኢቲሞለጂ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ አይደለም። አወዳዊ ፍቺና የቃሉ አገባብ ነው የሚተኮርበት።

**ኤክሰጀሲስ፡-** የተወሰነ አንቀጽን ለመተርጎም የሚውል ቃል ነው። ይህም ማለት ከጽሑፉ ወጣ ባለ መልኩ በመርመር የዋነኛ ጸሐፊውን ሃሳብ ለመረዳት የሚያስችል ነው። ከታሪካዊ ዳራና መቼት /መቼ እና የት/ ስነ ጽሑፋዊ ፈርጅ ለዋሰውና ወቅታዊ የቃሉን ፍቺ ይቃኛል።

**ዣነ፡-** የፈረንሳይ ቃል ሲሆን የተለያዩ የስነጽሑፍ ዘውጎች ማለት ነው። ተመሳሳይነት ያላቸውን የስነጽሑፍ ዓይነቶች አንድ ላይ ይመድባቸዋል። ለምሳሌም ታሪካዊ ትረካ ቅኔ ምሳሌ ትንቢታዊ /ምስል ከሳች/ ሕጋዊ ይገኙበታል።

**ግኖስቲስዝም፡-** ስለዚህ ጉዳይ ያለን እውቀት የሚመነጨው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩይ የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት የግኖስጢክ ጽሑፎች ሲሆን አስተሳሰቡ ግን ከ1ኛው ክፍለ ዘመን ወይም ቀደም ሲል የነበረ ነው።

አንዳንዶች እንደሚሉት የቫለንታይን እና የቀረንታይን የ2ኛው ዘመን ግኖስጢስ 1/ቁስ አካልና መንፈስ ዘላለማዊ ሲሆኑ አንድነትም ምንታኤም /ሁለትነትም/ ይዘው። ቁስ አካል ክፉ ሲሆን መንፈስ ግን ሰናይ ነው። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በቀጥታ ክፉ ነገርን በማበጀት ውስጥ አይገባም። 2/በእግዚአብሔርና በቁስ አካል መካከል የረጅም ጊዜ ወይም የመላዕክታዊ ደረጃ አለ። የመጨረሻው ወይም ዝቅተኛው ያህዌህ? /YHWH/ ሲሆን አለማትን የመሰረተ ነው። አንዳንዶች ከፍተኛ አድርገው በመመስጥ ከእግዚአብሔር ያነሰ /በመለኮትነቱ ሳይሆን/ የሰው አካል ለብሶ መለኮት ሊሆን አይቻለውም። እሱ መንፈስ ነው 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3 4፡1-6 /እና 4/ ደሕንነት ሊገኝ የሚችለው በኢየሱ በማመንና የተለያየ እውቀት በማግኘት ይህም ልዩ እውቀት በልዩ ሰዎች የሚታወቅ ነው። እውቀት /የማለፊያ ቃል/ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ያስፈልጋል። የአይሁድ የሕግ እውቀትም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ይህ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ።

የግኖስቲክስ የሀሰት መምህራን ሁለት ዓይነት ስነ ምግባራዊ ተጻራሪ ስርዓቶች ያስቀምጣሉ። 1/ለአንዳንዶች የአኗኗር ስርዓት /ዘዬ/ ከደሕንነት ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የለውም። ለእነሱ ደሕንነትና መንፈሳዊነት ምስጢራዊ እውቀት /የማለፊያ ቃል/ በሚሰለው የተጎዳኘ በመላዕክት ክልል ነው ይላሉ። ወይም 2/ለሌሎች ደግሞ የአኗኗር ስርዓት በደሕንነት ላይ ትልቁ ነጥብ ነው። ለተሻለ የሕይወት ዘይቤም አጽንኦን በመስጠት ለእውነተኛ መንፈሳዊነት በማስረጃ ያቀርባሉ።

**ሄርሜኒዩኒክስ፡-** ቴክኒካዊ ቃል ሲሆን ለ ኤክሴጂሲስ እንደ መርሕ ያገለግላል። ሁለትዮሽ የሆነ የተወሰነ መመሪያና ተሰጧዊ ጥበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም የተቀደሰ በሚል ሄርሜሊዮኒክስ በሁለት ምድብ ማለትም፡- አጠቃላይ መርህና ዝርዝር መርሆች በሚል። ይህም ከተለያዩ መከጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ስነ ጽሑፎች ጋር ይዛመዳል። እያንዳንዱ የተለየ የስነጽሑፍ ዘውግ የየራሱ የተለየ መመሪያ ያለው ሲሆን ከሌሎች ጋር ደግሞ ግምቶችንና የትርጓሜ አገባቦችን ይጋራል።

**ኃየር ክርቲዝም፡-** ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የትርጓሜ አገባብ /ደንብ/ ሲሆን አተኩሮቱም በአንድ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሓፍ ላው በታሪካዊ መቼትና በስነጽሑፋዊ መዋቅር ላይ ነው።

**ፈሊጥ፡-** ይህ ሐረግ የተለያዩ ባህሎችን ተንተርሶ ከዋናው ቃል ትርጉም ጋር ያልተያዘ ትርጉም የሚሰጥ ነው። አንዳንድ ዘናዋ ምሳሌዎች፤ የመጥፎ ጥሩ ነው ገደልከኝ የሚሉ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስም የዚይ ተመሳሳይ የሆኑ ሐረጎች አሉት።

**ማብራሪያ፡-** ይህ ስያሜ የተሰጠው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መናገሩን ለማመልከት ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ የሚገልጸው በሶስት መልክ ነው። 1/ራዕይ እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ፡- ለድርጊቱ ተገቢ የሆነ ትርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ በማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ ማድረጉ 3/ማብራሪያ፡- መንፈሱን ለሰው ልጆች በሰጡት ስለ እሱ እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻሉ።

**ኢንዳክራቭ፡-** የሎጂክ አንዱ ዘዴ ሲሆን ከዝርዝር ነገሮች ተነስቶ ወደ አጠቃላይ የሚተነትን ነው። ለዘመናዊው ሳይንስ በተግባር ዘዴ በመሆን በማገልገል ላይ ነው። ዘዴው በመሰረቱ የአርስቶትል ነው።

**ኢንተርላይነር፡-** ይህ የምርምር መሳሪያ ዘዴ ዓይነት ሲሆን የመጽሓፍ ቅዱስን ቋንቋ የሚያነቡትን እንዲተነትኑና ፍቺውንና መዋቅሩን እንዲረዱ ያስችላል። የእንግሊዝኛውን ትርጉም ቃል በቃል በማስቀመጥ ከዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ

ጋር አነጻጽሮ ያስቀምጣል። ይህ የምርምር አግባብ ትንተናዊ ስርወቃልን በመደባለቅ ለሰው ልጆች የተናገረው መሰረታዊ ለሆኑት የዕብራይስጥና ግሪክ ፍችዎች መልክ ይሰጣል።

**ተመስጦ**:- ይህ ጽንሰ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረው የመጽሐፍ ቅዱስን በጸሐፍት በትክክልና በግልጽ መገለጡን እንዲያፍሩ ነው። ሙሉ ጽንሰ ሐሳቡ በሶስት መልኩ ይገለጻል።
1/መገለጥ /ራዕይ/ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ መስራቱ 2/ ተመስጦ ለድርጊቱ ተገቢ ይርጓሜ እና ፍቺ ለተመረጡ ሰዎች በተመስጦ ለማስታወቅ መዝግበው ለሰው ልጅ እንዲያስተላልፉ 3/ ብርሃነ /ማብራሪያ/ መንፈሱን ለሰው ልጆች በመስጠት እሱ ሽሽግነት እንዲያውቁና እንዲያስተውሉ ማስቻል።

**የገለጻ ቋንቋ**:- ይህ ብሉይ ኪዳን የተጻፈውንና ፊሊጦቹን ለማገናኘት ታስቦ ነው። እሱም የዓለማችንን የአበጋገር አግባብ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት በማስመርኮዝ ያቀርባል። ሳይንሳዊ ገለፃ ማለት ግን አይደለም።

**ሕጋዊነት**:- ይህ አዝማሚያ የሚያመለክተው ለሕግጋትና ለክብረ በዓላዊ አምልኮተ ስነስርዓት አፅንኦት የመሰጡትን ነው። የሰው ልጆች የሚያደርጉትን ደንቦችና ስርዓቶች እግዚአብሔር ይቀነለዋል ብሎ መወሰን ነው። ግንኙነትን ዝቅ የሚያደርግና ክዋኔዎችን ከር የሚያደርግ ሆኖ ሁለቱንም ኪዳናዊ ግንኙነቶች /በቅዱሱ በእግዚአብሔርና በኃጢያተኛው ሰውነት እንደሚካሀወድ ያስምጣል።

**ጽሑፋዊ ፍቺ**:- ይህ የጽሑፋዊ ፍቺ ላይ የሚያተኩር እና ታሪካዊ የአተረጓጎም ዘዴ የሆነውን የአንቲሆችን ባህል ይከተላል። ይህም ማለት ትርጓሜ መያዝ ያለበት ተራ ወኔና ግልጽ የሆነውን ፍቺ በሰው ልጆች ቋንቋ እንዳለ ነው ይላል። ይህም ማለት ግን በተምሳሌታዊ ቋንቋ የተጻፉ ክፍሎች መኖራቸውን አይክድም።

**ጽሑፋዊ ዘውግ /ክፍል**:- ይህ የሰው ልጆች መግባቢያ የሆነ የጽሑፍ ክፍሎችን ማለትም ቅኔ ታሪካዊ ትረካ የመሳሰሉትን ያካትታል። እያንዳንዱ ዓይነት ስነ ጽሑፍ የየራሱ የትርጓሜ አገባብ ሲኖረው በተጨማሪም ለሁሉም የስነ ጽሑፍ መርሖችን ይከተላል።

**ጽሑፋዊ አሃድ**:- ይህ የሚያመለክተው ዋነኞቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ያስተሳሰብ ክፍሎችን ነው። ይህም በጥቂት ምንባቦች አንቀጾች ወይም ምዕራፎች ሊዘጋጅ ይችላል። በየራሱ ሙሉ የሆነና ማዕከላዊ የጽሑፍ ዓይነት የያዘ ነው።

**ሎወር ክርቲዝም**:- /ቴክስቲወሐነ ክርትዝም/ ተመልከት የእጅ ጽሑፍ /የብራና ጽሑፍ/። ይህ ቃል የግሪኩን የሐዲስ ኪዳን ልዩ ልዩ ኮፒዎች ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ በልዩ ልዩ ዓይነት ይመደባሉ። 1/ከተጻፈባቸው ቁሳቁስ /ፓፒረስ፤ ብራና/ ወይም 2/ የጽሑፍ የራሱ ቅርጽ /በካፒታል/ በቁም ጽሑፍ ወይም በቅጥልጣይ መሆኑ። በአጽሕሮተ ቃልም "MS" የብዙ ቁጥር ይባላሉ።

**ማአሶሪቲክ ቴክስት**:- የዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን በብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎችን ያመለክታል። ይህም በአይሁዳዊ ጠበብት የተጻፈና አካባቢ ድምጾችን ተጓዳኝ እዝሎችን የግርጌ ማስታወሻዎችን ያካተተ ነው። ለእንግሊዝኛው ብሉይ ኪዳን የሚሆነው ጽሑፍ ከዚህ የተገኘ ነው። ጽሑፍ በታሪካዊ መልኩ በዕብራይስጥ እንደሆነ የተረጋጠ ሲሆን በተለይ ትንቢተ ኢሳያስ በሙት ባሕር ጥቅሶች ታውቋል። በአጽሕሮትም "MS" ይባላል።

**ሚኢቶናሚ**:- ከንግግር ክፍሎች ሆኖ የአንድ ነገር ስም ከሌላው ጋር በተጓዳኝ በመጥቀስ የሚገለጥበት ነው። ለምሳሌ ጀበናው እተፈላ ነው ሲል በጀበናው ውስጥ ያለው ውኃ እየፈላ ነው ለማለት ነው።

**ሙርአቶርያን ፍራግመንትስ**:- ይህ የደንብ /የሕግ/ መጻሕፍትን ዝርዝር ያካተተ ኪዳን ክፍል ነው። የተጻፈውም በሮሜ ከ200 ዓ.ም ቀደም ብሎ ነው። እነዛኑ 27 የሐዲስ መጽሐፍት በፕሮቴስታንት አዲስ ትርጉም ነው። ይህም በሮም ግዛት የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋነኞቹ የቤተክርስቲያን ምክር ቤቶች /በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት/ በፊት እንደተበጀ ያመላክታል።

**ተፈጥሯዊ መገለጥ**:- ይህ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የሚገልጽበት አንደኛው ክፍል ነው። ተፈጥሯዊ ስርዓትን /ሮሜ 1፡ 19-20/ እና ሞራላዊ የሕሊና ሚዛንን /ሮሜ 2፡14-15/ ያካትታል። በመዝሙር 19፡1-6 እና ሮሜ 1-2 ተጽፏል። ከልዩ መገለጥ ይለያል፤ ማለትም የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በናዝሬቱ ኢየሱስ ማለት ነው።
ይህ የስነ መለኮት ምድብ እንደገና አጽንዖት እየተሰጠው እንደ ሁግሮስ በመሳሰሉ ክርስቲያን ጸሐፍት በአሮጌው ዓለም ንቅናቄ ላይ ተመልክቷል። እነሱም ይህን ምድብ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት እንደሆነ ያጸኑበታል። ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ለማወቅ የተከፈተ በር ነው ይህም ካልተመሰጠ /ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ይለያል ዘመናዊው ሳይንስ የተፈጥሮ ስርዓትን እንዲያጠና ነጻነትን ይሰጠዋል። እንደኔ አስተያየት ለዘመናዊው ሳይንሳዊ የምዕራቡ ዓለም ለመመስከር አዲስ አስደናቂ ዕድል ነው እላለሁ።

**ንስጥሮሳዊነት**፦ ንስጥሮስ በ5ኛው ክፍለ ዘመን የኮንስተንበኖፐል ፓትርያርክ የነበረ ነው። የተማረውም በንሪሆች ሶርያ ሲሆን የመከራከሪያ ነጥቡም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት ሲኖሩት አነደኛው ሙሉ ለሙሉ ሰው፤ ሌላኛው ሙሉ ለሙሉ መለኮት ነው ባይነው። ይህም ከአሌክሳንደሪያው የኦርቶዶክስ አንድ ባሕሪ /በተዋህዶ/ ከሚለው ያፈነገጠ ነው። የንስጥሮስ ዋነኛው አትኩሮቱ ለማርያም የተሰጠው የአምላክ እናት የሚለው ስያሜ ነው። ንስጥሮስ በሌክሳንደሪያው ሲሪል ነቀፋ ገጥሞታል። ይህም ዞሮ ዞሮ በተማረበት በአንቲሆች ማለት ነው። በወቅቱ አንቲሆች የታሪካዊ ሰዋሰዋዊ ጽሑፋዊ አገባብ ያለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረጓሜ ማዕከል ስትሆን አሌክሳንደሪያ ደግሞ በአራትዮሹ /ተምሳሌታዊ/ ጉባዔያት የትምህርት ትርጓሜ ማዕከል ነበረች። ንስጥሮስ ከማዕረጉ ወርዶ በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል።

**ዋነኛው ጸሐፊ**፦ ይህ  የሚያመለክተው ዋነኞቹን የቅዱሳን መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ነው።

**ትይዩ አንቀጾች**፦ እኒህ የጽንሰ ሐሳብ ክፍሎች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እና ፍጹም የሆነው የሆነው ተርጓሚም እሱ እንደሆነ፤ አደናጋሪ የመሰሉንን እውነቶች እንኳ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚፈታ ነው። ይህም አንድ ሰው ግልጽ ያልሆነለትን አሻሚ አንቀጽ ሲተረጉም ሲሻ ሊረዳው ይችላል። አንቀጾቹ በተጨማሪም ግልጽ ተዛማጅ ክፍሎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያመላክታሉ።

**አጽሕሮት**፦ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ይረጓሜ ንድፈ ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ቃል በቃል የተረገና ተያያዥነት ቅርጽ የያዘ ሆኖ የእንግሊዝ ቃል ለዕብራይስጥም ሆነ ለግሪክ ቃል ፍቺነት ተፈልጎ፤ የክፍሉ /የአንቀጹ/ ፍሬ ሐሳ ዝቅ ባለ ግምት ከዋናው ጽሑፍ ጋር እየተያየ የሚተረጎምበት ነው።  ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ንድፈ ሐሳቦች ፍጹም አቻዎች የሚባለው ግን ዋናውን ጽሑፍ በዘመናዊ ሰዋሰው እና በዘይቤና በፈሊጥ ለመተርጎም የሚሞክር ነው። ይህን በተመለከተ ደህና መብራሪያ /የትርጉም ንድፈ ሓሳቦች /በ Fee እና Stuart መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በመረዳት እናንብ ገጽ 35 ተመልከት።

**አንቀጽ**፦ ይህ በስድ ንባብ የሚደረግ ዋነኛው የትርጓሜ ክፍል ነው። አንድ ዋነኛ ሃሳቡን ይዞ እያዳበረ ይሄዳል። አንዳንድ በአነቀጽ ላይ ብቻ አኩረን ትርጉሙን ስነሻ /አናሳ አንቀጽ ላይ/ የዋናውን ጸሐፊ ሃሳብ ላናገኘው እንችላለን።

**ፖራኮሊዝም**፦ ይህ የሚያሳየው በአድሏዊነት የተያዘን የአጥቢያ ስነመለኮታዊና ባህላዊ ጉድኝትን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም ባህል /የባህሎች ሁሉ የበላይነት/ እና የአተገባበር እውነቱን ግምት ውስጥ እያስገባም /አይቀጠልም/።

**አያዎ**፦ ይህ የሚያመላክተው ተቃራኒነት ያላቸው የመሰሉ እውነቶችን ሲሆን /ይሆናሉ አይሆኑም/ የሚል መልክ ይዞ ነው። እውነትን የሚያቀርበው ተቃራኒ አቀጣጫዎችን ይዞ ነው። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የሚቀርቡት በዚህ /አያዎ/ ወይም በዲያሌክታካዊ ጥንዶች ተቃርኖ አገባብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ተለያይተው እንደተቀመጡ ከዋክብት ሳይሆኑ ምድብ ምድብ በያዙ የክዋክብት ክምችት ይመስላሉ።

**ፕላቶ**፦ ከጥንታዊ ግሪክ ፈላስፎች አንደኛው ነው። የሱ ፍልስፍና የጥንታዊዋን ቤተክርስትያን በአሌክሳንደሪያ ግብፅ ሊቃውንት እንዲሁም በአውግሰጦስ አማካኝነት ተጽዕኖ አሳድሯል። ፕላቶ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ነገር የመንፈሳዊ ዓለም ግለባጭ /ቅጅ/ ነው ብሎ ያምናል። የስነመለኮት ጠበብት በኋላ ይህን ተፐላቶን አስተሳሰብ ቅርፆች/ሐሳቦች በሚል ለመንፈሳዊ ተግባር ጥቅም ላይ አውለውታል።

**ቅድመ ግምት**፦ ይህ ስለ አንድ ነገር ቀድመን የምናስበው ወይም የምንገምተው ነው። ጽሑፉን ከመመርመራችን በፊት ብዙ ጊዜ አስተያየትና ፍርድን /አቋምን/ ስለ አንድ ነገር ማድረግ ይዘወተርብናል። ይህ ቅድመ ግምት፤ አድልዖ በመባልም ይታወቃል። ግምት ወይም ቅድመ እውቅና ይባላል።

**ፕሩፍ ቴክስቲንግ**፦ ይህ ተግባት ከለን በቁጥር ብቻ /ሙሉ ክፍልን ሳይሆን/ ወይም ዋናውን የክፍሉን አጠቃላይ ሃሳብ ሳይሆን የመተርጎም ስራ ነው። ይህም ቁጥሮቹን ከዋናው የጸሐፊው ሐሳብ ባፈነገጠ መልኩ የግል አስተያየትን በሚካተት የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ትቶ ማለት ነው።

**ይሁዳዊ መምህርነት**፦ ይህ ዓይነቱ የአይሁድ ሕዝቦች የኑሮ ስርዓት የተጀመረው ከ586-538 ቅ.ል.ክ ከባቢሎን ግዞት በኋላ ነው። የአይሁድ ቀሳውስትና ቤተመቅስሱ ከቀሩ በኋላ የአጥቢያ ምኩራቦች የአይሁድ ብሔራዊ የዕምነት ማዕከላት ለመሆን ቻሉ። እነዚህ አጥቢያ ማዕከላት የአይሁድ ባህል፤ ሕብረት የአምልኮና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ማካሄጃ በመሆን የብሔራዊ ሃይማኖታዊ የትኩረት ማዕከላት ሆነዋል። በጁሊየስ ዘመን እነዚህ የጸሐፍት ሃይማኖት ተብለው የሚታወቁት ቀሳውስቱ ጋር በትይዩ መልኩ አገልግለዋል። በ70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ጸሐፍቱ አካል የፈሪሳውያን የበላይ ለመሆን ከመቻሉም በላይ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሕይወት መቆጣጠር ችሏል። ባሕርዩም ተግባራዊ ሕጋዊ ትርጓሜዎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ ባህላዊ /ስነ ቃለዊ/ የሆነውን ዘዴ በመጠቀም ታልሙድን ማብራራት ነው።

**ራዕይ፡-** ይህ እግዚአብሔር ሰለው ልጆች የሚናገርበትን ጽንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ስያሜ ሙሉ ሐሳቡ ብዙውን ጊዜ በሶስት መንገዶች ይገለፃል፡፡ 1/ራዕይ፡- ማለትም እግዜአብሔርን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚከናውነውን 2/ ተመስ፡- እሱ ትክክለኛውን ትርጓሜ ለድርጊቱ ሁሉ የሚሰጥበትን ይህም በተመረጡ ሰዎች አማከኝነት ሆኖ መዝግበው ለሰው ልጆች የሚያስተላልፍበት አገባብ፡፡ 3/በማብራሪያ ማለትም መንፈስን በመስጠት የሰው ልጆችን በማገዝ ስለ እሱ ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

**የቃላት የዓረፍተነገር ትርጉም፡-** ይህ አጠቃላይ የቃላት ትርጉም ጋር የተያያዙ ደረጃዎችን ያመላክታል፡፡ በመሰረቱ የቃላት የተለያየ ትርጉም በየአግባቡ /በየጽሑፉ/ /በየወርዱ/ የሚታየበት ነው፡፡

**ሴፕቱኤጀንት፡-** የዕብራይስጥ ብሉይ የግሪክ ትርጉም ነው፡፡ ከባህል አንፃር በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት በሰባ ቀናት ተጽፎ ለአሌክሳንደሪያ ግብፅ የተፃፈ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ባሕላዊ ጊዜውም 250 ቅ.ል.ክ እነደሆነ ሲገመት /በተግባር ግን ጽፎ ለመጨረስ ከመቶ ዓመት በላይ እነደወሰደ ይገመታል/ ይህ ትርጉም ጠቀሜታው የላቀ ሲሆን፤ ይህም 1/ጥንታዊ የሆነውን ጽሑፍ ከዕብራይስጥ ማስረቲካ ጋር እንዲነጻጸር 2/የአይሁድን የትርጉም አገባብ በ3ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኂላ የነበረውን ያሳየናል፡፡ 3/የአይሁድን ሜስነክ መረዳት /አስተሳሰብ/ ማለትም ክርስቶስን ካለመቀበላቸው በፊት የነበረውን ያሳያል፡፡ አጽሕሮቱም "LXX" ነው፡፡

**ሲናቲኮስ፡-** የ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም የነበረ የግሪክ የብራና ጽሑፍ ነው፡፡ የተገኘውም ቲስከስዶርፍ በተባለ የጀርመን ሊቅ በቅድነት ናተሪኒ ገዳም፤ በጃቤሳ መሳ የተባለ ባሕላዊ ስም ባለው በሲናይ ተራራ ክልል ነው፡፡ ይህ የብራና ጽሑፍ /የእጅ ጽሑፍ/ በዕብራይስ የመጀመሪያ ፊደል በሆነው በአልፋ [x] ይታወቃል፡፡ እሱም ብሉይ ኪዳንና የተጠቃለለውን ሐዲስ ኪዳንን ይዟል፡፡ በጣም ጥንታዊ ከሆኑት የተለየ የእጅ ጽሑፎች አንደኛው ነው፡፡

**የመንፈሳዊ፡-** ይህ ቃል ተምሳሌታወኮ ከማድረግ ጋር ተመሳሳሰይ ሲሆን ሃሳቡም ታሪካዊና ተራ የሆነውን የፅሁፉን ክፍል በማስቀረት በልቶ መስፈርት የመተርጎም አግባብ ነው፡፡

**ተመሳሳይ፡-** ይህ የፅሁፉን ፍቺ ያመለክታል፡፡ 15/ምንም እንኳ ሁለት ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ትርጉም ባይኖራቸውም /በጣም የተቀራረቡ ከመሆናቸው የተነሳ በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ የትርጉም ለውጥ ሳይኖር አንዱ አንዱን ሊተካው ይችላል፡፡ በተጨማሪም የእብራይስጥ ቅኔ ከሆኑት 3 የትይዩ ዘርፎች አንደኛውን ለመመስረት ያስችላል፡፡ በዚህ መሰረት ባለሁለት መስመር የሆኑትን ቅኔዎች /ግጥሞች/ ያመላክታል፡፡ /መዝ 1-3-3/

**ሰዋሰዋዊ፡-** ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን የአረፍተ ነገርን አወቃቀረአ ያሳያል፡፡ ይህም የአረፍተ ነገር አደራደር ሙሉ አስተሳሰብን እንዲገልፅ ተደርጎ ሲዋቀር ያለውን ያሳያል፡፡

ሳይንዚቲካል፡- ከእብራይስጥ ቅኔ /ግጥሞች ከሶስቱ አይነቶች አንደኛውን ያመለክታል፡፡ ይህም የቅኔ /የግጥም/ መስመሮች /ሀረጎች/ አንደኛው ከአንደኛው በመቀናጀት አጠቃላይ ስሜት ሊሰጡ በሚችሉ መልኩ ሲዋቀሩ ነው፡፡ አንዳንዴም ተለዋዋጭ ይባላል፡፡ /መዝ 19፡7-9/

ስልታዊ የስነ መለኮት ትምህርት፡- ይህ ትርጉም ደረጃው አይነት የመፅሀፍ ቅዱስን እውነት ህብር እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሲያቀርቡ ነው፡፡ ከታሪካዊነቱ ይልቅ ሎጂካዊነቱ /ምክንያታዊነቱ/ ያመዝናል፡፡ የክርስትና የስነመለኮት ትምህርት በየምድቡ በማድረግ /እግዚአብሄር፣ ሰው፣ ሀጢያት፣ ደህንነት ወዘተ/ እያለ ይቀርባል፡፡

**ታልሙድ፡-** ይህ የአይሁድ የስነ ቃል /ባህል መለያ ነው፡፡ አይሁድ እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ በቃሉ እንደተናገረው ያምናሉ፡፡ በተግባር ሲታይ ግን ለዓመታት የተከማቸ፡፡ የአይሁድ መምህራን የጥበብ ክምችት ነው፡፡ ሁለት ዓይነት የተለያዩ የፅሁፍ ቅጂዎች /እትሞች/ አሉት ታልሙድ እነሱም የባቢሎኑና ያልተጠናቀቀው በአጭር የተፃፈው የፍልስጥሙ /የከነአኑ/፡፡

**የቃሉ ምርመራ፡-** ይህ የቅዱሳን መፃህፍትን ጡናት ማካሄድ በተመለከተ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው ዋነኞቹ ፅሁፎች ስለማይገኙ ቅጂዎቹ የተለያዩ በመሆኑ ነው፡፡ ልዩነቶችን ለማብራራትና በተቻለ መጠን ወደ ዋነኞቹ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ፅሁፎች መነሻ ለማድረስ ነው ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛው ምርመራ ይባላል፡፡

**የፅሁፍ አቀባበል፡-** ይህ ስያሜ የተስፋፊው ወደ አኤልዚጎር ትርጉም ከሆነው በ1633 የግሪክ አዲስ ኪዳን እትም ነው፡፡ በመሰረቱ ይህ የግሪክ የአዲስ ኪዳን የወጣው /የተገኘው/ ጥቂት ቀደም ሲል ተፅፈው ከነበሩ የግሪክ የእጅ ፅሁፎች እና የላቲን እትሞች ማለትም ከአራሳመስ /1510-1535/ እስጢፋኖስ /1546-1559/ እና ኤልዚጎር /1624-1678 ከተፃፉት ነው የአዲስ ኪዳን ፅሁፋዊ ምርመራ /ገፅ 27 መግቢያው ላይ ኤቲ ሮበርትስን/ የባይዘንታይን /የግሪክ/ ፅሀፀፍ በተግባር ሲታይ ፅሁፎችን መቀበል ነው ብሏል፡፡ የባይዘንታይን ፅሁፍ የመጨረሻው ዝቅተኛው የሆነ በጣም ጠቃሚ ከሆነፀ ከሶስቱ ከቀደምት የብራና /የእጅ ፅሁፎች/ /በምዕራብ በሌክሳንደሪያና በባይዘንታን/ ካሉት የሚመደብ ነው፡፡ በውስጡም በእጅ ሲፃፍ ለዘመናት የተደረጉትን ግድፈቶች /ስህተቶች/ አከማችቶ ይዟል፡፡ ሆኖም ግን ኤ ቲ ሮበርትሰን ደግሞ እንዳለው፣ ፅሁፎቹ የተወልን ነገር በውስጡ ያለው ተገቢ ፅሀፀፍ ነው ብሏል /ገፅ 21 ላይ/ ይህ የግሪክ ፅሀፀፍ

/በተለይም የአራስመስ 3ኛ እትም በ1522 /የንጉስ ጀምስ እትም ማለትም 1611 ዓ.ም የታተመውን መሰረት እንደሆነ ይታመናል።

**ቶራ፡-** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ማስተማር ማለት ነው። እሁም ለሙሴ ፅሁፎች /ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም/ ያለውን የሚያካትተ ርዕስ ነው። ይህ ለአይሁድ ታላቅ ስልጣን /ተቀባይነት/ ያለው ክፍል ነው።

**ታይፖሎጂካል፡-** ይህ ጥልቀት ያለው ሙያዊ ትራጓሜ ነው። ብዙውን ጊዜ የሀዲስ ኪዳን እውነት ከብሉይ ኪዳን ተምሌታዊ መልኩ የሚያስጠቅስና የሚያስማማ ነው። የትርጉም ምድብ ዋነኛው የአሌክሳደሪያን ዘዴ የተከተለ ነው። የዚህ አይነቱን ትርጉም በአግባቡ አለማከናወንን ለማስቀረት ትርጓሜው ሲካሄድ በተወሰኑ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች መሆን ይኖርበታል።

**ቫአቲካነስ፡-** ይህ የ4ኛ ክፍለ ዘመን የግሪክ የእጅ ፅሑፍ ነው። የተገኘውም በቫቲካን ቤተመጽሀፍት ሲሆን ዋናውን ብሉይ ኪዳን ተነባቢት /ራዕይ/ እና አዲሰ ኪዳንን ያካትተዋል። የተወሰኑ ክፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ሆኖም የተወሰኑ ከፍሎች ማለትም ከዘፍጥረት፣ ከዕብራውያን፣ ከሌዋውያን ፊሊሞና እና ከራዕያ ጎድለውበታል። ዋናውም የቃሉን የእጅ ጽሑፍ በመወሰን በኩል በጣም ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ ነው። መለያውም ፊደል "ቢ" ነው።

**ቫሰጌት፡-** ይህ የጀሮም የላቲን ትርጉም የሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ነው። ይህ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዋነኛ ትረጉም ተደርጎ ተወስዷል። በ380 ዓ.ም ነው የተፃፈው።
ጥበባዊ ሥነ-ጽሁፍ፡- ይህ ቃል የሥነ-ጽሑፍን ዘውግ/ዓይነት/ የተለመደ ዓይነት ሆኖ በቅርብ ምስራቅ የጥንት አካባቢ /ዘመናዊው ዓለም/ የሆነውን ያመለክታል። ይህ በቅኔ/በግጥም/በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በወገዊ ጽሁፍ አማካኝነት አዲሱን ትውልድ ለማስተማርና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችል ነው። መልእክቱም ለአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ሳይሆን በግለሰቦት ላይ ያተኮረ ነው። የታሪክን ሁኔታ በማጣቀስ አይጠቀምም፣ ይልቁንም የሕይወትን ልምድና አስተውሎትን ይቃኛል። ከመጽሀፍ ቅዱስ ከእዮብ ከመሃልየ ማሃልየ የሚታሰበው የያህዌን መገኘትና ማምለክን ሲሆን ይኼውም መንፈሳዊ ዓለም አስተሳሰቡ በግልፅ በየሰው የሕይወት ልምድ በሁሉም ጊዜ እንደማይደረግ ያታወቃል።
እነደ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፍ በአጠቃላይ እውነት ላይ ያተኩራል። ይህ የሥነ-ጽሑፍ ክፍል /ዕይነት/ግን በእያንዳንዱ ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውልም። እነዚህ አጠቃላይ ሀሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ባለበት ሁኔታ ላይ የማይከናወኑ ናቸው።
አነዚህ እነዚህ ፅሑፎች የሕይወትን ጠንካራ /ዋነኛ/ ጥያቄ ያነሳሉ። ብዙውን ጊዜ ሀይማኖታዊ ሆነው ባህል የሚደባለቁ አመለካከቶችን /ኢዮብ/መክብብ/ ያነሳሉ /ይከራከራሉ/። ለሕይወት ጥያቄዎች ሚዛናዊ ምላሽ በመስጠት በተለይ አሰዛኝ/ሰቆቃዊ/ በሆኑት ላይ ያተኩራሉ።

**ወርድ ፒክቸር እና ወርደ ቪው፡-** እነዚህ ተጓዳኝ ቃላት ናቸው። ሁሉም ፍልስፍናዊ ጽነሰ ሃሰቦች ሲሆኑ በአፈጣጠር ላይ ያተኩራሉ። የዓለም ምስል የሚሰጠው እንዴትን ሲያመለክት ስለአፈጣጠር ደግሞ የዓለም አመለካከት የሚለው ማን የሚለውን ያሳያል። እነዚህ ቃላት በተለይ ዘፍጥረት 1-2 ለመተርጎም በመጀመሪያ በመጀመሪያ ማን፣ የሚለውን ያነሳሉ "እንዴት" የሚለውን የአፈጣጠር ጥያቄ ትተው።

**ያህዌ፡-** ይህ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ስም በአዲስ ኪዳን ነው። ይህም ዘፀአትን 3.14 ያለውን ያነትናል። ይህ የዕበራይስጥ ምክነያታዊ ስም በመጥቀስ መሆን የሚሰውን ያሳያል። አይሁዶች ይህን ስም ለመጥራት ፍርሐት አለባቸው ምንም አንኳ ቢቀበሉትም። በመሆኑም ወደ ዕብራይስጥ ለውጠው አዶናይ/ጌታ/ ይሉታል። በዚህም ምክንያት ነው ይህ የቃል ኪዳን ስም ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው።

# ተጨማሪ መግለጫ አራት

# የእምነት መግለጫ

በግል በተለይ በእምነት መግለጫም ሆነ የዕምነት ማስታወቂያ ብዙ አያሳስበንም ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ማፅናቱ ይሻለኛል። ዳሩ ግን እኔ የዕምነት ሁኔታ ለመረዳትና ለመፈተሽ ለሚፈልጉ የዕምነት መግለጫው ይረዳቸው ይችላል። በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ሕጸጾችና የተዛቡ አመለካከቶች ባሉበት ሁኔታ የእኔን ሥነ- መለኮታዊ ትምህርት አጭር ማጠቃለያ አቀርባለሁ።

1. መጽሀፍ ቅዱስ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን ሁለቱም ተመስጧዊ የሆነ የማይወድቅ /የማይሻር / ሙሉ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ቃል ነው። ቃሉ የራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ሲሆን በመንፈሳዊ ምሪት በሰዎች አማካኝነት የተመዘገበ /የተፃፈ/ ነው። ስለ እግዚአብሄር ንፁህ እውነት እና ስለ ተግባሩ የሚገልፅ ብቸኛ ምንጭ ነው። እሱም ለራሱ ቤተክርስቲያን የዕምነትና የተግባር ብቸኛ ምንጭ ነው።

2. አንድ ብቻውን የሆነ ዘለዓለማዊ ፈጣሪ የሚቤዥ እግዚአብሔር አለ። እሱም የሚታየውንም ሆነ የማይታየውንም የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው። ራሱን በአፍቃሪነቱና በጠባቂነቱ /በተንከባካቢነቱ/ የገለፀ ሲሆን ራሱም ፍፁምና /መልካም/ ትክክለኛ ነው። ራሱን በሦስት አካላት ገልጧል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በእኩል አካል የተለያዩ ባህርያ ግን አንድ የሆነ።

3. እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ሁሌም ነው። እናም ዘለዓለማዊ እቅድ ለፍጥረቱ ያለ ሲሆን ይህም ማስተካከያ የማይደረግለት በእያንዳንዱ ሰው ነፃ ፍቅር ላይ ያተኮረ ነው። ያለ እግዚአብሔር እውቅናና ፍቃድ የመሆን ነገር የለም ይህም ቢሆን ግን ለሰዎችም ሆነ በመላእክት ነፃ ፍቀድን ፈቅዷል። እየሱስ አብ የመረጠው ሰው ነው። ሁሉም የሚመረጡት በሱ ነው። የእግዚአብሄር የሁኔታዎች ቀድመ እውቅና የሰው ልጆችን ቅድመ ፅሑፍ ቃሉን ከመቀበል ለመወሰን አያዳግታቸውም። እያንዳንዳችን ለምናስበውም ሆነ ለምንሰራው ሃላፊነትን እንወስዳለን።

4. የሰው ልጅ ምንም እንኳን በእግዚአብሄር አምሳል ቢፈጠርና ከሃጥያት ነፃ ቢሆንም በእግዚአብሄር ላይ ማመፅን መረጠ። አዳምና ሄዋን ምንም እንኳ ከተፈጥሮ በሆነ ወኪል ቢፈተኑም ፈቅደውና ወደው በግለኝነት በወሰዱት አቋም ሃላፊነት አለባቸው። የእነሱ አመፅ ነው የሰው ልጅንም ሆነ ፍጥረትን ለጉዳት የዳረገው። እኛ ሁላችንም ከእግዚአብሔር ምህረት ከአዳም ለወረስነውም ሆነ በሰውነታችን ለፈፀምነው አመፅ ያስፈልገናል።

5. እግዚአብሔር ይቅርታውንና ምህረቱን ለወደቀው ሰውነታችን ስጥቶናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ሰው የሆነ፣ ያለ ሃጥያት የተመላለሰ እኛን ውጢ በሞተልን፣ የሰው ልጆችን የአሃጢአት ቅጣት ተቀበለ። እሱ የደህንነት መንገድና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚምረው ስውረት ብቸኛ መንገድ ነው። ስለደህንነት ሌላ ምንም መንገድ የለም ራሱ ሰርቶ በጨረሰው ሥራ ከማመን በስተቀር።

6. እያንዳንዳችን በግል የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስጦታ በእየሱስ የሆነውን ደህንነት መቀበል ይኖርብናል። ይንንም ማግኘት የሚቻለው በእግዚአብሔር ተስፋ በማመን፣ በኢየሱስ በኩል ፍቃደኝነት ከሃጢአት መራቅ ነው።

7. ሁላችንም ሙሉ ምህረት እና መመለስ የምናገኘው ክርስቶስ እምነትና ሃጢአት በመመለስ ነው። የአዲስ ህይወቱ ማስረጃም በተለመደና እየተለወጠ ባለ ህይወቱ ይታወቃል። እግዚአብሄር ለሰው ሰጆች ያለው ዓላማ አንድ ቀን በመንግስተ ሰማያት የሚሆን ሳይሆን አሁን ክርስቶስ በመሰለ ሕይወት መመላለስ ነው። በትክክል መቤዠትን ያገኙ በስህተት ሃጢአት ቢሰሩም በዕምነታቸው ቀጥለውበት በንሥሐ ህይወት በሕይወት ዘመናቸው ሊመላለሱ ይገባል።

8. መንፈስ ቅዱስ ሌላው እየሱስ ነው። እሱም በዓለም ላይ አለ፣ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለመምራትና በዳኑትም ክርስቶስ የመሰለ ሕይወት እንዲኖሩ በማስቻል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ደህንነታችን ስንቀበል ይሰጡናል። እነርሱም የእየሱስ ሕይወትና አገልግሎቶች ሲሆኑ ለአካሉ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ፀጋዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጎቱንና ሐሳቦቹን ለማስፈፀም በመንፈስ ፍሬ የሚታዩ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ፊት እንደነነረ አሁንም ይጠራል።

9. አብ ከሙታን የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉም ፈራጅ አድረገታል። ወደ ዓለም ይመለሳል በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ለመፍረድ በኢየሱስ ያመኑና ስማቸውም በበጎ ሕይወት መጽሀፍ ላይ የፃፈ ሰማያዊ የከበረ አካላቸውን በዳግም ምፅአቱ ያገኛሉ ከእሱም ጋር ለዘለዓለም ይሆናሉ። የእግዚአብሄርን እውነት ለመቀበል ያልፈለጉ ለዘለዓለም ከእግዚአብሄር ህብረትና ደስታ ይለያሉ። ከሰይጣንና ከመልአክቱ ጋር ይፈረድባቸዋል።

ይህ በእውነቱ የተጠናቀቀና የጠለቀ ባይሆንም የልቤን ሥነ-መለኮታዊ መዓዛ ይሰጣቸኋል ብዬ አምናለሁ። ጽሑፉን እወደዋለሁ።

"ከአስፈላጊዎች ሁሉ — ህብረት፣ ከምርጫዎች- ነፃነት ከሁሉም ነገር- ፍቅር"